- ጊዜ ላለመጨረስ ያው ማን ነው የሰበረው የሚል ጥያቄ ስለሆነ ተገቢ ነው ቀጥሉ ብለናል
- ይቀጥሉ ምስክር ?
- ማን ነው የሰበረው የሚባል ነገር ላይ ላውቀው አልችልም
- አዎ በማለሰብ
- ሲባል ሰምቼአለሁ ፖሊስ መጥቷል ሲባል ሰምቼአለሁ በቦታው የለሁም ከመጣሁ በኋላ አርፍጄ ገባሁ መጡ ሲሉ በሌላ ጊዜ ነው የእዚያን ቀን አይደለም በ 7ቱም አይደለም በ 8ቱም አይደለም ከእዚያ በፊት በሣምንቱ ጊዜ በነበረው ነው መነሻው መጀመሪያ በእዚህ የተነሳ ነው የተነሳው
- እርሶ መስኪድ ገብተዋል የእዚያን ቀን ?
- አዎ ገብቼአለሁ
- መቼ ነው የገቡት ?
- ወላሂ በሣምንቱ ነው ቀኑን አላውቅም
- ቅድም አይ አይደለም የሣምንቱን ሳይሆን ቅድም በ 7/11 ብለዋል በ 7/11 እርሶ ገብተዋል መስኪድ ?
- አልገባሁም መልሰውኛል
- መልሰዎታል ?
- በቃ ምንድን ነው ይሄ እኮ እራሱ እኔ የምለው ነገር ላይ መጨመር መቀነስ አልችልም መልሰውኛል በእናንተ አልፈተሽም ብዬአለሁ
- ሀጂ ቆይ ያዳምጡ
- አልፈተሽም ብዬ ተመልሼአለሁ
- ጥሩ እኮ ?
- አልገባሁም መስኪድ
- ቆይ እስቲ ዐቃቤ ሕግ አሁን ቅድም ያሉት ምንድን ነው እኔ ስገባ ያልተለመድ ፍተሻ ሆኖ እኛ አልፈተሽም ብዬ ተመለስኩ በኋላ ስጠይቅ ብለው ቀጥለዋል ምናልባት እሱ ላይ ከእዚህ ተነስታችሁ የምትጠይቁት ካለ
- ምስክሩ ፍ/ቤቱ እንደሚያየው ለማስታወስ እንትን እያልን ነው መስመር ለማስገባት ነው ምስክሩን የምንደግመው እንጂ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ይሄ ግልፅ ነው ከእዚህ ጀምሮ ለምሳሌ ከእዚህ በኋላ ምን መጠየቅ እንደፈለጉ
- ታዲያ ማን ነው የተቆጣጠረው ውስጡን ተቆጣጠረ ያሉት ቅድም ማን ነው የተቆጣጠው መስኪዱን ?
- ማን ነው በምጠይቅ ጊዜ የ 17ቱ ኮሚቴ የጊዜው ኮሚቴ አበበከር አህመድ ነው
- ጥሩ እሺ መስኪድ ውስጥ ያሉት
- ሲባል ነው የሰማሁት በአይኔ አልገባሁም ብዬአለሁ መስኪድ አልገባሁም
- ይበቃል
- ስለዚህ መስታወት እና በር የተሰበረው እነዚያ ሰዎች ውስጥ እያሉ ነው ማለት ነው ?
- አይደለም እሱ በሌላ ጊዜ ምን ታሳስተኛለህ በሌላ ጊዜ በሃምንቱ በነበረው ወኸንብር ነው ይሄ ከመምጣቱ በፊት በነበረው ጊዜ ነው ይሄ መስታወት እና በሩ የሰበረው እነዚህ ቀን አይደለም
- ቆይ ያዳምጡኝ ቅድም ቅዳሜ እና እሁድ እኔ
- እሱ ሌላ ጉዳይ ነው ብዬአለሁ
- ቆይ ቆይ ይኸውሎት 1ኛ ቀጥ ብለው ይመልሱ እስካሁን ታጋሰናል የሚጠየቁትን ጥያቄ ያቺ የምትጠይቁትን ብቻ ነው መመለስ ያለቦት እንጂ ይሄ አያገባኝም አንተ ልትጠይቀኝ አትችልም ይሄ ተገቢ አይደለም ስለዚህ እርሶ የሚመልሱት የሚጠየቁትን ጥያቄ የሚያስታሱ ከሆነ የሚያስታውሷትን ብቻ ቃል መናገር ከእዚያ በኋላ ከጥያቄው ዉጪ መናገር
- እሺ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ቅዳሜ እና እሁድ ፈርቼ ቢሮ አልገባሁም ብለዋል አይደል ሌላ መስኪድ ነው የሄዱት ሰኞ ገቡ ?
- ሰኞም አልገባሁም
- መቼ ነው የገቡት ?
- ምን አውቃለሁ እኔ
- አይደለም መቼ ነው የገቡት ገብተዋል ?
- ከ 4 ቀን በኋላ
- ከ 4 ቀን በኋላ ገቡ ?
- አዎ



2208 646

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሲገቡ እነዚህ አሁን የጠቀሷቸው ነገሮች ነበሩ መስታወቱ በሩ ?
- መስታወቱም ገባለት በሩም ተገጠመ የገጠመውን ሰው አላወኩም
- ተሰብሮ አይተዋል ?
- መስታወት ሰብረዋል በሩ ተገንጥሎ ነው የቆመው በኋላ ያገባው ሰው አላውቅም ሄዶ ገብቶ ተገጥሞ አየሁት
- ስለዚህ እስከ ሰኞ እናንተ መደበኛ ስራችሁ ላይ ሳትኖሩ ማን ነው የነበረው መስኪድ ውስጥ ?
- በቃ መስኪዱ ብጥብጥ ነው ሰላም ስለሌለው መስኪዱ 4 ቀን ድረስ አልገባንም
- ሁሉም ሠራተኛ አልገባም ?
- የማውቀው ነገር የለም ስለራሴ ነው
- እዚህ ጋር ይበቃል ዐቃቤ ሕግ ሌላ ጥያቄ ካላችሁ
- ዋና ጥያቄ ይበቃናል
- የተከሣሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- ሀጂ ናስር ሀጂ እየሰሙኝ ነው ?
- እየሰማሁሽ ነው
- ያን ቀን አልፈታሽም ብዬ ተመለስኩ ብለዋል በኋላ ደግሞ ኑ እና ተረከቡ እያሉ ነበረ ብለዋል ይሄንን የሰሙት በእስፒከር ነው እንዴት ነው የሰሙት እስቲ ንገሩን ?
- በቃ አንድ በእዚያችው ሰዓት በእዚያችው ቀን ነው
- በእዚያች ?
- በእዚያችው ቀን ነው በእዚያችው ሰዓት ነው በቃ ሌላ ነገር ተመልሼ አልመጣሁም መስኪድ በኔ ሰፈር ሄጄ ሰግጄአለሁ በማግስቱ መጣሁ ይሻለዋል ብዬ መጣሁ አልተሻለውም ብሶበታል በቃ የመጀመሪያ ቃሌ ነው ፖሊስ ሌባ አዲስ መጅሊስ ሌባ ሲሉ የእዚያችው ቀን በእዚያ ሰውዬ ድምፅ ሰምቼአለሁ አሁን ደግሜ ደግሜ ያቺን ናት
- ስንት ሰዓት ላይ ነው ይሄንን የሰሙት ?
- አሁንም 2 ሰዓት ተኩል ነው
- 2 ሰዓት ተኩል ጠዋት ማለት ነው ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልፈተሽም ብለው በቆሙባት ቅፅበት ማለት ነው ያቺ ያኔ የሰሙት ?
- እንዴት እንዴት
- አልፈተሽም ብዬ ቆሜ ነበር ውጪ በእዚያው ተመለስኩ ነው ያሉት ?
- ተመልሼአለሁ ከእዚያ በኋላ አልተመለስኩም አሁንም
- እኮ ያኔ ቆመው በነበረበት ወቅት ነው ይሄንን የሰሙት ?
- አዎ
- ተመለሱ ኑ ቦታችሁን ውሰዱ ያሉትም ያን ጊዜ ነው ?
- የእዚያው ጊዜ ነው
- ያንኑ ጊዜ ነው ያሉት ?
- አይ ተመለሱ ግቡ ያሉ የትላንትናው ቀን ነው በ 7 ነው በማግስቱ ሌባ መስጂሊስ ፖሊስ ሌባ የተባለበት 7 ነው በ 8 ነው ቅዳሜ ነው
- በ 7 2 ሰዓት ተኩል ላይ ነው ኑ ተመለሱ እና ውሰዱ ያሉት ? ኑተረከቡ ያሉት በ 7 ነው ?
- ከገባችሁ ግቡ ካልገባችሁ ኢማሞች /ግልፅ ያልሆነ/ ሠራተኛ ካዲሞች ከገባችሁ ግቡ ካልገባችሁ በእናንተ ቦታ ላይ የራሳችን ሠራተኛ እንተካበታለን ብለዋል ነው አንድ ቃሌ ነው ይኸው ነው
- ይሄንንም የተናገሩት 2 ሰዓት ተኩል ላይ ጠዋት ?
- እንደዚያው ነው በሰዓቴ ነዋ የምገኘው እኔ በሰዓቴ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ በሰዓቴ ነው የምገባው እንጂ አሳልፌ አልገባም እቀጣለሁ
- ሌላ ጥያቄ
- በ 8 ጠዋት 2 ሰዓት ተኩል ?
- እንደዚያው ነው አዎ
- በ 8 አልገቡም አልተፈተሹም ተመልሰው ሄዱ ?
- አልፈተሽምም አልገባሁም ደርሼ እገባለሁ በምል ጊዜ ያው እነዚያው ፈታሾችም እነዚያ ናቸው የትላንት የነበሩ ሰዎች ናቸው መልሰው እዚያው ነው
- ስለዚህ ተመልሰው ሄዱ ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሀጂ ናስር እርሶ አልፈተሸም ብለው ተመልሰው እንኄዱ ነግረውናል ምን ያህል ቆዩ እዚያ ከመሄዶ በፊት ?
- እኔ ከግቢው ውጪ ሰው እየወጣ እየወጣ እየበዛ አላህክበር እያለ እየረበሸ ሲመጣ 4 ሰዓት ድረስ ቆይቼ በማይ ጊዜ ለራሴም ስጋት ፈርቼ ቢታ በእዚያ ቦታ ላይ የሚናገሩት ንግግር አንዳንድ ሰዎች እንትን ሲሉኝ ጊዜ ሄጄ አሁንም ደግሞ እዚያው ጋር ነው አሁንም በኔ ነው በማግስቱም በኔ ነው የሰገድኩት 4 ሰዓት ቆይቼአለሁ
- 4 ሰዓት ከግቢው ውጪ ሆነው ?
- ፊት ግቢ ገብቼአለሁ ብዬአለሁ ፊትም ከግቢ ውጪ ነኝ አሁንም ከግቢ ውጪ ነኝ
- እሺ ከግቢ ውጪ 4 ሰዓት ድረስ ነበሩ 2 ሰዓት ተኩል ላይ ቅድም የነገሩንን ነገር ሲነገር እንደሰሙ ነግረውናል ?
- አዎ
- እስከ 4 ሰዓት ተኩል አሁን የነገሩን ነገር በደቂቃዎች የሚያልቅ ነገር ነው ?
- 4 ሰዓት ነው የቆየሁት
- እሺ ልመጣ እኮ ነው ንግግሩን ያደረጉት 2 ሰዓት ተኩል ነው ያደረገው ቅድም አደረገ ያሉት ሰው እርሶ እስከ 4 ሰዓት ተኩል ቆዩ ከእዚያ ንግግር በኋላ ምን ሆነ ?
- ያው ተረበሸአ ምን ሆነ ሀገሩ ቀውጢ ነው ምን ሆነ ሀገር ፀሀይ ላይ እየሞቁ አይደለም እንዴ መንግስት እያየው አይደለም እንዴ እኔ ምን ትጠይቀኛለህ የእዚያ ቀን ሁሉ ቀን በሙሉ በማግስቱም ሁሉም ጊዜ እስከዛሬም ድረስ ብጥብጥ ነው ያለው ምንድን ነው የምትጠይቀኝ
- ማለቱ እስፒከር ስላለ ውጪም ሆነው
- እሰማለሁ ሰምቼአለሁ
- ይሄ አሁን የተናገሩት የደቂቃዎች ንግግር ነው ቅድም የተናገረው እርሶ ደግሞ 4 ሰዓት ስለሆኑ ረጋ ብለው አሁን ቅድም መሀላ ፈፅመዋል በእውነት ለመመስከር ስለዚህ ተረጋግተው ይንገሩን ከየትም ይጠየቁ እስከ 4 ሰዓት ድረስ በቆዩበት ጊዜ በእስፒከር ሌላ ምን ሰሙ ?
- ጩኸት ሰማሁ አላህክበር ሰማሁ ሁከት ሰማሁ ብጥብጥ ሰማሁ በቃ ሌላ ምንድን ነው
- ሌላ ንግግር ያደረገ ሰው የለም ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁንም አቡበከር አህመድ የሚባለው ሰውዬ ነው ብለው ነው አሁን የትላንትናው ሰውዬ ዛሬም እኮ አለ እዚያ ጋር ይሄ አሁን የሰማሁት እኮ እሱ ነው ሌላ ንግግር ምን አለ እዚያ እኮ በእስፒከር ነው የምሰማው እንጂ አቡበከር መልኩን አላውቀውም አላየሁትም
- ይበቃል ቀጥሉ ሌላ ጥያቄ
- እሺ አሁን በ 7 ያሉት ቀኑ ምን ቀን ነበር ?
- ቅዳሜ
- ቅዳሜ ነበር ?
- አዎ
- ጠዋት 2 ሰዓት ተኩል እዚያ እስከ 4 ሰዓት ነበሩ አየሩ እንዴት ነበር ?
- የምን አየር
- ማለት ፀሀይ ነበረ ዳመና ዝናብ ?
- እኔ ወላሂ ሚትሮጂ አይደለሁም እሱን የማውቀው ነገር የለም
- ይኸውሎት ምስክር እንግዲህ ባህሪዎ ሊሆን ይችላል እኛ እንደዚያ ነው የወሰድነው ከክፋት አልወሰድነውም ግን ስንነግሮት መስማት አለቦት ስንነግሮት ሳይሰሙ ሲቀሩ ነው ወደ ክፋት የመንወስደው ጥሩ ያልሆነ ነገር የምንወስደው ወደ እዚያ ነው ስለዚህ እርሶ ጥያቄውን ይመልሱ ሚትሮሎጂ ኖት ተብሎ አልተጠየቁም ግልፅ ነው ?
- አዎ
- ሜትሮሎጂ አይደለሁም ብለው የሚመልሱት ሜትሮሎጂስት ኖት ተብለው ሲጠየቁ ብቻ ነው ስለዚህ እርሶ የሚያውቁት ከሆነ አላውቀውም የነበረ ከሆነ ነበረ ያልነበረ ከሆነ ወይ የሚያውቁት እንደዚህ የሚያውቁትን ብቻ ?
- በቃ አላውቀውም
- እንጂ ሌላ መልስ ቆይ አይደለም እኔ አልጠየኮትም እኮ
- እሺ
- የሚጠይቅ ሌላ ሰው አለ እኛ ይሄንን እየመራን ነው እርሶ እኛን እያዩ እየመሰከሩ ነው እኛ ቁሙ ስንል ማቆም ተናገሩ ስንል ቀጥሉ ስንል መቀጠል ነው ስለዚህ ሌላ ምላሽ ጥሩ አይሆንም
- ቀጥሉ



2212 680

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ሲመሰክሩ በ 40 ዓመት ዕድሜ እንዲህ ነገር አላየሁም ብለዋል አንዋር መስኪድ በ 40 ዓመት ውስጥ አሁን በ 87 እንዲህ የተረበሸ ሁኔታ አልነበረም እንዴ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለ
- ምንድን ነው መቃወሚያ
- እኛ ጭብጥ አስይዘን በክሱ መሠረት እያስመሰከር ያለነው ሐምሌ 7/2004 ስለተፈፀመ ነገር ነው ስለ 1987 የአንዋር መስኪድ የኋላ ታሪክ አይደለም ምስክሩ ቢያውቁ ይመልሱታል ችግር የለውም ግን ምንድን ነው ቅድም ፍ/ቤቱ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ እና ትዕዛዝ የሚጥሰው ጊዜውን እና ወረቀቱን ከመፍጀት ውጪ ምንም ለክሱ የሚያመጣው ፋይዳ የለም ስለዚህ አግባብነት ያለው ጥያቄ ስላልሆነ እንዲታለፍ
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ በዋናው ጥያቄ ላይ እንዲህ ዓይነት ነገር የተለመደ ነው ወይ ብለው ሲጠይቋቸው በ 40 ዓመት ዕድሜ እንዲህ ነገር አይቼ አላውቅም ብለዋል አሁን ወደ ኋላ 40 ዓመት ስላሉ ከታአማኒነት ጋርም የተያያዘ ነው ስለዚህ ምስክሩ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ጥያቄ ተመስርቶ ይሄንኑ ካሉ በእዚህ ውስጥ የሆነ ነገር አለ የለም የሚለውን መጠየቅ አግባብነት ያለው እና ከጭብጡ ውጪ መጀመሪያ መስክረዋል እኛም ለማለት ነው እና በአግባቡ ነው
- የግራ ቀኛችሁን አዳምጠናል ምስክሩ መጀመሪያ ላይ ስንት ዓመት ሰርተዋል 40 ዓመት
- በ 40 ዓመት ውስጥ እንዲህ ዓይነት ድርጊት ተፈፅሞ አያውቅም ሲባል አይ ተፈፅሞ አያውቅም ያኔ ነው ያየሁ ተብሏል እና ጥያቄው ተነስቷል እንግዲህ ለግራ ቀኞቻችሁ ምን ያህል ሊጠቅማችሁ እንደሚችል ባናውቅም እንዲህ ብለው መልሰዋል ስለዚህ ጥያቄው ተገቢ ነው ቀጥሉ ብለናል
- ጥሩ ሀጂ ናስር አንዋር መስኪድ አሁን የተፈጠረው ዓይነት እርሶ የሚሉት ሁሉ ረብሻ ነው የሚሉት ነገር በ 87 ረብሻ አልነበረም እንዴ ?
- መልስ ነው
- አንዋር መስኪድ ውስጥ ከእዚያ በፊት 40 ዓመት ሙሉ ስቀመጥ ምንም ረብሻ አልነበረም ያን ቀን እና ያን ሰሞን ነው ብለዋል አሁን ወደ ኋላ እየተጠየቁ ያሉት በ 97 አካባቢ አንዋር መስኪድ ውስጥ 87 ላይ አልነበረም ወይ ነው ጥያቄው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ በእዚያን ጊዜ  ወደ ውጪ ሀገር ሳውዲአረብያ ነው የነበርኩት ሪብሻ እንዳለ እና ሰው እንዳለቀ በእዚያን ጊዜ በተወሰኑ ሰዎች አለመግባባት ሁሉም መንግስት የሚያውቀው ነገር ላይ ነው በእዚያ ወሬ ነው የሰማሁት እንጂ በእዚያ ባለቀው ጊዜ እኔ የለሁም በቦታው ላይ ጅዳ ነኝ
- ጥሩ ቅድም ልፈትሾት ያሉት ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው ?
- ወላሂ መልካቸውን አላውቃቸውም
- ፊታቸውን አይተዋል ?
- ፊታቸውን የፈለገም ባያቸው በእዚያ ቀን ሰው አይታወቅም መልኩ አይታወቅም ብዙ ሰው ነው እከሌ ብዬ ለመለየት አልችልም
- ወንድ ሴት ?
- ወጣቶች በቃ በአጠቃላይ ወጣቶች ናቸው
- ወንዶች ?
- አዎ ወንዶች ናቸው ሴት እዚያ አይደለም ሴቱ በሴቱ ክፍል በላይ በኩል ነው እንጂ ወንድ ጋር ሴት አይመጣም ክልክል ነው
- እርሶ በየትኛው በር ነው እንደዚያ ያሉት?
- በወዲኛው በምንጣፉ በር መዉጪያው ላይ መርካቶ መውጪያው ላይ ከባንኩ በታች ባለው
- ምን ነበር የሚፈትሹት ልጆቹ ?
- እኔ የሚፈተሸው ነገር የሆነ ነገር አላውቅም ማንም ሰው ሳይፈተሽ አይገባም ተብሎ ነው የታዘዘው ትዕዛዙ የእዚያን ቀን ማን እንዳዘዛቸው አላውቅም ምን እንደሚፈልጉ አላውቅም እኔ አልፈተሽም ነውያልኩት አንድ ቃል ነው
- ከእርሶ በፊት ሰዎች ሲፈተሹ አላዩም ?
- ማንም የሚገባ እነሱን የመሰለ ይገባል እነሱን የመሰለ ይመለሳል
- ማለት ከእርሶ በፊት ሰዎች ሲፈተሹ ነበሩ ?
- የሚፈተሹ እርስ በራሳቸው ይፈትሹ እንጂ እኔ ተፈትሾ ሲገባ ያው እርስ በራሳቸው ይፈታተሹ እንጂ ሌላው ሰው ጓደኞቼ ሲገቡ አላየሁም ስለሌላ የማውቀው ነገር የለም
- ማለት አሁን ፈታሾቹ መሣሪያ እንዳይገባ የመሳሰለው አደጋ እንዳይደርስ
- ተመልሷል እኮ ምን እንደሚፈልጉ አላውቅም



224

652

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በተዘዋዋሪ የሚያውቁት ነገር ካለ መስቀለኛ ጥያቄ ስለሆነ
- ይሄኛው ተመልሷል እኮ ምን እንደሚፈልጉ አላውቅም ይፈትሻሉ
- ፲ኛው እሱ ነው 2ኛው አልገቡም አልተፈተሹም ሳይፈተሹ ነው የተመለሱት
- እዚያው ነበሩ እኮ ውጪ ላይ በር ላይ ነበርኩ ብለዋል
- ትቼዋለሁ
- በማግስቱም ይሄ መጅሊስ ሌባ ይውረድ እያሉ ይናገሩ የነበሩ ማን
- እዚያ ያለ ፈታሹ ነዋ ሌላ አዲስ ሰው የታለ እዚያው ያለው ነው ይውረድ የሚለው ማን ብዬ ልንገርህ ሁሉም ሺ ሰው ነው ሺ ሰው ይውረድ ብሏል ብዬ ለእያንዳንዱ ካሜራ አልያዝኩ በምንድን ነው አንስቼ የምነግረህ ይውረድ የሚለው ነው የሰማሁት እኔ በቃ አለቀ ፖሊስ ሌባ መጅሊስ ሌባ እኛ አልመረጥነውም ያልመረጥነው ኮሚቴ ነው
- ይበቃዎታል ሌላ ጥያቄ አዳምጡ
- ሀጂ ናስር ቅድም እርሶ ጩኸት ብጥብጥ ረብሻ ብለው የተናገሩት ነገር ባልተለመደ ሁኔታ አላህከበር ስለተባለ ነው ሀጂ ናስር ቅድም እርሶ ረብሻ ጩኸት ብጥብጥ ነበረ ያሉት ባልተለመደ ሁኔታ ብዙ ሰው አላህከበር እያለ ስለተሰበሰበ ነው ሰምተውኛል ሀጂ ናስር ?
- እየሰማሁ ነው
- ብዙ ሰው ባልተለመደ ሁኔታ ተሰብስቦ አላህከበር ቅድም እንደውም አፉን አንድ አድርጎ አላህከበር ስላለ ነው ረብሻ ነው ያሉት ?
- መልስ ነው
- ይኸውሎት ረብሻ ብጥብጥ ብለዋል አይደለም ረብሻ እና ብጥብጥ መሆኑን እንዴት አወቁ ነው ?
- የብጥብጥ ብጥብጥ ነው እንጂ ከእዚያ በላይ ብጥብጥ ምን አለ ብጥብጥ ነው በቃ
- እኮ አላህ ከበር ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- በምን ይገልፁታል ነው ?
- አላህከበር የሚባለው ቃላት እኛ በቀን 5 ጊዜ እንሰግዳለን አላህከበር አሁንም ስንነሳም /ግልፅ ያልሆነ/ አላህከበር ማንኛውም ሙስሊም ይላል ይሄ ከተሰጠው ገደብ ውጪ ነው አላህከበር
- ከሰዓቱ ውጪ ስለተባለ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከሰዓት ውጪ በመሆኑ እና ገደቡ ያለፈ አላህክበር ነው በማይገባ ሰዓት የሚባል አላህክበር ነው
- ከሰላት ውጪ አላህክበር አይባልም ?
- ያው ግልፅ ነው መልሰውታል እኮ ሌላ ጥያቄ ነው
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት
- ከምን ውጪ ?
- ከሰላት ውጪ አሁን እሳቸው በ 5 ወቅት ስንሰግድ ነው አላህክበር የምንለው ከሰላት ውጪ አላህክበር አይባልም ሀጂ ?
- አላህክበር የሚባለው የሰውዬው እንደልማዱ ነው አንድ ነገር ሲያጋጥመው አላህክበር ብሎ የራሱ ያው ዘራፍ እንደሚባል በቃ ቃሉ አላህክበር የሚለው ነገር ላይ ይቀድመዋል ማንኛውም ሰው አይባልም አይደለም  ይሄ አላህክበር ከስነ ስርዓት ያለፈ አላህክበር ነው ሰዓቱን የጠበቀ እና
- ይበቃል
- ሁከት የተሞላት አላህክበር
- ሌላ ጥያቄ አዳምጡ
- ሀጂ የምንጠይቆትን ነገር አጠር አድርገው ብቻ መልሱልን አላህክበር ማለት ምን ማለት ነው ?
- አላህ ትልቅ ነው ማንም በቃ እሱን የሚያክል የለም በቃ በአለም ያለው እሱ ብቻ ነው በቃ ለማለት ነው
- ቅድም የሚናገረው ሰው አቡበከር ነው አቡበከር ስለመሆኑ እኔ አላውቅም ግን ሰው ነግሮኝ ነው ብለዋል ይሄ የነገሮት ሰው አቡበከር ስለመሆኑ በደንብ ይወቅ አይወቅ እርግጠኛ አይደሉም አይደል ?
- አይደለሁም
- ይሄ ነገረኝ ያሉት ሰው አቡበከር መሆኑን አቡበከር እስላማዊ ትምህርቶችን ሲያስተምር ያውቃሉ ?
- አላውቅም
- እርሶ ወደ መስኪድ ውስጥ ሲገቡ ጥበቃዎቹ በቦታው ነበሩ ?
- ማንም የለም የእኛ  ጥበቃ ማንም ሰው የለም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማንንም ሰው አልነበረም ?
- ያለ ጥበቃ በውስጥ በኩል ያሉ ጥበቃዎች ጥበቃ እና ካዲም ይለያል
- ግን ነበሩ እነሱ ?
- አይደለም አዳምጠኝ እንጂ ጥበቃ እና ካዲም ይለያል እኛ ጥበቃ ቁርአን ቦታ ቁልፍ ቦታ ላይ ካልሲ ማውጪያ ቦታ ላይ ዋና ቁርአን ኢማሙ ቦታ ላይ ነው የምንገባው እኛ ጥበቃው በራፍ ላይ ይኑር አይኑር እሱን የራሴ ነው እንጂ የማውቀው ስለጥበቃው የማውቀው ነገር የለም
- ሲገቡ አላዩዋቸውም ?
- የማውቀው ነገር የለም ስለራሴ ብቻ ነው
- ያው ካዲም ነኝ 40 ዓመት አንዋር መስኪድ ሰርቼአለሁ ስላሉ በደንብ ያውቃሉ ብዬ ነው ይሄንን ጥያቄ የምጠይቆት ?
- አውቃለሁ
- አንዋር መስኪድ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች እየገቡ እያደሩ ትቸገራላችሁ አይደል መስኪዱን ምንጣፉን እያበላሹ ትቸገራላችሁ አይደል የሚያስቸግሯችሁ ሰዎች አሉ አይደል ?
- እኔ አሁን ይሄ ነገር ጥያቄ አልገባኝም እሱ የራሴ የዕለት በዕለት ስራ ያስቸገሩኝ አስቸገሩኝ የእለት በዕለት ስራዬ የራሴ እንጀራዬ እስከሆነ ድረስ የምወጣበት እራሴ ነኝ እንጂ እዚህ ፍ/ቤት ቀርቦ ስለምንጣፍ ያስቸግሩኛል ያስቸግሩኝም የሚለውን እንትን ይሄ አግባብነት የለሌለው ጥያቄ ነው ይሄንን አስቁምልኝ ስነ ስርዓት
- የተከበረው ፍ/ቤት በእዚህ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ ካላስተካከለ መጠየቅ አንችልም እኛ
- ስርዓቱን እየመራ ያለው ይሄ ፍ/ቤት ነው በተደጋጋሚ እየነገርኖት ነው
- ይቅርታ እሺ
- በተደጋጋሚ የምንነግሮት የሆነ የቅንነት ነገር ውስጥ ላይ ያለ መሆኑን ስለምናውቅ ነው ቅድም ነግረናል ስለዚህ ይሄንን ስነ ስርዓት እየመራ ያለው ይሄ ፍ/ቤት ነው እርሶ የሚያውቁትን ብቻ ቅድም እንዳልኩት ቅድም ያልነውን ነው የምንለው አሁንም ይሄንን ነው መመለስ ያለቦት ጥያቄው ግን ምናልባት አግባብነቱ ብዙም አልታየኝም ሌላ ጥያቄ ብታደርጉት ይሄ አድሯል አላደሩም
- አግባብ ነው እስቲ ወይ አስተካክለን እንጠይቀለን የተከበረው ፍ/ቤት
- እዚያ ውስጥ ሌላ ሰው ነው ያደረ ለማለት ነው ?



224

655

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁሉም እንቸገራለን የሚል ነገር ስለተናገሩ የሚቸገሩት በምን ምክንያት ነው የሚለውን ፍ/ቤቱም እንዲረዳ ነው
- እኮ ወይ ሁሉም እሱን ወይ በምንድን እንደሚቸገሩ
- እኮ ያው መርቱን ለመጠየቅ
- እሱን መንገድ አስተካክላችሁ ጠይቁ
- እሺ ሀጂ ናስር አንዋር መስኪድ በተለይ አዲሱ መስኪድ ውስጥ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች እየገቡ እንደውም የሰከሩ ሰዎች እየገቡ ትቸገራላችሁ ምንጣፍ ያበላሻሉ እቃ ይሰብራሉ አይደለ?
- አሁን ይሄንን ጥያቄ
- አይደለም የሚያውቁትን ከሆነ ያውቁታል የማያውቁት
- የማውቀው ነገር ያ እቃም ሰበሩ አደሩም እኔ ብዬአለሁ የዕለት በዕለት ስራዬ ስራ የሰበረውም ነገር ላይ ጠግነን እኛ ባለው ነገር ላይ እንደጠባዩ ሙስሊም አትግባ አይባልም ሙስሊም መስኪድ አልፎ ከገባ በኋላ በሰላማዊ መንገድ ሰግዶ ማንኛውም ሰው የሚተኛውም ይተኛል የፈለገውም አረፍ ይላል
- አለ የለም ነው እሱ ነገር ነበረ ?
- አለ እሱ አለ ግን እኔ እነሱ ጋር
- መቼ ነው የነበረው ይሄ ?
- እሱ እድሜ ልኩን በቃ ሰው ባለበት ልክ ይኖራል እሱ ችግር ነዋ የመስኪዱ ችግር ነው በቃ ምንም ማድረግ አይቻልም
- አመሰግናለሁ መልሰውኛል አሁን በ 7 እና 8 ቀን ካሉት ቀን በፊት የነበረውን ማን እንደፈፀመው አያውቁም አይደል እርሶ ?
- አላውቀውም
- በወቅቱ ሰላት ተሰግዷል እንዴ መስኪድ ውስጥ ሰላት ተሰግዷል
- መቼ
- እዚያ አንዋር መስኪድ ውስጥ በ 7 ቅዳሜ ያሉት ቀን ሰላት ተሰግዷል ?
- ሰግደዋል የሰገዱትም እኔ በኔም ሰፈር ሆኜ ይሰማል ሀገር እየሰማሁ ነው ከመስገድም ሌላ አልፎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥሩ መልሰውልናል
- 10 ሺህ ሰው የሚሆን ሰግዷል
- መልሰውልናል ብዛቱ 10 ሺህ ሰው ያሉት ውጪ ድረስ በጣም ብዙ ሰው ስለነበረ ነው ?
- በቃ ሁሉም ያው እንግዲህ የመጣው ሁሉ አላህከበር ስለሚል መስገድ አለበት የሚለውን ጥርጣሬ አድሮብኝ ነው እንጂ እዚያ /ግልፅ ያልሆነ/
- ብዛቱን በተመለተ ?
- ብዛቱ በቃ 10 ሺህ በቀላሉ ይሞላል የእዚያን ቀን የእሁዱ ቀን
- ያው ግምት ነው ግምት ነው እሱን ግምት ይዛችሁ
- ግምት ነው 10 ሺህ ይሞላል ሴቱም በኩል አሁን ከወንዱ ሴቱ እየበለጠ ነው የመጣው ሴቱ ከወንዱ ሴቱ ይበልጣል
- ኢማሙ እና ሙአዚኑ ገብተው መደበኛ ስራቸውን እንዲሰሩ እንዲያሰግዱ አላህከበር እንዲሉ ተጠርተው ነበር አይደል ?
- ተጠርተዋል
- እርሶም ሌሎች ሠራተኞቹ መደበኛ ስራቸውን እንዲሰሩ ያለምንም ችግር እንዲያከናውኑ ተጠርተው ነበር አይደል ?
- ተጠርተዋል አዎ
- የአንዋር መስኪድ ደንበኛ የሆኑ ሽማግሌዎች የመጀመሪያው ሰልፍ እንዲለቀቅላቸው ተጠርተዋል አይደል ?
- እሱ ውስጥ አልገባውም አላየሁም ያላየሁትን አልናገርም ውስጥ ማን አስገባኝ አልገባሁም እኮ ውጪ ነው ያለሁት እኔ
- ሀጂ የቢሮ መስታወት እና በር ተገንጥሎ ነበር ብለው ነበር መቼ ነው ነበር የተገነጠለው ?
- ተናግሬአለሁ
- ቀኑን ያስታውሱታል ?
- ቀኑን አላውቀውም በሣምንቱ ባለው ጊዜ ውስጥ ተሰብሯል ያየሁት ነው አይኔ ነው እኔ ለአላህ ብዬ ነው የምናገረው ለማንም ብዬ አይደለም ግን እነሱ አይደሉ የሆነ ሰው /ግልፅ ያልሆነ/
- በቃ ይበቃል
- ቀኑን አያውቁትም ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላውቀውም
- ተገንጥሎ ነው ያዩት እርሶ ?
- አዎ ተሰብሮ አይቼአለሁ ተገንጥሎ አይቼዋለሁ አላውቀውም
- ይኸውላችሁ አዳምጡ 1ኛ መልስ ከተመለሰ በኋላ ባይደገም ጥሩ ነው ቅድም በገለፅነው መንገድ መልስ ከተደገመ በኋላ እንደገና ሲደገም ተመልሶ ሪደንደንት የሆነ ወረቀት ነው የሚወጣው እዚያ ስለዚህ አሁን እሳቸው መልሰዋል ከተመለሰ በኋላ ወደ ሌላ ጥያቄ መሄድ ነው አሁን እሳቸው መቼ እንደተሰበረ አላውቅም ቀኑን አላስታውስም አሉ በቃ ይሄ ከተመለሰ ሌላ ጥያቄ
- አዎ በእዚያን ቀን ነው እሺ ወይ ከእዚያ በኋላ መቼ ነው ያዩት ?
- መቼ እንደሆነ አላውቅም አላስታውስም ከሣምንት በኋላ ነው ያወኩት በፊት ነው ያወኩት እኮ
- የተከበረው ፍ/ቤት ሌላ ነገር አሁን እየጠየኩ ያለሁት መቼ ያዩት ነው ተሰብሮ መቼ አዩት ?
- መቼም ሆነ መቼም አላወኩትም ነው ቀኑን አላውቀውም ተሰብሯል
- ቆዩ እስቲ ምስክር ተመልሷል
- ሀጂ ናስር
- ጥያቄ ባይደገም ከእዚህ በኋላ በጣም እየተደገመ ስለሆነ አንድም ከተደገመ እናሳልፍም
- ሀጂ ናስር ቅድም ከሐምሌ 7 እና 8 ውጪ በቀን በቀን ሁሌም ረብሻ ነው ብለዋል አንዋር ይሄ ማለት አሁንም አለ ማለትዎ ነው ?
- አሁንም በሣምንት አርብ መስገድ አልተቻለም አሁንም ፈተና ነው የመጣብን በቃ በአጭሩ አሁንም
- ይበቃናል መልሰዋል
- ምንድን ነው ረብሻ ሲሉ አሁን እስቲ ይግለፁ ሰው ምን እያለ ነው የሚረብሸው ?
- በቃ የማውቀው ነገር ሰው ምንም ያለው ይኸው ነው በቃ አለቀ አሁንም ይኸው ነው አላህክበር ነው አሁንም የታሰሩ ይፈቱ ካልተፈቱ ያው ብጥብጥ ነው ምን ጊዜም የሚለው ነገር ላይ እየቀረበ ነው
- ይበቃል
- ጋሽ ናስር ይሰሙኛል ?
- እየሰማሁ ነኝ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም መጅሊስ ይውረድ ይሉ ነበር ሲሉ ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- እነዚያ ፊት የነበሩት መጅሊሶች በሕዝቡ ጥያቄ ወርደዋል አይደል አሁን ወርደዋል ስራ ላይ የሉም አይደል ?
- ያንን መስኪድ ያ መጅሊስ ቢወርድም
- ወርዷል አይደል አጭር
- ሕዝብ ነው የመረጠው መስኪድ ላይ አሁን ያለው ሕዝብ የመረጠው መጅሊስ ነው እንጂ
- ወርዷል ግን ዞሮ ዞሮ ?
- ወርዷል ሳይሆን ወርዶ ተመርጧል በቃ ድሮ ያላየነው ነገር ላይ አሁን አዲስ መጅሊስ ተቋቁሟል
- ቅድም የነገሮት ሰው 17ቱ ኮሚቴዎች ናቸው ብሎዎታል አይደለ ?
- አዎ
- በደንብ ተናገሩ
- ብለዋል ብለዋል ግልፅ ነው ጠይቁ
- እዚህ ላይ እንዲገባ ስለፈለኩ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- 17 እኮ ቅድም ብለዋል እኮ
- ላረጋግጥ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- 17 ኮሚቴ አሁንም እየተባለ ነው ያለው አሁንም ረብሻው 17 ኮሚቴ ካልተፈቱ አሁንም ነውጡ ይቀጥላል ነው አጭር ቃል
- ካልተፈቱ ይቀጥላል ነው ?
- አዎ በሣምንት ጁማ መስኪድ ለቀናል ማለት ይቻላል
- ቅድም አንዋር መስኪድ ውስጥ አንድ ፖሊስ መመታቱን ሰምቼ ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- ግቢ ውስጥ ነው የተመታው ፖሊሱ ነው አይደል ?
- እዚያው በራፍ ላይ ይሁን ግቢ ላይ ይሁን ቢሮ አካባቢ ላይ ሊገላግል በገባበት ተመታ ሲባል ወሬ ነው የሰማሁት እንጂ ፖሊስም አላየሁትም ሲመታም አላየሁትም ሲሰበርም አላየሁም ብዬአለሁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ የት ተመታ እንበል እስቲ ?
- ተመልሷል
- ቅድም ሰው ፖሊስ ሌባ ነው እያለ ነበር ብለዋል በሌላ በኩል ብጥብጥ ነበር ብለዋል ከማን ጋር ነበር ብጥብጡ ?
- እራስ በራሱ ነዋ
- ሰው እርስ በእርስ ?
- የሚያውቀው ነገር አለ አጀንዳው እራሱ ያውቀዋል እንጂ የማላውቀው ነገር
- አይደለም ጋሽ ናስር ይኸውሎት እኔ የምጠይቆት ብጥብጥ ነበረ ሲሉ ሕዝቡ ከፖሊስ ጋር ነው ሌባ ብሎ የነበረው ፖሊስን ፖሊስ እየመጣ ስለከለከለው ነው አይደል ነው አይደል ?
- አሁን የተመታም ሰው የለም
- ቆይ ቆይ ይኸውሎት ፖሊስ አይተዋል በእዚያ በነበሩበት ጊዜ ?
- ፖሊስ የለም እዚያ ጋር አንድም ፖሊስ የለም
- ሌላ ጥያቄ
- መቼ ነበር ያልነበረው ፖሊስ ?
- ቅዳሜም የለም እሁድም ፖሊስ የሚባል ነገር የለም ግን /ግልፅ ያልሆነ/ የለም አለፍ አለፍ ብለው ይቆማሉ እንጂ አይነኩም አይናገሩም የማንም ወገን አይደሉም ዝም ብለው ነው የሚያዩት
- አለፍ አለፍ የት ነበር የቆሙት ?
- ሲኒማ ራስ እዚያ አልፎ አልፎ በቃ የራሳቸው ተራ ፖሊስ ቆሞ ቆሞ እዚያ እንትን ይላል እንጂ ይሄንን ያህል ቀርቦ እዚያ ገብቶ ፖሊስ ገብቶ አልዳኘም እዚያ ውስጥ
- እኮ ሲኒማ ራስ ሕዝቡ አልደረሰም ነበር ?
- ማንም ሰው ይድረስ እንጂ ማንም ሰው በቃ ፖሊስ አይነካም ከአሁን በኋላ ፖሊስ እስቴዲየም ገብቶ እንኳን ኢማሙ ላይ እንኳን ገብቶ አንቆ ሲያወጡት ፖሊስ አልተናገረም ሠራዊቱ ያ ሁሉ መሣሪያ ተይዞ አልተነካም አልተናገረም ፖሊስ በቃ ስነ ስርዓት ነው
- ስለዚህ እያሉኝ ያለው ፖሊስ ባልነበረበት ነው እየተሰደበ የነበረው
- ይሄ ተመልሷል እኮ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፖሊስ
- ቆይ ቆይ ምስክር በቃ ተመልሷል ሌላ ጥያቄ
- አቡበከር ሌላ ነገር ሲናገር አልሰሙም እርሶ ?
- አልሰማሁም
- ጨረሳችሁ
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አንድ ጥያቄ አለኝ ሀጂ ቅድም ሲገልፁ ሀጂ ከእዚያ ሲጠየቁ ሼዎች እነኚህ ኢማሞች ስራ ጀምሩ ተብሎ ተገልፆ ነበር ወይ ሲባሉ አዎ ብለዋል እና ቅድም ደግሞ በእኛ በዐቃቤ ሕግ ሲጠየቁ መስኪዱን እነሱ እንደተቆጣጠሩት ኑ ብለው ጥሪ አድርገዋል ብለው ገልፀዋል ይሄ አጠራራቸው በአንድ መልኩ እነሱ ያንን መስኪድ እንደተቆጣጠሩት በማይክራፎን ሲናገሩ እና ኑ ስራ ጀምሩ ብለው ጥሪ ማድረጋቸው ተገልፆዋል በሌላ መልኩ ደግሞ አሁን እርሶ እንደገለፁት ይሄንን መስኪድ እነሱ ናቸው እንዴ የሚያስተዳድሩት ጥሪ ማድረጋቸው ምንድን ነው ማለቴ ነው እነሱ ስለሚያስተዳድሩት ነው ወይስ ምንድን ነው በአንድ መልኩ ተቆጣጥረነዋል ብለዋል ?
- እውቅና ስለሌላቸው መስኪዱን ስለማይወክሉ ነው
- አቤት
- በእዚያን ጊዜ እውቅና ሊወክሉ ግቢ ውጡ ለማለት ስለማይችሉ ነው እነሱ አይመሩንም በሚል ነው ያልገባነው
- ማን ነው ይሄንን የሚለው ?
- ግቡ ቢሉም እኛ አንገባም ለሕይወታችን አደጋ ስለሆነ በእዚያ ረብሻ ላይ እንዴት ገብተን ስራ እንሰራለን በሚል እራሳችንን ጥርጣሬ ላይ ስላለ ኑ ግቡ ቢባል ማን አምኖ በእዚያ ሕዝብ ሺ ሕዝብ ገብቶ እዚያ ውስጥ ገብቶ ስራ ልስራ ብሎ ይገባል በእዚያ ቀን በ2ቱ ቀን ላይ ምንም መግባት አይቻልም
- ሌላው ቅድም ሲጠየቁ ማለት ነው አንዳንድ ጊዜ የሰከሩ ሰዎች ይገቡ የለም እንደዚህ ምናምን ተብሎ ተጠይቀዋል ቅድም ደግሞ ሲነግሩ የአቶ አባስን ቢሮ ጨምሮ እንዲሁም ደግሞ የተለያየ ያ ያሉት በር እሱ ሁሉ ተገንጥሏል ልክ በእንደዚህ ሁኔታ እርሶ በሚያስታውሱት ማለት ነው



661

http://ethcriminalawnetwork.com/

ይሄ ነገር ከመከሰቱ በፊት ሰላማዊ በሆነ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ነገር ገጥሞት ያውቃል በር መገንጠል ቢሮ መሰበር እንዲህ ገጥሞት ያውቃል ሀጂ ?

- እንኳን ሊሰበር ሰው የሚመጣው ለፀሎት ከፈጣሪው ጋር ሊገናኝ ነው እንጂ እዚያ ቦታ ላይ አሁን በአጭሩ የአንዋር መስኪድ ጠጅ ቤት ሆኗል በእግር መንገዴ ልንገራችሁ እና አንዋር መስኪድ መስኪድ መሆኑ ቀርቶ ተበላሽቷል በቃ በአጭሩ
- ይበቃል
- በቃ አለቀ
- ሌላው ቅድም ሲገልፁ እርሶን ልፈትሽ ያለው የአንዋር ጥበቃ መደበኛ ጥበቃ ነው ?
- ካዲም ነኝ ከ 38 /40 ይገፍአለሁ መረጃ ያለኝ ሰው ነኝ መልሼ ነግሬሀለሁ እሱ ነገር
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/በት
- እናመሰግናለን ጨርሰዋል
- ቀጣይ ምስክር ካለ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት ?
- ትክክል
- ስምዎን ያው የአባትዎን ስም ሳይጨምሩ የራስዎን ስም ብቻ ይነግሩናል
- አብዲሳ
- ስንተኛ ናቸው ዐቃቤ ሕግ ?
- 42ኛ
- ለምስክርነት ስለመጡ ከእዚህም ከእዚያም ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል ፊትዎን ግን ወደ ፍ/ቤቱ እያዞሩ እያዳመጡ የሚያውቁትን ይመልሳሉ እነ ማን ላይ ለመመስከር ነው የመጡት ዛሬ ?
- እነ ሙባረክ
- ሙባረክ ማን ነው ?
- አደም
- ሙባረክ አደም ሌላ ?
- አዎ በእሱ ላይ ነው በእሱ እና ሌሎች ነበሩ /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌሎቹን ስማቸውን አታስታውስም ?

224 662



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሙባረክ /ግለፅ ያልሆነ/
- አይ ክሱ ውስጥ ያሉት
- እዚህ ያለው ነው
- አዎ
- እዚህ ያለው አሁን የምለውን ሰው ማለት ነው ሙባረክ
- ሙባረክ አደም ?
- አዎ
- ሙባረክን በአካል ነው በስም ነው የሚያውቁት ?
- በአካልም አውቃለሁ
- በአካልም ያውቃሉ ?
- አዎ
- ማሳየት ይችላሉ አሁን ?
- እችላለሁ
- እስቲ ስንተኛ ላይ የተቀመጡ እሱ ነው ስንተኛ ነህ 20ኛ ተከሣሽን አመልክቷል ዝምድና ጥል አሎት ከሙባረክ ጋር ?
- የለም
- ምንም የለም ?
- አዎ
- ምን ሲያደርግ ነው ያዩት አጠር አድርገው ?
- በአወሊያ ት/ቤት ማለት ነው አወሊያ
- አወሊያ ?
- አዎ
- መቼ ?
- ጥር ወር አካባቢ
- ጥር ወር አካባቢ አወሊያ አዩት ?
- ት/ቤት ውስጥ ማለት ያው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዋና ጥያቄ ዐቃቢ ሕግ
- ምስክር አሁን በቁመው ያሳዩት ተከሣሽ ከጥር ወር ጀምሮ ነው የማውቀው ብለዋል ?
- አዎ
- ጥር የትኛው ጥር ነው ?
- ያለፈው ዓመት
- ስንት ዓ.ም ማለት ነው ?
- 2004
- 2004 ?
- አዎ
- የት ነው ያዩት ?
- ያው አወሊያ መስኪድ እዚያው ት/ቤት ውስጥ አለ በእዚያ ት/ቤት ውስጥ ያው ተማሪዎችን አንዳንድ ነገሮች የማነሳሳት ስራ በሚሰራበት ወቅት እዚያ ተመድቦ ስከታተለው የነበረ
- አሁን ከመጀመሪያው ጀምሮ አሁን አንዳንድ ነገር ያሏቸው በዝርዝር ያስረዱ እስቲ ይጀምሩ እና ምን ምን ያደርግ ነበረ ሙባረክ ?
- ያው በት/ቤት ውስጥ ማለት ያው መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል መጅሊስ ያልመረጥናቸው የመጅሊስ አመራሮች ይውረዱልን እና
- ይሄንን የሚለው በምንድን ነው ?
- ማለት ተማሪዎችን በመሰብሰብ እንደዚህ መድረክ ነገር እንደዚህ አለ እዚያ ላይ በመሰብሰብ ማለት ነው
- ማን ነው የሚሰበስበው ?
- እሱ ነው ማለት ግቢ ውስጥ በጣም ተሰሚነት አለው
- ማን ነው እሱ ?
- ሙባረክ
- እየሰበሰበ አሁን የጠቀሱትን መጅሊስ አይወክለንም መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ይላቸው ነበር ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ይላሉ ተማሪዎቹ ?
- ያው ተማሪዎቹ እዚያ አካባቢ ላይ የመሬጫህ የተለያየ ሰብሰቦ የማስሬጫህ ነገሮች አሉ
- እንዴት ነው የሚያስሬጫሁቸው ምን እያለ ?
- ያው አላህከበር በማለት አላህከበር በታይማኖታችን ድርድር የለም ምናምን እያለ ብዙ ነገሮች
- ብዙ ነገሮች የሚሏቸው የሚያስታውሱት ካለ እንዲህ ይላል እንዲህ ይላል እያሉ ይንገሩን ?
- ከማስታውሳቸው አንዱ ያው የአረብኛ ኮሌጁ የቋንቋ ኮሌጅ መንግስት ዘግቶታል እና ያው እነዚህ ነገሮች ናቸው
- ምን ይሁን ታዲያ ?
- መከፈት አለበት እና ወገን ስማ ሙስሊም ስማ ንቃ ምናምን በሚል እዚያ እንትን ላይ ቆሞ የመናገር ነገሮች ነበሩ
- እኮ ይናገር ነበር ?
- አዎ
- ሁሉም ተማሪዎች ይከተሉት ነበረ ?
- በአብዛኛው ማለት የተወሰኑ የማይከተሉ ሰዎች አሉ ይሄንን ነገር የማይደግፉ
- ጥሩ ይሄንን ነገር የማይደግፉ የማይከተሉ ሰዎች አሉ ?
- አዎ
- ምን ያደርጋል ተከሳሽ እነዚህን ሰዎች ?
- እነዚያ ሰዎች አሁን ለምሳሌ መውጣት የሚፈልጉትን እንዳይወጡ በማድረግ በር ላይ እሱ እና ሌሎች የእሱ ጓደኞች አሉ እነዚህን ሰዎች የመከልከል ሁኔታዎች ነበሩ
- እኮ እንዴት አድርጎ ይከለክላቸዋል ?
- በቃ እንይወጡ በማድረግ ማለት ነው ይሄ ምንድን ነው ማለት በእዚህ በተቀደሰ ቦታ እንኳን ሌላ ቦታ ይታደር አይደለም ወይ ምናምን በሚል አንድ ቀን ያው አስተባብሮ ያሳደሩበት ሁኔታዎች አሉ
- እሱ ነው የሚያስተባብረው ?
- አዎ እሱ እና የሆኑ 2 ግብረአበሮቹ አሉ
- የት እደሩ ነው የሚለው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያው ት/ቤት ውስጥ አንድ ቀን አድሯል
- አድሯል ?
- አዎ
- ማደር አይችሉም እንዴ ት/ቤት ውስጥ የት ነው የሚያድሩ ሌላ ጊዜ ?
- ሌሎቹ ተማሪዎች ያው ወደቤታቸው የሚሄዱ ናቸው /ግልፅ ያልሆነ/ የእዚያን ዕለት ግን ማንም ሰው እንዳይወጣ እነሱ በማድረግ ግቢ ውስጥ እንዲያድሩ አድርገዋቸዋል
- ጥሩ ቅድም እነዚህ የእሱን ኃሳብ የማይደግፉ ተማሪዎች አሉ ብለዋል ?
- አዎ
- እነሱን እንዳይወጡ ከከለከለ በኋላ ምን ያደርጋቸዋል ?
- አሁን እንዳልኩት ማለት የማስጮህ ነገሮች እነዚህ ነገሮች ያደርግ ነበር
- እምቢ ያሉትን ሰዎች ?
- አዎ ያው ማለት እምቢ ያሉትን የመመለስ ስራ ወደ ግቢ ውስጥ እንዲመለሱ
- ምን እንዲያደርጉ ነው የሚመልሳቸው ?
- ያው የእነሱን ዓላማ ደግፈው እንዲጮሁ ማድረግ ማለት
- ጥሩ እሺ ከእዚያ በኋላስ ሌላስ ምን ያየኸው ነገር አለ ?
- ሌላ በአንድ ወቅት ማለት ከእስልምና ጉዳዮች ተወክለው የመጡ ሰው ነበሩ ስማቸውን አላስታውስም እና ምንድን ነው ችግራችሁ ብለው ያለውን ነገር ለመፍታት መጥተው ነበር እና የእዚያኔ ችግራቸውን አንድ በአንድ እየጠየቁ ነበር ሌሎቹ ከእዚያ ይሄ ማይኩን ይቀማው እና እሱ
- ማን ነው የቀማው ?
- ሙባረክ
- ሙባረክ ?
- አዎ
- ማን ነው ማይክ የተቀማው ሰውዬ ?
- ሰውዬው ከእዚያ ከእስልምና ጉዳዮች የመጣ ሰው ነው
- ስሙን ያስታውሳሉ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስሙን አላስታውስም
- አያስታውሱም ?
- ተናግሬአለሁ
- ከእስልምና ጉዳዮች የመጣው ለምንድን ነው ?
- ያለውን ነገር ለመፍታት ነበር ማለት ችግሮች አሉ እነሱ የሚሏቸውን ችግሮች ለመፍታት ነበር የመጣው ከእዚያ ያው ያለባቸውን ችግሮች ልጆች እየጠየቁ ነበረ የአረብኛ ቋንቋ መምህር ይመስሉ አስተማሪዎች ዘበኞች ምናምን የተባረሩት ይመስሉ በሚል ዓላማቸው ይሄ ነበር እነሱ የሚናገሩት ማለት ነው
- እነ ማን ?
- እነ ሙባረክም አጠቃላይ ግቢው ተማሪዎቹ
- መጀመሪያ ይሄንን ነበር የሚናገሩት ?
- አዎ ማለት የእዚያን ዕለት ሰውዬው ምንድን ነው ጥያቄአችሁ መፈታት ያለበት ነገር መፈታት አለበት በሚል ከእዚያ ተወክሎ የመጣ ሰው ነበር እና በወቅቱ እሱ ማይኩን ቀምቶ
- ቆይ አይደለም ጥሩ ወደ እዚያ ትመጣለህ እነዚያ የእስልምና ጉዳይ ሰዎች ሲመጡ አሁን ያልከው የአረብኛ ት/ቤቱ ተዘግቷል ይከፈትልን መምህራኖቻችንን ይመለሱ
- የተባረሩት አዎ
- ጥበቃዎቹ ይመለሱ ነው ያልከው ?
- ትክክል አዎ
- ጥበቃዎቹ ይመለሱ ?
- አዎ
- ይሄንን ብቻ ነው ያቀረቡት ለሰውዬው ?
- አዎ ሌላ ጥያቄዎቹን በአብዛኛው ያው እንትን ባልልም እነዚህን ግን በዋነኛነት
- ያኔ
- ያቀረቡ ጥያቄዎች እነዚህ
- ጥሩ ያኔ መጅሊስ አይወክለንም መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ብለውታል ለሰውዬው ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ አጠቃላይ እያሉ ነበር ሰውዬውም ከገባ በኋላ እያሉ ነበር ይሄንን እንደዚህ እያሉ ነበር ከእዚያ ሰውዬው ማይኩን ቀምተውት እሱ
- መልስ መስጠት ጀመረ ሰውዬው ?
- ማለት ጥያቄውን እየያዘ ነው መልስ መስጠት ማለት እነዚህ መምህራኖቹ የሚመለሱበት መንገድ ምናምን እየነገራቸው እያለ ነጥቆ እሱ
- ማን እሱ ?
- ሙባረክ
- ሙባረክ ማይኩን
- እኛ ብቻ የምንልህን መልስ ምናምን በሚል እኛ ብቻ የምንልህን መልስ ከእዚያ በኋላ የእዚያኔ በቃ ማለት ጥሩ ነገር አልተፈጠረም ሰውዬውም እንትን አለ
- ምን አደረጉ ጥሩ ነገር አልተፈጠረም እስቲ አብራሩት ?
- ማለት ያው ጥሩ ነገር አልተፈጠረም ያልኩት ሰውዬው እንዲናገርም አላደረጉትም በወቅቱ
- ከእዚያ ምን ሆነ ምን አደረጉት ?
- ሰውዬው ያው በተፈጠረው ነገር ያው በፖሊስ እርዳታ ወጥተዋል ከግቢ እና
- ለምን ፖሊስ ረዳው
- መልካም ሰዎች ማለት ነው
- ለምን ፖሊስ ረዳው ?
- ማለት በቃ እነሱ ለመደብደብም ሃሳብ ነበራቸው እንዲህ በወቅቱ ባየሁት ነገር
- እንዴት አወቁ እርሶ ?
- እዚያ ቅርብ ነበር
- እኮ ምን አይተው ነው ለመደብደብ ሃሳብ ነበራቸው ያሉት ?
- ማለት በቃ ከእዚያ በኋላ ጥያቄውን የመመለስ እንትኑን ሊያስቀጥሉት አልቻሉም እነሱ ከእዚያ ሰውዬው ወጣ እነሱ ሰውዬው መኪናውን እንደዚህ ወደአቆመበት ቦታ ተሰብስበው ሄደው
- እነ ማን
- እሱ ነው እንትን የሚላቸው
- ማን እሱ አይበሉ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሙባረክ
- ሙባረክ ምን ይላቸዋል ?
- ከነበሩበት ከእንደዚህ አውርደቻቸው ወደ ሰውዬው መኪናው ወዳለበት ሄዱ ከእዚያ ክብ ሰርተው እዚያ ጋር ሲጮሁ የተለያየ ነገር ሲናገሩ ነበር ሌላ ቀን እንደሚሉት ማለት ነው ቅድም የገለፅኩት ከእዚያ በኋላ የመኪናውን 4ጎማ ቱንዎ አተነፈሱ መኪናውን ይዞ እንዳይወጣ ማለት ይሄ ነው የማውቀው
- ጥሩ አንተ በወቅቱ ሙባረክን አናግራችሁት ነበር ተው ምናምን ብላችሁ ?
- አዎ እኔ እና አንድ ዋና ሣጅን ንጋቱ የሚሉት አለ የፌዴራል ፖሊስ በወቅቱ አብረን ስራ ላይ ነበርን እሱ ማለት በተደጋጋሚ ጊዜ የእዚህ እንደዚህ ሲያደርግ አንድ ቀን አግኝተነው ደጅ ያለውን ነገር ነግረነው ነበር ማለት የምትሄድበት አቅጣጫ ጥሩ አይደለም ማለት ጥያቄ ቢኖራችሁ በስርዓት እና በአግባቡ መጠየቅ ትችላላችሁ አሁን ግን የምታደርጉት ነገር መልካም አይደለም በሚል እሱ ለራሱ በአካል እኔ እራሴ ነግሬዋለሁ
- ምን አለ ?
- እስከ እኔ ለኃይማኖቴ እስከ ሕይወት ፍፃሜ ምናምን ብሎ ነው
- ምን ሆነ
- በቃ ለኃይማኖቴ እስከ ሕይወቴ ፍፃሜ ነው አልሰማም ነገር ነው በቃ ሁኔታው
- ዋና ጥያቄ አበቃን
- የተከሣሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- አቶ አብዲሳ እርሶ ጥር ወር ውስጥ አወሊያ ምን ያህል ቆዩ ?
- ለረጅም ጊዜ እዚያ ስራ ላይ ተመድቤ ነበር እዚያው አካባቢ ላይ ማለት ነው
- ከጥር ወር በኋላ ?
- ብዙ ጊዜ ነው ረጅም ጊዜ እዚያ ነበርኩኝ ስራውን ስከታተል ማለት ነው ስራ እዚያ አካባቢ ነበርኩኝ
- ስለዚህ ሁኔታውን ለመከታተል ነበር የሄዱት ማለት ነው ?
- አዎ ያለውን ሁኔታ
- በደንብ ተከታትለዋል ሁሉን ነገር ?
- ትክክል



230 669

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥሩ አሁን ሙባረክ ሰውዬውን ከእስልምና ጉዳይ መጣው ሰው ንግግር ለማድረግ የሞከረው ሰው መቼ እንደሆነ ቀኑን ያስታውሳሉ እንዴ ?
- ቀኑን በውል አላስታውሰውም እዚያው ጥር ወር አካባቢ ውስጥ
- ጥር መጀመሪያ መካከል መጨረሻ ይገምታሉ ?
- ቀኑን በአብዛኛው በውል አላስታውሰውም
- ጥሩ ሰውዬው መጥቶ ማይክ ብሏል ማይኩ የት ጋር ነበር የነበረው ?
- ፊት ለፊት እንደዚህ ደረጃ አለ ማለት እንደእስቴጅ ነገር በሲሚንቶ የተሰራ
- ምን ፊት ለፊት ?
- ከበሩ ፊት ለፊት
- ከየትኛው ግልፅ ያድርጉታ ?
- ፊት ለፊት
- አሁን እዚህ ያለን ሰዎች እንድናውቀው ?
- አወሊያ በሩ ፊት ለፊት የእዚህ በእዚኛው በር ማለት ነው በት/ቤቱ ሳይሆን በፊት ለፊቱ በር በመስኪዱ ባለበት በኩል
- አሁን አወሊያ ብለዋል አወሊያ ግቢ አለው እሺ ጥያቄውን ግልፅ ላደርግሎት ነው ግቢ አለው አወሊያ ?
- በጣም ትልቅ ግቢ አለው
- ጥሩ አሁን ከዋናው በር ወደ ግቢ ተገብቶ ነው ?
- ምኑ
- ማይኩ አለ ያሉት ቦታ በትክክል ስላልገባን ነው ?
- ማለት ግቢው በሩ እዚህ ጋር ነው ልበል በቃ እንደመጋረጃው ነው እስቴጁ ያለው
- ወደ ግቢ ከመግቢያው የመጋረጃውን ያህል ?
- አዎ ርቀቱ እንደዚያ ቢሆን ነው
- ቆይ እስቲ ቁጭ ካልክበት እስከ እዚህ መጋረጃ ነው አይደል ?
- አዎ
- በግምት 8 ሜትር



http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሜትር ብዘም /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚያ ይበልጣል ?
- አይበልጥም
- ጥሩ ሜዳ ላይ ነው ማለት ነው አይደል ?
- ሜዳው ከኋላ ነው ሜዳው ያለው
- አይደለም አሁን ወይም አስፋልት መግቢያው መንገዱ ላይ ነው ?
- አስፋልቱ አለ አይደል አስፋልቱ አሁን በሩ የበሩ አስፋልት አለ ፊት ለፊት የት/ቤቱ አንዳንድ
- አሁን የአወሊያ ግቢ ሲገቡ ግቢው አስፋልት አለው መኪና እንዲሄድበት ?
- ትክክል አዎ
- እዚያው 8 ሜትር ያህል ከዋናው ከግቢው መግቢያ በር ርቀው ሰው እዚያው ነው የተሰበሰበው አሁን ተማሪው አይደል ንግግር ሰውዬው ሲመጡ ሊያናግሯቸው ሲመጡ ተማሪዎች ያሉት እዚያው ጋር ነበረ ?
- አይ ከእዚያ ጋር ሳይሆን
- እስቲ
- መማሪያ ክፍሎቹ እኮ በጣም ሩቅ ናቸው
- እስቲ ቆይ አንዴ ንግግሩ የተደረገው ሜዳ ላይ ነው ቤት ውስጥ ነው ከእዚያ እንጀምር ?
- ፊት ለፊት እንደዚህ ሜዳ
- ሜዳ ላይ ?
- አዎ
- እንደዚህ እስቴጅ ነገር አለ በሲሚንቶ የተሰራ እንደበረንዳ እሱ ላይ ወጥቶ
- ሰውዬው መጡ ቁጭ አሉ ወይስ ቆሙ መጀመሪያ ከመናገራቸው በፊት ?
- መጀመሪያ የሰውዬውን መምጣት ያው መጡ በእነሱ ተወካይ አማካይነት አስተማሪዎቹም አሉ ሌሎቹ እንዲሰበሰቡ አድርገው ከእዚያ የመጡ ሰው አሉ ቢያንስ ጥያቄአችሁን አቅርቡ በሚል ያሉትን ተማሪዎች ሰብስበው አመጧቸው እና እዚያ ጋር እንትን አሏቸው አሁን ያልኩትን እስቴጁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከበር እንደመጡ በእዚያው ተንደርድረው ሳይቀመጡ መናገሪያውን መናገር ጀመሩ ነው እንደዚያ ነው የወረደው ?
- እንደዚያ አይደለም ያልኩት ያን ሰውዬው ገቡ መኪናው ገባ መምጣታቸውን አወቁ የሚመለከታቸው ሰዎች ተማሪዎቹን ሰብስበው አምጥተው ጥያቄአችሁን መጠየቅ ትችላላችሁ እንደዚህ ከመጅሊስ ተወክለው የመጡ ሰዎች አሉ በሚል እንትን ብለዋል እዚያ ጋር ተሰብስበው ተማሪዎች የነበሩም ነበሩ በአብዛኛው ሰብስበው አምጥተዋቸው አሁን ጥያቄዎቻችሁን መቀጠል ትችላላችሁ በሚል
- እኮ አሁን እኔ ለጠየኮት ግልፅ ያድርጉ እና ልክ መጥቶ መኪናው ገባ ከመኪናው ወረዱ ከእዚያ?
- እንደዚያ እኮ አይደለም አሁን ያሉት እኔ እንደተረዳሁት እንደመጡ ወዲያው ወደ ጥያቄ ነው የገቡት ነው መሰለኝ የእርሶ አባባል እኔ እንደዚያ አይደለም ያልኩት መጡ ሰውዬው ገቡ ግቢ ከእዚያ በተወካያቸው አማካይነት አስተማሪዎችም አሉ የእነሱ እነሱም አሉ እነ ሙባረክ ልጆቹን ሰብስበው አምጥተዋቸው ከእዚያ በኋላ ንግግር ማድረግ እንደጀመሩ ምንድን ነውያለው ችግር ችግሮቻችሁን አቅርቡ ተባሉ የተለያየ ተማሪዎች እጅ እያወጡ እየተናገሩ ነበር
- በቦታው ለሚመጡ ሰዎች የተዘጋጀ ወንበር ነበረ እንዴ ?
- ምንም ዓይነት ወንበር አልነበረም ቆመው ነውእሳቸውም የተናገሩት
- ቆመው ነው የተናገሩት ?
- አዎ
- ከእዚያ ማይክ ቀማቸው ብለሽናል እስቲ ከቀማቸው በኋላ የሰውዬው ሁኔታ ልክ ተቀሙ ከእዚያ ምን ሆነ እስቲ አሁን እኛ ላለነው ሰው ስዕሉን አሳየን በትክክል ?
- ማለት አሁን እንዲህ
- የሰውዬው እንቅስቃሴ እስቲ በትክክል አሳየን ?
- ያው ሰውዬው የመደናገጥ ሁኔታ በወቅቱ የመደናገጥ ሁኔታ ታይቶባቸዋል ያው ሲነጥቃቸው ማንም ሰው የሚሰማው ነገር አለ ከእጁ የሆነ ነገር ሲቀማ ትደነግጣለህ ያው የእዚያ ዓይነት ስሜት አይቼባቸዋለሁ
- ከእዚያ ደነገጡ እና ወደ በር ሄዱ ?



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወደ በር ሳይሆን በቃ እንትኑ አልተግባቡም ማለት ያው እሳቸው የሚመልሱት አመላለስ እና እነሱ የፈለጉት አመላለስ እንትን ስላላላቸው እዚያ ጋር የሆነ ግጭት ነገር ተፈጠረ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ሰውዬው እንዲወጡ ተደረገ ከግቢ
- ማለት እንዲወጡ ማለት ሰውዬው ሳይግባቡ ሲቀሩ ወደ ግቢ መሄድ ጀመሩ ወደ መኪናቸው?
- መኪናቸው አልሄዱም በእግር
- ወዴት ሄዱ እሺ አሁን ለእኛ ይንገሩና እርሶ እዚያው ስለነበሩ ?
- አት ዛት ታይም ከግቢ ለመውጣት በጣም ጭንቀት ነበር በወቅቱ ማለት ነው ማለት ሁሉም የራሱን አመለካከት እና የራሱ ፍላጎት እየገለፀ በነበረበት ሰዓት ሰውዬው በቃ ይሄ ነገር ሳይግባቡ ሲቀሩ ቀጥታ ሰውዬው እራሱን ለማዳን ቀጥታ ወጣ እዚያ ጥበቃዎችም ነበሩ አንዳንድ ማለት የእነሱን ዓላማ የማይደግፉ ሰዎችም ነበሩ በእነሱ ረዳትነት ከግቢ ወጣ ሰውዬው ከእዚያ በኋላ መኪናውን ለመውሰድ እንኳን ሲመጣ መግባት አልቻለም ወደ መኪናው ደግሞ እሱ አስተባብሯቸው ድጋሚ ይዘው ሄደው ጎማ አራቱንም አተንፍሰውት በወቅቱ
- አንድ ቀን እዚያው አስተባብሮ ሙባረክ አድሯል ብለዋል እርሶ ነበሩ እዚያው ነው ያደሩት እርሶ ?
- ያው የስራችን ባህሪ አንድ ቀን አይደለም 10 ቀንም 20ቀንም ላድር እችላለሁ ስታዘዝ ያው በወቅቱ ያው ያለው ነገር ጥሩ ስላልነበረ
- እኮ እኔ አጭር ነው ጥያቄዬ እርሶ በወቅቱ አድረዋል አላደሩም ?
- እኔ አድሬአለሁ
- አድረሀል ?
- አዎ
- ሌላው በፖሊስ እርዳታ ወጡ ብለሀል ፖሊሶቹ እዚያው ግቢ ውስጥ ነበሩ ?
- በር ላይ ነበሩ
- በር ላይ ማለት ከግቢ ውጪ ከግቢ ውስጥ ?
- እዚያው በሩ ጋር ማለት ነው ከጥበቃዎች ጋር በር ላይ ነበሩ እነሱ
- እኮ ከግቢ ውጪ ነው ?



613

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ውስጥ ?
- አዎ ግቢ ውጪ አጥር ውጪ
- ውጪ ነበሩ ?
- ከበሩ ውጪ እንደዚህ
- ተማሪዎቹ ከነበሩበት እስከ ፖሊሶቹ በፖሊሶቹ እርዳታ ወጡ ስላልከኝ ነው እስከ ፖሊሶቹ ድረስ እራሳቸው ነው የሄዱት ሰውዬው ማይኩን የተነጠቁት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሱ ተመልሷል ሌላ ካለ
- ሌላ እነ ሙባረክ ኢስላም ሰላም ነው ሕገ መንግስት ይከበር የኃይማኖት ነፃነት ይከበር እያሉ አልነበረም ?
- እሱንም በመሀል ይላሉ ግን በአብዛኛው
- እኮ ይሉ ነበር አልነበረም አጭር ስለሆነ ?
- በእዚያን ወቅት አላሉም
- እሺ ከእዚያ በፊት ነው በኋላ ሲሉ የነበረው ይሄ ?
- ከእዚያ በኋላ
- ሲሉ ነበር ይሄንን ?
- አዎ
- ሰውዬውን ሲነጥቀው ሙባረክ የተጠየከውን መልስ አለው አልከ ?
- አዎ
- ሰውዬው ያልተጠየቀውን ነበር የሚመልሰው ?
- ሰውዬውማ እነሱ የጠየቁትን ነበር ሲመልስ የነበረው እነሱ በሚፈልጉት አቅጣጫ አይደለም ሲመልስ የነበረው እኔ እንደገባኝ ማለት ነው
- ለእዚያ ነው ማይኩን የቀሙት ?
- እኔ እንደገባኝ እነሱ በሚፈልጉት አቅጣጫ አልነበረም ማለት ይሄ የእናንተ ጉዳይ አይደለም እንዲህ እንዲህ ነው አስተማሪዎቹ እንትን የተባሉት በእዚህ ምክንያት ነው እያለ የራሱን



674

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እንትን እየሰጣቸው ነበር ለእነሱ አልሳማቸውም በወቅቱ ነጠቀው እኔ የምልህን እኛ የምንልህን ብቻ መልስልን በሚል ሰውዬውን ያፋጠጡት

- መጀመሪያ ማይኩን ማን ነበር ለሰውዬው የሰጠው መጀመሪያ ማይኩን ማን ነበር የያዘው ማን ነበር የሰጠው ለሰውዬው ?
- አስተማሪዎቹም ነበሩ በወቅቱ ብዙ ሰዎች ነበሩ ይሄንን ሲያስተባብሩ የነበሩት ከእነ ሙባረክ ሌሎች ማለት አስተማሪዎች ምናምን ነበሩ ይሄ ነገር
- እኮ ሙባረክ ሲሰጠው አላየህም ማይኩን ?
- መጀመሪያ ማይኩን ሙባረክ አልሰጠውም ሙባረክ ከእጁ ሲነጥቀው ብቻ ነው ያየሁት እና የምንለውን ብቻ መልስልን ሲል ነው እንጂ
- አቶ አብዲሳ ቅድም ሙባረክ ተሰሚነት አለው ግቢ ውስጥ ብለዋል ከምን አንፃር ነው ተሰሚነት ያለው ?
- እሱን አላወኩም ምናልባት የግቢው ሲነየር ተማሪ ሊሆን ይችላል አላውቅም
- የተማሪዎች ካውንስል አባል መሆኑን አያውቁም የግቢው ተማሪዎች ካውንስል አባል ነው ሲባልም አልሰሙም ?
- ያን አላውቅም ውስጥ ብዙም እንትኑን አላውቅም አደረጃጀቱን አላውቅም ያው የውስጥ ያለውን የአሰራሩን ሁኔታ አላውቅም
- እርሶ አንድ ቀን ከተማሪዎች ጋር አድረዋል ከእዚያ በኋላ ተማሪዎች አላደሩም አይደል ?
- ባይዘዌ ማለት ግቢ ውስጥ ገብቼ ከተማሪዎች ጋር ሳይሆን ያው በውጪ ያለውን ሁኔታ ለመከታተል ያው እኔም ሌላም ባልደረቦቼ በስራ ላይ አድረናል
- ጥሩ ከአንድ ቀን በላይ አላደሩም ተማሪዎች ?
- አዎ ቤተሰቦቻቸው መጥተው በንጋታው ያደረጉት ድርጊት አግባብ አለመሆኑን እንትን ብለው ልጆቻቸውን በአብዛኛው አውጥተው ወስደዋቸዋል
- እርሶ ተማሪዎች ካደሩበት ቀን በኋላ ባለው ተከታታይ ጊዜም እዚያው ነበሩ አወሊያ ?
- ያው ለስራ እሄዳለሁ ስራ ስታዘዝ እሄዳለሁ
- የተከበረው ፍ/ቤት ሞላልኝ መለሰ የተከሣሾች ጠበቃ አርፍጄ መጥቼአለሁ
- ቀጥል



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ሲሉ ጣልቃ ገብቷል የሚሉበት ምክንያት ምንድን ነበር የሰማከውን?
- እሱ ያው ብዙ ውስጡን ባላውቅም ያው ሀበሽ የሚሉት እምነት አለ እሱን የግድ ተቀበሉ እያለ ነው የተለያየ ነገር እያሉ በወቅቱ ይሉ ነበር ግን ያንን ውስጡን እኔ ብዙም አላውቅም ማለት ያው እነሱ
- ሌላ ጥያቄ ቀጥሉ
- ሀባሽ የሚለውን ትምህርት መንግስት አምጥቶብናል የሚለውን ምክንያት በመጠቀም ነው መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ያሉት ?
- እኔ እንደራሴ አረዳድ እንደዚያ ይመስለኛል
- የመጅሊስ አባላት አይወክሉንም ያሉት የመጅሊሱ አባላት በሕዝበ ሙስሊሙ የተመረጡ አይደለም በሚል ምክንያት ነው ?
- እሱን እኔ አላውቅም
- ሲያስረዱስ እንግዲህ እዚያ ረጅም ጊዜ አከታተል ነበር ስላልክ ይሄ ጥያቄ አይነሳም ነበር ?
- ማለት ሕዝበ ሙስሊሙ ያልመረጠው ምናምን በሚል እኔ እሱን አላውቅም ውስጡን አላውቅም ማለት ያው እንደአዲስ ያው ምርጫ ይደረግ ምናምን በሚል እዚያ አካባቢ ላይ የሚናገሩት እንጂ የነበሩት እንደዚህ አልተመረጡም ምናምን በሚል ይናገሩ ነበር እነሱ እንጂ ይመረጡ አይመረጡ አላውቅም
- አዎ እዩ ተማሪዎቹ ይሉ የነበረውን ነው ?
- በወቅቱ ተማሪዎቹማ ሲሉ የነበሩት እኮ ቅድም ተናገርኩኝ ማለት ሀበሽ የሚሉት አስተምሮ መጥቶብናል መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ምናምን በሚል እነዚን ነገሮች ይናገሩ ነበር
- ስለዚህ አሁን ስለመጅሊሱ ይሉ የነበሩት ምርጫ ይደረግ ነበር ጥያቄአቸው ?
- አዎ እንደዚያም የማለት ነገሮች አሉ
- መጅሊሳችንን ለመምረጥ ዕድል ይሰጠን ይሉ ነበር አይደለም ?
- እሱን /ግልፅ ያልሆነ/
- ተማሪዎቹ ሁል ጊዜም ሲጮሁ የሚሉት አንድ ተመሳሳይ ነገር አለ ብለህል ምንድን ነው አላህከበር የሚለው ነው የሚሉት ሁል ጊዜ ?

T



236 676

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተመሳሳይ የሚል ቃል አልገለፅኩም
- ብዙ ጊዜ ሲጮሁ የሚሉት ነገር አለ ብለህ ነበር ምንድን ነው ሁል ጊዜ ሲጮሁ የሚሉት ነገር ምንድን ነው አላህክበር ነው የሚሉት ?
- አላህክበር ማለት መጨረሻ ላይ ይሆናል አሁን ያልኩትን ነገር ያልመረጥናቸው የመጅሊስ አመራሮች መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ምናምን የሚለውን ነገር በተደጋጋሚ ይሉ ነበር እነሱ
- የአረብኛ ቋንቋ ት/ቤቱ ተዘግቶ ነበር አይደል አንተ እዚያ ስትከተተል ስለነበር ?
- እሱ መከፈት አለበት
- እኮ ተዘግቶ ነበር አይደል ?
- እሱ መዘጋቱን እኔ አላውቅም ያው ውስጥ ያለውን አሰራር አላውቅም እነሱ ሲሉ የነበሩት እንጂ ይዘጋ ይከፈት እኔ የማውቀው ነገር የለም በወቅቱ
- ይከፈት ይሉ ነበር ግን ?
- አዎ እሱ ይሉ ነበር
- ከመዘጋቱ ጋር ተያይዞ የተቋረጠው የአረብኛ ትምህርትም ይቀጥል የሚል ጥያቄ ነበራቸው አይደል ?
- አይ ይከፈት ነው
- ትምህርቱ ይቀጥል የሚል ጥያቄ አልነበረም ?
- ይከፈት ጥበቃዎቹ የተባረሩት ይመለሱ አስተማሪዎቹ የተባረሩት ይመለሱ በሚል ነው እንጂ
- የተባረሩ አስተማሪዎች ነበሩ አንተ እዚያ ትከታተል ስለነበር ይሄንን አልተከታተልክም ?
- እኔ ከውጪ ስለምከታተል ያለውን ሁኔታ እንጂ አስተማሪዎች ስለማባረራቸው አላውቅም መረጃው የለኝም ማለት ያው ይባረሩ አይባረሩ አላውቅም
- እዚያ የተመደብኩት እነ ሙባረክን ለመከታተል ነበር እና ሙባረክን አንተ ባደረከው ክትትል የተረዳኸው ሙባረክ ተማሪዎችን ያስተባብር የነበረው ከት/ቤቱ ጋር በተያያዘ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ነው አይደል ?
- አዎ የማስተባበር ስራ በቃ እንዲህ እናድርግ ወደ እዚህ አሁን ይዟቸው የሚመጣው እሱ ነው ማለት ጥያቄዎቹ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከት/ቤቱ ጋር በተያያዘ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ነው ሲያስተባብር የነበረው አይደል ?
- ትክክል
- አይደል ?
- አዎ አንተ በእዚያው ስትከታተል ት/ቤት ውስጥ ምን ያህል ተማሪዎች ነበረ የነበሩት የምታውቀው ነገር አለ ?
- ቁጥራቸው እንዲህ ሲሰባሰቡ ብዛት እንጂ መገመት ይከብደኛል
- በግምት ምን ሊሆን ይችላል ምን ያህል ?
- 200/300 ልትል ትችላለህ ግን እርግጠኛ አትሆንም ያው የግምት ነገር ማለት ነው
- አዎ ግምት ነው እሺ ልክ ነህ ከእነዚህ ተማሪዎች ውስጥ እንደው ምን ያህል ተማሪው ነበር የእሱን ጥያቄ ይደግፍ የነበረው ?
- በአብዛኛው ማለት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች እዚያ በወቅቱ የነበሩት እንትን ይላል ግማሾች ደግሞ የማይደግፉም አሉ
- የእሱን ጥያቄ
- መውጣት የሚፈልጉ ማለት ነው እንደነሱ ማለት ያለውን ነገር መጮህ ወደ ቤተሰቦቻቸው መሄድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ነበሩ እነሱ በወቅቱ መውጣት እንደሌለባቸው እነሱ በሩን ይዘው በሩ አካባቢ ሆነው የመመለስ ስራ ማለት እኔ በራሴ ማለት እራሴን ማለት መውጣት የሚፈልግ ሰው ካለ መውጣት ግድ ነው የሚለው ነገር እኛም ገልፀንላቸዋል ለእነሱ ማለት ነው ለእነሱ ማለት አሁን በእዚህ በተቀደሰ ቦታ እንኳን ሌላ ቦታ ይታደር አይደለም ወይ ምናምን በሚል በግዳጅም ያደሩ ሰዎች አሉ ማደር ሳይፈልጉ
- ከተማሪዎቹ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ይደግፉት ነበር አይደል የሚደግፉ ተማሪዎች ይበዙ ነበር ?
- ተመልሷል
- መልሼአለሁ
- ተማሪዎች እዚያ ያደሩት ለአንድ ቀን ብቻ ነው አይደል /ግልፅ ያልሆነ/ ተብሎ ?
- አዎ
- ተጠይቋል ይሄ ጥያቄ
- በእዚህ ቀን በማደራቸው ምክንያት በተማሪዎቹ ላይ የደረሰ ጉዳት የለም አይደል ?



678

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንም ዓይነት ጉዳት የለም
- ቅድም ከእስልምና ጉዳዮች ተወክለው የመጡ ናቸው ያልካቸው ከእስልምና ጉዳዮች ተወክለው መምጣታቸውን እንዴት ነው ያወከው ?
- ሲናገሩ
- ከእስልምና ጉዳዮች ተወክለው የመጡ ነው ያልካቸው ሰውዬ ከእስልምና ጉዳዮች ተወክለው ስለመምጣታቸው እንዴት ነው ያወከው ?
- ማለት ያው በር ሲገባ ማንኛውም ሰው በወቅቱ ጥሩ ስላልነበረ እዚያ አካባቢ ያለው አትሞስፌር ያው እዚያ ጋር አባሎች ስለነበሩ ይጠይቁ ነበር ጥበቃዎቹ ይጠይቃሉ
- አባላች ስትል እነ ማን ማለት ነው ?
- የጥበቃ አባሎች ፖሊሶች ማለት ነው
- ፖሊሶች ?
- ደጅ ላይ ያለው ነገር ጥሩ ስላልነበረ ያንን ነገር እንትን ሲሉ ሲገቡ ያው ያንን የመጠየቅ ሁኔታዎች ነበሩ ሰውዬው ማንነታቸውን ሲገልፁ እነሱ ያው ስለምንገናኝ ከአባሎች ጋር እነሱ ነገሩን ከእዚያ ወደ ውስጥ ገባን ወደ ግቢ ውስጥ
- ከእስልምና ጉዳዮች ማለት ከየት ማለት ነው የእስልምና ጉዳዮች ትልቅ ተቋም ነው ከየትኛው ክፍል ነው ተወክለው እሳቸው የመጡት ?
- እኔ እንኳ ከአዲስ አበባ ይሁን አጠቃላይ ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ይሁን አላውቅም ሰውዬው የመጡት
- መጨረሻ ላይ የተጠየቀው ከመለሱት መልስ ልነሳ እና ከየት እንደመጡ አላውቅም ያሏቸው ሰው የተማሪዎችን ጥያቄ በትክክል የመመለስ ኃላፊነቱም ብቃቱም ይኑራቸው አይኑራቸው አያውቁም አይደል ?
- ማለት እኔ አይደለሁም ሰውዬው እንዲመጡ ያደረኳቸው
- እኮ ይሄንን አያውቁም እርሶ ?
- ቆዩ እስቲ
- ይሄንን ጥያቄ እንቃወማለን
- ቆዩ ይሄ የሙያ ጥያቄ ነው እየጠየቁ ያሉት እና ሌላ ጥያቄ



619

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለብዙ ጊዜ ትክክል አደርግ ነበር ብለዋል መቼ ነው መቼ መቼ ነው እየሄዱ ክትትል ሲያደርጉ የነበረው ?
- የነበረው አትሞስፌር ጥሩ ስላልነበረ ከጥር ወር ጀምሮ ያው በሚደረጉ ማንኛውም አርብ አርብም ከእዚያም በትምህርት ሰዓት ማለት ያው በውጪ የራሳችንን ክትትል እናደርጋለን
- በጣም ጥሩ አርብ አርብ ብዛት ያለው ሰው ይሰበሰብ ነበር አይደል ?
- እዚያ አዎ
- የተሰበሰበው ሕዝብ ሰላት ይሰግድ ነበር አይደል ?
- ትክክል አዎ
- እርሶ ምን ያደርጉ ነበር ሌላው ሲሰግድ ?
- እኔ ያው በደጅ ያው ሌላ ጊዜም በሰላማዊ ጊዜ በጥሩም ጊዜ ያው እኛ የራሳችንን ጥበቃ እናደርጋለን እነሱ ላይ አደጋ እንዳይደርስ እነሱም ሌላ አላስፈላጊ ነገሮች እንዳያደርጉ ከውጪ ጥበቃ
- እኮ ያው ክትትል አደርግ ነበር እና ብለዋል እና ክትትል ሲደረግ ደግሞ አብሮ
- ምናልባት
- ሲቪል ነው ወይስ የፖሊስ ልብስ ለብሰው ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያው
- እንዲህ የመሰለ ጥያቄዎች እንዳይጠየቁ ቀደም ተብሎ ብይን ተሰጥቷል የምስክሩን የስራ ሁኔታ
- ይኸውላችሁ ጥያቄውን አስተካክሉ ምንድን ነው ከእዚህ በፊት ተመልሶ ነበር የሚባለው ነገር ለአሁኗ ጠይቂ ምክንያቱም ከእዚህ በፊት ተነስቶ ነበር የሚለው ነገር ጉዳቢ ነው የሚሆነው ምናልባት የማይዘለሉ ብይኖች አሉ ትክክል ነው ግን አንዳንድ ጊዜ እንደ ጥያቄው ነው እንደጥያቄው ያስጣል አያሰጥም የሚባል ስለሆነ በተነሳችዋ ጥያቄ ላይ ተቃውሞአችሁን ብቻ አቅርቡ እንጂ ከእዚህ በፊት ብይን ተሰጥቷል እንደዚህ የሚባል ከሆነ ከእዚህ በኋላ ሌላ ጥያቄ እንዳይነሳ ማለት ነው ሌላ ምስክር ላይ የተነሳው እዚህ ጋር አይነሳም ማለት አይደለም ሌላ ቦታ ላይም ሊነሳ ይችላል ስለዚህ አሁን የቀረበውን ተቃውሞ ብቻ ነው ተቃውሞአችሁን አቅርቡ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ልክ ነው አይ የተከበረው ፍ/ቤት እኛ እንኳን እንዲህ ማለት የፈለግነው ፍ/ቤቱ አስገዳጅ ብይን ስለሰጠ ፍ/ቤቱ ችሎቱም ዝግ የሆነበት ዋነኛው ምክንያት ይሄ ስለሆነ ጠቅላላ ብይን ስለሆነ ነው ያነሳነው ለማንኛውም ግን አሁን የተከበሩ ጠበቃ ያነሱት ጥያቄ እርሶ በምን ምን ሲሰግዱ ምን ያደርጉ ነበረ በስውር ነው ወይስ የፖሊስ ልብስ ለብሰው ነው ይሄ የተከሣሹ የምስክሩን ከለላ በጣም አላማውን የሚስት እና የሚያሳሳው ነው ቀደም ብሎ የተሰጠው /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ ያየውን ነገር መጠየቅ ነው እንጂ የምስክሩን ግላዊ ሁኔታ ሲቪል ለበሰ የፖሊስ ልብስ ለበሰ አሁን ምስክሩ በቀጣይ ይሄንን ስራ ቢሰራስ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ አግባብነት ያለው አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ምላሽ ስጡበት
- መጀመሪያው የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ ያነሱት ላይ ፍ/ቤቱ ምላሽ ስለሰጣቸው ወደ እዚያ አንሄድም ከእዚያ በኋላ ግን እኚህ ምስክር እኮ እኛም ሳንጠይቃቸው ሙያዬ ነው ስራዬ ነው ክትትል አደርግ ነበር ብለው እራሳቸው ገልፀዋል እኛ ጠይቀናቸው አይደለም እዚህ ላይ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ የተከበረው ፍ/ቤት የእሳቸውንስ የምስክሩን ደህንነት የተመለከተ ነገር እኮ ምንም አላነሳንም ነበር እንዴት ነበር ስራዎትን ሲያከናውኑ የነበረው እየመሰከሩ ነው አይደል ስራዬ ነው አይ ነበር ከውጪም ኢቨን ውስጥ ሆኜ በረንዳው ላይ እያሉ መስክረዋል እና እንዴት ነበር ስራቸውን ሲያከናውኑ የነበረውን ነገር ነው የጠየቅነው እንጂ የምስክሩን የተመለከተ ነገር አይደለም እና መጠየቅ አለበት /ግልፅ ያልሆነ/
- ብይን ተሰጥቷል 1ኛው ምስክሩ ውስጥም ውጪም ሆኜ ስከታተል ነበር የሚለውን ነገር እኔ አልሰማሁም ውጪ ሆኜ የሚል ነገር ነው የሰማሁት ስለዚህ እሱ ይስተካከል 2ኛው ፖሊስ ነኝ ስራዬ ብለዋል ምስክሩ ከእዚያ በኋላ ምን ለብሰህ ትከታተል ነበር የሚለው ነገር ከእዚያ ያለፈ ነው ስራውን ከእነ ፖሊስ የፖሊስ ልብስ ለብሶ ይሰራል ሌላ ከፖሊስ ውጪ ለብሶ ይሰራል ወይ እሱ የእኛ ኢሹ አይደለም ምን ለበስክ የሚለው ስራውን ከእነ አካቴው ማጋለጥ ነው ይሄ ለምስክር ከተሰጠው ከለላ አንፃር አግባብነት የለውም ጥያቄው መጠየቅ የለበትም ተብሎ ብይን ተሰጥቷል ሌላ ጥያቄ ካላችሁ
- ምስክር ከመጅሊስ መጡ ያልካቸው ሰው የት ነው ንግግር ሲያደርጉ የነበረው ?
- ተጠይቋል
- ቅድም መልሼአለሁ

T



2241 681

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከውስጥ ሆነው ነው እርሶ ሲያዩ የነበረው
- ተጠይቋል
- ግን እርሶ የእሳቸውን ፖዚሽን በተመለከተ ፍ/ቤቱም አልሰማንም ስላለ እኔ ይሄንን ላረጋግጥ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ውስጥ ውጪ ነበርክ የሚለውን ነው ?
- አዎ
- መጠየቅ ትችላለህ ?
- እሺ እርሶ ውስጥ ሆነው ነው አይደል ሊከታተሉ የሚችሉት ይሄንን ?
- ማለት ያው እንደዚህ እና እንደዚያ ነበር በሩ  እዚህ ጋር ሆኖ ሰውዬው ሲናገር የነበረው /ግልፅ ያልሆነ/
- እስቲ እሱን ግልፅ አድርግ
- ሰውዬው የት ሆኖ ነው ?
- ሰውዬው ግቢ ውስጥ ነው
- የሰውዬው ተጠይቋል እሱ ተመልሷል ግን ግቢ ውስጥ ወይስ ?
- በሩ ላይ ከውጪ
- ውስጥ ነው ውጪ ?
- ከውጪ በር ላይ
- ቅድም ሲመሰክሩ ሙባረክ እና ሌሎችም እንዲህ በረንዳ ነገር አለ እዚያ ላይ ሆኖ ነው እንደእስቴጅ ነገር ብለው እንደውም ምሳሌ ይሄንን አሳይተውናል ይሄንን የት ሆነው ነው እርሶ ያዩት ይሄንን ከውጪ ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ በሩ እኮ ክፍት ነው
- እኮ መግባት አልቻሉም እንዴ እርሶ ?
- የሚገባ ሰው ይገባል ያው በወቅቱ እኔ ውጪ ነበርኩኝ
- ይሄንን ያህል ጊዜ ወደ መስኪዱ ወደ ግቢ ውስጥ ሳይገቡ ነው ስራ ሲከታተሉ የነበረው ማለት ነው ?



682

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው ማለት በወቅቱ እኔ ትዕዛዙ የተሰጠኝ ከውጪ ያለውን ሁኔታ እንድከታተል እና በውስጥ ያለውን ነገር ደግሞ በራሳችን አሰራር
- እርሶ ከግቢ ውጪ ሆኜ ነው ስከታተል ብለዋል ከመድሊስ መጡ የተባሉት ሰው ከእርሶ በምን ያህል ርቀት ላይ ሆነው ነው ይሄንን ለተማሪዎች ንግግር ሲያደርጉ የነበረው ?
- ይሄ እኮ መልሼአለሁ ማለት
- ይሄ ነገር ተጠይቋል
- ፊት ለፊት እንደዚህ እንደመጋረጃው እስቴጅ ነበረ
- ቆይ ቆይ ብዙ ጊዜ እንትን ማለቱ እንትን ስላለን ነው አንዳንድ ጊዜ እናንተ እንዲህ ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ ይጠየቅ እና እናንተም ትንሽ ስሜት ውስጥ ትገባላችሁ ተከሣሾም ተቀባይነት ያጣ ዓይነት ነገር መልዕክት ስለሚያስተላልፉ ተጠይቋል እሱ በግልፅ ስንት ጊዜ ተጠይቋል በሁሉም ጠበቆች እና እሱን ነገር አስተካክላችሁ ጠይቁ ተጠይቋል ድግግሞች ቅድም እንዳልነው ወረቀት ነው የሚያበዛው
- እንግዲህ ቅድም ሲናገሩ ያው የተባረሩ መምህራን ይመለሱ የተቋረጠው የአረብኛ ትምህርት ይቀጥል የሚል ዓይነት ንግግር ይናገሩ ነበር ይሄንን በአፋቸው ነበር አይደል ሲናገሩ የነበረው?
- አዎ እንደዚህ ፊት ለፊት ሆነው
- በአፋቸው ነው ሲናገሩ የነበረው ?
- አዎ ጩኸትም አለ በጣም ይሰማል ማለት ግቢው ፀጥ ያለ ቦታ ስለሆነ
- አሁን አንድ ሰው እስቴጅ ላይ እርሶ ያሉት የበረንዳ እስቴጅ ላይ ሆኖ እዚያ የሚናገረውን እርሶ እያንዳንዱን ነገር ይሰሙ ነበር ማለት ነው ?
- ማለት ይሰማል ማለት አካባቢው ፀጥ ያለ እና ጭር ያለ አካባቢ ስለሆነ
- አይ ጩኸት አለ እኮ ብለውናል አይደል እንዴ ?
- ጩኸትማ አዎ ጩኸት እኮ ያልኩት ማለት ያው ተሰብበው በሚናገሩበት ሰዓት እንደዚያ ነው እነዚህ እራሳቸው እየተቀያየሩ እየወጡ ነው እስቴጁ ላይ ይሄንን ነገር ሲሉ የነበረው 3 ልጆች ናቸው በስም መግለፅ እችላለሁ ማለት ያው እሱ ላይ ስለሆነ ብቻ
- ጥሩ መኪና 4 ጎማ ተነፈሰ ብለዋል እና ከበሩ የቱ ጋር ነበር የቆመችው ?
- ፊት ለፊት እስቴጁ እንደዚህ ሲሆን /ግልፅ ያልሆነ/
- መኪናው በምን ያህል ርቀት ላይ ነበር ከበሩ የቆመው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መገመት ቢያዳግተኝም
- ከመጋረጃው ያልፋል
- በግምት ምን ያህል ሜትር ይሆናል ?
- ርቀቱ ከመጋረጃው ያልፋል ወይስ ?
- 8 እራሱ /ግልፅ ያልሆነ/
- በግምት 8 ሜትር ?
- አዎ እንደዚያ አካባቢ ይሆናል
- ቀጥሉ
- 8 ሜትር ስለዚህ ቅድም ሲገምቱ መጋረጃውን ያህል ወይም 8 ሜትር ብለውናል መኪናው ያለበት ቦታ እና ንግግር የተደረገበት ቦታ አንድ ቦታ ነው ማለት ነው ?
- አይ ንግግር ያለበት እንደውም ይርቃል
- መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያ
- ማለት አሁን የተከበረው ፍ/ቤት ከጠዋትም ጀምረን ስንቃወም ነበር ይሄ አሁን የዲስታንስ ጉዳይ ፍ/ቤት ጁዲሻል ኖቲስ የሚወስድበት ሁላችንም የምናውቀው ቢሆን ኖሮ ይሄ ጥያቄ ተገቢ ነው ምስክሩንም አጠራጣሪ ነው የሚናገረው ነገር አጣራጣሪ ነው ወይ ውሸት ነው የሚለባለውን ነገር ለመውሰድ ተገቢ /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን እሳቸው የሚጠይቁት ጥያቄ ፍ/ቤቱም ስለማወቁ አናውቅም እኔ በግል እዚህ እንደዐቃቤ ሕግ አላውቀውም ቦታውን ስለዚህ ጁዲሻል ኖቲስ በማይወሰድበት ቦታ ላይ ምስክሩ እየተጠየቀ ገምት እየተባለ እየተደጋገመ መጠየቁ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት አይኖረውም በመስቀለኛ ጥያቄም ሊጠየቅም አይገባም ነው
- ምላሽ ስጡበት
- የጁዲሻል ኖቲስ ፕሪንስፐል የታወቀ ነው የተከበረው ፍ/ቤት አጠቃላይ የሆኑ ፋክቶች እንጂ ፍ/ቤቱ እያንዳንዱን ነገር ዝርዝር ሊያውቅ አይችልም
- ቆዩ ስለጁዲሻል ኖቲስ /ግልፅ ያልሆነ/ እሱ ደህና ቀርቶ ነበር እሱ ቀንሶልናል ብዙ ነገር አሁን አጠቃላይ ስለ ሕግ ፕሪንስፐል ሳይሆን ፋክቱን ነው እሱን እኛ እናገናኘዋለን በምንችለው አቅም አሁን ተነሳነው ላይ ነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን እኮ የተከበረው ፍ/ቤት ፍ/ቤቱም ሆኑ ዐቃቢ ሕግ ስለማያውቀው እኮ ነው እኛ እየታገልን ያለነው ይወቁት እንዲህ አይደለም እያልን እኮ ነው ትግል እያደረግን ያለነው የተከበረው ዐቃቢ ሕግ ፍ/ቤቱ ያውቀዋል እያሉን ነው እኛ ደግሞ አያውቀውም ርቀቱ እንደዚህ ነው እያልን እየመራንም በምናገኘው
- ፍ/ቤቱ ያውቀዋል አይደለም የእነሱ ጥያቄ ፍ/ቤቱም አጠቃላይ በማናውቀው ነገር የቦታ ክርክር ሆነ ነው ሌላ ነገር አይደለም
- እኮ እንዲያውቀው ነዋ የተከበረው ፍ/ቤት አዝ ዘ ማተር ኦፍ ፋክት አንድ ሰው ከእዚህ ርቀት ላይ ይሄንን ነገር ሊሰማ አይችልም የሚለውን ፍ/ቤቱ እንዲረዳን እና ግምት እንዲወስድ ነው ምስክሩን እንጂ እኛ ከእንትኑ ከዲስታንሱ ከርቀቱ ሌላ ነገር አናገኝበትም የተከበረው ፍ/ቤት ግንዛቤ እንዲኖረው እነዚህ ሰዎች ንግግር የሚያደርጉበት እና ምስክሩ ሰማሁ የሚሉበት ቦታ እይታም ሆነ ድምፅም ሆነ ሊያገኙ የሚችልበት ፖዚሽን ላይ ነበሩ ወይ የሚለውን ፍ/ቤቱ እንዲረዳን ነው አግባብነት ያለው ጥያቄ ነው ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ብይን ሰጥተናል መኪና ከቆመበት እና ንግግር ከተደረገበት የትኛው ይርቃል የሚለው ነው ጥያቄው ጥያቄው በጥያቄነቱ ችግር የለውም ነገር ግን ቅድም የተሰጠው ብይን አለ የንብረት ክርክር አደረጋችሁ የሚል ማለት ነው አሁን የተነሳው ጥያቄ ተገቢ ነው ይቀጥል ጥያቄው በእዚያ ተበይኗል ነገር ግን የዲስታንስ ክርክር በዝቶበታል እሱን እያሰባችሁ ቀጥሉ አሁን የተነሳው ጥያቄ ጥያቄነቱ ችግር የለውም
- ምስክር እርሶ ከቆሙበት ቦታ መኪናው ምን ያህል ይርቃል ?
- ማለት አሁን ከነበረበት ያነሰ ነው ማለት እንደዚህ አካባቢ ነው ይሄ እስትሬት እንደዚህ ሲሆን መኪናው እንደዚህ በጎን በኩል /ግልፅ ያልሆነ / ያው እስቴጁ ያለበት እና እኔ ያለሁበት እንደዚህ ፊት ለፊት ሲሆን መኪናው የቆመው በጎን በኩል ነው
- በጎን በኩል በምን ያህል ርቀት ?
- ከእዚያ ባነሰ ርቀት
- ከእዚያ ባነሰ ማለት ገምቱታ ?
- ማለት 6 ቢሆን
- በቃ 6 እሺ
- በመሀከላችሁ ሰዎች ነበሩ አይደል ተማሪዎች ብዙ ተማሪዎች ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ እዚያ በረንዳው አካባቢ ላይ የነበሩ ተማሪዎች ነበሩ
- እነሱ ሜዳው ላይ ይሰበሰቡ ነበር ባሉበት ወቅት በሩ ክፍት ሆኖ ሰው ይወጣ ይገባ ነበር አይደል ቅድም ሲያስረዱ ጥበቃዎች ወይም የፖሊስ አባላትም መታወቂያ እያሳዩ ያስገቡ ያስወጡ ነበር ብለዋል አይደል ?
- አይ ይሄ ከሆነበት በኋላ ነው እንደዚያ እንጂ መጀመሪያ ያው ሰውዬው ከገባ በኋላ የሚወጣ ሰው አልነበረም ?
- ሰውዬው ከመምጣታቸው በፊት በሩ ክፍት ሆኖ ሰው ይገባ ይወጣ ነበር ?
- አዎ ያው ማለት ሰብስበዋቸው ያለውን ነገር ጥያቄ ሊመልሱላቸው ስለነበረ የሚወጣ /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም ሲያስረዱ የተወሰኑ የማይደግፉ
- እሱን ያልኩት ምናልባት /ግልፅ ያልሆነ/ ተሳስተዋል እሳቸው
- የሚጠይቁትን ብቻ ይሄ ተጠይቋል ቆዩ ይጠይቁ እና
- ሌላ ጥያቄ
- ይሄ ተጠይቋል የሚጠይቁትን ብቻ
- ሌላ ጥያቄ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ከእዚህ ሳይሆን ሌላ ጥያቄ
- የሚጠይቁትን ቀጥሉ ይሄ ተጠይቋል
- እሺ ቅድም ሲያስረዱ የማይደግፉ መውጣት የማይፈልጉ መውጣት የሚፈልጉ ነበሩ ከእዚህ በላይ ይሄ ነገር ምን አለ የተቀደሰ ቦታ አይደለም ወይ በሚል አሳምነዋቸው ተመለሱ የሚል አደምታ ነው እኔ የተረዳሁት በሌላ ደግሞ ሁኔታ ሲጠየቁ ተገደውም ጭምር ብለው ነው
- ቆይ ይመልሱ
- አይ ምርጫውን ልጠይቃቸው
- ቆይ አይ ልመልስ እና ምናልባት
- ምርጫ ስለሆነ 2 የተለያየ ነገር ስለተናና ላስረዳቸው ብዬ ነው
- እሺ ይጨርሱት
- ከእዚህ ቦታ የተሻለ ምን የተቀደሰ ቦታ አለ ወይም ከእዚህ የተቀደሰ ቦታ ማደር በሚል ሰዎቹ አምነውበት ተመልሱ የሚል ነገር ነግረውናል ቅድም ደግሞ ተገደውም ጭምር የሚል ነገር ተናገሩ እና የትኛውን እንውሰድ ፍ/ቤቱ የቱን ይያዘው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መናገር ልጀምር
- እሺ ቀጥሉ
- ምናልባት አሁን ያልከው አንተ እኔ መጀመሪያ የተናገርኩት ሌላ ነው አንተ የምትለው ምናልባት ማለት አረዳዴ ይሁን አላዳመጠኝም ይሁን አላውቅም ማለት ስናገር የነበረው እኔ አንድ ቀን አደሩ የተባለው ሌላ ቀን ነው ሰውዬው ሊመልስላቸው የመጣው ሌላ ቀን ነው
- ሌላ 2 የተለያዩ
- 2 የተለያዩ ቀኖች ናቸው
- እሺ ያለጥርጥር ያልተለያየ ደግሞ እርሶ የተለያየ የተናገሩትን ላስታውሶት መጀመሪያ የተከበረው ዐቃቤ ሕግ ሲጠይቆ ፖሊሶች ደርሰው እንዲወጡ አደረጉ እኒህ ከመጅሊስ መጡ ያሏቸውን ሰዎች ፖሊሶች መጥተው እንዲወጡ አደረጉ ብለው ተናገሩ ባልደረባዬ ደግሞ ሲጠይቆት ጥበቃዎች መጥተው እንዲወጡ አደረጉ የትኛውን እንውሰድ እዚህ ላይስ ?
- እዚህ ጋር አሁን ምንድን ነው መጀመሪያ ያልኩት ያ ንግግር ያደረጉበት ቀን ነው ይሄ ማለት ሰውዬው ለጥያቄዎቻቸው መልስ ሊሰጡ የመጡበትን ቀን ነው እኔ ያልኩት
- እኮ እሱን አሁን እየተጠየቁ ያለው እሱን ነው
- እኮ የእሱ ቀን ማለት እና ተማሪዎች ያደሩበት ቀን ይለያያል
- እሱ ሳይሆን ቆይ ሰውዬው መጥተው ገብተው በወጡበት ጊዜ
- ሳይገባቡ ወጡ የእዚያኔ ማለት
- እሱ ላይ ያለውን ጥያቄ ነው 2 ጥያቄ የተጠየቁት ሰውዬው በመጡበት ቀን እና በወጡበት በእዚያው ቀን ማለት
- መልሼ ግልፅ ላድርግላቸው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ጥያቄው እሱ ነው ወይስ የተለየ ነው ?
- አዎ እራሱ ነው ግን ግልፅ ላድርግሎት አንዴ ስሙኝ እና ግልፅ ላድርግሎት
- ጥያቄው ይሄ አይደለ ግልፅ
- ይኸው ነው
- አንዴ ፖሊሶች አስወጡ ብለህል አንዴ ደግሞ ጥበቃ ሠራተኞች አስወጡ ብለሀል የትኛው ነው ትክክል ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት ጥበቃ ሠራተኞች ያልኩት የሚደግፉት ማለት ይሄ ነገር እንትን ያላሉ ሰዎች እና ጥበቃዎቹ ፖሊስ ሆነው ሰውዬው ከግቢ እንዲወጡ አደረጓቸው ነው
- ማለት ፖሊስም ግቢ ውስጥ ገብቶ ?
- ደጅ የነበሩ ማለት ነው ተከትለው መጥተዋል እስከ ደጅ ድረስ ማለት ነው እነሱ ሰው እየተከተሉ
- ተከትለው ምን ያህል መጡ ?
- እስከ በሩ ድረስ መጥተዋል
- እርሶ ይሄንን ሁሉ እዚያው በር ላይ ሆነው ያዩ ነበር ?
- አዎ ያው እያየን ነበር ሌሎቹ ከእኔ ጋር የነበሩ ብዙ አባሎች ነበሩ
- እና እንዴት ነው አሁን ምን ዓይነት ምላሽ እንደሰጧቸው ተማሪዎቹ ምን ዓይነት ጥያቄ ጠይቀዋቸው
- እሱን እኮ /ግልፅ ያልሆነ/
- ሊረዱ እና ሊያውቁ የሚችሉት ?
- እሱን እኮ ሲጠየቅ የነበረው
- ቆይ ቆይ እስቲ ተረጋጋ እስቲ ይሄኛው ስለመለሱት ተጠይቋል ቅድም እና ሌላ ካሎት
- ቅድም ሲያስረዱ የአረብኛ ቋንቋ በመንግስት ትዕዛዝ ትምህርት እንዳይሰጥ ተቋርጦ ነበረ የሚል ነገር ተናግረዋል ?
- እሱን እኮ አላልኩም እኔ ያልኩት የተዘጋው የአረብኛ ትምህርት ይከፈት እንጂ በመንግስት ትዕዛዝ ምናልን የሚል ቃል አልወጣኝም ከአፌ
- እሱን አረሙት ማለት ነው እኔ ግን /ግልፅ ያልሆነ/
- ያሉትን እንነሮት ተዘግቷል እያሉ ነበር እኔ ስለመዘጋቱ አላውቅም ነው ሲሉ የነበረው
- ከእዚያ በፊት ዐቃቤ ሕግ ሲጠይቃቸው የፃፍኩትን ነው የተከበረው ፍ/ቤት እሺ
- በተደጋጋሚ ተጠይቀው እዚህ እነሱ እና ፍ/ቤቱ የያዘው ተዘግቷል ተዘግቶብናል ይከፈትልን እያሉ ነበር መንግስት ዘግቶብናል አረብኛ ት/ቤቱን እያሉ ሲናገሩ ነበር እኔ ግን ይዘጋ አይዘጋ አላውቅም ነው እንደዚያ ነው
- ትክክል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለብዙ ጊዜ ስከታተል ቆይቼአለሁ ስላሉ በእርግጠኝነት ያውቁታል ብዬ ነው ይሄንን የምጠይቆት የመስኪዱ አሰጋጅ ኢማም ይመለሱ የሚል ጥያቄ አልነበራቸውም ተማሪዎች ?
- የተባረሩ አስተማሪዎች ይመለሱ
- የመስኪዱ አሰጋጅ ኢማምስ ?
- ብዙ እንትን አልልም ጥያቄዎቻቸው ብዙ ነበሩ እኔ የማውቃቸው የሰማዋቸው እነዚያ ናቸው አስተማሪዎቹ ይመለሱ እንትኑ /ግልፅ ያልሆነ/ የቋንቋ ት/ቤቱ
- የመስኪዱ አሰጋጅ ኢማም ስለመባረራቸው የሰሙት ነገር የለም ?
- እኔ አላውቅም ውስጡ ያለውን እንቅስቃሴ እኮ ማለት አደረጃጀቱ ብዙም አላውቅም
- ይበቃል
- አቶ አብዲሳ እስቲ ስለጎማ መተንፈስ ቅድም የነገሩንን ሰውዬው ተናግረው ወደ በር ሄዱ ልክ ሰውዬው ሲሄዱ ተማሪው ተነስቶ ቆመ እንጂ ወይ መጀመሪያም ቆሞ ነበር ብለውናል አይደል?
- ያው ተማሪዎቹ ቆመው እያዳመጡ ነበር መልሱን
- እዚያ አካባቢ ያለው ተማሪ ?
- አዎ /ግልፅ ያልሆነ/
- ተማሪዎች ስለቆሙ መኪናው ማለት አልተከበበም መጀመሪያውም ንግግር ሲያደርጉ ተውጠዋል አይደል በሰው ?
- አይ መጀመሪያ መኪናው የተወሰነ ይታይ ነበር ከእዚያ በኋላ ግን ሰውዬው በሚመልሱት መልስ ያው ሳይግባቡ ሲቀር ሲወጡ ቀጥታ
- ከእዚያ መኪናዋ ?
- ወደ መኪናው ነው የሄዱት
- መኪናው እየተዋጠ መጣ እናንተ አሁን በር ላይ ነው ያላችሁት ?
- አዎ
- ተማሪው ወደ መኪናው መጣ አሁን ተከበበ ስለዚህ መኪናው ሰው ሲያስተነፍሰው መቼም ጎንበስ ማለት አለበት ?
- እሱ ልክ ነው



689

2249

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሌላው ተማሪ ደግሞ ቆሟል ዙሪያውን ከቧል ስለዚህ እርሶ አሁን መኪናውን ሲያስተነፍሱ ከመገመት በስተቀር በ 8 ሜትር ቅድም በግምት 8 ሜትር ላይ ሆነው ማማሹ በቆመበት እንዴት ነው 4 ጎማ ተነፈሰ ለማለት ግምት ነው ያስቀመጡት ?
- አዎ በትክክለኛው ነገር ማለት ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ሄዱ እሱ ከፊት ይዟቸው ከእዚያ በኋላ ማለት ያው ይዟቸው ወደ መኪናው ወዳለበት ሄዱ ሰውዬው ከእዚያ በኋላ እራሱ መኪና ለማውጣት ፈልጎ ነበር መኪናዎቹ 4ቱም ጎማዎቹ አይሰሩም በቃ ሰውዬው ተመልሶ ያለውን ነገር መኪናቸውን ይዘው ሊሄዱ ነበር 4ቱም ጎማ አይሰራም ግቢ ውስጥ ለብዙ ጊዜ
- አሁን ጥያቄው ገብቶታል ሰው ከቦ ነበር እንዴት አዩት ነው ጥያቄው ?
- አይ ከሄዱ በኋላ መተንፈሱ እኮ ድጋሚ ሊወጣ ሲል መኪናው ለማውጣት ማለት ነው እንጂ መጀመሪያማ ከበውታል መኪናው አይታይም
- በኋላ ይታይ ነበር ነው ?
- በኋላ እነሱ ሄዱ ሲሄዱ መኪናው ባዶ እዚያ ጋር ለብቻው ነው ሲታይ 4ቱም ጎማ /ግልፅ ያለሆነ/
- ቀጥሉ ሌላ ጥያቄ
- ስለዚህ ለመኪና ለማገምጣት ሲመለሱ ጎማው ተንፍሶ ስላዩ ተማሪዎቹ ናቸው ከሚል ማጠቃለያ ደርሰው ነው ?
- በወቅቱ ያው ከእነሱ ሌላ ማንም እዚያ ጋር አልነበረም ጥበቃዎቹ ነው ያሉት ጥበቃዎቹም ስራቸው ላይ ነው ያሉት
- የመኪናው ዓይነት ያስታውሳሉ ?
- መኪናው ብዙም እንትን ባልል እንደቪታራ ነገር መሰለኝ በወቅቱ
- ቪታራ ?
- የሰውዬው እንደዚያ መሰለኝ
- አወሊያ ት/ቤት ምን ምን እንዳለ ያውቃሉ መስኪድ እንዳለ ?
- አዎ አውቃለሁ
- የኃይማኖት ት/ቤት እንደሆነ ያውቃሉ ?



690 250

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዮ. ት/ቤት ያው እንዳለ አውቃለሁ የኃይማኖት ትምህርት ያው እንደማንኛውም ኃይማኖት በፊ ይሰጣል ብዬ አስባለሁ እንጂ ውስጥ ይኑር አይኑር አላውቅም
- ቀድሞ ሲናገሩ ያው
- እነሱ ከሚሉት ነው የተናገርኩት
- ቆይ ጥያቄውን ይጠይቁ
- ቀድሞ ሲናገሩ ረጅም ጊዜ እዚያ እንደነበሩ ገልፀዋል እና ላስታውሶት ምናልባት የመጀመሪያ የተማሪዎቹ ጥያቄ እነዚህ የተባረሩ አስተማሪዎቻችንን ይመለሱ የአረብኛ ት/ቤቱ ይከፈት የሚል ነው አይደለም ?
- ትክክል አዎ
- ይሄ ጥያቄ
- ተጠይቋል ቆይ ይሄ ተጠይቋል ሌላ ካለ እየደገሙ ነው አዲስ ካሎት እሱን
- ልቀጥል ነው የተከበረው ፍ/ቤት ስለዚህ ከእዚህ በኋላ ነው አይደል ቅድም ሙባረክ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ሲሉ የሰሙት ከእዚህ ጊዜ በኋላ ወይም በሌላኛው ሣምንት ?
- የእዚያኔ የጥያቄአቸውም እንትን ይሄ ነበረ ማለት
- ስለዚህ የመጅሊሱ ሰውዬ ከመጣ በኋላ ነው ይሄ ነገር የተቀየረው ወይስ ከእዚያ በፊት ?
- ከመጀመሪያም ያው ማለት እነዚህ ነገሮች ይናገር ነበር እሱ
- ከመጀመሪያው ማለት መቼ ገና እርሶ እዚያ ስራ ተመድበው ሲሄዱ ?
- ማለት ጥር ወር ይሄ ነገር ከተጀመረበት ማለት ት/ቤት ውስጥ አንዳንድ ጩኸት ምናምን በሚያሰሙበት ወቅት ይሄንን ነገር ይነገር ነበር እዚያው እስቴጁ ላይ እየወጣ እሱ ማለት ሌላም ልጆች አሉ እየተቀያየሩ ማለት
- ይሄንን ነገር ሲሉ ቅድም ካልኮት ቀድሞ ነው የሚለው ወይስ ከእዚያ በኋላ የመጣ ነው ነው ?
- ይሄ ተመልሷል
- አልመለሱም
- የትኛው እስቲ
- ቆይ ቆይ እስቲ እንደማመጥ እስቲ ከጥር ወር ጀምሮ እሱ ከመምጣቱም በፊት ይሄ ጥያቄ ነበር ብለዋል እኮ
- ሲል ይሄንን እንዲገልፅ ፈልጌ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ብሎ ስላለፈ.



691

2251

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተረዳን እኮ የቅድሙ ጥያቄዎች አይደል አዲስ ነገር አይደለም 4 ነው ሲል የነበረው መጅሊስ ይወረድ ምንምን ሲል የነበረው ?
- አዎ
- እኮ እኔ ከእሱ በተቃራኒ የጠየኩት የተከበረው ፍ/ቤት
- የፈለጉትን በተቃራኒ ጠየቁዋ ያው እኛ የተረዳነው ቅድም ሲባል የነበረው
- እስከ መቼ እዚያ ቆዩ አቶ አብዲሳ ?
- ይሄም ተጠይቋል
- እኔ ማለት ያው
- ሌላ
- ስራዎን እዚያ አካባቢ እስካቆሙበት ጊዜ ድረስ ቅድም እንደገለፁት በየጊዜው አርብ አርብ እዚያ ጁማ ሰላት ላይ እነሱንም እንጠብቃለን ሌላውንም እንጠብቃለን ብለው ነበረ በእዚህ ጊዜ ውስጥ በእነሱ በኩል የተፈፀመ ነገር አለ ሌላ የሚያውቁት ?
- ሌላ የተፈፀመ ያየሁት ነገር የለም
- የለም
- እነሱስ ሌላ ጁማ ጁማ የምናካሄደው ትግል ሰላማዊ ነው እያሉ ሲናገሩ አይሰሙም ነበር ?
- ማለት በማይክ ይናገራሉ እንደዚያ ነገሮች ይናገራሉ አሁን ቅድም ያልኳቸውን ነገሮች ይናገሩ
- ይናገራሉ ?
- አዎ
- ቅድም ተማሪዎችን አሳድረዋል ብለው ነበረ ት/ቤቱ ማደሪያ የለውም ተማሪዎች የሚያድሩበት አዳሪ ት/ቤት አለው አይደል ?
- በአብዛኛው ማለት ብዙ ውስጡን ባላውቀውም የሆነ እዚያ ውስጥ የሚያድጉ ልጆች አሉ
- እኮ ማደሪያ አለው ማለት ነው ?
- ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ ግን ከውጪ ደግሞ መጥተው የሚማሩ አሉ ማለት በየቀኑ የሚመጡ ማለት ነው
- እርሶ እዚያ እስካሉ ድረስ እስከነበሩበት ጊዜ ድረስ እነዚህ መምህራኖች ወይም ጥበቃ ሠራተኞች ተመለሱ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ጥበቃዎቹ እራሱ አላውቃቸውም
- እዩ ተመለሱ ወይ ነው በወሬ ደረጃ መመለሳቸውን ተማሪዎቹ መመለሳቸውን ሰምተዋል ወይም ት/ቤቱ መከፈቱን ቅድም ያሉት የአረብኛ መከፈቱን ያውቃሉ በኢንፎርሜሽን ደረጃ ?
- ማለት ያው ትምህርት መጀመሩን አውቃለሁ
- እዩ አረብኛውን ?
- አረብኛ እንትኑን አላውቅም
- የመምህሮች የተባረሩት ተመልሰዋል ?
- እሱን አላውቅም የራሳቸው ውስጥ አስተዳደር ስራ ስለሆነ ከእኔ ጋር አያገናኘውም
- ይበቃል ቀጥሉ ሌላ
- የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል
- እሺ ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- እሺ ምስክር ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ስትጠየቅ ሙባረክ ይሄንን ድርጊት የሚፈፅመው ከት/ቤት ወይም ከመማር ማስተማር ጋር በተያያዘ ነው ወይ ስትባል አዎ ብለሀል ይሄንን እርግጠኛ ነህ ወይ ሙባረክ ይሄ አሁን ግቢ ውስጥ የሚያደርገውን አንተ የገለፅከውን የሚያስተባብረውን የሚያደርገው ንግግር ከመማር ማስተማር ጋር በቀያያዘ ብቻ ነው ወይ ሌላ ዓላማ ይኑረው አይኑረው የምታውቀው ነገር አለ ?
- እሱን አላውቅም
- የምታውቀው ነገር የለህም ?
- አዎ አላውቅም
- ማለት እዚያ ይደረግ የነበረው ጥያቄ ትምህርት ብቻ ነው ከመማር ማስተማር ጋር በተያያዘ ብቻ ነው ጥያቄ ሲጠየቅ የነበረው ?
- ማለት በወቅቱ ሲጠይቁ የነበሩት
- ብቻ ጥያቄ ነው ሲጠየቅ የነበረው ቅድም ስትነግረን ከመጅሊስ የመጡት ሰውዬ እኛ የምንፈልገውን ብቻ ጥያቄ መልስልን ብለውን ነበር ብለሀል ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ እነ መባረክ መባረክ ሲያስተባብሩቸው የነበረ መባረክን የመማር ማስተማር ጥያቄ ብቻ ነው ወይ ሲጠየቁ የነበሩት ወይስ ከእዚያ ውጪ ሌላ ዓላማ ኖሯቸው ያጠይቁ እያጠይቁ የምታውቀው ነገር አለ ?
- ዓላማውን ብዙ ባላውቀውም ያው የመጅሊስ አመራሮች ይውረዱልን ምናምን በሚል ሌላ እነዚህን ጥያቄዎች ይጠይቁ ነበር
- ከመማር ማስተማር ውጪ ማለት ነው ?
- አዎ ይሄ ሀበሽ የሚሉት እምነት እና እያሉ የተለያየ ይላሉ ግን እኔ ብዙም አላውቀውም ውስጡን
- ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ስትጠየቅ ጉዳት ሌላ የደረሰ ጉዳት አለ ወይስ የለም ስትባል አላውቅም ነው ያልከው ወይስ አላየሁም ነው ?
- ማለት እኔ መኪናዋ
- ግቢ ውስጥ ከመኪናው ውጪ ሌላ ንብረት ላይ ?
- ሌላ ምንም አላየሁም
- ያየኸው ነገር የለም ?
- በእኔ የሚታየው ፊት ለፊት ያለው እነዚህን ነው ያየሁት
- ሌላ ጉዳት ደርሶ ይሁን አይሁን የምታውቀው ነገር የለም?
- እሱን አላውቅም
- ጨርሰናል ድጋሚ ጥያቄ
- ምስክር እናመሰግናለን ጨርሰዋል ይመለሱ
- እሺ ያው ከእዚህ በኋላ ሌላ መስማት አንችልም 10 ሰዓት ሆኗል ስለዚህ የዛሬውን በእዚህ አጠናቀናል ነገ ጠዋት 3 ሰዓት ተኩል በተለመደው እዚሁ እንገናኛለን የምንሰማው የነገው ችሎት ከሰዓት በፊት ብቻ ነው የሚሆነው ምስክሮቻችሁን በእዚያ መንገድ አስባችሁ ይዛችሁ ትመጣላችሁ ዐቃቤ ሕግ፡፡



http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

የካቲት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ ፡- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድምአገኝ ፣ቴዎድሮስ ጌታቸው ፣ቴዎድሮስ ባህሩ እና፣ ዘረሰናይ ምስግና ቀርበናል

ተከሳሾች፡- ከ21ኛ በቀር ሌሎቹ ቀርበዋል ጠበቆች የ28ኛ ተከሳሽ አህመድ ጀማል ቀርቤያለሁ የሁሉም ተከሳሾች ጠበቃ ተካ ዳባ መሃመድ አብደላ ባህሩ መካንን አዲስ መሃመድ ቀርበናል ጠበቆቹ እንዲሁ የቀረቡት ስማቸውን በመቅረፀ ድምጽ አስመዝግበዋል ሌሎቹ አልቀረቡም 21ኛ ተከሳሽም አልቀረቡም ለምን ቀሩ እስቲ ማረሚያ ቤት ያለው አለ የተለየ ነገር አለ ትላንት ታመው ነው የቀሩት የሚል ነገር አለ 21ኛ ተከሳሽ እንደዚሁ ሕክምና ላይ ናቸው ተብሏል ፌደራል ፖሊስ ጠበቃ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቶ ነበረ እና አቶ ተማም አባ ቡልጉ ዛሬ እንዲቀርብ ነበር ከፌደራል ፖሊስ ምላሽ አለ አልቀረቡም ጠበቃው የታለ መርመሪው ፌደራል ፖሊስ መጥሪያ ማድረስ ነው እንዲያቀርቡ ሳይሆን መጥሪያ ማድረስ ነው የተሰጠው ትእዛዝ መጨረሻ ላይ ተገቢው ትእዛዝ ይሰጣል ደርሷል አልደረሰም ለምን አልደረሰም የሚለው ታይቶ ማለት ነው አሁን ምስክሩን መስማት እንቀጥላለን



695

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ የአቃቤ ሕግ ምስክር ይቅረቡ

⇒ በእውነት ለመመስከር

⇒ በእግዚአብሔር ስም

⇒ ምያለሁ

⇒ እንኳን ደህና መጡ አሁን ለምስክሮች ደህንነት ሲባል የአባቶን ስም እና የአያት ስራዎን አይገልፁም የመጀመሪያ ስሞን ብቻ ይገልፁልናን ስሞ ማን ነው ?

⇒ ግርማይ

⇒ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ ?

⇒ በተራ ቁጥር 55 ላይ የተጠቀሱት ምስክር ናቸው

⇒ ያው 51ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በቀረበው ክስ ማስረጃ ዝርዝር ላይ 55ኛ ላይ የተጠቀሱት ቀርበዋል ለምስክርነት ነው የቀረቡት አቶ ግርማይ?

⇒ አዎ

⇒ እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?

⇒ በሙስሊም አካባቢ የተነሳ አረብኛ ነው

⇒ ለይተው ሰው ላይ ለይተው የሚመስክሩት አለ?

⇒ ለይቼ የለየሁት ሰው የለም

⇒ የተፈጠረው ማለት መቼ ነው የተፈጠረው?

⇒ ሐምሌ 6 ቀን 2004

⇒ የት አካባቢ?

⇒ መርካቶ በተለምዶ አደሬ ሰፈር ተብሎ የሚጠራው ባይሺ መስኪድ ከምሽቱ አምስት ሰዓት

⇒ እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ

⇒ እሺ ኮማንደር ከጊዜው ይጀምሩ እስቲ ጊዜው መቼ ነው ?

⇒ ሐምሌ 6 ቀን 2004

⇒ እሺ ምንድን ነው የሆነው በዚህ ጊዜ?

⇒ በዛን ጊዜ ከምሽቱ አምስት ~~ሰዓት አካባቢ~~ ነበረ በግምት በወቅቱ የአፍሪካ ሕብረት መሪዎች አዲስ አበባ የሚገቡበት ወቅት ነበረ እና እስታንድ ባይ ነበርኩ እኔ የጣቢያ ኃላፊ ነኝ በወቅቱ የሰው ኃይል ይዘን ጣቢያችን ነበረ እየተንቀሳቀስን



696

2256

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እስቲ ድምፃን ከፍ ያድርጉ እሷን ጠጋ አድርገው

⇒ ከምሽቱ አምስት ሰዓት አካባቢ

⇒ እሺ ይቀጥሉ

⇒ ከምሽቱ በግምት አምስት ሰዐት በወቅቱ እስታንድ ባይ ነበርኩ በጣቢያችንን ክልል ማለት ነው ባልተለመደ አላህዋክበር በሚል ከመስኪዱ ድምጽ ሰማን ምንድን ነው ይሄ ብለን ተነጋገርን ከዛ በኋላ በርካታ ሕዝብ ወደ መስኪዱ እየተሰበሰበ ነው ያየነው ከዛ ምን የሚል ነው የሰማነው አጠቃላይ መንግስት በአወልያ ወገኖቻችንን እየገደለ እየደበደበ ነው በማይክራፎን ሲነገር ነው የምንሰማው ይሄ ሁሉ ሕዝብ ከተሰበሰበ በኋላ ነው ይሄም እኛም አወልያ ምን እየተደረገ እንዳለ ምንም የምንሰማው ነገር የለም ግን በዛ ማይክራፎን ሲናገሩ ነው የሰማነው ይሄን ንግግር ሕዝብ ከተሰበሰበ በአወልያ ወገኖቻችን እየተደበደቡ ነው እና እኛ ተሰባስበን እንሄዳለን ስለዚህ እኛ ብዙ ነን ፖሊስም አንፈራም በመሃላችን አንድ ሰው እንኳን ቢወድቅ እንዳንደናገጥ ይሄ ሁሉ ንግግር በማይክራፎን ነው የሚናገረው

⇒ የት ሆነው ነው የሚናገሩት ?

⇒ እዛ መስኪድ

⇒ የት መስኪድ?

⇒ ባዩሽ መስኪድ የሚባል አለ

⇒ እናንተ የት ሆናችሁ ነው የምትሰሙት ይሄንን ?

⇒ እኛ አራት ብለን ነው የለነው ጣቢያችን አካባቢ ነው ያለነው ከዛ በኋላ ሰወች ላኩና ወደዛ ወደመስኪዱ ከዛ ተሰባስበው መውጣት ጀመሩ እንዳለ ሕዝቡ ተሰባስቦ ወደ ጣቢያችን አቅጣጫ መውጣት ሲፈልግ እኔ በቀጥታ ወደዛ ሄጄ ወዴት ምን እየፈለጋችሁ ነው በአግባቡ በሕጋዊ መፍታት አለባችሁ ጥያቄ ካላችሁ በሕግ አምላክ ተመለሱ ብያቸዋለሁ

⇒ ወደናንተ ጣቢያ ለምን መምጣት አስፈለገ?

⇒ ለምን እንደሆነ ግልጽ አደለም አጠቃላይ መጀመሪያ ወደ አወልያ እንሄዳለን ፖሊስም አንፈራም ፖሊስ ጉዳት እንኳን ቢያደርስብን በመሃላችን ማንም እንዳይደነግጥ ሙስሊምም አይፈራም እንደዚህ የሚል ድምጽ ስለነበረ መጀመሪያ ኦሬዲ እነዚህ ሰወች ወደ ሁከት እየተነሱነው የሚል ግንዛቤ ይገኛ ነው ወደዛ የሄድኩት

⇒ ወደናንተ ጣቢያ ቀጥታ መሆኑን በምንድን ነው እርግጠኛ የሆናችሁት?

⇒ በቀጥታ ወደ ጣቢያችን ያለ ቅያስ ነው እሚመጡ ያለው



697

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እኮ መንገድ ሊያልፉ ነው አደለም የሚለውን እርግጠኛ ናችሁ?

⇒ አደለንም በቀጥታ ወደ ጣቢያ የሚያመጡ ቅያሶች ቅያስ ይዞ ነው እሚመጣ ያለው ሕዝብ ተሰብስቦ ከዛ ኋላ እኛ ወደ ጣቢያ ከመድረሳቸው በፊት ቀደም ብለን ለመነጋገር ሞከርኩኝ

⇒ በምን መልኩ ነው የምታናግሯቸው?

⇒ በቃል

⇒ እኮ በምን ዝም ብሎ በአፋቸው ነው የምታናግሯቸው?

⇒ አዎ እኛም በአፋችን በቃል ነው የምንነግራቸው ለእነዚህ የምናናግራቸው ቀድመው ለመጡ ሰዎች ነው

⇒ ቀድመው የመጡ ተሰልፈው ነው የሚመጣው ሕዝቡ ስለዚህ በሕግ አምላክ ወደት ፈልጋችሁ ነው ከዛ ለእኛ ጉዳት ማድረስ ጀመሩ ድንጋይ መወርወር ጀመሩ እኛጋ ስለዚህ እኛም እየተከላከልን ምንም ሳናሰማ ጥይትም አላሰማንም በወቅቱ

⇒ ምን ይዛችሁ ነበር እናንተ ?

⇒ ዱላ ነው የያዝነው

⇒ ፖሊስ መሆናችሁን በምን ይለዩዋችኋል?

⇒ ዩኒፎርም ለብሰናላ

⇒ ደንብ ልብስ ለብሳችኋል?

⇒ አዎ ደምብ ልብስ ለብሰናል በሕግ አምላክ ነው እያልን እየተከላከልን ያለነው

⇒ እሺ ምን ተፈጠረ ከዛ?

⇒ ከዛ በኋላ በድንጋይ ለፖሊሶች እኔ እራሴ በወቅቱ ጉዳት ደርሶብኛል

⇒ ምንድን ነው የደረሰቦት ጉዳት?

⇒ አንዱ በቀኝ አይኔ ጉዳት ደርሶብኛል በቀኝ እግሬም ግራ ትከሻዬም በርካታ ድንጋይ ነው እላዬ ላይ የወረደው ቀርቤ ስለነበር ከእነሱጋር በእኔ ላይ ከባድ ጉዳት ነው የደረሰብኝ በወቅቱ

⇒ ጉዳት ደረሰብኝ የሚሉትን እስቲ አብራርተው ይንገሩን ምንድን ነው ጉዳቱ ማለት የጉዳቱ መጠን ምን ያህል እንደሆነ አብራርተው ይንገሩን?

⇒ እንግዲህ የጉዳቱ መጠን እስካሁንም ህክምና እየተከታተልኩ ነው እየተመላለስኩ ነው

⇒ ምኖትን?



698

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አይኔ ላይ ይሄ አይኔ እራሱ እስካሁን ደም ነው ነጭ ፓቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ነው የደረሰብኝ እስካሁን እየተከታተልኩ ነው ያለሁት ሕክምና

⇒ ሌላ ምን ላይ ነው ጉዳት የደረሰቦት?

⇒ ቀኝ እግሬ ላይም ጉልበቴ ላይ በከፍተኛ በድንጋይ ተመትቼ ቢያንስ ከሦስት ወር በላይ ነው የዳነው ቁስሉ

⇒ በወቅቱ ጉዳት ደርሶብኛል ብለዋል ስንት ሰዓት ላይ ነው ?

⇒ ሰዓት በቃ አምስት ሰዓት አካባቢ ነው የተሰባሰቡት ቢያንስ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ነው ከዛ ተሰባስበው የወጡት

⇒ እኮ እርስዎ ላይ ስንት ሰዓት ላይ ጉዳት ደረሰ ከዛ እርስዎ ጉዳት ከደረሰቦት በኋላ ወዴት ሄዱ?

⇒ እኔ የደረሰብኝ ደቂቃ እኔ ሰዓት አላየሁም በወቅቱ በጣም ከፍተኛ ግርግር ስለነበረ በዛ በአምስት ሰዓት በተጀመረ እረብሻ የተመታሁ መሆኔ ነው እንጂ ደቂቃዎቹ

⇒ ወዴት ሄዱ ከዛ በኋላ ስራ ቀጠሉ ወደት ሄዱ?

⇒ ሰወቹ ወደ ሕክምና ወሰዱኝ ወደ ክሊኒክ ከኘርዘ ከክሊኒክ ወደ ፖሊስ ሆስፒታል አደረሱኝ እዛ ሕክምናዬን ተከታተልኩ

⇒ ምንድን ነው ምክንያታቸው አሁን ለማናገር ሞክረናል ብለዋል አንዋር መስኪድ ምንድን ነው ምክንያቱ ማለት እናንተ የሰማችሁት ነገር አለ?

⇒ ምንድን ነው ተቃውሞ?

⇒ የተከበሩ አቃቤ ሕግ የሚያርሙት ከሆነ ያርሙት አንዋር መስኪድ የሚባል ነገር አልተናገሩም

⇒ እሺ አርማለሁ እሺ ባዩሽ መስኪድ ነው ያሉኝ?

⇒ አዎ በወቅቱ ባዩሼ መስኪድ ነው

⇒ አዎ እዛ የተፈጠረው ባዩሽ መስኪድ የተፈጠረው በምን ምክንያት ነው አነጋግረናል ስላሉ ማለት ነው ?

⇒ ባዩሼ መስኪድ የተፈጠረው አጠቃላይ በአወልያ ወገኖቻችን እየተደበደቡ ነው ሙስሊሙ ጉዳት እየደረሰበት ነው የሚል ነገር በተደጋጋሚ ሲነገር የነበረ ነው

⇒ ሌላ ከዚህ ውጪ የሰሙት ንግግር አለ?



699

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከዚህ ውጪ መንግስት ጣልቃ ገብቷል ድምፃችን ይሰማ ይሄ ከመሆኑ በፊትም አስቀድሞም ይሄ ነገር ሲነገር የነበረ ነው ይሄም በተለይ መንግስተ በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል የሚል በተደጋጋሚ ሲነገር የነበረ ነው አርብ አርብ ሁል ጊዜ ምናልባት አሁን የተነሳው አንዋር መስኪድም ዋናው የአረብሻው መነሻ ነው እስቲል እስካሁንም ያለ አረበሻ ነው አርብ አርብ እንደሚደረግ እዛ ላይ የሚነገረው ንግግሮች ፍፁም የማይጠበቁ እና ሰላም ባለበት አገር መንግስት

⇒ ጥያቄውን እያዳመጡ

⇒ ምንድን ነው ለምሳሌ ኮማንደር የማይጠበቁ ንግግሮች የሚሏቸው ?

⇒ የማይጠበቁ ነገሮች አንዱ መንግስት ሌባ የሚል

⇒ ተቃውሞ አለ

⇒ ምንድን ነው ተቃውሞ ቆይ እስቲ

⇒ እኚህ ምስክር የመጡት የተከበረው ፍ/ቤት ሐምሌ 6 ባዩሼ መስኪድ ተፈጠረ ያሉትን ነገር ለማስረዳት ነው አቃቤ ሕግ ግን እያሰፉ ከጭብጥ ውጪ እያስወጧቸው ነው እና ወደ ጭብጡ ተመልሰው ጭብጡ ላይ የተቀመጠውን ነገር እንዲያስረዱ እንዲደረግ ነው

⇒ ይሄ አስተያየት መስጠትም አያስፈልገውም እናንተ በተለይ አሁን ያለውን ተውትና ወደ የወንጀል ድርጊቱ ወዳለበት በእርግጥ ምስክሩ ናቸው ያነሱት አቃቤ ሕግ  አልጠየቁም አሁን ወዳለው አሁን ምስክሩ ሰምተውኛል ያኔ ያዩትን እና በዚህ አካባቢ ያለውን ነገር ይመስክሩ አሁን ስላለው እዚህ የቀረበ አደለም ያን መሰረት አድርጋችሁ ጠይቁ

⇒ እሺ ኮማንደር አሁን ያሉት የማይጠበቅ ብለው የገለፁት ቋንቋ ከሐምሌ 6 አሁን እርስዎ ከሚሉት በፊት የሆነ ነው ከዛ በኋላ የሆነ ነው እስቲ እሱን ለይተው በጊዜ ይንገሩን?

⇒ ይሄ መንግስት ሌባ መንግስት በማያገባው በኃይማኖታችን ጣልቃ እየገባ ነው የሚለው ነገር ሁል ጊዜ አርብ አርብ የሚነገር ነው

⇒ ከመቼ ጀምሮ እርስዎ በሚያውቁት?

⇒ ቢያንስ ከ6 ወር በፊት ነው ይሄም የተለያየ በየሳምንቱ እየተገናኘን ስንነጋገርበት የነበረነው

⇒ 6 ወር ከየት መነሻ ማለት ነው ከየት ወደኋላ ከየትኛው ወደኋላ ከምን ወር ከምን አመተምረት ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከ2004 ውስጥ ሆኖ ቆይቷል አሁን በተጨባጭ የተነሳበትን ወቅት አላውቀውም ግን ከ6 ወር ቢያንስ ይሄም ድምፃችን ይሰማ በደረጃም እየተመዘገበ የሙስሊም የሚበተን ወረቀት አለ አርብ አርብ ሁልጊዜ የሚያስታውሰው

⇒ ምን የሚል?

⇒ ድምፃችን ይሰማ ኃይማኖታችን ይከበር ኮሚቴዎቻችን ወኪሎቻችን ናቸው ኮሚቴ ምናልባት የተመረጠ በተደጋጋሚ 17 ኮሚቴ ምናምን በተደጋጋሚ እዛ ጽሁፉ ላይም የእኛ ወኪሎች ናቸው መብታቸው ይከበር ከዛ ቅርብ ጊዜ ደግሞ እነሱ ተያዙ ከተባለ በወሬ ነው የሰማሁት እነማን እንደሆኑ ባላውቅም ኮሚቴዎችም መፈታት አለባቸው የሚል ሁል ጊዜ በአንዋር መስኪድ ቋሚ መነጋገሪያ ነው በተለይ ሰላት ካለቀ በኋላ አላህዋክበር በሚል በሚጀመሩ ቃላቶች ሁል ጊዜ የምሰማቸው ነው የዛ አካባቢ ኃላፊም ስለሆንኩ እከታተላለሁ

⇒ እሺ ማን ነው የሚበትነው ይሄንን ድምፃችን ይሰማ ያሉትን ?

⇒ ማን እንደሚበትነውማ ማወቅ አልችልም አጠቃላይ የሚበተን ወረቀት ነው የማየው እዚህ ላይ መጅሊስ አይወክለንም እኛ የሚመሩን 17 ኮሚቴ ናቸው አይወክለንም መጅሊስ የሚል ነገር ሁል ጊዜ መነጋገሪያ ነው የሚሆነው

⇒ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ዋና ጥያቄ

⇒ እሺ ኮማንደር አይኔ ላይ ጉዳት ደርሷል ብለዋል እስካሁንም እየታከሙ እንደሆነ ገልፀዋል ምንድን ነው የደረሰው ጉዳት?

⇒ እኔ በድንጋይ ተመትቼ ደምም ፈሷል

⇒ ከይኖት ነው?

⇒ አዎ አሁንም ጉዳት ላይ ነው ያለሁት በድንጋይ ተመትቼ ማለት ነው

⇒ ምን የከለከሎት ነገር አለ አገልግሎት እንዳይሰጥ አይኖትን?

⇒ አሁን ይሰበኛል እራሱ አንድ አይኔ የበለጠ ባለሙያ እሚያውቀው ቢሆንም እኔ እራሴ ይሰበኛል

⇒ ይሰበኛል ማለት ?

⇒ አሁን ወደዚህ ሳይ የሆነ ነገር የሚወጥረኝ ነገር አለ ውስጥ

⇒ ጨርሳችኋል የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ

⇒ ኮማንደር ያን ቀን እስከ መጨረሻው ሰዓት ነበር እርስዎ ለሊት ባዩሺጋ ግርግሩ?



101

2261

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ነበርኩ ተመልሼም መጥቻለሁ ከሕክምናም እንደገና ተመልሻለሁ

⇒ ተመልሰው መጥተው እዛው ነበሩ?

⇒ አዎ

⇒ ከዛ ምን እርምጃ ወሰዳችሁ እናንተ ሰው ወጣ እራሱ ነው ወይስ እናንተ ነው ያስወጣችሁት?

⇒ እራሱ ነው የወጣው መጀመሪያ ሲጀመር እኮ በራሱ ነው የወጣው

⇒ ተጨማሪ ኃይል አልመጣላችሁም ነበር?

⇒ ተጨማሪ ኃይል እርዳታ የመጣማ አለ የነበረ በተለያየ አቅጣጫ የነበረ ኃይልም ጨምረን አስመጥተናል

⇒ እኮ ፌደራል ፖሊሶች መጥተዋል?

⇒ ስለ ፌደራል እኔ አላውቅም

⇒ እሺ ጭስ መተኮሱን አያስታውሱም ያኔ?

⇒ ስለ ጭስ መተኮሱ አላውቅም እኔ

⇒ ምን ነበረ ጨለማ ነበር ብርሃን ነበር ምን ነበረ?

⇒ ብርሃን አለ የውጭ መብራት አለ

⇒ ይታይ ነበር?

⇒ አዎ ይታያል

⇒ እሺ ምን አደረጋችሁ ከዛ በኋላ?

⇒ ያደረግነው መጀመሪያ እኮ ተናግሪያለሁ ያደረግነው መጀመሪያ በሕግ በአግባብ

⇒ እኮ ሰው እንደሱ ስላላችሁት ተበተነ?

⇒ አልተበተነም

⇒ ምን አደረጋችሁ እናንተ ምን እርምጃ ወሰዳችሁ?

⇒ ይባስ ለእኛ በድንጋይ ጉዳት አደረሰብን በርካታ ሰው ነው የተመታው እኔ ብቻም አደለሁም

⇒ እሺ ለምጠይቆት ብቻ ኮማንደር አጭር ስለሆነ ጥያቄዬ ከዛ በኋላ ወጣቶቹን ይዛችሁ አልሄዳችሁም ወደ ጣቢያ?

⇒ በወቅቱ የተያዙ በአባሎች ተለይተው እነዚህ ሲወረውሩ ነበር ብለው የተያዙ ሰወች አውቃለሁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እነሱ ላይ የተመሰረተ ክስ ነበር?

⇒ የተመሰረተ ክስ አለ አዎ እነዚህ ድንጋይ ሲወረውሩ የነበሩ አሉ በወቅቱ ጉዳት ያደረሱብኝ ማን እንደሆነ ባለየውም ጉዳት ያደረሱት እነዚህ ናቸው ሲወረውሩ የነበሩት ተብሎ የተያዙ ሰወች ነበሩ ጉዳቱን ለማስረዳትም

⇒ እርስዎም ቀርበው አስረድተዋል ይሄን?

⇒ ቀርቢያለሁ

⇒ የት ነበር የት ምድብ?

⇒ ጳውሎስ መጀመሪያ ፍ/ቤት ቀርቤ ጉዳቱን አስረድቻለሁ

⇒ ምን ተወሰነባቸው ያስታውሳሉ?

⇒ አላስታውስም

⇒ እሺ ያን ቀን መብራት አልጠፋም ለሊት?

⇒ ትዝ አይለኝም መብራት መኖሩን ነው የማውቀው

⇒ እሺ እንትኖቹን ከመስኪድ ካስወጣችሁ በኋላ ፖሊሶቹ አስተኝተው እየደበደቡ ነበር ይሄን አላዩም እርስዎ ?

⇒ እኔ ከመስኪድ እኮ አላወጣንም እያልኩ ነው

⇒ ከመስኪድ ከወጡ በኋላ እሺ ወጡ በየትኛውም ኃይል እንግዲህ ጭስም ሆኖ ወጡ ሰወቹ ወጡና ፖሊሶቹ አስተኝተው መሬት ላይ እየደበደቧቸው ነበር ይሄን አይተዋል እርስዎ?

⇒ እኔ አላየሁም አስተኝተው ፖሊስ ሲደበድብ አላየሁም

⇒ እዛ አካባቢ ያሉ መኖሪያ ቤቶች ገብተዋል የተባሉ ልጆችን እየገባችሁ ስታወጡ ነበረ?

⇒ እኔ አላየሁም ከዛ አላወጣንም ከመኖሪያቤትም የወጣ የተያዘ

⇒ አየሩ ምን ነበር ማለት ዝናብ ነበረ ምን ነበር ዝናብ ነበረ በወቅቱ?

⇒ ዝናብ አልነበረም

⇒ ኮማንደር እርስዎ የተፈጠረውን ነገር ለማረጋጋት ሄጄ ነበር ብለዋል የት አካባቢ ነው ማለት መስኪዱጋ ቀርበው ነው ሲያረጋጉ የነበረው?

⇒ ከስኪዱ ቢያንስ በግምት ከሁለት መቶ ሜትር ይሆናል

⇒ አዎ ከመስኪዱ ሁለት መቶ ሜትር ላይ ሆነው ነው ሲያረጋጉ የነበረው?

⇒ አዎ



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ሰው ሁለት መቶ ሜትር ላይ ሆኖ ነው እርስዎ ሲያረጋጉ የነበረው?

⇒ እማረጋጋበት የነበርኩማ በቅርበት ነው ከመስኪዱ ስላሉ ነው ከመስኪዱ የነበረው እርቀት እኔ የነበርኩበት 200 መቶ ሜትር ይሆናል ብዬ ነው የተናገርኩት ያለሁት

⇒ እርስዎ አሁን እነዚህ ሰወች ከፊት ለፊቱ የሚያዩዋቸው ሰወች ምን ያህል እርቀት ላይ ነበር የነበሩት?

⇒ በጣም ቅርብ በአስር ሜትር ኦር በአምስት ሜትር ተቀራርበን ነው

⇒ ስለዚህ የወረወረቦትን ሰው ያዩታል ማለት ነው አይተውታል ማለት ነው ?

⇒ ብዙ ድንጋይ ስለሚወረወር የነበረ ማን ወርውሮ እንደመታኝ መለየት አልቻልኩም

⇒ ቅድም ባልደረባዬ ሲጠይቆት የተወሰኑ ሰወች ተይዘው ለፍርድ ቀርበዋል አሉ እነዛ ሰወች እርስዎ ላይ ጉዳት አደረሱ ተብለው ነው የቀረቡት?

⇒ አጠቃላይ በሌሎቹም በኔም ብቻም ሳይሆን በሌሎቹ ጉዳት ያደረሱ ስለነበሩ በወቅቱም እዛ ሲጠየቅም ይሄ ነው የመታኝ ብዬ ማስረዳትም አልቻልኩም ብቻ ጉዳቴን ለማስረዳት እዛ ፍ/ቤት ቀርቤ ተናግሬያለሁ

⇒ ጥሩ እነዚህ ሰወች ተቀጡ እንዴ ?

⇒ አሁን ከዚህ በኋላ ቅድም ተመልሷል ውሳኔ ምን ያህል ተሰጣቸው ተከሰዋል ሄጄ መስክሬያለሁ ከዛ በኋላ ተፈረደባቸው ወይ ሲባል አላውቅም ብለዋል ጥያቄውም ብዙ የሚጠቅማችሁም አደለም ወደዚህ ኑና ዋናውን ጥያቄ ጠይቁ

⇒ ቅድም ሲያስረዱ ሙስሊሞች አወልያ ጉዳት እየደረሰባቸው ነው እየተደበደቡ ነው ሲባል ነበር ብለዋል እና ይሄ ጉዳት ደርሷል ብለው አምነው ነው ሰወች የተሰባሰቡት ማለት ነው?

⇒ እነሱ በምን እንደተሰበሰቡ ብዙ የማውቀው ነገር የለም እኔ በማይክራፎን የሚነገረውን ነው የምሰማው እንጂ በአወልያ ምን እየተደረገ እንደሆነ ኢንፎርሜሽን የለኝም

⇒ ከባዩሼመስኪድ ወጥቶ አንድ ሰው በፖሊስ ጣቢያው በኩል አርጎ ማለፍ ይችላል አደል?

⇒ አዎ ወደ ጣቢያ አቅጣጫ ነው የሚመጣው

⇒ አሁን አባባሌ ገባዎት በፖሊስ ጣቢያው በኩል መንገድ አለ አደለም ወደ ግራም ወደ ቀኝም የሚያስኬድ መንገድ አለ አደል?

⇒ አለ



103 2264

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ስለዚህ ሊያልፉ ሊሆን ይችላል ወደዛ የሚመጡት በዛ መንገድ ሊያልፉ ሊሆን ይችላል አደል?

⇒ አይ ሊያልፉ መሆናቸውን እነሱ ነው የሚያውቁት እንጂ እኔ አላውቀውም

⇒ እርስዎ አያውቁም እሺ

⇒ ግን አጠቃላይ ዩኒፎርም ከለበሰ ፖሊስ ስርዓት አርጉ

⇒ በቃ በቃ ሲጠየቁ

⇒ ቅድም ሲያስረዱ እስካሁን ድረስ አስራሰባቱ ኮሚቴዎች ኮሚቴዎቻችን ናቸው እያሉ ነው ብለዋል ትክክል ነው አደለም?

⇒ ይሄን እኮ ብለዋል

⇒ መቃወሚያ

⇒ ኦሬዲ የተባለ ስለሆነ

⇒ ኮማንደር ቅድም አላህዋክበር የሚለውን የሰሙት ጣቢያ ሆነው ነበረ አደል?

⇒ አዎ

⇒ ጣቢያው ከባዩሽ ካሉት መስኪድ ሁለት መቶ ሜትር ያህል ይርቃል ነው ያሉት ወይስ እርስዎ የቆሙበት ነው ሁለት መቶ ሜትር ያሉት ምን ያህል ይርቃል ጣቢያው ከመስኪዱ?

⇒ ኪያንስ ከሦስት መቶ አራት መቶ በግምት አይበልጥም ሦስት መቶ አካባቢ ቢሆን ነው 300 መቶ ሜትር

⇒ ስለዚህ መስኪዱ እና ጣቢያው በመካከል ሌሎች ብሎኮች ወይም የቤት እንትን የለም እንዴ ከእርስዎ ጣቢያ ወደ መስኪዱ ለመድረስ የሚያቋርጧቸው የሚያልፏቸው መንገዶች ቤቶች የሚጋርዱት ነገር የለም?

⇒ ይሄ ከጣቢያ ብዙ የሚጋርደው ነገር የለም በቀጥታ መምጫ ነው ወደ ጣቢያ ወደ ጣቢያ መምጣ ቦታ ነው የወጣሁት ከጣቢያ እራቅ ብዬ መቶ ሜትር ሄጃለሁ

⇒ የኔን ጥያቄ ግልጽ ላርግሎት እና ጣቢያው በራፍ ላይ ሆነው ፊት ለፊት ወጥተው ቢያዩ መስኪዱን ማየት ይችላሉ ወይስ ሌሎች የሚጋርዱ ነገሮች አሉ ቤት የመሳሰለ ነገር ከጣቢያ ሆነው ማየት ይችላሉ መስኪዱን 300 ሜትር እርቀት ነው በነዚህ 300 ሜትር እርቀት መካከል ሌሎች ቤቶች የሉም የሚጋርዱ ጣቢያውን እና መስኪዱን?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሱ የሚጋርድ አለው መጋረድ አለው ቅያስ አለው ግን ወደ ባቢያ መምጫ ቀጥታ መስመር ነው ግን መስኪዱን ለማየት የሚከልሉ ቤቶች አሉ

⇒ ጥሩ አሁን ይሄ ጥሪው ከባዩሽ መስኪድ ለመሆኑ በምንድን ነው ያወቁት ?

⇒ ባዩሽ

⇒ አላህዋክበር የሚለው ከየት እንደወጣ እርስዎ ገምተው ነው ወይስ በምን አወቁ በ300 ሜትር እርቀት ነው በመሃል እሚጋርድ ነገር አለ ድምፁ ከዛ ለመሆኑ ወይስ ይሄን ጥሪ ብቻ ነው የሰሙት እርስዎ ከየት እንደሆነ አላወቁም?

⇒ በቀጥታ ከባዩሼ መሆኑም ይሰማል ሕዝብም እራሱ አላህዋክበር ተብሎ ሲጠራ ከየአቅጣጫው በጣቢያውም እራሱ እሚያልፍ ሕዝብ አለ ወደመስኪዱ

⇒ ከዛ መስኪድ መሆኑን በምን ለዩት እርስዎ?

⇒ በደምብ ለየሁት ቅርብ ስለሆነ

⇒ ማለት ከሚወጣው ድምጽ ተናጋሪውን ለይተው ነው አሁን 300 ሜትር ስለሆኑ ስለማይታዮት ለመለየት ያስቻሎትን ምክንያት ቢገልፁልን ማለቴ ነው ግምት ሊሆን ይችላል ?

⇒ ግምት አደለም ከዛ በሆነው እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው

⇒ እዛ ባዩሼ ያሉት መስኪድ አካባቢ ሌሎች መስኪዶች የሉም እንዴ በሱ አቅራቢያ ?

⇒ ሌላ የለም

⇒ እሱ ብቻ ነው?

⇒ አጠገቡ አለ አንድ ግን ከዛ አደለም እሱ እኔ ያለፍኩበት ነው እራሱ መቶ ሜትር ሄጄ ያለፍኩበት ነው መስኪዱ እዛ ያለው

⇒ ኦኬ ይቅርታ ቅድም ሲነግሩን ይሄ ሁልጊዜ ጁምአ ጁምአ ከስግደት በኋላ የሚባለውን ነገር የሚለው ሰው ይሄ አንዋር መስኪድ አካባቢ ይላል ያሉት ምን ያህል ይሆናል ቁጥሩ በግምት እንደው ብዙ ነው ትንሽ ነው ?

⇒ አላህዋክበር የሚለው

⇒ ይሄ ድምፃችን ይሰማ ኮሚቴዎች ወኪሎቻችን ናቸው መብታችን ይከበር ይፈቱ የሚለው ?

⇒ በቁጥሩ ብዙ ነው

⇒ ምን መስኪድ ውስጥ ነው ከመስኪድ ውጪ ነው?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከመስኪድ ውጪ መስኪድ ወስጥም እንደዛ የሚሉበት አለ በተለይ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ተለይተው በር ላይ ሌላ ሰግዶ ሲሄድ ተለይተው ቀርቶ እንደዛ አይነት የሚሳደቡበት ሁኔታ አለ

⇒ ቅድም ከተመቱ በኋላ ወደ ክሊኒክ ተወስደው ከዛ ወደ ሆስፒታል ሄደ ሕክምና ተከታተልኩ ብለውናል በዛው በእለቱ ነው ወይስ ወዲያው እንደተመቱ ነው ሆስፒታል ሄደው የተከታተሉት ክሊኒክ ታክመው ተመለሱ ወይስ በዛው ሄዱ?

⇒ ታክሜ ተመለስኩ

⇒ ወደ ስራዎ?

⇒ አዎ

⇒ ወዲያው ሕክምና 18 ክሊኒክ ውስጥ ገባሁ እዛ ማድረግ አንችልም በቀጥታ ወደ ሆስፒታል ላኩኝ ሆስፒታልም ታክሜ እንደገና ወደ ጣቢያዬም መጥቻለሁ በመኪና

⇒ ከዛስ በማግስቱ ስራ ላይ ነበሩ?

⇒ ነበርኩ እስቲል እየተከታተልኩ ነው ያለሁት እስካሁን

⇒ አሁን ያለመሣሪያ ነው አደል የሚያዩት?

⇒ እ

⇒ አሁን እያዩ ነው አደል ያለ መነጽር ያለ ሌላ ነገር አሁን ሲመሰክሩ ሌላ የአይን እንትን አርገዋል እንዴ?

⇒ እያየሁ ነው

⇒ ያለምንም ተጨማሪ ነገር እያዩ ነው?

⇒ አዎ

⇒ አንደኛው አይኔ ነው ጉዳት የደረሰው

⇒ ሃኪም የጉዳት መጠን ገልፆ ጽፍሎታል የደረሰውን?

⇒ እሱ ገልፆልኛል

⇒ በፐርሰንት የተቀመጠ ነገር አለ ይሄን ያህል የአይኖ የእይታ ችግር ወይም እንደዚህ ይሄን ያህል ፐርሰንት ብሎ ያስቀመጠው ነገር አለ?

⇒ አይ እንደዛ አልሰጠኝም መስጠት እንደሚችል ግን ነግሮኛል ሃኪም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት



706

2268

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ኮማንደር ቅድም ስወጣ አላህዋክበር ተብሎ ጥሪ ሲደረግ በጣቢያም ሰው እያለፈ ነበር ብለዋል ወደ መስኪዱ እየሄደ ማለት ነው ያን ጊዜ ውርወራ አልተጀመረም?

⇒ አልተጀመረም

⇒ እሺ እርስዎም ደግሞ ሰወቹን ሄጄ ለማረጋጋት ተው በሰላማዊ መንገድ ፍቱ ምንድን ነው ችግራችሁ ብዬ አናግሬያቸዋለሁ ያን ጊዜ ውርወራ አልተጀመረም?

⇒ አልተጀመረም

⇒ ምን ተፈጥሮ ነው ውርወራ የተጀመረው ምን ሲደረግ ነው መወርወር የጀመሩት እሱን በሰላማዊ መንገድ ካናገሩት በኋላ ምን ተፈጥሮ ነው ?

⇒ አደለም ከመስኪድ ጠቅላላ ተሰባስበው መውጣት ከጀመሩ በኋላ ነው ውርወራው የተጀመረው

⇒ እኮ ምንም ሳይፈጠር ነው እንዲሁ መወርወር የጀመሩት ነው ወይስ ሌላ የተፈጠረ ነገር ስለነበረ ነው እርስዎ በሰላም አናገሯቸው ከዛ በኋላ ነው መወርወር የተጀመረው?

⇒ አደልም በሰላም ሳናግራቸው እኮ ለሰላም አደለም እየመጡ የነበረው እኛ ነን ያላወቅነው እንጂ ለሰላም እንዳልሆነ እኮ እነሱ ነው የሚያውቁት እኛ ለሰላም መስሎን ነው ምንድን ነው ያልተለመደ በለሊት እንደዚህ የምታደርጉት ወዴት ፈልጋችሁ ነው ብለን በሕግ ፍቱት ስርዓት አርጉ ምናምን ስንላቸው ለእኛ ነው ድንጋይ የወረወሩት ይሄ ከመስኪድ ወጥተው የሚያደርጉት ያለ ድርጊት ነው

⇒ እኮ ገባኝ የኔ ጥያቄ ግን መወርወር ማለት እርስዎ አናገሯቸው ከዛ በኋላ እዛው ላይ ቆማችሁ እያለ ነው

⇒ መቼ አናገሩኝ እኔ እኮ ነገርኩት ፊት ለመጡት ሰወች ለመነጋገር ሞክርን ከዛ በኋላ የድንጋይ ናዳ ወደና ወረደ ነው

⇒ አልተነጋገራችሁም እሺ ሰው ወደ ጣቢያ እየመጣ ነበር ወደ ጣቢያ የሚያስኬደው መንገድ ወደ አወልያ ያስኬዳል አያስኬድም ?

⇒ ቆዩ እስቲ አሁን ያለው ነገር ስለ ፖሊስ ጣቢያ ወደ መሄዱ ተጠይቋል ከዛ ውጪ ሌላ ጥያቄ ካላችሁ?

⇒ እሺ ትቼዋለሁ

⇒ አሺ ኮማንደር ቅድም ተጠይቀው ሲመልሱ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰወች ነበሩ ብለዋል ምን ያህል ይሆናሉ በፖሊስ የተያዙ ሰወች?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በዛን ጊዜ?

⇒ አዎ በዛን ወቅት ምን ያህል ሰወች ተይዘው ነበር?

⇒ እንግዲህ የተያዙት ዝርዝራቸውን እኔ አላውቅም ግን እኔ በስድስት ሰው ተይዞ ወደ ጳውሎስ ቀርቦ

⇒ አይ እነሱ ያው ጉዳት አደረሱ የተባሉት ናቸው ግን አካባቢው ላይ በዛ ወቅት በአጠቃላይ ወደ ፖሊስ ጣቢያ የተወሰዱ ምን ያህል ሰው እና ያደሩ ምን ያህል ሰው ነው የሚያስታውሱት ኃላፊም ነኝ ስላሉ ያውቁታል?

⇒ እሱን በቁጥር አላውቅም

⇒ ብዙ ሰው ነው የነበረው?

⇒ በወቅቱ ጉዳትም ደርሶብኝ ስለነበረ እኔ ቢሮ ውስጥ ነው የነበርኩት

⇒ አይ ተመልሼ መጣሁ ብለዋል ሕክምና ተደርጉልኝ ተመልሼ መጣሁ ብለዋል

⇒ አዎ ተመለስኩና ቢሮ ጣቢያ ነው የገባሁት

⇒ እኮ ኃላፊ ስለሆኑ ያውቃሉ በሚል ነው እና ብዙ ሰው ነበረ የተያዘው?

⇒ የተያዙ ሰወች እንዳሉ ከነዚህ ደግሞ ዋናዎቹ ተብለው የተለዩ እኔ ጉዳት አደረሱብኝ ጉዳት ከደረሰብኝ ለማስረዳት በሄድኩበት ያየኋቸው

⇒ ከተያዙት ውስጥ ሴቶች ነበሩ?

⇒ ሴቶች አላስታወስኩም

⇒ አጠቃለይ ከተያዙት ውስጥ ሽማግሌዎች ነበሩ?

⇒ አላስታወስኩም በደምብ ስላለየኋቸው እነሱን አለየሁም እኮ አልኩኝ

⇒ እሺ ይሄ የተሰበሰበው ሕዝብ በምን ተበተነ ፖሊስ አካባቢውን በቁጥጥር ስርአድርጎት ነው የተበተነው?

⇒ ለሁሉ ቁጥጥር ያደረገውን ፖሊስ አላስታውስም

⇒ እስቲ ሰው በምን ተበተነ በምን ምክንያት ተበተነ ፖሊስ አካባቢውን አረጋጋ በቁጥጥሩ ስር አዋለ ?

⇒ አዎ ተጨማሪ ፖሊስ መጥቶ ሁኔታው ተበታትኗል አልቀጠሉም ወዳሰቡበት አልሄዱም አላለፉም

⇒ ፖሊስ በቁጥጥሩ ስር አደረገው ማለት ነው አካባቢውን ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ማለት ነዋ አንግዲህ

⇒ የባዩሺ መስኪድ ማማ ወይም ሚናራው ላይ ጉዳት ማን እንዳደረሰበት ያውቃሉ ?

⇒ አላውቅም

⇒ ሰወቹን አያውቋቸውም?

⇒ አላወቅኩም

⇒ ማማው ላይ ግን ጉዳት ደርሷል አደል?

⇒ ለማን ጉዳት አደረሰ እዛ ፖሊስ ገብቶ

⇒ አይ አሁን ፖሊስ እያልኩ አደለም እኔ የመስኪዱ ማማ ላይ ግን ጉዳት ደርሷል ?

⇒ መስኪዱ ጉዳት መድረሱን ኢንፎርሜሽን የለኝም ጣቢያ መጥቶ ያመለከተ ሰው ጉዳት ደርሶበታል ብሎም አላውቅም

⇒ እርስዎ የአካባቢው ጣቢያ ኃላፊ ኖት አደል ተመልሰው ሄደው መስኪዱን

⇒ በቃ አሁን አላውቅም ካሉ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ

⇒ መስኪዱን ሄደው አላዩም በንጋታው ወይ በሌላ ቀን

⇒ ይኸሉት አላየሁም ብለዋል ያመለከተም የለም ሄደ፣ አረጋገጥን በቂ ነው

⇒ ከመስኪዱ አትውጡ ቅድም ድምጽ ሲነገር እሰማ ነበር ስላሉ ከመስኪዱ አትውጡ ከመስኪዱ ውጪ ያሉት ከእኛ ጋር አደሉም እየተባለ ነበር አደል?

⇒ ከመስኪድ አትውጡ ሳይሆን ተሰባስበን እንሄዳለን መስኪድ ውስጥ ሆኖ ነው እንደዚህ እየተናገረ ያለው ከመስኪድ ወጥተን እንሄዳለን ፖሊስም አንፈራም

⇒ እሺ እዚሁ ሆነን ጥያቄያችንን እናቀርባለን ከመስኪድ አትውጡ ሲባል ነበር አደል?

⇒ አይ ይሄ አልተባለም አልሰማሁም

⇒ ኮማደር በቀኝ አይኖ ላይ የደረሰውን ጉዳት አሁንም እየተከታተልኩ ነው ብለዋል የተቀረው ይሄ ቀኝ እግሮ ግራ ትከሻዎ ላይ የደረሰው ከ3 ወር በኋላ ታክመው ዳኑ አደል?

⇒ አዎ ድኗል

⇒ ጨርሰናል ይተከበረው ፍ/ቤት

⇒ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ

⇒ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እሺ በፍ/ቤቱ ጥያቄ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ የተጐዳ ሰው አለ ብለዋል እና ከእርስዎ ውጪ ያሉት እነማን ናቸው የተጐዱት ምናቸውን ተጐዱ እስቲ ?

⇒ አንዱ ፊኛው እዚህ አካባቢ

⇒ ስሙን እየገለፀ ምን እንደተጐዱ?

⇒ ቡሽራ እዚህ ላይ

⇒ እዚህ ላይ ማለት እንዲመዘገብ

⇒ ሆዱ ላይ

⇒ ምን ሆኖ ነው?

⇒ በድንጋይ እኔ እንደዚህ ብዬ ያላለፍኩት ድንጋይ ነው የመታው

⇒ በድንጋይ ተመታ?

⇒ አዎ

⇒ እሺ ከዛስ ምን ሆነ?

⇒ ከዛ እንትኑ ዱላውን ጣለ ሽብረክ ብሎ ቁጭ አለ አይዞህ አይዞህ ምናምን አለው አንዱ

⇒ ዱላ ጥሎ ቁጭ አለ?

⇒ አዎ

⇒ ከዛስ?

⇒ ከዛ ተነስቷል

⇒ ከዛ በኋላስ?

⇒ ከዛማ ወደ ሕክምና ነው

⇒ በዛኑ ሰዓት ነው ከዛ በኋላ?

⇒ አብዛኛው በዛን ጊዜ ሕክምና ክሊኒክ የተለያየ

⇒ አይ ስለ ቡሽራ እንጨርሳ ?

⇒ ስለ ቡሽራ ሕክምና ሄዷል

⇒ እሺ ምን ተባለ ሕክምና ?

⇒ ምን እንደተባለ አላወቅኩም

⇒ ወደ ስራ ተመለሰ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አይ ይመለስ አይመለስ ትዝ አይለኝም ግን ደህና እንደሆነ ለብዙ ጉዳት እንዳልሆነ

⇒ እ?

⇒ ለብዙ ችግር እንደማያጋልጠው ነግሮኛል

⇒ ለብዙ ችግር ወደ ስራው ተመለሰ በነጋታውስ?

⇒ አዎ ተመልሷል

⇒ እሺ ከዛ በኋላ የተጐዳ አለ ከቡሽራ ውጪ?

⇒ አንበሴ ሞርካ

⇒ ምኑን ተጐዳ እሱስ?

⇒ እሱ ጭንቅላቱ ላይ

⇒ ምን ሆነ ጭንቅላቱ ?

⇒ በድንጋይ ተመታ

⇒ እሺ ከዛስ ምን ሆነ?

⇒ እሱም እንደኔ ክሊኒክ ሄዷል

⇒ ደምቷል የተመታው ቦታ?

⇒ ደምቷል አዎ

⇒ ክሊኒክ ሄዷል?

⇒ አዎ

⇒ ከዛስ ምን ሆነ?

⇒ ሆስፒታልም ሄዷል

⇒ እሲ ከዛስ?

⇒ እንደዛ ነው ያለው

⇒ ወደ ስራ ተመልሷል?

⇒ አዎ

⇒ መቼ በዛኑ ቀን ነው በማግስቱ ነው ቆይቶ ነው እስቲ እሱን?

⇒ እሱ ቆይቷል ይመስለኛል ሳይገባ

⇒ ምን ያክል?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አሁን መቁጠር አልችልም

⇒ ትንሽ ቆይቶ ወደ ስራ ተመልሷል?

⇒ አዎ

⇒ እሺ ሌላ የተጐዳ አለ?

⇒ አግኝቼ ምኑ ላይ እንደተመታ

⇒ እ?

⇒ በርካታ ሰው ነው የተመታው ኤኒ ዌይ

⇒ የሚያስታውሱት ያዩት ብቻ?

⇒ በቃ እነዚህ ቀድሜ የተናገርኳቸው ነው በበለጠ ያየኋቸው

⇒ ጨርሰዋል እናመሰግናለን

⇒ በእውነት ለመመስከር

⇒ በእግዚአብሔር ስም

⇒ ምያለሁ

⇒ ለምስክርነት ነው የመጣኸው ?

⇒ አዎ

⇒ የአባትህን ስም ሳትጨምር የራስህን ስም ብቻ ትነግረናለህ?

⇒ አስናቀ

⇒ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ?

⇒ በተራ ቁጥር 15 ላይ የተጠቀሱት ናቸው

⇒ በተሰሙት ዝርዝር ያው 52ኛ ላይ ደርሰናል በክስ ማስረጃ ዝርዝር ላይ 15 ላይ የተጠቀሰ አቶ አስናቀ

⇒ አቤት

⇒ ለምስክርነት ስለመጡ እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አጠር አርገው ?

⇒ እኔ

⇒ ሰው ላይ ለይተው የሚመሰክሩት ካለ እሱን ?

⇒ ሰው ላይ ለይቼ ሳይሆን በሰዓቱ የስራ ቦታዬ አካባቢ.



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ሰዓቱ ማለት መቼ ነው?

⇒ ሐምሌ 14 ቀኑ 8 ሰዓት 2004

⇒ ከቀኑ 8 ሰዓት ምን ሆነ?

⇒ የምሰራበት አካባቢ

⇒ የት  አካባቢ ነው?

⇒ ወደ ቦምብ ተራ ወይ ጆንያ ተራ አካባቢ የስራ ቦታዬ ነው

⇒ የት አካባቢ ነው እሱ ቦምብ ተራ ወይ ጆንያ ተራ?

⇒ መሃል መርካቶ ነው

⇒ እሺ አቃቤ ሕግ ይቀጥሉ ዋና ጥያቄ?

⇒ መቼ ነው ቀኑ?

⇒ 14

⇒ስንተኛ ወር?

⇒ 11ኛ ወር 2004

⇒ ስንት ሰዓት አካባቢ ነው?

⇒ 8 ሰዓት

⇒ ከቀኑ ነው ?

⇒ ከቀኑ 8 ሰዓት

⇒ እሺ ቦታው የት አካባቢ ነው?

⇒ መሃል መርካቶ ጆንያ ተራ አካባቢ

⇒ እሺ አሁን በጠቀሱት ቀን ሰዓት እና ቦታ ምን ገሀነ ምን ተከሰተ?

⇒ እዛ አካባቢ የነበረው ትንሽ ግርግር ነበረ በጣም አካባቢው ሁሉም ያው ንብረትም ሱቅ ያለው ንብረቱን ለማስገባት በሚሯሯጥበት ሰዓት ነው እኔም ንብረት ስለነበረኝ እሱን ለማስገባት እየተሯሯጥኩ ነው ግን ከመስኪድ አካባቢ ይመጡ የነበሩ ወጣቶች እንደማነሳሳተ አይነት እንትን እያደረጉ ነበረ

⇒ ምን እያሉ ነበረ የሚመጡት?

⇒ የተለያየ አላሁዋክበር አይሂችሁ በርቱ አይነት ነገር ነው እና ድንጋይም ትልልቅ ድንጋይ እየያዙ ይወረውራሉ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ማን ላይ ነው የሚወረውሩት?

⇒ ወደ ፎቅ ከፊት የሚመጡም ፖሊሶች ነበሩ ወደነሱ

⇒ እሺ?

⇒ እና እኛ በዛ ሰዓት ሱቃችንን ዘግተን ለመሸሽ ነው እንትናችን

⇒ አሃ እዛ አካባቢ ሱቅ አለት እርስዎ?

⇒ አዎ እዛ የምሰራበት አካባቢ የስራ ቦታዬ እና እኛ ዘግተን ለመሮጥ ነው ያው እኛም ወደቤታችን በዛ ሰዓት አካባቢ ፊት ለፊት መኪና ነበረኝ በዛው ቅስበት መኪናዬ ተሰብሮ ንብረት ተወስዶብኛል

⇒ ምን አይነት መኪና ነበር?

⇒ የራሴ የቤት መኪና

⇒ ምን አይነት መኪና ነው?

⇒ ቪታራ

⇒ እሺ ሰሌዳ ቁጥሩ?

⇒ 74608

⇒ ኮድ ስንት ነው?

⇒ 2

⇒ እሺ በዚህ መኪናዬ ላይ ጉዳት ደረሰ ብለዋል ምኑ አካባቢ የመኪናው የትኛው አካልላይ ነው ጉዳት የደረሰው?

⇒ ኮድ ሁለት ስትል የት አዲስ አበባ ነው ኢትዮጵያ ነው?

⇒ አ.አ

⇒ እሺ ቀጥል

⇒ ከእኔ ከምገባበት የኋላ በር መስታወት

⇒ ምን ሆኗል መስታወቱ?

⇒ መስታወቱ ተሰብሯል

⇒ በምንድን ነው የተሰበረው?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ የተሰበረው በድንጋይ ነው በዛ ሰዓት በዛው ቅስበት መኪናዬን እንዳለ ግርግር ስለነበረ አንስቼ ሄድኩኝ በንጋታው ግን የፖሊስ እንትን መጥቶ ስብርባሪ አይቶ ይሄ ሆነ ተብሎ አካባቢው ላይ መጥቶ የመታ እንትን ነው እንጂ ከሩቅ የተወረወረ አደለም ተብሏል

⇒ መኪናው ነው መስታወቱ ያሉት?

⇒ ከሹፌር ኋላ የጐን ሆኖ ከኋላ

⇒ እሺ የገንዘብ ግምቱ ምን ያህል እንደሆነ ያስታውሳሉ የደረሰበት ጉዳት?

⇒ ያው በግምት እንግዲህ ኮምፒውተር ላፕቶፕ ተወስዶብኛል የተለያዩ ዶክመንቶች የያዘ ቦርሳ ተወስዶብኛል እራሱ የመስታወቱ ግምትም አለ ቢያንስ እንግዲህ ግምቱን ገምቼዋለሁ ለመስታወቱ ያወጣሁት ብር አለ ኮምፒውተር አለ በአጠቃላይ ወደ አስር ሺ አስራአንድ ሺ ብር አካባቢ አውጥቻለሁ

⇒ ይሄን ያህል የሚገመት ጉዳት ደርሷል?

⇒ አዎ

⇒ ዋና ጥያቄ አበቃን የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እሺ መስቀለኛ ካለ

⇒ እሺ አቶ አስናቀ

⇒ አቤት

⇒ የስራ አካባቢዬ ጆንያ ተራ ነው መርካቶ መሃል ነው ብለዋል እዚህ መርካቶ መሃል ወይም ጆንያ ተራ አካባቢ የሆነ ግርግር ቢፈጠር ግርግሩን ተጠቅመው የሰው ንብረት ለመዝረፍ ወይም የሰው ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚፈልጉ ዱርዬዎች ወይም ሌላ አላማ ያላቸው ሰወች አሉ አደለም አካባቢው ላይ?

⇒ አካባቢው የስራ ቦታዬ ስለሆነ ለእንደዚህ አይነት ነገር ሰፈራችን ስለሆነ እንደዚህ አንጠቀምም በሩን ክፍትም እንኳን አርገን ብንወርድ ምንም ነገር ገጥሞን አያውቅም

⇒ ግርግር ቢፈጠር ግን ከመዝረፍም ወይም የሆነ ነገር ለማድረግ የናንተ አካባቢ ላይ ላይሆን ይችላል ከሌላ ቦታ የመጡ ሰወችም ማለቴ እዛው መርካቶ ሆኖ ከሌላ መርካቶ የተለያየ ክፍፍሎች ስላሉት እናንተ የማታውቋቸው ሰወች መጥተው ንብረት ሊወስዱ የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራል አደል?

⇒ እኛ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ጥያቄው በቀጥታ እነዛ አላህዋክበር የሚሉት ሰወች ሳይሆኑ ሌላ ሰፈር ላይ የሚወስዱ ሰወች አሉ አደለም ወይ ነው ጥያቄው እንደዛ ነው ?

⇒ ያው በዛ ሰዓት እኛ የራሳችንን ንብረት ለማሸሽ ስለሆነ ማን ሰበረው ይሄ ነው ለማለት እንቸገራለን ግን በዛ ቅጽበት የተሰበረብን እነሱ ባነሳሱት ነገር ነው እንጂ ሰፈራችን ላይ እንኳን በር ዘግተን በሩን ክፍት አርገን እንኳን አንነካም

⇒ ጥሩ እሺ እነሱ ያርጉት አያርጉት አላዩም አደል ?

⇒ ሰው ሲያረግ ባይማ እኔም አሳልፌ ንብረቴ ሲወሰድ ዝም ብዬ አላይም

⇒ ጥሩ እነሱ አላረጉትም ማለት ነው እየተሯሯጡ የሚመጡ ሰወች ነበሩ ብለዋል ማን ነበረ የሚያሯሩጣቸው ?

⇒ እየተሯሯጡ ማለት?

⇒ ማለት የሚያሯሩጣቸው ሰው ነበረ እየሮጡ ነበረ ሲመጡ የነበረው ?

⇒ ፀጥታ አስከባሪዎች አሉ በጣም የበዙ ሳይሆኑ ትንሽ ፖሊሶች ነበሩ እነሱ ከፊት ይመጣሉ እነዚህ ወጣቶች ወደፊት ለመሄድ ከኋላ ያለውን ሰው አይዟችሁ በርቱ አላህዋክበር እያሉ ያነሳሷቸዋል ፖሊስም ስለሚፈሩ ደግሞ

⇒ የእርስዎ አካባቢ ከአንዋር መስኪድ ምን ያህል ይርቃል?

⇒ በግምት ስምንት መቶ ሜትር ሊሆን ይችላል

⇒ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች አሉት  አደል ቀጥታ መንገድ አደለም?

⇒ ዋና መንገድ ነው ምንም ውስጥ ለውስጥ የለውም መሃል መርካቶ ነው

⇒ ማለት ከእርስዎ የስራ ቦታ ወደ አንዋር መስኪድ ለመድረስ የተለያዩ እንቅፋቶች አሉት?

⇒ ዋና መንገድ ነው ሹሉክሉክ መንገድ የለውም

⇒ በወቅቱ ከ7ኛ አካባቢ ወደዛ አላዩም እርስዎ?

⇒ ከሱ አይርቅም

⇒ አይ ከ7ኛ አካባቢ መንገድ መዘጋቱን ያውቃሉ?

⇒ እኔ ስራ ቦታዬ ወደ 7ኛ ከ7ኛ እና ከመስኪድ መሃል ነው

⇒ እርስዎ ይሄ ነገር እስኪያልቅ እዛው ሱቆት ላይ ቆዩ ወይስ?

⇒ እንዴ ነፍሴን ለማሸሽ ነው እንኳን

⇒ ወደፊት ሄዱ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ወደ መኖሪያ ቤቴ መኪናዬ ተሰብሮ እንደተሰበረብኝ ወደ ፖሊስም መሄድ ስለማልችል ቀጥታ

⇒ በየት በኩል ሄዱ?

⇒ ቀጥታ ወደታች በቦምብ ተራ አድርሬ ወደ በርበሬ በረንዳ አርጌ ነው የሄድኩት

⇒ በበርበሬ በረንዳ አርገው በአብነት ሄዱ?

⇒ አዎ ቀጥታ ወደዛ

⇒ እዛ አካባቢ ግርግር ነበር አብነት አካባቢ?

⇒ ፖሊሶቹ እየገፉ ሲመጡ ያው እንትትኑ ወደኋላ ነው እየሄደ የነበው ከዛ በኋላ ግን ያለውን ነገር እኔ አላየሁም

⇒ አይ እኔ የጠየቅኩት በርበሬ ተራ ወይም አብነት አካባቢ ግርግር ነገር አይተዋል?

⇒ እኔ እየሄድኩኝ በነበረ ሰዓት የፌደራል ፖሊስም እየመጣ

⇒ ቆይ ምስክር ከበርበሬ ተራ በኋላ እኔ አላየሁም የሆነውን ነገር ነው እያሉት ያለው

⇒ እንደዛ ነው የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እንደዛ ነው ሄድኩኝ በቦምብ ተራ በርበሬ ተራ አድርጌ ሄድኩኝ የሆኑ ፖሊሶች ነበሩ ከዛ በኋላ አላየሁም የሆነውን ነገር ነው እያሉ ያሉት

⇒ አቶ አስናቀ ቅድም ከመስኪድ የሚመጡ ወጣቶች ብለው ነበር ከመስኪድ መሆናቸውን በምን አወቁ?

⇒ አንደኛ አቅጣጫቸው ከመስኪድ ነው 2ኛ ያደረጉት አለባበስም የተጠቀሙትም እንትን በሙሉ ከዛ አካባቢ እንደሆነ ያስታውቃል

⇒ እርስዎ ከሚሰሩበት እንግዲህ በወቅቱ እርስዎ የሚሰሩበት ቦታ ላይ ነበሩ እዛ ሆነው ያሉትን መስኪድ በአይኖ ማየት ይችሉ ነበር ይታያል ከሚሰሩበት ቦታ?

⇒ አይታይም

⇒ አቅጣጫ ሲሉ በእርስዎ የስራ ቦታ እና በመስኪዱ አንድ አቅጣጫ ነው ያለው ?

⇒ አንድ መንገድ ነው ያለው እዛ መሆኑ ምንም እንትን የለውም ከሌላ ቦታ

⇒ አንድ ማለት እስቲ ይንገሩን እርስዎ ያሉበት ቦምብ ተራ ወይም መሃል መርካቶ ነው አንዋር መስኪድ ደግሞ ይታወቃል ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ የአንዋር መስኪድ መንገድ እና የኔ ሱቅ አንድ ሁለት ሱቅ ነው ያለው ከዋናው መንገድ ሁለት ሱቅ ነው ያለው ከዋና መንገድ አለ ከስኪዱ ከዛም ሁለት ሱቅ አልፎ ነው የኔ

⇒ ከአንድ አቅጣጫ ነበር ውርወራ የነበረው ነው ከሁሉም አቅጣጫ ነው ያኔ አንተ እቃ እያሸሽን ነበር ምናምን ስትል ከብዙ አቅጣጫ ነበር ሲወረወር የነበረው ወይስ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ነበር ውርወራ የነበረው ወይም ግርግሩ የነበረው ማለት ነው?

⇒ ወጣቶቹ እነሱ በነበሩበት አካባቢ ብቻ ነው ይወረወር የነበረው ሲያነሳሱ የነበሩ ወጣቶች እየተበተኑ ልክ እኔ ሱቁን እንደዘጋሁኝ እነሱ አልፈውኝ ሄደዋል ከዛ በኋላ ያየሁት ነገር የለም እኔ ሱቅ እስኪመጡ ድረስ ግን እነሱ ነበሩ ሲወረውሩ የነበሩት

⇒ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ነው ሲወረወር የነበረው?

⇒ አዎ በግሩፕ ናቸው

⇒ እኮ ገባኝ ከሌላ አቅጣጫ የሚወረወር ነገር አልነበረም?

⇒ ከሌላ ማለት እነሱ ወደፊት ይወረውራሉ ከፊት ያለው በታች የነበሩት ፖሊሶች ደግሞ ዱላ የነው የያዙት የሚወረውሩት ነገር የለም እነሱም እራሳቸዉን ያው እየፈሩ ነው እንትን ሲሉ የነበሩት

⇒ እሺ ፖሊሶቹ በያዙት እንትን የአይሰብዙ መስታወት ሲሰብሩ አላየህም አንተ እዛ ላይ ከነበርክ ?

⇒ እኔ አካባቢ ከኔ ሌላ የተሰበረበት እማውቀው ነገር የለም የኔን መኪና ግን ሲሰበር እነሱም ያዩት ነገር የለም እኔ ብቻ ነኝ በቃ በዛ ሰዓት ሁሉም

⇒ መሰበሩን ነው ያየኸው አንተ ከተሰበረ በኋላ ነው ያየኸው ወይስ ሲሰበር ነው ያየኸው የአንተን መኪና?

⇒ ልክ ሱቁን ዘግቼ ስሄድ ተሰብሯል ?

⇒ ማን እንደሰበረው እንዴት እንደተሰበረ አላየህም ተሰብሮ ነው ያየኸው?

⇒ አዎ

⇒ ፖሊሶቹስ እንደዚህ ልጆቹን መሬት ለመሬት ሲጐትቱ አላየህም?

⇒ አላየሁም እነሱን

⇒ አንድ ጥያቄ ብቻ ኮምፒውተር እና መኪና አንድ ላይ አስር ሺ ብር ብለዋል የደረሰው ጉዳት ያወጡት ከዚህ ውስጥ ለኮምፒውተር ስንት አወጡ ለመኪናው ስንት አወጡ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አጠቃላይ ግምቱ አስር ሺ አምስት መቶ እስከ አስራአንድ ሺ ብር የተባለው ለመስታወት ብቻ ከአንድ ሺ ሁለት መቶ ብር በላይ አውጥቻለሁ ቀሪው እንግዲህ ከምፒውተር ከነቦርሳው ግምቱ ያን ያህል ይስተካከላል

⇒ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ

⇒ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እሺ ጨርሰናል እናመሰግናለን የችሎት ውሎ በዚሁ ተጠናቋል

## ትእዛዝ

1ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች እስካሁን የተሰሙት ተገልብጦ ከመዝገቡጋር እንዲያያዝ ትእዛዝ ተሰጥቷል 2ኛ ትእዛዝ የፌደራል ፖሊስ ጠበቃ አቶ ተማም አባ ቡልጉ መጥሪያ አድርሷቸው ዛሬ ምላሹን እንዲያደርሰን ታዞ ነበር ምላሹም አልቀረበም ጠበቃውም አልቀረቡም ስለዚህ የፌደራል ፖሊስ ለምን ለጠበቃው ትእዛዙን እንዳላደረሱ እና ለሚቀጥለው ቀጣይ ቀነ ቀጠሮ አስቀድመው አድርሰው ከዛሬው ምክንያት ጋር ለችሎቱ እንዲያደርሱ ትእዛዝ ተሰጥቷል ይሄንን አጣርቶ ተገቢውን ከነምክንያቱ ተቀብሎ እንድውም የጠበቃውን መቅረብ ለመጠበቅ ለየካቲት 19 ቀን 2005 ሦስት ሰዓት ተኩል ቀጠሮ ተይዟል ድጋሚ ትእዛዝ ይሄኛውን ለፖሊሱ ትእዛዝ እንዲያየርስ ለፌደራል ፖሊስ ድጋሚ ትእዛዝ እንዲፃፍ ታዟል ሌላው 3ኛ ትእዛዝ ቀሪ የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት መጋቢት 24 እስከ 27 ቀጠሮ ተይዟል መጋቢት 24 3፡30 በተለመደው ይጀመራል ማለት ነው ሌላውን በዚሁ ጨርሰናል አጀንዳ ከዚህ ላይ ወደፊትም ወደኋላም ማድረግ አንችልም ያለውን አይተን ነው ያረግነው።



http://ethcriminalawnetwork.com/

4 ወ.ችሎት

የወ.መ ቁ.124754

መጋቢት 24/2005 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብስራት ተልዕቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሣሽ ፡- ዐቃቤ ሕግ አቶ ብርሃኑ ወንድማገኝ እና አቶ ቴዎድሮስ ባህሩ ቀርበናል

ተከሣሾች፡- እነ አቡበከር አህመድ 29 ተከሣሾች ማን ናቸው ያልመጡት ስንተኛ ተከሣሽ ናቸው በሕመም ምክንያት አልቀረቡም ሌሎቹ ቀርበዋል የተከሣሽ ጠበቆች

ስለ 28ኛ ተከሣሽ አህመድ ጀማል ቀርቤአለሁ 28ኛ ተከሣሽ ውጪ ላሉት ተከሣሾች አቶ ባህሩ መካንጋ አቶ ምላልኝ መለሰ አቶ መሐመድ አብደላ ቀርበናል

- መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ቀሪ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ነው ዐቃቤ ሕግ አንድ ተከሣሽ አልቀረቡም
- ዛሬ የምናሰማው የምስክርነት ጭብጥ በቀጥታ ከተከሣሹ ጋር ያልተገናኘ ስለሆነ ባለመቅረባቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- ምስክር ጥሩ
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ያው የዐቃቤ ሕግ ቀሪ ምስክሮች ቀርበው እንደሚከተለው ቃላቸውን ሰጥተዋል በፍ/ቤቱ ተራ ቁጥር 53ኛ ነው በዐቃቤ ሕግ ተራ ቁጥር ስንት ናቸው ?
- 97ኛ የተከበረው ፍ/ቤት



120 2280

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር እንኳን ደህና መጡ አሁን ለደህንነትዎ ሲባል የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ነው የሚነግሩን የአባት ስም የአያት ስም አለመናገር ይችላሉ ማን ነው የመጀመሪያ ስምዎ ?
- መሐመድ
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- ለምስክርነት
- እነ ማን በተከሰሱበት ነው ?
- ሀጂ ኢብራሒም
- ሌላ ያውቋቸዋል ?
- አዎ
- ፀብ ወይም ዝምድና አላችሁ ?
- አውቃለሁ ዝምድና የለንም
- ፀብስ አላችሁ የላችሁም በድምፅ ይግለፁ ሊያሳዩን ይችላሉ ?
- እሺ
- ሊያሳዩን ይችላሉ ?
- እችላለሁ
- እስቲ ዞር ብለው ያሳዩን
- እሳቸው
- የትኛው ናቸው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እስቲ ስንተኛ ተከሣሽ ኖት ሀጂ ኢብራሒም ምስክሩ 26ኛ ተከሣሽን ከተከሣሾች መካከል ለይቶ አሳይቷል ምን አደረጉ ተብለው ነው የተከሰሱት ?
- እኔ ሐምሌ ወር ረመዳን ውስጥ ከእሳቸው 290 2 ሺህ ብር
- አይ ቆይ መጀመሪያ ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችሁ በፊት ምን አደረጉ ተብለው ነው ሰው መቱ ተብለው ነው ወይስ ሰረቁ ተብለው ነው ?
- እሱ አይደለም እኔ የምመሰክረው



721 2281

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ ?
- እስቲ አሁን የጀመሩትን ይቀጥሉ መቼ ነበር ከመቼ ጀምሮ ነው የሚያውቋቸው ሀጂ ኢብራሒምን ከመቼ ጀምሮ ነው የሚያውቋቸው ?
- በእዚሁ ጊዜ
- በእዚሁ ጊዜ ማለት ?
- ወደ 7 ዓመት ይሆናል
- ረጅም ጊዜ አሁን ከተከሰሱበት ጉዳይ ጋር መቼ በተፈፀመ ድርጊት ነው የሚመሰክሩት መቼ በተፈፀመ ድርጊት ነው የሚመሰክሩት ?
- እኔ እኮ ረመዳን ውስጥ ሐምሌ
- ስንት ዓ.ም ነው ?
- 2004 መጨረሻ ላይ ሐምሌ
- እስቲ ቆይ አንዴ ምስክር አሁን ጥያቄ ይጠየቃሉ እርሶ መልስ ይሰጣሉ ስለዚህ በእዚህም ሲጠየቁ በእዚያም ሲጠየቁ ፊትዎን ወደ እዚህ በማድረግ መልሱን ብቻ ይነግሩናል ማለት ነው ቀጥሉ
- ሐምሌ 2004 ላይ ብለዋል ቀኑን ያስታውሱታል የወሩ ስንተኛ ቀን እንደሆነ ?
- አላስታውስም
- የወሩ መግቢያ አጋማሽ መጨረሻ ?
- ወደ መጨረሻ አካባቢ
- አሁን በገለፁት ጊዜ ምን ተከሰተ ?
- የተከሰተ ሳይሆን እኔ 2ሺህ 292 ብር ከእሳቸው ወደ ድርጅት ለመፍጠር
- ስንት ብር ?
- 2ሺህ 92 መቶ ሺህ
- እስቲ ተረጋግተው ስንት ?
- 292 ሺህ ብር
- 292 ሺህ ብር ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ከእሳቸው ተቀብዬ ለፋይናንስ እና አስተዳደር ገቢ አደረኩ
- ለምን ድርጅት ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ማህበር
- ከየት የመጣ ገንዘብ ነው ይሄ ገንዘብ ?
- እኔ ከእሳቸው ነው ያቀበልኩ እንጂ /ግልፅ ያልሆነ/
- ከየት መጣ ሲባል ሰሙ ግን ?
- ወሬ ሰምቼአለሁ በሳውዲ የሚባል ወሬ ነው
- ከየት ?
- ከሱውዲ የሚባል ወሬ ሰምቼአለሁ
- ሱውዲ ማለት ሳውዲአረቢያ ለማለት ነው ?
- አዎ
- ከሳውዲአረቢያ በማን የተላከ ገንዘብ ነው ?
- እሱ አላውቅም እኔ
- ለድርጅቱ ለእዚህ ለድርጅቱ ፋይናንስ አስገብቼአለሁ ነው የሚሉት ?
- አዎ
- እርሶ የድርጅቱ ሠራተኞ ኖት እንዴ ?
- እኔ ሠራተኛ ነኝ
- እስቲ ድገሙልኝ ?
- ሠራተኛ /ግልፅ ያልሆነ/ ማህበር ሠራተኛ ነኝ
- ምንድን ነው ኃላፊነትዎ ?
- ዳዋ ዘርፍ
- ከገንዘብ ጋር ያገናኞታል እንዴ እሱ የስራ ዘርፍ ?
- አልሰማሁም
- ከገንዘብ ጋር ይገናኛል የእርሶ የሚሰሩበት ዘርፍ ?
- አይገናኝም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ታዲያ እንዴት በምን አግባብ ያንን የሚያክል ገንዘብ ሰጡት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ እሱ ፋይናንስ እና አስተዳደር ተልኪ ነው የወሰድኩት እሳቸው
- ሲሰጥዎ ለምን ዓላማ ነበር የሰጡት ?
- ለመፍጠሪያ ሙስሊም ረመዳን /ግልፅ ያልሆነ/ ስለሆነ ለመፍጠሪያ የሚሆን ነው ብሎ ነው የተቀበልኩ
- ረመዳን በፆም ወቅት ከእዚያ ለፆም መፍቻ ማለት ነው ?
- አዎ ፆም መፍቻ ማለት ነው
- የት ነው ይሄ ፆም ፍቺ ወይም እንትን ማፍጠሩ ስነ ስርዓት የሚካሄደው የነበረው ?
- የተለያዩ ቦታ ነው እሱ
- ማለት እስቲ ?
- አዲስ አበባ ውስጥም ክፍለ ሀገርም
- ክፍለ ሀገር እና አዲስ አበባ ውስጥ ?
- አዎ
- እስቲ የኃይማኖት ቦታዎች ነው ወይስ የግለሰብ ቦታ ?
- አዎ
- የት ማለት ነው ?
- መስኪድ ላይ ነው የሚሰራው
- መስኪድ ?
- ደሀ ሕዝብ ደሀ ቤተሰብ ይሰጣል በ 2 ዓይነት ነው አንዱ በቤት ለደሀ ሕዝብ ሰው ይሰጥ እና አንዱ በመስኪድ /ግልፅ ያልሆነ/ አንድ ላይ ይበላል/ግልፅ ያልሆነ/ በኋላ ከሰላት በኋላ
- በምን ነበር የሰጡት ገንዘቡን ?
- ለማን
- እርሶ ሀጂ ኢብራሒም ቱፋ በምን አድርገው ነው ገንዘቡን የሰጡት ?
- በእጅ ነው የወሰድኩ ካሽ
- ካሽ ነው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- በምን ውስጥ ሆኖ ነበር የተሰጡት ?
- በፌስታል ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ዓይነት ፌስታል ነው ?
- ቢጫ ፌስታል
- ከእዚያ በፊት ሰጥቶዎት ያውቃሉ እንዴ ?
- አይ አላውቅም
- አያውቁም ?
- አዎ
- ከእዚያ በፊት  በነበረው ረመዳኖች ሰቶዎት አያውቁም ?
- አዎ
- ይሄ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው የሰጦት ?
- አዎ
- ሲሰጦት እርሶ ደረሰኝ ወይ  የድርጅቱን ሰነድ ሰጥዋቸዋል ?
- ነጭ ወረቀት ላይ ፈርሜአለሁ
- ነጭ ወረቀት ላይ ?
- አዎ
- ምን የሚል ፁሑፍ ነበረው ነጭ ወረቀት ላይ ?
- አረብኛ ነው
- በአረብኛ ነው ?
- አዎ
- አላነበቡትም ?
- አውቃለሁ እኔ አረብኛ
- ምን ይላል ትርጉን ሊነግሩን ይችላሉ ?
- ያው ገንዘብ ነዋ እኔ የ 292 ሺህ መቀበሉን /ግልፅ ያልሆነ/



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ በኋላ ገንዘብ ጨምረውለታል እንዴ ?
- እኔ አላውቅም እኔ እሱን
- እርሶ ለሚያውቁት ሰው ገንዘብ ሰጥተዋል እሳቸው ?
- አላወኩም
- የሚያውቁት ነገር የለም ?
- አዎ
- ሌላ ጥያቄ ካለ ባልደረባዬ
- አቶ መሐመድ ሀጂ እዚያ አሁን ያሉት ቦታ ምንድን ነው የእሳቸው ኃላፊነት ?
- አልሰማሁም
- ኃላፊነታቸው ምንድን ነው ሀጂ በእዚህ ዳዋ እና /ግልፅ ያልሆነ/ የሚባልበት ቅድም ያሉት ድርጅት ውስጥ የሀጂ እኚህ አሁን የመሰከሩባቸው ኢብራሂም ቱፋ ምንድን ነው ኃላፊነታቸው?
- አልገባኝም
- ኃላፊነታቸው ምንድን ነው ለእርሶ 292 ሺህ ብር የሰጡት ሀጂ ኢብራሒም ቱፋ የእሳቸው ኃላፊነት ምንድን ነው ?
- ኃላፊነቱ እሳቸው ያው ስራ አስኪያጅ ናቸው የድርጅታቸው
- የማን ማን የሚባል ነው ድርጅቱ ?
- አሮሚያ ጥሪ ማህበር
- እርሶ የሚሰሩበትስ ቦታ የት ነው የሚገኘው ?
- መካኒሳ አካባቢ ነው
- ማን ነው ስሙ ማን ነው የድርጅትዎ ማለቴ ነው ?
- አሮሚያ ጥሪ ማህበር
- እርሶ የሚሰሩበት አቶ መሐመድ እርሶ የሚሰሩበት ድርጅት ?
- እኔ የእስላማዊ /ግልፅ ያልሆነ/ ማህበር
- እዚህ አሁን ያሉበት ድርጅት ውስጥ አንዳንዴ የሚመጡ እንግዶች አሉ ወይም ለስብሰባ ለተለያየ ነገር የሚመጡ አሉ እንዴ ?



2286

126

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ አንድ ጊዜ አይቼአለሁ
- እነ ማንን አዩ ?
- አላወኩም ስሙን አናውቅም
- ማን እስቲ የሚያውቋትን ማንን አዩ ከእዚያ ውስጥ ?
- ያው ፋሚሊ ነው እሳቸውም /ግልፅ ያልሆነ/
- ችግር የለውም ቢገልፁ ?
- አልችልም እሱን
- እሺ እነኚያ ሰዎች ለምን እንደመጡ ያውቃሉ እነኚያ ሰዎች አሁን ቅድም እንደገለፁት ምን ያህል ይሆናሉ ?
- ከ 10 በላይ ነው
- ከ 10 በላይ ናቸው ?
- አዎ ከ 10 በላይ ይሆናሉ
- እነኚህ ሰዎች ከ 10 በላይ መሆናቸውን እንዴት አይተዋቸዋል ወይስ ?
- በጫማ ምናምን ነው
- በጫማ ነው ያወቁት ?
- አዎ
- ጫማቸውን የት አዩት ?
- ውጪ ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ውጪ ተቀምጧል ?
- አዎ
- ምን ሊያደርጉ ገቡ ምን ሰሙ ስለእነሱ ለምን እንደመጡ ምን ሊያደርጉ እንደመጡ ?
- እሱ ምንም የሰማሁት ነገር የለም
- እዚያ ከጓደኞችዎ እንደዚህ የሰሙት ነገር የለም ?
- የለም
- እና ከ 10 በላይ ሆነው ለምን እንደመጡስ ምን ቀን ነው የመጡት ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀኑን /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ውስጥ ገቡ ማለት ሲሰበሰቡ የት ቦታ ተሰበሰቡ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ አድናቆት ማህበር ቢሮ ውስጥ
- ቢሮ ውስጥ ነው ?
- አዎ
- ስለምን ዓላማ እንደተሰበሰቡ ያውቁ ነበር ?
- ምስክር ድምፅዎን መስማት አልቻልንም እኮ ስለዚህ ከፍ አድርጉ
- ስለምን ዓላማ እንደተሰበሰቡ በመረጃ ደረጃ እርሶ የሚያውቁት የሰሙት ካለ ቢነግሩን ?
- እሱ የለም ምንም የለም
- ስለምን እንደተሰበሰቡ አያውቁም ?
- አዎ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ያበቃ በመሆኑ የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- አቶ መሐመድ ቅድም እንግዶች ወደ እስላማዊ ዳዋ እና እውቀት ማህበር ይመጣሉ ብለዋል ይሄ እርሶ እዚያ ሠራተኛ ስለሆኑ በተደጋጋሚ ሰዎች ሲገቡ አላዩም እንዴ ?
- እኔ አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያየሁት
- ስንት ዓመት ሰርተዋል እስላማዊ እውቀት እና ዳዋ ?
- እኔ ወደ 5 ዓመት ይሆናል
- 5 ዓመት ?
- አዎ
- ምንድን ነው ድርጅቱ የእርዳታ ድርጅት ነው ?
- እምነት ላይ የሚሰራ ድርጅት ነው
- እኮ ባለጉዳዮች አይገቡም እንዴ እዚያ ቢሮ ?
- ይገባሉ
- ባለጉዳዮች ገብተው ይወጣሉ አይደል ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ይሄ እስላማዊ ድርጅት ስለሆነ የሚሰጠው እርዳታ የለም እንዴ ለባለጉዳዮች ?
- እርዳታ ሳይሆን ሰበካ ነው የሚሰራው መፅሐፍ እንሰጣለን ቁርአን
- እኮ መፅሐፍ ቁርአን ይሰጣል ?
- አዎ
- ይሄንን ባለፉት 5 ዓመታት ይሄንን ሲሰጥ ብዙ ጊዜ አይተዋል ?
- አዎ
- ስለ ተከሣሹ ማለት የሀጂ ኢብራሒም ድርጅት ምንድን ነው የሚሰራው ያውቃሉ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- ያው ስለ እምነት ላይ ነው የሚሰራው ሌላ ነገር የማውቀው ነገር የለም
- እምነት ላይ ሲሉ አሁን ለድሆች ገንዘብ አይሰጥም እንዴ የማስፈጠር እንደዚህ ነገር ቅድም ያነሱት ነገር አለ ማስፈጠር ማለት ይሄ ማስፈሰግ ወይም ፆም መፍቺያ ብለው ገንዘብ እንደሰጦት ነግረዋል ?
- ይሰራሉ
- የእነሱ ድርጅት ይሄ ስራ እንደዚህ ዓይነት ስራ ይሰራል አይደል ?
- ይሰራል ይሄ በየዓመቱ የሚሰራ ስራ ነው
- ቅድም ያሉት 292 ሺህ ብር መሆኑን ምን ቆጥረው ነው ቆጥረውት ነበር እንዴ እርሶ ?
- አዎ
- ቆጥረው ነው ?
- አዎ
- ምስክር ቅድም ሲመሰክሩ ገንዘቡን ለረመዳን ወይም የፆም ማፍጠሪያነው ፆም መፍቺያ ነው የሰጡኝ ብለሀል በየዓመቱ ነው ፆም መፍቺያ የሚደረገው ?
- አዎ በየዓመቱ ነው
- ሌሎች ግለሰቦችም ለፆም መፍቺያ የሚሆን ገንዘብ ይሰጣሉ አይደል ለደሀዎች የሚሆን ?
- አዎ ይሄ የተለመደ ነው በእስልምና



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፆም ማስፈጠር ወይም ፆም ማስፈታት በሃይማኖቱ የተወደደ ተግባር ነው አይደል ?
- አዎ እኔም /ግልፅ ያልሆነ/ እዚያ ላይ ያው በፍቃድ ስላለ በእቅድ እና ሪፖርት እናደርጋለን
- እርሶ 7 ዓመት ሰራሁበት ያሉት ድርጅት ይሄንን ስራ ለመስራት ፍቃድ አለው አይደል ?
- ፍቃድ  አለው
- እርሶ በእዚህ ጉዳይ ተከሰዋል እንዴ ?
- አልተከሰስኩም
- በፖሊስ የተጠየቁበት ነገር አለ ?
- ቃል ሰጥቼአለሁ
- የምስክርነት ቃል ሳይሆን በፖሊስ ተከሰው ያውቃሉ ወይ ?
- ቆይ ምንድን ነው ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ እንቃወማለን ምስክሩ በእዚህ ጉዳይ ላይ ስለ ክስም ሆነ ስለተከሣሽነት በዋና ጥያቄም አላነሳንም ከጉዳዩ ጋር የማይያያዝ ነው በእዚህ ጉዳይ ላይ ቃል ሰተዋል ተከሰዋል የሚለው ነገር ምስክሩን ሀራስ የሚያደርግ ነው ስለሆነም ይሄን  ጥያቄ ፍ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርገው ይገባል
- ምላሽ ስጡበት ?
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ፍ/ቤቱ መጀመሪያ ላይ ፀብ አለ ወይ ዝምድና አለ ወይ የሚለውን ጥያቄ የሚያነሳበት ዋናው ምክንያት ስነ ስርዓት ሕጉ ላይ የተፃፈ ነገር ስለሆነ ሳይሆን የምስክሩን ገለልተኛነት ለማጣራት ነው የምስክሩ ገለልተኛነት በእነዚህ ጥያቄዎች ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሁኔታዎች ሊጠራ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል እና አሁን እሳቸው በእዚህ ጉዳይ በፖሊስ ተከሰው ታስረው የነበረ ስለመሆኑ ወይም ተጠይቀው የነበረ ስለመሆኑ አለመሆኑን እንዲገልፁልን ነው ተከሰውበት የነበረ ጉዳይ ላይ ከሆነ ምስክርነት እየሰጡ ያለው ፍ/ቤቱ ይሄንኑ ተረድቶ ወደ ፊት ምርምር አሁን ሲያደርግ የሚመዝንበት ይሆናል በእዚህ ጉዳይ በፖሊስ ተከሰውም ተጠይቀውም የማያውቁ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቱ  ይሄንን ግምት ውስጥ ወስዶ ወደ ፊት በምዝናው ላይ የሚያየው ነገር ይሆናል እና ከእዚህ አነፃር ነው እሳቸው በእዚህ ጉዳይ በፖሊስ ተከሰው ታስረው የሚያውቁ መሆን አለመሆኑን እንዲመሰክሩ ነው

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት



290

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ስናየው ነበር የግራ ቀኞችሁን አይተናል ለነገሩ ቀደም ብሎ ነበር እኛ ማስቆም የነበረብን ምክንያቱም ተመልሷል አሁን ስንነጋገር ተከሰህ ታውቃለህ ወይ ተከሰሽ አላውቅም በፖሊስ ቃልህን ሰጥተህል ሰጥቼአለሁ የሚል ነገር ተናግሯል ስለዚህ ከእዚህ በኋላ ሌላ በእዚህ ላይ ሌላ ነገር መነጋገሩ ብዙም ጊዜ ስለሚጨርስ አሁን ወደ ሌላ ጥያቄ ይሂዱ
- ተቀብለን /ግልፅ ያልሆነ/ የሰጠው መልስ የሚያሻማ ትርጉም ያለው ስለሆነ ምናልባት ግልፅ እንዲሆን ለችሎቱ የምስክርነት ቃል ስለሆነ በእኛ መዝገብ ላይ የተያዘው ይሄ ደግሞ አንድ ሰው በ 27ም በ30 መሠረት ቃል ይሰጣል እና ይሄንኑ ፍ/ቤቱ ግልፅ/ግልፅ ያልሆነ/
- በምስክርነት ነው በምንድን ነው ቃልህን የሰጠኸው ?
- አዎ
- እኛም በእዚያ ነው የተረዳነው ቀጥሉ
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- ይኖረናል የተከበረው ፍ/ቤት አቶ መሐመድ ቅድም እኛ ስንጠይቅህ ለእዚህ ተግባር ከእዚህ በፊት በነበሩ ረመዳኖች ሼህ ሀጂ ኢብራሒም ቱፋ ገንዘብ ሰጥተው አያውቁም ያንን ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሰጡህ ነው የነገርከን በተከሣሾች ጠበቃ ደግሞ ስትጠየቅ በተደጋጋሚ የሚደረግ ነው ሁሉም ሰው ገንዘብ ይሰጣል የሚል ነገር አንስተህል እና ይሄ ገንዘብ ከእዚህ በፊት እንደዚሁ ከግለሰብ ነው እንዴ የሚሰበሰበው ለእንደዚህ ለሰደቃ ወይ ለማፍጠሪያ የሚሰጥ ገንዘብ ?
- ከበጎ አድራጎትም ይሆናል ከግለሰብም ይሆናል ሀብታም ከሰጠ እንሰጣለን
- እኮ የሚመጣው ወደ ድርጅቱ
- ከየት እንደመጣ እኔ እሱን የማውቀው ነገር የለም እኔ ሠራተኛ ነኝ ተራ ሠራተኛ ነኝ
- እርሶ ገንዘብ መቀበል ኃላፊነት የለኝም ብለዋል አይደል ?
- አዎ
- ስለዚህ እንዴት ከእዚህ ግለሰቦች ወይም ደግሞ ሌሎች ድርጅቶች ገንዘብ እንደሚሰጡ በምን ሊያውቁ ቻሉ እርሶ ?
- አልገባኝም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ኃላፊነት የሎትም አይደል ?
- አዎ
- ቅድም ሲጠይቁን የእርሶ ኃላፊነት የዳዋ እንትን እንደሆነ ነው የነገሩን ነገር ግን ሲጠየቁ በየዓመቱ እንደዚህ ከግለሰቦች ገንዘብ ይሰበሰባል በማለት መልሰዋል እና ስለዚህ ነገር እንዴት ሊያውቁ ቻሉ እርሶ ?
- ያው እዚያ ሠራተኛ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ የስራ ፕሮግራም ስላለ አያለሁ እንደሚሰራ
- ከእዚህ በፊት ሀጂ ኢብራሒም ቱፋ ሰጥተው ያውቃሉ ገንዘብ ?
- አያውቁም
- አያውቁም ?
- አዎ
- እሺ ይሄ ገንዘብ በ 292 ሺው ለድሆች ማፍጠሪያ እንደዚሁም ለድሆች የሚሰጥ ነው ብለዋል ይሄ ነገር ለምን ዓላማ እንደዋለ ለማን እንደተሰጠ እያንዳንዱን ገንዘብ የደረሰበትን ቦታ እና የዋለበትን ለምን ጥቅም እንደዋለ ታውቃለህ እንዴ አንተ ?
- እሱማ ፋይናንስ እና ፋይናንስ ክፍል ነው ሪፖርት ይኖራል
- አንተ የምታውቀው ነገር የለም ?
- የለም
- ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ
- ገንዘቡ 292 ሺህ ነው የሰጠኝ ነው ያሉት አይደል ሌሎች ግለሰቦችም ገንዘብ ይሰጣሉ ለማፍጠሪያ ብለዋል እና ምናልባት ሌሎች ግለሰቦች የሚሰጡትን ገንዘብ መጠኑን ያውቁታል ካወቁ ከእዚህ ጋር አነፃፅረው ይመልሱልን ይሄንን ያህል ገንዘብ ነው ከእዚህ ያነሰ ነው የሚሰጡት እስቲ ካወቁ ሌሎች ግለሰቦችን የሰጡትን ያዩ ካለ ?
- አላውቅም እሱን
- መጠኑን ነው የማያውቁት ወይስ መስጠታቸውን ?
- መስጠታቸውን መጠኑን አላውቅም

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ሌሎች ግለሰቦችም ለምም መፍቻያ ይሰጣሉ ብለው ነበረ እና ምናልባት መጠኑን አይተዋል ምን ያህል ብር እንደሆነ ?
- አላየሁትም እሱን
- አላዩትም ?
- አዎ
- የተከማቸውን ብቻ ነው ያዩት
- ቅድም ገንዘቡ ሲሰጠን ለማፍጠሪያ ነው የሚል ነበር አሁን ዐቃቤ ሕግም ሲጠይቅ ደግሞ ገንዘቡ ለምን እንደዋለ አላውቅም ነው ያልከው ያን ቀን ይሄ ነገር ማፍጠሪው በምን ተደረገ ?
- እኔ እኮ ገንዘቡ ተረክቤዋለሁ ለፋይናንስ ክፍል
- አንተ ነህ ያስረከብከው ?
- እኔ አይደለሁም የሰጠሁ እኔ ገንዘቡን ተቀብዬ ለፋይናንስ ክፍል ተረከብኩ
- እኮ ገንዘቡን ከፋይናንስ ክፍል ?
- ሄጀ ወደ ፋይናንስ ክፍል ነው
- እኮ ቆይ አንተ ለምን ሰጠን ?
- እኔ አልሰጠሁም እኔ
- ለማን ነው የሰጠህ ገንዘቡን ተቀበለህ ?
- ፋይናንስ እና አስተዳደር
- ለእሱ ሰጠህ ?
- አዎ
- እኮ ያ ገንዘብ ቅድም ለማፍጠሪያ ነው ስላልከን ከእዚህ ገንዘብ ለማፍጠሪያ የዋለ እና ያልዋለ ለመሆኑ ያየኸው ነገር አለ ወይ ስትባል ቅድም አይ እኔ ይሄንን አላውቅም አልክ ቀደም ብሎ ግን ለማፍጠሪያ ውሏል ዓይነት ነገር ነው ስትነግረን የነበረው ?
- ገንዘቡ የተሰጠ ለማፍጠሪያ ነው ገንዘቡን ተቀብዬ አስተዳደር እና ፋይናንስ ሰጥቼአለሁ እሱ ስራ ላይ ያደርጋል /ግልፅ ያልሆነ/
- ጨርሰሀል እናመሰግናለን ሌላ ምስክር
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በ ፍ/ቤቱ 54ኛ ተራ ቁጥር በዐቃቤ ሕግ ክስ ደግሞ 99ኛ ተራ ቁጥር ላይ የቀረቡ ምስክር እንኳን ደህና መጡ ለደህንነትዎ ሲባል የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ይናገራሉ የአባት ስም ሌሎቹን አይናገሩም ስለዚህ የመጀመሪያ ስምዎ ማን ነው ?
- አብዱርቃድር
- ስማቸውን ተናግረዋል ለምንድን ነው የመጡት እዚህ ?
- ለምስክርነት
- ማን በተከሰሰበት ነው ?
- እነ ሼር ጣሂር
- ሼህ ጣሂር ሼህ ጣሂር ማን ነው የሚባሉ ?
- ስማቸውን /ግልፅ ያልሆነ/ እንትን አላውቅም በእነ አቡበከር በተከሰሱበት መዝገብ /ግልፅ ያልሆነ/
- አሺ በእነሱ መዝገብ ላይ ነው የመጡት በማን ላይ ሊያስረዱ ነው የመጡት ?
- እኔ ስለድርጅታችን ለማስረዳት ነው የመጣሁት በድርጅቱ በምሰራበት
- በማን ድርጅት ?
- እስላማዊ ዳዋ እና እውቀት ማህበር
- ስለእሱ ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ከሱ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- አሁን አቶ አብዱርቃድር አሁን እሰራበታለሁ ያሉ ድርጅቶች አሉ 2 ድርጅቶች ጠቅሰዋል ከእነዚያ ድርጅት ጋር በተያያዘ ማን ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- በመጀመሪያ ድርጅቱ 2ቱ ድርጅት ያለው ግንኙነት ለማስረዳት እሞክራለሁ እስላማዊ ዳዋ እና እውቀት ማህበር ድርጅት ከተመሰረተ የቆየ ድርጅት ነው የልማት እና
- አናቋርጠዎት እኛ [illegible] አቶ አብዱርቃድር አሁን እኛ ስለድርጅቱ አመሰራረት አካሄድ ያለው እንደነት ልዩነት ዝርዝር ነገር ሳይሆን የእርሶን አጭር የምስክርነት ቃል ነው የምንፈልገው አሁን ከድርጅቱ ጋር በተያያዘ በየትኛው ጉዳይ ለመሰክሩ ነው የመጡት
- እሱ ወይም በሌላ አገላለፅ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ልመጣ እኮ ነው
- ቆይ እስቲ ይሄ ድርጅት ምን አደረገ ተብሎ ነው የተከሰሰው ምን አድርጎ ነው የተከሰሰው ?
- ስብሰባ ተካሂዶበታል
- ስብሰባ ተካሄደ ተብሎ ነው ?
- አዎ
- ቀጥሉ
- እና ድርጅቱ 2ቱ ድርጅት
- ምን ዓይነት ስብሰባ ነው ?
- በመጀመሪያ ልምጣ ይሄንን ልምጣ ወደ እዚያ
- እስቲ ምስክር ይኸውሎት አንድ ነገር አሁን ዐቃቤ ሕግ እየሆነ ስለሆነ እየጠየቀ ያለው የሚመልሱት ዐቃቤ ሕግ የሚጠይቆትን ነው እኛ ግልፅ ካልሆነ ኋላ እንጠይቆታለን አሁን ዐቃቤ ሕግ የሚጠይቀው ጥያቄ አለ እሱን ይጠይቃሉ እንደገና እዚያም የሚጠየቅ አለ በኋላ ወደ ፊትዎን ወደ እዚህ አድርገው የሚጠየቁትን ብቻ ይመልሳሉ ግልፅ ያልሆነውን ነገር እኛ እንጠይቃለን ?
- እሺ አቶ አብዱርቃድር ከስብሰባ ጋር በተያያዘ ነው የተከሰሰው ብለዋል የምን ስብሰባ ነው የሚካሄደው በድርጅታችሁ ?
- በመጀመሪያ እኔ እዚያ ያየሁት አሁን የተጠቀሱት ሰዎች በከፊል አላውቃቸውም ሁሉንም እዚያ አላገኘዋቸውም በከፊል መጥተው
- ማን ማን ?
- ግቢ ውስጥ አይቼአቸዋለሁ
- ማን ማን ናቸው ?
- በከፊል ካዩዋቸው ማን ማን ናቸው ?
- ሼህ ባሂር /ግልፅ ያልሆነ/ የማስታውሳቸው ካሚል እና ሌሎች /ግልፅ ያልሆነ/
- በመልክስ ያውቋቸዋል በስም የማያስታውሷቸው ወይ በመልክ ?
- በመልክ አውቃቸዋለሁ
- ሊያሳዩን ይችላሉ እነዚህን አሁን የጠሯቸው እና በመልክ የሚያውቋቸውን ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- ያሳዩና ይነሱ ተነሱ ሼህ ጣሂር የትኛው ናቸው ስንተኛ ተከሣሽ ናቸው /ግልፅ ያልሆነ/ 21ኛ ተከሣሽን እሳቸው ስንት ናቸው 17 የትኛው እርሶ 17ኛ ተከሣሽ አንተስ 4ኛ ተከሣሽ ሌላ ደግሞ አህመድ ስንተኛ ተከሣሽ ነህ አህመድ ጀባል 2ኛ ተከሣሽ ሌላ ቀሪ በሉ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ፀብ ወይም ዝምድና አላችሁ ?
- የለንም
- የላችሁም ቀጥሉ
- አሁን በመልከ የመረጧቸው እንዲሁም ስማቸውን የጠቀሷቸው ተከሣሾች ለምን ያህል ጊዜ መጥተው ተሰብስበዋል በቢሮአችሁ ?
- አይ የስብሰባውን ጊዜ አላውቅም እንጂ በየጊዜው ይመጣሉ ሌሎችም ይመጣሉ
- በተደጋጋሚ ይመጡ ነበር ?
- አዎ የድርጅታችንም የዳዋ እውቀት ማህበር ስለሆነ ለሌላ ጉዳይ ይመጣሉ ከእዚያ በፊትም ይመጣሉ
- ከእዚያ በፊት ማለት ከመቼ ጀምሮ ነው እዚያ መምጣት የጀመሩት ?
- ከእዚያ በፊትም ለጉዳይ ይመጣሉ ቁርኑአን /ግልፅ ያልሆነ/
- ለምሳሌ 4ኛ ተከሣሽ አቶ አህመዲን ጀባል እና አቶ ካሚል ሽምሱ ለምን ያህል ጊዜ መጥተው ያውቃሉ ወይ ከመቼ ጀምሮ ነው ቢሮአችሁ መምጣት የጀመሩት ?
- ምናልባት ጊዜውን በደንብ እንትን አላውቅም  ግን ከድሮም ጀምሮ
- ቢሮአችሁ ይመጣሉ ?
- አዎ የዳዋ ስራ ስለሚሰሩ /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄኛውን ስብሰባ እንዴት ለይተው ሊያስታውሱ  ቻሉ ?
- አሁን እኔ ያልኩት እዚያ ግቢ ውስጥ ተገናኝቶ የመሄድ ሁኔታ ነው እንጂ ስብሰባ ቁጭ ብሎ በትክክል ስብሰባ ሲያካሂዱ አላየሁም ግን
- ተሳትፈው አያውቁም ስብሰባውን ?
- እኔ
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነው ተቃውሞ ?
- ሲጀመር ይኸው ምስክሩ ስብሰባ አላየሁም ስብሰባ አላልኩም እያሉ ነው እና ተሳትፈው አያውቁም የሚለው ጥያቄ ይሄ መሪ የሆነ ጥያቄ ስለሆነ መታለፍ አለበት ከእዚህ በኋላ የሚጠይቁት ጥያቄ ላይ ስብሰባ የሚለውን መናገር የለባቸውም የተከበረው ፍ/ቤት አላልኩም እያሉ ነው ምስክሩ
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ፍ/ቤቱም ምስክሩን ሲጠይቃቸው ከመጀመሪያ ጀምሮ የተከሰሱት ከስብሰባ ጋር በተያያዘ ነው በሚል ነው በተደጋጋሚ እየመጡ ይሰበሰባሉ ብለዋል ምናልባት ስብሰባውን በአካል እንደዚህ ተገኝቼ አላየሁም በእርግጥ ብለዋል ተሳትፈው አያውቁም የሚለው ጥያቄ ምናልባት ካላዩም አላየሁም የሚለውን ያጠናክራል እንጂ የተከሣሽን መብት የሚጎዳ አይደለም ስለሆነም ተቃውሞው ያለአግባብ ነው
- ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል ብይኑ በ 2 ከፍሎ ነው ያየው 1ኛው ስብሰባ የሚለው ነው 2ኛ መጨረሻ ስብሰባ ተሰብስበው ነበር ወይ የሚለውን ጥያቄ ነው የመጀመሪያው ጥያቄ መጀመሪያም ስብሰባ እንደነበረ ተናግረዋል ያንን ግልፅ ማድረግ ጥያቄው ተገቢ ነው በ2ኛው ግን ስብሰባ ተሳትፈሀ ነበር ወይ የሚለው ግን መሪ ጥያቄ በመሆኑ እሱን አስተካክላችሁ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ስብሰባው በተደጋጋሚ ጊዜ እንደተካሄደ ገልፀውልናል በምን ያህል ጊዜ ልዩነት ነበር ግን ሲካሄድ የነበረው ?
- እኔ ስለሬጉላል ስብሰባው አላውቅም ግን ብዙ ጊዜ የማገኛቸው ግቢ ውስጥ ነው እና በግሩፕ የሆነ ነገር ይነጋገራሉ ለመንግስት የምናቀርበው ጥያቄ አለ ብለው የመገናኘት እና የመሄድ ነው በአብዛኛው እኔ ያየሁት
- ለመንግስት ስለሚያቀርቡት ጥያቄ ምን ይሄንን ምን ሲነጋገሩ ነው የሰሙት ?
- አዎ በግሩፕ ሜዳ ላይ ቆመው ሲነጋገሩ ለመንግስት ጥያቄ እናቀርባለን ከመንግስት ጋር እንነጋገራለን ሲሉ አይቼአለሁ
- እስቲ ሊላው ወደ ድርጅታችሁ ልመለስ እና እስቲ ቅድም ጀምረውልን ነበር ስለድርጅቱ አመሰራረት ምናምን የእርሶ ኃላፊነት ምንድን ነው በድርጅት ውስጥ ?
- እኔ እስላማዊ ዳዋ እና እውቀት ማህበር ሒሳብ ሹም ነኝ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- የድርጅቱ የሒሳብ ሹም ከሆናችሁ እስቲ ስለ ድርጅቱ የገንዘብ ምንጭ ጋር በተያያዘ የሚያውቁት ነገር ካለ ይግለፁ ለፍ/ቤቱ ?
- ድርጅታችን ከበጎ አድራጎት ነው ገንዘብ የሚያገኘው ያንን ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ያሰራጫል ከእነዚህም ውስጥ የዳዋ ስራ የቁርአን ማከፋፈል የፍጣር ስራዎችን ያከናውናል
- የገንዘብ ምንጩ እንዴት ነው ከምን ጋር ከየት ነው የገንዘብ ምንጩን የሚያገኘው ?
- የገንዘብ ምንጭ ከበጎ አድራጎት ብዬአለሁ ከውጪም ከሀገር ውስጥም ከምናገኘው እንጠቀማለን
- ከግለሰቦች ትቀበላላችሁ እንዴ ከግለሰቦች ድርጅቱ ይቀበላል ?
- ከግለሰቦች የሚቀበልበት ሁኔታ አልፎ አልፎ ይከሰታል
- እሺ እርሶ የሚያውቁት ምናልባት ማን ነው በማን ትዕዛዝ ነው ገንዘብ ሄደው የሚቀበሉት እርሶ?
- እኛ የምንቀበለው ወይም ያ የሚያመጣው ግለሰብ ገንዘብ አለ ውሰዱ ለድርጅቱ ሲል እኛ ገንዘብ የምንቀበለው በመጀመሪያ በጎ አድራጊው ለእዚህ ለእዚህ ይዋልልኝ ብሎ ይገልፅልናል የሚልክበት ሁኔታ በባንክ ሊሆን ይችላል ማለት ነው
- ሌላስ ?
- ሌላ በግለሰብም በቅርብ የተከሰቱ እንትኖች አሉ
- እስቲ እሱን ይግለፁት ?
- ባለፈው ረመዳን ውስጥ ሐምሌ ወር መጨረሻ ላይ ነው ለይፍጣር የሚከፋፈል ገንዘብ አላችሁ ወይ ብለን ተቀብለናል
- ከማን ነው የተቀበላችሁት ?
- ከሼህ ሀጂ ኢብራሒም
- ከሼህ ሀጂ ኢብራሂም ስንት ብር ተቀበላችሁ ?
- 500 ሺህ
- 500 ሺህ ብር አንዴ ነው የተቀበላችሁት 500 ሺህ ብር ?
- አንዴ ነው
- አንድ ጊዜ ማን ነው ሄዶ የወሰደው ማን ነው የተቀበለው ?
- እኔ ነኝ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እርሶ ጥት ከእዚህ በፊት ሼህ ሀጂ ኢብራሂም ቱፋ ለድርጅታችሁ በተመሳሳይ ገንዘብ ይሰጡ ነበር ?
- አላውቅም እኔ አላውቅም
- እርሶ እስከሚያውቁ ድረስ ሰተው ያውቃሉ ?
- አላውቅም
- ምን ያህል ጊዜ ሰርተዋል በድርጅቱ ?
- ብዙ ሰርቼአለሁ ወደ 10 ዓመት
- ወደ 10 ዓመት ሰርተዋል በእዚህ 10 ዓመት ጊዜ ሀጂ ኢብራሒም ቱፋ ሰጥተው ያውቃሉ ?
- አላውቅም
- ይሄ ገንዘብ ከየት የመጣ ገንዘብ ነው ብለው ሰጧችሁ ?
- ለይፍጣር ምዕመናን የሚከፋፈል ወይም ሚፍጣር በፆም መፆሚያ የሚሆን
- አዎ ፆም መፍቻ ?
- እንዲከፋፈል ተብሎ ነው የተሰጠን
- ከየት ነው ምንጩ ከየት የመጣ ነው ተብሎ ነው የተሰጣችሁ ከየት ሀገር የተላከ ?
- ምንጩን በትክክል አላውቅም
- ከሰሙት ከየት ነው እርሶ ?
- ሪል በግምት መስጠት አይቻልም /ግልፅ ያልሆነ/
- ገምቱ እያልን ሳይሆን እኛም ያለነው
- ምስክር አሁን ሲጠየቁ ምንድን ነው የሰሙ ከሆነ ሰምቼአለሁ ያዩ ከሆነ አይቼአለሁ ካልሰሙ ካላዩ ደግሞ አላየሁም አልሰማሁም ማለት ይችላሉ
- ገብቶኛል ይሄ ነገር ሶርሱን በደንብ የተገለፀልኝ ነገር የለም እና ገንዘቡ እንዲከፋፈል ነው የተሰጠኝ
- አንዴ አዳምጡኝ ቅድም እንደገለፁልን በጎ አድራጎት ድርጅቶት ወይም ግለሰቦች ለእዚህ ለእዚህ ዓላማ ይሄንን ያህል ገንዘብ አለ ውሰዱ ብለው ወይ በባንክ ያስገባሉ ወይም በእጅ ይሰጡናል ብለዋል ይሄኛው ገንዘብ ሀጂ ኢብራሒም ቱፋ አምጥተው ሰጥተውናል ብለዋል ከግላቸው ነው ከሌላ ሰው የተላከ ገንዘብ ነው ስለእዚህ ነገር ምንድን ነው የሚያውቁት ነገር ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በትክክል አላወኩም በደብዳቤ ቢሆን ኖሮ ይታወቅ ነበር እና በትክክል ይሄ ነው ብሎ የገለፁልኝ እንትን የለም
- ገንዘቡ ለምን ዋለ ?
- ገንዘቡ ለፍጣር ነው ለሰዎች ቁርአን ለሚያስቀሩት ሰዎች
- የት አካባቢ ነው የተሰጣቸው ይሄ ገንዘብ እነዚህ ቁርንአን ለሚያስቀሩ ወይም ቅድም ለማፍጠር ተብሎ ነው የመጣው ብለዋል አይደል ለማፍጠሪያ ወይም ለፆም መፍቻ ተብሎ የመጣ ገንዘብ ነው ብለዋል ለእነዚህ ቁርአን ለሚያስቀሩት ሰዎች በገንዘብ በጥሬ ገንዘብ ነው የሰጣቸው ወይስ በአይነት ነው የተሰጠው እንዴት ነው ?
- በጥሬ ገንዘብ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን እሳቸው ገንዘቡ እንዴት እንደተሰጠ ሲገልፁ ለማፍጠር ዓላማ ነው
- የአሁኗ ከሆነች የሆነ መልሰዋታል
- አይደለም ገና አሁን የጠየቁትን ነው አሁን ገና ዐቃቤ ሕግ ይሄ ገንዘብ ቁርአን ለሚያስቀሩ ሰዎች በጥሬ ገንዘብ ነው የሰጠው ወይስ እንዴት ነው የተሰጠው ብለው ነው እየመለሱ ያሉት እየጠየቁ ያሉት ይህ ማለት ምስክሩ በቁርንአን ለሚያስቀሩ ሰዎች ገንዘቡ ተሰጥቷል ያሉ ዓይነት አድርገው ነው ያቀረቡት ምስክሩ ግን ይሄንን አላሉም ስለዚህ ምስክሩ ካላሉት ነገር ላይ ተነስተው ምስክሩ ያሉ አድርገው ማቅረባቸው ተገቢ ስላልሆነ በአጠቃላይ ጥያቄው እንዲሰረዝ እና ጥያቄአቸውን አስተካክለው እንዲጠይቁ ነው በእዚያ ላይ መሪነቱ ያው በተደጋጋሚ የተነሳ ነው ፍ/ቤቱ /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄአችን ያቀረብነው እኛ ምስክሩ ከሰጡት ምላሽ ተነስተን ምስክሩ ያሉት ይሄ ገንዘብ መጀመሪያ ዓላማው ለማፍጠሪያ ነው ተብሎ ነው ብለዋል ከእዚያ ቁርአን ለሚያስቀሩ ሰዎች ሰጠን ብለዋል ይሄንን በዝግጅት መልኩ ነው እንትኑ የተሰጠው ነገሮች የማፍጠሪያ ነገሮች ተዘጋጅተው ነው የሰጡት ወይስ በምን መንገድ ነው የሚለውን ለማብራራት ነው አንድም ያልተለየ መሪ ጥያቄ የሚባለው ምስክሩ የማያውቁትን እንትን ወይም አንድ ቀጥተኛ መልስ እንዲመልሱ ሊድ የሚያደርግ ጥያቄ ሲሆን ነው እኛ በምን አግባብ ነው የሚለው እንዲብራራ ነው የጠየቅነው እና የመራንበትም ጥያቄው ያለአግባብ መሆኑ በምን አግባብ እንደሆነ አልጠቀሱም ተቃውሞ ያለአግባብ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ብይን ሰጥተናል
- የተቃውሞ መነሻ የሆነው ጥያቄ ገንዘቡ ቁርአን ለሚያስቀሩ ሰዎች ዓላማ ተብሎ ከበጎ አድራጊው ድርጅቶች ከሌሎችም ይሰጠናል ብለው ምስክሩ መልሰዋል መጀመሪያው እና እዚያው ላይ ቆሞ ድርጅቱ ቁርአን ለሚያስቀሩ ሰዎች የተሰጠው በካሽ ነው ወይስ በጥሬ ነው የሚል ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ አቀረበ በጠበቃ በኩል የቀረበው ይሄ ጥያቄ ምስክሩ አልመለሱም ምስክሩ ያልመለሰው ነገር ላይ ቆሞ ነው ጥያቄው የተጠየቀው 2ኛ ላይ የቀረበው ጥያቄው መሪ ነው የሚል ነው ለእዚህ ምላሽ ከተሰጠ ጥያቄውን ምስክሩ መልሷል መሪም አይደለም የሚል ተፅፏል እኛ ጥያቄው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚውን መርምረነዋል ምስክሩ ድርጅቱ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች አንዳንዴም ከግለሰብም ለተለያየ ዓላማ ገንዘቡን እንደሚቀበል አንዱ ዓላማ ደግሞ በቁርአን ቁርአን ለሚያስቀሩ ሰዎች ገንዘቡን መስጠት አንዱ ዓላማ ነው ምስክሩ ከመለሰ እና አሁን ካለው ሁኔታ ጋር እሱን ነው እና ገንዘቡ ከድርጅቱ አልፎ ቁርአን ለሚያስቀሩ ሰዎች ስለመስጠት አለመስጠቱ ምስክሩ መመለሱን እኛ አልመዘገብንም ለእዚያ ነው ጥያቄውም አሁን በጠበቃ በኩል የተነሳው ጥያቄ ምስክሩ ያልመለሰ ነው የተባለው በእኛም ምስክሩ ያልመለሰ መሆኑን አግኝተነዋል ስለዚህ ጥያቄው ተስተካክሎ ይቅረብ ?
- እሺ አቶ አብዱር ቃድር ይሄንን ገንዘብ ለማን ነው የሰጣችሁት ?
- ቅድም መልሼአለሁ
- ተቃውሞአችን አሁን የፍ/ቤቱ ብይን አልተከበረም ባይ ነኝ እነሱ አስፈጠርን እያሉ ነው ምስክሩ ያመኛ አስፈጠርን እያለ ነው እና ገንዘብ ለማን ሰጠህ የሚለው ግን መሪ ነው የሚል እምነት ነው ያለው እና ዐቃቤ ሕግ ወደ ገንዘብ እና ገንዘብ አከፋፈልኩ ወደ የሚል ነው እየሄዱ ያሉት ይሄ መሪ ስለሆነ የፍ/ቤቱ ብይን ተከብሮ በእዚያ መሠረት ጥያቄ ይጠየቅ ነው
- እናስተካክላለን ጥያቄአችንን እሺ አቶ አብዱርቃድር ይሄ በእርዳታ አገኘን ለድርጅታችን ተሰጠ ያሉት ገንዘብ ለምን ዓላማ ነው የዋለው ?
- ለኢፍጣር ብዬአለሁ
- ስንት ጊዜ ተዘጋጀ ይሄ ዝግጅት ?
- በአካባቢያችን አይደለም ሰዎቹ ያሉት እና ስለዚህ በካሽ ነው የላክንላቸው
- በምንድን ነው የላክንላቸው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በገንዘብ ነው የላክንላቸው
- በገንዘብ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ የሚያስፈልገውን ነገር ገዝተው እንዲጠቀሙበት ማለት ነው እና ዓላማውን ተነግሯቸው በእዚያ ፐርፐዝ ነው አሉ /ግልፅ ያልሆነ/
- ለስንት ሰዎች እንደሰጣችሁ ታስታውሳላችሁ ያስታውሳሉ እርሶ ?
- ዝርዝሩን አልያዝኩም
- ዝርዝሩን አልያዙም ?
- አዎ
- እርሶ ይሄ ገንዘብ ለማፍጠሪያ ዓላማ እንዲውል በማለት በጥሬ ገንዘብ የላኩ ቢሆንም ነገር ግን ይሄ ገንዘብ ለማፍጠሪያ ይዋል ለሌለ ዓላማ ይዋል የሚያውቁት ነገር አለ ?
- ለሌላ ነገር አይውልም
- የእርሶ እምነት ነው ይሄ ወይስ በአይኖ የታዘቡት ነገር አለ ?
- የሁላችንም እምነት ነው ፣ኛ ከእዚህ ሩቅ ስለሆኑ ነው እንጂ እነሱ በዝርዝር የሚታወቁ ናቸው ስራቸውም ይታወቃል ዓላማውንም የሚያውቁ ናቸው ረመዳን ስለሆነ ከረመዳን ጋር የተገናኘ ነገር እንዲጠቀሙበት እምነቱ አለ
- ቅድም የገንዘቡ መጠን 500 ሺህ ብር ብለውናል ከእዚህ ሌላስ ሌላ የተሰጣችሁ ገንዘብ አለ እንዴ ?
- ሌላ ጓደኛዬ የተቀበለው 292 ሺህ ብር
- ጓደኛዎት ማለት ማን ነው ?
- መሐመድ ሁሴን
- ከማን ነው ይሄንን ገንዘብ የተቀበለው ?
- ኢንፎርም እንዳደረገኝ /ግልፅ ያልሆነ/
- ከማን ?
- አልነበርኩም በቦታው አልነበርኩም
- እስቲ ድምፅዎ ስላልተሰማ እሱ በነገሮት መሠረት ከማን ተቀበልኩ አሎት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከሼህ ሀጂ ማን ?
- ሼህ ሀጂ አብራሔም
- ከሼህ ሀጂ አብራሔም እርሶስ ለምን ዓላማ ነው የተቀበለው ለምን ዓላማ ነው የተቀበለው እሱስ ?
- ከእዚሁ ጋር የተያያዘ ነው
- ከእዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው ?
- ወቅቱም ተመሳሳይ ነው
- ሌላስ የሚያቁት ገንዘብ አለ ከእዚህ ሌላ ?
- ሌላ ስሙን አላውቅም ሰውዬውን ለእዚህ ፐርፐዝ ጋር የተገናኘ /ግልፅ ያልሆነ/
- 242 ሺህ ስሙን አያውቁትም ?
- አላውቅም
- ለድርጅታችሁ ነው አምጥቶ የሰጠው አይደል ?
- አዎ
- ሲቀበሉ ከየት ነው ብላችሁ አላጣራችሁም ?
- ከየት እንዳመጣው በትክክል እንትን አይልም ኢንፎርሜሽን እንዲቀበል /ግልፅ ያልሆነ/
- ግልፅ አይደለም መልሶት እስቲ ይድገሙልን ?
- ከእዚያ በፊት እንትኑ ለእዚህ ኢፍጣር የሚያመጣ ሰው ስላለ እንድቀበል ኢንፎርሜሽኑ አለኝ
- ከማን ነው የተነገሮት ይሄ መረጃ ?
- ይሄንን ከአለቃዬ ነው
- አለቃዎት ማን ናቸው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ሼህ መሐመድ ሁሴን የት ናቸው ያሉት እሳቸው ?
- እሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- የት ?
- አሁን አላውቅም የት እንዳሉ በፊት ወደ ሱውዲ /ግልፅ ያልሆነ/



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይስማም
- አሁን አሊቃዩ ያሏቸው ግለሰብ ሀገር ውስጥ እያሉ ነው ከመውጣታቸው በፊት መቼ ነው ይሄንን ትዕዛዝ የሰጡት ?
- ከወጡ በኋላ ነው
- ከወጡ በኋላ ከውጪ ሆነው ማለት ነው ?
- ለኢፍጣር ይሄንን ሁኔታዉን ገንዘብ እንድቀበል /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌሎቹንም ገንዘቦች ለምሳሌ 500 ሺህ ብሩን እንዲቀበሉ ማን ነው ያዘዙት ?
- እሱን ከእዚሁ ነው የተነገረኝ
- ማን ነው የነገሮት ?
- ሼህ ሀጂ ናቸው የነገሩኝ
- እናመሰግናለን
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- አቶ አብዱርቃድር እርሶ የሚሰሩት በእስላማዊ ዳና እና እውቀት ማህበር ውስጥ ነው አይደለም?
- አዎ
- እዚያ ላይ ኃላፊነትዎ ምንድን ነው ኃላፊነትዎ ምንድን ነው ሂሳብ ሹምነት ነው የሚሰሩት ?
- ሂሳብ ሹም ነው
- ከመቼ ጀምሮ ነው እርሶ በእዚያ ስራ ላይ ያሉት ?
- ከ 2004
- 2004 መቼ ጀምሮ ?
- 2004 የካቲት
- ከየካቲት ጀምሮ የድርጅቱ ዓላማ ምን እንደሆነ በትክክል ያውቃሉ እርሶ ?
- የድርጅቱ ዓላማ የእስልምናን መሠረቶች ማስተማር ማስረዳት ለምዕመናን ይሄንን ቁርአን በማካፈል መስኪዶች መስራት /ግልፅ ያልሆነ/ የመሳሰሉትን ነገር ከምዕመናን ጋር በማድረግ ይሄንን ያከናውናል ዳዋ ስራ ነው በአብኛው ማስተማር ስለእስልምና መሠረቶች ማስተማር ነው



http://ethcriminalawnetwork.com/

ይሄንን ፋሲሊቴት ለማድረግ መስኪዶችን /ግልፅ ያልሆነ/ ለሕብረተሰቡ ማስረከብ ቁርአን ማከፋፈል የመሳሰሉትን ስራዎች ነው የሚያከናውነው

- እዚህ ውስጥ የማስፈጠር ስራ ቅድም አሁን ማፍጠር
- የማስፈጠር /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄንንም ይሰራል መደበኛ ስራው ነው ?
- አዎ ይታወቃል
- ኡዲያ ማለት ምን ማለት ነው
- ኡዲያ ማለት በአረፋ ጊዜ እርድ ተደርጎ ሕብረተቡ አቅም ለሌላቸው ስጋ የመስጠት ወይም የማከፋፈል ሁኔታ
- እነዚህን ስራዎች በመደበኛነት ይሰራል ?
- አዎ
- እነዚህን ስራዎች ለመስራትም ፍቃድ አለው አይደለም ?
- አዎ
- ድርጅታችሁ ይሄንን ስራ ሲሰራ እንዴ ነው የሚሰራው ከሰዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት እንዴት ነው ግንኙነቱን የሚያደርገው አሁን የማስተማሩ እነዚህ አሁን /ግልፅ ያልሆነ/ ስራም ያሏቸው ጠቅላላ ቅድም የዘረዘሯቸው ስራዎችን አገልግሎቱ ከሚያገኙት ሰዎች ጋር እንዴት ነው ግንኙነት የሚያደርገው ?
- ግንኙነት የምናደርገው በተወካዮቻችን በፁሑፍ በቴሌፎን በግንባርም በቦታው በመገኘትም የምናደርግበት ሁኔታ አለ እና ሰዎቹ የሚታወቁ ናቸው አካባቢው የሚታወቅ ነው በሪፖርት የሚቀርብበበት ሁኔታ አለ የሚያከናውኑት ስራ ከእዚህም ኮሚኒኬሽን /ግልፅ ያልሆነ/ 2ቱም በ2 በኩል እንገናኛለን ማለት ነው
- አገልግሎቱን ተቀባዮች እናንተ ጋርም ይመጣሉ ?
- ይመጣሉም እኛም እንሄዳለን በተወካዮቻችን መንገድ እንገናኛለን ማለት ነው
- ስለዚህ ቅድም በስምም በአካልም የለዩዋቸው ተከሣሾች እናንተ ጋርም የመጡት በእዚሁ መንገድ ነው ማለት ነው ? አሁን ቅድም የለዩዋቸው ሰዎች አሉ አይደለም ከተከሣሾች ውስጥ እነሱም እናንተ ድርጅት ውስጥ የመጡት በእዚሁ አሁን ባሉት መንገድ ነው የመጡት ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእዚህ መልክም ይመጣሉ በአብዛኛው በእዚህ ግንኙነት ነው የሚመጡት
- በእዚህ ግንኙነት ነው የመጡት ?
- አዎ
- ቅድም ለመንግስት ጥያቄ እናቀርባለን ብለው ሲነጋገሩ ሰምቼአለሁ ብለዋል በምን ጉዳይ ላይ ነው ጥያቄ እናቀርባለን ብለው የተነጋገሩት ?
- ጉዳዩን በዝርዝር ሁሉንም ባለውቅም ዋናዎቹ እምነታችንን በሚመለከት የአወሊያ ት/ቤትን በሚመለከት የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ ይሄንን በእዚህ ዙሪያ ነው በአብዛኛው እንትን የሚያደርጉት
- እነዚህን ጥያቄዎቻችንን ለመንግስት እናቀርባለን ነው ያሉት አይደል ?
- አዎ ለመንግስት ነው እናቀርባለን ብለው ነው የሚሄዱት በእዚያ ሲሄዱ
- ይሄንን ሲነጋገሩ በግልፅ ነበር የሚነጋገሩት ?
- በግልፅ ነው አዎ በግሩፕ በግሩፕ ውጪ ላይ ሳገኛቸው ግቢያችን ውስጥ ማለት ነው በግልፅ ነው የሚናገሩት
- ድርጅታችሁ እንግዲህ እርሶ ሒሳብ ሹም ከሆኑ በትክክል ያውቁታል የገንዘብ ይሄ ለሚሰራቸው ስራዎች የሚያስፈልጉትን የገንዘብ ምንጭ የሚያገኘው ከየት ነው ?
- በበጎ አድራጎት ነው የሚያገኘው
- በጎ አድራጎት ከድርጅቶችም ከግለሰቦችም ያካትታል አይደል ?
- ከውጪ ድርጅቶችም በጎ አድራጎት በጎ ስራ እንዲሰራ ከሀገር ውስጥም እንቀበላለን
- ከግለሰቦችም ትቀበላላችሁ ?
- እንቀበላለን
- ዓላማችሁን ደግፎ የእናንተን ቅድም ያሉትን ማህበሩ የሚሰራቸውን ዓላማዎች ደግፎ እርዳታ ከሚያደርግ ከማናቸውም ሰው ላይ ገንዘብ ትቀበላላችሁ ?
- አዎ
- ለምትቀበሉት ገንዘብ ደረሰኝ ትሰጣላችሁ አይደል ?
- እንሰጣለን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተቀበላችሁበት ሰው የገንዘብ መጠንም ጊዜውም ወቅቱም ሒሳብ ሰነዳችሁ ላይ በትክክል ይታያል አይደለም ?
- አዎ
- ድርጅታችሁ በእዚህ በማህበራት ማደራጃ ሕግ መሠረት በየጊዜው ኦዲት ይደረጋል አይደል ?
- በየዓመቱ ኦዲት ይደረጋል
- ኦዲታችሁን ለመንግስትም ታሳውቃላችሁ አይደል ?
- በትክክል
- ሼህ ኢብራሒም የሰጧችሁን ገንዘብ በተመሳሳይ ሼህ ሀጂ ኢብራሒም የሰጧችሁን ገንዘብ በተመሳሳይ መንገድ ደረሰኝ ሰጣችዋችዋል አይደል ?
- አልሰጠንም
- አልሰጣችሁም ?
- እሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- ለምንድን ነው ያልሰጣችሁት ?
- እሳቸው አልነበሩም
- ስላልነበሩ ነው ?
- አዎ
- በሒሳባችሁ ላይ ግን ተመዝግቧል ገንዘቡ ?
- ይቅርታ
- ሒሳቡ ገንዘቡ በሒሳባችሁ ላይ ተመዝግቧል ?
- እሱን ሒሳብ ሹሙን /ግልፅ ያልሆነ/ አካውንታት አለ
- ሲሰጣችሁ ዓላማው ለማፍጠር ዓላማ ነው ተብሎ ነው የሰጣችሁ በግልፅ ተነግሯችዋል አይደል?
- አዎ
- እናንተም ይሄ ገንዘብ ለማፍጠር ዓላማ እንዲውል ነው ያደረጋችሁት ?
- ለእዚህ ፕሮፐዝ ነው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት



2367 151

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለእዚህ ለመዋሉ ሪፖርት ተሰጧችዋል አይደል ?
- አቤት
- ሪፖርት ተልኮላችዋል አይደለም ቅድም እርሶ እንዳሉት ?
- አዎ
- የገንዘብ አቅም ያለው ማናቸውም ሰው ለድሆች የማስፈጠር ስርዓት እንዲፈፀም ኃማኖታዊ ግዴታ አለበት አይደል ?
- አዎ
- ሼህ ሀጂ ጣሂርም የሰጧችሁ ሼህ ሀጂ ኢብራሒምም ገንዘቡን የሰጧችሁ በተመሳሳይ መንገድ ነው አይደለም በእዚህ ሀላፊነቸው የሰጧችሁ ነው አይደል ?
- ይሄንኑ ብለው ነው
- ጠበቃ ድግግሞሽ አለው ድግግሞሹን አስወግዱት
- እሺ አይ እሳቸው ሲሰጡ በእዚሁ ኃይማኖታዊ ኃላፊነት ነው ወይ የሚለውን ነው
- አሁን መጨረሻ የጠየቁት ቅድም 2/3 ጊዜ ተጠይቀው መልሰውበታል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
- ምስክር ቅድም ከሀጂ ለኢፍጣር አቶ መሐመድም ለእርሶም የተቀበሉትን ብር ለኢፍጣር ተቀብለው ለኢፍጣር ስራ አውለውታል ይሄ ገንዘብ ለኢፍጣር አልዋለም ብሎ የቀረበ ሪፖርት አለ እናንተ ጋር ገንዘቡ ለሌላ ዓላማ ውሏል ?
- የለም
- የለም ቅድም እርሶ ከየካቲት 2004 ጀምሮ ነው በድርጅቱ መስራት የጀመርኩት ብለዋል ቅድም ደግሞ ዐቃቤ ሕግ ሲጠይቆት ሀጂ ኢብራሒም ከእዚያ በፊት እንደዚህ ዓይነት ገንዘብ ይሰጣል ወይ ብሎ ሲጠይቆት አይሰጡም ነው ያሉት መጀመሪያ ይሄንን ያረጋግጡልኝ አይሰጡም ነው ያሉት ወይስ ምንድን ነው ያሉት ?
- የሰጠውን አያውቁም ነው ያሉት ጥያቄውን ከእዚህ ተነስታችሁ ቀጥሉ ?
- አላውቅም ነው ያልኩት



308

758

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ኦኪ እርሶ ባሉበት ጊዜ ነው ከእዚያ በፊት አልሰጡም የሚሉት  አይደል ማለት እርሶ በመጡበት ጊዜ የተቀበሉት እርሶ 500 ሺህ እና የእርሶ ጓደኛ 292 ሺህ ይሄንን ነው የሚያውቁት አይደለም?
- ከእዚያ በስራ በእዚህ ስራ አልሰራም እንጂ ውስጥ ስለነበርኩ አላየሁም ነው ያልኩት
- ውስጥ ማለት የት ድርጅት ውስጥ ?
- እዚያው ድርጅት ውስጥ በሌላ ስራ እሰራ ነበር እና
- እኮ ከእዚያ በፊት ሀጂ በተመሳሳይ ጉዳይ ይስጡ አይስጡ አያውቁም ?
- አላውቅም አዎ
- ቅድም ከተከሣሾቹ የተወሰኑትን ጠቅሰው ግቢ ውስጥ ቆመው ሲነጋገሩ እንደሰሙ ገልፀዋል ድርጅቱ የሚተዳደረው በቦርድ ነው አይደል ?
- ትክክል
- የበላይ ኃላፊ ቦርድ ነው ?
- አዎ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ ይሄንን ነገር ተከሣሾቹ ቅድም ያሉትን ለመንግስት የሚያቀርቡትን ጥያቄ እንዲነጋገሩ ቦርዱ ሲፈቅድ አይተዋል ?
- አላየሁም
- ጨረሳችሁ
- ድርጅቱ ቅድም እንዳሉት የእርዳታ ድርጅት ነው ባለጉዳይ ገብቶ ይወጣል ተከሣሾቹ ለስብሰባ ከመውጣታቸው አስቀድሞም ለሌላ ጉዳይ /ግልፅ ያልሆነ/
- አቶ አብዱርቃድር በተደጋጋሚ ኢፍጣር ሲሉ ነበር እና ኢፍጣር ማለት ምን ማለት ነው ?
- ኢፍጣር
- ኢፍጣር ማለት ምን ማለት ነው?
- ኢፍጣር ማለት በረመዳን ወቅት ፅዋሚዎች ማታ በሚበሉበት የሚመገቡት ምግብ ማለት ነው
- ይሄንን ማድረግ በኃይማኖቱ የተወደደ ተግባር ነው አይደል ?
- አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእርሶ ድርጅት እንዲሰራ በመንግስት ከተፈቀደለት ስራ ውስጥ አንዱ ፆመኛን ማስፈጠር ወይም ኢፍጣር ነው አይደል ?
- ትክክል
- እሱ ድግግሞሽ ነው ብዙ ጊዜ ተመልሷል ብዙ ጊዜም ተጠይቋል
- ቅድም አለቃዬ እንድቀበል ነግረውኝ ነበር ብለዋል ሼህ መሐመድ ያሏቸው አለቃዎት ሼህ ሀጂ ኢብራሒም ብር ይሰጡሀል ተቀበል ነው አይደል ያሎት ?
- አዎ
- እርሶ የተቀበሉት ገንዘብ ለሽብር ተግባር ውሏል እንዴ ?
- አይደለም
- አልዋለም አይደል ከእርሶ ገንዘብ የተቀበለ ወይም እንዲያፈጥር የተላከለት ሰው የፈፀመው ሕገ ወጥ ተግባር ይኑር አይኑር ያውቃሉ የፈፀመው ሕገ ወጥ ተግባር የለም አይደል /ግልፅ ያልሆነ/?
- እኔ እስከማውቀው ድረስ የለም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ
- እስቲ እኚህ ውጪ ያሉ ሰው ሼህ መሐመድ የተባሉ ሰው ከመቼ ጀምሮ ነው የወጡት ?
- ወደ ውጪ ሀምሌ መጀመሪያ ላይ ነው መሰለኝ
- ሐምሌ መጀመሪያ ስንት ዓ.ም ነው ?
- 2004
- ለምን እንደሄዱ ግን እርሶ ያውቃሉ ?
- ለስራ ያው እንትን ለማስተባበርም ለኡምራም ጭምር ነው ዚያራ ወይም እዚያ ኡምራ የማድረግም እንደገና ለድርጅቱም የእገዛ በጎ አድራጎቶችን የማስተባበል ስራ ያከናውናሉ
- እዚህ እያሉ የድርጅቱ ምን ነበሩ ነው ያሉት ?
- ስራ አስኪያጅ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስራ አስኪያጅ ነበሩ አሁን አሉ እዚህ ሀገር ውስጥ ?
- አሁን የሉም
- የሉም ከእዚያ በኋላ አልተመለሱም ?
- አልተመለሱም
- የሚያውቁት ነገር አለ ለምን እንዳልተመለሱ ?
- አላውቅም
- ብሩን ሲሰጡት ቅድም ከተከላካይ ጠበቆችም ሲጠየቅ ከሌላ ሰው ተቀብለህ ተቀበሉ ነው ያሉት እና ዓላማዎቹ 2ቱን ብቻ ነው ለ 2 ነገር ብቻ ነው እንዴ ተቀበሉ ያሉት ነው ዝም ብሎ ተቀበሉ የሚል ብቻ ነው የተሰጡት መልዕክት ?
- ለእዚሁ ዓላማ እንዲውል
- እኮ በዝርዝር ነግሮዎታል ?
- ተቀበሉን
- በዝርዝር ?
- ተቀበሉ ብለው አዎ
- እነዚህ ድርጅቶች በቦርድ ነው የሚተዳደሩ የሚል ነገር ነው ቅድም የነገሩን ቦርዱ ከየት ከየት እንደሚዋቀር ያውቃሉ ?
- ቦርዱ ከአባላት /ግልፅ ያልሆነ/ ጀነራል አሴምቢሊ ከጠቅላላ ጉባኤ
- ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ከምኑ ጉባኤ ነው ጠቅላላ ጉባኤ ብዙ ነው ?
- መስራቾች የእዚህ ማህበር እንትን አለ ጠቅላላ ጉባኤ
- አባላት ብቻ ነው የሚሆነው አባላት ብቻ ነው ይሄ ማለት ይሄ የተመሰረተው ድርጅት
- የማህበሩ አባላት ነው
- የማህበር አባላት ተመዝግቦ ነው ያለው ከእዚያ ከተመዘገበው ውስጥ ቦርዱ የሚዋቀረው ?
- አዎ
- ሌላ ቅልቅል የለም ከኃይማኖት ድርጅቶች ወይም ከእስልምና ምክር ቤት ወይም ከሌላ ?
- ከሌላ የለም



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከሊላ የለም ከመጅሊስም የለም ?
- የለም
- ከእስልምና ምክር ቤት ወይም መጅሊስ ከሚባለው የእዚያ ማህበር አባል የሆነ አለ ?
- እኔ አላውቅም
- አያውቁም ለመንግስት የኦዲት ሪፖርት እናቀርባለን ለማን ነው የምታቀርቡት ?
- በፊት ለፍትህ ሚኒስቴር ነበር
- ለፍትህ ሚኒስቴር
- አሁን ለፌዴራል ጉዳዮች ኃይማኖት እና እምነት ጉዳዮች ነው የምናቀርበው
- ያኔ የተመዘገበው በፍትህ ሚኒስቴር ነው ወይስ
- በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ
- በፍትህ ሚኒስቴር ስለተመዘገበ በስንት ጊዜ ነው የምታቀርቡት ሪፖርቱን ?
- ሪፖርት በየዓመቱ ነው የሚቀርበው
- እምነትን የሚያስፋፋ ድርጅት ነው ስለእምነታችን ጉዳይ ነው የእምነታችሁ ጉዳይ በምን መንገድ ነው እያካሄዳችሁት የነበረው እየተካሄደ የነበረው በእናንተ ውስጥ በእዚያ ድርጅት ውስጥ አሁን የሚባሉ የእስልምና ዓይነቶችን ያውቃሉ አሁን የሚባለው በውጪ ?
- የእስልምና
- ዓይነቶችን ማለት አሁን ተከፋፍለው ሀበሽ አለ የሚባል ነገር አለ ወሀብይ የሚባል አለ ወይም ሌላ እኛ በደንብ ስለማናውቃቸው እንዲነግሩን ?
- በመሰረቱ ዋና 2 እንትኖች
- ምን ?
- ሱኒ እና ሺአ የሚባሉ
- ሱኒ እና ሺአ ነው ያሉን ?
- ሺአ የሚባሉ ክፍሎች ጀነራል በተረፈ ሌሎች እንደእንትን የሚታወቁ በእኔ እና ባለኝ እውቀት የማውቃቸው የሉም
- ስለዚህ እናንተ
- ሁሉም በእዚህ ስር ነው እንትን የሚሉት



23/12

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እናንተ ለታስፋፉት ወይም በእዚህ ድርጅት ውስጥ አስተምሮቶች የሚሰፉት ምን ዓይነቶች ናቸው ከእነዚህ ውስጥ የትኞቹ ናቸው ?
- ድርጅቱ የተለየ እንትን የለውም ሱኒ ነው
- ሱኒ ነው ?
- አዎ እና የሱኒን መሠረታዊ እንትኖች የቁርአንን መሰረታዊ እንትኑ አስተምሮት ቁርአን ማስተማር በአግባቡ ያንን ዳዋ የምናደርግ
- መስኪድ እናሰራለን ብላችዋል የት የት ነው የምታሰሩት ምን ዓይነት መስኪድ ነው የምታሰሩ ?
- በሕዝቡ ጥያቄ ነው የሚቀርበው
- እኮ በሕዝቡ ጥያቄ ማለት ሄዳችሁ አይታችሁ በየትኛው ሕዝብ ጥያቄ አዲስ አበባ ውስጥ ሌላ ክልል ወይ ?
- በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ጥያቄ ያቀርባሉ ባለን አቅም ማለት ነው የተገደበ የለውም ግን አቅማችን ይገድባል በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት /ግልፅ ያልሆነ/ በማየት የተጠየቀው መስኪድ ዓይነት በእንጨት የሚሰራው ወይ በብሎኬት ቫሊው ወጥቶ ይሰራል
- እንዲህ ዓይነት ሰርታችሁ ያስረከባችሁት አለ ?
- አለ ብዙ ነው በጣም ብዙ
- በግምት ስንት ይሆናል ?
- እኔ አሁን እትትኑን አልያዝኩም እንጂ ከ 100 በላይ ነው የሚቆጠረው
- ማን ነው የሚረከባችሁ ?
- ሕብረተሰቡ ነው እዚያ አካባቢ ማለት ነው
- ሕብረተሰቡ ማለት በምታስረክቡበት ጊዜ ሰው ኮሚቴ አዋቅሮ ነው ወይስ እናንተ በእናንተ ማለት በእስልምና ምክር ቤቱ መዋቅር ነው የሚረከቡት ?
- በእስልምና ምክር ቤት መዋቅር የመስኪዶች የለም በመሰረቱ
- የለም ?
- በሀገሪቱ ውስጥ እንደዚያ የለም ሕብረተሰቡ ጥያቄ አቅርቧል በጥያቄው መሠረት ይሰራላቸዋል እዚያ ያለው ኮሚቴ ሕብረተሰቡ የሚያዋቅረው ሕብረተሰብ /ግልፅ ያልሆነ/ ይረከባል እና የራሳቸው እንትን ያደርጉታል ማለት ነው እኛ ሰርተን ማስረከብ



163

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስራ አስኪያጆችን ውጪ ወጥተው አልተመለሱም ብለዋል እና የት ነው የሄዱት እስቲ ሀገሩን ያውቃሉ መጀመሪያ የሄዱበት ሀገር እስካሁን ያልተመለሱ መጀመሪያ ከኢትዮጵያ ሲወጡ የት ሀገር ነው የሄዱት ?
- ምናልባት ሳውዲ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ እኔ በትክክል /ግልፅ ያልሆነ/ አልነገሩኝም
- ምናልባት ሳውዲ ሊሆን ይችላል ነው ያሉት ?
- አዎ ለተወሰነ ጊዜ ነው ደርሼ እመጣለሁ ያሉት /ግልፅ ያልሆነ/ አልነገሩኝም
- ሌላው ጥያቄ ደግሞ ለመንግስት ጥያቄአችን እናቀርባለን ብለው ግቢያችን ውስጥ ሲነጋገሩ ነበረ ብለው ነበር ቅድም ስማቸውን የጠሩት ተከሣሾች ለመንግስት አቤቱታ ለማቅረብ ግቢአችሁ መምጣት ምን አስፈለገ ይሄንን የምታውቁት ነገር ካለ በእናንተ ግቢ በኩል ነው ወደ መንግስት የሚተላለፈው አቤቱታ ?
- በአሴምብሊ የተወሰነ ነገር የለም ያኔ ግን ምናልባት እንዲያመቻቸው መገናኛ ቅርብ ስለሆነ ሴንተር ላይ ስለሆነ ይመስለኛል እንጂ እንትን አይደለም ቦታው ሎኬሽኑ ሴንተር ስለሆነ ወደ እንትኑ ፌዴራል ጉዳዮች ለመሄድ ቅርብ ስለሆነ ይመስለኛል እንጂ ሌላ የተወሰነ እና እዚህ ስብሰባ እንትን የተደረገበት እንትን የለም ወይም ድርጅቱ ያሰባሰበበት ሁኔታ የለም
- ስለዚህ ለመንግስት ለማቅረብ የመጡበትን ዓላማ አያውቁም እዚያ ቦታ ስላገኙ ነው የተሰበሰቡበት ዓይነት ነገር ነው አሁን የተናገሩት ?
- ይሄንን አሁን በስብሰባ ላይ አይደለም እኔ ኢንፎርማል የሆነ
- የተነጋገሩት
- ኢንፎርማል ከሆነ ቆመው ቆመው በሚያወሩበት ጊዜ
- አዎ ንግግሩ በቡድን በቡድን ሆነው ቆመው ይነጋገሩ ነበር ብለዋል ቅድም እና እሱ ንግግር እንዴ ንግግራቸው ጥያቄአችን አለ ለመንግስት እናቀርባለን የሚል ነው ብለዋል እና እሱን ጥያቄ ለመንግስት ለማቅረብ ካስፈለገ ለምን እናንተ ግቢ መጡ ነው ጥያቄው የሚያውቁት ነገር ካለ ነው ካላወቁ አይገደዱም ?
- ትክክል በግልፅ እንትን አልሆነልኝ ግልፅ አልሆነልኝም
- /ግልፅ ያልሆነ/



ECLN

2314 764

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ እዚያ ለምን ይመጣሉ የሚለውን ቅድም ገለፅኩት መሰለኝ ምናልባት የአጋጣሚ ቦታ ሎኬሽኑ እንትን አለ እንጂ የትም ቦታ ተገናኝተው እንትን ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ምናልባት ይመስለኛል እንጂ ሌላ ብዙ የማውቀው ነገር የለም እዚያ እንትን ያደረጉበት
- /ግልፅ ያልሆነ/ የምንቀበለው ገንዘብ ገንዘቡን የሚሰጡት በጎ አድራጎት ድርጅቶችም ይሁኑ ሰዎች ዓላማቸውን ገልፀውልን ነው የሚሰጡን የሚል ነገር ተናግረው ነበር ቅድም ለእዚህ ለእዚህ ዓላማ አውሉልን ብለው ይሰጡናል የሚል ነገር ተናግረዋል እና ዓላማውን በፁሑፍ ነው በቃል የሚነግራችሁ በጎ አድራጎት ድርጅቶቹ ?
- በፁሑፍም በቃልም የሚሆንበት ሁኔታ
- ለእዚህ ለእዚህ ዓላማ ብለው ?
- ትክክል አዎ አሁን መስኪድ ስራ ከሆነ ለመስኪድ ስራ ለኢፍጣርም ከሆነ ጥያቄአችንም እንደዚያ ነው የሚቀርበው
- አይ የድርጅቶቹ ዓላማቸውን ይገልፃሉ በቃልም በፁሑፍም ሪፖርት ይደርሰናል ብለው ነበረ ከእዚያ በኋላ ለምን ዓላማ እንደዋለ ገንዘብ ከሰጣችሁ በኋላ ማለት ነው ከድርጅቱ ተቀብላችሁ ከሰጣችሁ በኋላ ሪፖርት ይደርሰናል ብለው ነበር እና የእርሶ ስራ ከሪፖርት ጋር ያገናኞታል ?
- ይገናኛል ያው ይመለከታል
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አዎ በጋራም በግልም እናያለን አያለሁ
- በጋራም በግልም ያዩታል ገንዘብ ሰጥተው ሪፖርቱን ያላዩበት አጋጣሚ የለም ?
- አላስታውስም
- እሱን አያስታውሱትም አላስታውስም ማለት ?
- አይ የተመለሰበትን አላስታውስም ማለቴ ነው የቀረ
- የቀረ ማለት ?
- ሁሉም ሪፖርት ይቀርባል
- ሪፖርት ይቀርባል ?
- አዎ
- ሁሉንም አይተዋል ወይ ?



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስጨኒያም እኮ ያፈልጋል እኛ ብቻ የሚፈልገው ከፍል ብዙ ነው ፍኛ ያደረጅን ባለእንትን ያፈልገዋል
- አይ በእርሶ እውቀት አሁን እርሶ ገንዘብ ሲሰጡ ያው ዓላማው ይታወቃል ዓላማው ስጨኒው ድርጅትም ዓላማ ያስቀምጣል የእናንተ ድርጅትም ዓላማ አለው ለእዚያ ዓላማ ስለመዋሉ ሪፖርት ይቀርባል ብለው እና እያንዳንዱ ገንዘብ ባወጣችሁ ቁጥር ሪፖርቱን ይከታተላሉ ወይ እርሶ አሁን የድርጅቱን አቋም አልጠየኩም የእርሶን ነው
- እከታተላለሁ
- ስለዚህ የወጣው ገንዘብ ያው ለአላማው መዋሉን አረጋግጠዋል ማለት ነው ?
- ትክክል
- አንድ ጥያቄ 500 ሺህ ብር ቅድም የተቀበሉት አለ ለምሳሌ የእሱን አውቀዋል የእሱን ዓላማ ?
- ገልጨዋለሁ ሚፍጣር ገልጨዋለሁ ቅድም ዓላማው ይታወቃል ለኢፍጣር ነው ለፆም ለፆመኞች
- እኮ አይ ማለት የፈለኩት ምንድን ነው በፁሑፍ ወይም በቃል የተነገሮት ነገር በፁሑፍ የተሰጠ ነገር አለ ስለ እሱ ?
- የለም ሪፖርት
- ሪፖርት ሳይሆን ?
- አይ የለም
- እናንተ ቆይ እርዳታ በምትጠይቁበት ጊዜ ምን እየሰጣችሁ ነው ምን እያዘጋጃችሁ ነው የምትሰጡት እናንተ ጠይቃችሁ ነው ሳትጠይቁ ነው የሚሰጣችሁ ?
- ይሄ አሁን እኔ በትክክል ስለጥያቄው እንትን አልልም
- አይደለም አሁን እያንዳንዱ የሚሰጠው ገንዘብ ወይም እርዳታ ጠይቃችሁ ነው ሳይጠይቁም ይሰጣችዋል ጠይቆ ሊሰጥ ይችላል ችግር የለውም እሱ ላይ ግን ሳትጠይቁ የተሰጠበት ጊዜ አለ ለእዚህ ድርጅት ይዋል ብሎ ?
- ስጡልን ብለው የሚሰጡበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል
- ሊኖር ይችላል ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ይሄ 500 ሺህ ብር በምትቀበሉበት ጊዜ በቃል ወይ በፁሑፍ ለእዚህ ዓላማ መዋል አለበት ብሎ የገለፀ ሰው አለ ወይ ስፊጺውንስ ያውቁታል ወይ አሁን 500 ሺህ ብር በነ አድራት
- ገልፀዋል እኮ ሺህ ሀጂ ገልፀውልኛል
- እራሳቸው ናቸው እንደ የሰጡት ?
- እራሳቸው ናቸው የተቀበልኩት
- እኮ ማን ሰጠኝ አሉ ይሄ 500 ሺህ ብር ማን ሰጠን አሉ ?
- እኔ አልጠየኩም
- አልጠየቁም እርሶ ?
- አዎ
- በእዚህ እንያዘው ?
- አዎ
- እና መስግናለን ጨርሰዋል ከ /ግልፅ ያልሆነ/ 10 ነው አሁን መስማት አንችልም 8 ሰዓት እንገናኛለን ማለት ነው፡፡



161

23/7

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንደምን ዋላችሁ ጠዋት የነበረው ችሎት እንቀጥላለን እሺ ጠዋት የነበረው ችሎት ከሰዓትም ቀጥሏል ዳኞች አልተለወጡም ዐቃቤ ሕግ አልተለወጡም
- ተከሣሾች 6ኛ ተከሣሽ ቀርቧል 6ኛ ተከሣሽ በስተቀር ሌሎቹ ቀርበዋል የተከሣሽ ጠበቆች
- አዲስ መሐመድ፡ በሀሩ መካንጋ መሐመድ አብደላ ፣ ሀሰን ሁሴን ቀርበናል ሞላልኝ መለሰ ቀርቧል
- ጠዋት ከነበሩት ጠበቆች በተጨማሪ 2 ጠበቆች በተጨማሪ ቀርበዋል ከሰዓት የተቀጠረው ቀሪ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ነው ዐቃቤ ሕግ ምስክር አቅርቡ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ቃል እገባለሁ
- እንቀጥላለን የዐቃቤ ሕግ ቀሪ ምስክር ቀርቧል ቃለ መሀላ ፈጽመዋል በፍ/ቤቱ [illegible] ናቸው በዐቃቤ ሕግ ክስ ላይ ስንተኛ ተራ ቁጥር ናቸው ዐቃቤ ሕግ 187ኛ [illegible] ቀርቧል እሺ ምስክር እንኳን ደህና መጡ አሁን የመጀመሪያ ስምዎን [illegible] የአባት ስም የአያት ስም ያለመናገር መብት አሎት ስለዚህ የመጀመሪያ [illegible]
- ስንታየሁ ——
- ለምንድን ነው የመጣኸው ?
- በአቶ /ግልፅ ያልሆነ/ ጌታቸው ላይ ምስክርነት
- በማን ላይ ?
- የሱፍ ጌታቸው
- ሌላስ ?
- በቃ
- ታውቀዋለህ ?
- አዎ
- ልታሳየን ትችላለህ እስቲ አሳየን እስቲ አሳየን ወይ ይነሳልህ እሱ እሳቸው ናቸው ይነሱ ማን ነው ስምዎ ስንተኛ ተከሣሽ ኖት ምስክሩ የሱፍ ጌታቸው 18ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ይሄንን ተከሣሽ ከእዚህ ተከሣሽ ጋር ፀብ ወይም ዝምድና አላችሁ ?
- የለንም

768

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን አደረጉ ተብለው ነው የተከሰሱት ?
- የተከሰሱበትን ጉዳይ አላውቅም በወቅቱ ወደ ፌዴራል ፖሊስ ጣቢያ በምሄድበት ጊዜ እሳቸው ላፕቶፕ እና ሀርድዲስክ ላይ ያለውን /ግልፅ ያልሆነ/
- ለእዚያ ነው እሺ ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ
- አቶ ስንታየሁ እስቲ አሁን በወቅቱ ብለው የጠቀሱት ጊዜ መቼ ነው ?
- በ 26/12/2004
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ?
- ከ 8 ሰዓት
- 8 ሰዓት የት ነው ቦታው /ግልፅ ያልሆነ/ ያዩት ?
- ፌዴራል ማረሚያ ቤት ጉዳይ ኖሮኝ ሄጄ እዚያ ውስጥ /ግልፅ ያልሆነ/ ከላፕቶፓቸው እና ከሀርዲስካቸው ላይ እንዲወጣ ምስክርነት እንድሰጥ ተጠርቼ በአጋጣሚ
- ለምን ጉዳይ ነበር የሄዱት ?
- በራሴ ጉዳይ ነበር የሄድኩት
- በራስዎ ጉዳይ ?
- አዎ
- ምን ፌዴራል ማረሚያ ቤት ብለዋል እና ተቋሙን እርግጠኛ ኖት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የት ተቋም ነው የሄዱት የት ነው የሚገኘው አሁን ያሉን ቦታ ?
- በቀድሞ 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ
- የት ነው ቦታው ?
- ልዩ ስሙ ወደ ሾላ ሰሜን አዲሱ ገበያ መሄጃ
- ወደ እዚያ መሄጃ አሁን በጠቀሱት ቀን እና አሁን በገለፁት ቦታ ምን ተመለከቱ ?
- በአቶ የሱፍ ጌታቸው ሀርድ ዲስክ እና ላፕቶፕ ላይ የነበሩ እላዩ ላይ የነበሩት /ግልፅ ያልሆነ/ የተፃፉት ፁሑፎች ኮፒ በራሳቸው ኮፒ እየተደረገ እሳቸው አምነው ሲፈርሙ እኔም ያየሁትን ነገር ለመመስከር ፈርሜአለሁ
- እሺ እስቲ ተረጋግተው ከስንት ላፕቶፕ ነው የወጣው ?



239 769

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንድ ላፕቶፕ
- አንድ ላፕቶፕ እሺ ሀርድ ዲስክስ ያሉትስ ስንት ነው ስንት ሀርድዲስክ ?
- 2
- እንዴት ነበር ላፕቶፑ የተከፈተው ማን ነው የከፈተው ?
- አቶ የሱፍ ጌታቸው
- የማን ላፕቶፕ ነበር ያ ላፕቶፕ ?
- የአቶ የሱፍ
- በምን አወቁ የአቶ የሱፍ መሆኑን ?
- የራሳቸው መሆኑን በወቅቱ ሲመሰክሩ ስለሰማሁ
- ማን ሲል ሰሙ ?
- አቶ የሱፍ
- እራሳቸው ?
- አዎ
- ምን የእኔ ነው ነው ያሉት ምንድን ነው ያሉት ?
- የራሴ ላፕቶፕ ነው
- ከእዚያስ ?
- ከእዚያ በኋላ በውስጡ ላይ ያለውን ኮፒ እየተደረገላቸው ሲወጣ እሳቸው
- ኮፒ እየተደረገ ሲሉ እንዴት እየተደረገ ነው የወጣው እስቲ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ በቦታው ላይ እንግዲህ ከላፕቶፑ ላይ የተጫኑትን ኮፒ እየተደረጉ ሲወጡ
- በምን ኮፒ ተደረገ ወደ ምን ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የኮምፒዩተር እውቀት አሎት ?
- የኮምፒዩተር እውቀት የለኝም
- ፅሑፍ ምንድን ነው ውስጡ የነበረው ላፕቶፕ ውስጥ [illegible]
- ውስጡ የነበሩት ፅሑፎች በእንግሊዘኛ ስለሆኑ አላነበብኩትም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት *



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ያህል ፁሑፍ ነው ያለው ማለት ስንት ገፅ እንደሆነ ያስታውሱታል ?
- ብዛቱን ከ 100 በላይ ይሆናል በቁጥር አላውቀውም
- ከእዚያ ምን አደረጉ ?
- ከእዚያ በኋላ ያንን የወጣሁን ሁሉ እሳቸው ከፈረሙ በኋላ እኔ ፈርሜ ጨርሼ ጉዳዩን ወጣሁ
- ምኑ ላይ ነው የፈረማችሁት ?
- እሳቸው በወጣው ወረቀት ላይ
- ከየት የወጣ ወረቀት ነው ?
- ከእሳቸው ላፕቶፕ
- ፕሪንት የተደረገ ወረቀት ነበረ ?
- ፕሪንት የተደረገ ወረቀት ነው
- ማን ነው ያተመው ወይም ፕሪንት ያደረገው ?
- አቶ የሱፍ
- አርዕስቱንስ ያስታውሱታል የወጡት ምን ያህል ወረቀቶች ናቸው ስንት ቦታ ነው የፈረሙት እርሶ ?
- ፕሪንት በተደረጉት ወረቀቶች ሁሉ ፈርሜአለሁ ቁጥራቸውን ግን በውል አላውቅም
- ምን ዓይነት ይዘት ነው ያላቸው ቅድም በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተፃፈ ነው ብለዋል ሁሉም በእንግሊዘኛ ብቻ ነው የተፃፈው ?
- አማርኛም አለባቸው
- አማርኛም አለው ሌላ ቋንቋስ አለው ?
- ሌላ ቋንቋ እንግሊዘኛ እና ከአማርኛ ውስጥ አልፎ አልፎ አረብኛ አላቸው
- አልፎ አልፎ አረብኛ አለው ?
- አዎ
- ምን ውስጥ እንትን ተደርጎ የነበረ ነው ማለት ዝም ብሎ የላፕቶፕ እንትን ውስጥ ተቀምጦ የነበረ ነው ወይስ ከሌላ ከምን ውስጥ የወጣ ነው ?
- ከላፕቶፕ ውስጥ ነው ላፕቶፕ ውስጥ ምኑ ምኑ ጋር ይቀመጥ እውቀቱ ስለሌለኝ አላውቅም



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ይሄ የሆነው ?
- ከ 8 ሰዓት እስከ 10 ሰዓት
- ቢሮ ቁጥሩን ያስታውሱታል ?
- ቢሮ ቁጥሩን አላስታውስም
- አያስታውሱትም ሌላ ሰው አብሮት ነበር ?
- ሌላ አንድ ጓደኛዬ አለ
- አብሮ ነበር ከጓደኛዎት ውጪስ ?
- ሌላ ሰው የለም
- ማለት እርሶ አቶ የሱፍ እና ጓደኛዎት ብቻ ኖት ብቻ ነበሩ ?
- ሌላ ባለሙያ አለ
- ባለሙያ ማለት ?
- ያንን ስራ አብሮ እሳቸው ሲሰሩ ሲያይ የነበረ /ግልፅ ያልሆነ/
- አላወቁም ሌላስ የምርመራ አካል አልነበረም በቦታው ?
- እኛ 4ታችን
- 4ታችን ማለት ?
- በመጀመሪያ የነበረው የምርመራ አካል ይሁን ምን አላውቅም አቶ የሱፍ እና እኔ እና ጓደኛዬ
- እሺ እነዚህ ከውስጡ የተገኙት ነገሮች በሁሉም ላይ ፈርሜአለሁ ብለዋል ሌላስ ምን የተያ። ነገር ነበር በወቅቱ ?
- እዚያው ጋር የተያያዘ ነገር የለም የመጣውን ላፕቶፕ እና ሀርድ ዲስክ ነበረ ሀርድ ዲስኩ ላይ ደግሞ ወደ ኮፒ ወደ እንትኑ ኮፒ ተደርጓል /ግልፅ ያልሆነ/
- ሀርድዲስኩ ላይ የነበረ ነገር ነበር ብለዋል ያ ምን ተደረገ ?
- ወደ ሲዲ ላይ በርን ሲደረግ አይቼአለሁ
- ከእዚያ በኋላስ ?
- ከእዚያ በኋላ ሲዲውን እሳቸው የእሳቸው መሆኑን እሳቸው አረጋግጠው ከፈረሙ በኋላ ፈርሜ ጉዳዩን ጨርሼ ወጥቼአለሁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነዚህ ሲዲዎች ምን አላቸው ውስጣቸው ?
- ውስጣቸው የተጫኑትን በደንብ አላየሁትም
- ማለት ፁሑፍ ነው ምስል ነው ወይስ ምንድን ነው ?
- ንግግሮችም አሉበት
- ንግግሮች አሉ ?
- አዎ
- ሌላስ ?
- ምስሎች አሉ
- ምን ዓይነት ምስሎች ናቸው ንግግሮቹስ ምን ዓይነት ?
- ንግግሮቹ እና ምስሎቹ ኮፒ እየተደረገ ስለሆነ አጣርቼ አልሰማዋቸውም
- ሌላስ ?
- በቃ
- እስከ ስንት ሰዓት ቆያችሁ ?
- ll ሰዓት ላይ ጨርሰን ወጣን
- ከእዚያ በኋላ እንዴት ነበር ተከሣሽስ የነበረው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር ?
- ተከሣሽ በወቅቱ የራሳቸው መሆኑን በፍሪ ነፃነት ሲገልፁ እና ሲዝናኑ በነፃነት ኃሳባቸውን ሲገልፁ ነው ያየሁት አልታሰሩ ምናምን ካቴና በምናምን አይደለም
- እንዴት ሆነው ነበር ?
- በነፃነት መጥተው ንብረታቸው የራሳቸው መሆኑን አይተው ነው እንትኑን ድርጊቱ ሲከናወን ሲከታተሉ የነበሩት
- ታትመው በወጡት ሰነዶች እና በሲዲው እንትን ላይ ማን ነው ቀድሞ ይፈርም የነበረው ?
- አቶ የሱፍ ጌታቸው
- ተከሣሽ ማለት ነው ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- አቶ ስንታየሁ እርስ ወደ እዚያ ለማል ጉዳዩ ብቻ ነው የሄዱት ?



773

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እሺ በእዚያ ቦታው ላይ እርሶ ስንት ሰዓት ነው የደረሱት ?
- 8 ሰዓት
- ምርመራውም የተጀመረው አሁንም ቅድም ያሉት 8 ሰዓት ነው ?
- ከ 8 ሰዓት ጀምሮ ነው ያልኩት
- ስለዚህ ለእዚሁ ጉዳይ ተጠርተው ነበር ?
- አይደለም አጋጣሚ ነው
- እዚያ ከገቡ በኋላ መጀመሪያ አዳራሽ ውስጥ የትኛው ቁጥር ነው የገባችሁት ?
- ቁጥሩን በውል አላስታውስም
- የምን ቢሮ ነው ቢሮውስ ?
- የፖሊስ ቢሮ ነው ቁጥሩን አላስታውስም
- እኮ የፖሊስ የምን ቢሮ ነው ?
- የምን ቢሮ እንደሆነ አላስታውሰውም
- እዚያ በሚቀርቡበት ጊዜ አቶ የሱፍን እዚያ ቁጭ ብለው ነው ያገኙት አይደል ?
- አዎ
- አቶ የሱፍ ከየት እንደመጣ ወደ እዚያ አያውቁም አይደል ?
- አላውቅም
- እዚያ ሲገቡ ላፕቶፑ እዚያ ቢሮ ውስጥ ነበር አይደል ?
- ነበር አዎ
- ላፕቶፑም ከየት እንደመጣ አያውቁም አይደል ?
- አላውቅም
- አቶ የሱፍን እዚያ ከማግኘትዎ ውጪ አያውቁትም አይደል ?
- አላውቃቸውም
- እዚያ ከገባችሁ በኋላ ላፕቶፑ ሲከፈት ፓስወርድ አልነበረውም አይደል ?
- ፓስወርድ ምን የኮምፒዩተር እውቀት ስለሌለኝ በዚም አላውቅም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ እንዴት እንደተከፈተም አያውቁም ?
- አዎ
- ከእዚያ ውስጥ ታትመው የሚወጡት ሰነዶች ይዘታቸው ምን እንደሆነ አያውቁም አይደል ?
- አላውቅም ፁሑፉን አላነበብኩም የእንግሊዘኛ እና አረብኛ በአማርኛ ስለሆነ አላነበብኩትም
- በሰነዶቹ ላይ እርሶ እንዲፈርሙ በሚደረግበት ጊዜ ሰነዶቹ ለሁላችሁም ሳይነበቡ ነው የፈረማችሁት አይደል ?
- እሳቸው አንብበው ከፈረሙ በኋላ ነው እኔ የፈረምኩት
- አልተነበበም ለሌሎቻችሁ ?
- አልተነበበም
- አቶ የሱፍ ፖሊሱ ሰነዱን በሚያወጣበት ጊዜ ያ ሰነድ በማስረጃነት የሚቀርብባቸው ስለመሆኑ አልነገራቸውም አይደል ?
- አልተነገረም
- ተከሣሹ የሱፍ ጌታቸው መሆኑ ስሙን በምን አወክ ?
- የሱፍ ጌታቸው መሆኑን ሲፈርሙ
- እስከ እዚያ ድረስ አታውቅም ነበር ስሙን ?
- አላውቃቸውም
- ስለዚህ ፊርማውን አይተህ የሱፍ ጌታቸው መሆኑን ነው ያወከው ?
- አዎ
- ሀርድዲስኩ አንድ ነው ሁለት ነው ሀርድ ዲስኩ ስንት ነበር ?
- ሀርድዲስኩ 2
- 2 ነበር ከ2ቱ ነበር ፕሪንት ሲደረግ የነበረው ?
- አዎ
- እሺ ሲዲው በርን ተደርጎ ፊርማአለሁ ብለሀል ሲዲው ላይ ነው የፈረምከ ወረቀት ላይ ነው የፈረምከ ምን ላይ ነው የፈረምከ ?
- ሲዲው ላይ እሱ ከፈረመ በኋላ ፊርማአለሁ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እላዩ ላይ ?
- እላዩ ላይ
- እያንዳንዱን ሙሉውን ስዕሉን አሳይቷችሁ ምስሉንም አስደምጠዋችሁ ነው የፈረማችሁት ወይስ ዝም ብለው ተገለበጠ ተብሎ ነው የፈረሙት ?
- ምስሉንም ፁሑፉንም አላየንም እራሳቸው ተገልብጠ አቶ የሱፍ አረጋግጠው ቀጥዬ ነው የፈረምኩት
- የሱፍ ወደ ክፍሉ ሲገባ ያነክስ ነበር ?
- ማንከሱን አላየሁም
- ሲያነክስ አላየኸውም ?
- አላየሁም
- ሲዲው ላይ የሚፈልጉትን ነገር መጨመር መቀነስ እንደሚቻል ታውቃለህ ?
- እውቀቱ ስለሌለኝ አላውቅም
- ይሄንን ጥያቄ ባይመልሱም ጥሩ ነው ብዙም ያን ያህል ለማንኛውም ሰው ግልፅ ነው
- ፕሪንት ሲደረግ እንግሊዘኛ አማርኛ እና አረብኛ ፕሪንት ይደረግ ነበር ብለሀል አረብኛውም ፕሪንት ተደርጓል ?
- አረብኛውም አለ
- አልፎ አልፎ ፕሪንት ተደርጎ ነበር ብለሀል አረብኛው ላይ ፈርመሀል አንተ ?
- 3ቱም ላይ ፈርሜአለሁ
- አረብኛው ላይ ፈርመሀል ?
- አዎ
- ምስክር አቶ ስንታየሁ የሱፍ ሲመሰከር ነፃ ሆኖ እንደውም እየተዝናና ነበር ያልከው እና አንተ ከመምጣትህ እና ከማየትህ በፊት የደረሰበት ጫና ይኑር አይኑር አታውቅም አይደል ?
- አላውቅም
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልጨረስንም
- ይኸው ጨርሰናል እያሉ እኮ ነው
- በስህተት ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ቀጥሉ ለማንኛውም አትድገሙ
- እንደግምም የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ስንታየሁ ቅድም ሲጠየቁ ፖሊስ ጣቢያ የሄድኩት ለግል ጉዳይ ነበር ብለው ነበር ጣቢያ የሄዱት በምስክርነት ነው በተከሣሽነት ነው በምንድን ነው ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ እንቃወማለን ምስክራችን በፖሊስ ጣቢያ የሄዱበት የግል ጉዳያቸውን ሊጠየቁ አይገባም የመጡበትን ምስክር የታዘቡትን ነገር ገልፀዋል በእዚሁም መስቀለኛ ጥያቄ ተጠይቋል ስለሆነም ይሄ እዚያ የሄዱበት የግል ሕይወታቸው ሊጠየቅ አይገባም
- /ግልፅ ያልሆነ/ እሳቸው ናቸው እራሳቸው ለግል ጉዳይ ሄድኩ ያልኩት ይሄ ደግሞ ዐቃቤ ሕግ ከእዚህ በፊት ካስከለከለው ነገር ጋር ግንኙነት የለውም ከሕይወታቸውም ጋርም የሚገናኝ ነገር አይደለም ጣቢያ በግሌ ሄድኩ ስላሉ የሄዱበት ጉዳይ ምስክር ሆነው ነው ከሣሽ ተከሣሽ ሆነው ነው ይሄንን ለፍ/ቤቱ እንዲገልፁ ቢደረግ ምናልባት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳል ከእዚያ ውጪ ዐቃቤ ሕግ ያቀረቡት ነገር ተገቢ አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት
- ብይን ሰጥተናል ብይኑ ምንድን ነው የተከሣሹ ማለት ምስክሩ ቀደም ሲል ወደ ፖሊስ ጣቢያ የሄደ መሆኑን ገልፆዋል ለምን እንደሄዱ ነው ጥያቄው ጠቅላላ ሲነሳ አሁን እዚህ ጋር ፍ/ቤቱ ይሄንን ጥያቄ ምርጫ የሰጠው ለምስክሩ ነው ምስክሩ እኔን ይጎዳኛል እኔን የወንጀል ድርጊት በራሴ ላይ ሊዞርብኝ ይችላል ብሎ ካሰበ ወይም ከማንነቱ ጋር የሚያያዝ ከሆነ እሱን ለፍ/ቤቱ ሊገልፅ ይችላል ከእዚያ ውጪ ግን ጥያቄው ቢመለስ በፍ/ቤቱ /ግልፅያልሆነ/ የሚያመጣው ችግር እንደሌለ ተገንዝቧል ይሄንን መሠረት አድርገህ ምስክሩ እራስህን የማይጎዳ መሆኑን አረጋግጠህ እሱን ትነግረናለህ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የሄድኩት በራሴ ጉዳይ ስለሆነ ከራሴ ጉዳይ በስተቀር እራሴን የማይጎዳኝ መሆኑን አረጋግጬ ምስክርነት
- ቀጥሉ በቃ ለምንድን ነው የሄድከው ቀጥል ?
- ወደ እዚያ የሄድኩት ጓደኛዬን ፈልጌ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀጥሎ ከእዚህ በኋላ ?
- ጓደኛዎት ጣቢያ ነው የሚገኙት ጓደኛዎት ጣቢያ ይገኛሉ ?
- ጣቢያ አይገኝም በቦታው በጣቢያው ላይ በመንገድ በጣቢያው መንገድ ላይ ሳልፍ ትብብር ተጠየኩ ወደ ጓደኛዬ እየሄድኩ ነበር
- ስለዚህ ለጉዳይ አይደለማ የሄደው ፖሊስ ጣቢያ ?
- ይበቃል እኮ ምክንያቱን ተናገረ
- ስንታየው ቅድም ቀኑ 26/12/04 ነው ብለው ነበር ይሄ ቀን የስራ ቀን ነው ወይስ ቅዳሜ እና እሁድ ?
- ስለዘገየ አላስታውሰውም
- ቀኑን በምን አስታወሱ ?
- ቀኑን በ 26 መሆኑን
- እኮ በምን አስታወሱ ?
- የስራ ቀን ይሁን የእረፍት ቀን አላስታውስም
- የለም ቀኑን በምን አስታወሱ እሱ ይቅር እሺ ቀኑን 26/12/04 በ 8 ሰዓት እዚያ ገብቼ ዮሴፍ ጌታቸው ሲናገር ሰምቼለሁ ብለዋል ይሄንን ቀን በምን አስታወሱ ነው ?
- የፈረምኩበትን ቀን እንዴት እረሳለሁ
- በመፈረምዎ ነው ያስታወሱት ?
- አዎ
- የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- እሺ ሲዲዎቹን ወይም እነዚህ የፁሑፎቹን ይዘት አላውቅም ብለሀል ነገር ግን ተከሣሹ ደግሞ ሲያነበው ነበር ብለሀል ምን ጮህ እያለ ነበር ሲያነብ የነበረው ወይስ እንዴት ነበር ሲያነብ ?
- አቤት አልገባኝም
- ተከሣሽ እንዴት ነበር ሲያነብ የነበረው ማለት [illegible] ረጅም ጊዜ ወስዶ ነበር ሲያነብ የነበረው ወይስ እንዴት ነበር ?

የፌዴራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍርድ ቤት · የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይደለም ኮፒ ሲደረጉ እያየ የራሴ ናቸው ሲል ብቻ
- የራሴ ናቸው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ትብብር ተጠይቄ ነው እኔ ውስጥ የገባሁት ብለሀል ጉዳዩን ለመታዘብ አሁን ደግሞ ቅድም ስትጠየቅ ጉዳዩ በማስረጃነት እንደሚቀርብበት አልተነገረውም በማለት ገልፀሀል እና ለምን ጉዳይ ነበር አንተ ቦታው ላይ የሄድከው እዚያ ቦታ እዚያ ቢሮ ውስጥ የገባኸው በምን ጉዳይ ነበር ምን ለማድረግ ነበር ?
- እዚያ ቦታ ላይ
- እዚያ ቢሮ ውስጥ ተከሣሹ ሲያወጣ እነዚያን ሰነዶች ፕሪንት እየተደረጉ ላፕቶፖቹ ሲወጡ ምን ታደርግ ነበር አንተ ቆመህ ለምንድን ነው እንድትፈርም የተደረከው ?
- የሚወጡትን በታዛቢነት እያየሁ ስለነበር
- ምኑን ነው የምትታዘበው ?
- ፕሪንት የሚደረጉትን
- ይበቃናል
- በፍ/ቤቱ ጥያቄ
- አንተ ስትገባ ላፕቶፑን ማን ነው ይዞት ያገኘኸው ?
- አቶ የሱፍ
- አቶ የሱፍ የከፈተውስ ማን ነው ?
- አቶ የሱፍ
- በምን ነበር የያዙት ላፕቶፑ የተያዘበት ቦርሳ አለው ?
- ላፕቶፑ ብቻውን ነው
- ብቻውን ነው ?
- አዎ
- ሀርድዲስኩንስ ማን ነው የያዘው ?
- ሀርድዲስኩም እዚያው ነው ያለው
- እኮ ማን ነው የያዘው ?



779

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሳቸው
- እሳቸው ናቸው የያዙት ?
- አዎ
- ክፍል ውስጥ ስትገቡ ስንት ፖሊስ ነው ያገኛችሁት ?
- እሳቸው አሉ ፖሊስ አለ
- አንድ ነው ሁለት ፖሊስ ?
- ሁለት አንዱ በሌላ ቦታ ነው የተቀመጠው
- እናንተን የወሰዳችሁ ማን ነው እዚያው የነበሩ ፖሊሶች ናቸው ሌላ ፖሊስ ነው የወሰዳችሁ?
- አይ ሌላ
- ሌላ ፖሊስ ?
- አዎ
- ቢሮ ሲገቡ አቶ ዮሴፍ ነው የሱፍ ነው አቶ ዮሴፍ እናንተ ከገባችሁ በኋላ ነው የመጣ ወይስ አቶ የሱፍ ቢሮ ውስጥ እያሉ ነው እናንተ የገባችሁት ?
- አቶ የሱፍ ቢሮ ውስጥ ነበሩ አቶ የሱፍ እኛ ከገባን በኋላ ተከትሎን ገባ
- እናንተ ከገባችሁ በኋላ መጣ ?
- አዎ
- ብቻውን ነው ከሌላ ሰው ?
- ከኋላው ሌላ ሰው አለ
- ከእዚያ በኋላ እንደመጣ እናንተ ለምን እንደመጣችሁ ለምን እዚያ ቢሮ እንደተገኛችሁ የተገለፀ ነገር አለ ወይስ የለም ?
- የለም
- ለምን እንደመጣችሁ የተነገረ ነገር የለም ?
- የለም
- ላፕቶፕ ቢሮ ውስጥ ነበር ወይስ እሱ ነው ይዞ የመጣው ?
- ላፕቶፑ ቢሮ ውስጥ ነበር



2330 780

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ መጀመሪያ አንተ ለምንድን ነው ታዛቢ ሁን ስትባል የተገለፀልህ ነገር አለ ምንድን ነው የተገለፀልህ ምንድን ነው የተባልከው ?
- ከላፕቶፕ ውስጥ እና ከሀርድ ዲስክ ውስጥ የሚወጡ ነገሮች ስላሉ እነዚህን ነገሮች ተመልከቱ በታዛቢነት ትመለከታለህ
- ለምንድን ነው ተመልከቱ የተባላችሁት ?
- አላውቀውም
- እናመሰግናለን ጨርሰሀል
- ሌላ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- በፍ/ቤቱ 56ኛ ተራ ቁጥር በዐቃቤ ሕግ ስንት ነው በዐቃቤ ሕግ 186ኛ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት ምስክር ቀርበዋል ምስክሩ የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ እንዲናገሩ የአባትዎን እና የአያትዎን አድራሻዎን ያለመናገር መብት አሎት ስለዚህ የመጀመሪያ ስምዎ ማን ይባላል ?
- መኮንን እሸቱ
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- ምስክርነት ታዛቢነት ያየሁትን ለመመስከር ነው
- በማን ላይ ነው ?
- በየሱፍ ጌታቸው ላይ
- የሱፍ ?
- ጌታቸው
- ቢያዩት ያውቁታል ?
- አዎ
- ሊያሳዩን ይችላሉ ?
- እችላለሁ
- እስቲ አሳዩን የትኛው ናቸው የተጠቆማችሁ ተነሱ ማን ነው ስምዎት ?
- የሱፍ ጌታቸው ስንተኛ ተከሣሽ ኖት 18ኛ ተከሣሽን ምስክሩ ለይቶ አሳይቷል
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. አቶ መኮንን መቼ ነው የሚያውቋቸው አቶ የሱፍን ?
- አቶ የሱፍን የማውቃቸው በ 26/12/2004 ዓ.ም
- የት ነው የሚያውቋቸው ?
- ማን ነው ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በአጋጣሚ ለራሴ ጉዳይ ወደ እዚያ በምሄድበት ሰዓት
- ስንት ሰዓት አካባቢ ነው የሄዱት ?
- እኔ የሄድኩት ወደ 5 ሰዓት ላይ ነው ለእሳቸው የቀረብኩት 8 ሰዓት ላይ ነው ታዛቢነት ተጠይቄ የቀረብኩት
- ማን ነው እንድትታዘብ ምን እንዲታዘቡ ነው የተጠየቁት ?
- ያው ያየኸውን ነገር እንድትመሰክር ነው የተባልኩት
- የት እንዲመሰክሩ ?
- እዚያው ማዕከላዊ
- ያንን የት ያዩትን ነገር የት ነው የሚመሰክሩት እስቲ ተረጋጉ እና ?
- እዚያው ማዕከላዊ ነው ያየሁት የታዘብኩትም ያው ግለሰቡን ያው የማስተዋወቅ ስራ ተሰራ ቁጭ አለ
- ምን ተባለ ማስተዋወቅ ሲሉ ?
- ከእዚያ በኋላ የራሱ የሆነ
- ማስተዋወቅ ያሉትን እስቲ እኔን እየሰሙኝ ግለሰቡን ማስተዋወቅ ሲባል ምንድን ነው የተደረገው ?
- ግለሰቡ ምንድን ነው 1ኛ ንብረቱ ይሄ ንብረት የእሱ መሆኑን 2 ሀርድ ዲስክ የእሱ መሆኑን እና ይሄ ላፕቶፕ የራሱ መሆኑን ተገለፀልኝ
- ማን ነው ይሄንን ያለው ?
- በወቅቱ የነበሩት እዚያ የነበሩት እንትኖች ናቸው የስራ ባልደረቦች ናቸው
- ተከሣሹስ ምን አለ ?
- ምንም የተናገረው ነገር የለም ዝም ብሎ በቃ ሂደቱን ተቀበለ አመነ ሲነገረው እሺ አለ ያው መጀመሪያ ያው
- ምኑን ነው እሺ ያለው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የራሱ መሆኑን አረጋገጠ
- እንዴት ነው ያረጋገጠው ምን ብሎ አረጋገጠ ?
- ይሄ ሀርድ ዲስኩን አነሳ ይሄ ሀርድ ዲስክ የራስህ ነው ሲለው አዎ የራሴ ነው አለ ላፕቶፑም የአንተ ነው ወይ ሲለው አዎ የእኔ ነው አለ ከእዚያ ከእነዚያ ውስጥ ያንን ፕሪንት አድርጎ እራሱ
- ምንድን ነው ፕሪንት የተደረገው ?
- ሀርድ ዲስኩን እና ላፕቶፑ ደግሞ የራሱ ንብረት መሆኑን እራሱ ገለፀልን
- ማን ከተፈው ላፕቶፑን ?
- የሱፍ ጌታቸው
- እንዴት አድርጎ ነው የከፈተው ምን ?
- ያው ሀርድዲስኩን እንትን አደረገ እና
- ላፕቶፑን እንዴት ከፈተው ላፕቶፑን እስቲ ከላፕቶፑ እንጀምር እና ?
- ላፕቶፑን እራሱ በራሱ እጅ ፕሪንት አደረገው ፕሪንት አደረገ እና ከፈተ
- ምን አድርጎ ከተፈተ ?
- ፕሪንት አድርጎ ከፈተ
- ምኑን ?
- ሀርድዲስኩንም ያኛውንም ላፕቶፑን
- ሲገቡ ኮምፒዩተሩ ክፍት ነበረ ወይስ ተዘግቶ ነበር የተቀመጠው ?
- ታሽጓል
- በምንድን ነበር የታሸገው ?
- በፕላስተር ተደርጎ ስሙ ተለጥፎበት
- ምን ይላል ስሙ ?
- የሱፍ ጌታቸው ይላል እና ያንን እዚያው እኛ ፊት ነው የተላጠው ወረቀቱ
- ከእዚያስ ?
- ከእዚያ በኋላ በቃ እያንዳንዱን ሂደቶች ወረቀቶቹ በርካታ ወረቀቶች ናቸው እየወጡ አየን
- ምን ዓይነት ወረቀቶች ናቸው ?



2337

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወረቀቶቹ አላነበብኳቸውም በርካታ ናቸው የተለያዩ ምስሎች አሉበት እና ያው እሱ በፈረመበት ላይ እያየን እኛም ፈርማችን /ግልፅ ያልሆነ/
- በምን ቋንቋ የተፃፈ ወረቀቶች ነበሩ ?
- እኔ ቋንቋው ያው እንግሊዘኛ ነው የሚመስለው ቋንቋው
- ሌላስ ?
- በቃ ሌላው የሌላ ምስሎች አሉ ምስሎቹም ትዝ አይሉኝም ምስሎች አሉ
- እሺ ይሄ ከላፕቶፑ ተገኘ የሚሉኝ ነው ?
- አዎ
- ከእዚያስ ከሀርድ ዲስኩስ ?
- ሀርድዲስኩም ያው እራሱ እንትን ያደረገው ፕሪንት ያደረገው እራሱ እያወጣ ያው ያሉትን ነገሮች ምስሎችንም ያለውን እንትኖቹን አየናቸው
- ከሀርድ ዲስኩ የወጣውስ በምን ቋንቋ የተፃፈ ነው ?
- ያው እንግሊዘኛ ነው የሚመስለው እሱ
- የሚመስለኝ ነው ማለት ?
- አዎ እንግሊዘኛ ነው እኛ አላነበብነውም ያው እንግሊዘኛ ነገር ነው
- እንግሊዘኛ ነገር ምን አንብባችሁታል ሰነዱን ሁሉን ነገር አይታችሁታል እንዴ በወቅቱ ?
- አላነበብነውም በቃ ከእዚያ ኮምፒዩተሩ የሚያወጣውን ወረቀት ለእሱ ነው የሚሰጠው እሱ ያያል ለእኛ ይሰጠናል
- ምን እያለ ነው የሚሰጣችሁ ?
- በቃ እራሱ ያመነበት ስለሆነ እራሱ በቃ ነፃ ነው ልጁ ግልፅ ነው ምንም የተናገረውም ነገር የለም በወቅቱ ለእኛ ይሰጠናል እሱ ይፈርማል
- ምን እያለ ነው የሚሰጣችሁ ለእናንተ ?
- በቃ ምንም ያው መጀመሪያም የራሱ መሆኑን አምኗል የራሱ መሆኑን ግልፅኝነት አስቀምጧል ሰውዬው ስለዚህ አሁን የሚደረጉት ሁሉ ድርጊቶች እሱ ለእሱ እንሰጠዋለን እሱ ይፈርማል ለእኔ ይሰጠኛል እኔ ደግሞ ከስር ከእሱ በኋላ በሀርድ ዲስኩም ላይ በእያንዳንዱ ወረቀት ላይ ፈርማችንን አስፍረን በእዚያ ተለያይተናል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ እነዚህ ምስሎች ምናምን ተቸንተዋል ብለዋል ምን ዓይነት ምስሎች ናቸው ?
- ምስሎቹን የውጪ የሀገር ምስል ያለው ምስልም አለ የታየ አልፎ አልፎ እኔ በወቅቱ ትንሽ ቀኑንም ስለረዘመ ትዝ አይለኝም የወረቀቱ ቁጥር እና ያ ትዝ አይለኝም
- እሺ ከእርሶ ጋር ማን ነበር ?
- ከእኔ ጋር የነበረ ስንታየሁ የሚባል
- ሌላስ ?
- ስንታየሁ ወልዴ ሌላ የለም
- ቢሮ ውስጥ ከእናንተ ከታዛቢዎች እና ከተከሳሹ ውጪ ሌላስ ማን ነበር ?
- ማንም አልነበረም
- ማን ነው ወደ እዚያ ያስገባችሁ ?
- ወዴት ወደ ቦታው ላይ እኔ በራሴ ጉዳይ ወደ እዚያ ቦታ ላይ ሄድኩኝ ስሄድ በእንደዚህ ዓይነት በፌዴራል ፖሊስ ተጠየኩ
- ምን ተብለው ?
- የታዛቢነት ፍቃደኝነት ትሆናለህ ወይ የሆነ ነገር ለማየት አለ ለምስክርነት አዎ ምን ችግር አለው የሚታይ እውነታ ነገር ከሆነ ይቻላል ችግር የለውም አልኩት ገባሁ አየሁ
- ከገባችሁ በኋላ ተከሣሹን የማስተዋወቅ ነገር ተደረገ ብለዋል ?
- አዎ
- እናንተስ ምንድን ነን አላችሁት ለተከሣሹ ?
- ምንም የተነጋገርነው ነገር የለም ከእሱ ጋር የተገናኘነው ነገር የለም እዚያቸው
- ማን ነው ያስተዋወቃችሁ ተከሣሽ ጋር መጀመሪያ ?
- በወቅቱ የነበረ የእዚያ ቦታ ላይ የተቀመጠ ሰው ነው
- ይሄ ሰው የሚሉት ምንድን ነው ስራው ?
- ቢሮ ውስጥ የተቀመጠ ነው ያው የእዚያ ስራ ባልደረባ
- የስራ ባልደረባ ?
- ይሄንን ጉዳይ የሚከታተለው ማለት ነው



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ስለዚህ ከእናንተ ውጪ ሌላ ሰው ነበር ማለት ነው ?
- አዎ እሱ ነበር አዎ /ግልፅ ያልሆነ/
- በስራ ማለት እርሶ ቅድም እኛ ብቻ ነን ያሉት ከስራ ባልደረባ እዚያ ውስጥ ካሉ ከስራ ባልደረቦች ውጪ እኛ ነን ለእዚህ ጉዳይ የገባነው ሰዎች ለማለት ነው እንዴት ነው እስቲ አብራሩት ?
- አሁን ያደረግነው እኔ ገባሁ እኔ ከገባሁ በኋላ ስንታየሁ ወልዴ የሚባል መጣ ከእዚያ በኋላ ቢሮ ውስጥ አንድ ሰው አለ ማን ነው የሱፍ ጌታቸው በኋላ መጣ
- ማን ይዞት መጣ ?
- እዚያ የስራ እንትን ነው
- ስለዚህ የሱፍ ጌታቸውን ይዞ የመጣ ሌላ ባልደረባ ነበር እዚያ ውስጥ ?
- አዎ ሌላ ባልደረባ ከውስጥ ይዞት መጣ እቃዎቹም ቁጭ ብለዋል እንደታሸጉ ናቸው ለእሱ ሰጠው አየ ያም ላፕቶፑም የራሱ መሆኑን ተገለፀልን እሱን
- እስከ ስንት ሰዓት ቆያችሁ ?
- ከ 8 ሰዓት እስከ 10 ሰዓት ባለው ሰዓት ግምት
- ረጅም ሰዓት ነው አልሞስት 2 ሰዓት ይሆናል ምን ስታደርጉ ቆያችሁ በእዚሁ ሁሉ ሰዓት ?
- ወረቀቶቹ ብዙ ነበሩ የሚወጡት ከላፕቶፕ ላይ የሚወጡ ወረቀቶች
- ከእዚያ ውስጥ እርሶ ያነበቡት ወረቀቶች ነበሩ ያነበቧቸው ?
- ምንም አላነበብኩም ወረቀት እኛ ያው ያለውን ሂደት ለእሱ ነው የምንሰጠው ለእሱ ያየዋል መጀመሪያ እሱ ካየ በኋላ እሱ ያነባል ወረቀቶቹን የተቀበላቸውን በሙሉ ወረቀት እሱ ያያል እሱ እያንዳንዱ የወጡትን ወረቀቶች ያያል
- እርግጠኛ ኖት ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ውጪ በሌላ ቋንቋ የተፃፈ ሰነድ አልነበረም ?
- አይ እኔ ልብ አላልኩም እሱን እንግሊዘኛውን ነው ያየሁት
- እርሶ ያዩት እንግሊዘኛውን ነው ?
- አዎ
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ አብቅቷል የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- አቶ መኮንን እርሶ እዚያ የሄዱት በ 5 ሰዓት ነው ብለዋል አይደለም ልክ ነኝ ?



5

2336

186

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ልክ ነው
- በ 5 ሰዓት ለግል ጉዳዮ ነው የሄዱት እዚያ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ?
- የሄድኩበት ጉዳይ ለራሴ ጉዳይ ነው የሄድኩት በአጋጣሚ እኔ እዚያ ቦታ ላይ ያው 5 ሰዓት የሄድኩበት የራሴ ጉዳይ ሲሆን እዚያ ያለኝን ሰዓት ገድዬአለሁ ከሰው ጋር
- ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ማለት ነው አይደለም ?
- አዎ እና ያንን ኃሳብ ከፌዴራል ፖሊስ ነው እኔም ወደ እዚያው አካባቢ ቅርበት ነበረ የምሰራበት ቦታ ላይ ይሄንን ነገር ተጠየኩኝ ፍቃደኝነቴን ተናገርኩኝ በቀጠሩኝ ሰዓት መሠረት እዚያው ቦታ ላይ ሄድኩኝ የሄድኩት ግን 5 ሰዓት ነው ለራሴ ጉዳይ ነው የሄድኩት ቦታው ላይ
- እዚያ ውስጥ  የግል ጉዳይ ነበሮት የራስዎ ?
- አዎ እዚያ የሚሰራ አንድ ሳይት አለ ጎኑ ላይ ለራሴ ጉዳይ እዚያ ገብቼ ነው በእዚያ አጋጣሚ እዚያው አካባቢ ላይ ስለነበርኩ የማውቀው ሰው አግኝቼ በእዚያ አማካይነት ተጠየኩኝ ፍቃደኝቴን ተናገርኩ
- በ 8 ሰዓት እርሶ ወደ ቢሮ ሲሄዱ ቢሮ ቁጥር ስንት ነበር የገባችሁት ?
- መጀመሪያ 27 ቁጥር ነበር የገባነው ከ 27 ቁጥር ነው ወደ ፎቁ ላይ  ይዘውን የወጡት ቁጥሩን አላስታውሰውም የገባንበትን
- ቢሮው የምን ቢሮ ነው ?
- ያው ቢሮ ነው ያው እራሱን የቻለ አንድ ቢሮ ነው የምን ቢሮ እንደሆነ አላውቀውም
- የምርመራ ቢሮ ይሁን የእስር ክፍል ይሁን ወይ የምን የሚያውቁት ነገር አለ ያ ክፍል ?
- አይ አላውቀውም የመጀመሪያ ጊዜዬ ስለሆነ አላውቀውም
- ወደ ክፍሉ ስትገቡ እርሶ እና አቶ ስንታየሁ አብራችሁ ነው የገባችሁት ?
- አይ እኔ ለራሴ ነው የገባሁት
- ክፍል ውስጥ ስትገቡ ከእርሶ ማን ነው የቀደመው ?
- እኔ ነበርኩኝ መጀመሪያ የቀደምኩት እኔ ነኝ ቀደም ብዬም የሄድኩት እኔ ነኝ እኔ ነኝ የቀደምኩት
- ከእዚያ በኋላ አቶ ስንታየሁ መጡ ተከሣሽ የሱፍ የመጣው ከእዚያ በኋላ ነው አይደል ?
- አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሲገባ ያነከሰ ነበር አይደል ያነከሰ ነበር አይደል ሲሄድ በደንብ አይተኸዋል ?
- አያነከሰም ሲመጣ አያነከሰም
- ከገባችሁ በኋላ እርሶ እዚያ ክፍል ውስጥ ላፕቶፕ አይተዋል እርሶ በሚገቡበት ጊዜ ?
- ላፕቶፑን አላየሁም እሱ ከመጣ በኋላ ነው ላፕቶፑንም ያየነው ያንንም ያሳዩን እሱ ከመጣ በኋላ ነው እሱ ከገባ በኋላ አብረው ሲመጡ ነው
- እሱ ሲገባ ላፕቶፑን ይዞ አልገባም አይደል ?
- አልገባም
- ሀርድዲስኩንም ይዞ አልገባም ?
- አዎ አንድ ላይ የራሱን ይዘውት ነው የመጡት እራሳቸው
- ፖሊሶች ናቸው ይዘውት የመጡት ?
- ፖሊስ መሆናቸውን አላውቅም ሲቪል ነው የለበሱት
- ሲቪል የለበሱ ሰዎች ናቸው ይዘውት የገቡት ?
- አዎ
- ላፕቶፑ ከገባ በኋላ ተከሣሽ ነው የከፈተው ብለዋል ?
- አዎ
- ያለፓስወርድ ነው የተከፈተው አይደል ?
- አቤት
- ያለፓስወርድ ነው የተከፈተው አይደል ?
- በራሱ እጅ ነው የከፈተው
- ፓስወርድ የሚባል ነገር አለ ኮምፒዩተር ሲከፈት ?
- አዎ
- ፓወስረድ አልነበረውም አይደል ኮምፒዩተሩ ?
- አይ ፓስወርድ እራሱ ነው ነበረው
- ፓስወርድ አስገብቶ ነው የከፈተው አይተሀል ?
- አዎ እራሱ ነው አዎ እንደዚያ አድርጎ ነው የከፈተው እራሱ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፓስወርድ በትክክል ያውቃሉ እርሶ ?
- አቤት
- ፓስወርድ ምን እንደሆነ ያውቃሉ ?
- አዎ
- ከተከፈተ በኋላ ፕሪንት የሚያደርገው ማን ነበር ፖሊስ ነበር አይደል ?
- አይደለም እራሱ የሱፍ ነበረ ፕሪንት ያደረገው
- ፕሪንተሩ የት ነው የነበረው ?
- እዚያው ቢሮ ውስጥ ነው ያለው አጠገቡ ነው ያለው የራሱ ንብረት እንደሆነ እንደውም 10 ሺህ ብር የገዛው ንብረት መሆኑን ሁሉ እየነገረን ነው እኛን
- ፕሪንተሩን ?
- እንትኑን ላፕቶፑን
- አሁን ፕሪንተሩን ነው የጠየኩት ?
- ፕሪንተሩም ያው የታሸገ ነው ያው የራሱ ንብረት መሆኑን ነው እኔ የተገለፀው እዚያ ሲገለፅ የራሱ ንብረት መሆኑን
- ፕሪንተሩም የእሱ ነው ተብሏል ?
- አዎ
- ከእዚያ ፕሪንት የተደረጉት ወረቀቶችን መጀመሪያ ከፕሪንተሩ ላይ አንስተን እንሰጠው ነበር ብለዋል ?
- አንስተን የምንጠሰው ለእሱ ነው እሱ ያመነበትን
- እኮ አንስታችሁ ማን ነበር እያነሳ ለየሱፍ የሚሰጠው ?
- ያው ወደ እሱ አጠገብ ላይ ነን 3ታችንም በአንድ በኩል ነው የተቀመጥነው ያው ሲወጣ ያኛው አጠገቡ የተቀመጠው እንትን የስራው ባልደረባ እዚያ ቁጭ ያለው ወረቀቱን ለእሱ ይሰጠዋል እሱ ያያል ያነባል እሱ ያየዋል ይለየዋል ይለያል ለእኛ ይሰጠናል እኛ እንፈርማለን
- እሱ ያልፈረመበት ወረቀት አለ እንዴ ከእዚያ ውስጥ ?
- ያልፈረመበት ወረቀት የለም
- እርሶስ በሁሉም ወረቀት ላይ ፈርመዋል ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔም እንትን ያልኩት የለም
- በሁሉም ላይ ፈርመዋል እርሶ ?
- አዎ ሁሉም ላይ ፈርሜአለሁ
- ወረቀቱ በሚወጣበት ጊዜ በማስረጃነት የሚቀርብበት ስለመሆኑ አልተነገረውም አይደል ?
- አይ አራቡ ምንም የተጠረጠረው ነገር የለም እንደውም አንዳንድ ግልፅ ያልሆነ ነገር እንደውም መልሶ እራሱ እያነበበ እራሱ የሚፈርምበት ሁኔታ አለ እያነበበ
- እኮ ፖሊሱ ወይም ያ የስራ ባልደረባ ያሉት እዚያ እሱን አጠገቡ የነበረው ሰው ይሄ ሰነድ በማስረጃነት ይቀርብብሀል ብሎ አልነገረውም አይደል ?
- አይ ምንም የተናገረው ነገር የለም ቀጥታ በቃ ያለውን ሂደት ያው እኛ እያለን የተነጋገሩት ነገር ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ነው ሌላ ነገር
- አቶ የሱፍ ከየት እንደመጣ አያውቁም አይደል ?
- አላውቀውም
- ከእዚያ በኋላም ወዴት እንደተመለሰ አያውቁም ?
- አላውቅም እኛ ያው ወጣን /ግልፅ ያልሆነ/
- አቶ የሱፍን እርሶ እዚያ ከማየትዎ ውጪ አያውቁትም አይደል ?
- አላውቀውም
- ሰነዶቹ ላይ እንድትፈርሙ ሲደረግ ለእርሶም ሰነዶቹ አልተነበቡሎትም አይደል ?
- ለእኔ በቃ ሰነዶቹ እሱ የፈረመባቸው ለእኛ ፈረምን መጨረሻ ላይ
- እኮ አልተነበበላችሁም ለሁላችሁም ?
- አልተነበበልንም
- ከሀርድ ዲስኩ እና ከኮምፒዩተሩ ላይ ከታተመው ውጪ ሌላ ምንም ያያችሁት ነገር የለም አይደለም ?
- አዎ ሌላ ያየነው ነገር የለም
- በሌላም ሰነድ ከሌላ ሰነድ ላይም አልፈረማችሁም ?
- አልፈረምንም ያው እራሱ በፈረመበት ወረቀት ላይ ብቻ ነው



2340

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወረቀቶች ላይ ነው በሙሉ የፈረማችሁት ?
- አዎ
- ከወረቀት ውጪ ሌላ ምንም ነገር ላይ አልፈረማችሁም ?
- አልፈረምንም
- እርሶም አቶ ስንታየሁም የፈረማችሁበት ነገር የለም ?
- የለም በቃ በእዚያችው እሱ በፈረመበት ወረቀት ላይ ብቻ ነው ፊርማችንን ያሰፈርን
- ስትወጡ እርሶም አቶ ስንታየሁም አብራችሁ ነው የወጣችሁት ?
- አዎ ከበር ወጣን እሱም ወደ እራሱ አድራሻ ሄደ እኔም ወደ ራሴ
- አቶ መኮንን የሱፍን በእዚያን ቀን ለታዛቢነት በሄዱበት ቀን ብቻ ነው ያየሁት ብለዋል ቅድም ከእዚያ በፊት አያውቁትም ?
- አላውቀውም
- አሁን ግን በቀጥታ ያለምንም ችግር ነው እንግዲህ ከረጅም ጊዜ በኋላ እንዴት ሊያስታውሱት ቻሉ ?
- እንዴት ነው እኔ አሁን ቀኑ ያው በ 26/12/2004 ዓ.ም ነው ያው ታዛቢነት ሲኮን ያንን ነገር በራሴ ማስታወሻ መያዝ እንደሚገባኝ አውቃለሁ ቀኑን ወሩንም ሰዓቱንም ያንን ይገፔአለሁ ምክንያቱም ነገ የተጠየቁትን ነገር መመለስ ስላለብኝ ብዬ ስለማስብ ይሄንን ይገፔአለሁ
- አኬ ማስታወሻ ይዘዋል ?
- አዎ
- ግን አንድ ጊዜ ያዩትን ሰው አሁን መልኩን እንዴት ረጅም ጊዜ ነው ያዩት እንግዲህ 12ኛ ወር 2004 ነው አሁን እዚህ ችሎት ግን በቀላሉ ነው ከእዚሁ ሁሉ ሰው ለይተው ያወጡት ምንድን ነው በሲዲ እያጠኑት ነበር ወይስ እንዴት ነው ሊያስታውሱት የቻሉት ?
- እኔ በእርግጥ የራሴ ተፈጥሮ እንትን ነው እኔ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ያየሁትን ነገር የማስተዋል እና የመመልከት እንትን የራሴ እንትን ነው ስለዚህ ለእኔ ያየሁትን ነገር ስለሆነብኝ ሊሸሸግብኝ አልቻለም
- አሁን ለምስክርነት ከመምጣትዎ በፊት በሲዲ እንዲያጠኑት አልተደረጉም ?
- አልተደረገም



2341 191

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት
- ያው ተመልሷል
- ቅድም አቶ የሱፍ ፕሪንት ያደርግ ነበረ ሲሉ ነበር ?
- አዎ
- እስቲ እንዴት አድርጎ ፕሪንት ያደርግ ምን ማለት ነው ፕሪንት ያደርግ ነበር ያሉ ?
- በራሱ እጁ ኮምፒዩተሩን ነኛ መከፈት ለመከፈት ለማለት ነው እና ሂደቶቹን እራሱ ንብረቱ ነው በራሱ ላይ ነው ያሳየን ያው ከተላጠ በኋላ እራሱ ከፍቶ ነው እንደውም አንዳንድ ጊዜ እዚያ ላይ እራሱ በጣም እንትን አድርጎ የሚያወጣበት ነገር አለ እኔ ይሄንን ከልምዱም አኳያ እኔ ስለኮምፒዩተር እንትን ስለማልል የታዘብኩት ነገር ያው ቀደም ሲል የገለፅኩት ነው
- ማለት አቶ የሱፍ ፕሪንት አደረገ ሲሉ አሁን እዚህ ላለው ሰው እንዴት አድርጎ ነው ፕሪንት ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው ኮምፒዩተር ከፍቷል አሉ ላፕቶፕ ?
- ከፍቶ መጀመሪያ እራሱ የከፈተው ሀርድ ዲስኩንም በሀርድ ዲስኩም እራሱ ከፈተ በላፕቶፑ ላይ እራሱ ከፍቶ ነው ያሳየን
- አሳያችሁ ?
- አዎ
- እሱን ከፈተ እሱን ነግረውናል ችግር የለውም ከፈተ አሁን ፕሪንት አደረገ ሲሉ የሆነ ፕሪንተር ፕሪንት የሚያደርግ ማሽን አለ ቅድም ፕሪንተሩ የእሱም ነው ያሉት ?
- አዎ
- እሱ ደግሞ ላፕቶፑ ጋር ቁጭ ብሏል ስለዚህ አቶ የሱፍ ፕሪንት አደረገ ሲሉ ምን አደረገ ነው ?
- ለማውጣት ነው ወረቀቶችን
- እንዴት አድርጎ ፕሪንት አደረገ ?
- በቃ እራሱ በእዚህ በእንትኖቹ ላይ በኮምፒዩተሩ ውስጥ እንዲወጡ ወረቀቶችን ያው ከእዚያ ከፁሑፎቹ እንትን የሚሉትን እያቀነባበረ እራሱ ወረቀቶቹ ወጥተው እንዲነበቡ ያደረገ ለማለት ነው
- አቶ መኮንን አቶ ስንታየሁ ያውቁታል ጓደኛዎት ነው ?
- አይደለም



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትተዋወቃላችሁ ?
- አንተዋወቅም
- አቶ ስንታየሁም ነበረ ያሉት ታዲያ እንዴት አወቀው ነው ?
- አቶ ስንታየሁ ያው እዚያ መጀመሪያ ስንባ መጀመሪያ በወቀረቱ ላይ ስንታየሁ የእኔንም ስም ከታች እንፅፋለን ምስክር የነበርነውን እየለየሁ ነው እዚያ ላይ ያ ወረቀታቸውን ያየሁት እንጂ በማንኛውም ነገር ከእሳቸው ጋር አንተዋወቅም
- አቶ ስንታየሁ የራሱን ስም እና ሌላ የማንን ስም ፃፈ ?
- የራሱን ስም ይፅፋል ይፈርማል ቀን ይፅፋል ይፈርማል እኔም ቀን እፅፋለሁ እፈርማለሁ 2ታችን ታዛቢ ብለን ነው ከታች ስማችን የምናስቀምጠው
- ሌላ የእሱ ጓደኛ የሆነ ሰው ነበር እንዴ እዚያ ውስጥ ?
- የእዚያን ጊዜ እዚያ ነው
- የአቶ ስንታየሁ?
- አልነበረም
- እዚያ ከነበሩት ውስጥ ሌላ ከአቶ ስንታየሁ ውጪ የሚያውቁት ሰው ነበር ?
- አይ የለም የማውቀው ሰው የለኝም
- የለም የሚያውቁት አልነበረም ?
- አልነበረም
- አቶ ስንታየሁ ኮምፒዩተሩ ሲከፈት ላፕቶፑ ሲከፈት አብራችሁ ነበር ወይስ ከእዚያ በኋላ ነው የደረሰው ?
- አይ አንድ ላይ ነው ቁጭ ብለን 3ታችንም ባለንበት 1ኛው ያው የቢሮ እንትን የሆነ ሰው ባለበት ቁጭ ብለን ነው በታዛቢነት
- ከአቶ ስንታየሁ እና ከእርሶ ማን ነው ቀድሞ ?
- እኔ ነኝ የቀደምኩት
- እርሶ ናት ቀድመው የገቡት ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ድግግሞሽ ነው እሱን አስተካክሉ ድግግሞሽ ነው ቅድም ተጠይቆ ተመልሷል 3 ጊዜ ነው የመለሰት
- ቅድም ተጠይቀው ሲመልሱ ኮምፒዩተሩ ሀርድ ዲስኩ እና ፕሪንተሩ የየሱፍ ነው ብለዋል በምን አወቁ ?
- እራሱ የገለፀው ሁኔታ ነው እራሲ የሱፍ ይሄ የ 10ሺህ ብር ንብረቴ ነው የራሲ ነው ብሎ እራሱ ነው የገለፀው
- ምኑን ?
- ላፕቶፑ
- ላፕቶፑም ሀርድ ዲስኩም እሺ
- ሀርድዲስኩን ሳይሆን የገለፀው በመጀመሪያ ላቶፑን ነው ላቶፑ የራሱ ንብረት ብዙ ዓመት አብሮት የቆየ ንብረት መሆኑን እራሱ ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ጥሩ ላፕቶፑን የእሱ መሆኑን 10 ሺህ ብር የገዛሁት ነው ብሎ ሲናገር ሰሙ ?
- አዎ
- ፕሪንተሩን እና ሀርድዲስኩንስ በምን አወቁ ?
- እሱን ያው የራሱ ንብረት መሆኑ እራሱ እዚያው የገለፀው
- የእኔ ናቸው አለ 2ቱም ?
- እንጂ አልተናገረም እንደዚያ ብሎ
- እኮ የእኔ ናቸው አለ ሀርድ ዲስኩ እና ፕሪንተሩ የእኔ ናቸው አለ ?
- ላፕቶፑን ነው ላፕቶፑን ነው እዚያ ያለው ያኛውን ግን የራሱ ንብረት መሆኑን ያው ገልፆዋል ይሄኛውን ግን ይሄም የራሴ ንብረት ነው ብሎ አላለም ግን ያሉትን ነገር ግን የራሱ መሆኑን ግን እራሱ አምኖበት የተቀበለው ነው በቢሮ
- ከሁኔታው ላይ የተረዱት እርሶ 3ቱም ኮምፒዩተሩም ሀርድ ዲስኩም ፕሪንተሩም የእሱ መሆናቸውን ነው የተረዱት ?
- አዎ
- እርግጠኛ ኖት የእሱ ናቸው ብለው አምነዋል ?
- አዎ የራሱ ነው የራሱ መሆኑን



2344 194

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሱፍ የእዚያን ቀን ምን ዓይነት ልብስ ነበር የለበሰው ?
- የእስፖርት ቱታ ነበር ያደረገው
- የእስፖርት ቱታ እግሩን አይተውታል ?
- የእስፖርት ቱታ እንደወይን ጠጅ ዓይነት ነገር ነው
- እግሩን አይተውት ነበር ?
- እግሩን ያው ነጠላ ጫማ ነው ያደረገው
- ሲያነክስ ነበር ብለው
- እሱ ተጠይቋል
- የአቶ የሱፍ አሁን ቅድም ሲመልሱ ነፃ ሆኖ ነው ሲያስረዳ የነበረው ብለዋል ከመምጣትዎ እርሶ ከመግባትዎ በፊት አቶ የሱፍ የት እንደነበረ አያውቁም ?
- አላውቅም
- እና ከምምጣትዎ በፊት ጫና ይደረግበት አይደረግበት አያውቁም አይደል ?
- አዎ በፊት የነበረበትን ሁኔታ አላውቅም
- አቶ መኮንን ይሄ ሁሉ ነገር ተደረገ የሚሉበት ቦታ ማዕከላዊ ነው አይደል ?
- አዎ ማዕከላዊ
- ስንት ሆናችሁ ነበር የተቀመጣችሁት እዚያ አጠቃላይ እርሶ ስንታየሁ እና
- ተመልሷል እሱ
- ተደግሟል
- የላፕቶፑንም ሆነ የፕሪንተሩን ማርክ አይተዋል ስሙን ?
- አላየሁትም
- አያስታውሱትም ?
- አላስታውስም
- ቅድም በዐቃቤ ሕግ ሲጠየቁ የተፃፈው ቋንቋ እንግሊዘኛ ነው ብቻ ብለው ነበር ?
- አዎ
- እርግጠኛ ኖት አይደል በእዚህ ?



2345

195

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ እኔ እንዳየሁት እንግሊዘኛ ነው ያው አላነበብነውም እንግሊዘኛ ነው
- እኮ ከእዚህ ሌላ ከእንግሊዘኛው ሌላ የተፃፈ ነገር የለም ?
- የለም
- ቅድም የስራ ባልደረባዬ የስራ ባልደረባዬ እያሉ ይገልፁ ነበር ማን እንደሆነ ያውቃሉ እሱን ማን ነው የስራ ባልደረባዎ ?
- የእኔ የስራ ባልደረባዬ ያው እዚያ አካባቢ ላይ ሌላ ሙያ የሚሰራ ነው ክፍሌ ይባላል እሱ ጋር ነው የሄድኩት 5 ሰዓት ላይ በእዚያ በሄድኩበት እንትን ነው እሱ ከእነሱ ጋር ይተዋወቃል እኔ ግን አላውቃቸውም ያው በኋላ
- እኮ ፖሊስ ነው አይደል እዚያ ውስጥ ያለ ሰው ?
- አዎ ክፍሌ ይባላል አሁን በእሱ አማካይነት ነው እንደዚህ ዓይነት ምስክርነት ልትሆን ትችላህ ሲል እኔ ባላየሁት እንዴት ምስክር ብዬ ስጠይቀው አይደለም እንደዚህ ዓይነት ቁጭ ብለህ ሰውዬውም ባለበት አንተም ባለህበት እራሱ ባመነበት አይተህ የሕሊናህን እንትን የምትልበት ነው ሲለኝ ይሄማ ችግር የለውም ብዬ ነው የገባሁት
- ቅድም ቀኑን 26/12/04 መሆኑን የማስታወስ ችሎታ አለኝ ብለው ነበረ ይሄ 26/12/04 የሚለው ምን ቀን እንደዋለ ያውቃሉ ወይ የስራ ቀን ነበረ አልነበረም ?
- የስራ ቀን አልነበረም ይመስለኛል የስራ ቀን እርግጠኝነት እርግጠኛ አይደለሁም የስራ ቀን አይደለም
- ቅድም እርግጠኛ አይደሉም ቀኑን ?
- አዎ
- የሱፍ ጌታቸው ቅድም ፕሪንት ያደርገው የነበረው በፖሊሱ እየታዘዘ ነው አይደል ?
- ፖሊስ መሆኑን አላውቅም ሲቪል ነው የለበሰው
- እሺ ሲቪል የለበሰው ሰውዬ እያዘዘው ነው አይደል ፕሪንት የሚያደርግ የነበረው ?
- እሱ ዝም ብሎ ነው የሚመለከተው ንብረቱ የእሱ ነው በቃ ለእኛ አስተዋወቀን ከእሱ ጋር አስተዋወቀን የማስተዋወቅ ስራ ስራ ከእዚያ
- እኮ በራሱ ነበር ፕሪንት የሚያደርገው ሳይታዘዝ ወይስ እየታዘዘ ?
- አይ በቃ አሳያቸው ብሎት አለው አሳየ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መሣሪያውን አሳዩትሁ ላፕቶፕ እና ሀርድዲስኩን አሳየ ?
- አዎ
- ፕሪንተሩንም አሳዩትሁ ?
- አዎ
- ከእዚያ ወዲህ ፕሪንት ሲደረግ ታዞ ነው የሚያደርገው ወይስ በራሱ ነው የሚያደርገው ነው እያልኮት ያለው ?
- አይ በራሱ እጅ ነው የሚያደርገው ያው ታዞ ነው እዚያ አለ
- ታዞ ነበር አይደል ?
- አዎ እዚያ ቢሮ ውስጥ አለ በቃ አሳያቸው ተባለ እሺ አለ እራሱ እየከፈተ አሳየ
- ቅድም አቶ ክፍሌ ፖሊስ ነው ብለው ነበር ባልደረባዬ ?
- አዎ
- ልክ ነኝ ?
- አዎ ልክ ነው
- ስለዚህ እርሶ ፖሊስ ኖት ?
- አይ እኔ ፖሊስ አይደለሁም
- ጓደኛዎ ፈልገው ነው ?
- አዎ እኔ ፖሊስ አይደለሁም
- ቅድም ሲመልሱ ስራ ላይ እያለሁ ነው ብለው ነበር ስራ ላይ እያሉ ነው መጥተው ምስክርነት ታዛቢ እንዲሆኑ የተጠየቁት ?
- አይ ስራ ላይ አይደለሁም እኔ ከስራ ውጪ ነኝ
- ከስራ ውጪ እረፍት ላይ እያሉ ነው ?
- አዎ እኔ እረፍት ላይ ነኝ እኔ ለራሴ ጉዳይ ነው የሄድኩት በቦታው ላይ
- ምስክር እርሶ 5 ሰዓት ሄዱ ማዕከላዊ ደግሞ የስራ ሰዓት አለው እስከ የስራ ሰዓት 6 ሰዓት ወይም እንደዚህ ሊሆን ይችላል እና የሚቀጥለው የከሰዓት ስራ እስኪደርስ ድረስ እዚያ ምን ይሰሩ ነበር ?



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ እዚያ አልቆየሁም እኔ
- ይሄ ጥያቄ ተመልሷል ምናልባት ካላስታወሰት በስተቀር ተጠይቆ ከጠበቆች ተመልሷል
- ማለት እንትኑ 8 ሰዓት ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- 5 ሰዓት እዚያ ደርሼ ከእዚያ ተነግሮኝ እንደገና ሌላ ቦታ ከሌላ ቦታ ላይ ጊዜ አጥፍቼ ተመልሼ 8 ሰዓት /ግልፅ ያልሆነ/
- ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ
- ይኖረናል የተከበረው ፍ/ቤት አቶ መኮንን እስቲ እዚያ እንደሄዳችሁ የገባችሁበት ቅድም ስንጠይቆ ቢሮ ነው የገባነው ብለዋል በተከሣሽ ጠበቆች ሲጠየቁ ደግሞ እስር ቤት ይሁን ቢሮ ይሁን አይለይም ብለዋል ምን ምን አለ እዚያ ቢሮ ውስጥ እስቲ ምን ምንድን ነው ያለው ስለ ቢሮው ይንገሩን እስቲ ?
- እዚያ ቢሮ ውስጥ ያለው ኮምፒዩተር ነው ያለው ኮምፒዩተር እና
- ስንት ኮምፒዩተሮች አሉ ?
- ወደ 3 ኮምፒዩተሮች አሉ ጠረቤዛዎችም አሉ በቃ እና ስልኮች ናቸው ያሉት ቢሮ ውስጥ ነው የገባነው ቢሮ ውስጥ ነው
- እሺ ሌላው ላፕቶፕ ነበረ ብለውናል ይሄ ላፕቶፕ በእዚህ ላፕቶፕ ፕሪንት ተደርጓል ብለዋል እንዴት ነው ፕሪንት የተደረገው ?
- እራሱ ነው ያንን እንትን አስተካክሎ እራሱ
- ላፕቶፑ ከምን ጋር ተገናኝቶ ነው ?
- ከኮምፒዩተሩ ጋር ተገናኝቶ
- ከምኑ ጋር ?
- ከኮምፒዩተሩ ላይ አገናኝቶታል
- ምኑ ጋር ያለው ኮምፒዩተር ጋር ?
- ከራሳቸው እንትን ላይ ተሰክቷል
- ቢሮ የነበረው ማለት ነው ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ በእሱ ነው ነበር ፕሪንት ሲደረግ የነበረው ?
- አዎ
- የታሸገ ፕሪንተር ምናምን ብለው ነበር አሁን በተከሳሽ ጠበቃ ሲጠየቁ ተከሳሽ ንብረቱ ነው ብሎ ያሳየው እንደ ላፕቶፕ እና 2 ሀርድ ዲስክ ብቻ ነው በማለት መጀመሪያ ላይ ገልፀው ነበር ይሄ ፕሪንተር ከየት የመጣ ነው ?
- የራሴ ነው የራሱ ነው ንብረት መሆኑን እራሱ ላይ መጀመሪያ ታሽጓል
- ፕሪንተር ምን ዓይነት ነገር ነው ያውቃሉ ፕሪንተር ምን ዓይነት ነገር ነው ?
- ይሄ እንትኑ ዲስኩ ማለት ነው ይሄ እንትኗ ሀርድ ዲስኳ ማለት ነው
- ስለዚህ ፕሪንተር የሚሉን እርሶ ሀርድዲስኩን ነው ?
- አዎ
- ተገናኝቶ ግን ፕሪንት ሲደረግ የነበረው ጠረቤዛ ላይ በነበረ ነገር ነው ?
- አዎ ጠረቤዛ በነበረ ነው
- ሌላው የፈረምንባቸው ወረቀቶች ላይ ነው ብለዋል ?
- አዎ
- ሀርድ ዲስኩ እንዴት ነበር የተደረገው ?
- ያው ሀርድ ዲስኩ ያው ከላዩ ላይ ስም ተፅፏል
- ወደ ምን ተቀየረ ሀርድ ዲስኩ ?
- ወደ እንትን ላይ ወደ እንትን ከተቱት
- ወደ ምን ?
- ወደ ሲዲ ላይ ከእንትን ላይ ከተቱት
- ወደ ሲዲ ላይ ?
- አዎ
- እሺ ከእዚያ በሲዲ ከተቀየረ በኋላስ ሲዲው ላይ አልፈረማችሁም እንዴ ?
- ያው የሚወጣውን እያየን ያው የሚወጣው ወረቀቱ ነው የሚወጣው
- የሚወጣው ወረቀት ላይ ሳይሆን ወደ ሲዲ ከተቀየረ በኋላ ሲዲ ያውቃሉ አይደል ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ሲዲው ላይ አልፈረማችሁም ?
- አልፈረምንም ሲዲው ከሩ ላይ ፈርመናል ካሴቱ ላይ ፈርመናል
- ሲዲው ላይ ፈርማችዋል ?
- አዎ
- ሌላው እናንተ እዚያ የተገኛችሁት ለመታዘብ እንደሆነ ተነግሮታል አይደል ተከሣሹ ?
- አዎ
- ፕሪንት ሲያደርግ የነበረው እንዴት ነው ቅድም እራሱ በራሱ ፍቃድ እየከፈተ ፋይሎቹን ፕሪንት ሲያደርግ ነበር እየነካካ ብለዋል እያቀናበረ በሚል አማርኛ ነው የገለፁት አሁን በተከሣሾች ጠበቃ ሲጠየቁ ደግሞ ታዞ ነው ብለዋል ማን ነው የሚያዘው የነበረው ?
- አይ ቢሮ ውስጥ ያለው ቁጭ ያለው ሰው ያው የራሱ ንብረት መሆኑን ገለፀለት ከገለፀ እሱም አመነ
- አሳያቸው ማለት
- አሳያቸው ብሎ ነው ያሳየው በቃ ያ ሂደቱን እንዲያሳየን ነው
- እንጂ ይሄንን ፕሪንት አድርግ ይሄንን ፕሪንት አድርግ እየተባለ አልታዘዘም ?
- አልታዘዘም እራሱ ነው ያሳየን እራሱ ነው
- ሌላው እዚያ ማዕከላዊ ጎን ያለ ኮንስትራክሽን ሳይት አለ እዚያ ነው የምሰራው ብለዋል ?
- አዎ
- መጀመሪያ ለስራ ነበር የሄድኩት ብለዋል አይደል ?
- አዎ
- እስቲ እንዴት ነው ግልፅ አድርጉ እና አካሄዶትን ጓደኛዬ ጋር ምናምን እያሉ ትንሽ ግልፅ ያልሆነ ነገር ስላለ ለፍ/ቤቱ ግልፅ ?
- እኔ ጥበቃ ነው የምሰራው ጥበቃ ነው የምሰራው
- የት ?
- ጥበቃ ነው የድርጅት ጥበቃ ነው የምሰራው ይሄ ስራ ፍለጋ ነበር እኔ ወደ እዚያ የሄድኩት በቃ አዲስ ስራ ለመለወጥ ፈልጌ /ግልፅ ያልሆነ/ የምሰራው በአጋጣሚ እዚያው አካባቢ ላይ



http://ethcriminalawnetwork.com/

ሳይት እየተገነባ ነው እዚያ ለመጠየቅ ሄጄ በአጋጣሚ ይሄ የፌዴራል ፖሊስ እዚያ እኔ የማውቀው ነው ጠየቀኝ እንዲህ ዓይነት ታዛቢነት ብሎ ቢጠይቀኝ

- ከእዚያ በፊት ትተዋወቁ ነበር ከፖሊሱ ጋር ?
- አዎ አውቀዋለሁ
- ቢሮ ውስጥ ነበር እንዴ እሱ ፖሊስ ?
- አይ ውጪ ነበረ በሩ ላይ መግቢያው
- ሰነዶቹ ፕሪንት የተደረጉበት ቢሮዎች ውስጥ ያ ፖሊስ ነበረ ?
- አይ የለም
- እሺ ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እናመሰግናለን ጨርሰናል መመለስ ይችላሉ አንድ ምስክር
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ፍ/ቤቱ 57ኛ ተራ ቁጥር ላይ በዐቃቤ ሕግ ክስ ላይ ስንት ነው የመጀመሪያ ስምህን ብቻ ትናገራለህ
- 184ኛ ተራ ቁጥር ላይ ነው
- 184ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱት የመጀመሪያ ስምዎን የአባትዎን የአያትዎን ወይ አድራሻዎን ያለመናገር መብት አሎት ስምዎን ብቻ ይነግሩናል የመጀመሪያ ስምዎን ?
- በለጠ ታፈሰ
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- ለምስክርነት
- ማን በተከሰሰበት ነው እነ ማን በተከሰሱበት ነው ?
- ያሲን ኑር
- ማን በተከሰሰበት ?
- ያሲን ኑር
- ያሲን ኑሩ ?
- አቡበከር አለሙ ፣ መሐመድ አባተ
- በእነዚህ ነው ?



የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ያውቋቸዋል እነዚህ ሰዎች ?
- አዎ በእዚያ ወቅት በምስክር ላይ ነው እንጂ ከእዚያ በላይ አላውቃቸውም ከእዚያ በኋላ
- ፁብ ዝምድና አላችሁ ?
- የለንም
- ሊያሳዩን ይችላሉ ?
- አዎ
- እስቲ ያሳዩን እስቲ አንዴ አሳየን እስቲ እዚያው ቆመህ ምን እንደለበሰ ንገረን በልብሱ ሹራብ ምን ዓይነት ሹራብ ነጭ ሹራብ የት በፊት መስመር ነው በኋላ እዚያው ቆመህ ማሳየት ነው መንካት አያስፈልግም የለበሰውን የትኛው ነው ማን ነው ስምህ ስምህን ተናገር ፍ/ቤቱ ነው እያዘዘህ ያለ እኮ ስምህ ማን ነው እሺ ሌላውን አሳየን ሌላ አቡበከር ይሄ ማለት መህል ነው መጨረሻ እሱ ነው ማን ነው ስሙ እስቲ ተነስ ማን ነው ስምህ ሀሰን ማን ነው ማለት ስንተኛ ተከሣሽ ነህ ሌላ ተነስ ቁጭ በል መሐመድ ስንተኛ ተከሣሽ ነህ ምን አደረጉ ተብሎ ነው የተከሰሱት ምን አድርገው ነው የተከሰሱት ?
- በተለያዩ ሰነዶች ላይ የሆነ የሚፅፏቸው ኢሜል ላይ የተለያዩ ፁሑፎች ላይ በኢሜል እና በፓስወርድ ምናምን ፁሑፎች ለማንበብ አልቻልኩም ነበር በእዚያ ፁሑፎች ላይ ነው የተከሰሱት
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- እሺ አቶ በለጠ መቼ ነው የሚያውቋቸው አቶ ያሲን ኑሩ አቶ አቡበከር አለሙ አቶ መሐመድ አባተ ብለው ገልፀዋል ከመቼ ጀምሮ ነው የሚያውቋቸው ተከሣሾችን ?
- አዎ እኔ በወቅቱ በምስክርነት እዚያ አካባቢ ባለው /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክርነት ጊዜ ነው የማውቃቸው
- የት ነው ቦታው ?
- የፌዴራል ከፍተኛ ወንጀል ምርመራ
- ወንጀል ምርመራ ?
- አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- መቼ ነው ቀኑ ?
- የእነ ያሲን ኑር እና አቡበከር አለሙ 05/1/2005 መሐመድ አባተ ደግሞ ነሐሴ 26/2004
- እስቲ ስለያሲን ኑሩ እና አቡበከር አለሙ ልጠይቆት ለስንት ቀን ነው ያዩዋቸው እነዚህን ተከሣሾች ?
- ለአንድ ቀን ነው እዚያ በምስክርነት ቃል የሰጡ ጊዜ
- ለአንድ ቀን ብቻ ነው ያዩዋቸው ?
- አዎ
- ስለዚህ መልካቸውን እርግጠኛ ሆነው መናገር ይችላሉ እንዴ ?
- መልካቸውን አሁን ትንሽ ስለተመሳሰለብኝ አሁን ትንሽ የለየሁ መስሎኛል አሁንግን ተሳስቼአለሁ አሁን ለይቼአቸዋለሁ የማስተካከያ ነገር ቢሰጠኝ
- በድጋሚ ሊመርጧችሁ ይችላሉ ?
- አዎ
- ምናልባት ፍ/ቤቱ የሚፈቅድ ከሆነ
- ጨርሱ መጀመሪያ
- እሺ እስቲ መጀመሪያ ላይ በ2ቱ ተከሣሾች ላይ የጠቀሱት ቀን አለ በ 05/01/05 ያሉት እስቲ በእዚህ ቀን ምን ተከሰተ ?
- በ05/2005 ያው የተለያዩ ሰነዶች ፁሑፎች ያለበት ሰነድም /ግልፅ ያልሆነ/ እና ከእዚያ እሱ ላይ እያዩ የእነሱ መሆኑን ፊርማቸውን እያስፈረሙ ምስክሮች ያው እዚያው ስላለን የእነሱ ባወጡበት እነሱ በፈረሙበት እኛም እማኞች ነን
- ለምን ነበር እዚያ ቦታ የተገኙት እርሶ ?
- ያው ጉዳይ ነበረኝ በእዚያ አጋጣሚ እዚያ ተጠርቼ
- በእዚህ አጋጣሚ ምን እንዲሆኑ ተጠየቁ ?
- ያው ምስክርነት
- ምንድን ነው የሚመሰክሩት ?
- በላፕቶፕ እና ኢሜል ላይ ሲወጣ በማየት ማለት ነው
- 2 ተከሣሾች ላይ አንድ ላይ ነበሩ እንዴ ሲያወጡ የነበረው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- 2ተኛም አይ 1ኛው ለብቻ ነው አንደኛው ለብቻ
- እስቲ እየለዩ ስለያሲን ኑሩ ይንገሩን ስንት ሰዓት አካባቢ ነበር ያሲን ኑሩ ?
- ያሲን ኑሩ ያው በነገ ሆኖ የራሱን ላፕቶፕ ምናምን አለው የራሱ ኢሜሎች አሉ እሱን ለመክፈት እኔ የተለያዩ ሰነዶችን
- ለማን ላፕቶፕ ነበረ ?
- ያሲን ኑር
- የያሲን ኑሩ የት ነበር ይሄ ላፕቶፕ ?
- ላፕቶፑ ያው በፌዴራል ምርመራ ክፍል ነበር ከእዚያ ከእዚያ ወጥቶ
- ምርመራ ክፍል ?
- አዎ በኢግዚቢት ተይዞ ነበር ከእዚያ በራሱ ወጥቶ ከእዚያ እራሱ ነው የከፈተው ከእዚያ
- ሲከፍተው እንዴት ነው የከፈተው ?
- ያው በሚታይ ነገር ነው የከፈተው ያው ላፕቶፕ እንደሚከፈተው ሁሉም ኮምፒዩተር እንደዚያ ነው የከፈተው እና ሀርድ ዲስክ ነበረው በእሱ ኮፒ ተደርጎ ወጥቷል
- የማን ነው ሀርድዲስኩ ?
- የያሲን ኑር
- ምን ምን ዓይነት ሰነዶች ነው የተገኙት ?
- ለማስታወስ አልቻልኩም በርካታ ፁሑፎች ምናምን አላቸው
- ገፃቸው በግምት ምን ያህል ገፅ ይሆናል ያስታውሳሉ ?
- ፁሑፎቹን አላስታውሳቸውም ገፃቸውን
- ፁሑፎቹ ምን አጭር ፁሑፎች ናቸው መፅሐፍት ናቸው ምንድን ናቸው ?
- አይ የተለያዩ ሰነዶች በነጭ ሉክ አለ አይደል በእሱ ዓይነት ነው እንጂ /ግልፅ ያልሆነ/
- አርዕስት አለው ያ የወጣው ፁሑፍ ?
- አርዕስት አንዳንዶቹ አላቸው ግን ያው አርዕስቱን ለማየት አልቻልኩም
- ለምን ያህል ጊዜ ቆዩ ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ነበር እነዚህን ሰነዶች ሲያወጣ የነበረው ?
- 4 ሰዓት

ECLN

- ከጠዋቱ ነው አይደል ?
- ከጠዋቱ 4 ሰዓት
- እስከ ስንት ሰዓት ነበር ?
- እስከ 6 ሰዓት አካባቢ ላይ
- ሌላ ከእርሶ ጋር ሰው ነበር እዚያ ቦታ ?
- ከእኔ ጋር አንድ ልጅ ነበር ምስክርነት እሱም አለ
- ምን ዓይነት ክፍል ነበር የገባችሁት ?
- አይቲ ክፍል የወንጀል ምርመራ /ግልፅ ያልሆነ/
- አይቲ ክፍል ማለት ምን ዓይነት ክፍል ነው እስቲ ?
- የሆነ ጠባብ የሆነ የአይቲ ክፍል የሆነ
- ምን አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል ነው ?
- የአይቲ አገልግሎት እነዚህ ምርመራ
- አይቲ የሚለውን ቃል በአማርኛ ሊገልፁ ይችላሉ ?
- ያው ኮምፒዩተር ምናምን የሚታይበት
- ቢሮ ውስጥ ሌሎች ኮምፒዩተሮች ነበሩ ?
- ሌሎች ኮምፒዩተሮች ያው በእሱ ብቻ የሚጠቀምበት ነበር የራሱ የሚወጣበት ኢሜል
- አንድ ላፕቶፕ አለ ብለውናል ?
- አዎ ላፕቶፑ ያው ከእሱ ሌላ ከላፕቶፑ ሌላ ተጨማሪ ነው ኮምፒዩተሩ
- ሌሎች ኮምፒዩተሮች ነበሩ ?
- አዎ አንድ ኮምፒዩተር ነበረ
- ምን አደረገ ከእዚያ ?
- በእዚያን ጊዜ ያው የራሱን ኢሜል ምናምን አወጣ ከእዚያ በኋላ በኮምፒዩተር ፕሪንት ተደረገ እያየ
- የእሱ ኢሜል መሆኑን አወቁ እርሶ ?

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው እራሱ ፓስወርድ አውጥቶ እራሱ ስለከፈተ እና እራሱ ደግሞ ስለፈረመበት የራሱ መሆኑን በዕኑ ሰነ ምግባር እና የራሱ እያመነ የፈረመበት
- ሰው ያሲን ኑሩ መሆኑን በምን አወቁ ?
- ያው የእዚያኑ የፈረመበት ሲፈርም ሰውን እና ፊርማውን ነው የሚያስቀምጠው
- ከእዚያ በፊት አልተዋወቃችሁም ማለት እዚያው ቢሮ ውስጥ መርማሪው አላስተዋወቃችሁም?
- አላስተዋወቀንም
- እናንተስ እዚያ ለምን ነበር የተገኛችሁት ?
- የሆነ ጉዳይ ነበር በእዚያ አጋጣሚ
- አይ እዚያች ቢሮ ውስጥ ከጉዳዩ በኋላ ለምን ነበር የተገኛችሁት ?
- ከየት ቢሮ
- እዚያ ቢሮ ውስጥ እሱ ፕሪንት ሲያደርግ ለምን ነበር እዚያ ቢሮ እንድትገቡ የተፈለጋችሁት ለምንድን ነው የገባችሁት ?
- ለማየት ታዛቢነት
- ታዛቢ መሆናችሁን ተከሣሽ ያውቃል ?
- ታዛቢ መሆናችንን አዎ
- ምን ተብሎ ተነገረው ?
- ያው ታዛቢዎች ናቸው ታዛቢ ባለበት የምትከፍተው ተብሎ ከእዚያ ተናግሮት
- እሺ እንዴት ነበር ሲያወጣ የነበረው ሰነዱን ማን እየነገረው ነበር ?
- እራሱ እያወጣ ነው እንጂ ማንም አልነገረውም
- በምን ቋንቋ ነበር የተፃፉት ሰነዶቹ ?
- በአረብኛ እና በእግሊዘኛ የተፃፉት ፁሑፎች ናቸው ፎቶ ግራፎች
- ሌላስ ?
- ፎቶግራፎች ምናምን ያላቸው ፁሑፎች አሉ ፎቶግራፍ /ግልፅ ያልሆነ/ አለበት
- እነዚህ ሁሉም ነው ፕሪንት የተደረጉት ?
- አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁሉንም ሰነዶች እናንተ አይታችዋል ?
- አዎ ሁሉም ሰነድ ላይ ያው ሰው እየፈረመ ያወጣው ላይ እኛ ታዛቢ ሆነን እየፈረምንበት ነው
- ሌሎችስ እነዚህ ሀርድዲስኮች ካላችሁቸው ውስጥ ምን ወጣ ከእዚያስ ምን ተገኘ ?
- ሀርድዲስክ ያው አንድ የተለያዩ ምስሎች ያለበት ያው እንትኑ አላስታውሰውም እና
- ምስሉ ማለት ፎቶ ነው ወይስ ተንቀሳቃሽ /ግልፅ ያልሆነ/?
- ተንቀሳቃሽ ምስል ቪዲዮ ምናምን የተቀረፀ ነገር ነው
- የተቀረፀ ቪዲዮ ነበር ነው እያሉን ያለው የተፀረፀ ቪዲዮ ነበረው ?
- አዎ
- ምን የሚል ቪዲዮ ነው ?
- እሱን አላየሁትም ምን እንደሚል ያው ረስቼዋለሁ ረጅም ጊዜ ስለሆነው ለማስታወስ አልቻልኩም
- ከእዚያ በኋላ ተከሣሾቹን አይተዋቸው አያውቁም ?
- አዎ ከእዚያ በኋላ አይቼአቸው አላውቅም
- ስለአበቡከር አለሙ ይንገሩን ?
- አቡበከር አለሙ ያው በካሴት በቪዲዮ ካሴት የተለያዩ ሰዎችን እጃቸው የተሰበረ ጭንቅላታቸው የተፈነከተ ምናምን በጨርቅ ጠቅልሎ ያው እነሱን ምስሎችን በመቅረፅ ያለውን ምስል ነው ያየሁት
- ከምን ውስጥ ነው የወጣው ይሄ ከእሱስ ?
- ከቪዲዮ ካሜራ
- ከቪዲዮ ካሜራ ?
- አዎ
- ወደ ምን ተቀየረ የቪዲዮ ካሜራ ውስጥ የነበረው ምስል ?
- ወደ ካሴት
- ምን ዓይነት ካሴት ?
- ሚኒዲቪ የሚል ካሴት አለች ትንሽዋ ወደ እሷ ካሴት ያው የተቀረፀ ነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያው ካሴት ውስጥ ቪዲዮ ካሜራ ውስጥ እንዳለ ነው ያያችሁት ወይስ ?
- አዎ
- ወደ ኮምፒዩተር ተቀይሯል ?
- አይ አልተቀየረም ወደ ኮምፒዩተር ሳይቀየር እዚያው ካሜራ ውስጥ ሆኖ ነው ያየነው
- እሱንስ ምን አደረጋችሁ ?
- እሱን ያው እሱም ባለበት አቡበከር አለሙ ከእዚያ እሱ ባለበት እራሱ በተገኘበት ከፈተ ከእዚያ ምስሎችን አየን ?
- ምን ምን ይል ነበር ምስሎቹ የሆነ ሌላ ነገር የላቸውም ?
- ሌላ ነገር የላቸውም ምስል ብቻ ነው ያየነው
- ስንት ካሴት ነበር ?
- አንድ ካሴት
- ከእዚህ ውጪ ሌላ ነገር የለም ?
- የለውም አዎ
- የሱስ ስንት ሰዓት ነው የተካሄደው ?
- የእሱ ያው 4 ሰዓት ነው
- ቅድም የያሲን ኑሩ ከ 4 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ብለውናል እና የሁሉንም ለማለት ነው ?
- አዎ ያው የእሱን
- ቅድሚያ የማንን ነው ያዩት ?
- ያሲን ኑሩ
- ስንት ሰዓት አበቃ ያሲን ኑሩ ?
- ያሲን ኑሩ 6 ሰዓት አበቃ
- ከእዚያስ ?
- ከእዚያ በመሀል ግን ያሲን ኑሩ እያለ የአቡበከር አለሙን ከእዚያ እሱን አየነው
- እዚያው ቢሮ ውስጥ ነው ?
- እዚያው ቢሮ ውስጥ አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የያሰ.ን ካለቀ በኋላ ነው ወይስ እየታየ እያለ ?
- አይ ያሰ.ን ኑር ካለቀ በኋላ ሳይሆን ግማሹ ላይ ያው አረዳ እያለቀ ነው
- የእሱስ ምን ያህል ጊዜ ፈጀ ?
- አይ የተወሰኑች ደቂቃ ነች የአበበከር አለሙ የሆነች የ 10 ደቂቃ የ 15 ደቂቃ ያህል ነች
- መሐመድ አባተ በማለት የገለፁት ሰው አለ እና ስለእሱ እስቲ ይንገሩን ?
- መሐመድ አባተ ያው የተለያዩ ሰነዶች ያወጣቸው በራሱ ፓስወርድ እና በራሱ ኮምፒዩተር ላይ ፓስወርዱን እራሱ
- ኮምፒዩተሩ የማን ነው የራሱ ኮምፒዩተር ነው ?
- አይ የምርመራ ወንጀል ምርመራ ክፍል የራሱ ፓወስረድ አለው በፓስወርድ እራሱ እየከፈተ ሰነዶቹን ፕሪንት እያደረገ እራሱ አምኖ እራሱ እየፈረመበት
- እስቲ ቆይ ላቋርጦት እና ኮምፒዩተሩ የወንጀል ምርመራ ነው ብለውናል ?
- አዎ
- በእዚህ ኮምፒዩተር ምንድን ነው የራሱን ከፈተ የሚሉት ?
- የራሱ ቁጥሮች አሉት የመክፈቻ የራሱ ፓስወርድ የሚጠቀምባቸው ማለት ነው ኢሜል
- ኢሜል ?
- አዎ እሱን ቁጥር በመንካት እራሱ ነው የከፈተው
- ኢንተርኔት ነው የተጠቀመው ማለት ነው ?
- አዎ
- ከእዚያስ ?
- ከእዚያ የተለያዩ ሰነዶች ምናምን አሉ ፕሪንት የሚደረጉ
- ምን የሚል ሰነዶች ተገኝተዋል ?
- እነሱ ፁሑፋቸውን ያው ኦሮምኛ ምናምን አንዳንድ እንግሊዘኛ ምናምን ስላለ ብዙም አላወኩትም
- ያላወቁት ነው ይሄ ኦሮምኛ እና እንግሊዘኛ የሚሉት ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ ውጪ ሌላ ሰነድ የለም ?
- ከእዚያ ውጪ ሌላ ሰነድ አላየሁም
- ሁሉም የተገፈው በኦሮምኛ እና በእንግሊዘኛ ነው በአማርኛ የተገፈ የለም ?
- በአማርኛ የተገፈ እና የተወሰኑ አሉ ግን ለማስታወስ አልቻልኩም እንጂ የተወሰኑ ትንሽ አይቼአለሁ
- የእሱ ስንት ሰዓት ተጠናቀቀ በተመሳሳይ ነበር የቀጠለው በአንድ ሂደት ላይ ?
- የእሱ ነሐሴ 26 ነው ነሐሴ 26/12/2004 በ 4 ሰዓት ጀምሮ ነው
- ስንት ሰዓት ?
- 4 ሰዓት
- መቼ ነው ቀኑ ?
- ነሐሴ 26
- ነሐሴ 26/12/2004
- ምን ምን እስቲ እንዴት ነበር ሲያሳዩ የነበረው ?
- ያው ኮምፒዩተሩን
- ምንድን ነው የታዘባችሁት ማለት ?
- የታዘብነው ያው የተለያዩ ሰነዶችን እራሱ ከፍቶ እራሱ ደግሞ እየወጣ ከእዚያ እራሱ እያየ ቼክ እያደረገ እየፈረመበት ከእዚያ የራሱ የተለያዩ ፁሑፎች አሉት እነሱ ላይ ያው እኛም እየፈረምን እሱም ያው እያነበባቸው ከራሱ
- ከእናንተ ጋር ይነጋገሩ ነበር ተከሣሾች ?
- አይነጋገሩም ኧረ
- ምንም ነገር አይነጋገሩም ?
- አዎ
- ምን ምን እያሉ ነበሩ ሲያሳዩዋቸው የነበረው ሰነዶቹን ?
- ሰነዶቹን ያው የተለያዩ ፁሑፎች ነው ይዘት ያላቸው እነሱ ላይ ያው እያወጣ የራሱ እየፈረመበት ከእዚያ እኛም ታዛቢ ሆነን በታዛቢነት እሱ ከፈረመበት በኋላ ነው እኛ የምንፈርመው ያየነውን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይበቃኛል
- የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- አቶ በለጠ እርሶ ወደ ፖሊስ ጣቢያው የሄዱት በግል ጉዳዮ ነው ?
- አቤት
- ወደ ፖሊስ ወደ ማዕከላዊ ፖሊስ ጣቢያ የሄዱት በግል ጉዳዮ ነው ወይ ?
- አዎ በግል ጉዳዬ ነው
- ስንት ቀን ነው የሄዱት ?
- የሄድኩት ያው 2 ቀን ነው የሄድኩት ነሐሴ 26 እና መስከረም ላይ 2005
- በእነዚህ በ2ቱ ቀኖች እንዲመጡ ተነግሮት ነው የሄዱት ?
- አይደለም ኧረ
- እሺ ነሐሴ 26 አንዱ ነሐሴ 26 ነው ሌላው መስከረም 5 ነው ?
- አዎ
- 2ቱን ቀን እንዴት በእዚህ ዓይነት ጉዳይ ሆነ ብዬ ነው ?
- ያው እነዚያን የሆነ ጉዳይ ነበረኝ በእዚህ አጋጣሚ ከእዚያ በእዚያው ታዛቢነት እንድሆን ከእዚያ ተነግሮኝ ከእዚያ በፍቃደኝነት ነው
- የስራ ቀን ነበር አይደል 2ቱም ቀን ?
- የ2ቱም ቀን አዎ
- የስራ ቀን ማለት ከሰኞ እስከ አርብ ባለ ቀን ማለት ነው ?
- ከሰኞ እስከ አዎ ሜይቢ ቀኖቹን ላስታውስ አልቻልኩም
- ለግል ጉዳዮ ስለሆነ የሄዱት ከጉዳዮ አንፃር ያስታውሱታል ሰኞ ወይም ማክሰኞ መሆኑን ባያስታውሱም ከሰኞ አርብ ባለው የስራ ቀን መሆኑን ግን ያስታውሳሉ ?
- እኔ እንጃ ትዝ አይለኝም ያው ረጅም ቀን ስለሆነ ቀኖቹን ለማስታወስ ትንሽ
- የሄዱበት ጉዳይ ከስራ ጋር የተያያዘ ጉዳይ አይደለም እዚያ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ?
- አይደለም
- አይደለም ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እስቲ መጀመሪያ የኃለሰ. 26ቱን ልጠይቆት ኃለሰ. 26 ሲሄዱ ስንት ሰዓት ነው የገቡት ኃለሰ. ስንት ሰዓት ነው ወደ ቢሮ የገቡት ?
- ኃለሰ. 26 ያው 4 ሰዓት ላይ ነው የቀረበው እሱ ከእዚያ በእዚያ ቀን ላይ ነው ምስክርነት የታዘበኩት
- እርሶ ያኔ የት ነበሩ ?
- እኔ እዚያው አካባቢ ለግል ጉዳይ ነበርኩ ከእዚያ በእዚያው
- እዚያው ግቢ ውስጥ ማለት ነው ?
- አይ ወጣ ከግቢው ወጣ ብሏል ትንሽ አይራራቅም ብዙም
- ከግቢ ከፌደራል ፖሊስ ከማዕከላዊ ፖሊስ ከግቢ ውጪ ነበሩ ?
- አዎ
- እርሶን ማን ጠራዎት ታዲያ ?
- እኔ ያው በአጋጣሚ ለራሴ ጉዳይ  እዚያው አካባቢ እኔ ስለምቀሳቀስ
- እኮ ማን ጠራዎት ነው ?
- አይ እሱ ማንም አልጠራኝም ግን እዚያው አካባቢ ለግል ጉዳይ ላይ ስንቀሳቀስ ከእዚያ ለምስክርነት እንደሆነ /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚያ
- እኮ ለምስክር ይፈለጋሉ ያሎት ማን ነው እኮ ነው የምሎት ?
- ለምስክርነት ያው በውስጥ በገባሁ ጊዜ እዚያው አካባቢ ነበርኩኝ ከእዚያ ወደ ውስጥ ገብቼ ከእዚያ ምስክር እንድሆን ያው በራሴ ፍቃደኝነት /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ እርሶ እዚያ በሚገቡበት ጊዜ የት ክፍል ነው የሄዳችሁት መጀመሪያ ወዴት ክፍል ነው የሄዳችሁት ?
- ወደ አይቲ ክፍል አይቲ የወንጀል ምርመራ አይቲ ክፍል
- አይቲ ክፍል መሆኑን እርሶ እንዴት አወቁ ?
- ያው በሩ ላይ የሆነ ፅሁፍ አለ /ግልፅ ያልሆነ/ ኤ ተብሎ ከእዚያ የኮምፒዩተር ምናምን አይቲ ክፍል መሆኑን ያው ምግረ ቃል ስለመሰለኝ
- ፖሊሱ እርሶ ጠርቶት ወደ ግቢው ከግቢ ውስጥ ነው ጠርቶት የገቡት አይደል ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፖሊሱ
- ወደ አይቲ ክፍል የወሰዶት ፖሊስ ጠርቶት ነው ከእዚያው ከግቢ ውስጥ ?
- አዎ
- ነሐሴ 26 ግን ቅዳሜ ቀን ነበር ግቢ ውስጥ መግባት አይቻልም እንዴት ገቡ እርሶ ነሐሴ 26 ማለት ቅዳሜ ቀን ነው በእዚህ ቀን ደግሞ ፌዴራል ፖሊስ ግቢ ውስጥ መግባት አይቻልም እርሶ በምን ሁኔታ ገቡ ?
- ያው እኔ በምስክርነት ያው ለታዛቢነት ተጠርቼ በእዚያ ጋር ሳልፍ
- እኮ ግቢ ውስጥ ከገቡ በኋላ ነዋ መጀመሪያ ግቢ ውስጥ ገብቼ ነው ፖሊስ ጠርቶኝ ገባሁ ያሉት?
- አዎ
- ነሐሴ 26 ቅዳሜ ቀን ስለሆነ ግቢ ውስጥ ፌዴራል ፖሊስ ግቢ ውስጥ መግባት አይቻልም ?
- አዎ
- እርሶ እንዴት ገቡ ነው ጥያቄው ?
- ያው ታዛቢነት ለመሆን ለመመስከር ያው ለእንትን ነው ለእዚያ ነው
- በኋላ ከምንመለስ የፌዴራል ፖሊስ ግቢ ውስጥ የገባኸው ተጠርተህ ነው ወይስ በራስህ ነው ግቢ ውስጥ የገባኸው ?
- አይ እሱማ ተጠርቼ ነው
- ግቢ ውስጥ የገባኸው ተጠርተህ ነው ?
- አዎ
- ወደ ምርመራ ክፍል ሳይሆን ግቢ ውስጥ ?
- አዎ ወደ ምርመራ ክፍል የገባሁት ማለት ነው
- ምርመራ ክፍል ሳይሆን የፖሊስ ግቢ ውስጥ የገባኸው ተጠርተህ ነው ወይስ በራስህ ?
- አይሱማ ታዛቢ ለመሆን ያው ተጠርቼ ነው ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ተጠርቼ ነው
- ተጠርተህ ነው ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የጠራዎት ማን ነው ?
- ያው ለማስታወስ ትንሽ /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ከእዚያ አይተ ከፍሉ አይተ ይላል ብለዋል እዚያ እርሶ እዚያ ሲገቡ መሐመድ አባተ እቤት ውስጥ ነበረ ክፍል ውስጥ ነበር ?
- እዚያ ቤት ውስጥ ቤት ውስጥ አዎ /ግልፅ ያልሆነ/
- ነበር ውስጥ ነበር ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእርሶ ሌላ ማን ነበር አብሮ እዚያ ውስጥ ?
- አንድ እንደዚሁ ከእኔ ጋር ታዛቢ የነበረ አለ
- ማን የሚባል ነው እሱ ?
- እሱ ኤልያስ
- አልያስ የሚባል ?
- አዎ
- እሱም እዚያ ነበር ?
- አይ ከእኔ ጋር አብሮ ነበር
- እኮ 2ታችሁ እዚያ ክፍል ውስጥ ገብታችዋል ?
- አዎ
- እናንተ ስትገቡ መሐመድ አልነበረም ክፍል ውስጥ ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላ ከየት መጣ መሐመድ ከየት መጣ መሐመድ ?
- አይ መጀመሪያውኑ እኔ እሱ ነበር እዚያ ከእዚያ በኋላ /ግልፅ ያልሆነ/ ባለበት ከእዚያ እኛ ገባን
- ይኸውሎት አቶ በለጠ ጥያቄውን ቀስ ብለው አዳምጠው ቀስ ብለው ይመልሱልን የሚያስጨንቅ ነገር የለውም እንትን ሲሉ እኛንም ያስቸግሩናል እርሶ ሲገቡ ማን ነበር ክፍል ውስጥ ?
- መሐመድ አባተ



2364

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ብቻውን ነው የነበረው ?
- የወንጀል ምርመራ የሚያደርጉ ነበሩ
- ምንኖች ነበሩ ፖሊሶች ነበሩ ?
- ፖሊሶች አዎ
- ስንት ፖሊሶች ነበሩ ?
- 2
- 2 ፖሊሶች ?
- አዎ
- እናንተ እሱ እዚያ ገብቶ ቁጭ ብሎ ነው ያገኛችሁት ?
- አዎ
- ከየት እንደመጣ እዚያ ጋር እንደተቀመጠ አያውቁም ?
- ተጠርጣሪ ሆኖ ተይዞ እንደመጣ የሚታወቅ ነው
- እኮ ከየት እንደመጣ ያውቃሉ እርሶ ?
- ከየት እንደመጣ አላወኩም
- አቶ ኤሊያስ ነው ያሏቸው አብረውት የነበሩት ሰው እሳቸውም አብረውት ነው የገቡት ከእርሶ ጋር ?
- አዎ አንድ ላይ ነው የገባነው
- አብራችሁ ነው የገባችሁት ?
- አዎ
- ስለዚህ 2ታችሁም ተከሣሽ ከየት እንደመጣ አላያችሁም ?
- አዎ
- እዚያ ክፍል ውስጥም በምን ሁኔታ እንደተቀመጠም አላያችሁም ?
- አዎ
- እዚያ ክፍል ውስጥ መቼ ገብቶም ተቀምጦ እንደነበር አላያችሁም ?

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ያው በምርመራ ወንጀል ምርመራ ክፍል ስለሆነ ያው በተጠርጣሪ በእዚያው ወቅት ነው ያየነው
- ተከሣሽ ከእዚያ በፊት እዚያ ጋር መጥቶ እንዲቀመጥ የተደረገው ለምን እንደሆነም አያውቁም እርሶ ?
- አቤት
- እዚያ መጥቶ እንዲቀመጥ የተደረገው ለምን እንደሆነም አያውቁም ?
- የእዚያኔ የተቀመጠው ያው በራሱ ሰነዶች ላይ የተለያዩ ሰነዶችን አውጥቶ በምስክር ፊት እንዲከፍት እና የተለያዩ ሰነዶችን እንዲፈርምበት ከእዚያ እኛ ደግሞ እማኞች ሆነን እንደምስክርነት ተጠርተን ስለሆነ ለእዚያ ነው
- እሱን እንዴት አወቁ እርሶ ?
- ያው በራሱ በተናገረው
- ማን ነው የተናገረው ፖሊሱ ነው የተናገረው ወይስ ተከሣሹ እራሱ ?
- አይ እራሱ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል ያው እነሱ ምስክሮች ናቸው እነሱ ታዛቢዎች ናቸው ከእዚያ በራሱ ኢሜል ላይ እያወጣ ሰነዶች ላይ እየፈረመበት ከእዚያ በነፃ ምንም ጫና ሳይደረግበት እየፈረመ ታዛቢዎች ደግሞ እየፈረማችሁ አስቀምጡ ተብሎ ነው
- አሁን እርሶ ያዩት እዚያ ፕሪንት አድርግ ተብሎ ፕሪንት ሲያደርግ ነው ያዩት ኢሜሉን ከፍቶ ፕሪንት ሲያደርግ ነው ያዩት ?
- አዎ
- ኢሜሉ የተከፈተው የተከሣሽ የራሱ ኢሜል ይሁን ወይም ሌላ ኢሜል ይሁን የሚያውቁት ነገር አለ እርሶ ?
- ያው በራሱ ኢሜል እየተከፈተ ነው ያው እዚያው ስለሆነ የራሱ ቁጥሮች አሉት መሰለኝ ያው
- እኮ ሲከፈት ነው እንጂ የራሱን ኢሜል ይክፈት የሌላ ሰው ኢሜል ይክፈት እርሶ የሚያውቁት ነገር የለም ?
- ያው የራሱ ፁሑፎች አሉት ስሞች ምናምን እና በእዚያው ነው በራሱ ኢሜል ላይ ነው እንደተከፈተ ነው
- ሰነዶቹን ቅድም ሲመሰክሩ አላየዋቸውም ይዘታቸውን አላየሁትም ብለዋል ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ የራሱን ኢሜል መሆኑን ያው በራሱ ቁጥር አናይ እና የራሱን መሆኑን እያረጋገጠ ስሙን ዕርበታል
- እኮ እዩ እሱ ሰነዱ የእኔ ነው ብሎ ሲፈርም አይተዋል ?
- አዎ የራሴ ነው ብሎ ሲፈርም አይቼአለሁ
- እኮ የተከፈተው ሰነዱንም አላየሁትም ይዘቱን አላየሁትም ብለዋል ቅድም ?
- አዎ
- ስለዚህ የእሱ ኢሜል የራሱ ኢሜል ይሁን የሌላ ሰው ኢሜል ይሁን የከፈተው እሱ ?
- አዎ ከከፈተ በኋላ ኢሜሉን ከከፈተ በኋላ ፕሪንት ሲወጣ አይቶት ከእዚያ ከራሱ ኢሜል እንደተገኘ እራሱ ስሙን እየፃፈ ከእዚያ እየፈረመ ስላየሁት ነው
- ሰነዶቹ ላይ እንድትፈርሙ ከመደረጉ በፊት እሱ ኢሜሉን እንዲከፍት ከመደረጉ በፊት ይሄ ሰነድ ከኢሜሉ የሚያወጣው ሰነድ በማስረጃ የሚቀርብበት ስለመሆኑ አልተነገረውም አይደል?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አልተነገረውም ?
- አዎ
- ከሰነዶቹ ከወጡ በኋላ እንድትፈርሙበት ሲደረግ ሰነዱ አልተነበበላችሁም ለእናንተም ?
- አልተነበበልንም ያው ፁሑፎቹን የኦሮምኛ ምናምን ስለሆኑ እሱን ትንሽ ለማንበቡም /ግልፅ ያልሆነ/ እንትን የለንም ያው አላወቅነውም ግን የተለያዩ ይዘቶች ምናምን ስለሆኑ
- ጥያቄው እኮ አጭር ነው አልተነበበላችሁም ?
- አዎ
- ከእዚያ ደግሞ መስከረም 5 ደግሞ ሲሄዱ በያሲን ኑሩ እና ያሲን ኑሩ ላፕቶፑን ከፍቶ ፕሪንት ሲያደርግ አይቼአለሁ ብለዋል እሱም ጋር ?
- አዎ
- የእዚያን ቀን እዚያ የሄዱት ለምንድን ነበር መስከረም 5 ?
- መስከረም 5 ምን ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- መስከረም 5 ቀን 2005 ዓ.ም እዚያ ፖሊስ ጣቢያ የሄዱበት ማዕከላዊ ፖሊስ ጣቢያ የሄዱት እርሶስ ለምንድን ነበር ?
- በእዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ያው የራሴ እዚያው አካባቢ ስለሆንኩ የራሴ የግል ስራ ስላለ በእዚያው ስተላለፍ ነው በእዚህን ቀን አጋጣሚ ሆኖ እንትን ያልኩት
- የእዚያን ዕለታስ የጠራዎት ፖሊስ ማን ነው ፖሊስ ጠርቶዎት ነው የገቡት የእዚያኑ ዕለት ?
- የእዚያን ቀን ፖሊስ ጠርቶኝ ነው አዎ
- አስቀድሞ አልተነገሮትም ቀኑ ?
- አስቀድሞ አልተነገረኝም
- ይሄንን ቀን ቅዳሜ ነበር ግቢ ውስጥ አልገቡም ነበር እርሶ ሲጠሩ ይሄም ቀን መስከረም 5 የምሎት ቅዳሜ ቀን ነው የነበረው ?
- አዎ
- የእዚያን ዕለት እርሶስ ግቢ ውስጥ ገብተው ነበር ?
- ግቢ ውስጥ አልገባሁም
- ከመጠራትዎ በፊት ማለቴ ነው ?
- አይ ከመጠራቴ በፊት አልገባሁም
- ከውጪ ተጠርተው ነው የገቡት ?
- አዎ
- በስንት ሰዓት ነው የገቡት በእዚስ ቀን ?
- በእዚህ ቀን 4 ሰዓት
- የእዚያን ዕለትስ የገቡት እዚያው መጀመሪያ ነሐሴ 26 ቀን ገብተው የነበሩበት ክፍል ነው ?
- ነሐሴ 26 ምን
- ቅድም ስለመሐመድ አባተ ሲያስረዱ ነሐሴ 26 አይ ቲ የሚል ክፍል ውስጥ ገብቼ ነበር ብለዋል?
- እሺ
- እዚያው ክፍል ውስጥ ነው አሁንም ድጋሚ የገቡት ወይስ ሌላ ክፍል ነው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዩ እዚያው ክፍል ውስጥ ነው
- እዚያው ክፍል ውስጥ ነው ?
- አዎ
- እዚያ ክፍል በሚገቡበት ጊዜ ያሲን ኑሩ ነበረ እዚያ ?
- ያሲን ኑሩ አይ ያሲን ኑሩ ያው ከእኛ ከመግባታችን በፊት ያው ስለነበረ ከእዚያ እዚያው ቁጭ ብሎ ከእዚያ እኛ ታዛቢዎች ገባን
- እሱ እዚያ ቁጭ ብሎ ነው ያገኙት ?
- አዎ
- አቡበከር አለሙስ እዚያው ነበር እሱም ?
- አቡበከር አለሙ ደግሞ ያው ከውጪ ተጠርቶ ማረፊያ የት ቦታ እንደሆነ አላወኩትም እኛ ውስጥ ነበርን ተጠርቶ መጥቶ ከእዚያ የራሱ ካሜራ አለ ካሜራውን መጥቶ ከእዚያ ለእሱም አሳይቶ ከእዚያ ተመልሶ ሄዷል
- አቡበከር አለሙ ሲመጣ ግን ካሜራ አልያዘም ነበር አይደል እሱ አቡበከር ሲመጣ ካሜራውን አልያዘውም ነበር አይደል ?
- ካሜራው አልነበረውም ያው በኢግዚቢት የተቀመጠ ካሜራ
- እኮ ያንን ያመጣው ማን ነው ከፖሊስ የመጣው አይደል ?
- ፖሊስ ነው ያመጣው አዎ ከእሱ የተገኘ ነው ተብሎ በኢግዚቢት የተያዘ ካሜራ ነበር እና ስሙ ተፅፎ ነበር ካሜራው ላይ ከእዚያ እራሱ ነው የከፈተው ካሜራውን
- ኤችዲ የሚል ካሜራ ነው ብለዋል ካሜራው ምን ዓይነት ካሜራ ነው ?
- ካሜራው ይዘቱ ዲጂታል ካሜራ ትንሽዋ ነች
- ትንሽዋ ካሜራ ነች ?
- አዎ
- እሷ ያው ማንም ሰው ሊከፍታት የሚችላት ካሜራ ነች ምንም የተለየ ነገር የላትም አከፋፈት አዮደል ?
- እሱ ማንኛውም ሰው የሚከፍት ነው ግን የራሱ ስም ስላለው የራሱ አበበከር
- አላዩ ላይ የተለጠፈበት ማለት ነው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ከእዚያ በኋላ እሱ ፎቶውን አይቶ ፎቶዎቹ ?
- ፎቶዎች ሳይሆኑ ቪዲዮ ካሜራ በቪዲዮ የተቀረፀ ናቸው
- የተጎዱት ሰዎችን ነው የሚያሳየው ?
- አዎ የተጎዱት ሰዎችን የሚያሳይ ነገር ነው
- የተፈነከቱ ምንድን ነበር ጉዳታቸው ?
- የተፈነከቱ እጃቸው የተሰበረ እግራቸው የተሰበረ ምናምን ነገር ነው
- በምንድን ነው ጉዳት የደረሰባቸው ይላል ቪዲዮ ከሆነ የሚናገረው ነገር አለ ቪዲዮው ?
- ድምፅ ነገር የለውም
- የእነሱ ፎቶ ብቻ ነው ምስል ብቻ ነው ?
- ምስል ብቻ ነው የሚያሳየው
- ከእዚያ በኋላ ይሄ ነው ወደ ካሴት ተለውጦ የተመለሰው ?
- አይ ከቪዲዮ ካሜራ ወደ ካሴት ነው የተቀረፀው
- ይሄ ሲለወጥም ለአቡበከርም ይሄ ማስረጃ ይሆንብሀል ተብሎ አልተነገረውም አይደል?
- አዎ ማስረጃ ባለው ወቅት ላይ ምርመራ ክፍል ክፍል ስለሆነ ያው ከራሱ ካሜራ እና የተቀረፀ የራሱ ስለሆነ ያው ተጠርጣሪ ስለሆነ እንደማስረጃ ምናምን ያው እንደሚቀርብ ያው የታወቀ ስለሆነ
- እኮ /ግልፅ ያልሆነ/ ያልኩት አልተነገረውም አይደል ፖሊሱ ይሄ በማስረጃነት ይቀርብብሀል ብሎ አልነገረውም ?
- በማስረጃነት ተቀጥሯል አዎ
- ይቀርብብሀል ብሎ አልነገረውም አይደል?
- አልነገረም
- ያሲን ኑሩ ላፕቶፑ ሲከፈት ላፕቶፑን ያመጣው ማን ነው ?
- ላፕቶፑን ያመጣው የወንጀል ምርመራ ክፍል በብርበራ ወቅት የተገኘ እና በእሱ ስም የተለጠፈበት የታሸገ ነው ያሲን ኑሩ ተብሎ

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ይሄንን እርሶ እንዴት ነው ያወቁት ?
- ያው የፖሊስ ምርመራ ክፍል ይዞ መጥቶ ከእዚያ ያሲን ኑርም እራሱ ባለበት ከራሱ አንደኛ እና የራሱ ስም በላዩ ላይ ተለጥፎበታል ስሙ ተለጥፎ ከእዚያ እራሱ ስለሆነ የከፈተው ከእዚያ የተለያዩ መክፈቻዎች ስላሉት እራሱ ነው የከፈተው
- ለእሱም ሲከፈት ይሄ ሰነድ ከእዚህ ውስጥ የሚወጣው ሰነድ በማስረጃነት ይቀርብበሀል ተብሎ አልተነገረውም አይደል ?
- አልተነገረኝም
- ሰነዶቹ ቅድም በእዚህ ሲወጡት ሰነዶች ሲፈረሙ ከላፕቶፕ ላይ የወጡት ሰነዶች ወጥተው ሲፈረሙ ለእናንተ አልተነበበላችሁም አይደል ?
- ከኮምፒዩተር ኢሜል ላይ የእዚህ ሲወጣ
- አዎ የያሲን ኑሩ
- ከላፕቶፕ የወጣው ሀርድ ዲስክ ነው አንድ ሲዲ ብቻ ነች
- ከሀርድ ዲስክ ላይ የወጣው ?
- አዎ
- ሰነዶቹ ታትመው ስትፈርሙ ሰነዶቹ አልተነበቡላችሁም አይደል ?
- አልተነበበልንም ኧረ
- ለተከሣሽም አልተነበበለትም ?
- አዎ
- አቶ በለጠ እስቲ ታዛቢዎች አሉ እነ ያሲን ኑሩ እና አቡበከር አለ መርማሪዎች አሉ አቀማመጣችሁትን እስቲ ለፍ/ቤቱ ያስረዱ ስንት ጠረቤዛ ነበረ እንዴት ነበር የተቀመጣችሁት ?
- አቀማመጣችን ነው አቀማመጣችን 2 ጠረቤዛ ነበር
- አንደኛው ላይ ማን ተቀምጧል ?
- አንደኛው ያሲን ኑር ያው አጠገብ ኮምፒዩተር አጠገብ እራሱ የሚወጣበት ላይ ተቀምጧል አንደኛችን ደግሞ አንድ ወንበር ተቀምጠናል
- አንድ ወንበር ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንደኛው አንድ ወንበር ላይ አንደኛው አንድ ወንበር ላይ አንደኛውም መርማሪ ፖሊስ አንድ ወንበር ላይ
- አንድ ወንበር ላይ መርማሪው አጠገብም ኮምፒዩተር አለ ?
- መርማሪው አጠገብ ሌላ ኮምፒዩተር የለም አንድ ኮምፒዩተር ነበር ያሲን ኑሩ የሚያወጣበት
- እዚያ ቤት ውስጥ ሌላ ኮምፒዩተር አልነበረም እንጄ የያሲን ኑሩ ላፕቶፕ ብቻ ነበር ?
- ያሲን ኑሩ ያው ተጨማሪ ነው ላፕቶፑ በመጀመሪያ የወጣው በኮምፒዩተር ነው
- እዚያ አይቲ ቅድም የኮምፒዩተር ቤት እንደሆነ ስለገለፁ እኮ ነው ከተከሣሾች ኮምፒዩተር ነው ከተባለው ውጪ ሌላ ኮምፒዩተር አልነበረም እዚያ ቢሮ ውስጥ ?
- ቢሮ ውስጥ ያው የስራ እንትን ሌላ ይስራ አይስራ አላወኩም እንጂ አለ ኮምፒዩተር
- ሌላ ኮምፒዩተር አለ ?
- አዎ
- እሱ ኮምፒዩተር ጋር መርማሪው አለ ?
- አይ መርማሪው ያለው ከእኛ ጋር ነው እዚያኛው ኮምፒዩተር ላይ ማንም የለም እንዳየሁት ታዛቢ በሆንኩበት መሠረት
- እናንተ ታዛቢዎቹ እና መርማሪዎቹ አንድ ላይ ነው የተቀመጣችሁት ?
- አይደለም ታዛቢዎቹ 2ታችን ለብቻ ከእዚያ ምርመራ መርማሪ ፖሊሶቹ ለብቻ ነው የተቀመጡት
- ያሲን ኑሩ ለብቻው ?
- ያሲን ኑሩ ለብቻው አዎ
- እስቲ በመካከላችሁ በግምት ምን ያህል ርቀት ነበር ?
- ብዙም ያህል
- መርማሪው አለ በእናንተ እና በመርማሪው መካከል የሆነ ርቀት አለ በእናንተ እና በታዛቢዎች እና ማለቴ ነው በታዛቢዎች እና በተመርማሪዎቹ በእነ ያሲን ኑሩ እና በአቡበከር መካከል የሆነ ርቀት አለ እስቲ በግምት ከእዚህ እስከ እዚያ ብለህ አሳየን እስቲ?
- ያው ብዙም ርቀት የለውም እንትኑ
- በግምት አሁን ከተቀመጥክበት እስከ እዚያ ፊት ለፊት እስካለው ጠረቤዛ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ እስከ እዚያ እንኳን አያርቅም እስከእዚቹኛዋ ቢሆን ነው እንትና አለች አይደል ደረጃዋ
- እስከ ደረጃው ድረስ ?
- አዎ እስከ እሱ ቢሆን ነው
- አቀማመጣችሁ እንዴት ነበር ፊት ለፊት ተፋጣችሁ ነው አሁን ያሱን ኑሩን ?
- ፊት ለፊት ያው እሱ እየከፈተ እያወጣ
- ቆይ ስለመከፈቱ አይደለም እርሶ እንደዚህ ቁጭ ብለዋል ከእነ ያሲን ጋር ፊት ለፊት ተፋጣችሁ ነው ?
- አዎ ፊት ለፊት ሆነን ነው
- ፊት ለፊት ?
- አዎ
- ትተያያላችሁ ?
- አዎ
- ከእዚያ ኮምፒዩተሩን ከፍቶታል እሱ ?
- አዎ
- የኮምፒዩተሩ ጀርባ ለእናንተ ይታያል ?
- የኮምፒዩተሩ ጀርባ
- እኮ ፊት ለፊት ስለተቀመጣችሁ ላፕቶፑን ይከፍተዋል ?
- አዎ
- ምንድን ነው ብራንዱ የኮምፒዩተሩ ቶሽባ ይላል ጀርባው ላይ ያለው ?
- አይ ኮምፒዩተሩን ያው ብዙም ባላስታውሰውም ግን ከእኛ የተቀመጥነው እዚያ ፊት ለፊት ሆኖ ግን ያው ከራሱ ኢሜል ከራሱ ፓስወርድ እንደተከፈተ
- ቆይ ስለ እሱ አልጠየኮትም አሁን ፊት ለፊት እርስ በእርስ ፊት ለፊት ተቀምጣችዋል ኮምፒዩተሩን ከፍቶታል ላፕቶፑን ስለከፈተው ለእናንተ ጀርባው ነው የኮምፒዩተሩ የላፕቶፑ ጀርባ ይታያችዋል ስለዚህ ጀርባው ላይ የሆነ ፁሑፍ የለውም ቶሺባ ወይም ሌላ ዲኤል እንደዚህ የሚል ነገር ብራንድ የለውም ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሁሉም ብራንድ አለው ግን ያው እዚህ ጋር ለማስታወስ ያው ሁሉንን ትኩረት አልሰጠሁትም እንጂ አለው ሁሉምማ አለው
- ሌላ ጥያቄ
- ጥሩ ስለዚህ ያሲን ኑሩ እና አቡበከር ኮምፒዩተሩን ከፍቶ ሆናችሁ የእጃቸውን ምልክት ነው የምታዩት ማለት ነው አይደል ?
- አይ ያሲን ኑሩ መጀመሪያ ሲከፍተው እኛ ጠጋ ብለን ብዙም ልዩነት የለንም ቢያንስ ከእዚች እስከ እዚች ነው ሲከፍተው እዚያው /ግልፅ ያልሆነ/ አየው
- እስከ ደረጃው ርቀት አለን ብለው ነበር እኮ ?
- አዎ አይ ለመፈረም እንዲያመቸን ያው ጠረቤዛ እዚያች ጋር ስላለች ትንሽ ርቀት ስላለ ጠረቤዛው ላይ አስደግፈን ስለሆነ የፈረምንበት እኛ እሱ ከፈረመበት በኋላ ምስክሮች ስለሚፈርሙ ከከፈተ ካወጣ በኋላ ነው እዚያ ቁጭ ብለን የፈረምንበት እንጂ ሲከፍተው እዚያው አጠገቡ ነበርን
- ጥሩ ሲከፍተው አያችሁ ከእዚያ ተመልሳችሁ ወደ ቦታችሁ ተቀመጣችሁ ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላ ፕሪንት አደረገው ሲሉ ምን ማለት ነው እንዴት አድርጎ ፕሪንት አደረገው ?
- ያው ፕሪንት ማለት ያው የኮምፒዩተር ወደ ወረቀት የሚያትሙ ማለት ነው
- የለም ያሲን ፕሪንት ያደረገው ለመሆኑ አሁን ፕሪንት ማድረግ የሆነ ኮምፒዩተር አለ ፕሪንት የሚያደርግ ደግሞ ሌላ ነገር አለ እሱ ያሲን ፕሪንት ያደርግ አያድርግ እናንተ ፊት ለፊት ሆናችሁ ነው አንዴ ከከፈተው በኋላ ቦታችሁ ተመለሳችሁ ?
- አዎ ቦታችን ተመልሰን ግን ያው ይታያል
- እንዴት ነው የሚታየው ማለት የላፕቶፑ ጀርባው ነው የሚታያችሁ አንዴ ከተቀመጣችሁ እሱ ፊት ለፊት ስለተፋጠጣችሁ ማለት ነው ?
- አዎ ከከፈተው በኋላ አይተን የራሱ ሰነዶች መሆኑን አይተን ከእዚያ በኋላ እሱም ፕሪንት ባደረገበት መሠረት የራሴ ሰነዶች ነው ብሎ ፈርሞበት ፕሪንት ካለ በኋላ
- ወረቀቱ የት ጋር ነበር የሚወጣው አሁን ፕሪንት ሲሉ ?
- አጠገቡ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያው ላፕቶፑ አጠገብ ነው ያለው ?
- አዎ ያሲን ጉሩ አጠገብ ነው የሚወጣው አዎ
- ቅድም መሐመድ ሲከፍት ፓስወርድ አስገብቶ ብለዋል ማለት ተመሳሳይ ከእነ ያሲን ጋር ተመሳሳይ አቀማመጥ ነበር የነበራቸው ?
- አዎ ብዙም የሚለያይ ነገር የለውም
- የለውም ?
- አዎ ተቀራራቢ ነው
- ማለት ፓስወርድ በማዕከል ፓስወርድ ነው የተከፈተው ብለህል ነኛ ምን ማለት ነው በማዕከል ፓስወርድ ማለት ምን ማለት ነው እንደሱ ከሆነስ እንዴት ነው ፓወስርድ ይኑረው አይኑረው በምን አወክ አንተ ?
- በማን ፓስወርድ ሳይሆን የራሱ ፓስወርድ ቁጥር አለው ከእዚያ የራሱ ቁጥር እና የራሱ ሚስጥር እንትን ይኖረዋል
- ገምተህ ነው ወይስ ሲከፍት አይተህ ነው ?
- አይ ሲከፍት አይቼ ነው ቆሜ እዚያው
- ቆመህ ነበር ቁጭ ብላችሁ ነበር ?
- አይ መጀመሪያ ሲከፈተው ቆሜ ነበር ያየሁት አጠገበ ቆሜ ማለት ነው ያው ለማየት እንዲመቸን ማለት ነው ከእዚያ ከከፈተ ከጨረሰ በኋላ ከእዚያ እራሱ እየፈረመበት ሲሰጠን ከእዚያ ለጠረቤዛው እንዲመቸን ለመፈረም እንትኖችን ለማድረግ ከእዚያ ቁጭ አለን ከእዚያ ቤቱ ስለማይበቃን ከእዚያ እኛ እማኞች ብለን ፈረምንበት
- ነፃ ነው ነፃ ሆኖ ሲፈርም ነበር ብለህል ?
- አዎ
- ነፃ ይሁን አይሁን ያወከው ነገር አለ ስለፈረመበት ነው ነፃ ነው ብለህ የገመትከው አንተ ?
- አይ ስለፈረመበት ብቻ አይደለም የሆነ ፊዚካሊ የምታነቢው ነገር ነፃ ሆኖ ሪላክስ ሆኖ እራሱ ዘና ብሎ እራሱ ስለሆነ የሚፈርምበት ከእራሱም እንደተገኘ እራሱ ያው ፊቱ ላይ
- እሱን አይተህ ነው ?
- አዎ የሚነበብ ነገር ስላለው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ተከሣሾች የ3ቱም ስማቸው ኮምፒዩተሮቹ ላፕቶፖቹ ላይ ተሰሮ ነበር ሀርድ ዲስኩም ላይ ብለሀል ፁሑፉን በደንብ አይተው አዘረው ነው ያሳዩዋችሁ ?
- የት አልገባኝም
- ምናልባት የ3ቱ ኮምፒዩተሮች ላይ 3ቱ ተከሣሾች ስም ተፅፉል የሚለውን እኛ አልያዝንም እና አስተካክሉ ጥያቄውን ?
- የተከሣሾቹ ኮምፒዩተር መሆኑን እርሶ ያወቁት በምንድን ነው ?
- የተከሣሾቹ ኮምፒዩተር መሆን ሳይሆን ኮምፒዩተሩ ሳይሆን 3 አይደለም ደግሞ የ2ቱ ነው
- እሺ ይቅርታ 2ቱን 2 ኮምፒዩተሮች ?
- አይ 2 ኮምፒዩተር ሳይሆን 2 ኮምፒዩተር አንዱ መጀመሪያ ነሐሴ 26 በራሱ ፓስወርድ ከፈተ ፈረመበት አንደኛው ደግሞ በ 5/01/2005 እራሱ ያሲን ኑር ፈረመበት እንጂ የራሳቸው ኮምፒዩተር ሳይሆን የራሳቸው የኢሜል ቁጥር ነው እራሳቸው በፓስወርድ የሚጠቀሙበት ነው የራሳቸው የተለያዩ ስራዎች የሚሰሩበት ነው እና የእነሱን በማውጣት እና እራሳቸው በሰነዱ ላይ በመፈረም የተለያዩ ፁሑፎች ያሉትን ነገር ላይ እነሱ ሲፈርሙበት እና እኛም በታዛቢነት መልኩ ያወቅነው
- ሀርድ ዲስኮቹ ላይም እንደዚያው ነው የእነሱ መሆኑን አያውቁም አይደል ?
- የራሱ ኢሜል መሆኑን እና
- ላፕቶፕ አለ
- ላፕቶፑ 2ኛ ነገር ነው 1ኛው እንትን ነው ፕሪንት የተደረገበት ወረቀት የኢሚል ነው ላፕቶፑ ደግሞ ተጨማሪ ሀርድ ዲስክ የወጣበት ነው ሲዲ ለብቻው
- ሀርድ ዲስክ ሲሉ ላፕቶፕ እና ሀርድ ዲስክ 2 ነገሮች ነው ወይስ አንድ ነገር ው ?
- አንድ ነገር ነው ላፕቶፕ አለ ከላፕቶፑ ያው የተለያዩ እንትኖች ያሉበት ምስሎች ምናምን ፁሑፎች ያሉበትን በሲዲ ኮፒ አድርገ ነው ያወጣው
- ከላፕቶፑ ከራሱ ፕሪንት ተደርጎ ኮፒ ተደርጎ ?
- ከራሱ ላፕቶፕ ፕሪንት ተደርጎ ነው የወጣው
- በሲዲ ?
- በሲዲ አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሀርድ ዲስክ የሚሉት ይሄንን ሲዲውን ነው ?
- አዎ
- አቶ በለጠ ቅድም መጀመሪያ ላይ ፍ/ቤት ተከሳሾችን እንዲለዩ በሚደረግበት ጊዜ ያሲን ኑሩ እና አቡበከር አለሙን በአካል መለየት አልቻሉም የእዚያን ዕለት በቢሮ ውስጥ ሆነው እነዚህን ሰነዶች ሲያሳዩ የነበሩት ሰዎች ስማቸው ያሲን ኑሩ እና አቡበከር አለሙ መሆኑን ያወቁት እንዴት ነው ?
- ስማቸውን ያወኩት ያው በሰነዶቹ ላይ እራሳቸው ሲፈርሙበት እና በራሳቸው የተገኘ ደግሞ ካሜራ እና ላፕቶፕ ስላለ ፁሑፉ ተፅፎበት ነበር
- የሚፈርሙት ሰዎች ስማቸውን ያሲን ኑሩ እና አቡበከር አለሙ ብለው ስለፈረሙ ነው ?
- አዎ እዚያው ላይ ካሜራው ላይ ተፅፎበታል ላፕቶፑም ተፅፎበታል ያሲን ኑሩ ተብሎ ካሜራው ላይ አቡበከር አለሙ ተብሎ ተፅፏል
- እንጂ ተከሳሾቹ እዚያ የነበሩት ሰዎች ወይም መርማሪው ፖሊስ ስሜ ያሲን ኑሩ ነው አቡበከር አለሙ ነው ብለው አልተናገሩም አይደል ?
- አይ እንደሱ /ግልፅ ያልሆነ/
- ምስክር አሁን እነዚህ ባዩዋቸው ላፕቶፖችም ሆነ ሌላ ፕሪንት ተደርጎ የወጡ ሰነዶች ፕሪንት ተደርጎ ወጡ ሲወጡ አየዋቸው ያሉት ሰነዶች ለማን እንደተፃፉ ያውቃሉ ወይም ከማን እንደተፃፈ አይተዋል ?
- ያው የተለያዩ ፁሑፎች ናቸው የተላኩም ሊሆኑ ይችላሉ ወደ እነሱ ኢሜል እነሱም የላኳቸው ሊሆን ይችላል ያው
- ይችላል ሳይሆን አይተዋል እርሶ በትክክል ለምሳሌ ?
- አይቼአለሁ ሳይሆን የወጣበት ሰነዱ እራሱ ያስታውቃል የተላከ እና እንትን ያለ ቢያንስ
- ለምሳሌ ያህል ተላከ የሚሉት ለመሐመድ አባተ ከሆነ ተ፡ መሐመድ አባተ የሚል አይተዋል በአይንዎ ?
- አይ እሱ አላየሁም ያው ፁሑፉ ስለማይልችል
- አላዩም ?
- ማንበቡ ያው የተለያዩ እንትኖች ይዘቶች ስላሉት ኢሜል ምናምን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱን አይደለም የጠየኩት እኔ አጭር ጥያቄ ነው የጠየኩት
- ያው እንደተላከ እና
- ልጠይቆት እኔ እያልኩት ያለው
- ሊሆን ይችላል እያለ ነው እርግጠኛ አይደለም ምስክሩ እና እዚህ ላይ ቆሞ ሌላ የሚጠይቁ ነገር ካለ እንጂ
- የተከበረው ፍ/ቤት ግልፅ ነገር ስለሆነ ምናልባት ጥያቄው አልገባቸው እንደሆነ ብዬ ነው
- ይሄንን መልሰዋል ሌላ ካሎት ሊሆን ይችላል ነው እርግጠኛ አይደለም
- እንጂ እርግጠኛ አይደሉም
- ይሰማሉ ጠበቃ እስቲ አንዴ የሚሰሙ ከሆነ ሊሆን ይችላል ብሏል ምስክሩ ይሄንን ነው እሱ እርግጠኛ ሊሆን ይችላል እርግጠኛ አይደለም ይሄ አማርኛ ግልፅ ነው እዚያ ላይ ቆሞ ሌላ ካሎት ነው ሊሆን ይችላል ነው ያሉት እሱ ያለውን ቃል ነው እኛ የደገምነው እና ምናልባት ብይንም ቢቀበሉ
- ተቀብዬአለሁ እኮ የተከበረው ፍ/ቤት እንዲያረጋግጥ ለማድረግ እንጂ ተቀብዬአለሁ ቅድም ፁሑፎችን እኔ አላነበብኳቸውም ብለው ነበር በሌላ በኩል ደግሞ ኦሮምኛም አለበት ብለዋል በምን ለዩ እነዚህን ነገሮችን ?
- ኦሮምኛ ያለበትን ያው በማየት ያው የዛፍ ምልክቶች ምናምን አሉበት
- እንጂ ፁሑፍን አላዩም ?
- እንጂ ፁሑፉን አላነበም አዎ
- ዛፎች ስላዩ ነው ?
- የዛፍ ምልክቶች ምናምን አሉበት አዎ የኦሮምኛ እንትን የሚያሳውቅ ነገር
- ቅድም በቪዲዮ ካሜራ ያሲን ኑሩ ተገኙ ያሉት ነገር ?
- በቪዲዮ ካሜራ ሳይሆን አቡበከር አለሙ ነው ቪዲዮ ካሚራ
- ቪዲዮ ካሜራው ላይ ምስሎችን አይተዋል ?
- አዎ
- እነዚህን ምስሎች እኔ አንስቼአለሁ ብሎ ሲናገር ሰምተዋል እርሶ ?
- አዎ እራሱ የቀረፃቸው መሆኑን በራሱ ቃል ሰምቼአለሁ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ብሎ ተናገረ ?
- ያው እራሱ የቀረፅኳቸው ነው ብሎ
- ከየት ቀረፅኳቸው አለ ?
- ያው ከተለያየ ቦታ ነው/ግልፅ ያልሆነ/ ቦታውን /ግልፅ ያልሆነ/
- እራሴ ነው የቀረፅኩት ብሎ ተናገረ ?
- አዎ
- ምስክር እስቲ እርሶ ታዛቢ በሆኑበት ጊዜ የያሲን ኑሩ አለባበስ ምን ይመስል ነበር ?
- ያሲን ኑሩ አለባበስ ያው ባህሉን የሚያንፀባርቅ ነገር ነው የለበሱት
- መልኩ ምን ዓይነት ?
- ያው ነጭ ኮፍያ እና የድሪያ ልብስ አለ አይደል ይሄ ሙስሊሞች የሚለብሱት ቀሚስ ነገር እንደሱ
- ምን ዓይነት ከለር ?
- ነጭ
- ከታችስ የተጫማው ነገር ?
- ከታች ያው ነጠላ ጫማ የሚመስል ቆዳ አለ አይደል
- የአቡበከር ?
- አቡበከር ደግሞ ያው እንዳሁኑ እንደለበሰው ቲሸርት ነው የለበሰው እና የሆነ ሻማ ነገር የሚመስል ነገር ነው ሱሪ ያደረገው
- ከታች ምንድን ነው ?
- ከታች ያደረገው ነጠላ ጫማ የሚመስል ነው
- መሐመድ አባተ ?
- መሐመድ አባተ ያው እሱም ቀሚስ ነገር ነው ያደረገው ቡኒ ጥቁር መሳይ የሚባል ከለር ነው እንትኑ ልብሱ ቀሚሱ ማለት ነው እና ፂሙ ትንሽ ወረድ ያለ እና ያው ፂሙ ትንሽ አደግ ያለ
- ነሐሴ 26 እርሶ በሄዱበት ሰዓት አየሩ ሁኔታ እንዴት ነበር ?
- ነሐሴ 26 አየሩ ያው የክረምት ወቅት ነበር



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት ይዘጉበ ነበር ?
- አይ አይዘጉበም
- ደመና ?
- ደመና ነገሮች አሉት እንዷ አይዘጉበም
- መስከረምስ መስከረም ?
- መስከረም ያው እንትኖች ካፊያ ነገር አለው
- ካፊያ ነበር ?
- አዎ
- ምስክር በወቅቱ በታዛቢነት በመጣንበት ጊዜ ወይም በታዘብኩበት ጊዜ ሌላ ሰው አቶ ኤልያስ የሚባሉም አብረው ነበሩ ብለዋል ከአቶ ኤልያስ ጋር ትተዋወቃላችሁ ?
- ከአቶ ኤልያስ ጋር አንተዋወቅም ያው በአጋጣሚ እሱም እዚያው ተጠርቶ ነው የተገናኘነው እና እዚያው
- ዛሬ ለምስክርነት መጥተዋል ?
- እዚያው /ግልፅ ያልሆነ/ ተገናኝተን እዚያው እራሱ ሲፈርምበትም ያው እዚያው ስለተያየን ነው
- ዛሬ ለምስክርነት መጥተዋል ?
- አዎ
- መጥተዋል ዛሬ ለምስክርነት መጥተዋል ዛሬ ?
- አዎ ያው እንግዲህ እዚያው የተገናኘነው ለምስክርነት መጥተው ነው
- አይ ዛሬ አሉ እዚህ ለምስክርነት መጥተዋል ?
- አዎ ዛሬ መጥተዋል አዎ
- ምን ዓይነት አለባበስ ነበር የለበሱት አቶ ኤልያስ ምን ዓይነት ልብስ ነበር የለበሱት ?
- መቼ አሁን
- የዛኔ የእዚያን ጊዜ በታዛቢነት በመጡ ጊዜ ምን ዓይነት ልብስ ነበር የለበሱት ?
- የእዚያኔ የታዛቢነት ያው ጨርቅ ሱሪ እና ከእዚያ ቲሸርት ከውስጥ አለ
- ምን ዓይነት ጨርቅ ሱሪ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥቁር መሳይ ነው ፊቢርቅ
- ጥቁር መሳይ ቲሸርት ምን ዓይነት ?
- አሁን የልብስ ከረጅም ዓመት በኋላ ምን ያህል ያስታውሳል የሚለው በኋላ የሚመዘን ነው ወደ ምስክር ልብስ አልፏል አሁን መስከረል ለማገናኘውም
- አስታውሶ እየመለሰ ነው
- ግን ምን ያህል የሚለው ሌላ ጥያቄ ካላችሁ ወደ ልብስ ወደ ሱሪማ የሚለው ነገር ሲመዘን የሚታይ ነው የሚሆነው እና ወደ ሌላ ጥያቄ
- ከአቶ ኤልያስ ውጪ ስንት ሰዎች ነበሩ ?
- ከአቶ ኤልያስ ውጪ ያው እኔ እና እሱ
- ተጠይቋል ይሄ ሌላ ጥያቄ ካለ
- በወቅቱ ሲዲ ላይ ፈርመናል ብለዋል ስንት ሲዲዎች ነበር ?
- ያሲን ኑር የተገኘበት አንድ ሲዲ ነው
- አንድ ሲዲ ላይ ነው የፈረማችሁት ?
- አዎ
- የፈረማችሁትም አንድ ሲዲ ላይ ነው ?
- አንድ ሲዲ ላይ ከላፕቶፑ ወጥቶ ከእዚያ አንድ ሲዲ ላይ እሱ ስም የፃፈበት ከእዚያ በኋላ እኛ ስላየን ምስሉን ፃፍንበት
- የሲዲውን ይዘት አላያችሁትም አይደል ?
- የሲዲው ይዘት
- እሱም ተጠይቆ ተመልሷል
- እሺ በወቅቱ መሐመድ አባተ ወደ እኔ የተላኩ ኢሜሎች በተመለከተ ልፈርም አልችልም ወይም አልፈርምም እያለ ነበር አይደል ?
- አዎ በወቅቱ ትንሽ የመደናገር ነበረበት እሱም እራሱ አልፈርምበትም ብሎ ትንሽ ሲከራከር አይ ያንን ፈርምበት እና እኔ አይደለሁም የምትለው ነገር ለፍ/ቤቱ አስረዳ ተብሏል
- ፈርም ብሎ አግባባው ፖሊሲ ?
- አልፈርምም ሲል ከእዚያ በኋላ በመግባባት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለምንድን ነው እሱ አልፈርምም ያለው ?
- እኔ እንጃ እሱ ያው ሊያውቃቸው ይችላል
- አዎ አሁን እሱ አልፈርምም አለ ብለሀል እና የማይፈርምበት ምክንያት ምን ብሎ ነበር ሲናገር የነበረው ?
- ያው ለፍ/ቤቱ የራሱ ብሎ የማስረዳቱን ነገር ፍ/ቤቱ /ግልፅ ያልሆነ/ ይመስለኛል እንዲያስረዳ
- ፖሊሱስ ፈርም ሲለው ምን ብሎ አግባባው ?
- ያኛው እኛም ስላለን ያው እንደታዛቢ እንደምስክርም ስለሆነ ያው ነፃ ስለሆነ እኛም ባለንበት ያው ለማስረዳት እና ያው የመግባባት እሱም አምኖበት
- ስለዚህ እሱ ፍቃደኛ አልነበረም ግን ፈርም ስለተባ ፈረመ ?
- አይ ያው ፍቃደኝነቱን ያው በኋላ ላይ እያመነ መጣ ፈረመበት
- እንጂ መጀመሪያ ፍቃደኛ አልነበረም ለመፈረም ?
- አዎ
- ያሲንም እንደዚያው ነበር ?
- አይ ያሲን ኑር
- ወደ እኔ የተላከ ልፈርም ?
- አይ ያሲን ኑር እንኳን ምንም ችግር የለበትም እንደውም እራሱ ሪላክስ እያደረገ እራሱ ዘና እያለ ነው የፈረመበት
- እርሶ እዚያ አይቲ ሩም ካሉት ወይም የአይቲ ክፍል ካሉት ውጪ የደረሰበትን ነገር አያውቁም አይደል ?
- አይ እሱን አላውቅም
- ማለት ጫና ይደረግበት አይደረግበት አያውቁም አይደል ?
- አላውቅም
- ከእርሶ እና ከአቶ ኤልያስ ማን ነው ቀድሞ ደርሶ የነበረው ?
- አይ 2ታችንም ነበርን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ሲገቡ ወደ ኮምፒዩተር ክፍል ወይም አይቲ ያሉት ሲገቡ አብራችሁ ነው የገባችሁት ኢሊያስ ቀደመ ወይስ አንተ ቀደምክ ?
- አዎ በሩ ጋር ነው የምትለኝ አይቲ ክፍል በሩ ጋር
- ወደ አይቲ ክፍል
- አይ አብረን እኔ ገባሁ ከእዚያ በኋላ ተከትሎኝ ገባ
- አንተ 2 ጊዜ ነው በታዛቢነት የሄድከው እሱም 2 ጊዜ ነበር ?
- አዎ
- አንተ ምን እንደተመረጥክ ተነግሮሀል እንዴ ለታዛቢነት ለምን አንተ እንደተመረጥክ ተነግሮህ ነበር ?
- አይ
- ለታዛቢነት ለምን አንተ ተመረጥክ ምክንያቱም አሁን የስራ ቀን አይደለም ቅዳሜ ነው ተጠርቼ ነው ነው ያልከው አንተ ለምን እንደተመረጥክ ተነግሮሀል ?
- አይ አልተነገረኝም
- ለምን አንተስ ታውቃለህ ለምን እንደተመረጥክ ?
- አይ ያው በጥሩ እንትን ስለሆነ በጥሩ እንትን ስለሆነ ለታዛቢነት ስለሆነ ያው ያየሁትን ስለሆነ ለመመስከር ስለሆነ በእንትን
- ቅድም አሁን ስታስረዳ ኮምፒዩተሮቹ ኤግዚቢት ናቸዉ እያልክ ነበር ኤግዚቢት መሆኑን በምን አወክ ?
- መርማሪው እራሱ በነገረኝ እዚያ ታዛቢ ሆነን ይዞን መጥቶ ይሄ ኤግዚቢት
- ኤግዚቢት ማለት ምን ማለት ነው ?
- ያው በተጠርጣሪነት ያው የተያዘ ማለት ነው
- ጨርሻለሁ
- ጨረሳችሁ
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ
- እሺ. አቶ በለጠ ክፍሉ አይቲ ሩም ነበር ብለሀል እዚያ ክፍል ውስጥ አይቲ ሩም መሆኑን በምን አወክ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው በሩ ላይ ኢ የሚል ፅሑፍ ስላለው የአይቲ ክፍል መሆኑን
- በወቅቱ እዚያ ቦታ የነበሩ ሰዎች መርማሪዎች ናቸው በማለት በተደጋጋሚ ገልፀሀል የአይቲ ባለሙያዎች ይሁኑ መርማሪዎች ይሁኑ በምንድን ነው የለየኸው ?
- መርማሪዎች ነበሩ እና ራሳቸው መርማሪዎች ባሉበት ነው የወጣው
- ኮምፒዩተሩን ምን ሲከፍቱ የነበሩት ወይም ሲያመቻችሉት የነበሩት የአይቲ ባለሙያዎች ናቸው ወይስ መርማሪዎች ናቸው ?
- አይ መርማሪዎችም ባሉበት ያው እነሱ ባሉበት መርማሪዎቹ ከእዚያ የአይቲ ባለሙያ አንድ ነበር ከእዚያ ከእሱ ጋር አብረው ከመርማሪዎች ጋር ያው እራሱ
- ስንት መርማሪዎች ነበሩ ?
- 2
- 2 መርማሪዎች ?
- አዎ
- የአይቲ ባለሙያውም ነበር ከመጀመሪያ ጀምሮ ?
- የአይቲ ባለሙያው እንጃ አላስታውሰውም እሱን እንኳን
- አታስታውስም ?
- አዎ
- ቢሮ ውስጥ ኮምፒዩተሮች ነበሩ አይደል ?
- ኮምፒዩተሮች ነበሩ አዎ
- ቀድመን ከመግባታችሁ በፊት ተጠርጣሪው እና ያሲን ኑሩ እና ፖሊሶች ነበሩ ብለሀል ስትገባ ምን የታዘብከው ነገር አለ የሆነ የማስጨነቅ የማስገደድ ነገር ነበር እንዴ ?
- የማስጨነቅ የማስገደድ ነገር የለም
- ምን እያደረገ ነበር ያሲን ስትገባ ?
- ያው እዚያው ያው ስንገባ በወቅቱ ባለበት ያው ዘና ብሎ ከራሱ ኤሜል እንደወጣ እና ከራሱ እንትን እንደወጣ ዘና ብሎ እየፈረመበት አምኖ የራሱን ስም እየፃፈ ነው እንጂ የማስገደድ እና የጫና የተደረገበት ነገር የለም



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም በጠበቆች ስትጠየቅ አቀማመጣችን ለኮምፒዩተሩ ተቃራኒ ነበረ ብለሀል እና አይታችሁ ፕሪንት የሚደረገው ወይም ከተከሳሾች ኢሜላቸውን ሲከፍቱ እና ፕሪንት ካደረጉ በኋላ ለመፈረም ነው የተቀመጣችሁት ወይስ እንዴት ነበር ጀርባው የሚታያችሁ ከሆነ ምንን ነበር ስትታዘቡ የነበረው ?
- መጀመሪያ ያው ሲከፍተው ምናምን ሲያወጣ አይተናል ከእዚያ በኋላ
- ሲከፍተው እና ምን ሲያደርግ ?
- ሲከፍተው እና ሲያወጣ አየን
- ሲያወጣ ማለት ምን ማለት ነው ፕሪንት ሲያደርግ ነው ?
- ፕሪንት ሲያደርገው ማለት ነው ከእዚያ ለመፈረም
- ከጨረሰ በኋላ ነው የተቀመጣችሁት ?
- አይ ከጨረሰ በኋላ ሳይሆን ያው ተራ በተራ ስለሆነ እሱም እየፈረመበት እየወጣ እየፈረመ እያወጣ ስለሆነ ከእዚያ ብዙም ርቀት የለውም ቁጭ ብንልንም ጠረቤዛ ላይ ይታየናል እንትኑ ሲወጣ ማለት ነው ከእሱ እንደወጣ
- ፕሪንት ሲያደርግ ይታያችዋል ?
- አዎ ይታያል አዎ
- ይበቃናል አንድ ጥያቄ እንጨምር የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ጨርሱ
- እሺ ነሐሴ 26 ቀንም መስከረም 5 ቀንም ዕለቱ ቅዳሜ ነበር የፖሊስ የምርመራ ጊዜ ወይም የስራ ጊዜ በማናቸውም ጊዜ እንደሆነ ይታወቃል የሄድከው ለራስህ ጉዳይ ነው ወይስ ይሄንን ነገር ለመታዘብ ብቻ ነው እንዴት ነው ቅዳሜ በእዚያን ቀን ስራ የለም ወይም የሚለው ኮንኩሊዥን ላይ የደረስከው ከምን ተነስተህ ነው ?
- አይ ለራሴ ጉዳይ ነው
- እኮ ለምስክርነት ተጠርቼ የምትለው በእዚህ ጉዳይ ብቻ ነው የተጣራኸው ወይስ በሌላ መዝገብ ነበር ተጠርተህ የሄድከው ?
- አይ በእዚህ ጉዳይ ላይ ነው እንጂ በሌላው በራሴ ጉዳይ ላይ ነው በአጋጣሚ ሆኖ ነው
- ቀድመህ የነበረው በሌላ ጉዳይ ነበር ተጠርተህ የሄድከው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ይበቃኛል
- ማጣሪያ ጥያቄ
- ቅድም 3 ተከሣሾችን ስም ጠቅሰህ ነበር ?
- አዎ
- ያሲን ኑሩ አበበከር አለሙ እና ሌላም 3ኛ ጠቅሰሀል አሳይ ስትባል ያሳየኸው ተከሣሽ ከስሙ ጋር ሌላ ነው የነገርከን እና እንዴት ልትለየው ቻልክ እስቲ ተከሣሾቹን ?
- ያው ስማቸውን ነው እኔ ያው ያስታወስኩት ስማቸውን በእዚያን ወቅት በምስክር ጊዜ የሰጡት ስም ነው ያስታወስኩት አሁን ግን ያው ትንሽ ስለተመሳሰሉብኝ አለየዋቸውም ነበር አሁን አንደኛውን ለይቼዋለሁ እና እነሱን ተጨማሪ ካስፈለገ ለማሳየት እችላለሁ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አንድ ቀን የእዚያን
- በእዚያን ቀን ብቻ አይተህ ረጅም ጊዜ ነው አልሞስት ብዙ ወራት ነው እንዴት አስታወስካቸው ዛሬ ?
- ዛሬ ያስታወስኩት አልገባኝም
- ረጅም ጊዜ ነው እና ዛሬ መለየት ትችላለህ አሁን ?
- አሁን መለየት አዎ አንደኛውን ለይቼዋለሁ አሁን ለይቼዋለሁ ያሲን ኑሩ ለይቼዋለሁ
- የቀሩትንስ ?
- የቀሩትን አንደኛውን ትንሽ ጊዜ ካለኝ ለመለየት እችላለሁ
- ማለት መለየት ትችላለህ በእርግጠኝነት የምትችል ከሆነ ተነስተህ መለየት ትችላለህ ?
- አንደኛውን እችላለሁ በእርግጠኝነት
- እሺ ማንን ነው የምትችለው ?
- ያሲን ኑሩ
- እስቲ አሳየን ቀና በሉለት ሳትነካ በልብሱ ብቻ ትነግረናለህ ቀና ብላችሁ ትክ ብላችሁ እዩት የትኛው ምን እንደለበሰ ንገረን እስቲ ነጭ ቲሸርት ወይ ስንተኛው 2ኛው ሊላውስ ሊላውን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አሳየን እስቲ እዚያው ቆመህ በለበሰው ሆረህ ማየት ትችላለህ ነገር ግን ቀና በሉለት ሁላችሁም የተደገፋችሁ ቀና በሉ የትኛው

- ነጭ ያደረገው ይመስለኛል
- ነጭ ያደረገው ማለት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የተነሳው ነው እሱ ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የተነሳው ነው እሱ ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሱ ይመስላል ማን ነህ ካሊድ ኢብራሒም እሱን ይመስለኛል ነው ያልከው ስንተኛ ነህ ካሊድ 22ኛ ተከሣሽ ይመስለኛል እሺ ሌላውን መለየት ትችላለህ
- አይ አልችልም
- ጨርሰሀል እናመሰግናለን እንግዲህ ቅሬታችሁን አዳምጠናል አስተያየት ያው ማሰብ ምንም መገደብ



http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

መጋቢት 25 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ብስራት ተሀልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ፡- የፌደራል አቃቤ ሕግ አቶ ብርሃኑ ወንድማገኝ እና አቶ ቴዎድሮስ ባህሩ ቀርበናል

ተከሳሾች፡- እነአቡበከር አህመድ ለሎቹ ቀርበዋል ጠበቆች ሃዲስ መሃመድ ፣በሃሩ መካንጋ፣ ሃሰን ሁሴን፣አህመድ ጀማል ስለ 28ኛ ተከሳሽ

- ✓ አቤቱታ ነበረ የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ ምንድን ነው
- ✓ ባለፈው በተደጋጋሚ ወደ 15 ሲዲዎች አሉ የተጠቀሱት ያልተሰጡን ማለትነው እና ትላንትናም ምስክርነት እንደዋለው ከዛ ሲዲዎች የተገለበጡ ነገሮች አሉ እነሱን አይተን በመስቀለኛ ልናነሳ የምንችላቸው ጥያቄዎች አሉ ስለዚህ አልተሰጠንም አቃቤ ሕግ ሁለቱ ሦስቱ እየተናገሩ ነበር ጊዜው ገና ነው ተብለው ነበረ የታለፈው ስለዚህ አሁን ግን ሊሰጡን ሰዓቱ ስለሆነ ከዛ ተገልብጠው እንደዚህ አይነት ስእሎች እንዲህ አይነት እያሉ ስለሆነ የምናነሳቸው ትክክለኛ አስተያየት ለመስጠት አመቺ እንዲሆን ሲዲዎቹ እንዲደርሱን ቢደረግ በበቂ ኮፒ
- ✓ /የማይሰማ/ ማስረጃ እንዳል በተደጋጋሚ ባለፈውም ያመለክቱ ነበር ስለዚህ /ግልጽ ያልሆነ/ ካለ ሁሉንም



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት መልስ እንደንሰጥበት ከተፈቀደልን ምናልባት ያው በክሳችን ላይም እንደጠቀስነው ሲዲዎቹ በችሎት የሚቀርቡ ብለን ነው እኛ እንትን ያልነው ምክንያቱም ሲዲዎቹ የቀስቃሽነት እና ሌሎችን ለተመሳሳይ ወንጀል የሚያነሳሳ ይዘት ያላቸው ናቸው ስለሆነም ሙሉ ይዘታቸው በፍ/ቤት ተከሳሾቹም ጠበቆቹም እንዲያዩት ይደረጋል ነገር ግን ይሄንን ሲዲ ተመልሶ ለነሱ መስጠት ማለት በተመሳሳይ ተባዝቶ ለተመሳሳይ ተግባር ሲውል ይችላል ብለን ነው ስለሆነም በክሳችን ላይ እንደጠቀስነው በችሎት የምናቀርበው እንደሆነ ነው ምናልባት ይሄንኑ ማቅረብ ነው እንጂ ከፐብሊክ ኢንትረስት አንፃር እኛ ሲዲውን አለማቅረቡ ነው የሚሻለን ከመስጠቱ እና ከዚህ አንፃር እንዲታይልን ነው
- ✓ ማስረጃውን አለማቅረብ ነው?
- ✓ ማለት አዝ የላስት እሪዞርት ምንድን ነው 1ኛ በችሎት እንዲታይነው በክሳችን ላይም በችሎት የሚቀርብ ብለን ነውያቀረብነው ሁለተኛውም ከሲዲጋ ሲዲ ተገኝ ነው እንጂ ከሲዲ ጋር እየመሰከረ ያለ ነገር የለም ስለሆነም ምናልባት አደጋው ሲመዘን አደጋው ሲመዘን ማስረጃ ሆኖ በችሎት ከምናሰማው ይልቅ አለማቅረቡ ነው ምናልባት ፍ/ቤቱ የመጀመሪያ ላይ ያቀረብነውን እንትን የማይቀበለን ከሆነ  አለማቅረቡን ነው የምንመርጠው
- ✓ እናንተጋ አለ የለም ነው ብይኑን ፍ/ቤቱ ይሰጣል
- ✓ እኛጋ የለም
- ✓ በቃ ብይን እንሰጣለን ነገ ጠዋት ብይን እንሰጥበታለን
- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት ኮፒው ይኖራቸዋል ብለን ነው የምናስበው ምክንያቱም 1ኛ በብርበራ የተገኘው ከነሱ ከተጠርጣሪዎች የተለያየ ከተከሳሾች የተለያየ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ውስጥ የተገኘ ነው ስለሆነም አንድም በነሱ  ያዩት እና ይዘቱን ሙሉውን የሚያውቁት ነው ሁለትም ሊኖራቸው ይችላል ብለን ነው የምናምነው እስቲል ነገር ግን ይሄኛውን አንድ በማስረጃነት እዚህ ላይ እንትን ያልነው ይሄን ነገር በማሰራጨት ወይንም ለወንጀሉ መፈፀሚያነት ተጠቅመውበታል ነው ስለሆነም በድጋሚ እነዚህን ሲዲዎች መስጠቱ ይሄ ነገር ለዚህ ለሌላ ወንጀል እንደማያውል ለተመሳሳይ ወንጀል እንደማያውል ምንም ማረጋገጫ የለንም ሌላው ቀድሞ መታየት አለበት የብርበራ ታዛቢዎች ከመሰማታቸው በፊት ቀድሞ መታየት አለበት የሚባል ከሆነ ለፍ/ቤቱ አመቺ ከሆነ እኛ ከታዛቢዎች በፊት ሲዲውን እንድናሰማ ፍ/ቤቱ በሚሰጠን ቀጠሮ አቅርበው ለችሎት ማቅረብ እንችላለን ምናልባት ይሄ ከመስቀለኛ ጥያቄ ጋር ተይዞ የሚያጣብብ ነገር ካለ መብት ያጠባል የሚለው ነገር ካለ ማለት ነው



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት ትላንትና ካሳሰብነው የተለየ የሚናስበው የለንም ዛሬ የምንቀርበው ማስረጃ 6ኛ ተከሳሽን በቀጥታ የሚመለከት ስላልሆነ ዝርዝሩ እንዲቀጥል ነው እሺ
- ✓ በእውነት ለመመስከር
- ✓ በእግዚአብሔር ስም
- ✓ ምያለሁ
- ✓ በተራ ቁጥር 2ኛ ላይ የተመሰከረው ነው
- ✓ እሺ ምስክሩ በተሰሙት ምስክሮች ዝርዝር ልክ ከ58ኛ ላይ ደርሶዋል በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ ተራ ቁጥሩ ላይ የተጠቀ ስምህን ያዉ የራስህን ስም ብቻ ነው የምትባለዉን [illegible] የአያት ሌላ ዝርዝር ውስጥ አንገባም እስቲ ስምህ ማን ነው?
- ✓ አበበ እባላለሁ
- ✓ ዛሬ ለምስክርነት ነው የመጣኸው በነማን ላይ ነው የምትመሰክረው?
- ✓ በሙራድ ሽኩር
- ✓ ሌላስ?
- ✓ በዚህ ብቻ ነው
- ✓ ታውቀዋለህ ሙራድን?
- ✓ አላውቀውም ምክንያቱም 1ኛ ጊዜውም እረጅም ነው 2ኛ ደግሞ በዛን ሰዓት ስንይዝ አመሻሽ ነበር መሽቷል ወደ አንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው
- ✓ ስለዚህ በአካል መለየት አትችልም?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ አ.ቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- ✓ እሺ ምስክር በዛን ቀን ስንይዘው መሽት ብሎ ነበር ብለዋል መቼ ነው ያ ቀን ቀኑን ያስታውሱታል?
- ✓ ቀኑ በ4/8/2004 ዓ.ም ነው
- ✓ ስንት ሰዓት አካባቢ ነው?
- ✓ አንድ ተኩል አካባቢ
- ✓ አሁን በጠቀሱት ቦታው የት አካባቢ ነው?
- ✓ ቦታው ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ልዩ ቦታው ካርል አደባባይ ነው
- ✓ እሺ አሁን በጠቀስኩት ቀን ሰዓት እና ቦታ ምን ተከሰተ ምንድን ነው ያዩት ነገር እርስዎ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ያው በዛን ሰዓት እዛ ቦታ ላይ ከተሰጠን ኦረንቴሽን ተነስተን እዛ ቦታ ላይ ከዋዜማው የአካል ፍተሻ ነበር በእለቱ ደግሞ
- ✓ የምን ዋዜማ?
- ✓ ይሄንን ወረቀቱን ከመፈተሻችን ዋዜማ የአካል ፍተሻ ነበረ በእለቱ ደግሞ የመኪና እና መኪና ውስጥ ያሉት ሰወች ፍተሻ ነበረ እና በዛን ወቅት እዛ ቦታ ላይ ያው በተሰጠን
- ✓ ማን ነው ይሄንን ፍተሻ የሚያደርገው?
- ✓ ፍተሻውን እኛ ነን የምንፈትሸው
- ✓ ምንድን ነው ሥራዎ እርስዎ በምን አግባብ ነበረ ሲፈትሹ የነበረው?
- ✓ እምንፈትሸው ያው ከኃላፊዎች በተሰጠን ኦረንቴሽን ነው
- ✓ ከምን ኃላፊዎች ?
- ✓ ከእኛው ኃላፊዎች ማለት ነው
- ✓ የእናንተ ቢሮ ምንድን ነው ስራችሁ?
- ✓ ማለት ኃላፊዎች በዛን ሰዓት የሰጡን ኦረንቴሽን በዛን ወቅት አዲስ አበባ ውስጥ
- ✓ ይኸውሎት የኔን ጥያቄ ይመልሱልኝ የኔ ኃላፊዎች በተሰን ኦረንቴሽን መሰረት ብለዋል ምንድን ነው ስራቸው ኃላፊዎቹ የእርስዎ ስራ ምንድን ነው ለፍ/ቤቱ መገለጽ ስላለበት ነው ?
- ✓ ኃላፊዎቹ ያው የእኛ የቅርብ ኃላፊዎች ናቸው የእኛ ተቆጣጣሪዎች ማለት ነው
- ✓ ዝርዝር ጥያቄ የተገባው ወደ ግለሰቡ ስለሆነ ስራህ ምንድን ነው አድራሽ ምንድን ነው ወደሚል ከሆነ ይሄ ፍ/ቤት አንዴ ከለላ ያስፈልጋችኋል ብሎ ብይን ሰጥቷል ስለዚህ እንዲህ በሆነ ጊዜ ምስክሩ ምናልባት ላያውቁ ይችላሉ ምስክሩ ያሎት መብት 1ኛ ሥራዎን ያለመናገር የአባት ስም እና የአያት ስም አለመናገር አድራሻዎን ያለመናገር መብት አሎት ይሄንን አውቀው አይጐዳኝም ብለው የሚያስቡ ከሆነ መመለስ ይችላሉ ይጐዳኛል ብለው የሚያስቡ ከሆነ ለፍ/ቤቱ እያመለከቱ የሚታለፈውም ጥያቄ እርስዎን ብቻ በተመለከተ ሌላ አደለም እርስዎን የሚጐዳ በዚህ በአድራሻ ዙሪያ በሌላ ዙሪያ የተሰጠውን ከለላ እሱን ይጐዳኛል ብለው ካሰቡ ለፍ/ቤቱ ማመልከት ይችላሉ አይጐዳኝም ብለው
- ✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር ይሄን ኦረንቴሽን የሰጡት የእርስዎ የቅርብ አለቃ ማእረግ አላቸው ?
- ✓ ትክክል እኔም ያው ስራዬ ፖሊስ ነኝ ኃላፊዬም ማእረግ አላቸው ለኔ በጣም የቅርብ የሆኑ ም/ሳጅን ስማቸውን መጥቀስ እችላለሁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አይ. ቢቃ ም/ሳጅን የአባታቸውን ስም ሳይገልፁ ም/ሳጅን ማን ናቸው ትእዛዝ የሰጡት?
- ✓ አበራ ይባላሉ
- ✓ እሺ. ምን እንዲያደርጉ ነበረ ትእዛዝ የተሰጡት?
- ✓ ፍተሻ እንድፈትሽ
- ✓ ምን አይነት ተሽከርካሪ ነበረ ስትፈትሹ የነበረው?
- ✓ ስንፈትሽ የነበረው ያው ፒካፕ ነው ባለ ሁለት ጋቢና አይሱዙ
- ✓ የሰሌዳ ቁጥሩን ያስታውሱታል?
- ✓ በትክክል 3574ኤአ
- ✓ ማን ነበር የሚያሽከረክረው ይሄን መኪና?
- ✓ ባእሙ ጨሌሃ ይባላል
- ✓ ሌላስ ማን ነበር መኪና ውስጥ?
- ✓ መኪና ውስጥ ያው አንደኛው ሙራድ ሽኩር ናቸው ለላም ደግሞ ጀማል አብዱልቃድር የሚባል አለ
- ✓ አይተዋቸዋል የዛን ቀን አቶ ሙራድን መኪና ውስጥ?
- ✓ ማየት አይቻቸዋለሁ ግን እኔ ማለት 1ኛ ጨለማ ስለሆነ 2ኛ ደግሞ ትኩረታችን ስራው ላይ ስለነበረ መልካቸውኝ በደንብ አጣርቼ
- ✓ አንድ ሰዓት ተኩል ያሉት ከምሽቱ ነው?
- ✓ አዎ ከምሽቱ ነው
- ✓ እሺ. ከዛስ ፈትሻችሁ ምን አገኛችሁ?
- ✓ ስንፈትሽ ያው በጣም ብዛት ያለው ወረቀት በሦስት ቦታ በክብ በክብ ተጠቅልሎ የሆነ ፌስታል ዉስጥ ተቀምጧል
- ✓ ምን አይነት ወረቀት ነው?
- ✓ ነጭ ወረቀት ማለት ነው
- ✓ ምን ባዶ ልሙጥ ነጭ ነው?
- ✓ አይ ውስጥ ከተጠቀለለው ከውስጥ ያው የራሱ የሆነ ጽሁፍ ይዟል
- ✓ እህ ለማየት ችለዋል እንደ ጽሁፉን?
- ✓ በትክክል
- ✓ ምን ይላል ይዘቱን ያስታውሳሉ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ይዘቱ ድምፃችን ይሰማ ይላል አንድነታችንን እና ማንነታችንን ለመሸጥ ቆርጠው የተነሱትን የመጅሊስ አመራሮች ምናምን የሚል ጽሁፍ አለ
- ✓ የመጅሊስ አመራሮች ምን እናድርግ ይላል?
- ✓ አይ እስከዚህ ድረስ ያለውን ነው
- ✓ ሌላስ ተጨማሪ የሚያስታውሱት ይዘት አለ ?
- ✓ አይ ከዚህ የተለየ የማስታውሰው የለኝም
- ✓ ጽሁፉ ግን ይሄ ብቻ ነው ወይስ አያስታውሱትም ሌላውን?
- ✓ አይ ጽሁፉ በአብዛኛው እኔ ልብ ያልኩት ይሄን ብቻ ነው
- ✓ ልብ ያልኩት ማለት ያዩት እርስዎ ያነበቡት ነው?
- ✓ ያየሁት እና ያነበብኩት ማለት ነው
- ✓ ምን ያህል ይሆናል ብዛቱን ያስታውሱታል ወይን ተቆጥሯል በፊታችሁ?
- ✓ አይ ፊቴ እንኳን አልተቆጠረም በግምት ቢያንስ ከዘጠኝ መቶ እስከ አንድ ሺ አካባቢ ይሆናል
- ✓ ስንት ጥቅል ነው?
- ✓ ሦስት
- ✓ ሁሉም አንድ አይነት ነው ጽሁፉ?
- ✓ አይ እኔ ሙሉ በሙሉ ጠቅላላ አላየሁትም አንዱን ጥቅል ብቻ ነው
- ✓ ማን ነበረ ይዞት የነበረው ይሄንን ነገር የማን ነው ተባለ ይሄ ወረቀት ?
- ✓ አይ ለጊዜው አሽከርካሪ ነው እኔ የጠየቅኩት ያው የሳቸው ነው ያለኝ እሱ
- ✓ የማን ነው?
- ✓ የሙራድ ሽኩር
- ✓ እሳቸውስ ምን አሉ?
- ✓ እሳቸው በወቅቱ ማለት በጣም የመደንገጥም አይነት ነገር ስለነበረባቸው ለጊዜው ብዙም እዛ ቦታ ላይ አልተናገሩም እና እኔም ያደረግኩት በወቅቱ ወዲያው ለኃላፊ አሳውቄ ሃላፊ ወደሚመለከተው ቦታ ነው ይዞ የሄደው
- ✓ እሺ ይሄ ሦስቱ ጥቅል ተለያይቶ ነበረ የተቀመጠው ወይስ በአንድ ቦታ ነወ?
- ✓ ሦስቱ ጥቅል አንድ ላይ የሆነ ጥቁር ፌስታል ውስጥ ነበረ የተቀመጠው
- ✓ ፌስታሉ ማንን ነበረ ማን ነበረ ይዞት የነበረው ወይንም ከመኪናው የኋለኛው ነው የፊተኛው የቱጋ ነው ያገኛችሁት?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ አይ መኪና ውስጥ ነው ከፊተኛው ጋቢና ማለት ነው

✓ ጋቢና ማን ነበረ ተቀምጦ የነበረው?

✓ ጋቢና የተቀመጠው ጀማል አብዱልቃድር ነው

✓ እሺ ነገርየውስ የት ነው የተገኘው ይሄ ጥቁሩ ፌስታል?

✓ እዛው ጋቢና ውስጥ ነው

✓ ጀማል አብዱልቃድርን የማን ነው ብላችሁታል?

✓ አይ የማን ነው ብዬ እኔ አልጠየቅኩትም

✓ እሺ ከዛስ ምን አደረጋችሁ?

✓ ከዛ በኋላ ያው እኔ እንደዚህ አይነት ሃሳብ ያለው ወረቀት አለ ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ ብዬ ለኃላፊዬ አሳወቅኩ ኃላፊ መጣ ወዲያው ወደ ጣቢያ ነው ይዘው የሄዱት

✓ ከዛ በኋላ የሆነውን ያውቃሉ?

✓ ከዛ በኋላ ያለውን እኔ አላውቅም መጨረሻውን በማግስቱ ባየሁው ነገር ላይ ቃል ስጥ ተባልኩ እኔም ቃል ሰጠሁ

✓ እሺ ስትፈትሹ የነበረው መኪና እሱን መኪና ብቻ ነው ወይስ ሌሎቹንም መኪና በጠቅላላ ነው ስትፈትሹ የነበረው?

✓ አይ ሌላም መኪና ፈትሸናል

✓ እንድትፈትሹ ትእዛዝ የተሰጣችሁ ምን አይነት መኪና ነበር?

✓ ማንኛውንም መኪና ነው

✓ አሃ ማንኛውንም መኪና እያስቆማችሁ ትፈትሹ ነበረ በወቅቱ?

✓ እሺ ይሄኛው መኪና ቅድም ሰሌዳ ቁጥሩን ነግረውናል የመኪናውን አይነት ነግረውናል የማን እንደሆነ ያውቃሉ?

✓ የድርጅት መኪና እንደሆነ ነው የማውቀው እኔ

✓ የማን ድርጅት?

✓ አልበር ዴቨሎፕመንት ኤንድ ኮፕሬሽን አሶሴሽን የሚል ድርጅት

✓ በምን አወቁ የዚህ ድርጅት መሆኑን?

✓ ማለት አጣርቼ ነው እኔ ጠይቄ ማለት ነው

✓ ሹፌሩን ነው በወቅቱ የጠየቁት?

✓ አዎ

✓ ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- ✓ አቶ አበበ ቅድም ጨለማ ነበረ መልኩን መለየት አልቻልኩም ብለዋል መልኩን ካለዩ ሙራድ መሆኑን እንዴት አረጋገጡ ታዲያ?
- ✓ ስሙን ጠይቄ ማለት ነው ያወቅኩት
- ✓ ማንን ነው የጠየቁት?
- ✓ እዛው መኪና ውስጥ በወቅቱ የነበሩትን ስማቸውን እየመዘገብኩ በማስታወሻ ይዤለሁ
- ✓ እኮ ስም የነገሮት ማን ነው?
- ✓ እሳቸው
- ✓ እኔ ሙራድ ነኝ አሉ?
- ✓ ትክክል
- ✓ ከዚህ ውጪ ሌላ ያረጋገጡበት ነገር የለም ?
- ✓ የለም
- ✓ ማለት እርስዎ ውጪ ሆነው ቆመው ስምህ ማን ነው ሲሉ የሚነግሮትን እየመዘገቡ ነው የወቁት አደል?
- ✓ ትክክል
- ✓ ሌላ ሰው እኔ ሙራድ ነኝ ብሎ አስመዝግቦ ከሆነስ እንዴት ማረጋገጥ ይችላል ?
- ✓ እኔ በትክክል እፊቱ ቆሜ ነዋ የጠየቅኩት ሌላ ሰው የመዘገብኩት የለም
- ✓ ወረቀቱን በፌስታል የተጠቀለለውን ጋቢና አግኝተውታል ጋቢናው ደግሞ ጀማል የሚባል ሰው ነበረ የጠየቁት ግን ሹፌሩን ነው ይሄ ፌስታል የማን ነው ብሎ የጠየቁት ሹፌሩን ነው አደል?
- ✓ ትክክል
- ✓ ከፌስታሉ አጠገብ የነበረው ግን ጀማል ነው?
- ✓ ትክክል
- ✓ ማለት ፌስታሉ አጠገብ ጀማል ነው ያለው ሹፌሩ የሙራድ ነው አሎት ስለዚህ በወቅቱ የሙራድ መሆን አለመሆኑን እንዴት አላረጋገጡም?
- ✓ ምክንያቱም እኔ በዛን ሰዓት ትኩረት የነበረውም 1ኛ በዛው በተመሳሳይም ሌላ አይነት ወረቀት እና ከተሰጠውም ኦረንቴሽን ደግሞ ሌላ የጦር መሣሪያም ይዘው አዲስ አበባ ውስጥ በተመሳሳይ አሸባሪዎች እንደገቡ ከዛ ከዛ አንፃር ኦረንቴሽን ስለተሰጠ ሌላም መኪና ላይ



http://ethcriminalawnetwork.com/

እንደዚሁ ተመሳሳይ የሆነ ነገር እናገኛለን ብለን ቀጣይ ስራችንን ነው እንጂ ትኩረት ያደረግነው እዚህ ላይ እስከ መጨረሻው ድረስ የማጣራት ስራ አልሰራሁም

- ✓ አለቃዎ ፍተሻ አድርግ ብለው ሲያዙት ከምን ተነስተው እንደሆነ ገልፀውሎታል ለምሳሌ የፍ/ቤት የብርበራ እንደዚህ ነገር አሳይተውታል?
- ✓ ስለፍ/ቤት ወረቀቱ መኖር አለመኖሩን የሚኖረው እዛው ኃላፊዎች ጋር ነው የሚያውቁት እነሱ ናቸው እኔ ግን በወቅቱ የተሰጠኝ ትእዛዝ ለኔ ብቻ አደለም ለስራ ባልደረቦቼም የተሰጠው ኦረንቴሽን ከበራሪ ወረቀት እና ሌላም የጦር መሣሪያም ይዘው አሸባሪዎች አዲስ አበባ ውስጥ እንደገቡና በዚህም መኖር አለመኖሩን በፍተሻ ማረጋገጥ እንዳለብን በዚህ ላይ ጠበቅ ያለ ቁጥርር እንድናደርግ እና በቁጥጥሩ ላይ በፍተሻው ላይ አስፈላጊውን ስራ እንድንሰራ ነበር በወቅቱ ኦረንቴሽን የተሰጠን
- ✓ ሌሰ ጊዜስ እንደዚህ አይነት ፍተሻ አድርገው ያውቃሉ?
- ✓ ቆይቷል እንጂ እንደዚሁ አይነት ፍተሻ እናደርጋለን
- ✓ ያኔም ያዘዙት የቅርብ አለቃዎ ነው ወይስ የበላይ አለቃ ነው ?
- ✓ ያው ለእኔ የሚያዘኝ የቅርብ ኃላፊ ነው ለሱ ደግሞ በየደረጃው የበላይ ኃላፊ እያየዘው በየደረጃውን ጠብቆ ነው ትእዛዙ የሚመጣው
- ✓ ቅድም መልክ ለመለየት ተቸግረው እንደነበረ ነው ማታ በሌላ በኩል ደግሞ ወረቀቱን አንብቤያለሁ አሉ መልክ ለመለየት ሳይችሉ ቀርተው ይሄ ደቃቁን ጽሁፍ እንዴት ሊያነቡ ቻሉ ?
- ✓ መክንያቱም እንደዚህ ተመሳሳይ የሆነ ወረቀት ሌላ መኪና ውስጥ ተይዞ ስለነበረ በዛው በቅርብ ኃላፊዬ በዛኑ እለት ማለት ነው በዛው አካባቢ ላይ እንደዛ አይነት ወረቀት ስለተገኘ አብዛኛው ትኩረታችን እንደዚህ ወረቀቶች እና ሲዲ ምናምን ካለ ይሄን የማጣራት ስራ ነበር የሰራነው
- ✓ መኪና ውስጥ ስንት ሰው ነን ነበረ ያሉት አጠቃላይ ቆጥረውታል ውስጥ የነበረውን ሰው?
- ✓ አጠቃላይ እስከ ሹፌሩ 3 ነበረ የማውቀው
- ✓ ከዘጠኝ አቶ እስከ አንድ ሺ ይሆናል ብዛቱ ብለዋል ይሄ እርስዎ ያዩ የተወሰነውን ነው ያነበቡት ከምን ተነስተው ነው ይሄንን ግምት የሰጡት?
- ✓ ግምቱን የሰጠሁበት ምክንያት ወረቀቱ በጣም ብዛት ያለው ነው 3 ቦታ ነው የተጠቀለለው ግምት ነው ደግሞ ቆጥሬ አደለም በግምት ይሄን ያህል ይሆናል ብዬ ነው
- ✓ በንጋቱ ነው ቃል ያሰጡት እርስዎ ወረቀቱ እንደተያዘ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ቃል የሰጠሁት በማግስቱነው
- ✓ ከዛ በኋላ ቃል አልሰጡም የት ነበረ የሰጡት መጀመሪያ ቃል ሲሰጡ የት ነበረ ቃል የሰጡት?
- ✓ መጀመሪያ ቃል ስሰት መምሪያ ንፋስል ላፍቶ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ ቃል ሰጠሁ ድጋሚ በ12
- ✓ ድጋሚ ማለት ከስንት ጊዜ በኋላ ከስንት ወር በኋላ?
- ✓ ያው ከሚያዝያ እስከ መስከረም ያለውን ወር ማስላት ይቻላል
- ✓ እሺ ሚያዝያ ላይ መጀመሪያ ቃሎትን ሰጥተው ይሄ በዚህ ጉዳይ ቃሎትን ሰጥተዋል በድጋሚ መቼ ሰጡ?
- ✓ መስከረም ወር ውስጥ
- ✓ የት ሰጡ በዚህ ጊዜ?
- ✓ ማእከላዊ
- ✓ ቅድም ወረቀቱን ሲነግሩን ይዘቱንም ነግረውናል ምን የተቆራረጠ ወረቀት ነው ሙሉ ወረቀት ይሄ ፕሪንት የሚደረግ ወረቀት ያውቁታል ለፕሪንት የሚሰጥ ትልቅ ወረቀት አለ የተቆራረጠ ወረቀት አለ እንዴት አይነት ነበረ ወረቀቱ?
- ✓ ወረቀቱ አልተቆራረጠም ልሙጥ ሉክ ማለት ነው የተቆራረጠ አደለም ይዘቶቹ ግን ያው እዛ በወረቀቱ ላይ መሃል መሃል ላይ በአጭር በአጭር የተፃፉ ናቸው
- ✓ ማህተም ፊርማ አለው እንዴ?
- ✓ ማህተም የለውም እኔ አላየሁም ማህተም
- ✓ ፊርማም የለውም?
- ✓ ፊርማውንም አላየሁም
- ✓ ከታች ወረቀቱ ከከሌ የተፃፈ ብሎ የሚል ነገር አለው?
- ✓ ከዚህ ውጪ ሌላ ነገር ያነበብኩት ነገር የለም
- ✓ በእለቱ ተመሳሳይ ወረቀት ይዟል እንዴ ከሌላ?
- ✓ ሌላ ወረቀት አላገኘሁም
- ✓ ከዚህ ብቻ ነው?
- ✓ ትክክል
- ✓ እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. የተከበረው ፍ/ቤት አ/ሳጅን በወቅቱ ተከሳሹን ስሙን ጠይቄ ነው ብለዋል እስቲ እንደፖሊስ ሌላ ማንነቱን ለማረጋገጥ ያዩት ነገር የለም ?
- በዛን ሰዓት ያደረግኩት ነገር የለም ምክንያቱም ጊዜም አልነበረኝም ያው ቀጣይ ስራ እንድሰራ ነው እንጂ ትእዛዝ እየተሰጠኝ የነበረው ይሄንን ጊዜ ሰጥቶ በዚህ ላይ ሰፋ ያለ ነገር እንዳጣራ ጊዜም ስላልነበረኝ ሌላ ስራ ወደ ቀጣይ ስራዬ ነው
- ምንድን ነው ያደረጋችሁት ወዲያው ሰወቹን ለቃችኋቸው እንዴ?
- አልተለቀቁም በፖሊስ ታጅበው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ነው የሄዱት
- በማግስቱስ አላገኟቸውም እዛ ፖሊስ ጣቢያ ?
- ፖሊስ ጣቢያ መኪናውን ብቻ ነው እራጂ ያገኘሁት ሰወቹን እኔ  አላገኘሁም
- እሺ. እነሱስ ቃል ሰጥተዋል አደል በማግስቱ ?
- ስለነሱ ቃል ይስጡ አይስጡ እኔ የማውቀው ነገር የለም ምክንያቱም እኔ እዛጋ የራሴን ስራ ነበረ እንጂ የምሰራው እነሱን ተከትዬ እዛ ቦታ ላይ ቃል ይስጡ አይስጡ
- አይ እርስዎ ለፖሊስ ቃል ሲሰጡ አሁንም ስማቸውን እዛ ማታ ላይ እሳቸው ነግረዎት በእጅ ጽሁፍ እርስዎ በማስታወሻው የያዙትን መሰረት አድርገው ነው ወይስ መርማሪ ፖሊሱ ማንነታቸውን አረጋግጦ ነው ሙራድ ሽኩር ያሉት?
- አይ መርማሪው ስማቸውን ታስታውሳለህ ወይ አለኝ እኔ ስማቸውን በውል በእለቱ በማስታወሻ ይዣለሁ እነ እከሌ እከሌ ይባላሉ ብዬ ነግሬዋለሁ
- ምን አለ መርማሪው ያኔ?
- ምንም ያለው ነገር የለም ያው የሰጠሁትን ቃል ነው የተቀበለኝ
- እሺ. ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ. የፍ/ቤቱ ጥያቄ
- እሺ. እስቲ አሁን ማታ  አንድ ሰዓት ተኩል ነው ፊታቸውን ለይቼ አላየሁም ብለዋል እና ወረቀቱን እንዴት አነበቡት?
- ወረቀቱን መብራት ወዳለበት ቦታ ይገፍ ሄጄ ነው ያነበብኩት
- መብራት ወዳለበት ቦታ ይዘው ነው ያነበቡት ?
- ትክክል
- ጨርሰዋል እናመሰግናለን ቀጣይ ምስክር
- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ምያለሁ
- ✓ እሺ ለምስክርነት ነው የመጡት አደል?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ ስሞን መግለጽ
- ✓ ኤልያስ
- ✓ ስንተኛ ላይ የተጠቀሱ ናቸው አቃቤ ሕግ
- ✓ በተሰሙት ልክ 59ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል በክሱ ዝርዝር 85 ላይ የተጠቀሱት አቶ ኤልያስ ቀርበዋል እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አቶ ኤልያስ?
- ✓ ያሲን ኑር፣መሃመድ አለሙ አብደላ
- ✓ ተረጋግተው የሚያስታውሱትን ብቻ
- ✓ አብዱራዛቅ የ3ኛ ስም ትንሽ እንትን ብሎኛል ትንሽ ቆይቼ
- ✓ 3ኛ ስሙ ጠፍቶብሃል?
- ✓ አዎ አመጣዋለሁ
- ✓ ሌላ ሰው አለህ ?
- ✓ ሦስት ሰወች
- ✓ እነዚህን አሁን በስም የጠሩትን እና ስሙን ያላስታወሱትን ተከሳሽ በአካል ለይተው ማወቅ ይችላሉ ?
- ✓ አዎ ትንሽ ቆይቷል ለማየት በመሞከር እችላለሁ ትንሽ ግን የቆየ ስለሆነ ለማየት የሚቻል ከሆነ እሞክራለሁ
- ✓ እሺ ሞክር
- ✓ ተነስተህ ማየት ትችላለህ መናገር ትችላለህ ወይ ስንተኛ ላይ የተቀመጠ ኢኸው ማለት በልብስ ንገሩኝ እሱ ነው ?
- ✓ 1ኛ እሱ ነው
- ✓ እሱ ማን ነው ስሙ?
- ✓ እሺ በስም ማወቅ ካልቻልክ ሌላኛውን /ግልጽ ያልሆነ/ እሱ መሃመድ ነው መሃመድ ማን ትክክል ነው ስንተኛ ነው 8ኛ እሺ ቀጣዩን መቀመጥ ትችላለህ
- ✓ እሺ ምስክሩ 8ኛ ተከሳሽን ለይቷል ሌሎቹን አላስታውስም /ግልጽ ያልሆነ/ ብሏል ከሃመድ ጋር ዝምድና ወይ ጥላቻ አለህ?
- ✓ የለም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ. ምንድን ነው ያየኸው እስቲ አጠር አርገህ ክሦስቱ?
- ✓ እኔ ወደ ለስራ ጉዳይ ወደታች ስወርድ
- ✓ ምን አየህ እስቲ አጠር አርግና ?
- ✓ ከኢሜል ውስጥ ተጠርተን እኛ ቀድመን ውስጥ ነበርን
- ✓ ታዛቢ ነው የሆንከው?
- ✓ ታዛቢ ነኝ ከውስጥ ተቀምጠን ነበር ቁጭ ብለን
- ✓ እሺ. አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- ✓ እሺ. አቶ ኤልያስ እስቲ አሁን በችሎት የለዩዋቸውን ተጠርጣሪ መቼ ነው ያዩዋቸው?
- ✓ በ26
- ✓ ምን 26 ምን ወር ?
- ✓ ነሐሴ
- ✓ ነሐሴ ስንት?
- ✓ 26
- ✓ እሺ. አመተምህረቱ?
- ✓ 2004
- ✓ ስንት ሰዓት አካባቢ ነው?
- ✓ ሰዓቱ አራት ሰዓት
- ✓ ከጠዋቱ ነው ምሽት ስንት ሰዓት ?
- ✓ ጠዋት
- ✓ እሺ. የት አካባቢ ነው ያዩዋቸው ?
- ✓ ፌደራል ወንጀል በታዛቢነት ገብቼ
- ✓ ማን ነው ታዛቢ እንዲሆኑ የጠየቆት?
- ✓ በዛ ሳልፍ በዛ አካባቢ በአጋጣሚ የስራ ጉዳይ ተጠርቼ ገባሁኝ እና እኛ ቀድመን ቁጭ ብለን አጠገን መሆን ያለበትን አየን እሳቸውን ያመኑበትን
- ✓ መቼ ነው እስቲ ቆይ ከገቡ በኋላ የት ነው ቢሮ ቁጥሩን ምናምን ያስታውሱታል?
- ✓ ቢሮ ቁጥሩን አላስታውሰውም
- ✓ ምን አይነት ክፍል ነው ቢሮ ምን አይነት ክፍል ነው?
- ✓ ኮምፒውተር ያለበት ነው ኮምፒውተር ክፍል ውስጥ
- ✓ ስንት ኮምፒውተር አለ ክፍል ውስጥ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ሃስት አራት ኮምፒውተር አለ
- ✓ እሺ ወምበር ጠረጴዛ ምናምንስ አለ ?
- ✓ አለ አዎ
- ✓ ስንት ወምበር አለ?
- ✓ የቢሮ ፋሲሊቲ የተሟላ ነው ወደ 3 ወምበር ጠረጴዛ
- ✓ እዛ ሲገቡ ማንን አገኙ?
- ✓ እኔ ከፍቼ እነሱ ያጠነጠኑትን እንዳየሁ እነሱ ተጠርተው መጡ
- ✓ ማንና ማን ?
- ✓ አሁን የተባሉት
- ✓ ብቻዎን ነው የገቡት እርስዎ ከእርስዎ ጋር ማን ነበር?
- ✓ እኔ ገባሁኝ ከዛ እነሱ ተጠርተው ቀረቡ
- ✓ ማን ነው ተጠርተው የመጡት?
- ✓ አቶ መሃመድ
- ✓ እሺ?
- ✓ ፈረምን አየን ከኮምፒውተሩ አጠገብ ሆኜ እሳቸው ከፊቱ መሆን ያለበትን አደረጉ ያመኑበትን እየፈረሙ እኛም አንብበን እየፈረምን
- ✓ ስማቸው መሃመድ መሆኑን እንዴት አወቁ?
- ✓ በዛን ሰዓት ገብተን አምነውበት ወረቀቱ ላይ እንትን ስል የተፃፈ ነበር አንብበን
- ✓ እስቲ ተረጋጉና እስቲ ቀስ እያሉ እኔ ለምጠይቀው ጥያቄ እንትን ይሉናል ማለት ምን ሲያደርጉ ነው ያዩዋቸው እርስዎ?
- ✓ እሳቸው እኛ ገብተን ቁጭ ካልን በኋላ አምጥተው
- ✓ ለምን እናንተ እዛ እንደገባችሁ ተነግሯችኋል?
- ✓ ወንጀል ምርመራው ለኤግዚቢትነት የተያዘው ነበሩ አመጡ መግባት ያለበትን እራቸው አሳይተውን ተከፈተ እራሳቸው አድርገው ያመኑበትን አደረጉ
- ✓ እናንተ እዛ ክፍል ለምን እንደገባችሁ
- ✓ /ግልጽ ያልሆነ/
- ✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እናንተ ለምንድን ነበረ የገባችሁት እዛ ?
- ✓ ለታዛቢነት
- ✓ ምን ታደርጋለህ ተብልክ ለምሳሌ አንተ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ምንድን ነው የምትታዘባለህ ምን ሲሆን ትታዘባህ ነው የተባልከው?
- ✓ ያው ኮምፒውተር እስከ ላፕቶፑ የወጣውን አይተን ወጥቷል አይተናል በጽሁፉ ማንበብ አልተቻለም ቋንቋው የተለየ ስለሆነ እሱን አይተን ፕሪንት ተደርጎ የወጣውን ፊርመን የሳቸውን ስም አይተን
- ✓ እሺ. ሌላስ ከዚህ ሌላ የታዘቡት ነገር አለ?
- ✓ አዎ አሁን ስሙ ትንሽ የጠፋኝ አንደኛው ቪዲዮ ነበረ
- ✓ ምን አይነት ሰው ነው በመልክ በቁመት በምን ያስታውሱታል?
- ✓ አዎ እሱ ነው መልኩን አይቶ የመጣልኝ
- ✓ ስሙንም እረስተውታል?
- ✓ ትንሽ ስለዘገየ ጠፋ አለኝ እንጂ አስታውሰዋለሁ እሱ ቪዲዮውን አምጥቶ እኛ ከገባን ቁጭ ብለን አያለን ክር አለው ቪዲዮ ውስጥ እሱን በምስል አይተናል እጁ ላይ የሆነ ቁስል ያለው ይሄን በፋሻ የተጠቀለለ እዚህ ላይ የታሸገ ምስሎችን አይቻለሁ በቪዲዮ ላይ
- ✓ ሌላስ ?
- ✓ ሌላ ምንም አላየሁም እሱን
- ✓ እሺ. ሌላ ተከሳሽስ አይተዋል ሌላ የታዘቡት ነገር አለ?
- ✓ ያሲን ኑር እሱ ላይ ልክ እንደአሁኑ መጥተን የወጡትን አምኖበት እሱ እራሱ የፈረመበትን እኛም አይተን ፊርመን
- ✓ እንዳመነበት በምን አወቁ የተናገረው ነገር አለ ምን እያለ ነበረ ሲያወራ የነበረው?
- ✓ ከእንትን ውስጥ ከራሱ ኮምፒውተር እና እንትን ውስጥ ሲወጣ ተጠይቆ እንደውም አንደኛው የሆነ ይሄ እንትን አላሉበትም ብሎ ይሄ ከዚህ ውስጥ ነው የወጣው እኛ እራሳችን ተነጋግረን የነበርነው ይሄ ከዚህ ውስጥ ነው የወጣው ያንተ ነው በሚል ተነጋግረን ተማምነን እሱም አምኖ ፈርመናል
- ✓ ምን እዚህኛው ላይ የተለየ ሃሳብ ነበረው?
- ✓ አንድ የሆነ ወረቀት ላይ ትንሽ እንደዚህ ብዥታ የሚፈጥር ሃሳብ አቅርቦ ከዚህ ውስጥ ነው የወጣው ከሌላ የመጣ የለም ተባብለን አሁን ያልኩት ያየሁት ሰው ይመስለኛል እሱ እንደዚህ አይነት ነገር ጠየቀኝ አቅርቦ ነበረ ተማምነን ተነጋግረንበት ወደዛው አምኖ ፈርሞ ሰጠን እኛም ፈርመን ተቀበልን
- ✓ እሺ. አንብባችሁታል እንዴ ወረቀቱን እናንተ?
- ✓ እንግሊዘኛ ምናምን እንትን ስለሆነ አላነበብኩትም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አማርኛውን አረብኛውን አላነበባችሁም ?
- ✓ አላነበብንም ብዛት ስለነበረው በዛን ሰዓት
- ✓ ነውን በማምት ታስታውሱታላችሁ?
- ✓ አላስታውሰውም ብዛት አለው እየፈረምን ነበር በቁጥር አላስታውሰውም
- ✓ በምን በምን ቋንቋ ነበረ የተፃፈው ሰነዶቹ?
- ✓ እንግሊዘኛ ፣በአረብኛ
- ✓ ተቃውሞ አለን መጀመሪያ መርተው ነበረ የጠየቁት በረብኛ በእንግልዚህ በአማርኛ ስለተፃፈ ነው ያላነበባችሁት አሉት አለፍኩት አላነበብነውም ስላሉ ይሄ ጥያቄ ሊታለፍ ይገባል ሊመዘገብ አይገባም አሁን ደግሞ ከነገረው በኋላ አቃቤ ሕጉ ሊያስመሰክር ነው እንጂ ሊመሰክር አደለም በምን በምን ቋንቋ ነው ቋንቋውን ከነገረው በኋላ በምን በምን ቋንቋ ብሎታል ጥያቄው ሊታለፍ ይገባል አግባብ አደለም
- ✓ ምላሽ ይስጡበት
- ✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አይ መጀመሪያው ላይ መርተን ከሆነ ያኛውን ጥያቄ መቃወም ነው እኛ አሁን ያልነው ሰነዶች በምን በምን ቋንቋ ነው የተፃፉትነው የሚል ነው አላነበብንም የሚል ነው በእንግሊዘኛ የተፃፈውን አላነበብንም አሉ በሌሎች ቋንቋ የተፃፉትስ አሉ ወይ ለምንድን ነው ያላነበባችሁት አላነበብንም ነወ መልሳቸው ድፍን ያለ ነው እና አሁን የተነሳው ጥያቄ ጠቅላላ ነው መሪ አደለም በምን በምን ቋንቋ የሚል ጥያቄ ነው እና ምናልባት ከነዚህ ከሁለቱ ቋንቋ ሌላ ቋንቋም ሊኖር ይችላል አይታወቅም ከአረብኛ ከአማርኛ ምን እንደሚመልስ  አይታወቅም እና ተቃውሞው አላግባብ ነው
- ✓ እሺ ብይን ተሰጥቷል ጥያቄው መሪ ነው ሊቀጥል አይገባም የሚል መቃወሚያ ቀርቧል መሪ አደለም የሚል ምላሽ ተሰጥቷል ፍ/ቤቱ መሪ ነው ወይስ አደልም የሚለውን አይተውት መጀመሪያ አቃቤ ሕግ የጠየቁት በእንግሊዘኛ አማርኛ እና ከዛ አረብኛ ስለተፃፈ ነው አደለ ያላነበባችሁት የሚለው መሪ ነው ነገር ግን መቃወሚያ አልቀረበበትም ያኔ በኋላ ላይ በምን በምን ቋንቋ የተፃፈ የተባለው መሪ አደለም ስለዚህ የመጀመሪያው መቃወሚያ የቀረበበት አሁን እንደምክንያት ሆኖ ሊነሳ ስለማይችል በኋላ የተጠየቀው ጥያቄ ደግሞ መሪ ስላልሆነ የኋለኛው ጥያቄ ተገቢ ነው ይቀጥል ብለን ብይን ሰጥተናል
- ✓ በምን በምን ቋንቋ ነበር ሰነዱ የተፃፈው?
- ✓ እንግሊዘኛ ፣ ላቲንኛ

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አሁን እንደዚህ እየተጠራጠርክ ምናምንኛ ላቲንኛ እንዲህ አይነት መልስ ሊሆን አይችልም አንተ ልታውቀው የምትችለውን ነው ልታስታውሰው የምትችለውን ከሆነ ልታስታውሰው የምትችለውን ካልቻልክ ደግሞ ማስታወስ አልቻልኩም ነው እንጂ ምናምን ምናምን መልስ አይሆንም ስለዚህ በትክክል የምታስታውሰውን መልስ የማታስታውሰውን አላስታውሰውም እያልክ መልስ
- ✓ እንግሊዘኛ ነው ይሄኛው ደግሞ የተለየ ቋንቋ ነው
- ✓ እሺ እስቲ አሁን የታዘቧቸው ሰወች እስቲ በምን ሁኔታ ነበሩ እንዴት ሆነው ነበረ ሲያሳዩ የነበሩት
- ✓ አቡበከር በቪዲዮ እነዛ ደግሞ ወይተው /ግልጽ ያልሆነ/
- ✓ ምን አይነት ሁኔታ ላይ ሆነው ነበር እስቲ ተቀምጠው ነው ቆመው ነው እንዴት ሆነው ነበር ሲያሳዩ የነበረው ?
- ✓ ቁጭ ብለን ነው እኔ ከኮምፒውተር ወደዚጋ ሆኜ ነው እሱ ወደዛ ሆኖ ነው ኮምፒውተሩ እንደዚህ ፊት ለፊት ይታየናል
- ✓ ቢሮ ኮምፒውተር ክፍል ነው ብለዋል እና ምን እነማን ነበሩ እዛ እንትን ውስጥ የነበሩት እዛ ኮምፒውተር ክፍል ውስጥ ?
- ✓ አላውቃቸውም /የማይሰማ/
- ✓ የምን ባለሙያዎች?
- ✓ የፌደራል ኮምፒውተሩ እዛው ነው እዛው ቢሮ ውስጥ ነው
- ✓ ማን ነው ኮምፒውተሩን የከፈተው?
- ✓ እሱ እራሱ
- ✓ እሱ እራሱ ማለት ማን ነው?
- ✓ /የማይሰማ/
- ✓ ከምን ውስጥ ነበር እነዛን ሰነዶች
- ✓ ብዙ ተከሳሾች ነው የጠቀሱት አሁን ስለስንተኛው ነው ስለማን ነው አሁን እየመሰከሩ ያሉት?
- ✓ አሁን 3ኛ ተከሳሽ
- ✓ እኮ አሁን ተከሳሹ ብለው ያሉት ወደ 3 ተከሳሾች ነው የጠቀሳችሁት
- ✓ አሁን ያሳየሁት
- ✓ አይ ኮምፒውተር ከፈተ ያሉት



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እዎ መሃመድ እራሱ ሲዲዎቹን ውስጥ የሚደረገውን አሳየ እራሱ ነው /ግልጽ ያልሆነ/
- ✓ ቆይ ቆይ አሁንም የምልክት ቋንቋ ነው እየገለፁልኝ ያሉት
- ✓ ኢንዉሉት አሁን እርስዎ የሚያስታውሱትን ያዩትን በየአንዳንዱ ተከሳሽ ላይ ቅድም ጠቀስኳቸው በመልክ አላውቃቸውም ያሏቸውን እያንዳንዱን አሁን እኛ ማወቅ አልቻልንም እኮ አሁን ተከሳሹ ይሉናል ከሦስቱ የትኛው የሚለውን ነገር እያንዳንዱ ተረጋግተው ይግለፁ ምንም የሚያስፈራ ነገር አለ እንዴ እዚህ?
- ✓ የለም
- ✓ ስለዚህ ከሌለ በትክክል እያንዳንዱን ይግለፁልን ግልጽ እንዲሆን
- ✓ 1ኛው መሃመድ ያልኩት ነው አሁን ያሳየሁ
- ✓ እሺ ከሱ ላይ ምንድን ነው የተመለከቱት በእያንዳንዱ ላይ ቅድም ያሉትን ምን እንዳዩ እሱን ይንገሩን?
- ✓ መሃመድ ላይ ኢሜል እና ኮምፒውተር ላፕቶፕ
- ✓ እሺ ኮምፒውተሩን እና ኢሜሉን ማን ነው የከፈተው ነው ጥያቄው አሁን የመሃመድ ያሉትን?
- ✓ /የማይሰማ/
- ✓ መሃመድ እራሱ እሺ
- ✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እሺ ኮምፒውተር ነበረ ብለውናል እንደዚሁም ኢሜል ከፍተዋል ብለውናል እስቲ ምን አይነት ኮምፒውተር ነው ከየት የመጣ ኮምፒተር ነው ኮምፒውተሩ?
- ✓ አንደኛው ላፕቶፕ ነው
- ✓ አሁን የሚነግሩን መሃመድን በተለከተ ብቻ ነው የሚነግሩን እና ስለሱ ይቀጥሉ
- ✓ ፊትህን ወደዛ አታዙር እንደዚህ ቁጭ እንዳልክ ተረጋግተህ የምታውቀውን ወደዛ ወደዚህ አትበል ከዛም ከዚህም ሊሆን ይችላል ጥያቄው ፊትህን ግን ወደዚህ ወደኛ
- ✓ መሃመድ ኢሜል ነው
- ✓ እሺ ኮምፒውተሩ ማን ያመጣው ኮምፒውተር ነው ኮምፒውተር ያሉን?
- ✓ ያው ቢሮውስጥ ያለ ኮምፒውተር
- ✓ እሺ ሌላስ ላፕቶፕ ነበረ?
- ✓ በእግዚብሔትነት የተያዘ ላፕቶፕ አለ
- ✓ ምን አይነት ላፕቶፕ ነው ማርኩን ያስታውሱታል ?
- ✓ አላስተውስውም



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ከኢሜሉ ምን ያህል ሰነድ ወጣ ብዛቱን ያስታውሱታል ?
- ✓ ብዛቱን አላስታውሰውም ብዙ ነው ግን እየፈረምን ነው የተጠቀምነው
- ✓ ትድሚያ የሚፈርመው ማን ነበር ኢሜሉን?
- ✓ አቶ መሃመድ
- ✓ ምን እያለ ነበረ የሚፈርመው?እ
- ✓ አምኖ አይቻለሁ ብለው እኛ አይተናል ብለን አሳቸው ከኔ ኢሜል ላይ ወጥቷል ብለው ይፈርማሉ እኛ አይተናል ብለን ነው
- ✓ እንዴት ነበረ ማን ነበረ እንዴት ነው የከፈቱት ማን ከፈቱ ብሏቸው ነው መጀመሪያ ሲከፍቱ?
- ✓ መጡ እዛው የወንጀል እንትን ውስጥ ቁጭ ብለን እንዳለ የሳቸው ነው ተባለ እነሱ ናቸው ብለው አየን
- ✓ እነሱ ናቸው ብለው እናንተን አስተዋወቃቸው?
- ✓ አዎ እኛ መጣን ቁጭ አልን ታዛቢዎች ነን
- ✓ ታዛቢዎች ስለመሆናችሁ የተነገረ ነገር አለ?
- ✓ እ?
- ✓ ታዛቢዎች ነን ብለን ተቀመጥን ብለዋል እስቲ ይሄንን ማን ነው ያለው ማን ነው ታዛቢዎች ናቸው ያለው?
- ✓ ስንገባ የላፕቶፑ እንትኑን አይታችሁ እንድትታዘቡ ነው ተብለን እዛው ስንመጣ ገባን አይተን ወጣን
- ✓ ይሄንን ሲናገር ተከሳሽ ሰምተዋል?
- ✓ አዎ እዛው ነበር እዛው ነው ያየሁትም እዛው ነው
- ✓ እሺ ከያሲን ኑሩ ላይ ከምን ከምንድን ነው ሰነዱ የወጣው እስቲ ከምን ከምን ላይ ነው?
- ✓ ላፕቶፕ አለ ሲዲ
- ✓ እሺ ሌላስ?
- ✓ አዎ ሲዲ ላፕቶፕ አለ ላፕቶፕ አይቻለሁ
- ✓ ምን ምን ወጣ ከዚህ አሁን ካሉን?
- ✓ የተፃፈ በጽሁፍ አይቻለሁ ከኔ ኢሜል ላይ ነው የወጣው ብለው ፈርመን እኔም አይቻለሁ ከእሳቸው ኢሜል ላይ የወጣ ነው ብዬ ፈርሜያለሁ
- ✓ ይሄኛው ሰነድስ በምን ቋንቋ የተፃፈ ነበር ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እንግሊዘኛ እና አማላውተው ሌላ ቋንቋ
- ✓ ሰነዶቹን አላዩዋቸውም አያተዋል ሰነዶች?
- ✓ አዎ አያቻለሁ
- ✓ እሺ. ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ እሺ. የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄካላችሁ?
- ✓ አቶ ኢልያስ በእለቱ እርስዎ ለምን ተመረጡ ያውቁታል ምክንያቱን?
- ✓ አቤት
- ✓ ታዛቢ. እንዲሆኑ ለምንድን ነው የተመረጡት?
- ✓ በዛው ሳልፍ እዛ አካባቢ. ለስራ ጉዳይ ወደዛ ሳልፍ በዚህ ትፈለጋለህ ተብዬ ወደዛው ገባሁ
- ✓ እስቲ አገባቦን ይንገሩን ትፈለጋለህ በር ላይ ነው ትፈለጋለህ የተባሉት?
- ✓ ለስራ ጉዳይ በዛው ሳልፍ ማለት ነው
- ✓ እኮ ከግቢ. ውጭ ነው ያናገሮት?
- ✓ አዎ ሳልፍ እዛው
- ✓ ከዛ ምን አደረገ ያ ፖሊስ ይዘዎት ገባ እየመራዎት ወሰደ እስቲ እሱን እንዴት እንደገቡ?
- ✓ እኔ ለስራ ጉዳይ እዛ አካባቢ. መጥቼ ነበረ እና እዛ እንደዚህ አይነት እንትን አለ እንትን ሲሉኝ እሺ. ብዬ ፈቅደኛ ሆኜ ገባሁ
- ✓ እኮ ገቡ ከዛ ምን ያ ፖሊስ ይዘዎት ሄደ ያናገሮት አንድ ፖሊስ ነው ያናገሮት?
- ✓ ምንም ያው አሁን ለተባለው ለታዛቢነት ትፈለጋለህ እንትን እንላለን አሉ እኔም በስራ ጉዳይ እያለፍኩ ስለነበረ እተባበራለሁ ቀና ነው ብዬ ገባሁኝ ውስጥ ቁጭ አልን እንደተቀመጥን እሱ ይሄ አሁን የተባለው ተከሳሽ መጣ ታዛቢ. ናቸው እሱ ይሄ ነው ተብለን ቁጭ አልን ማየት ጀመርራ
- ✓ ጥሩ ወደ ውስጥ ገባችሁ ኮምፒውተር ክፍል ገባችሁ እስቲ ስለ ክፍሉ ሁኔታ ይንገሩን ውስጥ ገቡ ስንተ ጠረጴዛ ነበረ እዛ?
- ✓ ቢሮ ውስጥ 3 ጠረጴዛ የቢሮ ፋሲሊቲ
- ✓ ቆይ ለጥያቄው ብቻ 3 ጠረጴዛ አቀማመጡ እንዴት ነበር የጠረጴዛው?
- ✓ እንደዚህ እዚህጋ አለ እዚህጋ ለብቻው አለ ወደዚህ ጀርባ
- ✓ ጠረጴዛዎቹ እርስ በእርስ ተፋጠው ነው ያሉት ጠረጴዛዎቹ አደል ወምበር አለ ጠረጴዛ አለ?
- ✓ አዎ ኮምፒውተርም አለ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ጥሩ ተከሳሹ ለብቻው ነበረ የተቀመጠው አሁን ለምሳሌ የያሲን ኑሩን እንውሰድ ?
- ✓ እኛ ከገባን በኋላ መጣ ገባ እሱም ከኮምፒውተሩ ፊት ለፊት ተቀመጠ እኛም ቁጭ አልን
- ✓ እናንተ የትጋ ተቀመጣችሁ እሱ መጥቶ ከኮምፒውተሩጋ ቁጭ አለ?
- ✓ እኛ ቀጥለን ተቀመጥን
- ✓ ከሱ ጐን?
- ✓ አዎ
- ✓ ከሱ ጐን ነው የተቀመጣችሁት?
- ✓ ወምበር አንዳንድ ነው እራሱን የቻለ አንድ ወምበር ነው እሱን የቻለ ለብቻ ወምበር ነው እንደዚሁ አይነት ወምበር ያው
- ✓ እስቲ አንዳንድ ጥያቄዎች እየተቀረፁ ስለሆነ በኋላ ያስቸግራሉ እና ወደ ትክክለኛው ተርም እየመጡ ለምሳሌ ወምበር እና ወምበር ተፋጠው ነበር የሚል ሰው አይኖርም ምን ለማለት ነው ወይ ፊት ለፊት ናቸው ወይ ፊትና ኋላ ናቸው በትክክለኛ በኖርማል ቃል ምክንያቱም የሚፋጠጥ ሕይወት ያለው ነገር ስለሆነ ወይ ሰው በመሆኑ ምክንያት አንደኛ መፋጠጥ ሌላ ትርጉምም ስላለው ነው መጣላትንም ሲገልጽ የሚችል እንዲህ እንዲህ ትላንትም ብዙ በተደጋጋሚ ሲባል ስለነበረ እሱ ተስተካክሎ የወምበር አቀማመጥ ቋንቋዎችን ወይም ተርሞችን ብንጠቀም ለምርመራው ምቹ ይሆናል ብለን ነው
- ✓ ጥሩ እናንተ ገባችሁ ያሲን ኑሩ መጣ ከኮምፒውተሩ አጠገብ ቁጭ አለ ከዛ እርስዎ ከሱ ጐን ተቀመጡ ?
- ✓ ሁለት ነን
- ✓ ማን ነው ከእርስዎ ጋር ሌላ?
- ✓ ሌላ የማላውቀውም አንድ ታዛቢ ነበር
- ✓ ስለዚህ እሱ በመሃል ነበር በእናንተ መሃል ነበረ የተቀመጠው?
- ✓ እሱ ወደዛ እኔ ወደዚህ መሃል ላይ ሌላ ታዛቢ ነበር እማላውቀው ታዛቢ
- ✓ መሃል ላይ ሲሉ ተከሳሹ አለ እርስዎ አሉ ተከሳሹ በሁለቱ ታዛቢዎች መሃል ነው የተቀመጠው?
- ✓ ከኮምፒውተሩ አጠገብ
- ✓ ከዳር በኩል ማለት ነው?
- ✓ ከኮምፒውተሩ ቀርቦ ማለት ነው
- ✓ እኮ እናንተ ከእሱ ጐን ተከታትላችሁ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ
- ✓ መርማሪዎቹስ የት ነበሩ
- ✓ አልገባኝም
- ✓ እናንተ ታዛቢዎች እና ተከሳሹን ነግረውናል 3 ጠረጴዛ አለ ብለዋል መርማሪዎቹ እንዴት ተቀምጠው ነበር ከእናንተ ፊት ለፊት ?
- ✓ ከተከሳሹ ከተባለው ከሱ ወደዚህ ደግሞ ሌላ አንድ ሲቪል የለበሰ አለ
- ✓ ኮምፒውተር አጠገብ ነው የተቀመጠው እሱ ?
- ✓ አዎ
- ✓ አንድ ሲቪል የለበሰ ብቻ ነበር እንዴ?
- ✓ ሁለት
- ✓ ከዛ ስለ ኢሜል አንስተው ነበር ኢሜል ምንድን ነው የሚለው ስለ ኮምፒውተር ያሉት እውቀት ምን ያህል ነው ?
- ✓ ምንም እውቀት የለኝም
- ✓ እሺ ምንድን ነው ያረገው ተከሳሹ ያሲን ኑሩ ኮምፒውተሩን ምን አረገ?
- ✓ ማለት አልገባኝም
- ✓ ቅድም ኢሜል የሚል ነገር ስላነሱ ነው?
- ✓ አዎ ኮምፒውተር መጥቷል አልኩኝ ያየሁት ማለት ነው ያ ደተርጓል መውጣል ያለበት ወረቀት ወጥቶ አምኖበት ሲፈርም አይቻለሁ ሌላውን ይሄ የላይ ኮምፒውተር ሲስተሞች አላውቅም እያልኩ ነው
- ✓ ስለዚህ እርስዎ ወረቀት ወጥቶ ሲፈረም እንጂ ሌላ ያዩት ነገርየለም ወረቀቱ ይወጣል የኔ ነው ብሎ ይፈርምበታል እናንተ ትፈርማላችሁ?
- ✓ ከራሴ ኢሜል ነው የወጣው ሲል በጽሁፍ ላይም አይቻለሁ
- ✓ ከራሴ የወጣ ይላል?
- ✓ ከራሴ ኢሜል ላይ የወጣ በጽሁፍ አይቼ አንብቤ ፈርሜያለሁ
- ✓ እሺ አቶ ኤልያስ መጀመሪያ ስለ መሃመድ ልጠይቆት መሃመድ ኢሜሉን የከፈተው በፖሊሶች ኮምፒውተር ነው አደለም?
- ✓ ይደገምልኝ
- ✓ መሃመድ ኢሜሉን ከፈተ ያሉት በፖሊሶች ኮምፒውተር ነው አይደል?
- ✓ ላፕቶፑ የፖሊስ ነው ወይስ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እዛ ቢሮ ውስጥ ያለ ነው የፖሊስ ይሁን የተከሳሽ ይሁን እርስዎ አያውቁም?
- ✓ ያመጡት ከኢግዚቢቱ ላይ ነው
- ✓ አቶ ኢልያስ እምጠይቆትን ብቻ ይመልሱልኝ ኮምፒውተሩ የፖሊሶች ነው ወይ ነው ያውቃሉ ወይ ኮምፒውተሩ የፖሊስ ስለመሆኑ ወይንም የተከሳስ ስለመሆኑ የሚያውቁት ነገር አለ?
- ✓ ኢግዚቢት የተያዘ ሲባል ነው
- ✓ እኮ የተከሳሽ ነው ወይስ አደለም ነው ይሄንን የሚያውቁት ?
- ✓ የተከሳሽ ማለት ነው
- ✓ ያውቃሉ የተከሳሽ መሆኑን ?
- ✓ አዎ
- ✓ እንዴት ነው ያወቁት?
- ✓ ኤግዚቢት የተያዘ ነው ተብሏል
- ✓ እኮ ከማን ላይ የተያዘተባለ?
- ✓ መሃመድ የተባለውን እሺ ያኛውም አሁን ሦስቱ ላይም ገባሁ /ግልጽ ያልሆነ/ በዚህኛውም ቪዲዮውንም አይቻለሁ
- ✓ እሺ ለሦስቱም ተከሳሾች ልጠይቆት ለሦስቱም ተከሳሾች ፖሊስ ኢሜላቸውን ወይንም ኮምፒውተር ውስጥ ያለውን መረጃ ለመፈተሽ የፍ/ቤት ትእዛዝ ያለው ስለመሆኑ አልነገራቸውም አደል?
- ✓ እኔ እዛው ተጠርቼ ነው የገባሁት
- ✓ እርስዎ ባሉበት ዛጋር ይሄን ለመፈተሽ የፍ/ቤት ትእዛዝ አለን ብሎ አልተነገራቸውም አደል?
- ✓ አልገባኝም
- ✓ እርስዎ የፍ/ቤት ትእዛዝ ስለመኖሩ ፖሊሱ ሲናገር ሰምተዋል?
- ✓ እዛ ውስጥ ነው ያገኙኋቸው የፍ/ቤት
- ✓ አልተነገረም አደል?
- ✓ አልሰማሁትም እዛው ቦታ ላይ ስላለ የሆነ መረጃ ነው ተብሎ
- ✓ አቶ ኢልያስ ለምን ያስቸግሩናል ይገባሉት ጥያቄው ግልጽ ነው የሰሙትን እና የሚያውቁትን ብቻ ነው ቀስ ብለው ይመልሱልን ፖሊሱ ወይንም እዛ ያዩዋቸው ሰወች



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለተከሳሾች ይሄን ኮምፒውተር ውስጥ ያለውን መረጃ ለመፈተሽ የፍ/ቤት ትእዛዝ አለን ብለው ሲነግሯቸው አልሰሙም እደል?

- ✓ እሺ ተጥል የገለፀላችሁ ነገር ካለ ?
- ✓ ያው እኛ ስንገባ ይሄ በኢግዚቢትነት የተያዘ ነው
- ✓ አይ አይ እሱን ተውና ፖሊስ ኢሜሉን ለመፈተሽ የፍ/ቤት ፍቃድ አለን ብለው ነግሯችኋል ወይ ጥያቄው ይሄ ነው ነግሯችኋል ?
- ✓ በፍ/ቤት ነው ጨርሰን በሕጋዊ በፖሊስ ስነምግባር ነው አምጥተን የያዝነው ሲል ሰምቻለሁ
- ✓ የፍ/ቤት ትእዛዝ መኖሩን በጽሁፍ አሳይተዋችኋል የፍ/ቤት ትእዛዝ ?
- ✓ በጽሁፍ አላየሁም
- ✓ አቶ ኤልያስ ቅድም አልፈርምም ያለው ተከሳሽ ማን ነበረ?
- ✓ አሁን ያሳየኋችሁ
- ✓ ቆይ
- ✓ በዋና ጥያቄ ስናስመሰክር አልፈርምም ስላለ ተከሳሽ ምስክሩ አልገለፀም እና ምናልባት ሚስ ሊድ እየተደረገ ነው ያለው ይሄ ጥያቄ አላግባብ ነው
- ✓ ምላሽ
- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄው 1ኛ ተመልሷል በሌላ በኩል ግን ቅድም የተለየ ነገር አምጥቶ መሃመድ እያሉ እያስረዱ ነበር በኋላ በእሳቸው ጠያቂነት ነው /ግልጽ ያልሆነ/ ዞሮ ዞሮ ግን ጥያቄው ስለተመለሰ ነው
- ✓ ጥያቄው አልተመለሰም ሲጀምር ነው ምስክሩ ያቆሙት
- ✓ መሃመድ ብሎ እኮ አሳየ
- ✓ እኔ አለመዘገብኩትም ነገር ግን ሌሎቹ መልሰዋል ብለዋል ለማንኛውም ጥያቄው መጀመሪያ ተነስቷል አንገራግሮ ነበር በኋላ ተስማምቶ ፈርሟል የሚል ነገር ነበረው በመጀመሪያው በዚህ መሰረት የአሁኑ ተመልሷል ስለተባለ ወደ ሌላው ቀጥሉ
- ✓ ለምን ነበረ አልፈርምም ያለው አቶ ኤልያስ ?
- ✓ ወረቀቱን ሲወጣ የሆነች ጽሁፏ ላይ ፕሪንት ሲደረግ ወረቀቱ ሲወጣ ችግር ይኑር አላውቀውም የሚልነበረ እኛ እዚሁ ነው ያየነው እና ይሄ ከአንተ ኢሜል ላይ ስለወጣ ብለን ተነጋግረንበት አምኖ አድርጎታል
- ✓ ከኢሜሉ ላይ ያወጣው ማን ነው ሌላ ሰው ከኢሜሉ መሃመድ እራሱ ነው ያወጣው ወይስ ሌላ ሰው ነው ፕሪንት ያረገው ማለት ነው?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፕሪንት ሲወጣ ነው
- ማን ነው አወጣው?
- ኮምፒውተሩ ነዋ
- ያወጣው ሰው የለም ኮምፒውተሩን ያዘዘው ሰው የለም ፖሊስ ነው አደል?
- እሱማ ያዘዘው
- ፖሊስ ነው አደል?
- አዎ ከራሳቸው እንትን ላይ የወጣ ሰው አለ
- ጥያቄው ሲታዘዝ የነበረው ኮምፒውተሩ ሲወጣ የነበረው በፖሊሱ ነው ወይስ በተከሳሹ ነው ጥያቄው?
- እሱ አሁን ወረቀቱን እኔ ያልኩት ማለት ነው ወረቀቱን አይቶት ይሄ ወረቀት ፕሪንት ላይ አልነበረም ነው ይሁን ብሎ የራሱን ሃሳብ አቀረበ
- እኮ ወረቀቱን ማን ነው ያወጣው ከየት ነው የወጣው?
- ከዛው ከኮምፒውተሩ ላይ
- ኮምፒውተሩ ላይ ማን ነው ያወጣው?
- ያዘዘው ፖሊስ ነው ወይስ ተከሳሹ ነው?
- አደለም
- አልፈርምም ያለው ተከሳሹ ነው ነገር ግን ፕሪንት እንዲደረግ ኮምፒውተሩን ያዘዘው ፖሊሱ ነው ወይስ እሱ ተከሳሹ እራሱ ?
- ያው እየጠየቅን ነው እና እያቋረጡን ነው
- አቃቤ ሕግ ለምስክር መልስ ይሰጣል እዛ ተብሎ መጠበቅም ከኤቲክስ የወጣ ነው አቃቤ ሕግ የሚከሰው ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ነው ለማንኛውም ወገን አደለም ያለው ሮል ማለት ነው ስለዚህ በምስክርነት /ግልጽ ያልሆነ/ በምልክት ይናገራል ማለት አይጠበቅም ከኤቲክስ እና ስርዓት ቢያረገ ወደዛ አይዙሩ ወደማንም ብለን ለምስክሩ ደግሞ እየተናገርን ነው
- የተጠየቅከውን ጥይቄ ቀጥል
- ግልጽ ሆኖልሃል አደል ?
- አዎ
- ግልጽ ከሆነልን ማን ነው ያዘዘው የሚለውን ምላሽ ስጥ?
- ኮምፒውሩን በመጀመሪያ ያወጣው
- አዎ ኮምፒውተሩን አዎ ነካክቶ ያዘዘው ማን ነው ፕሪንት እንዲደረግ ማለት ነው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ቆይ እስቲ ከዛ በፊት ፕሪንት ማድረግ አለማድረግ ታውቃለህ?
- ✓ አዎ የኮምፒውተር እንትን አላውቅም እኮ አልኩኝ አስተድሚ ይሄንን ቃሉን ሰጥቻለሁ
- ✓ እሺ ኮምፒውተሩን ሲነካ የነበረው እና ወረቀቱን ሲያወጣው የነበረው ማን ነው ?
- ✓ የሆነ ሲቪል የለበሰ ሰው
- ✓ ሲቪል የለበሰ ሰው ነው ኮምፒውተር ሲነካ የነበረ እሺ ሌላ ጥያቄ
- ✓ እሺ አቶ ኤልያስ በወቅቱ እዛ ቢሮ ውስጥ ከመሃመድ ቅድም ከጠቀሷቸው ሰወች ውስጥ ውጪ ሌላ ሰው እዛ ቢሮ የሚያለቅስ ሰው አልነበረም ?
- ✓ አላየሁም
- ✓ መሃመድ አልፈርምም ካለ በኋላ እንዴት ሊፈርም ቻለ እርስዎ እዛ ከነበሩ ስታግባቡት ነበረ አደል እንዲፈርም ስታግባቡት ነበር ፈርም እያላችሁት ነበር አደል?
- ✓ ከኢሜል ውስጥ ከአንተከተባለው ወረቀት ላይ ነው ከየትም አልመጣም እዚሁ እያየን ነው ያለነው አሉ
- ✓ አሉት እሺ ከዛስ?
- ✓ እና እሱ እንዴት ነው እኔ የማላውቀው እዚህ ውስጥ የሚል ነገር ነበር እየመጣ ያለው ይሄ ከየትም የመጣ የለም ወረቀቱ ሲወጣ እያየነው ነውያለነው ብለን አልን
- ✓ ከእናንተ ነው የምትሉት ?
- ✓ አዎ ሁላችንም እዛ ያለነው ማለት ነው
- ✓ እሺ?
- ✓ እሱም አመነ እኛም ሌላ የተፈጠረ አዲስ ነገር የለም እዛ ውስጥ ያለ ነው አልነው እሺ ብሎ ፈረመ እኛም ከሱ ተቀብለን ከኔ ወጣ ሲል እኛም
- ✓ ስለዚህ እርስዎ ከታዛቢነት ስራ ውጪ እያግባቡት ነበረ እሱን ማለት ነው?
- ✓ እያየን ስለነበረ ሲናገር ሁላችንም ቁጭ ብለን ዝም ብለን እየተጠቀምን ነበር በዛን ሰዓት ሲናገር ይኸው ዝም ብሎ እርስ በእርስ መነጋገር አለ አደል እንደዛ አመነ ወደዛ
- ✓ ከእሱ ኢሜል መሆኑን በምን አረጋገጡ እርስዎ?
- ✓ እራሱ አምኖበት ፈርሞ
- ✓ ምን ብሎ አመነ?
- ✓ ከኔ ኢሜል ወጣ ብሎ ፈረመበት ዝም ብሎ የመነጋገር ነው በዛን ሰዓት የነበረው ወረቀቱ ከዛ እስከወጣ ድረስ ከየትም አልመጣም ብለን አልነው አመነ
- ✓ እናንተ ነገራችሁት?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እራሱም አመነ
- ✓ እኮ እናንተ ስትነግሩት እሱ አመነ እና ፈረመ?
- ✓ አዎ ወይም አይደለም በሉዋ ለፍ/ቤቱ?
- ✓ አዎ እያልኩ እኮ ነው ተነጋገርንና እዛው አመነ እሱ አምኖ ፈረመበት እኛም አምነን ተቀበልን ለእዛው ላይ አይተናል ከኢሜል ሲወጣ ብለን ፈረምንበት
- ✓ እነዚህ ዲስኮች የተያዙት ስንት እንደሆኑ ያውቃሉ ቁጥራቸው?
- ✓ በቁጥር አላውቅም
- ✓ ላፕቶፑ የማን ነበረ ያሉት?
- ✓ በኤግዚቢትነት የተያዘ የእሱ
- ✓ እኮ የማን ነበረ ያሉት ነው ጥያቄው?
- ✓ የተከሳሽ
- ✓ የየትኛው ተከሳሽ?
- ✓ አሁን እንግዲህ
- ✓ የመሃመድ ነው?
- ✓ ሁሉም አለ ኮምፒውተርም አለ ላፕቶፕም አለ ቪዲዮም አለ ይሄኛው ከተባለ ሁለቱም ላይ ኮምፒውተር አለ ላፕቶፕም አይቻለሁ
- ✓ ኮምፒተሩ የማን ነው ላፕቶፑ የማን ነው ቪዲዮ የማን ነው?
- ✓ ቪዲዮ አሁን 3ኛ ያልኩት ሰው ነው
- ✓ እሺ ኮምፒውተሩስ?
- ✓ ኮምፒውተሩ የሁለቱም ነው
- ✓ የማን እና የማን?
- ✓ የዚህኛውም የዛኛውም ያው ስማቸው ግልጽ ነው ብዬ ነው
- ✓ የተከሳሾች ማለት ነው?
- ✓ አዎ የተከሳሾች አዎ
- ✓ እርግጠኛ ኖት አደል?
- ✓ አዎ አይቻለሁ
- ✓ ምናልባት አሁን ቅርብ ስለሆንን እኛ ልናውቀው እንችላለን እዚህ የምናየው ቅድም ጠበቃ የምንነግራቸው ነገር አንተ የምትመሰክረው ይሄ ፍ/ቤት መጨረሻ ላይ አይቶ ነው የሚወስነው አንብቦ ይሄኛው ወይ ያኛው የሚል ነገር በሚገኝበት ጊዜ እናስታውሰውም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ይሄኛው የሚለውን ከሌ ይሄኛው የሚለውን ከሌ ብለህ በስም ዘርዝረህ ለእኛ ብቻም ሳይሆን 3ኛ ወገንም የሚያነበው ነው

- ✓ ያሲን ኑር መሃመድ
- ✓ እኮ የነሱ ምን ምንድን ነው ?
- ✓ ኮምፒውተር እና ኢሜል አሁን 3ኛ ያልኩት ስሙ አይያዝልኝም ቅድምም
- ✓ ሲዲ ያሉት የማን ነው ?
- ✓ ቪዲዮ አፊ ላይ አልመጣልኝም አሁን አስታውሼ ነግሬያለሁ ሲዲ የያዘው እሱ ነው ቁስል
- ✓ ስሙን ያላስታወስከው ሰው ምንድን ነው የቡ?
- ✓ ቪዲዮ
- ✓ ቪዲዮ ማለት ምንድን ነው?
- ✓ ካሜራ
- ✓ የተቀረፀ ነው?
- ✓ የተቀረፀ ውስጡ ክር አለው ድምጽ  አልሰማሁም ውስጡ ያለውን አይተን ቁስል እጁ ላይ አለ እጅ ላይ የተመታ
- ✓ እሱ ማለት ቪዲዮ ላይ ያለ ነው?
- ✓ አዎ
- ✓ እነዚህ ያዩዋቸው ምስሎች የውጭ አገር ሰው ነው የኢትዮጵያ ናቸው?
- ✓ ተሸፋፍኗል እዚህ ላይ ቁስል አለ እዚህ ላይ ቁስል አለ ቪዲዮ ነው ያየሁት ድምጽ የለም
- ✓ ሲያዩዋቸው ምን አይነት ሰወች ናቸው ኢትዮጵያውያን ናቸው አይደሉም?
- ✓ በቪዲዮ ላይ ያየሁት ቁስል ተሸፍኗል እያልኩ ነው እጁ ላይ አለ ከለር ፋል አይታየኝም የተሸፈነ አለ ቁስል እዚህ ላይ ነጭ
- ✓ አይ መለየት ከቻልክ እሱን መናገር ነው አልገባህም ?
- ✓ አይ ኢትዮጵያውያን ነው የኔ ሳይንት
- ✓ ናቸው ወይስ አደለም ?
- ✓ ኢትዮጵያውያኖች ናቸው
- ✓ እሺ ቪዲዮ  ከየት የመጣ ነው ተባለ ምስሉ እዛ ላይ ያለው ምስል ከየት የመጣ ነው ተባለ?
- ✓ እሱ ቀርያ ይሏቸው በኤግዚቢት የተያዘ እንደሆነ አይቻለሁ
- ✓ እኮ ከዛ ውጭ የተናገረውወ ነገር አለ?
- ✓ ኤግዚቢቱ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ባለ ቪዲዮ ሰውዬ እነዚህ ምስሎች ከዚህ መጡ ወይም ከሌላ ተገኙ ብሎ ስለ ቪዲዮ የተናገረው ነገር አለ?
- ✓ ኢግዚቢት ነው የተያዘው ተብሎ ፎቶው ተከፍቶ ይሄ ነው የቀዳው ተብሎ አይተን ተቀመጠ
- ✓ ከዛ ውጪ ከሰውየው የሰሙት ነገር የለም ?
- ✓ አዎ የሰማሁት ማለት እኮ ነው እሱ ነው የቀዳው ተብሎ አይቼ እንደተቀመጠ
- ✓ እነዚህ ከኢሜል ወጡ ወይም ከኮምፒውተር ወጡ ያላቸው ሰነዶች ለማን እንደተላኩ ከወዴት እንደተላኩ ያዩት ነገር አለ ?
- ✓ ለማን እንደተላከ የሚያረጋግጥ ነገር አለው?
- ✓ አዎ እላዩ ላይ አንብበን እንትን ለማለት የቋንቋ /ግልጽ ያልሆነ/ ስለነበረ በብዛት እሱን እንትን አላልንም
- ✓ እንግሊዝኛ አልነበረውም እላዩ ላይ?
- ✓ አላነበብኩም በዛን ሰዓት ላነበውም የምችልበትም ጊዜ አልነበረም ወረቀቱም ብዛት እዳላቸው እና
- ✓ ስለዚህ ሰነዶቹ ምን እንደሚሉም አያውቁም እርስዎ?
- ✓ አላነበብኩም
- ✓ አያውቁም?
- ✓ አላነበብኳቸውም በወረቀት ታትመው ሲወጡ አይቻለሁ
- ✓ ቀኑ ምን ቀን ነበረ ያሉት?
- ✓ 26 የአንድ የመሃመድ ሁለቱ የያሲን ኑር እና አንደኛው በ5 1ኛ ወር እንደሆነ አስታውሳለሁ 2005 አንደኛው
- ✓ በተለያየ ቀን ነው?
- ✓ አንደኛው 2005 አንደኛው 2004 አንደኛው ነሐሴ አንደኛው መስከረም ነው
- ✓ እሺ እንትኑ ሲወጣ የነበረው ከአንድ ኮምፒውተር ነው ብለዋል ሁለቱንም ሲያወጣ የነበረው ሲቪል የለበሰው ፖሊስ ነው ፕሪንት እያረገ ሲያወጣ የነበረው ማለት ነው?
- ✓ እሱ ከፈተ እሱ ሁሉን ነገር አደረገ
- ✓ ከዛ ፕሪንት እያረገ ያወጣና ይሰጣቸዋል ለነሱ?
- ✓ እያየ እያመነበት እየፈረመ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አቶ ኤልያስ ቀኑ ምን ነበር የስራ ቀን ነበረ ወይስ የረፍት ቀን ነበረ ቅዳሜ እሁድ ከሰኞ እስከ አርብ በየትኛው ቀን ነበረ እርስዎ የታዘቡት?
- ✓ እኔ በአጋጣሚ ወደዛ የሄድኩበት ቀን ቅዳሜቀን ይመስለኛል
- ✓ ያየሩ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር ዳመናማ ፀሐያማ ?
- ✓ ዳመናማ ነው
- ✓ ሁለቱም ቀን?
- ✓ አዎ ዝናም አልታየም እዛ ጉብኙ ስወጣ ግን አንደኛው ነሐሴ ነው ይዘምባል ግን እኔ ጉብኙ በወጣሁበት ታይም አልዘነበም ወቅቱ የዝናብ ወቅት ነው እኔ ጉብኙ በወጣሁበት ሰዓት ግን አልዘነበም
- ✓ እሺ አሁን በአንደኛው ቀን ሁለቱም ተከሳሾች ጉዳይ ታዝበዋል መጀመሪያ የማንን ነው የታዘቡት ከዛ የማንን እስቲ ቅደም ተከተሉ እንዴት ነበር?
- ✓ ግልጽ ቢሆንልኝ ይሄ በተለያየ ቀን ነው እያልኩ ነው የአንደኛው ?
- ✓ በ26 አለ
- ✓ በ5/01 ያሉትን ይንገሩን?
- ✓ ያሲን ኑር
- ✓ ሁለት ሰው አይተዋል አደል በዛን ቀን በዛን ቀን መጀመሪያ ማን ነው የታየው ያሲን ኑሩ ነው ወይስ ሌላኛው ነው እናንተ ገባችሁ ለመታዘብ መጀመሪያ ማንን አያችሁ ከዛ ቀጥሎ ማንን?
- ✓ ያሲን ይመስለኛል መጀመሪያ ከዛ መሃመድ መሰለኝ
- ✓ እሺ አራት ሰዓት ተጠየቁ እስከ ስንት ሰዓት ቆያችሁ እዛ በመታዘብ?
- ✓ ወደ አምስት ሰዓት ነው እንደዚህ አካባቢ ወጥተናል ከዛ የገባነው አራት ሰዓት ከዛ አምስት ሰዓት አካባቢ ወጥተናል
- ✓ እሺ ያሲን ኑሩ አለባበሳቸው እስቲ ያስታውሳሉ አለባበሳቸውን ምን ይመስል ነበር?
- ✓ አዎ አስታውሳለሁ ጅለቢያ አርገው ነበር
- ✓ ማን ነው ጀለቢያ ያሲን ነው?
- ✓ አዎ ያሲን ኑር ጀለቢያ አርገው እንደነበረ አስታውሳለሁ
- ✓ እናቱ ላይስ?
- ✓ ኮፍያቸውን
- ✓ ከታችስ መጫሚያው?



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ነበላ ሜማ ያመስለኛል
- ✓ ሌላኛውስ?
- ✓ አላስታውሰውም
- ✓ በነሐሴ ውስጥም ያዩትንም አያስታውሱም?
- ✓ እሳቸውን አላስታወስኩም ነበር
- ✓ ይቅርታ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ኤልያስ ቅድም ከኮምፒውተር ውስጥ የወጣው የተለየ ቋንቋ ነው ብለው ነበር ይሄ የተለየ ቋንቋ ፊደሉን ወይ አልፋ ቤቱን ያውቃሉ አይተውታል ?
- ✓ አንደኛው አጋጣሚ ስፈርም እንግሊዘኛ አይቻለሁ እየፈረምኩ እያለሁ ሳየውእንግሊዘኛ ፊደሎች አይቻለሁ
- ✓ እሺ ሌላስ?
- ✓ በስንተኛው ስፈርም ሊነበብልኝ ያልቻለ ያላወቅኩት ቋንቋ ያልኩት እሱን ነው
- ✓ እኮ ምንድን ነው ፊደሉ ?
- ✓ ያላወቅኩት ያልኩት እሱን ነው ቋንቋዉ ይሄ ነው ለማለት ላቲንኛ ይሁን ምን ይሁን አላወቅኩትም
- ✓ ላቲንኛ እኮ ማለት ፊደሉ ያው እንግሊዘኛ ነው አደል ?
- ✓ አዎ እንግሊዘኛው ሌላ አይነት ሁኔታ አለው
- ✓ ምን አይነት?
- ✓ ይሄኛውን አላውቀውም ጽሁፉን እንዳለ ብቻ ነው ያየሁት አላነበብኩትም ዲፕሊ. ገብቼ ባነበረ ይሄ ነው የሚለውን አሲዩም ላደርግ እችላለሁ እኔ ግን አየሁት የተለየ ቋንቋ ነው ይሄ እንግሊዘኛ ነው ብዬ
- ✓ የወጣውን ሰነድ ሁሉንም አንብበዋል እርስዎ?
- ✓ አላነበብኩም እኮ አልኩኝ
- ✓ ቅድም ስጠይቆት መሃመድ የመሃመድን ያወጣው ሲቪል የለበሰ ፖሊስ ነው ብለው ነበረ የያሲን ኑሩን ያወጣው ያሲን ኑሩ ነው ወይስ ሌላ ሰው
- ✓ ተጠይቋል ይሄ
- ✓ እሺ ጨርሻለሁ አመሰግናለሁ
- ✓ ድጋሚ ካለ
- ✓ አለን የተከበረው ፍ/ቤት



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ አቶ ኤልያስ ቅድም ሲጠየቁ ስለ ፖሊስ ይሄን ነገር በፖሊስ ስነምግባር ወይም በሕግ መሰረት ነው ያመጣነው ብሏል ያሉት ነገር አለ
- ✓ ወደ ፍ/ቤቱ ያመልክቱ
- ✓ ጥያቄውን ብቻ በትክክል ያሰሙ ተረጋግተው የሚያውቁትን ያዩትን መግለጽ ነው የማያውቁትን አላውቅም ማለት ይችላሉ
- ✓ ማን ነበረ ያንን ኮምፒውተር ሲከፍት የነበረው ቅድም ለእኛ በዋና ጥያቄ ስንጠይቅ ኮምፒውውተሩን የከፈተው ተከሳሽ ነው መሃመድ ነው እሱ ነበር ከፍቶ ፕሪንት ሲያደርግ የነበረው ብለዋል አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቅ ደግሞ
- ✓ ተቃውሞ አለን አቃቤ ሕግ አሁን እሳቸውእራሳቸው አስተካክለውት ነው ምስክሩ ቅድምም ሲመሰክር መጀመሪያ ላይ በአቃቤ ሕግ ጥያቄም ሲመሰክር ተከሳሽ ወይም መሃመድ እራሱ ፕሪንት ሲያደርግ ነበር አላለም ተከፍቶ ፕሪንት ይደረግ ነበር ነው ሲያስረዳ የነበረው እንደውም ስለፕሪንት ብዙ ጭቅጭቅ ነው የነበረው ኋላ ተጠይቆ
- ✓ አይ ስለመክፈቱ ችግር የለውም ግን ስለ ፕሪንት ስለተናገሩ ነው እሱ ፕሪንት ሲያደርግ ነበር ብለሃል ስላሉ ነው አላለም በአቃቤ ጊዜ ነው እና ጥያቄው ቢታረምልን
- ✓ ምስክሩ አላለም ነው
- ✓ በአቃቤ ሕግ ጊዜ መሃመድ ነው ፕሪንት ያደርግ የነበረው አላለም ነው አሁን አቃቤ ሕግ ግን ብለሃል ብለው
- ✓ እሺ ምላሽ ስጡበት
- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት መቅረፀ ድምፁን ቼክ ማረግ ይቻላል እኛ ያላለውን አለ ልንልበት የምንችልበት የሕግ አግባብም የሕግ መሰረትም ፍላጐትም የለንም ቅድም ተከሳሹ ኢሜሉን ከፈተ ኮምፒውተሩንም ከፈተ ከዛ ወረቀቶቹን እያወጣ ሲፈርም ነበረ በማለት በተደጋጋሚ ገልፀዋል በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ይሄ ፍሬ ነገር ለማስተባበል ጥረት ተደርጓል የድጋሚ ጥያቄ ዋና አላማው ደግሞ በመስቀለኛ ጥያቄ የፈረሰ ነገር ማስተካከል ነው ስለሆነም ያን ነገር ለማስተካከል እየሞከርን መሆኑ እንትን በተባለ ሰዓት ይሄ መሰረት የሌለው ተቃውሞ ማንሳቱ ተገቢ አደለም ተቃውሞ ውድቅ ይሁንልን ነው
- ✓ እሺ ብይን ተሰጥቷል ማን ፕሪንት አረገ የሚለው ላይነው ተቃውሞ የተነሳው ተከሳሹ ፕሪንት  አርጓል የሚል ነገር ምስክሩ መጀመሪያ መስክሯል የሚል በአቃቤ ሕግ በኩል ቀርቧል ምስክሩ አልተናገረም ኮምፒውተሩን ማን ከፈተ የሚለው ላይ አደለም የኛ ተቃውሞ የሚል በጠበቃ በኩል የቀረበ ተቃውሞ አለ ምስክሩ አስቀድሞ ይሄን ተናግሯል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ወይስ አልተናገረም የሚለውን ፍ/ቤቱ አይቶታል ከመዘገብነው ሰነደው ኮምፒውተሩም እራሱ ከፍቶ ወረቀት ሲያወጣ ነበር ከዛ በኋላ እሱም ይፈርማል እኛም እንፈርማለን የሚል ነገር ተናግሯል ምናልባት ፕሪንት የተባለው ቃል ብቻ ነው ያልተገለፀው እራሱ አውጥቶ የሚል ነገር አለ እና በዚህ መሰረት ጥያቄው አዲስ አይደለም መጀመሪያም ተነስቷል እና ያው ተገቢ ነው ማን አወጣ በሚል ተከሳሹም በሚገባም ተስተካክሎ ጥያቄው ይቀጥል ተብሎ ብይን ተሰጥቷል

- ✓ እሺ እናመስግናለን አቶ ኤልያስ ምስክሩ ኮምፒውተሩን ማን ነው ተከሳሹ እነዚህ ኢሜሉን እንደከፈተ እና ወረቀቶችን እንዳወጣ ቅድም እኛ ስንጠይቆት በዋና ጥያቄ ገልጨው ነበር አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ሲጠየቁ ሲቪል የለበሰ ሰው ሲያወጣ ነበር ሲሉ ነበር ከየት ነው ይሄ ሲቪል የለበሰው ፕሪንት ከተደረገበት ቦታ ነው ያወጣው ወይስ ኮምፒውተሩ ላይ የሚያዘውም እሱ ነው ፕሪንተር ያውቃሉ ወይንም ማተሚያ ?
- ✓ አይ ያወጣውን ነው
- ✓ እስቲ የነበረውን ድርጊት ይሄ እንዲህ ነው ከመጀመሪያ ጀምሮ እስቲ ለፍ/ቤቱ ይግለፁ ማን ወረቀቱን አወጣ ማን ኢሜሉን ከፈተ ማን እነዚህን ሲፈርም የነበረውን እስቲ ዘርዘር አድርገው የነበረውን ነገር ያስረዱ ተረጋግተው ?
- ✓ መጀመሪያ እሱ መጣ ከዛ እራሱ ከፈተ በራሱ ሁሉን ነገር አደረገ ከዛ እራሱ እየፈረመ ለእኛ ሰጠ ያመነበትን እኛም ከዛ የወጣውን እየፈረምን ተቀበልን
- ✓ ሁሉን ነገር አደረገ ሲሉ ማለት እሺ ሲቪል የለበሰ ሰው አወጣ የሚሉት ምንድን ነው ያወጣው ሲባል የለበሰው ሰው ?
- ✓ ወረቀቱን የሆነ እዛ ያለ ሰው ወረቀቱን ይሄ አሁን የተከራከርንበት የተባለ ወረቀት ማለት ነው
- ✓ ሌሎቹንም ስለሁሉም ይንገሩን ይሄ ሲቪል የለበሰ ሰው ሲያወጣ ነበር ብለውናል ይሄን ወረቀት ከየት ነው ያወጣው እስቲ ይንገሩን ?
- ✓ ከዛው ከእንትኑ
- ✓ እስቲ ለፍ/ቤቱ ይግለፁት ይሄ እንትኑ የሚሉት ምንድን ነው?
- ✓ ሲቪል የለበሰው ሰው አሁን እኔ እዚጋ/ግልጽ ያልሆነ/ እራሱ እኛ ገብተን ቀጭ ብለን አይተን በስነስርዓቱ እራሱ ፈርሞ አወጣ /ግልጽ ያልሆነ/ አሁን ይሄ ሲቪል የለበሰው ማን ያወጣው የሚለው ብዥታ የፈጠረው
- ✓ /የማይሰማ/



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ኮምፒውተሩ ነዋ ፕሪንት እያደረገ የሚያወጣው
- ✓ /የማያስማ/
- ✓ ተጠቅሜ አላውቅም እንዲሁ እያለሁ ማን ነው ለሚለው እኔ እኮ አላውቅኩም ያቺን ወረቀት ተነስታ እየተነጋገርን ያለው የሆነ ሰው አንስቶ
- ✓ የትህርት ደረጃህ ስንት ነው?
- ✓ 12ኛ ክፍል
- ✓ መቼ ነው የጨረስከው?
- ✓ 80 አካባቢ
- ✓ ቀጥሉ እስቲ
- ✓ ይኸሎት አቶ ወደዚህ እያዩ ይሄኛው ኮምፒውተር ነው እንበል እዚጋ ፕሪንተር አለ ማን ነበር እዚጋ ተቀምጦ ፕሪንት ሲያደርግ የነበረው ከዚህ ከፕሪንተሩ ውስጥ ወረቀቱን ሲያወጣ ማን ነው የነበረው እስቲ ይሄንን ለይተው ያስቀምጡልን ይሄኛው አጀንዳ አለ እዚጋ መዝገብ አለ በዚህ መልኩ ያብራሩ ጥያቄው ለሁለቱም ወገን ለሁለቱም ተከራካሪዎች /ግልጽ ያልሆነ/?
- ✓ ይሄኛው
- ✓ ቆይ እሱ ፊቶ ላይ ያሳዩን እስቲ እንዴት እንዴት እንደሆነ ኮምፒውተሩ ጥግ የነበረው ማን ነው?
- ✓ እራሱ
- ✓ ማን?
- ✓ ተከሳሽ
- ✓ ኮምፒውተሩ ጥግ ምን ያረግ ነበረ እዛ ኮምፒውተሩ ላይ አሁን?
- ✓ ከፊተ አሳየን ሁኔታውን
- ✓ ወረቀቱ በሚወጣበት ጊዜ?
- ✓ ያወጣና ያነባል እላዩ ላይ አሁን ማውጣት ከኮምፒውተሩ ሳይሆን እላይ ፕሪንት ተደርጐ የሚወጣውን ከዛ አንስቶ አንብቦ ይኸው ነው ተብሎ እሱ ፊርሞ ሲመጣ እኛ እንፈርማለን
- ✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ተከሳሹ ሲያንገራግር ነበር በነዚህ ሰነዶች ላይ አልፈርምም በማለት እንትን ሲል ነበረ ብለዋል ቅድም እነዛ ሰነዶች ወደኔ የተላኩ ናቸው እንጂ እኔ የማውቃቸው አደሉም ነበር ነው አደል ሲል የነበረው?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ እንደሱ ነው እኔ አላውቀውም ይሄ ምንድን ነው ሲል ከንተ ኢሜል ላይ ነው የወጣው እንዴት እኔን አላውቀውም ትላለህ አልነው ከዛ የሆነ ሁለት ጥያቄ ቀረበለት እኛ አየነው ከዚሁ
- ✓ እኮ ሲል የነበረው ይሄ የተላከልኝ ነው እንጂ እኔ የላኩት አልነበረም ነው ሲል የነበረው አደለ?
- ✓ እንዲህ ያሉትን ነገር ይግለፁት
- ✓ እኔ የማላውቀው ነው ብሎ ሲል ለአንተ የተላከልህ ነው በአንተ የተላከው ሲባል እሱ ብሎ ፈርሞ ተቀበለ
- ✓ እሺ እናንተ ስታናግሩት የነበረው በዚህ የተላከ ነው በሚለው ነጥብ ላይ ነው እንጂ ሌላ የማግባባት ነገር አናግራችሁታል እንዴ?
- ✓ አይ በዚሁ ላይ ነው ሌላ የማግባባት ነገር የለም ይሄ ከኔ አደለም
- ✓ እንዲፈርም ያስገደደው ሰው አለ?
- ✓ የለም እራሱ አምኖ ነው የፈረመው
- ✓ እሺ ሌላው በእለቱ የነበረውን የአየር ሁኔታ አለባበሱን ከጊዜው እርዝመት አንፃር በእርግጠኛነት ያስታውሱታል?
- ✓ የሁለቱን አላስታውስም ይሄ ያሲን ኑር የተባለው ብቻ ትንሽ አይረሳኝም
- ✓ አሁን የያሲን ኑር  እና የአቡበከር ቀን አንድ ቀን ነው የአቶ መሃመድ ቀን አንድ ቀን ነው ቅድም እርስዎ በገለፁት መሰረት ማለት ነው እነዚህን ቀናቶች የነበረውን የአየር ሁኔታ ያስታውሳሉ ወይ?
- ✓ አንደኛው ቀን ዝናብ አለ አንደኛውቀን ዝናብ የለውም
- ✓ ዝናብ አለው የሚሉት የትኛውን ቀን  ነው?
- ✓ የነሐሴው
- ✓ እሺ ሌላው ፖሊስ የሱን ኢሜል ሲበረብር ነበር እንዴ የዛን ቀን?
- ✓ እ?
- ✓ ፖሊሱ እነሱን እያስነሱ የሱን ኢሜል ሲበረብሩ ነበር?
- ✓ ኢኸውሎት ይሄ አሁን ያ
- ✓ አይተሃል አላየህም?
- ✓ አላየሁም
- ✓ ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ. ምስክር ጨርሰዋል እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ አሁን የቀረው ሰላሳ ደቂቃ ብቻ ነው በተረችው ሰላሳ ደቂቃ ምስክር ሰምተን ስለማንጨርስ ልክ ስምንት ሰዓት ላይ ነው የምንገናኘው ተከሳሿን አስባችሁ ማለት ነው የጠዋቱን በዚህ ጨርሰናል
- ✓ ያው ጠዋት የነበረውን ችሎት ከሰዓት በተለመደው መንገድ እንቀጥላለን የተፈጠሩ የተቀነሰ ተከሳሽ አለ ከ6ኛ ውጪ ስንተኛ ጠዋት 6ኛ ነበር አሁን 3ኛ ታመው ቀርተዋል የሚል አለ አቃቤ ሕግም እንደዚሁ አንድ ቀርቷል ያለው ያስመዝግብ እሺ አቃቤ ሕግ
- ✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት እኚህ ምስክር የሚመሰክሩባቸው ስለሆነ የኚህ ምስክር መሰማት ወይ ለነገ እንዲሆንልን ነው በተረፈ ክርክሩ እንዲቀጥል ነው
- ✓ ቀጣይ ምስክር ይቅረብ
- ✓ ወይንም እሳገርውን በሚመለከት ባለው ፍሬ ነገር ላይ ሳይመሰክሩ ለሌሎቹ ላይ የሚመሰክሩት አለ ሌሎቹን እንዲቀጥሉ ማድረግ ይቻላል
- ✓ አይ አንድ ላይ
- ✓ በ3 ሰው ላይ ነው የሚመሰክሩት እንፈልጋቸዋለን
- ✓ ስለዚህ ነገር ይምጡ
- ✓ ቀጣይ የአቃቤ ሕግ ምስክር
- ✓ /የማይሰማ/ ከ28ኛ ያው ለራሱ ነው ሌሎቹ ያው ጠዋት የነበሩ
- ✓ በእውነት ለመመስከር
- ✓ በእግዚአብሔር ስም
- ✓ ምያለሁ
- ✓ ለምስክርነት ነው የመጡት?
- ✓ አዎ
- ✓ የእርስዎን ስም የራስዎን ብቻ ነው የሚገልፁልኝ የአባት ስሙ እድሜ አይጠየቅም የራስዎን ስም ብቻ
- ✓ ስሜ አሰራት ይባላል
- ✓ እሺ አቃቤ ሕግ ስንተኛ ናቸው እሺ አቶ አስራት በተሰሙት ምስክርነት ስድሳኛው ላይ ደርሰዋል በማስረጃ ዝርዝረ 189 ላይ የተጠቀሱት እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ዛሬ?
- ✓ ሀሰት ላይ ነው ለምስክርነት የመጣሁት አህመዲን ጀበል እና አህመድ ሙስጠፋ
- ✓ እሺ እነዚህን ተከሳሾች በአካል ለይተው ያውቃሉ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ማለት ያው አሁን ጊዜው እረዘም ስላለ ወደ 8 ወር 7 ወር አካባቢ ስለሆነ ምናልባት ፊታቸው ሊጠፋኝ ስለሚችል በወቅቱ አይቻቸው ነበር
- ✓ ስለዚህ አሁን መለየት ይችላሉ አይችሉም የማይችሉ ከሆነ አይገደዱም የሚችሉ ከሆነ ለይተው ያሳዩናል
- ✓ ሊጠፉብኝ ይችላሉ አሁን ምናልባት እንጃ
- ✓ 2ኛ ተከሳሽን ለይቶ አሳይተዋል እሺ አቤት እሺ 9ኛ ተከሳሽን ምስክሩ ለይተው አሳይተዋል ቀጥሉ ቁጭ በል ለይተው ካሳዩን ተከሳሾች ጋር ዝምድና ወይም ጥላቻ ነገር አለ‐ት?
- ✓ ያው ዝምድና የለንም እኔ ባጋጣሚ ላራሴ ጉዳይ ነው የሄድኩት
- ✓ ዝምድና የሉትም የተጣሉበት ነገርስ አለ?
- ✓ አይ እኔ እሱን ሁሉ አላውቅም
- ✓ እሱም የለም?አ
- ✓ አዎ
- ✓ ያዩት ነግር ምንድን ነው እስቲ አጠር አርገው ምን ሲያረጉ ነው ያዩት?
- ✓ በአጋጣሚ እኔ ለራሴ ጉዳይ ሄጄ ነበረ
- ✓ ምንድን ነው ያዩት አጠር አርጉና ወደ ዝርዝሩ በኋላ ይገባሉ?
- ✓ ማለት ያየሁት እዛ ታዛቢ ሁንልን እንደዚህ ምናልን ስላሉ
- ✓ ታዛቢ ሆነው ነው ያዩት?
- ✓ አዎ ሁንልን ኮምፒውተሩ በኢሜል
- ✓ እሺ ወደ ዝርዝሩ ይገባሉ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- ✓ እሺ አቶ አስራት መቼ ነው ያዩዋቸው?
- ✓ ነሐሴ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት
- ✓ የት ነው ያዩዋቸው?
- ✓ እኔ ባጋጣሚ ያው ፌደራል ቢሮ ሄጄ ነበረ ለራሴ ጉዳይ ከዛ በአጋጣሚ የራሴን ጨርሼ ስወጣ አንዴ ይቅርታ ምናምን ትንሽ እዚጋ የሚሰሩ ስራዎች ስላሉ እነሱን እንድትመለከትልን በታዛቢነት እንጋብዝሃለን ስላሉኝ
- ✓ ማን ነው ይሄን ያሉት?
- ✓ ያው ፌደራል ፖሊስ ነው ይሄንን ያለኝ
- ✓ መርማሪ ነው ?
- ✓ መርማሪ መሰለኝ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ. አንድ ቀን ነው ያዩዋቸው ሁለቱንም?
- ✓ ሁለቱንም አንድ ቀን ነው ያየኋቸው
- ✓ እሺ. አሁን በጠቀሱት ሰዓት ታዛቢ ወደ የሚሰራ ስራ አለ ብለው ነገሩኝ ብለዋል ከዛን በኋላ ምን ሆነ?
- ✓ ከዛን በኋላ ያው ማለት እኔ ቆምኩ ከዛ በኋላ እሚፈልገው ሰውዬ ያው እሱ ነው ምናምን ብለው አስገቡና ከዛ እኛ የሚሰራውን ኢሜሉ በራሱ
- ✓ የት ነው ቦታው ማለት ግቢ ውስጥ ሜዳ ላይ ምንጋ ነው?
- ✓ ኖ ማለት ቤት ውስጥ ነው ቁጥሩን እራሱ አውቀዋለሁ 26 ቁጥር ነው
- ✓ ስንት ቁጥር?
- ✓ 26 ቁጥር ኤይባላል
- ✓ የምን ክፍል ነው ክፍሉ?
- ✓ ክፍል ውስጥ ማለት በራሳቸው ክፍሉ ኖርማል ክፍል ነው ያየሁት ማለት
- ✓ ምን አለ ክፍሉ ውስጥ?
- ✓ ክፍሉ ውስጥ ኮምፒውተር ምናምን አለ
- ✓ ስንት ኮምፒውተሮች አሉ?
- ✓ 3 ኮምፒውተር አይቻለሁ በአንድ ኮምፒውተር ላይ ነው ስራው የተሰራው ስለዚህ ያ የተሰራው ስራ እዛው እኔ በአይኔ አይቻለሁ በራሱ አድራሻ በኢሜሉ አድራሻ እራሱ ከፍቶ
- ✓ ማንና ማን ነበር ክፍሉ ውስጥ ስትገቡ ?
- ✓ ማለት ሌሎች ሰወች ነበሩ
- ✓ ምኖች ናቸው እነዛ ሰወች?
- ✓ ሰራተኞች መሰሉኝ
- ✓ እሺ?
- ✓ ግን ያው ማለት ኢሜሉን የከፈተው እራሱ ነው በራሱ ኮድ ነው
- ✓ ማን ነው ይሄ አሁን እራሱ ነው የሚሉት?
- ✓ አህመዲን ጀበል እና አህመድ ሙስጠፋ
- ✓ እኮ ለየብቻ ሁለቱም አንድ ላይ ነበሩ እናንተ ስትገቡ የነበሩት?
- ✓ አይ ለየብቻ
- ✓ እስቲ መጀመሪያ ቅድሚያ ያዩት የማንን ነው?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አህመዲን ጀበል
- ✓ እስቲ አቶ አህመዲን ጀበል ምን ሲያረጉ ነበር ያዩት እርስዎ?
- ✓ እኔ በራሱ ኮድ በኢሜል ማለት ነው ያንን ከፍቶ እራሱ በራሱ ከፍቶ ፕሪንት እየተደረገ ወረቀቶች ሲወጡ እሱ ያያል እሚያየው የራሱ መሆኑን ነው
- ✓ ማን ነው ፕሪንት የሚያደርገው?
- ✓ እራሱ
- ✓ እሺ ፕሪንት ካደረገ በኋላ ነው አውጥቶ የሚያየው ?
- ✓ አዎ እራሱ አውጥቶ ያያል ከዛ በኋላ ይፈርምበታል እኛ ደግሞ ያው እኔ ፈርሜያለሁ እሱ ከፈረመ በኋላ
- ✓ እስቲ ስሙ አህመዲን መሆኑን በምን አወቁ ስትገቡ ተነግሯችኋል ወይስ?
- ✓ ያው እነሱ ማለት አስተዋውቀውናል
- ✓ ምን ብለው አስተዋወቋችሁ?
- ✓ ስሙን ነግረውናል
- ✓ እሺ የናንተንስ ስም አስተዋወቁ ወይንም እናንተ እዛ ለምን እንደሄዳችሁ አስተዋውቋል ፖሊሱ?
- ✓ እኛ ያው ታዛቢ እንደሆንን ያው ገለፃ ተደርጓል
- ✓ ለተከሳሽ ተደርጕለታል?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ ምንድን ነው እስቲ ምን ምን አለ ፖሊሲ ወይንም እናንተን ወደዛ የወሰዳችሁ አካል እናንተ ታዛቢ እንደሆናችሁ ነገር ብለውናል ሌላስ ምን ምን አለ?
- ✓ ሌላ ምንም ያለን ነገር የለም ያው ታዛቢ እንድትሆን ብለው ፍ/ቤት ስለሚቀርቡ ስለዚህ እንድትገልፁ ያያችሁትን በትክክለኛ እንድትገልፁልን ስለተባለ ከዛ አየን
- ✓ ተከሳሹንስ ምን አለው ፖሊሱ?
- ✓ አይ ኖ ምንም አላለውም ግን ያው ይሄ በራስህ ከፍተህ እራስህ እንድትከፍት ስላለው እራሱ ነው የሚከፍተው እንጂ ፖሊሱ አይከፍትም እዛ ኢሜሉን
- ✓ እንድትከፍት ሲለው ትእዛዝ ነው ወይስ ፍቃደኛ ከሆንክ እንዴት ነው ያለው?
- ✓ አይ በፍቃደኛነት ነው የጠየቀው እንጂ በቁጣ ምናምን አደለም በፍቃደኛነት ነው
- ✓ እስቲ የተጠቀመው ቃል ካለ ያንኑ በግልጽ ያስቀምጡት እንትን ያድርጉት እንደዛ ነው ግምት የሚመስል ነገር ሳይሆን የነበረው የንግግር ለውጥ እንዴት ነበረ የተነጋገሩት



http://ethcriminalawnetwork.com/

ምንድን ነው ያለው ፖሊሱ እናንተን ምን ብሎ ነው ያስተዋወቀው ይሄን እስቲ ዘርዘር ያርጉት?

- ✓ እኛን አስተዋወቀን እኛን አንደታዛቢነት አስተዋወቀን ከዛ አንተ በራስህ ኮድ ክፈተው እና ፕሪንት ወረቀቱ ይደረግ ተብሎ ያው እራሱ ነው የከተው እራሱ አህመዲን ጀበል ማለት ነው
- ✓ እሺ ምን ምን ወረቀቶች ወጡ?
- ✓ አሁን በወቅቱ ባላስታውሳቸውም ፕሪንት ወረቀቱ ላይ ፎቶ ግራፎች አሉ እና ያው በተለይ አህመዲን ጀበል በእንግሊዝኛ የተፃፉ ወደ 50 ምናምን ገጽ የሚሆኑ ናቸው የመጀመሪያው ነሐሴ 25 ከዛ በተረፈ በቃ ይሄንን ነው ያየሁት
- ✓ እንግዘኛ ብቻነው ያዩት?
- ✓ መስከረም 5 ቀን 2ኛ ጊዜ ተጠርቼ መጥቻለሁ
- ✓ እስቲ ስለ 25 እንጨርስ ?
- ✓ ነሐሴ 25 እንግሊዘኛ ብቻ ነው ያየሁት በማለት ነው
- ✓ እሺ የዛን ቀን ሌላ ተከሳሽ አይተዋል በወቅቱ ቅድም የጠቀሱት ሰው አለ ?
- ✓ አዎ አህመድ ሙስጠፋ ነው
- ✓ እስቲ የአቶ አህመዲን ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ነበር?
- ✓ ያው እኛ 3 ሰዓት አካባቢ ጠዋት
- ✓ እስከ ስንት ሰዓት ቆያችሁ?
- ✓ እስከ 5 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ቆይተናል
- ✓ ከዛስ?
- ✓ ከዛ በቃ አለቀ ሌላ ጊዜ ስትጠሩ ትመጣላችሁ ምናምን ተብለን ወጥተናል በቃ
- ✓ ቅድም ስለሌላ ተከሳሽ ጠቅሰው ነበረ እና
- ✓ አህመድ ሙስጠፋ
- ✓ እስቲ እሳቸውንስ መቼ ነው ያዩዋቸው?
- ✓ ነሐሴ 25
- ✓ የዛኑ ቀን ማለት ነው?
- ✓ የዛኑ ቀን
- ✓ ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ነበር የሳቸውስ?
- ✓ ያው ተመሳሳይ ሰዓት ያው ከሱ ትንሽ እንትን ይላል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ሁለቱ አንድ ላይ ነው የተካሄደው?

✓ አይ አንድ ላይ አይደለም የተካሄደው

✓ ከፋፍተው ይንገሩኝ?

✓ ኦኬ አንደኛው አህመድ ጀበልን ከጨረስን በኋላ የአህመድ ሙስጠፋ ተጠለ

✓ እዛው ነበሩ ሌላኛው ተከሳሽ?

✓ አይ ተጠርቶ ነው የመጣው እኛ ወደ ውጭ ወጥተን ተጠርቶ መጣ ከዛ በኋላ በቃ አንድ ላይ ነው የገባነው

✓ እሳቸውስ ከምንድን ነው ያወጡት?

✓ ኦኬ እሱም ያው ከኢሜሉ ላይ ነው የወጣው ወደ 46 ገጽ የሚሆን ስለዚህ በአረብኛ በእንግሊዘኛ በአማርኛ የተፃፉ ጽሁፎች ወጥተዋል በራሱ አድራሻ ከፍቶ ኢሜሉን ማለት ነው በኢሜሉ ላይ

✓ አድራሻውን ያስታውሱታል የኢሜሉን ?

✓ አድራሻውን አላስታውስም

✓ እሺ ከዛስ ይሄ 46 ገጽ ያሉት ብቻ ነው የወጣው?

✓ አዎ ወደ 46 ገጽ የሚሆን በአረብኛ በአማርኛ በእንግዚኛ የተፃፉ ወረቀቶች ወጥተዋል እና እላዩ ለይም ፎቶ ግራፎች አሉ

✓ ምን ምን ይላል እስቲ ይዘቱን በአጭሩ የሚያስታውሱት?

✓ አይ ኖ እኔ ብዙም አላስታውስም አሁን አይመጣልኝ

✓ አርእስት እና ሌሎች ትንሽ ነገሮች?

✓ አላስታውሳቸውም

✓ በነዚህ ላይ ምን አደረጋችሁ ከዛ?

✓ ከዛ በእነዚህ ላይ ያው ከታዘብን በኋላ ወጣን ያው አሁን በስልክ አድራሻችሁን ስጡን ለድጋሚ ስትጠሩ እንፈልጋችኋለን ምናምን ብለው አድራሻችንን ሰጥተን

✓ ቃላችሁን ሰጣችሁ እንዴ የዛን ቀን ?

✓ እ?

✓ ቃላችሁን ሰጣችሁ ወይስ እንዴት ነው?

✓ አዎ ድጋሚ ስንጠራ ለመምጣት ቃሌን ሰጥቻለሁ

✓ እሺ?

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ በሰጠሁት ስልክ አድራሻ መሰረት ተደውሎልኝ ተጠርቼ መጥቻለሁ ስለዚህ እውነታው ትክክለኛውን ነገር ለመናገር ማለት ነው ያየሁት
- ✓ እስቲ የዛን ቀን ከዚህ ከሰነዱ ሌላ አሁን የመጣውን ሰነድ ፈርሜያለሁ ብለዋል?
- ✓ አዎ
- ✓ ከዚህ ሰነድ ውጪ የፈረሙበት ሰነድ ሌላ ነገር አለ?
- ✓ አይ ከዚህ ማለት ስተመጣ
- ✓ ጥያቄው ግልጽ ነው?
- ✓ አዎ ገብቶኛል ስለዚህ እንድትመጣ
- ✓ ጥያቄው ቅድም የፈረሙት ሰነድ አለ ከዚህ ውጪ ሌላ ቦታ ላይ የፈረማችሁት ነገር አለ ወይ?
- ✓ አዎ ማለት አድራሻ ተጠይቼ አድራሻ ሰጥቼ እንደመጣ
- ✓ ለምንድን ነው አድራሻ የሰጡት ማለት የሰጡት የምስክርነት ቃል አለ ወይስ ለምንድን ነው የሰጡት ?
- ✓ የሰጠሁት ምንድን ነው አሁን ያየሁትን ነገር ሲወጣ ፕሪንት ሲደረግ ከኢሜሉ ሲወጣ ያየሁትን ነገር በምጠራበት ሰዓት መጥቼ ያየሁትን እውነታውን እንድናገር ነው አድራሻ እዚህ ላይ እንድጠቅስ የተደረገው
- ✓ እሺ ከዛስ ?
- ✓ ከዛ በተጠራሁ መሰረት መጥቻለሁ
- ✓ መቼ ተመለሱ ?
- ✓ ማለት 2ኛ ለመምጣት አህመዲን ጀበል መስከረም 5 የመጣሁት አለ በሰጠሁት አድራሻ መሰረት ተጠርቼ እሱንም አይቼዋለሁ መስከረም 5 ቀን 2005 ዓ.ም.
- ✓ ስንት ሰዓት አካባቢ ነበር?
- ✓ ወደ ሦስት ሰዓት ተኩል አካባቢ
- ✓ ምን አዩ አሁን ባሉት ቀን?
- ✓ ባየሁት ቀን ከላፕቶፕ የወጡ ፕሪንት የተደረጉ ወረቀቶች አይቻለሁ በራሱ አድራሻ እራሱ ከፍቶ ስለዚህ እንግሊዘኛው ወደ 50 የሚሆን እና አማርኛው ወደ 54 የሚሆን ፕሪንት ተደርጎ ወረቀቱ አይቻለሁ
- ✓ ገፁን እርግጠኛ ኖት አሁን የሚጠሩትን የገጽ ብዛት ?
- ✓ እ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አሁን የወረቀቱን ይሄንን ሰነድ የገሁን ብዛት እርግጠኛ ኖት ወይ?
- ✓ እርግጠኛ ነኝ
- ✓ እህ ጽፈው ነበር ?
- ✓ እኔ እራሴ?
- ✓ ገሁ ምን ያህል እንደሆነ ማስታወሻ ይዘው ነበር ወይስ?አ
- ✓ አዎ ማለት እኔ እራሴ ማለት ለሚቀጥለው ጥያቄ ስለምጠራ ያየሁትን እውነታ ያየሁትን ነገር ለመጥቀስ በራሴ ይገፎዋለሁ
- ✓ ይሄን ያህል ገጽ ምን አይነት ወረቀት ተገኘ ለማለት ነው የያዙት ማለት የወረቀቱን ይዘት አላዩትም ገፁን ከያዙ በዚህኛው ?
- ✓ አይ የወረቀቶቹን ገፆች ማለት
- ✓ ይዘቱን?
- ✓ ይዘቱ ተለቅ ያለ ነው ማለት የወጡት ወረቀቶች
- ✓ ይዘቱ ሲባል ውስጡ ምንድን ነው የወረቀቱ የሚለው ምንድን ነው የሚነበበው ነው?
- ✓ እሚነበበውን አሁን አላስታውሰውም ግን ያው የተፃፉ አሉ ፎቶ ግራፎችም አይቻለሁ ግን አሁን በወቅቱ ትንሽ ጊዜዎች ስለሄዱ አላስታውሳቸውም
- ✓ እሺ እግሊዘኛ ይሄን ያህል ገጽ ሆኗል ሌሎችስ?
- ✓ ኦኬ ማለት ያው አማርኛ ወደ 54 ገጽ ጠቅሻለሁ እንግሊዘኛ
- ✓ ሌለ ካለ ነው ሁለቱንማ ሰምተናል
- ✓ ሌላ በአህመድ ሙስጠፋ ላይ ነው ያየሁት በአረብኛ በእንግሊዘኛ እና በአማርኛ የተፃፉ
- ✓ እሱን ቅድም ጠቅሰዋል ሌላ
- ✓ አዎ እዚህኛው ላይ ግን በቃ ሁለት ነገር ነው ያየሁት በአህመዲን ጀበል ላይ ማለት ነው የላፕቶፑን
- ✓ ይሄ ላፕቶች የማን ላፕቶፕ ነው ?
- ✓ የአህመዲን ጀበል
- ✓ በምን አወቁ የእሳቸው መሆኑን ?
- ✓ ተነግሮን ነው
- ✓ ማን ነወ የነገራችሁ?
- ✓ ያው እኛን የጠራን  አካል ነው የነገረን እሱ ባለበት እራሱ ባለበት
- ✓ ምን አለ ተከሳሽ ሲባል?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ እሱ ምንም አላለም በራሱ ኮድ ከፈተው ከዛ በኋላ እራሱ ፕሪንት አደረገው ወረቀቱን በራሱ ኮድ በሰላማዊ መንገድ ማለት ነው
- ✓ ኮዱን ከፈተ ሲሉ ኮዱ ተሰጥቶት ነው ወይስ ከራሱ ነው እንትን ያለው?
- ✓ ኖ ከራሱ
- ✓ በምን አወቁ ከራሱ መሆኑን?
- ✓ በፊት ለፊት ስላየሁ በአይኔ ማለት ነው
- ✓ ከዛስ ምን አደረገ?
- ✓ በቃ ያዉ ፕሪንት እየተደረገ ወረቀቶት ወጡ
- ✓ እንዴት ነው ፕሪንት የተደገው?
- ✓ ማለት ያው ፕሪንት የተደረገው በራሱ ኮድ ከፍቶት ነው ፕሪንት እየተደረገ ወረቀቶች የወጡት አሁን የጠቀስኳቸው ነገሮች አሉ በተለያዩ ጽሁፍ የተፃፉ ማለት ነው ስለዚህ እነሱን በአካል በደምብ አይቻለሁ ፊት ለፊት ሲወጣ ሲከፍት ሁሉ በደምብ ተመልከቱ እየተባለ
- ✓ ምን እያለ ነበር የፈረመው ሰነዶቹ ላይ?
- ✓ ሰነዶቹ ላይ ከላፕቶፑ ከኔ ከእራሴ ከላፕቶፕ በራሴ ኮድ ከፍቼ አውጥቼዋለሁ ሲል ይፈርማል እኔም እሱን አይቼ እፈርማለሁ እታዘዛለሁ ማለት ነው
- ✓ እሺ ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- ✓ እሺ አቶ አስራት ሁለት ቀን ነው እንግዲህ ታዘብኩኝ ያሉት እና እስቲ ነሐሴ 25 ቀን የነበረውን ልጠይቆት ነሐሴ 25 መጀመሪያ አህመዲን ጀበልን ነው የተመለከቱት አደል?
- ✓ አዎ
- ✓ የዛን እለት ክፍሉ ውስጥ ቁጥር 26 ኤ የተባለው ቁጥር ውስጥ ሲሉ 26 ኤ ማለት ምን ክፍል እንደሆነ እርስዎ ያውቃሉ ወይም ተነግሮታል?
- ✓ ኤ ያልኩት ክፍል ምንድን ነው አልተነገረኝም ግን ስገባ ቁጥሩን አይሁት ለምን ለቀጣይ ለሌላ ነገር ምናልባት ይጠቅማል ምናምን ብዬ ቁጥሩን እና ጽሁፉን ያገኩት የክላሱን ጽሁፍ ማለት ነው
- ✓ እኮ ይሄ 26 ኤ የሚለውን ማለት ነው ?
- ✓ 26 ኤ የሚለውን ማለት ነው
- ✓ እኮ እሱ ክፍል የምን ክፍል ነው?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ክፍሉን አላውቀውም እኔ የምን ክፍል እንደሆነ አላውቀውም ግን ያው እዚህ ነው የምታተዘበት ተብለን ነው የተነገረን ግን ክፍሉ የምን ክፍል እንደሆነ አልተነገረኝም
- ✓ ከዛ እርስዎ ከማን ጋር ነው የገቡት በታዛቢነት ከእርስዎ ጋ ታዛቢ የነበረው ሌላ ሰው ማን ነው?
- ✓ ወንደሰን ሰይፉ ይባላል
- ✓ እሺ አብራችሁ ነው የገባችሁት ሁለታችሁ?
- ✓ አብረን ነው የገባነው
- ✓ እሺ ሁለታችሁ ስትገቡ አህመዲን ጀበል ክፍሉ ውስጥ አልነበረም አደል
- ✓ አልነበረም እኛም ክፍሉ ውስጥ አልገባንም ውጭ ነው የቆምነው ከዛ በኋላ እሱ መጣ
- ✓ ከየት እንደመጣ ያውቃሉ?
- ✓ እኔ እንጃ ብቻ ማለት እንትኑ ላይ ብረት አለ እጁ ላይ ማለት ነው
- ✓ እጃ በካቴና ታስሯል ?
- ✓ አዎ እጁ ላይ ብረት አለ ከዛ በኋላ መጣ በቃ እሱ ነው እሱ ነው እንትን የሚባለው ስለዚ እናንተ ከሱጋራ ግቡ ተባልን
- ✓ ከየት እንደመጣ አያውቁም?
- ✓ አብረን ገባን ማለት ነው
- ✓ እኮ ይሁት የመጣው ሰው ከየት እንዳመጣው አያውቁም እሱን ?
- ✓ አዎ እኔ ማለት እኔ አላውቅም ግን የፖሊስ አካል አለ አብሮ ማለት ነው ስለዚህ አብረን አንድ ላይ ነው በጋራ የገባነው ወደዚህ ወደጠራሁት ቁጥር ክፍል ማለት ነው እኛ ቀድመን አደለም የገባነው አንድላይ ነው የገባነው
- ✓ እሺ ክፍሉ ውስጥ ከገባችሁ በኋላ ክፍሉ ውስጥ ባለው የፖሊሶች ኮምፒውተር ነው ኢንተርኔት እሱ የተገናኘው እና ኢሜሉን የከፈተው ?
- ✓ ማለት ክላስ ውስጥ ስንገባ ኮምፒውተሮች አሉ ከዛ ቁጭ በል ተባለ እና እዚጋ ቁጭአልን ስለዚህ ክፈት ተባለ በፊት ለፊት እራሱ ሲከፍት እኛ አየነው ማለት ነው
- ✓ መጀመሪያ ኮምፒውተሮቹ ክፍት ነበሩ ማለት ነው?
- ✓ ኖ እራሱ ክፍትነት አደለም እኛ ያየነው ዝግ ነው እራሱ ነው የከፈተው
- ✓ እሺ ኢንተርኔትን እንዴት ነው የተገናኘው በዛ ክፍል?
- ✓ አይ ዶ ኖው እሱን እኔ አላውቅም
- ✓ ኢንተርኔት መገናኘቱን አያውቁም??



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ እሱን አላውቅም
- ✓ ኮምፒውተሩ የፖሊሶች ነው ትልልቁኮምፒውተር ነው አደለም?
- ✓ አዎ ማለት ኮምፒውተሮች አሉ ትላልቅ ኮምፒውተሮች አሉ ስለዚህ እዛ ላይ በራሱ ኮድ ነው እራሱ የሚከፍተው ፖሊሶቹ አደሉም የሚነኩት እራሱ ነው የሚከፍተው ፓስወርዱን ይዞ ማለት ነው
- ✓ ኮምፒውተሩ ላይ አህመዲን ጀበል የሚል የተለጠፈ ስም የለውም አደል?
- ✓ የለውም
- ✓ እሺ ኮምፒተሩን ከመክፈቱ በፊት ፖሊሱ እናንተን አስተዋውቋችኋል ታዛቢ ናችሁ ብሎ አደል ልክ ነኝ ?
- ✓ አቤት?
- ✓ እናንተ ታዛቢ ናችሁ ብሎ አስተዋውቋችኋል አደል?
- ✓ አዎ እናንተ ታዛቢ ናችሁ እዚጋ የሚደረገውን ከይቅርታ ጋር ነው እኔ ለስራ ለሌላ ጉዳይ ስሄድ እነሱ ከይቅርታ ጋር ጠይቀውኝ ነው ወንድሜ አንዴ ትንሽ ትብብር ብታደርግልን ምናምን ብለው ነው ጥያቄ ያቀረቡት እንጂ እኔን አስገድደው አደለም የጠየቁኝ ስለዚህ በግዳጅም አደለም የቀረብኩት እውነታውን ነገር ለማየት ነው የቀረብኩት
- ✓ እሺ በወቅቱ ፖሊሱ ለአህመዲን ጀበል የፍ/ቤት ትእዛዝ ወይም የፍ/ቤት ፍቃድ ያለው መሆኑን አልነገውም አደል ?
- ✓ እ?
- ✓ ኮምፒውተሩ የሱን ኢሜል ለመፈተሽ የፍ/ቤት ትእዛዝ ወይም ፈቃድ ያለው ስለመሆኑ አልነገረውም አደል?
- ✓ አይ እኔ ስለሱ የማውቀው ነገር የለም
- ✓ እኮ አንተ ሲነገር አልሰማህም?
- ✓ ስለሱ እኔ የማውቀው ነገር የለም
- ✓ የሚያውቁት ሳይሆን አሁን ስለሰሙት ስላዩት ነገር ነው እየመሰከሩ ያሉት እና በወቅቱ ፖሊሱ ለአህመዲን ጀበል የፍ/ቤት ትእዛዝ ያለው ስለመሆኑ አልነገረውም አልሰሙም አደለም ወይ ?
- ✓ አህመዲን ጀበልን ቁጭ በል ብሎት እኛም ቁጭ እንድንል ከደረገ ከዛ በኋላ እነሱ እንግዲህ ያኘው ኢሜሉን ስትከፍት እንደታዛቢ ሆነው ነው የምጡት ተብሎ ተነግሮ ነው በራሱ ፓስወርድ ከፍቶ እንዲወጣ ያደረገው



http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ስለዚህ ስለፍ/ቤት ትእዛዝ መኖር ወይም አለመኖር የተነገረህ ነገር የለም?

✓ አዎ እኔ ስለሱ ምንም የማውቀው ነገር የለም

✓ ከዛ በኋላ የተከፈተውን ሰነድ የወጡትን ሰነዶች እሱ ሲፈርም ምን እያለ ነበረ የፈረመባቸው?

✓ በራሱ ኮድ ማለት ነው ከፍቶ የራሱ መሆኑን አምኖበት ሲፈርም እንደዛ እያለ ነው የሚፈርመው

✓ ምን ብሎ ሲጽፍ ምን ብሎ ነው የፃፈው አይተውታል አደለም ሲጽፍ?

✓ አይቼዋለሁ ከራሴ በራሴ አድራሻ ከፍቼ የራሴ መሆኑን ሳረጋግጥ የሚል ይጽፋል ይፈርማል እኛ እሱን ደግሞ በማየት

✓ ስለዚህ በፈረመባቸው ሰነዶች ላይ ሁሉ ይሄ ሰነድ ከራሴ ክምፒውተር ላይ የተገኘ የራሴ ሰነድ ነው ብሎ እያረጋገጠ ነው የፈረመው?

✓ ያው እራሱ አምኖበት የራሱ መሆኑን አምኖበት ሲፈርም

✓ እኮ ይሄን እየፃፈ ነው የፈረመው አደል ?

✓ አዎ ይሄን ገለፀ ሲፈርም እኛም ደግሞ እሱ የገለፀውን ነገር በማየት እኛም ፊርማ እንፈርማለን ከሱ እራሱ መውጣቱን በራሱ አድራሻ እራሱ ማውጣቱን እኛ ጽፈን እንፈርማለን

✓ እሺ ሰነዶቹ ይዘታቸው ምን እንደሆነ እርስዎ አላነበቧቸውም አደል?

✓ እኔ አላነበብኳቸው አሁን ትዝ አይሉኝም አይመጡልኝም ማለት አላነበብኳቸውም ግን ፕሪንት ሲደረግ ፎቶግራፎች ሁሉ አሉ እላዩ ላይ ፒክቸሮች አሉ ፒክቸሮቹን አይቻቸዋለሁ

✓ አቶ አስራት እኔ ለምጠይቆት ቀጥተኛ ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ቢሰጡኝ ሰዓቱም ያጥራል

✓ እ?

✓ ለምጠይቆትነገር ቀጥተኛ መልስ ቢሰጡኝ ሰዓቱም ያጥራል አያርዝሙት ነው አሁን እርስዎ ሲፈርሙ ሰነዶቹ ይዘታቸው ምን እንደሆነ አላነበቡም ሳያነቡ ነው የፈረሙት አደል ?

✓ እኔ አሁንም ማለት የሚወጡትነ ወረቀቶች ማለት ጊዜው አሁን ለማንበብ ጊዜውአይፈቅድልኝ ማለት ከራሴም ከስራም አኳያ እንትን ለማለት

✓ አልተነበበም አላነበቡትም እርስዎ አንብቤያለሁ ወይ አላበብኩም ብቻ እኮ ነው መልሱ?

✓ አላነበብኩትም መፈረም ብቻ ነው እኔ የሱን የሚጽፈውን አይቼ ነው

✓ በቃ ይበቃል

✓ አህመዲን ጀበልም ወረቀቶቹን አንብቦ አደለም የፈረመው አደል?



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ሞኖ ወረቀቶቹ ሲወጡ አህመዲን ጀበል ወረቀቶቹን ያያቸዋል በደንብ ካያቸው በኋላ ነው የሚፈርመው
- ✓ እንጂ ዝም ብሎ አይፈርምም ተነቦለት ወይም አንብቦ አይደለም የሚፈርመው ?
- ✓ አይደለም ካያቸው ወረቀቶቹን ያያል ጽሁፎቹን ያነባቸዋል እራሱ ይፈርማል እራሱ እያየው ሲፈርም እያነበበ እኔ አየዋለሁ እና በዛ ላይ ነው እራሱ አምኖ የፈረመው
- ✓ እሺ እርስዎም የሰነዶቹ ይዘት እምን እንደሆነ አያውቁም አደል?
- ✓ አይ የሱን ይዘቱን አላውቀውም
- ✓ እሺ ያ ኮምፒውተር ከየት እንደመጣም አያውቁም አደል?
- ✓ እሱን አላውቅም
- ✓ እሺ ከዛን በኋላ አህመዲን ጀበል ወዴት እንደተመለሰም አያውቁም አደል?
- ✓ አይ እሱን አላወቅኩም አንድ ላይ ነው ማለት እንትን ያልነው
- ✓ ብራችሁ ነው የወጣችሁት ወይስ እሱ ?
- ✓ አይ እሱ ወጥቷል ቀድሞ ነው የወጣው ቀድሞ ሲወጣ እጁ በካቴና እንደታሰረ ነው የሄደው አደል?
- ✓ መጀመሪያ ማለት በካቴና ታስሮ መጣ ተፈታለት በራሱ እጅ እንዲንቀሳቀስ ማለት ከዛ በኋላ ከጨረሰ በኋላ እንደገና ያው
- ✓ ሲወጣም በተመሳሳይ ካቴናው ታስሮ ነው የተመለሰው?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ ስለ አህመድ ሙስጠፋም ልጠይቅት ነሐሴ 25 ?
- ✓ እ አህመድ ሙስጠፋ?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ
- ✓ እሱስ እዛው ቁጭ ብላችሁ ነው የመጣው?
- ✓ ያው እኛ ውጪ ወጣን
- ✓ ተመልሳችሁ ወጣችሁ?
- ✓ አዎ ተመልሰን ወጣን ከዛ በኋላ እሱም መጣ አብረን አንድ ላይ ገባን
- ✓ እሺ አህመድ ሙስጠፋም ሲመጣ በተመሳሳይ በካቴና ታስሮ ነበር አደል?
- ✓ አዎ ታስሯል ከዛ በኋላ ተፈታለት ያው እራሱ በራሱ ኮድ ኢሜሉን እንዲከፍት ተደርጐ ፕሪንት ተደርገው ወረቀቶቹ ወጥተዋል በራሱ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እዛው ክፍል ውስጥ 26 ሊ የሚለው ክፍል ውስጥ ነው አደል?
- ✓ 26 ሊ
- ✓ እዛው ቅድም አህመዲን በከፈተበት ኮምፒውተር ነው የተጠቀመው አደል?
- ✓ ማን?
- ✓ አህመድ ሙስጠፋም መጀመሪያ አህመዲን ጀበል ነው የገባው አደል ?
- ✓ አዎ
- ✓ ቀጥሎ አህመድ ሙስጠፋ ሲመጣ እዛው ክፍል ተመልሳችሁ ስትገቡ አህመድ ሙስጠፋም ኢሜል የከፈተው በዛው በአህመዲን ጀበል በተጠቀመበት ኮምፒውተር ነው አደል?
- ✓ የሱ ደግሞ ማለት ያው በዛው ኮምፒውተር ነው አጠቃቀማቸው ማለት ነው ግን ጠፍቶ እራሱ ነው የሚከፍተው
- ✓ አይ ኮምፒውተሩን ነው የጠየቅኩት ያው ኮምፒውተሩ አንድ ኮምፒውተር ነው
- ✓ ኮምፒውተሮች አሉ 3 አሉ ግን አንዱ ላይ ነው እንትን የተባለው
- ✓ እሺ ለሱም ኢሜል አድራሻውን ለመፈተሽ የፍ/ቤት ትእዛዝ ያለው ስለመሆኑ ፖሊሱ አልነገረውም አደል?
- ✓ እንግዲህ ማለት እኔ ሲመጣ አብረን ውጪ ነበርን
- ✓ አደለእ እርስዎ ስላዩት ነገር ብቻ አሁን እርስዎ እዛ ቁጭ ብለው ያዩትን እና የሰሙትን ብቻ ነው የሚመልሱልኝ አሁን እርስዎ ቁጭ ብለው ባሉበት ጊዜ የኢሜል አድራሻው ሲከፈት ይሄን የኢሜል አድራሻውን ሲከፈት የፍ/ቤት ትእዛዝ ያለው ስለመሆኑ ፖሊሱ ለአህመድ መስጠፋ አልነገረውም አደል?
- ✓ አህመድ ሙስጠፋ የተነገረው ምንድን ነው እኛ
- ✓ ይኸውሎት እኔ የጠየቅኩትን ብቻ ይመልሱልኝ
- ✓ ማለት የትክክለኛውን መደማመጥ ስላለብን ነው የምንናገረውን ነገር የስ ማብራራት ማለት እኛ ውጪ ቆመን ታዛቢ መሆናችንን ተነገረው ለእሱ ስለዚህ በራስህ አድራሻ እራስህ ትከፍታለህ እምትከፍተውን ለማየት ነው የመጡት ተብሎ ተነገረው እሺ አለ ከዛ በኋላ በቃ ግልጽ ነው
- ✓ የፍ/ቤት ትእዛዝ መያዝ አለመያዛቸውን ገልፀውለታል ወይ ነው?
- ✓ አይኖ እሱ ነገር ሲነገረኝ አልሰማሁም
- ✓ በቃ ሌላ ጥያቄ
- ✓ እሺ የአህመድ ሙስጠፋ ታትሞ የወጡት ወረቀቶች ላይ ምን ብሎ ነው የፈረመው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ በራሱ ኮድ
- ✓ አይ ሲፈርም ምን ብሎ ጽፎ ነው የፈረመው ነው የምሉት ?
- ✓ እኮ የሚፈርመውን እኮ ግልጽ ለማድረግ ነው በራሲ ኮድ ከፍቼ የራሲ መሆኑን አረጋግጣለሁ ጽሁፍ ጽፎ ይፈርማል እኛ ደግሞ እሱን አይተን እንፈርምለታለን
- ✓ ይሄ በራሲ ኮድ የራሴ መሆኑን አረጋግጣለሁ የሚል ነገር በግልጽ ጽፏል እሱ ?
- ✓ አዎ
- ✓ እናንተም በዚሁ ስር አረጋግጣችሁ ፈርማችኋል?
- ✓ አዎ እያነበበ ነው የፈረመው እራሱ የራሱ መሆኑን አረጋግጦ ማለት ነው
- ✓ የሱም ወረቀቶች የወጡት ላይ እርስዎ አላነበቧቸውም ወረቀቶቹን በሙሉ አደል?
- ✓ አላበብኳቸዉም
- ✓ ይዘታቸውንም አያውቁም?
- ✓ አላውቅም
- ✓ እሺ አህመድ ሙስጠፋ ከጨረሰ በኋላ በተመሳሳይ እጁ በካቴና ታስሮ ነው የተመለሰው አደል?
- ✓ አዎ
- ✓ አቶ አስራት
- ✓ አቤት
- ✓ ቅድም ማእከላዊ ለራሴ ስራ ሄድኩ ብለው ነበር ማእከላዊ ከሰው ወይስ ተከሰው ወይስ ለምስክርነት ነበር?
- ✓ ማእከላዊ የሄድኩት ለራሴ ስራ ነው
- ✓ የምን ስራ ?
- ✓ ተቃውሞ አለን ያው ምንድን ነው ምስክሩ አሁን በራሳቸው ጉዳይ እንዲገልፁ እየተደረገ ነው ተከስሼ ካሉ በምን ጉዳይ እንዴ እያለ ዝርዝር ሊኬድ ነው ወይንም ለምስክር ከሆነ ይሄንንም አሁን ዝርዝር ሊገባ ነው ስለሆነም አንድም በራሳቸው መመስከር ግዴታ የለባቸውም ይህም የሕገመንግስታዊ ጥበቃ ያለው ነው ስለሆነም ይሄ ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግልን
- ✓ አሁን የተጠየቁትን ጥያቄ ለእርስዎ ነው ምርጫውን የምንሰጠው
- ✓ እሺ
- ✓ ይሄ የተጠየቀው ጥያቄ /የማይሰማ/



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ መግለጽ አልፈልግም ብገልጽ እራሴን ልጎዳው እችላለሁ የመጣሁበትን እራሴም ትክክለኛውን መንገድ ስለማውቀው በቃ ስለዚህ እራሴን ስለሚጎዳኝ ይሄን ነገር ልገልጽ አልፈልግም
- ✓ ሌላ ጥያቄ ይቀጥል
- ✓ እሺ. ቀኖቹን በምን አስታወሱ እነዚህን ሁለት ቀኖች 2004 የሚሉት እና 2005 ዓ.ም. የተደረገውን ቀን በምን አስታወሱ ?
- ✓ ያስታወስኩት ማለት ድጋሚ ትጠራለህ የሚለውን አማርኛ ሲነገረኝ ስለዚህ እንደታሣቢነቱ እነዚህ የገባሁባቸውን ቀኖች በራሴ ጭንቅላት ጽፌ ይገርቸዋለሁ የገባሁበትን ቀን ስለዚህ ድጋሚም ስጠራ የተጠራሁበትንም ቀን በጭንቅላቴ ይገፑዋለሁ ስለዚህ እነዚህን መቼም አረሳቸውም
- ✓ በታሣቢነት ተገኝተው ያውቃሉ ከዚህ በፊት ?
- ✓ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው
- ✓ እሺ. ቅድም አህመዲን ጀበልም አህመድ ሙስጠፋም በራሳቸው ኮድ ከፈቱ ብለው ነበረ እነዚህን ኮዶች ያውቋቸዋል ?
- ✓ እኔ አላውቃቸውም
- ✓ አይተዋል ሲከፍቱ በኮደቹ ?
- ✓ ሲጽፉ አይቻለሁ
- ✓ ኮዱን?
- ✓ ኮዱን ሲጽፉ አይቻለሁ
- ✓ እኮ ምን ብሎ እስቲ ካስታወሱ?
- ✓ አላስታውስም እኔ አሁን
- ✓ ቅድም ፎቶ ግራፍ ነበራቸው ብለዋል እንዚህ ሲከፈቱ ምን አይነት ፎቶ ግራፍ ነበረ የነበራቸው?
- ✓ ፎቶ ግራፎቹ ማለት የመስኪድ መስኪድ ላይ የተደረጉ አሉ ማለት መስኪድ ነገሮች ተጎትተውኛል አላዩ ላይ.
- ✓ ምን አለ መስኪዱ ላይ ?
- ✓ ማለት መአት ሕዝብ እንዳለ እቶ ግራፎቹ ላይ. ማለት ነው የወጡት ፎቶ ግራፎች ላይ እነዚህን ማን አሁን
- ✓ የምን መስኪድ ነው ይላል ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ መስኪዱን እኔ አሁን አላስታውሰም የትኛው መስኪድ እንደሆነ አላውቅም መአት መስኪድ ስላለ የትኛው እንደሆነ ስላላወቅኩት ይሄንን ብዙም ለመግለጽ እንትን
- ✓ ሌላስ ምስል ምን አለ?
- ✓ በቃ አሁን ማለት ጊዜዎቹ ስለሄዱ አሁን ብዙም ላይመጡልኝ ይችላሉ
- ✓ የሚያስታወሱት መሲኪድ ብቻ ነው?
- ✓ አዎ መስኪድ እና መአት ሕዝብ ያለበት ታይቶኛል
- ✓ ከሁለቱም ላይ የተገነው ምስል አንድ አይነት ነው መስኪድ ብቻ የሚያሳይነው ?
- ✓ እ?
- ✓ ሁለቱም ላይ ያዩት ምስል መስኪድ ብቻ የሚያሳይ ነው?
- ✓ ሕዝብም እያልኩ ነው መስኪዱ ውስጥ ሕዝቦችም ይታዩኛል ታይተውኛል
- ✓ እሺ?
- ✓ በቃ ከዛ ሌሎቹን አላስታውሳቸውም
- ✓ አቶ አስራት
- ✓ አቤት
- ✓ እስቲ ቅድም ስለ ክፍሉ ሁኔታ ነግረውናል ስንተ ጠረጴዛ ነበረ ነው ያሉት?
- ✓ ማለት ሁለት ጠረጴዛ አይቻለሁ
- ✓ እሺ አንደኛው ላይ ማን ነው የተቀመጠው ?
- ✓ ሁለቱም ይኸውልህ ሁለቱም ጠረጴዛ ላይ ማለት ሁለት ጠረጴዛ አለ አንደኛው ጠረጴዛ ላይ ነው እኛ የተቀመጥነው አህመድ ጀበልም እንደዚህ ጠረጴዛዎች አሉ አህመድ ጀበልም ቁጭ ብሏል እኛም ቁጭ ማለት አህመዲን ጀበል ወደ ኮምፒውተሩ ተጠግቶ እንዲከፍት ተደረገ ከዛ በኋላ የወጡ ወረቀቶችን
- ✓ ቆይ ወደዛ እመጣለሁ ሁለት ጠረጴዛ አለ እናንተ አህመዲን ጀበል ለብቻው ነው የተቀመጠው?
- ✓ አንድ ላይ ነው
- ✓ ከማንጋር እናንተ?
- ✓ ከእኛጋር
- ✓ ከታዛቢዎች ጋር?
- ✓ አዎ
- ✓ መርማሪውስ ወይም እዛ የነበሩ ሰወች?

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ለብቻ ነው የተቀመጡት
- ✓ በሌላኛው ጠረጴዛ?
- ✓ አዎ
- ✓ አጠገቸው ምን አለ መርማሪዎቹ አጠገብ ኮምፒውተር አለ?
- ✓ ኮምፒውተር አለ ኮምፒውተር እነሱ አልነካኩም እነሱ እሱ የሚከፍተውን ብቻ ነው
- ✓ ኮምፒውተር አለ እሺ እናንተ ስትገቡ ታዛቢዎች ስትገቡ አህመዲንም አልነበረም ኮምፒውተሮቹ ስትገቡ በየቦታቸው ተቀምጠው ነው ያያችሁት አደል?
- ✓ ኮምፒውተሩ ተቀምጦ ነው ያገኘናቸው ስንገባ
- ✓ በአህመዲን ጀበልም በመርማሪውም ፖሊስ ያለው ኮምፒውተር እዛው ተቀምጦ ነው ያያችሁት?
- ✓ አዎ
- ✓ ቅድም እንደገለፁት ኮምፒውተሩ ላይ ምንም የተፃፈበት ነገር የለም ?
- ✓ ምንም ነገር የለም
- ✓ እሺ ጥሩ ከዛ የአህመዲንን ስትጨርሱ አህመዲንም ወጣ ታዛቢዎችም ወጣችሁ?
- ✓ አዎ
- ✓ ፖሊሶቹ ውስጥ ነበሩ?
- ✓ እነሱም ወጥተዋል
- ✓ ፖሊሶቹም አብረዋችሁ ወጡ?
- ✓ አብረን ነው የወጣነው
- ✓ ከዛ ባዶ ነበረ ክፍሉ?
- ✓ እ?
- ✓ አህመድ ሙስጠፋ እስኪመጣ ድረስ ክፍሉ ባዶ ነበር?
- ✓ ባዶ ነው
- ✓ ከዛ በኋላ አህመድ ሙስጠፋ መጣ ፖሊሶችም ታዛቢዎችም አህመድ ሙስጠፋም ገባችሁ?
- ✓ አዎ
- ✓ ከዛ ያው ኮምፒውተር ላይ ነው የተቀመጡት አደል?
- ✓ አዎ
- ✓ ይሄ ተደግሟል
- ✓ ሌላ ጥያቄ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አህመድ ሙስጠፋ በየራሳቸው ኮድ ከፈቱ በለዋል?
- ✓ አዎ
- ✓ ኮዶችን አያስታውሱም?
- ✓ አዎ
- ✓ በየራሳቸው ይሁን በአንድ ኮድ ይሁን በምን ማረጋገጥ ይችላሉ ተመሳሳይ ኮድ ከፍተው ይሁን የተለያየ ይሁን እርስዎ የተፃፈውን ካላዩ ካላስታወሱ ተመሳሳይ ኮድ ላለመጠቀማቸው በምን ያውቃሉ ?
- ✓ እሱን አሁን አላታውሰውም
- ✓ አያስታውሱም?
- ✓ አዎ
- ✓ ፕሪንተሩ የት ጋ ነበረ የተቀመጠው ፕሪንተር ያውቃሉ?
- ✓ እ?
- ✓ ቅድም ፕሪንት ሆኖ ወጣ ሲሉ ነበረ ፕሪንተሩ የት ጋ ነበረ የተቀመጠው?
- ✓ መሬት ተቀምጧል
- ✓ ማለት ከአህመዲን ስር ነው ከመርማሪው ስር?
- ✓ አህመዲን ስር
- ✓ እሺ አቶ አስራት ፓስወርድ ለአህመዲን በዚህ ፓስወርድ ክፈተው ብሎ በወረቀት ጽፎ የሰጠው ማን ነበረ ?
- ✓ እ?
- ✓ ፓስወርድ ጽፎ በወረቀት የሰጠው የለም አብራችሁ ከገባችሁት ?
- ✓ አይ እኔ እሱን አላየሁም
- ✓ በሱ ፓስወርድ አልከፈት ብሏቸው አማን የሚባል ሰው ላይ ስልክ ደውለው ፓስወርድ ሲቀበሉ ሰምተሃል አልሰማህም?
- ✓ አልሰማሁም
- ✓ ነበርክ አደለም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻዉ ይሄንን አታስታውስም?
- ✓ አላስታውስም
- ✓ ስልክ እሺ ሲደውሉ እዛው ቆመው ፓስወርድ ሲቀበሉ አልሰማህም ፓስወርዱ ተቀይሯል ብለው?
- ✓ አላስታውስም እሱን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ የከፈተው አህመዲን እራሱ ነው የከፈተው?
- ✓ አዎ እራሱ ነው
- ✓ የትኛውን ነው የከፈተው ክነሱ ኮምፒውተር ላይ ነው የከፈተው?
- ✓ ቆይ ይሄ ተጠይቷል ሌላ ካለሽ
- ✓ እሺ አልፈርምም ያለበት ሁኔታ አልነበረም አህመዲን?
- ✓ አይ እንደዚህ የለም
- ✓ እሺ ይሄኛው የአምነስቲ ኢንተርናሽናል እሪፓርት ነው እኛ ከታሰርን በኋላ ስለሆነ አልፈርምም ብሎ የተጨቃጨቁበት አልነበረም?
- ✓ የለም እንደዚህ የለም
- ✓ ከዛ መጨረሻ ላይ ወደ ኢምቦቅሴ ገባ ብለህ ፈርም ተባብለው ሲስማሙ አልነበርክም?
- ✓ እ?
- ✓ ወደ ኢምቦቅሴ የገባ ነው ብዬ እፈርማለሁ ሲባባሉ?
- ✓ እኛ የነበርነው ልንገርሽ  እኛ የነበርነው ኖ ይሄንን ማለት እራሱ እንዲከፍት ሲነግረው አይተናል በራሱ ኮድ እራሱ  እንዲከፍተው ማለተ ነው
- ✓ አይ ጥያቄው /የማይሰማ/
- ✓ አልሰማሁም እሱን
- ✓ ፕሪንት ሲደረግ የነበረው ከኮምፒውተሩ ነው ከላፕቶፑ ነው ?
- ✓ ከሁለቱም ላይ
- ✓ ፕሪንት እምቢ ብሏችሁ ወደ ሌላ ክፍል አልሄዳችሁም ?
- ✓ አልሄድንም
- ✓ በድጋሚ የመጣህ ጊዜ ማለት ነው ሁለተኛው ምስክርነት ላይ ስትሄድ መጀመሪያ ቀደም ሲል የፈረምክበት ስለሆነ በድጋሚ አልፈርምም ሲልስ አልሰማህም?
- ✓ አይ እሱን አልሰማሁም
- ✓ ድጋሚ የመጣህበትን በተመለከተ ነው መጀመሪያ ታዘባችሁ ለምን ድጋሚ እንደተጠሩ የተነገሮት ነገር አለ?
- ✓ ባለፈው ላይ መጥተህ ባየኸው ነገር ላይ አሁንም ድጋሚ  እንድታዩልን ብለው ጠርተውኝ ነው ያየሁት የአህመዲን ጀበልን መስከረም 5 ቀን 2005 ዓ.ም.
- ✓ በመጀመሪያው ቀጠሮ ለምን ይሄ እንዳልወጣ የተገለፀሎት ነገር አለ?
- ✓ እ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ በመጀመሪያው ነሐሴ በመጡበት ጊዜ ለምን ያኔ እንዳልወጣ ከኮምፒውተሩ የተገለፀለት ነገር አለ?
- ✓ አይ እሱ የለም ማለት መስከረም 5 የመጣሁት ከላፕቶፑ ፕሪንት ሲደረግ ነው ያየሁት መስከረም 5 አንደኛ ወር ላይ ማለት ነው 2005 ዓ.ም.
- ✓ ከዛ በፊት በየትኛው ነው ፕሪንት የተደረገው?
- ✓ ከኢሜሉ ላይ በኢሜሉ ነሐሴ 25 ከኢሜሉ ላይ ነው በአህመድ ጀበል ላይ የመጣው ያየሁት ማለት ነው መስከረም 5 ደግሞ ላፕቶፑ ላይ ላፕቶፑን ሲከፍት ፕሪንት ሲያረግ መስከረም 5 መጥቼ አይቻለሁ
- ✓ ኢሜል እኮ በሆነ ኮምፒውተር ውስጥ ያለ ነገር ነው እራሱ  እንደ ኮምፒውተር ሳይሆን አድራሻ ነገር ነው ይሄን ያውቃሉ?
- ✓ እ?
- ✓ ከኢሜል ላይ ሲሉ ኢሜል የሚባለው ትርጉሙን ያውቁታል ኢሜል ምንድን ነው ነሐሴ ያዩት ከኮምፒውተር ውስጥ የሚወጣውን አደለም እንዴ ያዩት?
- ✓ አዎ ከኮምፒውተሩ የሚወጣውን
- ✓ ከየትኛው ኮምፒውተር ከዴስክ ቶር ላፕቶፕ የሚባል አለ?
- ✓ ኦኬ እነዚህ ምናልባት አሁን ማለት
- ✓ በእጅ የሚያዝ ላፕቶፕ ማለት
- ✓ እ?
- ✓ ላፕቶፕ በእጅ የሚንጠለጠለው ነው ዴስክ ቶፕ ጠረጴዛ ላይ የሚቀመጠው ነው ስለዚህ ነሐሴ 25 ጠረጴዛ ላይ ከሚቀመጠው ከትልቁ ፕሪንት ሲሆን አይተው መስከረም ሲመጡ ከላፕቶፕ ነው ይሄን ነው ?
- ✓ መስከረም 5 ከላፕቶፑ ሲወጣ
- ✓ ነሐሴስ?
- ✓ ነሐሴ 5 ከኮምፒተሩ
- ✓ በጠረጴዛ ላይ ካለው?
- ✓ አዎ ጠረጴዛ ያለ ኮምፒውተር የአህመድ ጀበል ማለት ነው መስከረም 5 ደግሞ ከላፕቶፑ ሲከፍት
- ✓ እሺ አቶ አሰፋት
- ✓ ቆይ ጠበቃ ስምን ገልፀው ያግቡ ከሰነት የተመዘገቡ አይስለኝም



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ. ከ28ኛ ተከሳሽ ውጪ ላሉት ጠበቃ መሃመድ አብደላ ዘግይቼ ቀርቢያለሁ አቶ አስራት አህመድ ሙስጠፋም በራሱ ላፕቶፕ ነው ሲከፍት የነበረው አህመዲን በራሱ ላፕቶፕ ሁለት ጊዜ ነው እንትን ያለው ብለዋል የአህመዲን ጀበል ሁለት ጊዜ ብለዋል አህመድ ሙስጠፋም ሲከፍት የራሱን ላፕቶፕ ነበረ ሲከፍት የነበረው ?
- ✓ አዎ አህመዲን ጀበል ያው ሁለት ጊዜ ነው የመጣሁት አህመድ ሙስጠፋ አንድ ጊዜ ነው የመጣሁት
- ✓ ላፕቶፑ የአህመድ ሙስጠፋ የራሱ ነበር ?
- ✓ አህመዲን ጀበል ላፕቶፕ አለው የራሱ
- ✓ አህመድ ሙስጠፋስ?
- ✓ አህመድ ሙስጠፋ ከኮምፒውተር ብቻ ነው ነሔሴ 25
- ✓ አህመዲን ጀበል ሁለቱንም ጊዜ በላፕቶፕ ነው ወይስ በምን ነበረ ሲከፍት የነበረው?
- ✓ ቆይ ተጠይቋል እሱ ብዙ ጊዜ ነው የተጠየቀው እሳቸው አቶ ባህሩ ጠይቀዋል
- ✓ እሺ. አህመድ ሙስጠፋ ክፈተው ሲሉት ለምን ፓስወርዱን ወይም ኮዱን ቀየራችሁት ሲላቸው ሰምተሃል?
- ✓ አልሰማሁም እሱን
- ✓ ኢሜል እምቢ ብሏቸው ኢሜል ለመክፈት?
- ✓ ተጠይቋል እሱ
- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት የኢሜል ጉዳይ ቢጠየቅም እኔ ሌላ እንትን ነው የምጠይቀው
- ✓ እሺ. የሚጠይቁትን ቀጥታ ይጠይቁዋ
- ✓ እሺ. ኢሜል እምቢ ብሏቸው ፕሪንት የተደረገ አለልህ እሱ ላይ ፈርም ሲሉት ተስማምቶ ነው የፈረመው?
- ✓ እስቲ ይደገም ይሄ ጥያቄ
- ✓ ኢሜል ለመክፈት ኢሜል ክፈትና ከዛ ላይ ፕሪንት አርገህ ትፈርማለህ አሉትና ኢሜል ሲሞክር እምቢ አለ እና ፕሪንት የተደረገ አለ እዛው ላይ ፈርም ሲሉት እዛው ላይ ነው የፈረመው አደል?
- ✓ አደለም እንደዚህ አይነት አደለም አሰራሩ የተካሄደው እራሱ በራሱ ከፍቶ እራሱ ነው ወረቀት ፕሪንት የተደረገው ወረቀት የወጣው ከዛ በፊት ግን የለም ወረቀት
- ✓ ሳይበሳጩ፡ እረጋ ብለው ይመልሱልኝ
- ✓ እሺ. ከአህመድ ሙስጠፋ እና ከአህመዲን ጀበል ውጪ ሌላ ታስሮ የገባ ሰው ነበረ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ የለም
- ✓ ሁለቱ ብቻ ነው የነበሩት?
- ✓ ሁለቱ ብቻ ናቸው
- ✓ መስከረም 5 ላይ በታዛቢነት ሲመጡ አህመዲን ጀበል በራሱ ላፕቶፕ ኢሜሉን ከፍቶ ፕሪንት አደረገ ብለዋል በራሱ ላፕቶፕ ወይም ላፕቶፑ የሱ መሆኑን ተነግሮትነው ነግረዎት ነው ይሄ ላፕቶፕ የሱ ነው ተብለው ነው?
- ✓ ተጠይቋል ይሄ እየደገሙ ነው
- ✓ እሺ አንተ በታዛቢነት የፈረምክባቸው ወረቀቶች ለነሱ የሚጠቅም ይሁን ወይም በማስረጃነት የሚቀርብባቸው ይሁን የትኛውን ነው የተረዳኸው የተነገራቸው ነገር የለም ብለሃል ቅድም የትኛውን ነው እነሱ ተረድተው ሲፈርሙ የነበረው ይጠቅመናል ብለው ነው ወይስ በማስረጃነት ይቀርብብናል እያሉ ነው ሲፈርሙ የነበረው ?
- ✓ እነሱ ማለት ይሄ ፕሪንት ያደረጉትን ወረቀት ማለት ነው የራሳቸው እንደሆነ አምነውበት ነው የፈረሙት
- ✓ ገባኝ እኮ አሁን የራሳቸውመሆኑን አምነውበት እያልከን ነው ግን አሁን ሲፈርሙበት ይሄ ነገር ለኔ የሚጠቅመኝ ሰነድ ነው ወይስ በማስረጃነት ይቀርብብኛል እያሉ ነው የትኛውን አምነው ነው ሲፈርሙ የነበረው ?
- ✓ ይመስለኛል ይሄን ነገር ከራሱ ጭንቅላት ጋራ ተነጋግሮ ይመስለኛል የፈረመው
- ✓ አይ አንተ የተረዳኸውን ነው ?
- ✓ እኔ የተረዳሁት ደግሞ እንደሚጠቅመው አርጌ ነው እኔ በራሴ ጭንቅላት
- ✓ ይሄ ኦፒኒየን ጥያቄ ነው እየጠየቁ ያሉት
- ✓ አይ ከሁኔታው የተረዳውን ነው የጠየቅኩት
- ✓ በቃ እስቲ ወደሌላ ይሄ ኦፒኒየን ነው
- ✓ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- ✓ እሺ አቶ አስራት
- ✓ አቤት
- ✓ ተከሳሾች ሁለቱም ሲመጡ ወደዛ በእጃቸው በካቴና ታስሮ ነበር ብለዋል?
- ✓ አዎ
- ✓ ከየት ነበረ የመጡት?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ማለት የመጡበትን እኛ መሃል ላይ.
- ✓ ማለት ከውጪ ነው የመጡት ወይስ ከእስር ቤት ነው የመጡት ምንድን ነው የተረዱት ነገር ምንድን ነው እስቲ?
- ✓ ይመስለኛል ከእስር ቤት መሰለኝ
- ✓ እሺ በአጃቢ ነው የመጡት  አደል?
- ✓ በአጃቢ ነው የመጡት ከዛ  አጃቢው ካቴናውን ፈቶላቸው ሄደ?
- ✓ አጃቢው ካቴናውን ከፈታ በኋላ እሱ ተመለሰ እኛ ከሌላው አካል ጋራ ግቡ ስንባል አንድ ላይ ገባን ወደ ክፍሉ ይቺ አሁን የጠራኋት ቁጥር ክፍል ማለት ነው
- ✓ ቅድም የእግር ብረት በማለት የገለፁት ነገር አለ እና ይሄንኑ ካቴና ለማለት ፈልገው ነው ወይስ ሌላ ነገር የታሰሩበት ሌላ ነገር ነበር?
- ✓ ማለት የግር ብረት ምናልባት እኔ አጠቃቀሴ ስተት ሊኖረው ይችላል ግን ይሄ ካቴናው ነው
- ✓ የእግር ብረት  አላሉም እጃቸው ለይ ብረት ነበረ ነው
- ✓ ብረት እጃቸው ላይ አለ ነው ያልኩት
- ✓ እሺ ሌላው ኢሜላቸውን ሲበረብር የነበረው ፖሊስ ነው ወይስ እራሳቸው በፍቃዳቸው ነው የከፈቱት ?
- ✓ እራሶቸው በራሳቸው ፍቃድ ነው
- ✓ ከነሱ ውጪ ከከፈቱ በኋላ ፖሊስ ተቀምጦ የነሱን ኢሜል ሲያይ ነበር እንዴ?
- ✓ በቃ ማለት ፖሊሱ ከጐን ይቀመጣል እኛ ሲወጣ እሱ ፕሪንት ሲደረግ እኛ እናያለን ያው እኛ የተቀመጥነው ደግሞ ፕሪንት የሚደረገውን ወረቀት እንድናይ ነው በራሱ ኮድ ከፍቶ ማለት ነው
- ✓ ኢንተርኔት ተጠቅመው ያውቃሉ እርስዎ?
- ✓ ኢንተርኔት ተጠቅሜ አላውቅም
- ✓ ኢሜል ምን እንደሆነ?
- ✓ ያው በስም ነው ግን ያው እንትኑ የለኝም ግን በስም
- ✓ ቢያንስ አድራሻው አንድ አይነት ነው ወይስ የተለያየ ነው ሁለቱ አቶ አህመድ እና አቶ አህመዲን የከፈቱት ኢሜል አንድ ነው ወይስ የተለያየ ነው አድራሻው ኢሜል አድራሻው?
- ✓ አይ እኔ ኢሜል አሁን አላስታውሰውም ኢሜል አድራሻው ይመስለኛል የተለያየ ይመስለኛል
- ✓ እሺ ሌላው በሰነዶች መፈረም ላይ የተፈጠረ አለመግባባት ነበረ እንዴ?



2496

896

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ የለም
- ✓ ቀድሞ ፕሪንት በተደረገ ሰነድ ላይ ተፈርሟል በወቅቱ ?
- ✓ ፕሪንት የተደረጉት እኛ በራሱ ኮድ ወረቀቶች የሉም ሌሎች ወረቀቶች ግን እራሱ በራሱ ኮድ ከፍቶ ሲወጣ ነው አምኖበት የሚፈርመው ስለዚህ እሱን ደግሞ እኛ በማየት አምኖበት የፈረመውን ወረቀት በማየት ነው
- ✓ እሺ. ሌላው ስለ ፓስወርድ በስልክ የተጠየቀ ሌላ ሰው አለ?
- ✓ እኔ ይሄንን አላውቅም ማንም የተጠየቀ የለም
- ✓ አሁን እርስዎ እዛ በነበሩበት ሰዓት ፓስወርድን አስመልክቶ የተደዋወለ ስልክ የሰሙት ነገር አለ?
- ✓ ይሄን አልሰማሁም
- ✓ እሺ. ሌላ እስቲ ምስሎቹ ላይ ይሄን ጥያቄ እንተወውና ቢሮው ላይ ቅድም የቢሮቁጥሩን ገልፀዋል ይሄ 26 ኤ የሚል ማለት ነው ?
- ✓ አዎ
- ✓ ቢሮ ውስጥ ምን ምን አለ ብለን ቅድም መጀመሪያ ስንጠይቆት 3 ኮምፒውተሮች ነበሩ እንደዚሁም ጠረጴዛ አለ ምናምን በማለት ጠቅሰዋል ?
- ✓ አዎ
- ✓ የምን ቢሮ ነው እርስዎ ከተረዱት ያ ቢሮ?
- ✓ አሁን ቢሮ ማለት ቢሮን አላስታውስም ግን ግቡ ስንባል ብቻ ነው የገባነው እዛ ክፍል ቁጥር ውስጥ ማለት ነው ስለዚህ ቢሮ የምን እንደሆነ አላውቀውም እኔ አሁን አላስታውስም እሱ የምን እንደሆነ ግን ያው እንደታዛቢነት ነው እዛው እንድንገባ የተደረገው
- ✓ ግልጽ ነው ጥያቄውን እኮ አልሰሙንም ያ ቢሮ እቃ ማስቀመጫ ወይ ኤግዚቢት ክፍል ነው ወይስ መደበኛ ቢሮ ነው ወይስ ሌላ የእስር ክፍል ነው ምንድን ነው ያ ቢሮ እርስዎ እንደተረዱት?
- ✓ መደበኛ ቢሮ ነው
- ✓ መደበኛ ስራ የሚካሄድበት ቢሮ ነው?
- ✓ አዎ
- ✓ ይሄን በምራ እንትን አሉ?
- ✓ ማለት ያው ካየኋቸው መሣሪያዎች
- ✓ ምን ምን አለ ሌላ ቢሮው ውስጥ እናንት ቅድም ከገለፁት ነገሮች ውጪ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔም እንትን ያልኩት የለም
- በሁሉም ላይ ፈርመዋል እርሶ ?
- አዎ ሁሉም ላይ ፈርሚአለሁ
- ወረቀቱ በሚወጣበት ጊዜ በማስረጃነት የሚቀርብበት ስለመሆኑ አልተነገረውም አይደል ?
- አይ እራሱ ምንም የተጠረጠረው ነገር የለም እንደውም አንዳንድ ግልፅ ያልሆነ ነገር እንደውም መልሶ እራሱ እያነበበ እራሱ የሚፈርምበት ሁኔታ አለ እያነበበ
- እኮ ፖሊሱ ወይም ያ የስራ ባልደረባ ያሉት እዚያ እሱን አጠገቡ የነበረው ሰው ይሄ ሰነድ በማስረጃነት ይቀርብብሀል ብሎ አልነገረውም አይደል ?
- አይ ምንም የተናገረው ነገር የለም ቀጥታ በቃ ያለውን ሂደት ያው እኛ እያለን የተነጋገሩት ነገር ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ነው ሌላ ነገር
- አቶ የሱፍ ከየት እንደመጣ አያውቁም አይደል ?
- አላውቀውም
- ከእዚያ በኋላም ወዴት እንደተመለሰ አያውቁም ?
- አላውቅም  እኛ ያው ወጣን /ግልፅ ያልሆነ/
- አቶ የሱፍን እርሶ እዚያ ከማየትዎ ውጪ አያውቁትም አይደል ?
- አላውቀውም
- ሰነዶቹ ላይ እንድትፈርሙ ሲደረግ ለእርሶም ሰነዶቹ አልተነበቡሎትም አይደል ?
- ለእኔ በቃ ሰነዶቹ እሱ የፈረመባቸው ለእኛ ፈረምን መጨረሻ ላይ
- እኮ አልተነበበላችሁም ለሁላችሁም ?
- አልተነበበልንም
- ከሀርድ ዲስኩ እና ከኮምፒዩተሩ ላይ ከታተመው ውጪ ሌላ ምንም ያያችሁት ነገር የለም አይደለም ?
- አዎ ሌላ ያየነው ነገር የለም
- በሌላም ሰነድ ከሌላ ሰነድ ላይም አልፈረማችሁም ?
- አልፈረምንም ያው እራሱ በፈረመበት ወረቀት ላይ ብቻ ነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ መቼ ነው ያነገሩን?
- ✓ ሐሙስ ቀን
- ✓ የወሩ ስንተኛ ቀን ነው ወሩን እንደዚሁም አመተምሬቱን?
- ✓ በ12/11/2004
- ✓ ስንት ሰዓት አካባቢ ነው?
- ✓ ከ4 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት
- ✓ የት  አካባቢ ነው ?
- ✓ ወረዳ 6 ኮንዶሚኒየም
- ✓ ክ/ከተማው የት ነው?
- ✓ ኮልፌ ቀራንዮ
- ✓ ምን ኮንዶሚኒየም ነው?
- ✓ ጂቲዜድ ቀራንዮ 1
- ✓ እሺ አሁን ወደጠቀሱት ቤት በምን አግባብ ነው የሄዱት እርስዎ ?
- ✓ እቃ ልገዛ አጋጣሚ ወጣሁት አጋጣሚ ስወጣ ያው የፖሊስ  አካል ክፍ/ቤት በሽብር አቶ አህመዲን ጀበል የሚል በትብብርነት ለማድረግ ትብብር እንዲያደርጉልኝ ጠየቁኝ የፍ/ቤት ትእዛዝ ከነቀኑ አሳዩኝ የፍ/ቤቱን ሕግ አክብሬ ተከትዬ ገባሁ
- ✓ የምን ትብብር አድርጉ ነው የተባሉት ምን በማድረግ ነው የሚተባበሩት እርስዎ?
- ✓ ታዛቢ
- ✓ ከዛ ወዴት ሄዱ?
- ✓ ቀጥታ የአቶ ጀብል ሚስት በሩን ከፍተው ቀጥታ እሳቸው ከገቡ በኋላ እኛ ገባን
- ✓ ብሎኩን ያስታውሱታል ብሎክ ቁጥሩን ከዛ የቤቱን?
- ✓ ብሎክ 16 የቤት ቁጥር 431
- ✓ እሺ ቅድም አሁን የማን ባለቤት ነው ያሉት?
- ✓ የአህመዲን ጀበል
- ✓ በምን አወቁ የእሳቸው ባለቤት መሆናቸውን?
- ✓ ያው የአህመዲን ጀበል ባለቤት ቅድደያ እንዲከፍቱ በሩን ከፍተው እንዲገቡ ሲታዘዙ
- ✓ እሳቸው ምን አሉ ማን ነው ስማቸው?
- ✓ ዘቢባ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ/የአህመዲን ጀበል ባለቤት ነኝ ብለው ነው እሳቸው ወይስ እንዴት ነው ያወቁት ይሄን እ/ርስዎ?
- ✓ አዎ ባለቤት ነኝ
- ✓ እሺ. ከዛስ የማንን ቤት ነው የከፈቱት?
- ✓ የአቶ አህመድ ጀበልን ቤት .
- ✓ ከዛ በፊት ያ ቤት የአቶ አህመዲን መሆኑን ያውቃሉ ወይስ እንደ. አወቁ አሁን የአቶ አህመዲን ቤት ሲሉን ማለት ነው ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ በምን አወቁ የዛን ቀን የእሳቸው ቤት መሆኑን ?
- ✓ እቃ ልገዛ ወጥቼ
- ✓ የዛን ቀን እዛ ቦታ ደረሱ አሁን ብሎክ 16 ብለው የቤት ቁጥሩንም ገልፀውልናል?
- ✓ አዎ
- ✓ ከዛ በፊት ያ ቤት የአቶ አህመዲን መሆኑን ያውቃሉ ወይስ እንደት አወቁ አሁን የአቶ አህመዲን ቤት ሲሉን ማለት ነው?
- ✓ አላውቅም
- ✓ በምን አወቁ የዛን ቀን የእሳቸው ቤት መሆኑን?
- ✓ እቃ ልገዛ ወጥቼ
- ✓ የዛን ቀን እዛ ቦታ ደረሱ ?
- ✓ አዎ
- ✓ አሁን ብሎክ 16 ብለው የቤት ቁጥሩንም ገልፀውልናል ይሄ ቤት የአቶ አህመዲን ነው ብለውናል ?
- ✓ አዎ
- ✓ በምን አወቁ ያ ቤት የአቶ አህመዲን ስለመሆኑ
- ✓ በፍ/ቤት ማዘገቢ ውስጥ አይቼ
- ✓ የቤት ቁጥር አለው?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ. ከዛስ?
- ✓ ባለቤቱ ከፍተው ገቡ ከዛ እኛ ተከትለን ገባን ከዛ በኋላ እየፈተሹ እኛ ቆመን የሚደረገውን በማየት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ይሄን የፍ/ቤት ትእዛዝ እርስዎ አይተውታል?
- ✓ አዎ አይቻለሁ
- ✓ የመዝገብ ቁጥሩን ያስታውሳሉ ?
- ✓ አዎ አስታውሳለሁ ልንገርዎት
- ✓ ይችላሉ ለፍ/ቤቱ ይንገሩ ?
- ✓ 102991
- ✓ እሺ. ምን ምንድን ነው ከዛ ቤት ፖሊስ በብርበራ ምን ምን ይውሰድ የሚል ትእዛዝ ነው ያለው?
- ✓ በሽብርተኝነት ምክንያት ስለሚጠረጠሩ በቤት ውስጥ የሚገኘውን እሱን እየወጣ በማየት ያው ቆመን አይተን የተገኘውን አይተናል
- ✓ ምን ምን ተገኘ?
- ✓ ሲዲዎች ፍላሽ ላፕቶርፕ
- ✓ ስንት ሲዲዎች ተገኙ ቁጥራቸውን ያስታውሳሉ?
- ✓ አላስታውስም
- ✓ እሺ. መጠናቸውስ አነስተኛ ብዙ?
- ✓ ብዛት አለው
- ✓ በግምት ምን ያህል ይሆናል ሲዲው?
- ✓ ዘጠና ቤቶች
- ✓ እሺ?
- ✓ የተሳሳተ እምነት አትከተል የመለስ አምልኮ የሚል ትራክ ማህተም
- ✓ ምን አሉን?
- ✓ ማህተም
- ✓ ምን የሚል ማህተም ?
- ✓ ማለት ማህተም የራሱ የቻለ ማህተም የሚሰራበት ተባራሪ ወረቀቶች
- ✓ ምንድን ነው ይዘታቸው ወረቀቶቹን ያነባሉ እርስዎ ማንበብ መፃፍ ይችላሉ ?
- ✓ እኔ አነባለሁ አላነበብኩትም ተባራሪውን መጽሃፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳን አይቻለሁ ቁርአኖች አይቻለሁ
- ✓ እሺ. ፖሊስ ምን ምን ወሰደ ከነዚህ እቃዎች ውስጥ ምን ምን ወሰደ?
- ✓ ቁርአን ይዞ ወጣ መጽሄት ሲዲ ላፕቶፕ ፍላሽ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ፣ ላፕቶፕ ሲ.ዲ. ፍላሽ የእምነት ሞባይል ስንት ሞባይል ወሰደ?
- ✓ አራት ሞባይል ኖኪያ
- ✓ እሺ፣ ሌላስ የተለያዩ መጽሔቶች ብለዋል የመጽሔቶቹን አርእስት ያስታውሳሉ ?
- ✓ አላስታውስም
- ✓ ምን እንደሚል አላዩም?
- ✓ አላየሁም
- ✓ ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ተደረገ ብርበራው ?
- ✓ ከአራት ሰዓት እስከ ስድስት ሰዓት
- ✓ እሺ. ከዛስ እናንተ ምን አደረጋችሁ እነዛ እቃዎች ስለመገኘታቸው መታዘባችሁን በምን አረጋገጣችሁ ?
- ✓ በፊርማችን አረጋግጠናል
- ✓ ምን ላይ ፈረማችሁ?
- ✓ በተገኙ እቃዎች ማቴሪያሎች ላይ ፊርመን ወጣን ከዛ የአቶ ጀበል ሚስት ከቤት የተገኘ እያለ ብለው ፊርመው አብረን በዛ ወረቀት በአንድ ወረቀቶች ላይ በተገኙ ላይ ሁሉም
- ✓ እሺ. ስለተከሳሹ ምን ተባለ ማለት ተከሳሹ ለምን በቦታው ላይእንዳልተገኘ ያውቃሉ እርስዎ ?
- ✓ እ?
- ✓ ተከሳሽ አሁን ስሙን የጠቀሱት አቶ አህመዲን ጀበል ለምን በቦታ ላይ እንዳልተገኘ ያውቃሉ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ ፖሊሶቹስ ባለቤታቸው በማለት የጠቀሷቸው ሰው ወይንም ወ/ሮ ዘቢባን አልጠየቁም ስለዚህ ጉዳይ?
- ✓ ተጠይቀዋል አላውቅም አሉ
- ✓ ምን ብለው ጠየቁ ፖሊሶች?
- ✓ የት እንዳለ ጠቁሚ አለውቅም የት
- ✓ እንዲጠሩስ ያደረጉት ጥረት የለም ተከሳሹ እንዲመጣ ወደቦታው እንዲመጡ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ እሺ. ይበቃናል
- ✓ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ምስክር፡ እርስዎ በታዛቢነት ገብተው የትጋ ነበረ የቆሙት ቤት ውስጥ ማለት የትጋ ነበሩ?
- ✓ በሚገኝበት ቦታ
- ✓ አቤት?
- ✓ እቃው በሚፈተሽበት ቦታ ላይ
- ✓ አሁን የምትመልሺው የት ቦታ ነው የቆምሽው ምናምን ሲባል ቤት አለ ውስጥ ስለዚህ ቤት ውስጥ ወይ ክፍልፍሎች አሉ የተከፋፈሉ ክፍሎች አሉ አልያም ደግሞ ሳሎን አለ የት ቦታ ላይ ነው እሱን ነው?
- ✓ ሳሎን ላይ
- ✓ ምክንያቱም የተገኘበትን ቦታ እኛ አናውቅም እንድታሳይን ነው
- ✓ ስለዚህ እርስዎ ቤት ውስጥ ገቡና የትጋ ሆኑ?
- ✓ ሳሎን
- ✓ ሳሎን ቁጭ አሉ ወይስ ቆሙ?
- ✓ ቆሜያለሁ
- ✓ ፖሊሶቹስ ከዛ የት ሄዱ ማለት የሚበረብሩት?
- ✓ የበረበሩት ያው እየበረበሩ ሳሎን ጨረሱ ከሳሎን ወደ ጓዳ ገቡ
- ✓ እሺ እርስዎ ሳሎን ሆነው እነሱ ወደጓዳ ገቡ ከዛ ጨርሰው ወጡ?
- ✓ እኔም ተከትዬ ጓዳ ገባሁ
- ✓ እሺ ከጓዳ በኋላ የት ሄዱ?
- ✓ አቤት
- ✓ ሳሎን በረበሩ ጓዳ ገቡ በቃ አለቀ ወጡ ከዛ?
- ✓ ጓዳ ተበረበረ አልጋ ተነሳ ቁምሳጥን ተፈተሸ
- ✓ /የማይሰማ/
- ✓ መኝታ ቤት
- ✓ እሺ ከእርስዎጋ ሌላ ታዛቢ ነበረ እንዴ?
- ✓ አዎ
- ✓ ማን ነው የመጀመሪያ ስሙን ብቻ?
- ✓ ናዝሬት
- ✓ እርስዎ የዛ አካባቢ ነዋሪ ኖት?
- ✓ አዎ ነዋሪ ነኝ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ቅድም የአቶ አህመዲን ባለቤት ከውስጥ ነበሩ ወይስ ከውጪ መጥተው ነው የከፈተት?
- ✓ ከውጪ
- ✓ ማለት እናንተ አሁን ታዘቡልን ተብላችሁ ተጠራችሁ ወደቤት ስትሄዱ ሴትየዋ በር ላይ ነው የጠበቀችው ?
- ✓ ይደገም
- ✓ የአቶ አህመዲን ባለቤት የቤቱ በር ላይ ጠብቀው ነው ወይስ ተጠርተው መጥተው ነው ?
- ✓ ከግባታቸው በፊት
- ✓ አዎ ለእናንተ የከፈተቱት?
- ✓ ወጪ ተብቀውን
- ✓ እሺ ወይንሸት ታዛቢ እንድትሆኚ የተነገረሽ የት ቦታ ላይ ነው?
- ✓ ከቤቴ ወደ ሱቅ እየወጣሁ ሱቁጋ እየደረስኩ እያለ አጋጣሚ የአቶ ጀበል አካባቢ ነው ሱቁ እዛ አካባቢ ፖሊሶች ቆመው ነበር ሲያገኙኝ ጊዜ የፍ/ቤት ማዘዣ አሳዩኝ እንዲህ እንዲህ ትተባበሪኛለሽ ወይ ሲሉኝ የፍ/ቤቱን ማዘዣ አይቼ
- ✓ ስለዚህ ሱቁጋ ነው የተነገሮት የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አነበቡሎት ወይስ እርስዎ እራሶ አነበቡት?
- ✓ እራሴ አነበብኩት ?
- ✓ እራሴ አነበብኩት
- ✓ ምንድን ነው የሚለው እስቲ ዝርዝሩን እስቲ የሚያስታውሱትን ?
- ✓ በሽብርተኝነት ምክንያት ሊጠረጠሩ ስለተቻለ በቤት ብርበራ እንዲደረግ
- ✓ እሺ እርስዎ አቶ አህመዲንን ከዛ በፊትም ከዛ በኋላም አያውቋቸውም አደል?
- ✓ ይደገም
- ✓ አቶ አህመዲን ጀበልን ከዛ ቀን በፊትም ከዛ ቀን በኋላም አያውቋቸውም አደል ?
- ✓ እስቲ ቆይ ይሄንን በግልጽ አላውቃቸውም ብለዋል ሲመጡም አላውቅም ብለዋል ምናልባት ከሱ ተነስታችሁ የምታነሱት መስቀለኛ ጥያቄ ካለ ያው የመጀመሪያ ዋና ጥያቄ እየተደገመ ስለሆነ ነው
- ✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ከዛ በኋላ ወደሚፈተሸው ቤት የአቶ አህመዲን ቤት ይፈተሸነው የሚለው የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሄዳችሁ እንዲታይ የተደረገው ቤት የአቶ አህመዲን ቤት ስለመሆኑ ፖሊሶቹ ያደረጉት ማጣራት የለም አደል ?
- ✓ ይደገምልኝ
- ✓ ይፈተሽ የተባለው ቤት ቅድም ቁጥሩን የገለፁት ቤት አለ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ
- ✓ ያ ቤት የአቶ አህመዲን ቤት ስለመሆኑ የተደረገ ማጣራት የለም አደል?
- ✓ የለም
- ✓ እሺ. ከዛ ቤቱም ከደረሳችሁ በኋላ ቤቱን የከፈቱት ሴት የአቶ አህመዲን ባለቤት ናቸው የተባሉት ከውጭ ነው መጥተው የከፈቱት ብለዋል ?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ. የአቶ አህመዲን ባለቤት ለመሆናቸው የተደረገ ማጣራት የለም አደለም?
- ✓ አለውቅም
- ✓ እሺ. ቤቱ ክፈቱ ተብሎ ተከፍቶ ሲገቡ እሳቸው በዛ በታዘዙት መሰረት ከፍተው ብቻ ነው ያስገቧችሁ አደል?
- ✓ አዎ
- ✓ ስትገቡ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ለእሳቸው አልተሰጣቸውም አደል?
- ✓ አልተሰጣቸውም
- ✓ አልተነበበላቸውም ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ እሺ. ከዛ በኋላ ቤቱ ተፈትሾ የተገኘው እቃ ቅድም የገለጿቸው ዝርዝር በአንድ ወረቀት ላይ ነው የተፃፈው ወይንስ በየ እቃዎቹ ላይ ነው እናንተ ከዛ ቤት የተገኘ ስመሆኑ እየፈረማችሁ ያረጋገጣችሁት?
- ✓ በየእቃዎቹ ላይ
- ✓ የእቃዎቹ ዝርዝር የተፃፈበት ሌላ ወረቀት ላይ አልፈረማችሁም አደል?
- ✓ ይደገምልኝ
- ✓ የእቃዎቹ ዝርዝር የተፃፈበት ሌላ ዝርዝረ ወረቀት ላይ አልፈረማችሁም አደል?
- ✓ ወረቀቶች ላይ ነው የፈረምነው
- ✓ እዛው ወረቀቶቹ ላይ ብቻ ነው የፈረማችሁት?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ. ከዛ በኋላ እናንተ ስትወጡ እቃዎቹን ፖሊሶቹ ጭነዋቸው ወጡ?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ. ከዛን በኋላ የአቶ አህመዲን ባለቤት ነኝ ያሉት ሴትስ አብረዋችሁ ወጡ?
- ✓ አልወጡም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሳቸው እዛው ቀሩ?
- ✓ አዎ
- ✓ ከዛ በኋላ የሆነውን አያውቁም ?
- ✓ እ
- ✓ ከዛ በኋላ ምን እንደሆነ እዛ ቤት ላይ አያውቁም አደል?
- ✓ ይደገምልኝ
- ✓ ከዛ በኋላ እዛ ቤት ላይ የሆነውን ነገር ምንም አያውቁም እርስዎ አደል?
- ✓ አላውቅም
- ✓ ምስክር ፖሊሶቹ ሲገቡ ምን ምን ነገር ይዘው ነበር?
- ✓ የማዘገር ወረቀት
- ✓ ሌላስ እነ ቪዲዮ እንደዚህ ካሜራ ነገር ?
- ✓ አዎ
- ✓ ምን ቦርሳ ነገር ይዘዋል ?
- ✓ አዎ
- ✓ በቦርሳ ይዘውት የገቡትን ነገር ፍተሻ ሲያደርጉ አብረው ይዘውት ይዞሩ ነበር?
- ✓ አዎ
- ✓ ወይንሸት ሃሙስ ስንት ሰዓት ላይ ነው ገባን ያልሽው?
- ✓ ሃሙስ ከ4 እስከ 6 ሰዓት
- ✓ የተፈተሸው ማለት ነው?
- ✓ አዎ
- ✓ ስንት ይሆናሉ ብዛታቸው ፖሊሶቹ?
- ✓ ብዛታቸውን አላስናትውስም
- ✓ ብዙ ናቸው ትንሽ ናቸው በመጠን አሰር አስራአምስት ሃያ ሰባት በግምት ?
- ✓ ከ10 ያልፋሉ
- ✓ አብራችሁ ሄዳችሁ ከነሱ ጋር?
- ✓ ወደት
- ✓ ማለት እቃ ልገዛ ወጥቼ አገኝቻቸው ሄድኩኝ ነው ያልሽኝ ?
- ✓ አዎ
- ✓ እዛው አካባቢ ነሽ አንቺ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ
- ✓ ምዲር ላይ ነው ፎቅ ላይ ነው ?
- ✓ የእሳቸው 1ኛ ፎቅ ላይ
- ✓ ሃሙስ 12 ሰዓት አደለም እንዴ ፍተሻ የጀመሩት እነሱ ?
- ✓ አራት ሰዓት
- ✓ ጠዋት አራት ሰዓት?
- ✓ አዎ
- ✓ ስድስት ሰዓት ላይ አንቺ ጨርሰሽ ወጣሽ ወይስ ፖሊሶቹ ይውጡ አይውጡ የምታውቂው ነገር አለሽ?
- ✓ እ
- ✓ አንቺ የራስሽን ፈርመሽ ሄድሽ ወይስ እዛው ቆየሽ ከነሱ ጋር ?
- ✓ ጨርሰን ከነሱ ጋር አብረን ነው የወጣነው
- ✓ አብራችሁ ወጥታችሁ ሄዳችሁ ?
- ✓ አዎ
- ✓ ፖሊሶቹም አብረዉ ወጥተው ሄዱ?
- ✓ አብረን በቃ እሳቸው እቃዎቻቸውን ይዘው ወጡ እፀው ተከትለን ወጣን ከዛ እቃቹ መና ላይ ተጫነ እቃዬን ገዝቼ ወደቤቴ ገባሁ
- ✓ ፖሊሶቹ ከዛን በኋላ እዛ ቤት ይቆዩ አይቆዩ የምታውቂው ነገር አለሽ ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ ቤት ውስጥ ሕፃናት ነበሩ?
- ✓ አዎ
- ✓ ያለቅሱ ነበር?
- ✓ ሕፃን ልጅ አለች
- ✓ ታለቅስ ነበር?
- ✓ አዎ ታለቅስ ነበር
- ✓ እሺ ግለሰቦች ሲመጡ ሞባይላቸውን እየተቀበሉ ዉስጥ ያስገቧቸው ነበር ፖሊሶቹ?
- ✓ እ
- ✓ ለምሳሌ አሁን ሚስጡ ያልሻት ሌላ አንድ ሴቶች አብረው አልነበሩም ?
- ✓ አለች ፖሊሶቹ ተቀበሏቸው ሞባይላቸውን አልተቀበሏቸውም ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አላስታውሰም
- ✓ ኖኪያ ሞባይሎች ተገኝተዋል ያልሻቸዉ ከነሱ የተቀበሏቸው ናቸው?
- ✓ ከቤተሰብ የተገኘ
- ✓ ወይንሸት ቅድም ስትናገሪ አህመዲን ጀበል ቤት የወሰዱሽ ፖሊሶች ናቸው አይደል?
- ✓ አዎ
- ✓ ሚስቱም ዘቢባ ነች ይቺ ነች ብለው ያሳዩሽ ፖሊሶች ናቸው?
- ✓ አይደለም
- ✓ እ ታውቂያት ነበረ አንቺ ከዛ በፊት?
- ✓ አላውቅም ሲጠየቁ ሚስት እንደሆኑ ገለፁ ሲፈርሙ ጊዜ በተገኙ እቃዎት ላይ ባለቤት የተገኘ እቃ የባለቤቱ ብላ በመፈረሟ ነው
- ✓ አዎ ይሄን ፖሊሶች ስላሏት የፈረመችው አንቺ ግን በግል ያረጋገጥሽው ነገር አለ ከዛ በኋላ ሚስት ስለመሆኗ የአንቺን ነው የጠየቅኩት ?
- ✓ አዎ
- ✓ ከዛ ወዲያ ያረጋገጥሽው ነገር አለ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ ቤቱንም ከዛ ወዲህ የሱ ይሁን አይሁን የምታውቂው ነገር የለም?
- ✓ ተከራይ ነው
- ✓ እኮ የምታውቂው ነገር የለም አንቺ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ የዛን ቀን ስትሄዱ ማለት ነው የብርበራ ትእዛዝ ላይ ቅድም የተናገሩት 1991 በሚለው መዝገብ ላይ የፍ/ቤት ትእዛዝ ምን እንዲያዝ ነው የተሰጠው ወረቀት ነው መሣሪያ ነው ምን እንዲያዝ ነው የተሰጠው ካስታወሱ ማለት ነው ?
- ✓ እሱ ተጠይቋል እኮ ቅድም ተጠይቆ ምላሽ ተሰጥቶበታል
- ✓ /ግልጽ ያልሆነ/
- ✓ እኮ ትእዛዙ ምን ምን የሚባል ነው ሲባል መልሰው አልፈዋል አሁን ድጋሚ ወይ ጠይቁ
- ✓ እሺ አህመዲን ሸጀቀል ቤት አራት ኖኪያዎች ተያዙ ብለሽ ነበር ላፕቶፕሳ ምን አይነት ነበር የተያዘው ?
- ✓ ይደገም
- ✓ የተያዘው ላፕቶች ምን ነበረ ማርኩ ?



2458 906

http://ethcriminalawnetwork.com/
ECLN

- ✓ አላውቅም
- ✓ አይተውታል ማነን
- ✓ አዎ
- ✓ ትናንትም አቃቤ ሕግ ሲጠይቆት የአህመዲን ጀበል ቤት መሆኑን ያወቁበት በቅድሚያ በሩን ከፍተው እንዲገቡ ሲታዘዙ ነው የአህመዲን ጀበል ባለቤት በቅድሚያ በሩን ከፍተው እንዲገቡ ሲታዘዙ ነው ብለዋል አደል ?
- ✓ አዎ
- ✓ አብራችሁ ከውጭ መጥታችሁ ነው እሳቸው በሩን ከፍተው እንዲገቡ የታዘዙት ?
- ✓ ማን
- ✓ የአህመዲን ጀበል ባለቤት
- ✓ ይሄ ተጠይቋል ከዚህ ቀጥሎ የምትጠይቁት ካለ ጠይቁ ይሄ ተጠይቋል ቤቱ አካባቢ ነበረች ከፍታ ገባች አብረን ገባን ነው ያሉት
- ✓ ባለቤቱ ፊቷን አይተሻል ?
- ✓ አቤት
- ✓ ባለቤቱን ፊት አየሽ?
- ✓ ምኗን?
- ✓ ፊቷን አይተሻል ወይ?
- ✓ አላየሁም ተሸፍናለች
- ✓ ከውጭ ሁላችሁም ባለቤቱም አንቺም ፖሊሶችም ከውጭ ነው ወደቤት የገባችሁት ?
- ✓ አዎ
- ✓ ቅድሚያ የከፈተችው እሷ ነች ?
- ✓ ባለቤታቸው
- ✓ ዝግ ነበረ ከዛ በፊት?
- ✓ አዎ
- ✓ ከዛ በፊት ሰው ወይም ፖሊስ ይግባ አይግባ የምታውቂው ነገር አለ ?
- ✓ አውቅም
- ✓ ያ ብርበራ ከመደረጉ በፊት ሌላ ፖሊስ ይግባ አይግባ የምታውቂው ነገር አለ ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ ጨርሰናል



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ጠይንሽቅ
- ✓ አቤት
- ✓ እዛው አካባቢ ነው ያለሽው?
- ✓ በቃ ስንቴ ተደጋገመ
- ✓ እሺ አይ ስላስማሁ ምናልባት
- ✓ በቃ ሌላ ካለሽ
- ✓ እኮ ከሱ ተነስቼ ጥያቄ ልጠይቅ
- ✓ ከዚህ ተነስተሽ የምትጠይቂው ካለ ይሄ ተጠይቋል
- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ ይሄ ተጠይቆ ተመልሷል አሬዲ ስንቴ ስለዚህ እዚህ ላይ አንደግምም
- ✓ እሺ ፖሊሶቹ ከሃሙስ እስከ ሰኞ እዛው አካባቢ ከሆንሽ ቤቱ በፖሊስ ተከቦ እዛው ቤቱ ውስጥ መሆኑን ታውቂያለሽ አንቺ?
- ✓ አላውቅም
- ✓ እዛው አካባቢ ነሽ ግን?
- ✓ ትሰሚያለሽ አደል ብይን
- ✓ እሺ ጨርሰናል
- ✓ እሺ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ አቃቤ ሕግ
- ✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ወይንሸት
- ✓ አቤት ፖሊሱ መጀመሪያ ላይ ለብርበራ ታዛቢነት ተባበሪን በማለት ነግሮኝ ወደ ቤቱ ይዞኝ ሄደ ብለሻል በር ላይ ስትደርሱ ከንቺ ውጭ ሌላ ታዛቢ ነበር አደል?
- ✓ አዎ ነበረ
- ✓ እሺ እዛጋ ትእዛዙ አልተነበበላችሁም ምንዴ ?
- ✓ ስንገባ አንብበነዋል እያንዳንዳችን
- ✓ በሩ ላይ ሁላችሁም አንብባችሁታል?
- ✓ በሩ ላይ ሳንደርስ መጀመሪያ ሲያዙን ጊዜ መልእክቱ የፍ/ቤት ነው ሲሉን ማንበብ አለብን ብለን ስናነበው ነው
- ✓ እዛ ቦታ ላይ በሩ ላይ ከደረሳችሁ በኋላ ትእዛዙ ለባለቤታቸው አልተነበበም ወይም እንዲያነቡት አልተደረገም?
- ✓ አላውቅም



460

908

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ ባለቤታቸው ከፖሊሶቹ ጋ ነበሩ ወይስ ለብቻቸው ነበሩ ቦታው ላይ ?
- ✓ ከፖሊሶቹ ጋ
- ✓ ክፈቺ ሲሏት ምን ለማድረግ ነው ነው ያሉት ክፈቺ በሩን ሲሏት እሷ ናት የከፈተችው ብለዋል ለምን አላማ ነበረ የከፈተችው ?
- ✓ እኛ ስንመጣ ጊዜ ክፈቱ ነው
- ✓ የፍ/ቤት ያሉት ነገር አለ በምንድን ነው የከፈቱት ፍ/ቤቱ ምን ስላለ ?
- ✓ ከዛ በፊት የማውቀው ነገር የለም ከፍታ ስትገባ ብቻ ነው ያየሁት
- ✓ እርስዎ ከደረሱ በኋላ?
- ✓ አዎ
- ✓ ውስጥ ገብታችሁስ ብርበራ ከመጀመሩ በፊት የፍ/ቤት ትእዛዙ ምን ምን መያያዝ እንዳለበት አልተገለፀላችሁም?
- ✓ አላውቅም
- ✓ እሺ ሌላው ሰነዱ ላይ ፊርመናል ብለሻል ምን ምን ነበረ የሚለው ሰነዱ ላይ እናንተ የያዛችሁበት ላይ ምን ምን ተገኘ የሚል ሰነድ ላይ ነው የፈረማችሁት?
- ✓ ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ ጥያቄውን እንተወዋለን
- ✓ ምን ላይ ነው ይሄ እንትን ብለን አርገን ነው የምንቀይረው እያንዳንዱ ወረቀት ላይ ፊርመናል ብላችኋል እስቲ ምን የሚል ወረቀት ላይ ነው የፈረማችሁት?
- ✓ የተገኙ እቃዎች የሚለው ነው እንዳለ አልወጣም እቃዎቹ ምክንያቱም መአት ናቸው እቃዎቹ የተገኙትም የተገኙትን እቅ ያው ከነባለቤቶት ባለቤቶ የፈረሙትን እኛም ፊርመናል
- ✓ ስንት ገጽ ላይ ነው?
- ✓ አላስታውስም
- ✓ በግምት ስንት ገጽ ይሆናል ?
- ✓ አላስታውስም
- ✓ እሺ ሌላው /ግልጽ ያለሆነ/
- ✓ አራት አምስት
- ✓ እሺ እዚህ ሰነድ ላይ የመጨረሻ ላይ የፈረማችሁበት ሰነድ ላይ የተከሳሽ ባለቤትም ፈርማለች አይደል?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ
- ✓ እንተም ፈርማችኋልና
- ✓ አዎ
- ✓ አንብባችሁታል ጉዳዩ ወረቀቱን?
- ✓ አላነበብኩም
- ✓ ፖሊሱን አላነበበላችሁም?
- ✓ አላስታውስም
- ✓ አላውቅም ማለት ያ ሰነድ
- ✓ አላስትውስም
- ✓ ምን እንደሚል አውቀሽ ነው ታዲያ የፈረምሽው ምንድን የሚል ወረቀት ነው ?
- ✓ እኔ
- ✓ እነዚህን ዝርዝሮች ይጠቅሳል ብለሻል አደል?
- ✓ አዎ
- ✓ በምን አወቅሽ እነዚህን መጥቀሱን?
- ✓ ያው በአይኔ ያየሁትን እቃዎችን ስም ዝርዝሮችን ያው በአይኔ ስላየሁኝ ሰነዶችም ላይ ያው የተመሳሳይ
- ✓ አሁን ስም ዝርዝሮቹ ብለሽናል እነዚህ ስም ዝርዝሮች እዛ ላይ ስለመኖሩ በምን አወቅሽ እምብበሽው ነው ተነቦልሽ ነው በምን አግባብ ?
- ✓ እቃዎቹን አይቻለሁ ለምሳሌ ሲዲዎች ላፕቶፕ ስልኮች ትራኮች
- ✓ እንደዚህ ይላል ይሄ አሁን የፈረሙበት ወረቀት?
- ✓ አዎ
- ✓ አንብበውታል ወረቀቱን ወይስ እንዴት አወቁ  እንደዚህ ማለቱን ?
- ✓ ዝም ብዬ ያው በተገኘው መሰረት
- ✓ እቃው ሲበረበር ነው ያዩት አደለም ?
- ✓ አዎ አይቻለሁ
- ✓ አዎ እነዚህ ደገሞ አራት ገጽ ወይንም አምስት ገጽ የሚሆን ወረቀት አለ ብለዋል እዚህ ወረቀት ላይ ፈርመዋል አደል?
- ✓ አዎ ፈርሚያለሁ



http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እሺ ይህ ወረቀት ላይ አሁን የተዘረዘሩት ነገሮች ስለመሟላታቸው በምን አውቀው እርስዎ ይሄ ነው ጥያቄው?

✓ አላውቅም

✓ እየዘረዘርሽ ነው ከዘረዘርሽ በኋላም በወረቀት ላይ ብለሻል እሱን አይቻ ነው የፈረምኩት አልሽ ስለዚህ እንዴት ነው ያ አንብበሽ ነው ሰው አንብቦልሽ ነው ወይ ወረቀት እንዴት መጀመሪያ ያየሽው እቃ እዛው ወረቀት ላይ ስላለ ነው የፈረምኩት ብለሻል እንዴት አወቅሽ ?

✓ በርባሪውን አካል እዛ ላይ አስፍሮታል

✓ እኮ ማስፈሩን አንብበሻል ወይ አንብበሻል ወይ ሌላ ሰው አንብቦልሻል ወይ ነው ጥያቄው ?

✓ አንብበውልኛል

✓ ስለዚህ ይሄ ሰነድ ሲነበብላችሁ በምን ምክንያት በተደረገ ብርበራ ነው የሚለው?

✓ አቤት

✓ በማን ትእዛዝ በተደረገ ብርበራ ነው የሚለው እነዛ ነገሮች ተገኙ የተባሉት ነገሮች የተገኙት እዛ ሰነድ ላይ ቃለ ጉባዔው ላይ በምን ትእዛዝ የተደረገ ብርበራ ነው የሚለው?

✓ በፍ/ቤት

✓ ይሄ የተነበበው ለእርስዎ ብቻ ነው ወይስ የተከሳሽ ባለቤትም አሉ እዛጋ?

✓ የተከሳሽ ባለቤትም አሉ

✓ እሳቸውን ሲነበብ ተነቦላቸዋል?

✓ አዎ

✓ ፈርመዋል እሳቸውም?

✓ አዎ

✓ እሺ ሌላው ሕፃናት ሲያለቅሱ ነበረ ብለዋል እና እነዛ ሕፃናት በምን አግባብ ምን ሆነው ነው የሚያለቅሱት?

✓ አላውቅም እሱን

✓ ቦታው ላይ እያለቀሱ ነበረ አደል ማለት የመታቸው ሰው ነበረ እንዴ?

✓ አይ የመታ ሰው የለም ዝም ብላ በመደናገጥ ነው

✓ በግምት የስንት ዓመት ሕፃን ትሆናለች?

✓ የ3 የሁለት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እሺ ሌላው ነገር ፖሊሶቹ እኛም ፖሊሶችም ግቢውን ከበረበሩ በኋላ ሄደናል ብለዋል ድጋሚ ደግሞ እኔ ከሄድኩ በኋላ ፖሊሶቹ ይቆዩ አይቆዩ የማውቀው ነገር የለም ብለዋል እስቲ ይሄን ነገር ግልጽ ያርጉት እንዴት ነው የሄዳችሁት ያ ብርበራ ከተጠናቀቀ በኋላ እንዴት ነው የሄዳችሁት?

✓ ብርበራው አለቀ ሰነዶች ላይ ፈረምን እቃዎቹን ቅድሚያ በርባሪ አካል ይዞ ወጣ እኛ ገብተን ወጣን በዛ እቃዬን ገዝቼ ወደ ቤቴ ሄድኩን

✓ የቀረ ፖሊስ ነበረ እንዴ በወቅቱ እዛ ቦታ ላይ ?

✓ የለም

✓ እሺ ሌላው ፖሊሶች ሲገቡ ቦርሶ ይዘው ነበረ በማለት ቅድም ገልፀዋል ቦርሳ ?

✓ አዎ

✓ በዛ ቦርሳ ውስጥ ምንድን ነበረ ይዘው የየነሩት?

✓ ካሜራ

✓ ምን ካሜራ?

✓ ቪዲዮ

✓ ባምን አወቁ ቦርሳው ሲከፈት ነው በምን አወቁ ያ ቪዲዮ ካሜራ መሆኑን እዛ ውስጥ?

✓ ካሜራውን እያወጡ እና እያስገቡ እያየን ነበር

✓ ካሜራውን ሲያወጡ አይተዋል?

✓ አዎ

✓ ምን አረጉበት ያን ካሜራ?

✓ ቀርፀውበት አለቃዎችም ቦታ ላይ አሲዘው ተቀረፀ

✓ ካሜራው ከወጣ በኋላ እዛ ቦርሳ ውስጥ የቀረ ሌላ እቃ ነበረ ?

✓ የለም

✓ ባዶ ነበረ ቦርሳው?

✓ አዎ

✓ እሺ. ፖሊሶቹ በየክፍሉ እየዞሩ ሲበረብሩ እርስዎ ሳሎን ነው የተቀመጡት አብረዋቸው ዞረዋል አደል?

✓ አብሬ ነው የሄድኩት

✓ እሺ. ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አቤ. በፍ/ቤቱ: ጥያቄ ካሜራውን ከመቼ ጀምሮ ነው መቅረጽ የጀመሩት ከተገናኛችሁ በኋላ ካሜራ ቀርፀዋል ብለዋል ከየት ጀመሩ ካሜራ ቀረፃ?
- ✓ ከቤቱ ያ እቃዎቹን የተገኙ እቃዎችን ቦታ ላይ ሳሎን ላይ ተደርድረው ያ እቃዎቹ ባሉበት ቦታ
- ✓ ሲቀረጽ ቦታው ብቻ ነው ሌላ ሰውም የተቀረፀ አለ ?
- ✓ አይ እቃው ነው
- ✓ እሺ እናመሰግናለን ጨርሰዋል መመለስ ይችላሉ ዛሬ የምናያት አንድ መዝገብ ስላለች ከዚህ በላም መጨረስ ስለማንችል ነገ በ3 ሰዓት እዚህ እንገናኛለን እንጀምራለን፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ በፊት ሌላም መዝገቦች ስላሉ እነሱንም እናያለን ለየት የሚያደርገው ከሌላው ቀን እሱ ነው ቀርቧል ተከሣሾች ?
- በተለመደው እንቀጥላለን

4ኛ ወ.ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

መጋቢት 26/2005 ዓ.ም

*ዳኞች፡- ብስራት ተልዕቁ*

*ባህሩ ዳርቻ*

*ቀናቴ ሆራ*

*ከሣሽ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወ/ማገኝ አቶ ቴዎድሮስ ጌታቸው ቀርበናል*

*ተከሣሽ፡- ተከሣሾች የቀረ ሰው አለ ከእናንተ ስንተኛ ነው ምን ሆነው ነው የቀሩት 3ኛ እና 6ኛ*

*አዲስ መሐመድ፣ ባህሩ መካንጋ፣ ሞላልኝ መለሰ፣ መሐመድ አብደላና ሀሰን ሁሴን ቀርበናል ስለ ከ28ኛ ተከሣሾች ሁላችንም የሁሉም ተከሣሾች*

- ዐቃቤ ሕግ 2 ተከሣሾች አልቀረቡም እነሱን በተመለከተ የመታነሱት ካለ 6ኛ እና 3ኛ ተከሣሾች አልቀረቡም ?
- ያው ባልቀረቡት ተከሣሾች ላይ የቀረቡትን ምስክሮችን አናሰማም በሌሎቹ ላይ እንድንቀጥል ነው የምናመለክተው
- በእዚሁ መሠረት እንቀጥላለን ከእዚያ በፊት ትላንት የቀረበው /ግልፅ ያልሆነ/ ሲዲ ማስረጃ አስቀድሞ ሊደርሰን ይገባል እሱን በተመለከተ የምናቀርበው ጥያቄ ለማቅረብ እንዲያመቸን እሱ አስቀድሞ ይድረሰን የሚል የተከሣሾች ጠበቆች አመልክተዋል በዐቃቤ ሕግ በኩል የተሰጠው ምላሽ ሲዲዎቹ ምናልባት ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ ለመፈፀም የሚያነሳሱ ሊሆኑ ይችላሉ ለሌላ ድርጊት ሊሆኑ ስለሚችሉ ሊደርሳቸው አይገባም የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል ፍ/ቤቱም



2466 914

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሲዲዎቹ አስቀድመው ሊደርሳቸው ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምሮታል ስለማስረጃ ለተከሣሽ መድረስ በግልፅ የተቀመጠ ሕግ የምናገኘው የኢፌድሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 4 ላይ ብቻ የተመለከተውን ነው ሌላ ስለ ማስረጃ በዝርዝር ለየት ይደርሳል ለማን ይደርሳል የሚለው ዝርዝር ሕግ አናገኝም እሱ ላይ የተመለከተው ሕግ የሚለው ተከሣሽ የቀረበ ተከሣሾች የቀረበባቸውን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት መብት አላቸው የሚል ነው ይሄ የመመልከት መብት ምን ማለት ነው የሚለውን ተያያዥነት ካላቸው ሕጎች ጋር ተመልክቷል የመመልከት መብት ማለት የፁሑፍ መተርጎም ያለበት የፁሑፍ ማስረጃ ከሆነ የፁሑፍ ማስረጃ ያው በግልፅ በችሎት ለማየት ምንም ጊዜ ስለማይፈቅድ ለተከራካሪ ግራ ቀኝ ወገኖች ደርሶ አስተያየት ሊሰጡበት ስለሚገባ የፁሑፍ ማስረጃ ከሆነ አስቀድሞ ሊደርሳቸው እንደሚገባ ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል ከእዚያ ውጪ ያሉ የኤሌክትሮኒክ ማስረጃዎች ውስጥ እንዴት ይሆናሉ የሚለውን ስንመለከት በተለይ ከኦዲዮ ቪዢዋል ጋር የተያዘ ሲዲዎች የያዙት ጋር የተያያዘ መሆን ያለበት ለግራ ቀኝ ለችሎቱም ሊቀርብ የሚችለው ችሎት ላይ ቀርቦ መታየት ነው ከእዚህ ያለፈ ይዞ ቤት ገብቶ የተለየ ነገር ከእሱ አያለሁ የሚለውን ፍ/ቤቱ ግንዛቤ አልወሰደም በሌላ በኩል ከተከሣሾቹ የመጠየቅ መብት ጋር የተያያዘ እንዴት ሊተረጎም ይገባል የሚለውን ስናይ በተለይ ከሲዲዎቹ ይዘት ጋር የሚገናኙ ምስክሮች ካሉ ዐቃቤ ሕግ ምስክሮቹን ወደ ኋላ እንዲያስቀር እና እነኚህ ምስክሮች ከእዚህ የሲዲውን ይዘት የሚመሰክሩ ከሆነ እነሱ ወደ ኋላ ቀርተው ሲዲዎቹን ካየን በኋላ ምስክሮቹን እንድንቀጥል ትዕዛዝ ተሰጥቷል ሌላው ዝርዝር ፁሑፉ በኋላ ከብይን በኋላ ማግኘት ይችላሉ አጠር ያለ መልኩ ይሄንን ነው የምንለው ስለዚህ አስቀድሞ በእዚህ ምክንያት አስቀድሞ ሊደርሳቸው አይገባም ሲዲው ሲቀርብ ችሎት ላይ ግራ ቀኙ ማየት ይችላሉ ተብሏል በእዚሁ መሠረት ቀሪውን የዐቃቤ ሕግ መስማት የዐቃቤ ሕግ ምስክር መስማት እንቀጥላለን

- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጣኸው ?
- አዎ
- ስምህን የአባትህን የአያትህን ሌላ ዝርዝር ውስጥ ሳትገባ የራስህን ስም ብቻ ትነግረናለህ
- መልካሙ
- ስንተኛ ናቸው ዐቃቤ ሕግ መልካሙ ዐቃቤ ሕግ 151 ላይ የተጠቀሱ ናቸው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይቅርታ የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት ፔጅ 30 ገፅ 30 ላይ ነው እና እሱን
- አዎ
- እዚያ ላይ መልካሙ
- እንግዲህ መልካሙ ያለው 151 ላይ አለ
- 151ኛ አዎ
- ሌላ መልካሙ
- በቃ
- 151
- አዎ 151
- እሺ በተሰሙ ዝርዝር ልክ ያው 62ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ 151 ላይ የተጠቀሱ ምስክር ናቸው አቶ መልካሙ በእነ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- በአህመዲን
- አህመድ ?
- አህመዲን
- አህመዲን ?
- አህመዲን
- አባቱስ ?
- የአባቱ ስም በወቅቱ አላስታውሰውም
- አህመዲን ነው የሚባለው ?
- አህመዲን የሚባል ነው
- የአባቱን ስም አያስታውሱም በመልክ ለይተው ያውቃሉ ?
- በመልክ አዎ
- ማሳየት ይችላሉ አሁን ?
- አዎ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተነስተው ያሳዩ እሺ. እሱ ነው አህመዲን ኖት ስንተኛ 2ኛ ምስክሩ 2ኛ ተከሣሽን—በቁም አሳይቷል የአባታቸውን ስም አላስታውስም ብሏል ከአህመዲን ጋር ዝምድና ወይ ጥላቻ አሎት?
- ዝምድና የለኝም ጎረቤቴ ነበር በእርግጥ አውቀዋለሁ
- የተጣላባችሁበት ጉዳይስ አለ ?
- ኧረ በምንም ዓይነት ጓደኛዬ ነው
- ጓደኛሞች ናችሁ ?
- አዎ ጎረቤት ነን በመልካም እንትን ነው የምንተዋወቀው
- ምን ፈፅመው ነው የተከሰሰው አጠር አድርጉ እና ምን ፈፀመ ተብሎ ነው ?
- እኔ በወቅቱ በእርግጥ በእዚያ አካባቢ የልማት ኮሚቴ ነበርኩኝ ስሄድ ፖሊሶች ነበሩ አባሉን በአህመዲን በአሸባሪ ስለምንጠረጥረው ብሎ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ወረቀት ይዘው አሳዩኝ ታዛቢ ሁንልን ብለው ሲያመጡኝ እዚያ አካባቢ ስለነበርኩኝ
- ታዛቢ ሆነው ነው ያዩት ?
- ታዛቢ ሆኜ ነው ማለት
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ ምስክር የመጡበትን ጉዳይ በዝርዝር ያስረዳሉ ከጊዜው ይጀምራሉ ጊዜውን ያስታውሳሉ ?
- አዎ አስታውሳለሁ
- መቼ ነው ?
- ሐምሌ 12 ሐሙስ ቀን ነው
- ሐምሌ 12 ስንት ዓ.ም ነው ?
- በ 2004 11ኛ ወር ላይ
- ስንት ሰዓት ነው ?
- 4 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ነው
- ከምሽቱ ነው ?
- ከጠዋቱ
- ከጠዋቱ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- የት ነው ክፍለ ከተማውን ያውቃሉ ?
- አዎ ኮልፌ ቀራንዮ ወረዳ 6 አካባቢ ወይራ ሰፈር በሚባል ኮንደሚኒየም ከብሎክ 16 የቤት ቁጥር 431 በሚባሉ 1ኛ ፎቅ ላይ
- ይሄ አሁን የጠቀሱት 431 ብሎክ 16 የማን ቤት ነው ?
- የአህመዲን ቤት ነው ተከራይቶት የሚኖር ቤት ማለት ነው
- ጥሩ እንዴት አወቁ እርሶ ?
- እኔ እዚያው ግቢ ውስጥ ነው የምኖረው አውቀዋለሁ በፊት ብሎክ 1 አካባቢ ነበር በብሎክ 1 ብሎክ 2 ነበር ከብሎክ 2 ወደ ብሎክ 16 መሄዱን አውቃለሁ ባለቤቱንም እሱንም አውቀዋለሁ
- አኬ ጥሩ እሺ አሁን በጠቀሱልኝ ቀን ጊዜ እና ቦታ ምን ሆነ እርሶ ምን እያደረጉ ነበር ?
- እኔ አካባቢ ልማት ኮሚቴ ነኝ ኮብል እስቶን አጋጣሚ ይነጠፍ ነበር ሰቤዝ ተነጥፎ ነበር መኪናዎች ገቡ ተብሎ ሲባል የፖሊስ መኪና እዚያ አካባቢ ገባ ሲባል ጥበቃዎች ሲጠሩኝ ስሄድ አጋጣሚ ፖሊስ ነው በእዚያም አጋጣሚ ነው እኔ በቦታው ልገኝ የቻልኩት
- ከእዚያ ምን አሉህ ፖሊሶቹ ስታገኛቸው ?
- ያው ፖሊሶቹ ለእንትን እንፈልግሀለን ለምንድን ነው እዚህ ጋር ሰቤዝ ነው ለምን /ግልፅ ያልሆነ/ ስላቸው አይ እኛ ለስራ ጉዳይ ነው እዚህ ጋር የምንጠረጥረው ሰው ስለነበር ለእዚህ ለእዚህ ነው አሉኝ አህመድ የሚባል በእዚህ በእዚህ ነው ሲሉኝ
- በምን በምን ?
- በአሸባሪ ስለምንጠረጥረው /ግልፅ ያልሆነ/ የፍ/ቤት ደብዳቤ አሳዩኝ ከእዚያ በኋላ
- አየኸው ደብዳቤውን አየኸው ?
- አዎ
- ምን ይላል ?
- ደብዳቤው ያው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ነው እንግዲህ ያለው ሁኔታ የፍ/ቤት ትዕዛዝ መሆኑን ከእዚያ ጋር አነበብኩ እና
- ስሙ ማን ይላል የተፃፈው ?
- አህመዲን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አህመዲን ይላል ?
- አዎ
- ቁጥሩን ታስታውሳለህ የእዚህን ደብዳቤ ?
- አላውቀውም
- መቼስ እንደተፃፈ ቀኑን ታስታውሳለህ ?
- ቀኑን አላስታውሰውም ምክንያቱም ረጅም ጊዜ ነው ማለት ይሄንን ያህል ልብ ብዬም /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚያስ ደብዳቤውን አሳዩህ ወዴት ሄድክ ?
- እዚያው ባለቤቱ ጋር በር ላይ ቆማ ነበረ
- የማን ?
- የአህመዲን ባለቤት
- እሺ ?
- ከእዚያ በሩን ከፈቺልን አሏት ለእሷም አሳዩላት አነበቡላት ከፈተች ገባን አንድ ላይ ገባን ፍተሻው እንዲካሄድ ተደረገ
- አህመዲን ይሄ ሁሉ ነገር ሲደረግ ነበር በቦታው ?
- አልነበሩም
- አልነበረም ?
- አዎ
- ባለቤቱ ፖሊሶቹ ካነበቡላት በኋላ የብርበራ ትዕዛዙን ምን አለች ?
- ምንም አላለችም ከፈተች ገባች ከእዚያ ተቀበለች
- ይቅርታ የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄው ተመልሷል ግን ምስክሩ ያላሉትን ነገር ዐቃቤ ሕግ የሚናገሩ ከሆነ ኋላ ለሪከርድም ለምርመራም ችግር ነው የሚሆነው ደግሞ በጣም መሠረታዊ የሆነውን ጉዳይ ነው ዐቃቤ ሕግ እራሳቸው መልሰው የተነሱት ፖሊሶቹ ለባለቤቱ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ካነበቡላት በኋላ ብለው ነው የጠየቁት ምስክሩ መጀመሪያ ይሄን ተነቧል የሚለውን ነገር አልመሰከረም እሱ ሳይል እሳቸው ይሄንን ከተናገሩት ችግር ነው የሚሆነው ደግሞ ይሄ ዋናው ጥያቄ ነው የሕገ መንግስታዊ ፕሮሲጀሩ ዋናው ጥያቄ ነው እሳቸው መልውት ከተጀመረ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ትክክል አይሆንም ስለዚህ ጥያቄው ሙሉ በሙሉ ለሰረዝ ይገባል ከእዚያ በኋላ ሊጠየቅ አይገባም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ ከሆነ ምስክሩ መስከሯል አልመሰከረም የሚለውን ነገር ሪከርዱን ያዳምጠው ይሄ መሠረታዊ ጉዳይ ስለሆነ ምስክሩ ከእዚህ በኋላ ይሄንን መመለስ የለባቸውም

- ያው ፍ/ቤትም ችሎቱም ሲከታተለው እንደነበረው ምስክሩ አሁን የተናገርኩትን ቀድመው ተናግረው ነው እንደገና መልሼ የጠየኳቸው እና ምናልባት የተከበሩ ጠበቃ እንዳሉት ወደ ኋላ ተመልሶ መስማት ይቻላል ፍ/ቤቱ
- ምናልባት እዚህ ከያዝነው ነገር ላይ የሚያሳየው ቀደም ብሎ ምስክሩ እሱ እንደተነበበለት በኋላም ለባለቤቱ ከሄዱ በኋላ እዚህ በር ላይ እንዳገኙት እና እንደተነበበ ገልፀዋል ምናልባት ከእዚህ የተለየ የምታነሱት ካለ ነው መጀመሪያ ገልፀዋል ከእሱ ቀጥሎ ዐቃቤ ሕግ ያነሳ መሆኑን ነው የእኛ እንትን የሚያሳየው የሚያነሱት ነገር ካለ /ግልፅ ያልሆነ/
- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ያልነው እሱ አንበቤአለሁ ብሏል ተሰጥቶት አንብቧል ምስክሩ ለራሱ አሁን ዐቃቤ ሕግ የጠየቁት የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለባለቤቱ ተነቦላታል ነው እና ተነቦላታል የሚለውን እሳቸው ተናግረው ነው የጠየቁት ካነበቡላት በኋላ ብለው ነው የጠየቁት ምስክሩ ግን ፖሊሶቹ ለባለቤቱ አነበቡላት ብሎ አልመሰከረም
- እኮ እሱን እሱን እንግዲህ ወይ እኛ የያዝነው /ግልፅ ያልሆነ/ ይመዘናል እኛ የያዝነው ነገር እንደዚያ ነው
- እሺ ምስክር ቅድም ስትመልስ ለእኔ ካነበቡልኝ በኋላ ወደ ቤቱ ሄድን ባለቤቱን በር ላይ አገኘናት ተነበበላት እና ቁልፉን ከፍታ አስገባችን ብለሀል አይደል ?
- አዎ
- በሩ ዝግ ነበር ማለት ነው ?
- በመጀመሪያ በእርግጥ ፖሊሶች ነው እዚያ አካባቢ የደረሱት እሷ ወጥታ ነው ማለትም እንግዲህ አወጣጧን እንዴት እንደሆነ መጀመሪያ አንኳኩተውላት ወጥታ ሊሆን ይችላል ግን ውጪ ላይ እንደነበረች ነው እኔ የማውቀው ከእዚያ በኋላ ነው እንግዲህ ያለውን ነገር እኛ ፍተሻ ልናካሂድ ነው አቶ አህመዲንን ጥርጣሬ ላይ በአሸባሪ ጠርጥረናቸው ስለነበረ በፍ/ቤት ትዕዛዝ ነው የመጣነው በሚለው ላይ ይሄ ሲያስረዱ
- ለማን ?
- ለባለቤቱ ለአህመዲን ባለቤት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስሚን ያውቃሉ ?
- ስሚን እንግዲህ እኔ /ግልፅ ያልሆነ/
- አይ ችግር የለም እሺ ምን አስረዳት ከእዚያ ምን አለች ?
- ካስረዳት በኋላ ከእዚያም በኋላ ከፊተኛ ገባን ስንገባ ያሉትን ያው መረጃዎችን አንዳንድ መረጃዎችን ፍተሻ ፖሊስ እንትን አለ እኛ በታዛቢነት ቆምን ያለው ሁኔታ ከተፈተሸ በኋላ
- ቆይ ፍተሻው ተጀመረ ምን ምን አገኛችሁ ?
- ያገኘነው /ግልፅ ያልሆነ/ መፅሐፎች የሙስሊም ቁርአን መፅሐፎች በርካታ ናቸው በቁጥር እንኳን ባላውቃቸው ካሴቶች አሉ የሲዲ ካሴቶች አሉ በቁጥር እንኳን ባላውቃቸው 3 ሞባይሎች እና
- የሲዲ ካሴት ምን ያህል ?
- በቁጥር አላውቀውም ምክንያቱም በወቅቱ ያው ድንገትም እንትን ስለሆንኩኝ ያሰብኩት ነገር አልነበረም ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ፈርምበት አለኝ
- ጥሩ ኤግዛክትሊ በቁጥር ላያውቁ ይችላሉ አንድ ነው አንድ ሺህ ነው ይሄንን መገመት አይችሉም ?
- እኔ በግምት ማስቀመጥ አልችልም ምክንያቱም ያልቆጠርኩትን ነገር ገምቼ ይሄንን ያህል ነው ብለው
- ትንሽ ነው ?
- አይ ብዙም አይባልም መቼም መካከለኛ ነው ማለትም ብዙዎች ናቸው ባይባልም መካከለኛ የሆነ ነገር ነው
- እስካሁን የገለፁልኝ ሲዲ አግኝታችዋል ?
- ሲዲዎች ኮምፓስ ወይም የአቅጣጫ መጠቆሚያ አንድ አንድ ላፕቶፕ አነስተኛ ላፕቶፕ እና የኦርቶዶክስ መፅሐፎች እነዚህ እነዚህ ነገር ናቸው ሞባይል 3 ሞባይሎችን ያየዋቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- የማን ናቸው ?
- የማን እንደሆኑ ያው እዚያው ቤት ውስጥ የተገኙትን ነው
- የማን እንደሆኑ አልጠየቃችሁም ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ባለቤቱ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለነበረች ያለውን ነገር እንግዲህ ከቤቱ የተገኘውን ነገር ነው የማን ነው ብለን መጠየቅ ኃላፊነት ያለበት ፖሊስ ይመስለኛል
- ጥሩ ባለቤቱ አብራ ከነበረች ?
- አዎ ባለቤቱ አብራ ነበረች
- ትቃወም ነበረ እናንተ ስታነሱ ፖሊሶች ያንን ሲያነሱ ?
- አልተቃወመችም
- የማን ነው ስትል ነበር ?
- የማን
- የማን ነው ይሄ ይሄንን አትንኩ የእከሌ ነው ይሄ የአህመዲን አይደለም እንዲህ የምትለው ነገር ነበር ?
- ምንም የተናገረችው ነገር የለም ያለውን ነገር ከተረዳዳች በኋላ ያው ተረጋግታ መጨረሻ ላይ ማለትም እኛንም ስለምታውቀን መጨረሻ ላይ ተረጋግታ ያውን ነገር ስንፈርም ቃለ ጉባኤ ተፅፎ ከተነበበ በኋላ ያለውን ነገር እንትኖችን መፈረም ጀመርን ካሴቶችን ያሉትን ንብረቶች መፅሐፎችን ፖሊስ ኢግዚቢት የሚያደርጋቸው ነገሮችን እየፈረምን እሷም እኔም ምስክሮችም ሆነን ጠቅላላ ያለውን ነገር ፈርመን ያው ፖሊስ ይዞ ሄደ በጋራ ወጣን ሲሄዱ እኛም ወደ ቤታችን ሄድን
- ሌላ በዝርዝር የሚያስታውሱት ነገር አለ ከያዛችዋቸው አሁን ከጠቀሱልኝ ከኮምፓስ ከሲዲ ከቁርአን መፅሐፎች ከክርስትና ኃይማኖት መፅሐፎች ካሏቸው ውጪ ?
- መፅሔቶች ምናምን ይኖራሉ መፅሔቶች በስም እንኳን ባላውቃቸው ለጊዜው ረስቼአቸዋለሁ መፅሔቶች ይኖራሉ ዝም ብለው ማንኛውም የሚነበብ መፅሐፍ መፅሔቶች ይሄ ሚዲያ ላይ የሚወጡ መፅሔቶች እነሱ እነሱ አሉ አንዳንድ ጋዜጣዎች ነገሮች አሉ በወቅቱ ባላስታውስም በቁጥር ስላልያዝኳቸው
- ጥሩ ብርበራው ስንት ሰዓት አለቀ ?
- 4 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት
- ዋና ጥያቄ አበቃን
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር እርሶ ታዛቢ ሆነው እንዲገኙ በፖሊሶች ተጠይቀው ወደ የሚበረበረው ቤት ቪላ በሩ ላይ ሌሎች ፖሊሶች አልነበሩም እንዴ ?
- አልተሰማኝም
- ማለት እርሶን ታዛቢ እንዲሆኑ የጋበዙት ፖሊሶች አሉ ?
- አዎ
- ተያይዛችሁ ወደ ቤቱ ሄዳችሁ ልክ በሩ ጋር ስትደርሱ ሌሎች ፖሊሶች አልነበሩም ?
- ሌላ ፖሊሶች አልነበሩም
- ቅድም ተከሣሽዋ የተከሣሽ ባለቤት ያሏት በመልክ አውቃታለሁ ብለዋል ?
- አዎ ምንድን ነው በወቅቱ የነበሩ ፖሊሶች እዚያው ላይ ሆነው ነው በሩ ላይ ፊት ለፊት ስለነበር መኪናውን እኔ የፖሊስ መሆኑን ሳውቅ እዚያው ጋር ሆነው ፖሊሶቹ እሷም ቆማ ነበር ና እንደዚህ እንደዚህ ብለው 1ኛው ፖሊስ ወረደ አናገረኝ ከእዚያ ያለውን ጉዳይ ይሄ መኪና ምንድን ነው ብዬ ጠይቄአቸው ስለነበር ነው ሰቤዝ ነው በወቅቱ መኪና መርገጥ አይችልም ብዬ ጠይቄው ስለነበር ና እንደውም ለታዛቢነት እንፈልግሀለን
- ስለዚህ እያሉ ያሉት እርሶን ነው ታዘቡ ያሎት ፖሊሶቹ የሚበረበረው ቤት በር ላይ ሆነው ነው የጠሮት ?
- አዎ ፖሊሶቹ 3 ፖሊሶች ናቸው 2 ፖሊሶች ከላይ ናቸው አንደኛው ፖሊስ ወረደ አናገረኝ ከእዚያ በኋላ ሄድኩኝ ስሄድ 2ቱን ባለቤቱ በእዚያ ጋር ነው የነበረችው ያለውን ነገር አነበቡላት የፍ/ቤት ትዕዛዝ ነው አሉን ለእኔም አሳዩኝ ያለውን ነገር በእዚያ መልኩ ፍተሻው እንዲሄድ ሆነ ከፈተች ገባን
- ታዛቢ እርሶ ብቻ ነበሩ እንዴ እርሶ ብቻ ነው የታዘቡት ?
- 3 ነን
- እስቲ የመጀመሪያ ስማቸውን ይነግሩናል የመጀመሪያ ስማቸውን ብቻ የሌሎች ታዛቢዎች ?
- አይሰማኝም
- ሌሎች ከእርሶ ጋር 2 ታዛቢዎች ነበሩ ከእርሶ ጋር 3 ናችሁ ?
- አዎ
- እስቲ የ2ቱን የመጀመሪያ ስም ይነግሩናል የመጀመሪያ የአባታቸውን ሳይጨምሩ የእነሱን ብቻ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነሱን እኔ እዚያው ጋር ነው ያገኘዋቸው
- አያውቋቸውም በስም ?
- በስም አውቃቸዋለሁ
- ስማቸው ማን ነው የአባታቸውን ሳይሆን የራሳቸውን ብቻ ?
- የምስክሮችን
- ታዛቢዎችን ?
- ናዝሪት እና ወይንሸት
- ፖሊሶቹ ወደ ቤት ሲገቡ ምን ይዘው ነበር ?
- ምንም ያው ማለት ያው ወረቀቶችን እና የፍ/ቤት ትዕዛዙን አንዳንድ ቃለጉባኤ የሚይዙባቸው መዝገቦችን ይሄንን ነው ይዘው የነበሩት
- በእጃቸው ነበር የያዙት ይሄንን ?
- በምን
- በእጃቸው ነበር ወይ ፖሊሶቹ መዝገቦችን ወረቀቶችን የፍ/ቤት መያዣውን እንዲህ በእጃቸው አንጠልጥለው ነበር የሚሄዱት?
- በእጃቸው ነው አዎ የያዙት
- ከእዚያ ውጪ ሌላ የያዙት ነገር ነበር ?
- እኔ ሌላ ያየሁት ነገር የለኝም
- ቦርሳ ነገር አልተሸከሙም ነበር ?
- ቦርሳ እኔ እንግዲህ ያው ባይንደር በወቅቱ እኔ ቦርሳም ይሁን ባይንደርም ይሁን ብቻ የሆነ መያዣ ነገሮች ይዘዋል ያንን እንግዲህ /ግልፅ ያልሆነ/ ያለውን የራሳቸው መረጃ ይኖራል በራሳቸው መረጃ ላይ ነው የያዙት ቦርሳ ነገርም ባይሆን ወደ ክላሰር ነገር እንደዚህ ይመስለኛል በእሱ ነገር ነው የያዙት መዝገቡን
- ቅድም የተከሣሽን ባለቤት ባለቤት መሆኗን በምን አወቁ ባለቤት ነች የአህመዲን ባለቤት ነች በመልክም አውቃታለሁ ብለዋል ፊቷን አትሸፈንም እንዴ ያዩዋት ሲትየዋ በር ላይ የነበረችው?
- አውቃታለሁ
- ማለት ፊቷ ክፍት ነበር ?



2476 924

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ከእዚህ በላይ ገልጣው ነበረ
- ፊቷን ከፍታው ነበር ?
- አዎ እንደዚህ አስራት ነበረ
- እንደዚህ እንደዚህ የምትለውን በድምፅ
- ማለት
- መመዝገብ ስላለበት እንደዚህ እንደዚህ የሚለው ከምን ወዲህ በድምፅ አስመዝግብ እሱን
- አዎ በፊቷ እና ግማሽ ፊቷ አፍንጫዋ እስከ አይኗ ያለው ከፍት ነበር ከእዚያ በፊት ጎረቤቴ ስለነበረች አውቃታለሁ በምን መልኩ መከናነብ እንደምትችል ሁሉ አውቃታለሁ ምክንያቱም በጉርብትና ለብዙ ዓመት ያህል ቆይተናል አውቃታለሁ ስለዚህም ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌላም ጊዜ ፊቷን እንደዚህ በግማሽ ከፍታ ነው የሚያዩት ?
- አቤት
- ለብዙ ጊዜ ስለሚያውቋት ፊቷን ከፍታ ነው የሚያዩት ?
- ፊቷን ከፍታ ያው ተሸፋፍና የአይኗ ጋርት እስከ አፍንጫ ያለው ከፍት ነው ከፍታ ትሄዳለች
- እሺ ገባችሁ ወደ ቤት ?
- አዎ
- እስቲ ብርበራው እንዴት እንደተካሄደ እርሶ ታዛቢ ስለሆኑ ያው መጀመሪያም ሁሉን ነገር በጥንቃቄ አይተዋል ተብሎ ስለሚገመት ልክ በሩን ከፍታው ገባች ስትገቡ ሌላ የቤተሰቡ አባል የሆነ ነዋሪ አልነበረም ውስጥ ?
- ነዋሪ አለ ወንድሙ ይሁን ልጁ አዲስ ነው ለእኔ አንድ ወጣት ልጅ ነበረ በወቅቱ እሱም እዚያው ውስጥ ነው የነበረው አልወጣም እሷ ከፍታ ስትገባ እራሱ እዚያ ውስጥ ነው የነበረው ከእዚያ ውጪ አለ እናቷ ደግሞ ከውጪ ነበረች በኋላ መጨረሻ ላይ ገባች እናቷም ከጎረቤትም አንድ ልጅ ነበረች ሙስሊም ናት አብረው ገቡ ቁጭ ብለው ነው ሕፃን ልጅ ነበረች እንደውም አቅፈዋት ተኛች ከእዚያ መጨረሻ ላይ ፍተሻው ተካሄደ የት የት ጋር መጀመር እንዳለበት እሷን እያስቀደሙ ፍተሻውን ጀመሩ
- እስቲ ፍተሻው ከየት ተጀመረ ?
- ፍተሻው የመጀመሪያ ገና ባለ 2 መኝታ ቤት ነው በቀኝ በኩል ነው ከሽንት ቤቱ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- መጀመሪያ ከመኝታ ቤት ነው ተጀመረ የሚሉት ?
- ወደ መኝታ ቤቱ ሳንገባ ሳንደርስ ኮሪደር አለ በኮሪደር ላይ መደርደሪያ አለ በመደርደሪያው ላይ የመጀመሪያ የመፀሐፍ ቅዱሶች የኦርቶዶክስ ካለዚያም ደግሞ የሙስሊም እንትን ብዛት ያላቸው እነሱን አዩ ያለውን ነገር መዘገቡ ብዛቱን የተወሰነውን ነው እዚያ ላይ ቀንጨብ አድርገው የወሰዱ ሁሉንም የወሰዱት የሙስሊሙን አልወሰዱም የኦርቶዶክስ እንደዚያው የተወሰነ ወሰዱ ከእዚያ መጨረሻ ላይ ወደ ውስጥ ገባን ወደ መኝታ ቤት ተገባ ተፈተሸ 2ኛ ፓርት ላይ ተፈተሸ ከእዚያ ዞርን ወደ በረንዳው በመስታወት የበረንዳው በመስታወት የተሰራ ነው በበረንዳው ፈተሽን ያለውን ተፈተሸ እኛ ያው እንደታዛቢ ነው የምንከታተለው ምን ምን እንደተነሳ ምን ምን እንደተገኘ ከእዚያ በኋላ ካለው ሁኔታ ላይ መጣ እዚያው ሳሎን ላይ ሆነ ያለውን ነገር እቃው እየተቆጠረ እየታየ እየተመዘገበ ቃለጉባኤ ተያዘ በቃለ ጉባኤ መጀመሪያ ተነበበ ፈረምን ከፈረምን በኋላ ባለቤቱ የመጀመሪያውን ትፈርማለች ቀጣይ እንደዚህ እያለ በደረጃ እየፈረምን እያስቀመጥን ሄድን
- ጥሩ አሁን በተገኙ የተገኙ እቃዎችን ዝርዝር ቆጥራችሁ በወረቀት ላይ ነው የፈረማችሁት በቃለ ጉባኤ አይደል ?
- አዎ
- በእቃዎቹ ላይ በተገኙት እቃዎች ላይ ግን አልፈረማችሁም ፈርማችዋል አሁን ሲዲ በተባሉት ላይ ?
- አዎ በተወሰዱት እቃዎች ላይ አጠቃላይ  እዚያ ውስጥም የቀሩ እቃዎች አሉ የቀሩ እቃዎች እንዳሉ ሆኖ
- የለም አሁን
- እኛ የፈረምነው ግን ከተወሰደው እቃ ላይ ነው የተወሰደው እቃ ምንድን ነው ማስታወሻ አልያዝንም ዝም ብለን እየፈረምን ስማችን እና ፊርማችን ስማችን እያስቀመጥን እዚያ ኢግዚቢት የሆኑትን ነገሮችን ሄዱ
- ለምሳሌ አሁን ሲዲ ቅድም ያሉት ቁጥሩን የማያውቁት ሲዲ ሲዲውን ቆጥራችሁ ብዛቱ ይሄንን ያህል እያላችሁ ነው የፈረማችሁት ይሄንን ያህል ሲዲ ይሄ 3 ሞባይል ስልኮች እንደዚህ እያላችሁ እንደዚያ ብላችሁ ነው አይደል የፈረማችሁት ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነው ሲዲዎችን እና መዕሐፎችን አልቆጠርኩም እነዚህ ግን ሞባይሎች 3 ስለነበሩ አነስተኛ ስለሆኑ በቃሌም አውቃቸው ስለነበረ ኮምፓስ ወይም አቅጣጫ መጠቆሚያውን ግን አንድም ስለነበረ ስለማውቀው ላፕቶፑንም አንድ ስለነበረ ስለማውቀው ነው በቃሌ መጥቀስ የፈለኩት ከእዚያ ውጪ ግን ባለው ነገር ማስታወሻ ባልያዝኩት ነገር መኖራቸው ብቻ ነው ካሴቶች አሉ አዎ አሉ መካከለኛ የሆኑ ካሴቶች ብዙም ባይባሉ
- የለም አሁን ጥያቄው ሲዲ ቅድም በርካታ ብለውናል ግምቱን የማያውቁት ሲዲ ከአንድ በላይ ቢያንስ ከ 1 በላይ የሆነ ነው ስለዚህ ስትፈርሙ እናንተ አንድም ሲዲው ላይ ወይም ደግሞ ይሄንን ያህል ሲዲ ወይም ደግሞ ዝም ብላችሁ በርካታ ሲዲ በሚል ነው የፈረማችሁት ወረቀቱ ላይ በቃለ ጉባኤ ስትፈርሙ ?
- እንግዲህ ቃለጉባኤው ተነቧል ሲነበብ እኔ አሁን አላስታውሰውም በቃል በእዚያን ወቅት ተነቦልናል
- አይ ምስክር ቆይ እስቲ ግልፅ ነው እኮ ጥያቄው ሲዲ አለ አይደል ያውቁታል ሲዲ ሲዲው ላይ ፈርማችዋል ወይስ ሲዲውን ብዛት በሚገልፅ ወረቀት ላይ የፈረማችሁት ነው ጥያቄው ?
- አይ በሲዲው ላይ በሽፋን ባላቸው ነገሮች ሽፋን ባላቸው ነገሮች ፈረምን ሽፋን አላቸው ከቨር ባላቸው ነገሮች ላይ እሱ ላይ ፈረምን ወረቀት የሆኑ
- ሲዲው ላይ ፈርማችዋል ?
- ሲዲው ላይ ወረቀት ያላቸው ነገሮች ላይ ከእዚያ ውጪ ግን በአጠቃላይ የማይፈረሙበት ነገር አሁን ሲዲ እነዚህ የማይፈረሙበት ነገሮች በፁሑፍ የማይዙት ነገሮች ላይ አልፈረምን ለምሳሌ ላፕቶፕ ላይ አልፈረምንም ኮምፓስ ላይ አልፈረምንም እንደገናም ደግሞ አቅጣጫ መጠቆሚያ ኮምፓስ እና ሞባይሎች ላይ አልፈረምንም
- ፁሑፍ የሚይዙት ነገር
- በፁሑፍ የተያዘ ፖሊስ የያዘው ነገር ስለሆነ አነበበልን በወቅቱ ያለውን ነገር
- ቀጥሉ
- ጥሩ አሁን ብርበራ አካሄዳችሁ ተፈራረማችሁ ከእዚያ ከእዚያ ውጪ ፖሊስ ያደረገው ነገር አለ?
- ምንም ነገር አላደረገም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቤቱ ተፈራረማችሁ ፔሬሰናል ተብላችሁ ወጣችሁ ?
- አዎ ፔርሰናል አሉ መዝገባቸውን ያዙ ሁላችንም ወጣን በአንድ ላይ ነው የወጣነው አወጣጣችን 3ቱ ፖሊሶችም እኛም ባለቤቱ እና የባለቤቱ እናት አንድ ጓደኛዋ አንድ ልጅ ነበሩ እዚያው ቀሩ እኛ ወጥተን ሄድን
- ቪዲዮ አልተቀረፀም ?
- አልተቀረፀም እኔ አላየሁም ያልተቀረፀውን ነገር አልተቀረፀም እኔ አላየሁትም ምናልባት የራሱ ፖሊስ በራሱ ወይም በራሳቸው ሞባይል ቀርፆ ሊሆን ይችላል ግን እኔ አላየሁም
- እሺ አቶ መልካሙ መጀመሪያ ፖሊሶቹ ሲመጡ ትዕዛዙን አሳይተውኝ አንብቤዋለሁ ብለሀል ልክ ነኝ አይደል የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ፖሊሶቹ አሳይተውኝ አንብቤዋለሁ ብለሀል ትክክል ነኝ አይደል ?
- አዎ የፍ/ቤት ትዕዛዝ አንበውልኛል ነው እንጂ አንብቤዋለሁ አነበቡልኝ አየሁት የፍ/ቤት ትዕዛዝ መሆኑን ከላይ አይቼዋለሁ የፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚለውን ከእዚያ የተሰጠውን አየሁት ከእዚያም በኋላ ለባለቤቱ ባለችበት እኛ ሁላችንም ባለንበት ሙሉ ንባቡን አነበበው በወቅቱም ያው ባለው የአህመዲን ነው የሚለው ያለውን ነገር እንዲህ እንዲህ ስለሆነ በወቅቱ ስለምንጠረጥረው ተብሎ ያንን ነገር ፍ/ቤት ትዕዛዙን በእዚህ መልኩ ነው ሲሏት
- ቆይ ይኸውሎት አሁን የእኔ ጥያቄ አጫጭር ናቸው መልሶቹ ቤቱ ላይ በግልፅ የአህመዲን ጀባል ቤት ይፈተሽ ይላል ትዕዛዙ ?
- አዎ
- መቼ ይፈተሽ ነው የሚለው ?
- በ 12 ማለት ፍተሻው የተካሄደው በ 12
- አይደለም የተካሄደበት ሳይሆን ትዕዛዙ ፍተሻው መቼ ይካሄድ ነው የሚለው ነው ?
- መቼ ይካሄድ የሚለውን ነገር እኔ እዚ ጋር ልብ ብዬም አላውቀውም ግን ፍተሻው የተካሄደው በ 12/11ኛ ወር
- እሱን ገልፀሀልናል ትዕዛዙን አንተ የምታውቀውን ብቻ መልስልኝ አሁን ካላወከው አላውቀውም ነው የምትለው አሁን መቼ ይታዘዝ የሚለውን አይተሀል ከትዕዛዙ ላይ መቼ ይፈተሽ የሚለውን ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ በእርግጥ እኛ ይሄንን ያህል ትኩረትም ባለማድረጋችን ባለማድረጊ በበኩሌ ሙቹ እና ሙቹ የሚለውን ነገር ትዝም አይለኝም ቀኑን አንበውልናል ግን ሙቹ እንደሆነ
- እሺ መልካሙ ትዕዛዙ ምንድን ነው እንዲበረበር እና እንዲያዝ ትዕዛዝ የሚሰጠው ምን እቃዎች ነው ይያዙ ይፈተሹ የሚለው ?
- አጠቃላይ እንግዲህ ባለቤቱ በወቅቱ
- አይደለም የምጠይቅህ ስለወረቀቱ ፖሊሶቹ አንበቡልን ስላልከው ወረቀት ነው የምጠይቅህ የተሰራውን ስራ ቅድምም መልሰህል ወደ ፊትም ምናልባት እንጠይቅሀለን አሁን አሁን የምጠይቅህ ወረቀቷን ብቻ ነው ፖሊሶቹ ያነበቡላችሁን ወረቀት ያ ወረቀት ምንድን ነው ምን እቃ ይያዝ ነው የሚለው በግልፅ ነው ?
- እዚያ ላይ ይሄ እቃ ይያዝ ይሄ እቃ አይያዝ የሚል የተገለፀ ነገር የለም ቤቱ እንዲፈተሽ ነው
- እሺ አሁን የምጠይቅህን ነገሮችን ትመልስልኛለህ ሲዲ ይያዝ የሚል ግልፅ ትዕዛዝ አለው
- አቤት
- ሲዲ ይያዝ የሚል ትዕዛዝ አለው ?
- የለም
- ኮምፒዩተር ይያዝ የሚል ትዕዛዝ አለው ?
- የለውም
- መፅሐፎች ይያዙ የሚል ትዕዛዝ አለው ?
- ቆዩ እስቲ ይሄ እኮ ግልፅ ነው ይሄ ይሄ እቃ የሚል ዝርዝር ነገር አላየሁም
- አይ ስነ ስርዓት ሕጉ የሚለውን ነገር አረጋግጦት እንዲሄድ ብቻ ነው
- ስነ ስርዓት ሕጉ እኮ ይታወቃል እሱን ተው እና ዝርዝር ይሄ እቃ ይያዝ የሚለውን ዝርዝር አላውቅም ብለዋል
- ከተያዙት እቃዎች ጋር መጣራት ስላለበት ነው የተከበረው ፍ/ቤት ያው እሱ አሁን እየመሰከረ ያለው በታዛቢነት ያየውን ነገር ስለሆነ
- ይሄ ይሄ እቃ ይያዝ የሚል ነገር አላየሁም ካለ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ቅደም ወደ ቤት ስንሄድ ባለቤቱ ውጪ ላይ አገኘናት ነው ያልከው እና አስቀድመው ነግረዋት የቆሙች ይመስለኛል የጠበቀችን ይመስለኛል ብለህ ነበር ማን ነግሯት ነው እዚያ ጋር ቆማ የምትጠብቃችሁ ?
- እንግዲህ በእዚያን ሰዓት እኔ እኮ ቅድምም ጠቅሼዋለሁ ፖሊሶቹ በወቅቱ መኪና እዚያ ሰቤዝ ቦታ ላይ ሲያቆሙ እኔ ተጠራሁ እና ጥበቃዎች ጠርተውኝ ክልክል ስለነበር በወቅቱ አካባቢው ላይ ሰቤዝ ኮብል እስቶን ሳይነጠፍ ኮምፓክት ሳይደረግ ስለማይቆም መኪና ሲገባ ይሄ ምንድን ነው ምናምን ፖሊሶች ናቸው ከእዚያ ምንድን ነው እዚህ ጋር ምናምን ብዬ ስጠይቃቸው እንደውም
- ይኸውሎት አታርዝመው ቅድም የመሰከርከልን ከደገምከው ችግር ይሆናል አሁን እኔ አስቀድሞ ነግዋት ሊሆን ይችላል ስላልክ ነው አንተ ማን ነው የሚነግራት ነው አንተ ነህ ቤቱ ጋር ይዘሀቸው የሄድከው ቤቱ ጋር ይዘሀቸው የሄድከው አንተ ከሆንክ ለእሷ አስቀድሞ ማን ይነግራታል ነው ?
- ፖሊሶችም እዚያው አሉ በር ላይ ነበሩ እንግዲህ አንኳኩተው ጠይቀዋት ሊሆን ይችላሉ
- ስለዚህ አንተ ስትሄድ ቆይ ቆይ አንተ ስትሄድ ፖሊሶቹ እዚያ ሌሎች ፖሊሶች ነበሩ በሩ ላይ?
- 3 ፖሊሶች ናቸው 1ኛው ፖሊስ ወርዶ አናገረኝ እንደውም እንፈልግሀለን ለእዚህ ሲለኝ ቀጥታ ሄድኩኝ ስሄድ የፍ/ቤት ትዕዛዙን በፍ/ቤት ትዕዛዝ ታዘን ነው አህመዲንን በአሸባሪ ስለምንጠረጥረው ይሄ ይሄ ነው አለ ከእዚያ በኋላ ባለቤቱ እኛ ባለንበት ምስክሮች ምናልባት ወይም ታዛቢዎች
- ይበቃል ዝርዝሩ 1ኛ የሚጠየቁትን ብቻ መዘው ለምሳሌ የተጠየቁት አንድ ጥያቄ ነው መጀመሪያ ሰምተው ነበር ወይ ባለቤትየዋ እንዴት ሰሙ እሱን ግለፁልን ነው የተባሉ እርሶ ከመጀመሪያ ጀምሮ አሁንም እያዳመጡ እሱን ብቻ ሳይሆን የተጠየቁትን ጥያቄ ብቻ
- እሺ እዚያ ቤቱ ጋር ስትደርሱ አሁን ፖሊሶቹ ስላደረጉት ነገር ነው እንድታስረዳኝ የምጠይቅህን በግልህ የአንተን ሳይሆን የፖሊሶቹን ነው የምጠይቅህን እና በደንብ አዳምጠህ መልስልኝ ፖሊሶቹ ያ የሚፈተሸው ቤት የአህመዲን ጀባል ቤት ስለመሆኑ ያጣሩት ነገር አለ ?
- እኔ ያጣሩ አያጣሩ አላውቅም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ በራፍ ላይ ቆማ የአህመዲን ጀባል ሚስት ነች እኔ አውቃታለሁ ያልካት ሴት በር ከፍታለች ያቺ ሴት የአህመዲን ጀባል ሚስት ስለመሆኗ ፖሊሶቹ ያጣሩት ነገር አለ ?
- እኔ ማጣቅ አለማጣቃቸውን አላውቅም
- ያጣሩት ነገር የለም ?
- አዎ
- ፖሊሶቹ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ለእዚያች ሴት አልሰጧትም አይደል ወረቀቱን የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ወረቀት ለእሷ በእጅዋ አልሰጧትም አይደል ?
- አነበቡ ካነበቡ በኋላ ለእሷ መጀመሪያ ያለውን ነገር
- አይደለም መልካሙ አሁን ጥያቄዬ ግልፅ ነው እኮ ቅድም አንብበውላታል አስረድተውናል ብለሀል ?
- አዎ
- እሱን አይደለም አሁን ወረቀቱን ለእሷ ሰጥተዋታል ወይ ነው የጠየኩህ ?
- መጨረሻ መጀመሪያ ያለውን ነገር
- ለእሷ ሰጥተዋታል አልሰጧትም እኮ ነው መልካሙ አታርዝመው
- ሰጥተዋታል
- እሺ እሷ አንብባዋለች ወረቀቱን በራስዋ ?
- ወረቀቱን መጨረሻ ላይ ካነበብን በኋላ ወረቀቱን ሰጠዋት አየችው ያለውን ከተፈተች ገባን
- እሺ በፍተሻው እንግዲህ ሁሉንም ክፍሎች ነው ቤቱ የተፈተሸው ብለሀል እና ተፈትሾ ፖሊሶቹ ይዘውት የሄዱት እቃ አለ አይደል ?
- አዎ
- ያ እቃ በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ላይ የተዘረዘሩትን እቃዎች ብቻ ይሁን አይኑን ያጣራችሁት ነገር የለም አይደል ?
- እንግዲህ የተዘረዘሩ እቃዎችን እኔ በወቅቱ የማውቃቸው ነው የነገርኩት
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለ አይ አሁን የጠየቁትን ነው የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ዝርዝር አይታችዋል ወይ የእቃ ዝርዝር አይታችዋል ወይ የሚለው ጥያቄ ስነ ስርዓታዊ አግባብነት ስለሌለው ነው የተቃወምነው

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት እስቲ ግልፅ ያድርጉልን ?
- ይሄ ብርበራ የተደረገው በሽብርተኝነት
- እይ የመጨረሻው ጥያቄ አሁን እሱ የጠየቀው ላይ ነው አይደል ተቃውሞ ?
- አዎ
- መጨረሻው ላይ ?
- አዎ
- ተቃውሞውን ግልፅ ያድርጉ ?
- ብርበራው የተደረገው በሽብርተኝነት ሕጉ መሠረት በከቨርት ሰርች ወይም ድብቅ ብርበራ በሚባለው ያ ደግሞ እነዚህን ነገሮች ማካተት ስለማይጠበቅበት ይሄ ጥያቄ አግባብነት የለውም ከጭብጡም ውጪ ነው እና ስለዚህ ያንን ነው የምንቃወመው
- የተከበረው ፍ/ቤት በእርግጥ አሁን የተከበረው ዐቃቤ ሕግ እንዳሉት የፀረ ሽብርተኛ አዋጁ ድብቅ ብርበራ ሊደረግ እንደሚችል ትዕዛዝ ይሰጣል ያ ድብቅ ብርበራ ማለት ግን በምን መሠረት ሊፈፀም እና ምንድን ነው ድብቅ የሚሆነው ስለሚለው ነገር የሚሰጠው ትርጉም የለም ነኛው ነገር 2ኛው ነገር ድብቅ ብርበራ በሚለው ነገር የሚለው ነገር ከፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ውጪ የሚሰራ ስለመሆኑ ነገር ግን የሚገልፀው ነገር የለም ሕጉ ይልቅ የሚለው ድብቅ ብርበራውን ቢሆንም በፍ/ቤት ትዕዛዝ መፈፀም አለበት ነው የሚለው በፍ/ቤት ደግሞ ትዕዛዝ የብርበራ ትዕዛዝ በሲጥበት ጊዜ በስነ ስርዓት ሕጉ አንቀፅ 33 ቁጥር 33 መሠረት ትዕዛዝ የሚሰጠው ቁጥር 33 ላይ ደግሞ በግልፅ የተቀመጠው ነገር የሚፈተሸው እና የሚያዘው እቃ ምን እንደሆነ ፍ/ቤቱ በግልፅ ማስቀመጥ አለበት ፍ/ቤቱ በግልፅ ካስመቀመጠው እቃ ውጪ መያዝም መውሰድም አይቻልም ነው የሚለው አሁን እሳቸውን እየጠየኩ ያለሁት ከእዚህ ስነ ስርዓት ሕግ አኳያ ፖሊሶቹ ይዘውት የሄዱት እቃ በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ላይ የተገለፀውን እቃ ነው ወይስ ከእዚያ ውጪ የሚለውን ነገር አጣርታችዋል አላጣራችሁም ነው ይሄ ደግሞ በታዛቢነታቸው ያዩትን ነገር ነው የሚመሰክሩት የሕጉን ጉዳይ ፍ/ቤቱ በራሱ ጊዜ ሲመረምር ጉዳዩን ትዕዛዝ የሚሰጥበት ነው የሚሆነው አሁን እሳቸው የፍሬ ነገር ጉዳይ ነው የሚያስረዱት
- ብይን ተሰጥቷል በተነሳው ጥያቄ በፍ/ቤት የመበርበሪያ ትዕዛዝ ላይ የተዘረዘረው ንብረት ነው የተያዘው ወይስ እንዴት ነው አጣርታችዋል ወይ የሚል ጥያቄ ቀርቧል እዚህ ላይ የተነሳው መቃወሚያ በፀረ ሽብርተኝነት አዋጁ መሠረት ድብቅ ብርበራ ስለሆነ ይሄንን ምስክሩ ሊመልሱ



http://ethcriminalawnetwork.com/

አይገባም የሚል መቃወሚያ ቀርቧል ጥያቄው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ፍ/ቤቱ አይቶታል በእርግጥ በዐረ ሸብርተኝነት አዋጁ መሠረት ድብቅ ብርበራ እንደሚደረግ ሕጉ ያስቀምጣል ያ ድብቅ ብርበራ ማለት ግን ምስክሩ ድብቅ ምርመራ ዓላማው ማስረጃ እንዳይባክን ነው አስፈልጎ ያሉ ነገሮች በተገቢው መንገድ እንዲያዙ ለማድረግ ከዘለለ ምስክሩ በብርበራ ወቅት ታዛቢው በብርበራ ወቅት ያየውን ነገር ለፍ/ቤት በዝርዝር እንዳይመሰክር የሚከለክል ባለመሆኑ የቀረበውን ተቃውሞ አልተቀበልንም ስለዚህ ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥል ተብሏል

- መልካሙ መጨረሻ በወረቀቱ ላይ በተገኙት እቃዎች ዝርዝር ላይ ፈርመናል ብለሀል ያንን ስትፈርሙ እዚያ ላይ የተያዙት እቃዎች ዝርዝር በፍ/ቤቱ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መሆን አለመሆኑን አጣርታችዋል ?
- ማለት ያው ቤቱ እንዲፈተሽ እና የሚለው ደብዳቤው የተሰጠው የፍ/ቤት ትዕዛዝ የተሰጠው ቤቱ እንዲፈተሽ ነው ከእዚያ ውጪ ግን እቃው ይሄ ይሄ እቃ ተለይቶ ይሁን የሚለውን እኔ እዚያ ጋር የሚል ነገር የለውም
- ስለዚህ አላጣራችሁም
- አቶ መልካሙ አቶ አህመዲን ይኖርበታል ካሉት ሕንፃ ላይ የሚያውቁት አቶ አህመዲንን ብቻ ነው ወይስ ሌሎች ጎረቤቶችን ያውቃሉ ?
- በወቅቱ በአህመዲን ጋር የነበሩት እንደውም ከሌላ ብሎክ መጥታ ነው እኔ አንዲት ሴት ያየዋት
- ጥያቄዬ ግልፅ ካልሆነሎት ልድገምሎት አቶ አህመዲን ይኖርበታል ካሎት ብሎክ ላይ የሚያውቁት አቶ አህመዲንን ብቻ ነው ወይስ ሌሎች ጎረቤቶችንም ያውቃሉ የአቶ አህመዲን ጎረቤቶች ሌሎችንም ያውቃሉ ወይስ አቶ አህመዲንን ብቻ ነው የሚያውቁት ?
- ሌሎችን እኔ በስም አላውቃቸውም በአይን አውቃቸው በእርግጥ ግን አቶ አህመዲንን ከእኔ ጋር ብሎክ ፣ አካባቢ ከእኔ ጎረቤቴ ስለነበሩ በእሱ ስለማውቃቸው ነው እዚያ ጋር /ግልፅ ያልሆነ/ መሄዳቸውን ስለማውቅ ነው
- አቶ አህመዲን ብቻ ነው ከእርሶ ብሎክ ወደ እዚያኛው ብሎክ ለውጦ የመጣው ?
- እሳቸው ተከራይተው ነው የሚኖሩት
- ገባኝ እሱ ብቻ ነው የለወጠው ሌላ የለወጠ ሰው የለም ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያኛው አሉ ግራ እና ቀኝ አሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ከጎኑ አሉ
- ስለዚህ ተተዋወቃላችሁ ከእነሱም ጋር ?
- ከእሱ ጋር እኔ ብዙም አላውቃቸውም ማለት
- የብሎኩ የልማት ተጠሪን አያውቁትም ?
- ግልፅ ይሁንልኝ
- የልማት አስተባባሪ ነኝ ብለዋል ?
- አዎ
- የልማት አስተባባሪዎች ከየብሎኩ ነው የሚመረጡት አይደለም ?
- አዎ
- የእዚያ ብሎክ የልማት አስተባባሪን ያውቁታል አያውቁትም ትተዋወቃላችሁ አይደል ከእዚያ ብሎክ የልማት አስተባባሪው ?
- ምንድን ነው እዚያ /ግልፅ ያልሆነ/ ሰዎችን እንዴት አላወቋቸውም ሊሉኝ ፈልገው ነው
- አይደለም አሁን የምታውቃቸው ከሆነ አውቃቸዋለሁ የማታውቃቸው ከሆነ አላውቃቸው ማለት ትችላለህ ጥያቄዬን ግልፅ ላድርግልህ አቶ አህመዲን ከሚኖርበት ብሎክ ላይ የምታውቀው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ብሎክ 16
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አስተባባሪ የምለው ሰው የለም
- ከብሎኩ ላይ ከአቶ አህመዲን ውጪ ሌላ የሚያውቁት ሰው አለ ?
- ተመልሷል
- መልሱን ስላልሰማሁ ወይ ችሎቱ ይንገረን
- /ግልፅ ያልሆነ/ ሪከርድ ተደርጓል
- ወይ ችሎቱ ያስታውሰኝ እና ልቀጥል
- ሪከርድ ተደርጓል ይሄ ሪከርድ ተደርጓል ይለፍ ማዳመጥ አለማዳመጥ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፍተሻውን በተመለከተ ከጎረቤቶች ጋር ወይም ከምታውቃቸው ሰዎች ጋር ያደረከው ውይይት አለ ከፍተሻው በኋላ ?
- እኔ ያደረኩት ውይይት የለም
- ከማንም ጋር ምንም አልተነጋገርክም ?
- አልተገናኘሁም
- ከፍ/ቤት መጥሪያ የወጣው በ 12/ ሐሙስ በ 12/ 9 ሰዓት ላይ ነው አንተ የፍ/ቤት ትዕዛዝ አየሁኝ የምትለው 4 ሰዓት ላይ ነው እንዴት ሊሆን ይችላል ይሄ ?
- አይ እኔ የፍ/ቤት ትዕዛዙ ያየሁት ወይም የመጣ በወቅቱ ከጠዋቱ 4 ሰዓት ፍተሻውን የጀመርንበት 6 ሰዓት የጨረስንበት ሐሙስ በ 12/11ኛ ወር 2004 ዓ.ም ነው
- ቀድሞ እንደሚመጣ የምታውቀው ነገር ነበር እንዴ ? የፍ/ቤት የብርበራ ትዕዛዝ ቀድሞ ይመጣ እንደሆነ የምታውቀው ነገር ነበር ?
- እኔ አላውቅም ድንገት ነው ያየሁት እኔ አላውቅም
- እሺ የግቢው የኮንደሚኒየም ግቢ የልማት አስተባባሪ ነኝ እና ፖሊሶች ሲገቡም ያወኩት በእዚያ ምክንያት ነው ብለሀል እና የኮሚቴው ወይም የልማት አስተባባሪ ከሆንክ ታውቃህ ብለህ ስለምናምን ፖሊሶች እዚያ ግቢ ውስጥ ከፍተሻው ጋር በተያያዘ ምን ያህል ቀን ነው የቆዩት ?
- እኔ ድንገት ነው መቼም ያው አንድ ሰው እንዲህ ነው ሲባል
- ድንገትነቱ ሳይሆን አሁን ጥያቄዬ ግልፅ ነው ምን ያህል ቀናት ነው የቆዩት ግቢ ውስጥ ?
- ማይኩ ላይ እንትን ስለሚል ጆሮዬ አይሰማኝም
- ፖሊሶች ግቢ ውስጥ ስንት ቀን ቆይተዋል ?
- እኔ እሱን አላውቅም
- ፍተሻ የተካሄደው ሐሙስ በ 12 ሲሆን ከግቢ ወይም አቶ አህመዲን ቤት ለቀው የወጡት በ 16 ወይም ከ 5 ቀን በኋላ ነው እዚያው ቤት እያደሩ ይውሉ እንደነበር ታውቃለህ ?
- አላውቅም ይሄንን
- ከእዚያ ከአካባቢው ላይስ የሰማኸው ነገር አለ ?
- እኔ የሰማሁት ነገር የለኝም ምክንያቱም እኔ እንደልማት ነው ያንን ልማት በወቅቱ ስርተን ጨርሰን ስለነበረ በወቅቱ በእዚያ አካባቢ አልመላለስም ሊሆን ይችላል እኔ አላውቅም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. ፖሊሶቹ ፍተሻውን ከጨረሱ በኋላ የላከን አካል ውጡ ካላለን አንወጣም ማለታቸውንስ ታውቃለህ ?
- ይደገምልኝ
- የላከን አካል ውጡ ካላለ ከቤቱ አንወጣም ማለታቸውን ታውቃለህ ወይ ?
- እኔ አላውቅም
- እሺ ፍተሻው ሲካሄድ በቦታው ስለነበርክ እዚያው ፍተሻው ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ልጠይቅህ 3 ሞባይሎች ተይዘዋል ብለሀል ?
- አዎ
- እህቱ የአህመዲን ባለቤት የባለቤቱ እናት የባለቤቱ እህት ነበሩ ብለሀል እነዚህ ሞባይሎች የእኛ ናቸው ማለታቸውንስ አልሰማህም ?
- ምንድን ነው የባለቤቱ እህትም አልነበረችም የባለቤቱ እህትም ትሁን ግን ጎረቤት እንደሆኑ እና በስመ ሙስሊም ይመስለኛል ትውውቅ እንዳላቸው አውቃለሁ
- የእኔ ነው ይሄ ሞባይል የእኛ ነው ሲሉ አልሰማህም ?
- ከሌላ መንደር ነው የመጣችው
- ይሄ ሞባይል የእኛ ነው ሲሉ አልሰማህም ?
- ሞባይሉ
- ለምን ይወሰድብናል ይሄ ሞባይል የእኛ ነው ሲሉ አልሰማህም ?
- ማንም ያለ የለም
- ስንት ሴቶች ነበሩ አጠቃላይ ?
- እናቲቱ
- አይ እናቲቱ አባቲቱ ሳይሆን ስንት ሴቶች ነበሩ አጠቃላይ ?
- በአጠቃላይ 3 ናቸው
- 3 ከፖሊሶች ሴት ነበረ ?
- ከፖሊስ ሴት የለም ወንዶች ናቸው
- ከታዛቢዎች ሴት ነበረ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከታዛቢዎች 2 ሴቶች እና አንድ ወንድ እኔ ወንድ ነኝ
- ማን ነበር ከታዛቢዎች ?
- ከታዛቢዎች
- ቆይ ቆይ ተገልፆዋል ይሄ ተጠይቋል
- እሺ የአህመዲን ቤተሰቦች ወይም የሚስቱ እናት እህቱ የሚስቱ እህት እንዳይወጡ እና እንዳይገቡ ታግደው የነበረ መሆኑንስ ታውቃለህ በፖሊሶች እንዳይወጡ ተደርገው የነበሩ መሆኑን ታውቃለህ ?
- ምንድን ነው እዚህ ጋር ፖሊሶች ያሉት ነገር የለም እንደውም ከሌላ መንደር መጥታ ገብታ ሁሉ ዝም ብላ ቁጭ ብላ ስታይ የነበረ እህቷ ሳትሆን ዘመድ ይሁኑ እኔ በስመ ሙስሊም ይሁን እኔ አላውቅም ግን 2ቱንም አውቃቸዋለሁ
- ቅድም የአህመዲን ባለቤት ውጪ ነበረች ስንገባ እቤት ውስጥ ሰው ነበር ብለሀል አይደል ?
- አዎ
- እነዚህ ሰዎች እንዳይወጡ ተደርገው መሆኑን የምታውቀው ነገር አለ ?
- የማውቀው ነገር የለኝም
- ፖሊሶቹ ግቢ ውስጥ ምን ያህል ቀን እንደቆዩ አታውቅም አይደል ?
- አላውቅም
- ቆይ ቆይ እየደጋገሙ ነው ጥያቄ
- ስንት ፖሊሶች ነበሩ ?
- 3 ፖሊሶች
- 3 ፖሊሶች ነበሩ እርግጠኛ ነህ ?
- አዎ
- እርሶ የአቅጣጫ መጠቁሚያ ወይም ኮምፓስ ያሉት የሰላት አቅጣጫ መጠቆሚያ ነው አይደል?
- አዎ እንግዲህ እኔ በወታደራዊ ሳይንስ የማውቀው ኮምፓስ እንላቸዋለን አቅጣጫ መጠቆሚያ ነው
- የሰላት አቅጣጫ መጠቆሚያ አይተህ ታውቃለህ ?



2438 937

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ድሮ በደርግ ጊዜ ወታደር ነበርኩኝ አውቀዋለሁ
- አንተ ሙስሊም ነህ ሰላት ትሰግዳለህ እንዴ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት አግባብነት ያለው ጥያቄ አይደለም
- የተከበረው ፍ/ቤት እናስተካክለው ጥያቄአችንን እናስተካክለው ከወታደር ወይም ወታደርኩ ነበርኩ ስላሉ ኮምፓስ ሊያውቁ ይችላሉ ሙስሊሞች ሰላት ለመስገድ አቅጣጫ ለማየት የሚጠቀሙበትን አይተህ ታውቃለህ ወይ ?
- እኔ አላውቅም ሊኖር ይችላል ግን አላውቅም
- እሱን አይተህ አታውቅም እሺ መጠኑ ምን ያህል በእጅ ላይ የሚቀመጥ ነው ?
- ትንሽ ክብ ነገር ያው በእጅ የሚያዝ ነገር የምትያዝ ናት አቅጣጫ መጠቆሚያ ናት አቅጣጫ የምሳይ ናት
- ሙስሊሞች ሰላት ለመስገድ አቅጣጫ ማወቅ እንዳለባቸውስ ታውቃለህ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን
- ሊሆን ይችላል እኔ ግን ኦርቶዶክስ ስለሆንኩ
- ምስክር ዝም በል
  - ፍ/ቤቱ ያስቆማል
  - ልክ ነው
  - ከእዚያ ውጪ ግን ምስክሩ ዝም በል ብሎ ምስክሩ ላይ የሚፈጠረው ነገር አለ ደንግጦ ሊሮጥ ይችላል ወይ አንድ ነገር ሊሆን ይችላል ስለዚህ እሱን ያስተካክሉ ?
  - እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
  - ይቅርታ አሁን ይሄ ምስክር እንግዲህ የብርበራ ምስክር ነው ያገኛቸውን ነገሮች የሚያስታውሳቸውን ተናግሯል አሁን ክርክሩ አግኝቷል አላገኘም እንጂ መሆን ያለበት ሙስሊሞች ኮምፓስን ለምን ይጠቀሙታል የኮምፓስ ጥቅም ተብሎ የኤክስፐርት ዓይነት ጥያቄ ሊጠየቅ አይገባውም እኛም ካስያዝነው ጭብጥ ከምስክሩም እውቀት ውጪ ስለሆነ አግባብነት ያለው አይደለም እና ለእዚህ ነው በተረፈ ግን ያው የተከበረው ፍ/ቤት ይቅርታ እጠይቃለሁ ቅድም ምስክሩ ቅድም ሊያቆም ስላልቻለ ጣልቃ ስለገባሁ



2490

938

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለነገሩ ምላሽ እዚህ ለመስጠት ተገቢ አይደለም ምክንያቱም መልሶታል ምስክሩ ሊኖር ይችላል እኔ እሱን አላውቅም ብሏል ወደ ሌላ ጥያቄ ይሂዱ ጥያቄው ግን አይደጋገም ሲደጋገም ነው ይሄ ሁሉ ችግር የሚፈጠረው
- እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት
- አቶ መልካሙ ፍተሻ እየተደረገ በነበረበት ወቅት በመሀል ፖሊሶች ቤትህን እየፈተሹን ስለሆነ ብትመጣ ብለው ደውለውለት ነበር አይደል አቶ አህመዲን?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- በመሀል የደወለስ ሰው የለም ለእሱም ባይሆን የደወለ ሰው ?
- በፍፁም እኔ ማንም የሚያውቀኝ የለም አልደወሉልኝም
- መልካሙ ቅድም ከግንኙነታችሁ ልጀምር እና አህመዲን ጀባል ጎረቤቴ ነው ጓደኛዬ ነው ብለህ ነበረ ጓደኝነታችሁ እንዴት ነው እስቲ
- ይሄ ተጠይቋል ሌላ
- ተጠይቋል
- አዎ
- እሳቸው እኮ ነው ጓደኛ ያሉት
- ስለግንኙነታቸው ተጠይቋል ከእዚያ ላይ ቆሞ ሌላ የሚጠይቁት ካለ ይሄ /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ አይቼአለሁ ብለው ነበረ ከየትኛው ፍ/ቤት እንደወጣ አይተዋል ?
- ይሄንን እንግዲህ በፍ/ቤት ትዕዛዝ የትኛው ፍ/ቤት እንደሆነ እንግዲህ ያው የአዲስ አበባ ፍ/ቤት ማለትም የክልሉ ፍ/ቤት ነው የሚለው ፌዴራል ፍ/ቤት ነው
- ፌዴራል ?
- ማለት በፌዴራል የመጀመሪያ
- የት ነው እርሶ አህመዲን ጀባል ቤቱ ያሉት ?
- የአህመዲን ጀባል
- ኮልፌ ቀራንዮ ነው አይደል ጂቲዜድ
- አዎ
- ስለዚህ ትዕዛዙ የመጣው ከየት ነው ?



939

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትዕዛዙ የመጣው ከፍ/ቤት ነው
- ከየትኛው ፍ/ቤት
- ከየትኛው ፍ/ቤት እንደሆነ ለይቼ ባላውቅም ብቻ ከእዚሁ ፍ/ቤት ነው የሚለው ፌዴራል ፍ/ቤት ነው የሚለው
- እኮ የትኛው ፍ/ቤት ብዙ አለ እና አያውቁትም ወይስ አላዩትም ?
- እኔ አላውቀውም በወቅቱ ረስቼው ሊሆን ይችላል እንጂ እኔ በእርግጥ ለይቼ ያንን ያህል /ግልፅ ያልሆነ/ ብቻ ነው እንጂ የትኛው ፍ/ቤት የሚለውን ነገር እጠየቃለሁ ብዬ ስላልገመትኩ ነው ጠንቅቄ ላውቀው እችል ነበር
- ማህተሙን አይተዋል ?
- አዎ
- ምን ይላል እሱስ ?
- ማህተሙ ያው ማህተም ያለው ማህተም አለው ከላይ የፌዴራል ፍ/ቤት የሚለውን ያንን ካነበብኩ በኋላ ነው
- ከየትኛው ፍ/ቤት ጋር እንደሆነም አይገልፅም ከየትኛው ፍ/ቤት እንደሆነ አይገልፅም እሱም?
- ገልፆዋል ግን የትኛው ጋር እንደሆነ እኔ ያላወኩት እንጂ እሱን እንዳለ አውቃለሁ
- የዳኞቹንስ ፊርማ አይተዋል ?
- ፊርማ ያለበት ፊርማ የተፈረመበትን አይቼዋለሁ ብቻ ያለውን ነገር
- ስንት ዳኞች ነው ስንት ዳኞች ፈረሙበት ?
- እኔ እንጃ ስንት ዳኞች እንደሆኑ አላወኩም በወቅቱ
- እሱንም አያውቁም ?
- ትዝም አይሉኝ
- ስለዚህ በእርግጠኝነት የዳኛ ፊርማ አይተዋል ?
- አዎ
- ማን የሚል እንደሆነ አላወቁም ?
- አዎ ወቅቱም ጊዜውም ስለረሳሁ ሊሆን ይችላል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ቤት ውስጥ ስገባ ሕፃን ልጅ ተኝታ ነበር ብለዋል የትኛው ክፍል ነበር-የተኛችው ባቱን ስላየችሁት ማለቱ ነው ?
- ላይ ሳሎን ላይ ነው
- ቀይ ይለፉት ይሄ /ግልፅ ያልሆነ/ የት ተኛች የሚለው ይለፉት እና ሌላ
- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ከትላንትናው ምስክር ጋር የምናየይዘው ነገር ስላለ ነው
- እስቲ ወይ እሱን ግልፅ አድርጉ የሕፃን ክርክር አይደለም ክርክሩ እና
- ክርክሩ አይደለም ግን
- ካእዚህ ጋር እንዴት እንደሚያያዝ እስቲ ለእኛ ይግባን መጀመሪያ ምስክሩን ከምትጠይቁ ምንድን ነው የፈለጋችሁት እስቲ አብራሩ ?
- የት ክፍል እንደተኛች አይተዋል
- ምንድን ነው የፈለጉት ከሕፃን ጋር በተያያዘ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ሕፃን ልጅ ተኛች ብለዋል የት ክፍል ነው ስትተኛ ያዩዋት ?
- ባመጀመሪያ ልጅቷ ሕፃኗ አልተኛችም አያቷም ስለነበሩ ከእዚያ አያቷ አቀፏት እና እኛ ፍተሻውን አካሂድን ቆጠራ በምናካሄድበት ጊዜ
- ክፍሉን ነው የጠየኩት የት ክፍል ተኛች ?
- ሳሎን ነው
- ሳሎን ነው የተኛችው ?
- ላዎ አያቷ ጋር አቅፈዋት ተኝታለች
- እሳቸው አልተኛችም እያሉ ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ተኝታለች ነው ያሉ ?
- ላያትዋ አቅፈዋት ስትጫወት ነበር መጀመሪያ ከእዚያ
- ላይ ማለት አልጋ ላይ ነው አልጋ ላይ ነው እኛ አንደርስታንድ ያደረግነው ?
- ላያቷ አቅፈዋት ነው ቁጭ ብለው ሳሎን ላይ ቁጭ ብለው አቅፈዋት ከእዚያ ተኛች እኛም ዎው እዚያው ቁጭ ባሉበት እንዳሉ ነው ወጥተን ሄድነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለአህመዲን ስልክ ተደውሎ ነበር ፍተሻ ላይ እያላችሁ ለአህመዲን ና ተብሎ ስልክ ተደውሎ ነበር ፖሊሶች ?
- ድጋሚ ነው ይሄ
- ያው ተጠይቋል እና አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች እየደጋገሙ ነው ቅድምም ተደውሏል ወይ ተብሎ በአቶ መሐመድ ተጠይቋል አሁንም አቶ ሀሰን እየደገሙት ነው
- ቆይ መድገም አለመድገም ያው አካሄድ ነው ይሄ ተደግሟል ይለፉ
- እዚያ ቤት ፍተሻ በገባችሁበት ዕለት መብራት ነበር ያስታውሳሉ መብራት ነበር ያስታውሳሉ?
- መብራት እኔ አላስታውስም መብራት መኖሩን አላስታውስም
- የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ ?
- ድጋሚ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- 2 ሰው መጥቷል እንዴት ነው ዐቃቤ ሕግ ?
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት
- አስተርጓሚ ነው ወይስ
- አዎ 136ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለችው ናዝሬት ከቀረቡት እና ከተሰሙት በ2ኛ ተከሣሽ አህመዲን ጀባል ላይ ከተሰሙት የብርበራ ምስክሮች የተለየ የምታስረዳው ነገር የለም በእዚሁ እንድትሰናበት ነው
- 100 ስንት ?
- 136ኛ
- ቀሪውን እንዲመሰክር ?
- አዎ አቶ ሱራፌል ግን እንዲመሰክሩ ነው የመጡት
- ይቀመጡ እሳቸው
- ናዝሬት ነሽ ለምስክርነት ነው የመጣሽው የፍ/ቤቱን መጥሪያ አክብረሽ ፍትህ ለማገዝ በመምጣትሽ ያው ያለውን የሕጋዊ ግዴታ መወጣትሽን አክብረሽ በመምጣትሽ

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

እናመሰግናለን ዐቃቤ ሕግ የተሰሙት ምስክሮች ይበቁናል ስላለ በክር አሰናብተናቸዋል መሄድ ይችላሉ

- ቃለ መሀላ ይፈፅሙ
- የተከበረው ፍ/ቤት እነዚህ 2 ምስክሮች ሌላ ስራ አለን ስላሉ እንዲሰናበቱ ቢፈቀድላቸው
- የተሰሙት ናቸው ?
- አዎ
- የተሰሙት ምስክሮች ያው ከቀሪ ምስክሮች ጋር ሳይገናኙ መሄድ ይችላሉ
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- ለምስክርነት ነው የመጡት ?
- አዎ
- ስምዎን የአባት ስም ሌላ ዝርዝር ውስጥ ሳይገቡ የራስዎን ስም ብቻ [illegible]
- ሱራፌል
- ስንተኛ ናቸው ዐቃቤ ሕግ ?
- ሌላ ሱራፌል ከሌለ 192 ላይ የተጠቀሱ ናቸው በተሰሙት ምስክሮች ዝርዝር 63ኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ በ 192 ላይ የተጠቀሱ ምስክር ተሰምቷል በ 136 ላይ የተጠቀሰው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ያው ቀድሞ ተመሳሳይ ናቸው ስለተባለ ተሰናብቷል አሁን የቀረቡት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- ሀሰን አሊ /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌላ ሰው አለ ከእዚያ ውጪ ከእሱ ውጪ ሌላ አለ የሚመሰክሩበት ?
- የለም
- እሱ ላይ ብቻ ነው ?
- አዎ
- ሀሰን አሊ ነው ?
- አዎ
- ያውቁታል በአካል ሀሰን አለ. ?
- አላውቀውም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአካል ለይተው አያውቁትም ?
- አላውቀውም
- ምን ፈፀመ ተብሎ ነው የተከሰሰው የሚያውቁት ነገር ካለ በአጭሩ ?
- የሽብር ወንጀል ተጠርጥሯል የሚል
- ተጠርጥሯል የሚል ነው እርሶ ምንድን ነው ያዩት እርሶ ያዩት ምንድን ነው ከእዚያ ጋር በተያያዘ ?
- ማለት ያው ቤቱ ላይ ነው የሄድነው ቤቱ አካባቢ ነበርኩኝ እኔ
- ቤቱ ምን ሆነ ?
- ያየሁት ነገር ቤቱ ነው ሄጄ ያየሁት
- ቤቱ ምን ሲደረግ ?
- ሲበረበር ማለት ነው
- ቤቱ ሲበረበር ታዝበዋል ?
- አዎ
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ሱራፌል መቼ ነበር ጊዜው ቀኑ ይሄ የብርበራው ቀን መቼ ቀን ነበር ቦታው ክፍለ ከተማው የት ነበር እስቲ የሚያስታውሱት ?
- የተበረበረው ሐምሌ 12 ቀን ነው ቦታው ደግሞ ወረዳ 4 አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የቤት ቁጥር 139 /ግልፅ ያልሆነ/ አካባቢ 26 ቀበሌ
- ስንት ሰዓት ነበር ?
- 11 ሰዓት
- እሺ በእዚህ ዕለት ማለት ነው እርሶ እስቲ መጀመሪያ ምን አዩ መጀመሪያ ማንን አገኙ ማን ጠራዎት እንዴት ተገኙ ከእዚህ በኋላ ምን አዩ ምንድን ነው ወደ ብርበራው ከመፈፀሙ በፊት የነበረው ስነ ስርዓት ምን ነበር እስቲ ይንገሩን ?
- እኔ በአጋጣሚ ወደ አካባቢ እዚያው አካባቢ ስለሆነ ወደ አካባቢ እየገባሁ እያለ ፖሊሶች እንድታዘብ ጠየቁኝ እኔ ፍቃደኛ ሆንኩኝ ገባን ማለት ነው አብረን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ልክ ፖሊሶቹን እንዳገኟቸው ፖሊሶቹ ምን አሉት ወይም ያሳዩት ነገር ካለ ?
- የመበርበሪያ ትዕዛዝ አሳዩኝ የሚያስፈልገውን ፎርማሊቲ ሲያቀርቡልኝ ሕጋዊነቱን ካረጋገጥኩኝ በኋላ ገብቼአለሁ
- ከእዚያ ወዴት አመራችሁ ወዴት ሄዳችሁ ይሄንን የበርበራ ትዕዛዝ ካሳዩት በኋላ ወዴት ሄዳችሁ ?
- ወደ ቤቱ
- ማን ቤት ?
- ሀሰን አሊሻባ ቤት
- እሱ ነበረ ?
- የለም
- አልነበረም ?
- አዎ
- እሺ ቤቱን ማን ከፈተ ወይስ እንዴት ነበር ቤቱ ?
- አንኳኩተን ገባን
- ማን ከፈተላችሁ ?
- ቤት ውስጥ የነበሩ አንድ ሴት እና /ግልፅ ያልሆነ/
- ከመግባታችሁ በፊት ፖሊሶቹ ምን አሉ ?
- ያው ትዕዛዙን እንደመጡ እና ቤቱን ሊበረብሩ እንደመጡ ነግረው ገቡ
- እኮ ያንን ትዕዛዝ ምን አደረጉ አሳዩዋቸው ወይስ ትዕዛዙን ከመግባታቸው በፊት ምን አደረጉት ?
- የፍ/ቤት ትዕዛዝ ይዘው እንደመጡ እና ቤቱን ሊበረብሩ እንደሆነ ነግረው
- ይሄንን ነገሯቸው ?
- አዎ
- ከእዚያስ ገቡ ?
- ገቡ አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ተገኘ ?
- በቃ ወደ ብርበራ ገቡ እኔም እነሱ ሲበረብሩ ቆሜ ታዝቤአለሁ
- እስቲ እዚያ ውስጥ እንግዲህ አሁን ምን ምን ተገኘ አሁን ገባችሁ ትዕዛዙ ተነበበ ገባችሁ ሰዎችም ነበሩ ምን ምን ተገኘ እቤት ውስጥ ?
- የተገኘው ብዙ ነገር ተገኝቷል ማለት የማስታውሰው ነገር ብቻ
- አዎ የሚያስታውሷቸውን ይግለፁዋቸው ?
- ፲ኛ ሲዲዎች ተገኝተዋል
- ስንት ይሆናሉ ብዛት አላቸው ?
- ከ 200 በላይ የሆኑ ሲዲዎች አሉ
- ስለምን የሚያመለክቱ ናቸው ይታወቃል ?
- ከእምነት ጋር የተያያ`` ናቸው ብዙዎቹ
- ሌላስ ?
- ሌላ መፅሐፍ ቅዱስ ተገኝቷል
- መፅሐፍ ?
- መፅሐፍ ቅዱስ ቁርአኖች ተገኝተዋል ቪኤችኤስ ተገኝቷል ካሴት
- እሺ ሌላስ ?
- ሬዲዮ መቅረጫ ተገኝቷል መቅረጫ ድምፅ መቅረፃ ተገኝቷል ሲዲኤም ተገኝቷል ቪዲዮ መቅረጫ ተገኝቷል በእጅ ፁሑፍ የሚፃፉ ፁሑፎች ተገኝተዋል
- ምንድን ናቸው ይዘታቸውን ለማስታወስ ይችላሉ የእጅ ፁሑፎቹን ?
- አላስታውስም
- ምን ዓይነቶች ናቸው በርካታ ናቸው ወይስ ብዛታቸው ይለያል
- ምኖቹ ?
- ወረቀቶቹ የተገኙት ማለቴ ነው ?
- መፅሐፍቶቹ ብዙ ናቸው
- ወረቀቶቹስ የእጅ ፁሑፍ ያለባቸው ያኗቸው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- የሚያስታውሱት አለ እነኚህ ተገኙ ከተገኙ በኋላ ምንድን ነው የተደረገው እኒኚህ አሁን በብርበራ እነኚህ ከላይ ቅድም የገለፁዋቸው ዝርዝሮች ከተገኙ በኋላ ምን አደረጋችሁ መጨረሻ ላይ ምን ተባለ መተማመኛ ?
- ተቆጠረ ባለቤቱ ነበረች ባለቤቱ ፈርማ /ግልፅ ያልሆነ/
- ባለቤቱ ፈርማለች ?
- አዎ
- እናንተስ ?
- እኛም ፈርመናል
- ፖሊሶቹስ ?
- ፈርመዋል
- የፈረማችሁት ስለምን ምን ስለመሆኑ ነው እዚያ ስለመገኘቱ ነው ?
- እዚያ ስለመገኘቱ ሲቆጠር የነበረውን ነገር ስላየን እንፈርማለን
- ይሄንን እዚያ ምን ላይ ነው የፈረማችሁት ?
- መተማመኛ ላይ
- ስለዚህ ይሄ ዝርዝሩ ተፅፏል ?
- ዝርዝሩ ተፅፏል
- ተፅፏል ?
- አዎ
- እና መጨረሻ ላይ ያው ባለቤቱም አውቃ ፈርማለች ?
- አዎ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ እርሶ የሀሰን አሊ ጎረቤት ኖት እንዴ ?
- አይደለሁም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሀሰን አሊ. እስከነአያቱ ሲጠሩት ነበር ከእዚያ በፊት ያውቁታል እንዴ ከብርበራው ቀን በፊት ?
- አላውቀውም
- ከብርበራው በኋላስ አይተውስ ያውቃሉ ?
- አላውቀውም
- እንዴት ሊያስታውሱ ቻሉ ታዲያ አንድ ቀን ከሆነ ?
- ያው ጉዳዩ የሕግ ጉዳይ ስለሆነ የተገኘሁበትን ነገር ማወቅ ስላለብኝ በእዚያ ደረጃ ይገፄዋለሁ
- ቅድም ሲነግሩን አንኳኩታችሁ ገባችሁ እና አንዲት ሴት ከፈተች ነው ይቺ ሴት ማን ነች የከፈተችው ?
- አላውቃትም
- ፖሊሶቹ በሩን ሲያንኳኩ የእከሌ ቤት ነው ይሄ የማን ቤት እንደሆነ ለማረጋገጥ ሞከረዋል ወይስ ዝም ብለው አንኳኩ እና የፍ/ቤት ወረቀት አሳይተው ዝም ብለው ገቡ ?
- አንኳኩ የቤቱን ማንነት ጠየቁ አዎ ነው ተባሉ ገባን
- እርሶ የት ጋር ነው ፖሊሶች ታዛቢ እንዲሆኑ የጠየቁት ከቤቱ ምን ያህል ርቀት ላይ ነው ከሚበረበረው ቤት በምን ያህል ርቀት ሆነው ነው እርሶ ታዛቢ እንዲሆኑ ፖሊሶች የጠየቁት መጀመሪያ ?
- በሜትር ደረጃ አላውቀውም ግን ከ 1 እና ከ 2 ቅያስ ያለፈ ቦታ ላይ ነው
- ስንት ፖሊሶች ነበሩ ?
- አላስታውሳቸውም
- ወደ ቤቱ ሲጠጉስ ሌሎች ፖሊሶች አልነበሩም በሩ ላይ ?
- አላየሁም
- ጥሩ ወደ ውስጥ ገባችሁ እስቲ ብርበራው ከየት እንደተጀመረ ይግለፁልን እንዴት እንደነበረ እዚህ ያለን ሰዎች ስለማናውቅ ስዕሉን ቤቱ ስንት ክፍል ነበረው
- አላስታውስም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. ብርበራው ከየት ተጀመረ ?
- ሳሎን ላይ ካሉ ሸልፎች የመፅሐፍ መደርደሪያዎች /ግልፅ ያልሆነ/
- እዚያው አበቃ ?
- ከእዚያ በኋላ አንድ ኮርደር ላይ ነበረ የብፌ መደርደሪያ ነበር ከእዚያ ላይ የሲዲዮ ካሴቶች እና ቪዲዮ መቅረጫው ተገኝቷል እዚያ ላይ
- እዚያ ላይ አቆመ ?
- አዎ
- እርሶ ብቻ ነበር እንዴ ታዛቢ ?
- እኔ እንጃ እኔ ስለራሴ ነው የማውቀው ሌላ ይኑር አይኑር
- ማለት አሁን ታዛቢ ኖት እኮ እርሶ አሁን እዚህ ደግሞ እውነቱን ሁሉን የመመስከር ኃላፊነትም አለቦት መህላም ሲፈፅሙ ስለዚህ ዩኒፎርም ሲቪል ፖሊሶቹ የደንብ ልብስ ነው አይደል የለበሱት ?
- አዎ
- የደንብ ልብስ የለበሱ አሉ በሩን የከፈተችው ሴት አለች እርሶ አንድ ታዛቢ ኖት ሌላ ሰው አልነበረም እንዴ በእዚያ ?
- አብሮኝ ታዘበ ልጅ ነበር ግን አላውቀውም መጥቶ እንደፈረመ ነው
- እሺ ቤት ውስጥ ከከፈተችው ውጪ ሌላ ሰው ነበረ ?
- ነበሩ አላስተዋልኳቸውም ብዛታቸውን
- የሴት ፖሊስስ ነበረች ?
- አልነበረችም
- ቅድም በብርበራ ወቅት ተገኙ ያሉትን ሲዲዎች አሉ መፅሐፍት እነዚህ ሲዲዎችን አሁን ከሲዲዎች እንጀምር እና ሲዲዎችን በተመለከተ ብዛቱን እየቆጠራችሁ ነው መተማመኛ ላይ የፈረማችሁት ወይስ ሲዲው ላይ እራሱ ነው የፈረማችሁት ?
- ብዛቱን እየቆጠርን
- ብዛት የሲዲውን ብዛት እንጂ እያንዳንዱን ሲዲ ዓይነቱ ምን እንደሆነ አልተዘረዘረም አይደል ወረቀቱ ላይ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልገባኝም
- የሲዲው ብዛት ቆጠራችሁ እና ሲዲ ይሄንን ያህል በሚል ነው የፈረማችሁት ?
- ሲዲ ይሄንን ያህል በሚል ነው የቆጠርነው
- ፖሊሶቹ ሲገቡ ምን ይዘው ነበር እርሶ ታዛቢ ሆነው ከጠየቆት ተያይዛችሁ ስትሄዱ የያዙት ቦርሳ ነገር ሌላ ነገር ቅድም ወረቀት እንደያዙ ነግረውናል ከእዚያ ውጪ ምን ይዘው ነበር ?
- አላስታውስም
- ቤቱ ውስጥ ገቡ ብርበራ አካሄዱ መተማመኛ ላይ ፈረማችሁ ከእዚያ በኋላ ፖሊሶች ሌላ የሰሩት ነገር አለ ?
- የለም
- ቪዲዮ አልቀረፁም ቪዲዮ ነገር የተገኘውን እቃ ?
- ቪዲዮ የያዙ ይመስለኛል
- ቀርፀዋል ?
- እንግዲህ መያዛቸውን ነው እንጂ መቅረፃቸውን ምናምን አላስታውስም
- አሁን እርሶ ቤት ውስጥ ሆነው ሲቀርፁ አይተዋል
- ምን አሉኝ
- ሲቀርፁ አላዩም ከውጪ ቪዲዮ ይዘው ሲገቡ አይተዋል ?
- የያዙ መሰለኝ አዎ ማለት በነገራችን ላይ ጊዜው ረዘም ስላለ ብዙ ነገር እንትን አልልም ማለት ሐምሌ 8 ወር እንደዚህ ያህል ነው እና ካሜራ እንደያዙ ትዝ ይለኛል ያው ካሜራ የሚያዘው ለመቅረፅ ነው ስለዚህ እየቀረፁ ነበር
- ካሜራ የያዙት ቅድም በብርበራም ካሜራ ተገኝቷል ስላሉ ከውጪ ይዘው የገቡት ነው ወይ ወይስ ከውስጥ ያገኙት ?
- ከውጪ ይዘው የገቡት መሰለኝ
- ካሜራውን በእጃቸው ነበር በቦርሳ ነበር ?
- በእጃቸው ነበር
- በእጃቸው እያሳዩ ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚያ በኋላ ከተፈራረማችሁ በኋላ ማን ቀድሞ ወጣ ፖሊሶች አሉ ታዛቢዎች ሌላ ከእርሶ ጋር ሌላ ሰው አለ ማን ነው ቀድሞ የወጣው ?
- ይሄ ትዝ አይለኝም ማለት አብረን ነው ሁላችንም የወጣነው እገሌ ቀደመ እገሌ ቀደመ የሚለው
- ፖሊሶችም ሌላኛውም ታዛቢ አብራችሁ ወጣችሁ ?
- አብረን ነው የወጣነው
- አቶ ሱራፌል ቅድም ዐቃቤ ሕግ ሲጠይቆት ብርበራው 11 ሰዓት ላይ ተጀመረ ብለዋል ከምሽቱ ስንት ሰዓት ላይ አለቀ ?
- በሰዓት 3 ሰዓት አካባቢ ከምሽቱ
- ከምሽቱ 3 ሰዓት ሌላ ደግሞ ቅድም ዐቃቤ ሕግ ጠይቆት ከ 200 በላይ ከእምነት ጋር የሚያያዙ ሲዲዎች ተገኝተዋል ብለዋል አቶ ሀሰን አሊ ሙያው ቪዲዮ ኤዲቲንግ እና አስተርጓሚ ወይም ተርጓሚ መሆኑን ያውቃሉ ?
- አላውቅም
- አቶ ሱራፌል ቅድም የፍ/ቤት ትዕዛዝ አይቼአለሁ ብለው ነበረ ?
- አዎ
- የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ መዝገብ ቁጥር ያስታውሳሉ ?
- አላስታውስም
- ከየትኛው ፍ/ቤት እንደተፃፈስ ያስታውሳሉ ?
- አላስታውስም
- ምን ይፈተሽ እንደሚል ወይም ምን ይበርበር እንደሚል ያታውሳሉ ?
- አላስታውስም
- የዳኛ ፊርማ ማህተም እንዳለው ያስታውሳሉ ?
- ማህተም እንዳለው ምን እንዳለው ሕጋዊ እንደሆነ አስታውሳለሁ
- የዳኛ ፊርማ እንዳለው ያስታውሳሉ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ምን ይላል ዳኛው ማን ይላል ?
- አላስታውስም እሱን
- ቁጥሩንም አያስታውሱም ?
- አላስታውስም
- ወደ ቤቱ ጉዳይ ስንመጣ ፖሊሶች ይሄ ቤት የሀሰን አሊ ነው ከማለት ውጪ እርሶ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- አላውቅም እሱን
- በመካከሉ ለሀሰን የደወለለት ፖሊስ ነበረ ከእናንተ ውስጥ ፍተሻው እስከ 3 ሰዓት አምሽቷል ብለሀል ?
- አዎ
- በእዚያ መካከል ለባለቤቱ የደወለለት ፖሊስ ነበረ ምን እያለ ሲነጋገር ነበር
- ለማን
- ለሀሰን ለተከሳሽ ሲደውልለት የነበረ ፖሊስ ነበር ካልመጣህ ባለቤትህን ይዘን እንሄዳለን ሲለው አልሰማህም ?
- አልሰማሁም
- ስልክ የደወለ ፖሊስ አልነበረም ?
- አላየሁም እሱን
- ነበርክ አይደል አንተ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ?
- ነበርኩ አላየሁም እኔ
- ፖሊሶቹ ስልክ ሲደውሉ አልሰማህም አላየህም ?
- እሱን አልሰማሁም
- ፖሊሶቹ አንተ ስትወጣ ፖሊሶቹ እዚያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ይደሩ አይደሩ የምታውቀው ነገር አለ ይቅሩ አይቅሩ ያወከው ነገር አለ ?
- አብረን መውጣታችን እንጂ ከእዚያ በኋላ የነበረውን ነገር አላውቅም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስንት ቀን እንዳደሩም አታውቅም ?
- ከእዚያ በኋላ አላውቅም
- /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክሩ አብረን መውጣታችን እንጂ ከእዚያ በኋላ ስላለው ነገር አላውቅም ነው ያለው እና እዚህ ላይ /ግልፅ ያልሆነ/
- ቤት ውስጥ ስንት ሰው ነበር የነበረው አጠቃላይ ?
- አላስታውስም
- ቤት ውስጥ የነበረውን ሰው
- ተጠይቋል ተጠይቋል እሱ ቀደም ብሎ ተጠይቋል ስንት ሰው ነበር
- ፖሊሶቹ እቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎችን እንዳትወጡ ብለው ሲከለክሉ ነበር አልነበረም ?
- አላየሁም
- ተጠይቋል እሱ
- ቤት ውስጥ ከነበሩት ሰዎች አንደኛውን ልጅ ና ከእኛ ጋር ትሄዳለህ ብለው ይዘው መሄዳቸውን ያስታውሳሉ አብራችሁ ከወጣችሁ አብረው ይዘውት የወጡት ሰው ነበረ አልነበረም ?
- ከእኛ ጋር አብሮ የሄደ ልጅ ?
- አዎ እዚያው ቤት ውስጥ የነበረ ልጅ ማለት ነው ?
- እኔ የማውቀው አብረን መውጣታችንን እኔም ወደ ቤቴ መሄዴን ነው እንጂ ሌላ ያየሁት ነገር የለም
- ከፖሊሶቹ ይውሰዱት አይውሰዱት አታውቅም ታውቃለህ አታውቅም ?
- አላውቅም
- ባለቤቱ ፈረመች መጨረሻ መተማመኛው ላይ ብለዋል እርሶ ደግሞ የአካባቢው ነዋሪ ስላልሆኑ ባለቤት ትሁን አይሁን በምን ያውቃሉ እርሶ ?
- ባለቤቱ መሆኗን ስንገባም ነግራናለች
- እሷ ስለነገረቻችሁ ነው ?
- አዎ
- ከእዚያ ውጪ የጋብቻ ወረቀት አሳይታችዋለች ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላየሁም
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን ይሄ ሀራስመንት ነው ምስክሩን ሀራስ ማድረግ ነው ምስክሩ የጋብቻ ወረቀት አይተሀል ወይ ባለቤቱ ነች ባለቤቱ ነኝ አለች ብሎ መስክሯል ይሄ ምስክር አሁን ስምተሀል ወይ እዚያ ላይ ነው ክርክሩ ሊሆን የሚገባው እንጂ የጋብቻ ወረቀት አይተሀል ወይ ማለት ጠበቆችም ይሄ ሆነ ተብሎ ምስክርን ሀራስ ማድረግ ነው እንጂ ፍትህን የሚያስገኝ ጥያቄ አይደለም አሁን ብቻ አይደለም እስካሁን ያሉትን ጥያቄዎችንም ላለመረበሽ ነው ዝም የምንለው እንጂ በጣም አግባብ አይደለም እና ፍ/ቤቱ ማስጠንቀቂያ ቢሰጥበት ጥሩ ነው ተደጋገመ በጣም
- ይሄ ምላሽ የሚሰጥበት አይደለም አካሄድ እና የምስክሩ አያያዝ ነው ስለዚህ አሁን የሰማነው ጥያቄ የጋብቻ ሁኔታውን ለማረጋገጥ ስለሆነ ሀራስመንት ብለን ለመውሰድ የሚቻልም አይደለም ስለዚህ ጥያቄውን ቀጥሉ ብለናል
- አቶ ሱራፌል በሩን እዚያ ወስጥ ሚስት ማለት ሴትየዋ ሚስት ነኝ ከማለትዋ ውጪ ሚስት ስለመሆኗ ከእዚህ ባለፈ ሄዳችሁ ያጣራችሁበት ነገር አለ ?
- ይደገምልኝ ጥያቄው
- ሚስት ሴትየዋ ባለቤትህ ነኝ ከማለቷ ውጪ እናንተ በእርግጥም ባለቤት መሆን አለመሯን ከእዚህ አልፋችሁ ለማጣራት ያደረጋችሁት ነገር አለ ?
- የለም
- ጨርሰናል ተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ
- አለ ምስክር ቅድም በተከሣሾች ጠበቆች ሲጠየቁ እርሶ የእዚያ አካባቢ ነዋሪ አይደሉም ቤቱ የሀሰን አሊ ቤት መሆኑን ያውቃሉ ወይ ሲባሉ አላውቅም ብለዋል አይደል ቤቱ ውስጥ ስትገቡ የሀሰን አሊ ቤት አይደለም ያለስ አለ ?
- ማንም የለም
- ማንም የለም ?
- አዎ
- ባለቤቱ ነኝ ያለቻችሁ ሴት የማን ባለቤት ነኝ አለቻችሁ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሀሰን አሊ.
- ቤቱ የማን ነው ብላችሁ ጠይቃችዋል ?
- የአቶ ሀሰን አሊ ቤት ነው ወይ ተብሎ ተገብቷል አዎ ነው ተብሎ /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም በድጋሚ መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ብርበራው ያለቀው ከምሽቱ 3 ሰዓት ነው ብለዋል?
- አዎ
- ፖሊስ ብርበራው ወደ ምሽት ሲያልፍ ብርበራውን ወደ ምሽት ለማሳለፍ ፍቃድ እንደጠየቀ አያውቁም ?
- ወደ 12 ሰዓት አካባቢ ላይ ለዳኛ ደውሎ ፍቃድ እንደጠየቀ ነግሮን ሲደውልም አይተን /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም አንድ የመጨረሻ አሁንም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ካሜራ ተገኝቷል ብለው በዋና ጥያቄ መስክረው ነበር ይሄ ካሜራ ፖሊሶች ይዘውት የመጡት ነው ወይ ሲሉ አዎ ብለው ነበር ፖሊሶች ይዘው የመጡትን ነው እንዴ ብርበራ ላይ የተፈራረማችሁበት ተገኘ ብላችሁ?
- አይደለም
- አይደለም ?
- አዎ
- ስለዚህ ስንት ካሜራ ነበር ማለት ነው ?
- አንድ ካሜራ ከቤቱ ተገኝቷል
- ከሀሰን ቤት ተገኝቷል ?
- አዎ
- ፖሊሶች ይዘውት ከመጡት ውጪ ነው ?
- አዎ
- ድጋሚ አበቃን
- አሁን ከእዚህ በኋላ ሌላ መስማት አንችልም 8 ሰዓት ላይ እንገናኛለን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የጠዋቱን መዝገብ በያዝነው መሰረት እንቀጥላለን ዳኞቹ ያው የጠዋቱ አልተቀየሩም በአቃቤ ሕግ በኩል ያለው የጠዋቱ ናቸው አልተቀየሩም ተከሳሽ ምናልባት የተጨመረ የተቀነሰ ካለ ሁለት የጠዋቱ 3ኛ እና 6ኛ እሺ ሌሎቹ አሉ ጠበቃ የተጨመረ የተቀነሰ አለ

- ✓ ስለ 28ኛ ተከሳሽ አህመድ ጀማል ቀርቤያለሁ
- ✓ ~~አህመድ ጀማል ቀርቧል ሌሎቹ የጠዋቱ ናቸው~~
- ✓ ስለዚህ እንቀጥላለን
- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት ያው 144ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያሉ የአቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ቢኒያም ቀርበው ከተሰሙት በ14ኛ ተከሳሽ ላይ ቀርበው ከተሰሙት ምስክሮች የተለየ የማያስረዳ በመሆኑ በዚሁ እንዲሰናበት
- ✓ 144 ላይ የተጠቀሱት ?
- ✓ 144ኛ
- ✓ እሺ ቢንያም ማን ነው ሌላ የፍ/ቤቱን ጥሪ አክብረው ፍትህ /ግልጽ ያልሆነ/ ስለመጡ እናመሰግናለን የተሰሙት ይበኛል ስላለ አቃቤ ሕግ በዚሁ እናሰናብትሃለን አንተን መሄድ ትችላለህ እሺ ቀሪው ቃለ መሃላ ይፈጽም እሱ
- ✓ በእውነት ለመመስከር
- ✓ በእግዚአብሔር ስም
- ✓ ምያለሁ
- ✓ የአባህን ስም ሳትጨምር የመጀመሪያ ስምህን ብቻ ትነግረኛለህ?
- ✓ ስሜ ሳሙኤል እባላለሁ
- ✓ ስንተኛ ላይ የተጠቀሱ ናቸው ?
- ✓ 181



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እሺ. በ64ኛ ተራ ቁጥር ላይ የቀረበው የአቃቤ ሕግ ምስክር ያው ተመሳሳይ ነው ስለተባለ ተመልሷል አሁን 65ኛ ላይ ደርሰናል አቶ ሳሙኤል ቀርቧል በምስክር ዝርዝሩ 181 ላይ የተጠቀሱ ናቸው እሺ ሳሙኤል እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?

✓ እኔ የምመሰክረው ካሚል ሸምሱ ላይ

✓ ሌላ ሰው አለ?

✓ ሌላ የለም

✓ ካሚል ሸምሱን ታውቀዋለህ?

✓ በአካል በጣም እረጅም ጊዜ ነው 8 ወር ይሆነኛል እኔ በአካል አለየውም

✓ እሺ ካሚል ሸምሱ ምን ፈፀመ ተብሎ ነው የተከሰሰው ?

✓ ካሚል ሸምሱ ማለት

✓ አንተ ያየኸው ነገር ምን ሲያደርግ ነው?

✓ ያየሁት አጋጣሚ ለስራ ጉዳይ ነው እዛ ሄጄ ነው ወንጀል ምርመራ

✓ ወደ ዝርዝሩ በኋላ እንሄዳለን ምን ሲያደርግ አዩት?

✓ ያየሁት ከኢሜል አድሬሱ ያው የተለያዩ ሳይዝ ያላቸው እንትኖችን ሲወጣ ነው

✓ ሰነድ ሲወጣ ነው የታዘብከው?

✓ አዎ

✓ እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ

✓ ያው የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለሃል እና ቅድም እንደገለጽከው

✓ ሳሙኤል እስቲ ፊትህን ልክ ወደኛ ጆሮህን በዛም በዚህም ማረግ ይቻላል ፊትህን ወደ ችሎቱ

✓ ቅድም እንደገለጽከው ያው የመጣሁት ለምስክርነት ነው እና በአቶ ከሚል ሸምሱ ነው ላይ ነው ብለሃል እስቲ ምንድን ነው የምታውቀው ጊዜው መቼ እንደሆነ እና ምን



http://ethcriminalawnetwork.com/

እንደታዘብክ ምን እንደነበረ የት ቦታ እንደነበረ የምታውቀውን ያው ለተከበረው ፍ/ቤት እንድትገልጽ ነው የምንጠይቀው ጊዜው መቼ ነበር?

- ✓ ጊዜው ነሐሴ 25 ቀን 2004 ነው አጋጣሚ ለግል ስራ ወደዛ ሄጄ ነበር ወደ ወንጀል ምርመራ ማለት ነው
- ✓ የት አካባቢ ነው ወንጀል ምርመራ ነው ያልከው እሺ የት አዲስ አበባ ነው ወይስ ?
- ✓ እዚሁ አዲስ አበባ
- ✓ ማለት የት ነው ልዩ ቦታው የት ነው ?
- ✓ አካባቢው
- ✓ እ?
- ✓ ከጊዮርጊስ ትንሽ ከፍ ብሎ እና ለግል ጉዳዬ ነበረ የሄድኩት አጋጣሚ አንድ ሲቪል የለበሰ ፖሊስ ነው መጥቶ አናገረኝ
- ✓ እሺ ምን አለህ?
- ✓ ማለት በሽብር የሚጠረጠር አንድ ሰው አለ እና መጥተህ አብረን ትገባና ከግል ኮምፒውተሩ እና ኢሜል አድሬሱ የተለያዩ መረጃዎችን ያመጣልናል እሱ እሱን በቅርበት ሆነህ ታይልናለህ
- ✓ እስቲ ማይኩን አስተካክልለት ድምጽህ ትንሽ አልተሰማንም ችግሩን አላወቅነውም ወይ ከማይኩ ትንሽ እራቅ በል ወይ እስቲ ሞክር እንደዚሁ
- ✓ ገብተህ ከኢሜል አድሬሱ ሲያወጣ ምን ምስክርነት ትሰጣለህ እንደታዛቢነት ማለት ነው
- ✓ እሺ ይሄ ከተነገረህ በኋላ ወዴት ገባህ ?
- ✓ ቢሮ ውስጥ ነው
- ✓ ቢሮ ስትገባ ማንን አገኘህ ማን ነበር?
- ✓ እሺ ጠጋ በልና



2809 0959

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ ውስጥ ገባሁ አልክ ቢሮ ስትገባ ማንን አገኘህ?
- ✓ ቢሮ ውስጥ እኔና እንደዚሁ አንድ ታዛቢ አለ ስሙን አላውቀውም በአካል ነው የማውቀው እኔና እሱ ገባን እኔና እሱ ፖሊሱ ዘንድ ሄደን ካሚልን እንትን ነው /ግልጽ ያልሆነ/ የለበሰ ፖሊስ ከውስጥ ይዞት መጣና ለአንደኛው መርማሪ ሰጠው መሰለኝ ሰጠው
- ✓ ከዛስ ?
- ✓ አንድላይ ከመርማሪዎቹ ጋራ አብረን ሦስታችን ገባን ማለት ነው
- ✓ እሺ ከዛ ምን ሆነ?
- ✓ ከዛ ያው ገባ ካሚል መጀመሪያ ከግል ላፕቶፑ የራሴ ነው ብሎ ማለት ነው የራሱን ላፕቶፑን ከፍቶ ሁለት ፔጅ ፕሪንት አድርጐ አውጥቷል
- ✓ ይሄንን ላፕቶፕ የራሴ ነው ብሎ ሲናገር ሰምተዋል ከሚል?
- ✓ አዎ ሰምቻለሁ
- ✓ እሺ ከዛ ሁለት ገጽ አወጣ ፕሪንት አድርጐ ይሄ ሁለት ገጽ ምንድን ነው ምን ይፃፍበት ?
- ✓ አላስታውስም እሱን
- ✓ ትዝ አይልህም ከዛስ በመቀጠል ምን ወጣ ?
- ✓ ከዛ በመቀጠል ያው የእንትኑ እዛ የነበረ ሌላ ኮምፒውተር አለ ከዛ ላይ እራሱ ኢሜል አድሬሱን እና ፓስወርዱን እራሱ ጽፎ በተያየ ቋንቋ ሲፃፉ ጽሁፎችን አውጥቷል
- ✓ እራሱ ነው ያወጣው?
- ✓ አዎ እራሱ አዎ
- ✓ ምንድን ናቸው እነኚህ በተለያዩ ቋንቋ ያልካቸው ይዘታቸው ወይም ደግሞ በምን በምን አይነት ቋንቋ እንደተፃፉ ታስታውሳለህ ?
- ✓ ማለት ትንሽ ጊዜው እራቅ ስላለ ነው ወደ 8 ወር ይሆነዋል ግን በአማርኛ በእንግሊዘኛ እና በአረብኛ የተፃፉ በግምት ወደ 150 ፔጅ ይሆናል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እሺ ውስጥ ገባሁ አልክ ቢሮ ስትገባ ማንን አገኘህ?

✓ ቢሮ ውስጥ እኔና እንደዚሁ አንድ ታዛቢ አለ ስሙን አላውቀውም በአካል ነው የማውቀው እኔና እሱ ገባን እኔና እሱ ፖሊሱ ዘንድ ሄደን ካሚልን እንትን ነው /ግልጽ ያልሆነ/ የለበሰ ፖሊስ ከውስጥ ይዞት መጣና ለአንደኛው መርማሪ ሰጠው መሰለኝ ሰጠው

✓ ከዛስ ?

✓ አንድላይ ከመርማሪዎቹ ጋራ አብረን ሦስታችን ገባን ማለት ነው

✓ እሺ ከዛ ምን ሆነ?

✓ ከዛ ያው ገባ ካሚል መጀመሪያ ከግል ላፕቶፑ የራሴ ነው ብሎ ማለት ነው የራሱን ላፕቶፑን ከፍቶ ሁለት ፔጅ ፕሪንት አድርጐ አውጥቷል

✓ ይሄንን ላፕቶፕ የራሴ ነው ብሎ ሲናገር ሰምተዋል ከሚል?

✓ አዎ ሰምቻለሁ

✓ እሺ ከዛ ሁለት ገጽ አወጣ ፕሪንት አድርጐ ይሄ ሁለት ገጽ ምንድን ነው ምን ይፃፍበት ?

✓ አላስታውስም እሱን

✓ ትዝ አይልህም ከዛስ በመቀጠል ምን ወጣ ?

✓ ከዛ በመቀጠል ያው የእንትኑ እዛ የነበረ ሌላ ኮምፒውተር አለ ከዛ ላይ እራሱ ኢሜል አድሬሱን እና ፓስወርዱን እራሱ ጽፎ በተያየ ቋንቋ ሲፃፉ ጽሁፎችን አውጥቷል

✓ እራሱ ነው ያወጣው?

✓ አዎ እራሱ አዎ

✓ ምንድን ናቸው እነኚህ በተለያዩ ቋንቋ ያልካቸው ይዘታቸው ወይም ደግሞ በምን በምን አይነት ቋንቋ እንደተፃፉ ታስታውሳለህ ?

✓ ማለት ትንሽ ጊዜው እራቅ ስላለ ነው ወደ 8 ወር ይሆነዋል ግን በአማርኛ በእንግሊዘኛ እና በአረብኛ የተፃፉ በግምት ወደ 150 ፔጅ ይሆናል



2811 960

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ምን ያህል ገጽ እንደሆኑ ብዛታቸውን መገምገም?

✓ የአማርኛ ይበዛል 120 ምናምን አካባቢ ይሆናል

✓ እነኚህ በተለያየ አይነት አሁን እንበልና የአማርኛው አሁን ምን አይነት ይዘት እንዳለው ይታወቃል የወጣው?

✓ የምኑ?

✓ የአማርኛው ካስታወስክ ማለቴ ነው ይዘቱ ስለምን እንደተፃፈ ማስታወስ ትችላለህ?

✓ ፔጁ ነው ብዛቱ ?

✓ ገፁ ሳይሆን እነኚህ የተፃፉት ጽሁፎቹ ይዘታቸው ስለምን እንደሆነ?

✓ እሱን አላስታውስም

✓ እሺ እነኚህ ሁሉ አሁን ያልካቸው ከላፕቶፕም ከኮምፒውተሩም እነኚህ ከወጡ በኋላ በወቅቱ ይሄ ነገር ካሚል ሲያወጣ ማለት ነው እንዴት ነበረ ማለት እራሱ ፈቃደኛነቱ ሁኔታዎች እንዴት ነበሩ?

✓ እሱ በጣም በፍቃደኛነት ፈታ ብሎ ነው ማለት በቃ ዘና ብሎ ነው እራሱ በፍላጐቱ ቀድሞም ተነግሮታል እኛ ማለት ምንም የምናውቀው ነገር የለም ቀድሞ ተነግሮታል በፍቃደኛነት ሲያወጣ የነበረው

✓ እሺ እነኚህ ሰነዶች ማለት ነው አሁን ያልካቸው ሰነዶች ከወጡ በኋላ ምንድን ነው ያረጋችሁት በመጨረሻ ማለት ነው ስለመገኘታቸው እሱ ስለማውጣቱ ምን የተደረገ ነገር አለ ?

✓ ያው የመጀመሪያውን ከግል ላፕቶፔ መውጣቱን ብሎ ያው ቅድመ እሱ ጽፎ ፈረመ ከዛ እኛ ማየታችንን ፈረምን ከኢሜል አድሬሱም እንደዛው ማለት ነው በተመሳሳይ



961

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ከኢሜሉስ በወጣው ማለት ሲፈርም ማለት ነው እንዴት ነው የፈረመው እናንተስ ፈርማችኋል ወይም ታዛቢ የሆናችሁት ማለቴ ነው ስለመውጣቱ ከኢሜል ከላፕቶፕም በየገፁ ፈርማችሁ ወይ ማለቴ ነው?
- ✓ ከኢሜል ምናምን ሲወጣ አዎ ፈርመናል
- ✓ ካሚል ፈርሟል?
- ✓ አዎ ቀድሞ እሱ ነው የፈረመው
- ✓ ምን ብሎ ፈረመ?
- ✓ ከኢሜል አድሬሴ የወጣ መሆኑን ብሎ ፈረመ
- ✓ ከላፕቶፕስ ከወጣው?
- ✓ ከላፕቶፑም እንደዛው በተመሳሳይ
- ✓ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- ✓ ምስክር ከእርስዎ ታዛቢ እንዲሆኑ የተጠየቁት ጊቢ ውስጥ ገብተው ነው ወይስ ከጊቢ ውጪ?
- ✓ ለግል ጉዳይ ግቢ ውስጥ ገብቼ
- ✓ ግቢ ውስጥ ነበሩ እንዴት ነው ማን ነው የጠየቆት?
- ✓ ማንነቱን አላውቀውም
- ✓ እስቲ ሂደቱን ይንገሩን ጠየቆት ከዛ እንዴት ነበረ የገቡት ?
- ✓ መጀመሪያ መጥቶ ሰላም አለኝ የሆነ እዚህ በሽብር የሚጠረጠር ሰው አለ እና እንደዚህ እንደዚህ ከኢሜል አድሬሱ የተለያዩ ሰነዶችን ሲያወጣ በታዛቢነት እንዲያዩልን ብሎ ጠየቀኝ /ግልጽ ያልሆነ/ ፍቃደኛ ሆኜ ገባሁ
- ✓ ያው የጠየቆት ሰው ነው ይዞት የሄደው?



ን513 962

http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እ

✓ ይህ ታዛቢ እንዲሆኑ የጠየቆት ፖሊስ እየመራ ወሰዶት እርስዎን?

አዎ

✓ የት ገቡ?

✓ ያው ቢሮ ቁጥሩን ባላስታውስም እኔንና እንደዚሁም ሌላ ሰው ይዞ ነበረ

✓ እሺ ወደ ቢሮው ወሰዶት ቢሮው ሲደርሱ ክፍቶ አስገባዎት ወይስ ክፍት ነበረ?

✓ ክፍት አልነበረም

✓ ዝግ ነበር ?

✓ አዎ

✓ እሺ እርስዎ ሄደው ቢሮጋ ደረሱ ከዛ ምን ሆነ?

✓ እኛ እየሄድን በጉን ካሚል መጣ ከዛ አንድ ላይ ገባን ማለት ነው ቢሮ ውስጥ

✓ እሺ ካሚል መጣ ቢሮው ተከፈተ?

✓ አዎ

✓ እሺ ቢሮ ውስጥ ስትገቡ ስንተ ጠረጴዛ ነበር?

✓ ቢሮ ውስጥ ስንገባ ሁለት ጠረጴዛ

✓ ሁለቱ ጠረጴዛዎች ላይ ምን ነበር ኮምፒውተሮች?

✓ አዎ

✓ እሺ ኮምፒውተር ምን አይነት ላፕቶፕ እና ይሄ ጠረጴዛ ላይ ኮምፒውተር ?

✓ የራሱ ላፕቶፕ አለ

✓ የራሱ ማለት የማን?

✓ የራሱ የካሚል

✓ የካሚል መሆኑን በምን አወቁ?



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እራሱ ተናግሯል በሰዓቱ
- ✓ የኔ ኮምፒውተር ነው አለ?
- ✓ አዎ የራሴ ላፕቶፕ ነው ብሎ ማለት ነው
- ✓ ከዚህ ውጪ ላፕቶፑ ላይ የካሚል የሚል ተጽፎበት ነበር?
- ✓ እሱን አላስተውስም
- ✓ እሺ ከዛ የጠረጴዛ ኮምፒውተር አለ ሌላ ትልቅ ?
- ✓ አዎ
- ✓ እዛ የጠረጴዛው ኮምፒውተር ላይ ማን ተቀመጠበት?
- ✓ መጀመሪያ እራሱ ከግል ላፕቶፑ እንዳልኩት መጀመሪያ እንደተናገርኩት ሁለት ፔጅ ወረቀት አወጣ
- ✓ ቆይ ካሚል ላፕቶፑ ጋር ሄዶ ተቀመጠ እዛ ኮምፒተር ጠረጴዛ ያለው ኮምፒተር ላይ ማን ተቀመጠ?
- ✓ እ
- ✓ ጠረጴዛ ላይ ያለው ትልቁ ኮምፒውተርጋስ ማን ተቀመጠ?
- ✓ ማንም አልተቀመጠም
- ✓ እሺ እርስዎ የትጋ ተቀመጡ?
- ✓ አጠገቡ ነበርኩ
- ✓ ከማን?
- ✓ ከካሚል አጠገብ እኔና ሌላኛው ታዛቢ ነው የተጠራነው ማለት ነው
- ✓ ስሙን ያውቁታል የታዛቢውን?
- ✓ አላውቀውም
- ✓ እሺ መርማሪው ፖሊስስ የት ተቀመጠ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ መርማሪው ፖሊሱ ከፊት ለፊታችን ነው የቆመው

✓ ማለት ጠረጴዛ የሌለው ቦታ ላይ ነው የተቀመጠው ?

✓ አቤት

✓ ጠረጴዛ አጠገቡ አልነበረም መርማሪው ጋር ?

✓ አልነበረም ጠረጴዛ

✓ እሺ ስንት ፖሊሶች ነበሩ እዛ?

✓ ሁለት

✓ ሌላ ሲቪል የለበሰ ሰው አልነበረም ከፖሊሶች ውጪ?

✓ ከሁለቱ ውጪ ማንም የለም

✓ ቅድም የራሱን ኢሜል እና ፓስ ወርድ ተጠቀመ አሉ በምን አወቁ?

✓ መጀመሪያ እራሱ ተናግሯል

✓ ማለት ፓስወርዱ ምን እንደሆነ እርስዎ ያውቃሉ?

✓ አላውቅም

✓ የኢሜል አድራሻውስ ምን እንደሆነ ያውቃሉ?

✓ እሱንም አላውቅም

✓ ስለዚህ የራሱ ይሁን ወይም ፖሊስ የሰጠው ይሁን በምን ያውቃሉ?

✓ እራሱ ጽፎ ጽፎ መሆኑን ብቻ ነው የማውቀው

✓ ስለዚህ እሱ ሲጽፍ ስላዩት ነው?

✓ የራሴ ነው ብሎ ጽፎ ነው እንትን ያለው

✓ ማን ጠይቶት ነው የራሴ ነው ያለው ?

✓ እራሱ የራሴ ኢሜል ብሎ ጽፎ ነው

✓ ገና ሲቀመጥ ነው ሳይጠየቅ ?



965

2816

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ኖ መጀመሪያ እኮ እራሱ ተናግሮ ነው ወደዛ ነገር የገባነው

✓ ማለት ካሚል መጣ ጠረጴዛ ላይ ቁጭ አለ ከዛ ምን አለ?

✓ በቃ ከኢሜል አድሬሴ የወጣ እራሱ ኢሜሉን ፃፈ ፓስወርዱን ፃፈ ሲያወጣ ነው የማውቀው

✓ ፕሪንተሩ የትጋ ነበረ ?

✓ እዛው ከኮምፒውተሩ አጠገብ

✓ ጠረጴዛው ላይ?

✓ አዎ

✓ ፕሪንት አረገ ሲሉ ምን ማለት ነው?

✓ እስክሪን ላይ የታየውን ነገር ወደ ወረቀት በወረቀት ማውጣት ማለት ነው

✓ ከፕሪንተሩ ሲወጣ ስላዩ ነው ፕሪንት አረገ የሚሉት ?

✓ ይመስለኛል እራሱ ያዘዘውን መሰለኝ በፕሪንተሩ የሚወጣው

✓ እሺ ሳሙኤል ነሐሴ 25 ቀን ምን ቀን ነበረ የዋለው እለቱን ታስታውሳለህ ሰኞ ማክሰኞ ?

✓ አስታውሰዋለሁ አርብ ቀን ነበረ

✓ እሺ ፖሊሱ መጀመሪያ ውስጥ ግቢ ውስጥ እያለሁ ነው የጠራኝ ብለሃል እና ሲጠራህ ካሚል ከእራሱ ኮምፒውተር ላይ ሰነዶችን የሚያወጣ መሆኑን ነገሮህ ነው አደለም ታዛቢ ትሆናለህ ያለህ ?

✓ አዎ

✓ እሺ ወደ ቢሮ ስትገባ ካሚል አልነበረም አደል ቢሮ ውስጥ ?

✓ አልነበረም አብረን ነው የገባነው

✓ እሺ ታዛቢ ያው ሌላ ከአንተ ጋር አብሮ ስሙን አላውቀውም ያልከው ሌላውም ታዛቢ እኩል አብሯችሁ ነው የገባችሁት አደል ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ
- ✓ እሺ ስትገቡ ቢሮ ውስጥ ቢሮ ውስጥ ሌሎች ፖሊሶች ነበሩ አደል ?
- ✓ ማንም አልነበረም
- ✓ ቢሮ ውስጥ ስትገባ ላፕቶፑ  ቢሮ ውስጥ ነበረ ?
- ✓ እሱን አላስታውስም
- ✓ ኂላ ላፕቶፑ ከየት መጣ ታዲያ ?
- ✓ ማለት እረጅም ጊዜ ነው ቅድምም ተናግሬያለሁ
- ✓ ስለዚህ ላፕቶፑ ከየት እንደመጣ አታስታውስም ?
- ✓ ቴብል ላይ እንደነበረ ነው የማስታውሰው ከነእንትኑ
- ✓ ይኸውልህ ስማይ ቀስ ብለህ ጥያቄውን እየተረዳህ መልስልኝ ስትገባ እምታስታውሰውን

  ደግሞ ስትገባ ጠረጴዛው ላይ ላፕቶፑን አይተኸዋል ?
- ✓ ስንገባ አዎ ነበረ
- ✓ እሺ ሌሎችም ኮምፒውተሮች ነበሩ?
- ✓ አንድ ላፕቶፕ እና ከአጠገቡ ሌላ ኮምፒውተር አለ
- ✓ አንድ ኮምፒውተር ብቻ ሌላ የለም?
- ✓ እና ፕሪንተሩ
- ✓ እሺ ካሚል እዛ ቢሮ እያላችሁ ነው የመጣው አደል?
- ✓ አዎ
- ✓ ከየት እንደመጣ ታውቃለህ ካሚል?
- ✓ ሌላ ወታደር ልብስ የለበሰ ፖሊስ ይዞት ሲመጣ አይቻለሁ
- ✓ ከየት እንደመጣ አታውቅም ?
- ✓ እሱን አላውቅም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እሺ. ፖሊሱ ይዞት ሲመጣ እጁ በካቴና ታስሮ ነበር አደል?
- ✓ አልታሰረም
- ✓ ካሚል ከመጣ በኋላ ኮምፒውተሩን እንዲከፍት ከመደረጉ በፊት የኢሜል ልውውጡን ለመርመር ፖሊስ የፍ/ቤት ትእዛዝ ያለው ስለመሆኑ ለካሚል አልነገረውም አደል?
- ✓ እሱን አልሰማሁም
- ✓ ሲነገር አልሰማህም ወይስ አልተነገረውም ፖሊሱ የኢሜል አድራሻህን የኢሜል መረጃዎችህን ለመመርመር የፍ/ቤት ትእዛዝ አለኝ ብሎ ለካሚል የፍ/ቤት ትእዛዝ አላሳየውም አደል?
- ✓ ዞሮ ዞሮ የነገረው ነገር የለም ግን
- ✓ እሺ. ከኮምፒውተሩ እና ከኢሜል አድራሻው ላይ የሚያወጡት ሰነዶች በካሚል ላይ በማስረጃነት የሚቀርቡበት ስለመሆኑ አልተነገረውም አደል?
- ✓ ለማ ለሱ?
- ✓ ለካሚል?
- ✓ ተነግሮታል
- ✓ በማስረጃነት ቀርቦብሃል ተብሏል ?
- ✓ ተነግሮታል ያው
- ✓ ሰምተሃል አንተም?
- ✓ ሰምቻለሁ
- ✓ እሺ.
- ✓ ላፕቶፑ የካሚል የራሴ ነው ሲል ሰምቻለሁ ብለሃል ይሄ ላፕቶፕ በምን ሁኔታ ተይዞ እንደመጣ ለካሚል አልተነገረውም አደል?
- ✓ ይደገምልኝ



2019 968

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ላፕቶፑ የካሚል ካሚልም የኔ ነው ሲል ሰምቻለሁ ብለሃል እና ያ ላፕቶፕ በምን ሁኔታ ተይዞ የመጣ ላፕቶፕ እንደሆነ አልተነገረውም አደለም ካሚል?
- ✓ አዎ
- ✓ በሰነዶቹ ላይ እንግዲህ ያው ሰነዶቹ የወጡት ካሚል ከኔ ኢሜል እና ከኔ ኮምፒውተር የወጣ ነው ብሎ እያረጋገጠ ሲፈርም እኛም ፈርመናል ብለሃል በዚህ ሰዓት ሰነዶች ላይ ከመፈረማችሁ ውጪ በሌላ በቃለ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ታውቃለህ አደል?
- ✓ አዎ
- ✓ በቃለ ጉባኤ ተዘጋጅቶ ሰነዶቹ ተመዝግበው አልተፈራረማችሁም አደል?
- ✓ አልተፈራረምንም ከኢሜሉ
- ✓ እሺ ከዛ ካሚል ወዴት እንደተመለሰ አታውቅም አንተ አደል ?
- ✓ አቤት?
- ✓ መቀረጽ ስላለበት በድምጽ እንደትነግረኝ ነው ወዴት እንደተመለሰ አታውቅም አንተ አደል?
- ✓ ይቅርታ አልሰማሁም ይደገምልኝ
- ✓ ከዛ ካሚል ወዴት እንደተመለሰ አታውቅም አንተ አደል ?
- ✓ አቤት
- ✓ መቀረጽ ስላለበት በደምጽ እንድትነግረኝ ነው ወዴት እንደተመለሰ አታውቅም አደል?
- ✓ ይቅርታ አልሰማሁም ይደገምልኝ
- ✓ የት ሄደ ከጨረሳችሁ በኋላ?
- ✓ እሱም ተነስቶ ይዘውት ወጡ እኛንም ይዞን የመጣው መርማሪ ይዞን ሄደ
- ✓ እሺ ካሚል በሽብርተኝነት የተከሰሰ መሆኑና ወይም የተጠረጠረ መሆኑን ያ ኮምፒውተሩ በሚፈተሽበት ቀን አልተነገረውም አደል ?



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ለማን ለካሚል
- ✓ እ?
- ✓ ተነግሮታል
- ✓ በሽብርተኛነት ነው የተከሰሰከው ተብሎ ተነግሮታል?
- ✓ ተነግሮታል
- ✓ አቶ ሳሙኤል እርስዎ በታዛቢነት በሄዱበት ወቅት ስንት ሰዓት ነበር ?
- ✓ አቤት
- ✓ ለታዛቢነት በሄዱበት ወቅት እና የታዘቡ የነበሩት ስንት ሰዓት ላይ ነበር?
- ✓ አምስት ዘጠኝ ተኩል  አስር ሰዓት አካባቢ
- ✓ ስንት ሰዓት ፈጀ እርስዎ እየታዘቡ ስንት ሰዓት ቆዩ እስከ ስንት ሰዓት ቆዩ ?
- ✓ አስራ አንድ ሰዓት ጨርሰሺ ወጥቻለሁ
- ✓ ከእርስዎጋ ሌላ ታዛቢ ነበር ብለዋል እሱ ከእርስዎ እኩል ነው ገብቶ አብራ አንድ ሰዓት የወጣው ?
- ✓ አብረን ገባን አብረን ወጣን
- ✓ ሲቪል የለበሰ ፖሊስ መጥቶ ጠየቀን ብለዋል እና ሲጠይቆት አብረው ነበሩ ከዚህ ታዛቢጋር አብሮ አንድ ላይ ነው የጠየቃችሁ አብረን ነበርን ስላሉ ማለት ነው ?
- ✓ አይ አንተዋወቅም አጋጣሚ ነው እኔን ካናገረኝ በኋላ ነው እሱን ሄዶ ያናገረው
- ✓ እርስዎ ከዚህ ታዛቢጋር የተገናኙት የት ነው ?
- ✓ ከታዛቢ ጋር የተገናኘነው ወደ ቢሮ ስንሄድ
- ✓ ማን ነው ቀድሞ የደረሰው ከእርስዎና ከዚህ ታዛቢ?
- ✓ ከማንጋር
- ✓ እርስዎ ኖት ወይስ ሌላኛው ታዛቢ ነው ቀድሞ እዛ ቢሮ የደረሰው ?



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ቢሮ ላይ አብረን ነው የደረስነው አንድ ላይ ይዞን ነው የሄደው
- ✓ እኮ ሲያገኛችሁም አንድ ላይ ነበራችሁ ማለት ነው ?
- ✓ አንተዋወቅም አጋጣሚ ነው በቃ እኔን አናገረኝ እንደገና ሄዶ እሱን በጉን አናገረው ከዛ ኑ ብሎ አንድ ላይ ይዞን ሄደ
- ✓ ኦኬ እርስዎን ሲያናግሮት እና ጨረሰና ሌላ ሰው ፍለጋ ሄደ ወይስ ይሄንን ለፍ/ቤቱ ግልጽ እንዲያደርጉ ነው ማለት አብረን ነው የደረስነው ስላሉ የት አግኝቷችሁ ነው አብራችሁ ወደ ቢሮ የደረሳችሁት?
- ✓ እሱን ግቢ ውስጥ ነው ያገኘሁት እሱንም
- ✓ እሺ አጠቃላይ ክፍሉ ውስጥ የተገኙ ሰወች ብዛት ስንት ነበር?
- ✓ /የማይሰማ/
- ✓ ካሚል ሚሊተሪ የለበሰ ሰው ይዞት መጣ ብለሃል መጥቶ የት ተቀመጠ ?
- ✓ /ግልጽ ያልሆነ/
- ✓ እሺ ከአንተና ከዛኛው ታዛቢ አንፃር ካሚል ለአንተ ነው ለዛኛው ታዛቢ ነው ቅርብ የነበረው አቀማመጣችሁ እንዴት ነበረ ለማን ይቀርብ ነበር?
- ✓ ለኔ ይቀርብ ነበር
- ✓ ስለዚህ አንተ ከዛ ያኛው ታዛቢ ከዛ ካሚል ነው አቀማመጣችሁ አንተ በታዛቢው እና በካሚል መሃል ነበርክ ማለት ነው?
- ✓ ኖ እኔ በዚህ በኩል ነኝ ካሚል በመሃላችን ነው
- ✓ በግራ ወይስ በቀኝ?
- ✓ እኔ የነበርኩት በቀኝ ነው
- ✓ ስለዚህ አንተ በቀኝ በኩል ከሆንክ ያኛው ታዛቢ ከካሚል ቀጥሎ ነው የተቀመጠው ማለት ነው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ በግራ በኩል አዎ
- ✓ ላፕቶፑ በገመድ ወይም በኬብል ከሌላ ኮምፒውተርጋ ተገናኝቶ ነበር?
- ✓ አልተገናኘም
- ✓ ኢሜሉም ከላፕቶፑ ላይ ነው የከፈተው?
- ✓ አደለም በኮምፒውተሩ ነው የተከፈተው
- ✓ በየትኛው ኮምፒውተር?
- ✓ ቅድም ገልጨዋለሁ ፊት ለፊት የነበረው ሌላ ኮምፒውተር ነበረ
- ✓ አሃ ከላፕቶፑ አደለም ማለት ነው ኢሜሉን የከፈተው ከሌላ ኮምፒውተር ላይ ነው ?
- ✓ አዎ
- ✓ ስለዚህ ከላፕቶፑ ላይ ምንም የተገኘ ነገር የለም ከዛ ከኮምፒውተሩ ላይ ነው?
- ✓ ከላፕቶፑ ላይ ሁለት ፔጅ
- ✓ ሁለት ሉክ ወጥቷል ፕሪንት አድርጕ አውጥቷል
- ✓ ከላፕቶፑ ላይ ሁለት ፔጅ ወጥቷል ?
- ✓ አዎ
- ✓ ከላፕቶፑ ላይ ሲያወጣው አይተሃል አንተ?
- ✓ አይቻለሁ
- ✓ ካሚል አጠገብህ ነበረ የተቀመጠው?
- ✓ አጠገቤ ነው አዎ
- ✓ ከላፕቶፑ ላይ ከየቱ አካል ላይ ነው ያወጣው ለምሳሌ ዴስክ ቶፕ ፋይል አለ ?
- ✓ እሱን አላስታውስም



969

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ከኮምፒውተሩ ላይ ኢሜሉን የከፈተው በፈቃደኛነትነው እና ዘና ብሎ ነው እኔ የማውቀው ነገር የለም ቀደም ብሎ ተነግሮታል ብለህ ነበር ቀደም ብሎ ተነግሮታል ያልከው ነገር ምንድን ነው እንዲከፍት ቀደም ብሎ ተነግሮት ነበር ማለት ነው?

✓ የተነገረው እኛ ባለንበት ማለት ነው

✓ አይ አሁን ይሄንን አንብቤልህ አዎ ብለኸኛል እኔ የማውቀው ነገር የለም ቀደም ብሎ ተነግሮታል አንተ ያልከውን ቃል በቃል ጽፌ ነው ያነበብኩልህ ቀደም ብሎ የተነገረው ነገር ምንድን ነው ቀደም ብሎ የተነገረው ነገር አለ ማለት ነው አደል አንተ የማታውቀው አደል?

✓ ይሄን እንቃወማለት የተከበረው ፍ/ቤት

✓ ቆይ እስቲ ጥያቄው ምንድን ነው እሱ ያለውን ላስተካክለውና ከዛ ተነስታችሁ አስተካክሉት እሱ ያለው ምንድን ነው እኔ ቀደም ብሎ ተነግሮት ይሁን አላውቅም እኔ ተነግሮታል ብዬ ነው የማስበው አይነት ነገር ነው እንትኑ እንጂ በቀጥታ ቀደም ብሎ ተነግሮት የሚል ብቻ አልነበረም

✓ የተከበረው ፍ/ቤት እኔ ቃል በቃል ጽፌ ነው እየጠየቅኩት ያለሁት

✓ ልክ ነው አንዳንዴ ያው በአምሮዋችን አንዳንዴ አምሮዋችንም ቢሆን ይመርጣል በራቡ እንግዲህ እንደዛ ተመርጦ ካልሆነ የመለሰው በዚህ መንገድ ነው ምስክሩ እራሱ አሁን ይሄንን ሊመልስ ይችላል ምንድን ነው ያልከው እስቲ ንገረን ቀሪው የተነገረው ነገር ምን እንደሆነ አላውቅም እኔ

✓ እሺ እናንተ እያላችሁ የተነገረውን ?

✓ እኛ እያለን ግን የተነገረው ይሄ ከኢሜልህ ስታወጣ የምታወጣው ነገር እንደሚያስጠይቅህ በወንጀል እንደሚያስጠይቀውና እሱም አምኖበት እንደሆነ ያን ነገር እሚያመጣው ማለት ነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ቀደም ብሎ የተነገረው ነገር ስለ አንተ የምታውቀው ወይ ይኑር አይኑር አታውቅም?
- ✓ አላውቅም
- ✓ ከካሚል ኢሜል ኢሜል ወጡ እያልክ እየመሰከርክ ነው ኢሜል ምን እንደሆነ ታውቃለህ?
- ✓ አውቃለሁ የራሱ የሆነ አድሬስ ነው የራሱ የሆነ አካውንት ነው
- ✓ እሱ ለሌላ ሰው መላክ ይችላል ሌሎች ለሱ መላክ ይችላሉ አደል በኢሜል ?
- ✓ ይችላሉ አዎ
- ✓ እሺ አይ በደንብ የምታውቀው ጥያቄም ቢሆን እኛ ስለሚጠቅም ነው የምንጠይቅህ ቀላል ጥያቄ ተጠየቅኩ ብለህ እንዳታስብ የተላከለት ያየኸው ከኢሜሉ ወጣ የተባለው ነገር ለሱ የተላኩ ናቸው አደል ?
- ✓ እሱን አላስታውስም
- ✓ አላየህም ?
- ✓ ከኢሜሉ መውጣቱን ነው የማውቀው እኔ አስታውሳለሁ
- ✓ ቅድም አቃቤ ሕግ ጠይቀውህ ይዘቱ ምን እንደሆነ አላውቅም ብለሃል ዝም ብለህ ነው እያነሳህ ስትፈርም የነበረው አደል እሱ ስለፈረመ?
- ✓ ማለት ግልጽ ይደረግልኝ
- ✓ ማለት ይዘቱን ሳታይ ነው አደል ስትፈርም የነበረው ምክንያቱም በጣም ብዙ ወረቀቶች እንደወጡ ነገርኸናል ከኢሜሉ ስለዚህ ያንን ሁሉ ጊዜ ያንን ሁሉ ለማንበብ አንድ ሰዓት ስለማይበቃህ እሱ ሲፈርም ዝም ብለህ ነበር አደል ስትፈርም የነበረው?
- ✓ ዝም ብዬ አደለም የፈረምኩት
- ✓ ስንት ገጽ ወረቀቶች ወጡ ከኢሜል ውስጥ ?
- ✓ በአማርኛ ከመቶ በላይ ናቸው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ በሌላ ቋንቋ?
- ✓ እንግሊዘኛ አለ አረብኛ አለ
- ✓ የሦስቱንም ቋንቋዎች ይዘት ተረድተህ አደለም አደል የፈረምከው ያው ስለተፈረመበት ነው ሦስቱንም ቋንቋዎች አትችልም አደለም?
- ✓ አልችልም አማርኛ ነው
- ✓ አማርኛ ብቻ ነው የምትችለው?
- ✓ አዎ
- ✓ ከኢሜሉ ወጣ ያልከው ነገር ለሱ የተላከለት ይሁን ሌላ ሰው የላከለት ይሁን ማረጋገጥ አትችልም አደል?
- ✓ ተጠይቋል እሱ ሌላ ጥያቄ
- ✓ ቅድም አቃቤ ሕግ ጠይቀውህ ስትመሰክር ከኢሜል አድራሻዬ የወጣ ነው ብሎ ፈርሟል ነው አደል ያልከው ?
- ✓ አዎ
- ✓ እዛ ወረቀት ላይ ከኢሜል አድራሻዬ የወጣ ነው እያለ እየፃፈ ነው ሲፈርም የነበረው?
- ✓ አዎ
- ✓ እርግጠኛ ነህ ይሄን እየፃፈ ነው የፈረመው?
- ✓ እርግጠኛ ነኝ
- ✓ አንተስ ምን እያልክ ነው ጽፈህ ስትፈርም የነበረው ?
- ✓ ከኢሜል አድሬሱ ሲወጣ አይቻለሁ
- ✓ ሁሉም ከኢሜል አድራሻው ውስጥ የወጡ ወረቀቶች ላይ ከኢሜል አድራሻዬ የተገኘ ነው እያለ ነው የፈረመው አደል?
- ✓ አዎ



2826

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ሳሙኤል ይሄ ከላፕቶፑ ተገኘ ያልከውን ሁለት ገጽ የኔ አደለም አልፈርምም ብሎ ሲከራከር ነበረ አልነበረም?
- ✓ አልተከራከረም
- ✓ እሺ ከኢሜሉ ውስጥ ሲወጣ ወደኔ የተላከ ነው እንጂ የኔ ስላልሆነ ይሄን አልፈርምም ብሎ ሲከራከር አልነበረም ለፖሊሱ ወዳንተም እኮ ሊላክ ይችላል ወደኔ የተላከ ስለሆነ እንድፈርምበት አልገደድም ይሄን አልፈርምም እያለ ሲል አልነበረም ?
- ✓ ምንም አይነት ክርክር አልተከራከረም በፍቃደኛነት ነው ሲያደርግ የነበረው
- ✓ እዛ የነበራችሁበት ክፍል ውስጥ ሴት አልነበረችም ?
- ✓ አልነበረችም
- ✓ ኮምፒውተር ላይ ቁጭ ያለች አልነበረችም?
- ✓ አልነበረችም
- ✓ ኮምፒውተሩ እምቢ አላለም አላስቸገራችሁም ነበር ፕሪንት ስታደርጉ ?
- ✓ በፍፁም አላስቸገረንም
- ✓ ሌላ ኮምፒውተር ቀይራችሁ ነበር በመካከል ?
- ✓ አልቀየርንም
- ✓ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ከካሚል ጉን ነው የነበርከው አንተ?
- ✓ ሲጀመር ጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ አብሬ ነበርኩ
- ✓ ከካሚል ጉን ቁጭ ብሎ ሲያዝ የነበረ ኮምፒውተሩ ላይ ሲከፍት የነበረ ሰው አልነበረም ባለሙያ ?
- ✓ አልነበረም
- ✓ ጨርሰናል
- ✓ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ



ፌደራል

973

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ድጋሚ የለንም
- ✓ እሺ እናመሰግናለን ምስክር ይመለሱ
- ✓ በእውነት ለመመስከር
- ✓ በእግዚአብሔር ስም
- ✓ ምያለሁ
- ✓ ለምክርነት ነው የመጡት?
- ✓ አዎ
- ✓ ስሞን ያው የአባት ስም ሌላ ዝርዝር ሳይጨምሩ የራሶን ስም ብቻ ይነግሩናል
- ✓ ብሩ
- ✓ ስንተኛ ነው አቃቤ ሕግ
- ✓ 174ኛ
- ✓ እሺ 66ኛ ላይ ደርሰናል 174 በማስረጃ ዝርዝር ላይ የተጠቀሱ እነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አቶ ብሩ?
- ✓ ሃሰን አቢ
- ✓ እሺ ሌላ ሰው አለ ?
- ✓ ሌላ ሰው የለም
- ✓ ሃሰን አቢን ያውቁታል?
- ✓ አላውቀውም
- ✓ እሺ ምን ፈፀመ ብሎ ነው ምንድን ነው ያዩት እርስዎ ?
- ✓ በወቅቱ ሐምሌ 13 ቀን ነው ጠዋት ሦስት ሰዓት ላይ አዛው አካባቢ ስንቀሳቀስ በነበረበት ጊዜ ፖሊሶች በዛን ጊዜ የፍ/ቤት ማዘዣ ይዘው በታዛቢነት ትፈለጋለህ እና እዛ ተገኝልን አሉኝ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ምን ሲያደርጉ ?

✓ ቤቱን ለመፈተሽ ነው በአሸባሪነት ተጠርጣሪ ስለሆነ በአካባቢው ተገኝተው ታዘብልኝ አሉኝ

✓ እሱን ነው የታዘቡት?

✓ አዎ

✓ እሺ ዋና ጥያቄ አቃቤ ሕግ

✓ እሺ ምስክር እምጠይቆትን እየሰሙ በዝርዝር ያስረዳሉ ከጊዜው ይጀምራሉ ጊዜውን ያስታውሳሉ?

✓ ጊዜው በሦስት ሰዓት ላይ ነው

✓ አደለም ከቀኑ ይጀምሩ?

✓ ቀን ሦስት ሰዓት ጀምረን እስከ ስድስት

✓ ሐምሌ 13 ነው ያሉት አደለም?

✓ አዎ

✓ ሐምሌ 13 ቀን 2004

✓ አዎ እንደዛ ብለው ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም ስንት ሰዓት ላይ ነው ?

✓ ከ ሦስት እስከ አምስት ስድስት ነው

✓ እሺ ክፍለ ከተማውስ?

✓ ክ/ከተማ ኮሣፊ ቀራንዮ ነው

✓ ቀበሌው?

✓ ቀበሌ 15/16

✓ የት ነው የሰፈሩ ልዩ መጠሪያ

✓ አስኮ አካባቢ ነው አስኮ አዲስ ሰፈር የሚባለው

✓ እሺ አሁን በጠቀሱልኝ ጊዜና ቦታ እርስዎ ምን እያረጉ ነበር?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እዛ አካባቢ ስንቀሳቀስ ነበረ

✓ አኬ እሺ ምን ተፈጠረ?

✓ የተፈተሸው በአቅራቢያው በበት ውስጥ የነበረ መጀመሪያ

✓ ቆይ እርስዎ እየተንቀሳቀሱ ነበረ ከዛ ምን ሆነ ደረጃ በደረጃ ያስረዱን?

✓ እየተንቀሳቀስኩ ባለበት ጊዜ እሚፈተሽ ሰው ስላለ ተጠርጣሪ ሰው ስላለ እዛ አካባቢ መፈተሽ አለብን ነው

✓ ማን ነው ያለው?

✓ አሊ አብዲ የሚባለው

✓ አደለም ማን ነው ያለው እንደዚህ?

✓ ፖሊሶች ናቸው

✓ ለእርስዎ እንደዚህ አሉት ፖሊሶች?

✓ ፖሊሶቹ ለኔም ለአካባቢው ለሴትየዋም የሰውየው ሚስትም እዛው አለች ተነበበላት እና ከተነበበላት በኋላ ቤቱ ይፈለጋል ተባለ እና ለብርበራው እሷ ቀድማ ገባች ያው ሁላችንም ሌሎቹ ቆሙ የተወሰኑት ፖሊሶች ከእኛ ጋር አብረው ገቡ ፍተሻ ተከናወነ ፍተሻው ላይ ሲዲ ተገኘ ሲዲ

✓ ተከሳሽ ነበሩ በወቅቱ?

✓ ተከሳሽ የለም

✓ ሃሰን የለም?

✓ ሃሰን አልነበረም በዛን ጊዜ

✓ ፖሊሶች ለእናንተ ዝም ብለው ነው እንበርብር ያሉት ?

✓ አቤት

✓ በምንድን ነው እናንተ ለምን ብላችሁ አልጠየቃችሁም?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ተጠርጣሪ ስለሆነ
- ✓ በምን?
- ✓ በአሸባሪነት ተጠርጣሪ ስለሆነ እንድትታዘቡልን በትክክለኛ ለመስራት ታዘቡልን ብለው ነው ያስገቡን
- ✓ ምን አሳዩዋችሁ?
- ✓ የፍ/ቤት ማዘዣ አሳዩን ፍርድ ቤት ማዘዣውን አየን
- ✓ የተከበረው ፍ/ቤት ያው ተመልሷል ብሎ እንደሚያልፍብን እያሰብን ነው
- ✓ አቤት
- ✓ ተመልሷል ተብሎ እንደሚታለፍብን እየሰጋን ነው ተቃዉሟችንን የምናቀርበው ምን አሳያችሁ የሚለው
- ✓ ቆይ እስቲ አሁን ከተመለሰው ባንደክም ነው ጥሩ የሚሆነው ካልተመለሰ እሱ ነው ምክንያቱም ወደኋላ ይሄን ጥያቄውን እንቀበላለን እስቲ
- ✓ ምንድን ነው ተቃውሞው
- ✓ ምን አሳዩዋችሁ እያሉ ነው እየመሩ እየጠየቁ ያሉት ስለዚህ መሪ ነው መሰረዝ አለበት
- ✓ ቅድሚያ ተመልሷል እኮ ቅድሚያ ከዚህ ጥያቄ በፊት ካልተከታተሉ እንጂ የፍ/ቤት ትእዛዝ ተነቦልን ለእኛም ለሴትየዋም ብሎ ነው የጀመረው ሲጀምር
- ✓ ይቅርታ የተከበረው ፍ/ቤት አልሰማሁም
- ✓ ሲጀምር ለእኔም ለሴትየዋም የፍ/ቤት ትእዛዝ ተነቦልን ነው
- ✓ እኮ እኔ የተቃወምኩት ይሄንን ጥያቄ ነው ምን አሳዩዋችሁ የሚለውን ነው የተቃወምኩት
- ✓ እስቲ ጠይቁ
- ✓ አሁን የተከበረው ፍ/ቤት አጠያየቃቸውን በዚህ ጥያቄ ላየም ከዚህ በኋላ በሚጠይቁት ላይም የተከበሩ አቃቤ ሕግ እንዲያስተካክሉ ነው መሪጥያቄ አይጠይቁ ነው ያልኩ



http://ethcriminalawnetwork.com/

ያለነው ስለዚህ መሪ ነው ይሄ ፍ/ቤቱ ከፈቀደ ይሄንንም ጥያቄ መጠየቅ የለበትም እያልን ነው እየተቃወምን ያለነው

- ✓ ምን አሳዩዋችሁ የሚለው
- ✓ አዎ ምን አሳዩዋችሁ የሚለው አጥንተው የገቡትን እንዲናገሩ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ግልጽ ነው
- ✓ መልስ
- ✓ እሺ ብይን ተሰጥቷል ከአካሄድ ጋ የተያያዘ ስለሆነ ምላሽ ማስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም አንደኛው እዚህ ላይ ያየነው ነገር መሪ ነው አደለም የሚል ነው ምን አሳዩዋቸው የሚለው ለመጀመሪያው መሪ አደለም መአት ነገር አለ የሚታየው ግን መሪ አደለም ለነገሩ ግን ከዛን በፊት ቅድም የተናገርነው ነገር አለ የፍ/ቤት ትእዛዝ ለሴትየዋም ለእኛም ተነቦልን የተወሰኑ ከውጪ ቀሩ የተወሰኑ ፖሊሶች ደግሞ አብረን ገባን ብለው ነበረ ምስክሩ ሲጀምሩ እና እሱን ያለመከታተል ነው አንድም መሪም አደለም መሪም ቢሆን አንዴ ከተመለሰ መሪ የሚባል ኮንሰፕት የለም አንዴ የተመለሰው እዛው ከሆነ ካልተለየ ምንም ይሄ ኮንሰፕት የለም ያስጠኑትን እንዲመልሱ የሚለውም ተገቢ አደለም እሱን ያስተካክሉ ያስጠናል አያስጠናም ይሄ የኛ ቢዝነስ አደለም ስላስጠናው እዚህ የችሎቱ አካል ያልሆነውን ነገር ብታርሙት ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥሉ
- ✓ እሺ ምስክር ካቆሙበት ይቀጥሉ ምንድን ነበር ያሳዩዋችሁ ፖሊሶች ለታዛቢነት ሲጠሯችሁ?
- ✓ ያሳዩን እኛን
- ✓ እስቲ ምስክር ወደዛ ይዙሩና
- ✓ ያሳዩን ነገር መጀመሪያ ደብዳቤ ነው ብዬሃለው የፖሊስ ትእዛዝ ነው የፍ/ቤት
- ✓ ቆይ እስቲ አንዴ ምስክር ቆይ አንዴ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እና መጀመሪያ ፖሊሶቹ ገና ሲመጡ እኛን ሲያነጋግሩን በፍ/ቤት በኩል በአሸባሪነት ተጠርጣሪ ስለሆኑ በፍ/ቤት ትእዛዝ ይኸው ደብዳቤ ይዘናል እና ቤቱን እንፈትሻለን አሉ እኛም ደብዳቤውን አየን ወደቤቱ ተጠጋን መጀመሪያ ሴትየዋን በር ላይ አገኘናት ሴትየዋም ተነበበላት እሷም ተረዳች ቀድማ ገባች የተወሰኑ ሰወች ገብተን ፍተሻው ተጀመረ ተፈተሸ ይሄ ነው እኔ የማውቀው

✓ ስለዚህ ያያችሁት የብርበራ ትእዛዝ ነበር የፍ/ቤት የብርበራ ትእዛዝ እንደዛ ነው ያሉኝ አደለም ?

✓ በደንብ አልሰማሁም

✓ ፖሊስ ያሳያችሁ ምንድን ነው ?

✓ ያሳየው ጽሁፍማ የፍ/ቤት ትእዛዝ ነው

✓ የምን ትእዛዝ?

✓ የብርበራ ትእዛዝ ቤቱ እንዲበረበር ማለት ነው

✓ የማን ቤት እንዲበረበር?

✓ የሃሰን አቢ ቤት

✓ የሃሰን አቢ ቤት ይበርበር የሚል ነገር አለው ትእዛዙ ላይ ?

✓ ትእዛዙ እንደዛ ነው አዎ

✓ ጥሩ ይሄን ትእዛዝ ካያችሁ በኋላ ወዴት ሄዳችሁ ?

✓ ወደቤት ገባን አመራን ሴትየዋም

✓ ወደማን ቤት?

✓ ወደ ሃሰን አቢ ቤት ገባን ሴትየዋም እሬት ቀደመች ገባች

✓ ሴትየዋ ማን ናት?

✓ ሚስትየዋ ናት ሚስቱ ነኝ አለች



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ የማን?
- ✓ የሰውየው ሚስት ነኝ ነው ያለችው
- ✓ ስለዚህ የሰውየው የሴትየዋ አይበሉ የተከሳሽ ሚስት ?
- ✓ የተከሳሽ ሚስት ነች አዎ የተከሳሽ ሚስት ነኝ አለች መጀመሪያም የተቀበለችን እሷ ነች ሚስቱ ነኝ አለች ያው ፊት ቀደመች እና ቤቱን ማስፈተሽ ጀመረች በሷ መሪነት ቤቱ ፍተሻ ተጀመረ ፍተሻው ተጀመረ
- ✓ ምን ምን ፈተሻችሁ ?
- ✓ የተለያዩ ቦታዎች ሳጥኖች አሉ ኮመዲኖች አሉ እነዛ እየተከፈቱ ታዩ የተለየ ሲዲ ወደ 10 ሲዲ ተገኘ እንደገና ካሴትም ደግሞ የተወሰነ ተገኘ ቁጥሩንም አላስታውሰው ተገኘ ከዛ ሞባይል ተገኘ
- ✓ ሞባይል ስንት ተገኘ?
- ✓ ሁለት ሞባይሎች
- ✓ ቆይ ይጠብቁኝ አቶ ብሩ ሞባይል ሁለት ነው የተኘው ?
- ✓ ኮመዲኖ ስር ነው የተገኘው ቁምሳጥኑ አጠገብ
- ✓ የዚህን የተያዘውን ሞባይል አይነት ያውቃሉ?
- ✓ ሁለቱም ሞባይል ነው የተያዘው እንግዲህ ምን እንደሚል እሱን ሁለቱ ተያዘ መጨረሻ ላይ መጽሄት ነበረ የተለያዩ መጽሄቶች
- ✓ ቆይ ወደ መጽሄት ሳንሄድ ሞባይሉ የማነው ተባለ ?
- ✓ የነሱ ነው እዛው ነው የተገኘው
- ✓ እዛው ነው የተገኘው የሃሰን አደለም ብሎ የተቃወመ ሰው አለ?
- ✓ የእኛ ነው አለች እሷ የተከሳሽ ሚስትየእኛ ነው አለች ሞባይሉ ተመዘገበ ተያዘ
- ✓ ሲዲዎች 10 ነው ያሉኝ?



2534 980

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ሲዲዎች ወደ 10 ሲዲዎች ገደማ ተያዙ ሌላም ደግሞ የሆነ ካሴት አለ መጽሄት የተለያዩ

✓ ምን የሚሉ?

✓ በአማርኛ እና በአረብኛ

✓ የሚያስታውሱት አለ ምን የሚል ነው መጽሄቱ ?

✓ ብዙ አላስታውሰውም

✓ እርእሱን የሚያስታውሱት አለ?

✓ እርእሱ ብዙም አላስታውሰውም

✓ ይቀጥሉ እሺ ሌላ?

✓ እና እንደገና መጽሃፍት እና አጀንዳዎች ተገኙ አጀንዳዎች ነበሩ እና የተለያዩ ስም ዝርዝር የያዙ እንደ ፔሮል ነገር ሁሉ ነገር ነበር ስም ዝርዝር በእንግሊዘኛ የተፃፉ ስም ዝርዝር የያዙም ነገሮች ነበሩ ስም ዝርዝር እና ገንዘብንም የሚያመላክቱ እንትኖች ነበሩ

✓ ጥሩ እነዚህ የተገኙ ነገሮች ላይ ብርበራውን ካጠናቀቃችሁ በኋላ ምን አደረጋችሁ?

✓ ብርበራው ከተጠናቀቀ በኋላ አንድጋ ቁጭ አልን የተከሳሽ ሚስትም ተቀመጡ እነሱ ባሉበት ቃለ ጉባዔ ተያዘ በእያንዳንዱ መጽሄት ላይ በተገኘው ነገር ላይ ምልክት አደረግን ቃለ ጉባዔ ተያዝን ተፈራረምን

✓ ምልክት ማለት?

✓ ተፈራርምንበት እያንዳንዱ ላይ ቃለ ጉባዔ ነው በመጽሄቱም ላይ እያንዳንዱ ገጽ ላይ አጀንዳው የተለያየ ገጽ ላይ ፊርማችንን አኖርን ያን አጠቃለሉ ፖሊሶችም ሄዱ ቀድመው እኛም ሄድን የተከሳሽ ሚስትም ተመልሳ ወደቤቷ ገባች

✓ ይሄ የሆነው ስንት ሰዓት ላይ ነው?

✓ ወደ ስድስት ሰዓት ላይነው መጨረሻው

✓ ዋና ጥያቄ አበቃሁ



2835

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እሺ. የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ

✓ አቶ ብሩ ቅድም ቀኑ ሐምሌ 13 ቀን ነው ብለዋል ይሄን ቀን በምን አስታወሱት?

✓ አቤት

✓ ቀኑን በምን አስታወሱ ሐምሌ 13 ማለት ?

✓ እንዴት አላስታውስም ማስታወስማ አለብኝ እኮ ቀኑንማ አስታውሳለሁ በደንብ

✓ እኮ እንዴት ?

✓ በዛን ጊዜ ፍተሻ የተካሄደበት ስለሆነ ቀኑን ማስታወስማ አለብኝ በዛን ጊዜ እኔ በእያንዳንዱ ቀን የሰራሁት ስራ እኮ የማስታውሰው እኔ ነኝ በዛን ጊዜ መሆኑን እንዴት አላስታውስም

✓ መዝግበው ነበር?

✓ ለምን እመዘግባለሁ ባልመዘግብም እኮ

✓ ቆይ ምስክር እስቲ

✓ እሺ.

✓ አሁን ይሄ የምስክርነት ስለሆነ የሚጠየቁትን ብቻ ነው ለምን እንደዚህ ሆነ ምናምን የሚል ጥያቄ መልሰው አይጠይቁ ስለዚህ እርስዎ ይጠየቃሉ ሲጠየቁ ጥያቄውን ብቻ የሚችሉ ከሆነ ይመልሳሉ የማያስታውሱ ከሆነ አላስታውስም ማለት ነው

✓ እሺ. ቅድም ታዘብ ተባልኩና ለመታዘብ ሄድኩ ብለው ነበረ ፖሊስ ሲያናግሮት የፍ/ቤት እንዳሳዮት ገልፀው ነበረ እና ይሄ የፍ/ቤት ትእዛዝ ከየት የመጣ ነው ከየትኛው ፍ/ቤት የታዘዘ እንደነሆነ አይተዋል ?

✓ ከከፍተኛ ፍ/ቤት የተፃፈ ደብዳቤ ነው ማህተም ያለው ቤቱን ለመፈተሽ የሚያስችል የተፃፈ ደብዳቤ ነው

✓ ከየትኛው ፍ/ቤት?



2536

982

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ እንግዲህ እኔ እያንዳንዱን ፍ/ቤት እኔ የማውቀው ፍ/ቤት መሆኑን ነው እንጂ ከዚህኛው ከዚህኛው ፍ/ቤት ለማለት ለይቼ ለማወቅ አልችልም
- ✓ አላነበቡትም?
- ✓ ያነበብኩት ከፍ/ቤት መሆኑን ነው እዚህኛው መደበኛ ፍ/ቤት እዚህኛው መደበኛ ፍ/ቤት የሚል መለየት አልችልም ብዙም አላስታውስም
- ✓ ከአዲስ አበባ ፍ/ቤት ነው የሚለው ከመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው የሚለው ከፌደራል ነው ከየትኛው ካነበቡ እንግዲህ ማየት አለቦት ?
- ✓ ከፌደራል ፍ/ቤተ ነው
- ✓ ቆዩ ቅድም ቀን አስታውሳለሁ አሉ ጉብዝናዎን በሱ ገለፁ አሁን የሚያነቡትን ነገር እንዴት አያስታውሱም?
- ✓ ቆይ ቆይ እሱም ተገቢ አደለም ጠበቃ ማን ነው ስሞ ሃሰን ሁሴን እሱም ተገቢ አደለም ጉብዝናዎን ገልፀዋል እካ ማለት ምስክሩን ሃራስ ማድረግ ነው ስለዚህ እንደነዚህ አይነት ነገሮችን አስወግደው ጥያቄውን ቢጠይቁ
- ✓ ከየትኛው ፍ/ቤት እንደሆነ አያስታውሱም?
- ✓ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እኮ ነው ያልኩት
- ✓ ትእዛዙ ላይ ምን የሚል ነገር አይተዋል የሚያስታውሱት ምን ይፈተሽ ይላል?
- ✓ ተጠርጣሪ ስለሆኑ ቤታቸው እንዲፈተሽ ይላል
- ✓ ቤታቸው ውስጥ ምን ምን ይፈተሽ ይላል?
- ✓ ይሄ ይሄ ይፈተሽ የሚል ነገር ዲቴል የለም ቤታቸው ግን የተገኘው እንዲፈተሽ ነው
- ✓ የተገኘው ነገር ነው የሚለው ?
- ✓ አዎ በተለያዩ ነገሮች
- ✓ ይሄን ትእዛዝ ማን ነው ያመጣው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አቤት
- ✓ ትእዛዙን ለኔም ለባለቤቱም አነበበ ብለው ነበር ማን ነው ያነበበው ?
- ✓ በወቅቱ የነበው ፖሊስ ነው
- ✓ስንት ነበሩ ፖሊሶቹ ?
- ✓ ወደ 6 ናቸው ብዙ ናቸው እዛ አካባቢ የነበሩት
- ✓ ስድስት ?
- ✓ አዎ የተወሰኑት ገብተዋል የተወሰኑት ግን ውጪ ነበሩ
- ✓ አጠቃላይ ስንት ይሆናሉ?
- ✓ ስድስት ይሆናሉ ከስድስት አያንሱም ቁጥራቸውን ግን ብዙ አላስታውስም
- ✓ ቤቱጋ የወሰዶት ፖሊስ ነው አደል?
- ✓ አብረን ሄድን
- ✓ እኮ አብራችሁ ሄዳችሁ ቤቱን ያሳዮት ግን ፖሊስ ነው?
- ✓ ፖሊስ ነው አዎዋ
- ✓ እርስዎ ከዛ በፊት ይሄን ቤት አያውቁትም?
- ✓ አላውቀውም እኮ ቤቱን እራሱ
- ✓ ስለዚህ ይሄ ቤት የሃሰን መሆኑን ያወቁት ፖሊስ ስለነገሮት ነው ?
- ✓ አይደለም ሚስቱ እራሷ ነች የተናገረችው
- ✓ ምን አለች?
- ✓ ይሄ የሃሰን ቤት ነው ወይ ስትባል የሱ ቤት ነው ብላ አራሷ ነች የተናገረችው
- ✓ ስለዚህ እርስዎ ያወቁት በምን ምክንያት ነው በመናገሯ?
- ✓ አዎ እሷ ተናገረች ከሷ የበለጠ ሰው የለም እሷ ነች መናገር ያለባት
- ✓ ባለቤቱስ መሆኗን በምን አወቁ እሷ እኔ ነኝ ከማለት ውጪ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ባለቤቱ ነኝ አለችን እሷ
- ✓ እኮ ከዚህ ውጪ ያወቁበት ነገር አለ ሌላ ?
- ✓ እኔ አላውቅም እሷ ስላለች ብቻ ነው
- ✓ እነዚህ የተገኙ ካሴቶች እና ሞባይሎች ተፈርሞባቸው ነው መጨረሻ ላይ ?
- ✓ ሞባይሎቹ እና ካሴቶቹ ላይ ምናቸው ላይ ይፈረማል
- ✓ አልተፈረመም እላያቸው ላይ ?
- ✓ በዝርዝር ተጠይቀው በቃለ ጉባዔ ተይዘው ዝርዝራቸው ላይ ግን ተነበ ፈርመናል ዝርዝራቸው ላይ
- ✓ እነሱ ላይ አልተፈረመም?
- ✓ እነሱ ላይ ምናቸው ላይ ይፈረማል
- ✓ እኮ አልተፈረመም በሉኛ ወይ ተፈርሟል ወይ አልተፈረመም ተፈርሟል?
- ✓ ምኑ ላይ
- ✓ ሲዲው ላይ ወይ ሞባይሉ ላይ ምልክት መደረጉ ወይ መፈረሙ እንዴት እንዲያረጋግጡልኝ ነው እቃዎቹ ላይ ዝርዝሩን ሳይሆን የተከበረው ፍ/ቤት እቃዎቹ ላይ በራሱ ከሃሰን አቢ ቤት ስለመገኘቱ ተፈርሟል ወይ ነው እቃዎቹ ላይ ነው ጥያቄው ለምሳሌ ሞባይሉ ላይ ምልክት ተደርጐ ከሆነ ሲዲው ላይ እንደዚሁ
- ✓ እስቲ ምኑ ላይ ነው የፈረማችሁት እሱን ንገሩን ቅድም የጀመሩት ነገር ነበ የሆነ ዝርዝር ተቀምጦ ነው ያላችሁት ምንድን ነው ?
- ✓ ሞባይሉ ላይ ሊፈረም አይችልም
- ✓ እኮ ምኑ ላይ ነው የፈረማችሁት እሱን ንገሩን በቃ ?
- ✓ ዝርዝሩ ላይ ነው
- ✓ ዝርዝሩ ላይ ነው የፈረማችሁት?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ዝርዝራቸው ላይ እያንዳንዱ እቃ ዝርዝር ላይ ሞባይሉም ላይ የተለያዩ ዝርዝሮች ላይ በቃለ ጉባዔ ተይዟል ቃለ ጉባዔዎቹ ላይ ፈርመናል
- ✓ ቀጥሉ
- ✓ አቶ ክብሮም ቀደም አቃቤ ሕግ መጀመሪያ ላይ ሲጠይቆት ብርበራው ከ ሦስት እስከ አምስት ቆይቷል ይላሉ እና አሁን መዝጊያው ላይ ደግሞ ስድስት ሰዓት ላይ ብርበራው ተጠናቀቀ አሉና ሁለት የሚጋጩ ነገሮች ስለነገሩን የትኛውን እንያዝ የትኛው ነው ትክክል ገብቶታል ጥያቄው?
- ✓ እኔን ነው በደንብ ድገምልኝ እስቲ
- ✓ እሺ መጀመሪያ ምስክርነቶን ሲጀምሩ አቃቤ ሕግ ቀኑን ሰዓቱን ሲጠይቆት ከሦስት እስከ አምስት ብለው ተናገሩና አሁን ደግሞ መጨረሻ ላይ አቃቤ ሕግ ሲጠይቆት ብርበራው ስንት ሰዓት አለቀ ሲሎት ስድስት ሰዓት አሉ እና እነዚህ ሁለቱ የተለያዩ ስለሆኑ ትክክለኛው የቱ ነው ?
- ✓ የሰዓቱ መጀመሪያ እና መጨረሻው እኛ ጠዋት ሦስት ሰዓት ነው የጀመርነው እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ነው ከዛ አካባቢ አጠናቀን የወጣነው ብርበራው እስከ አምስት ሰዓት ሊያልቅ ይችላል መጨረሻ ግን ተፈራርመን የወጣነው ስድስት ሰዓት ላይ ነው
- ✓ እሺ በብርበራ ሂደት ውስጥ በተከሳሽ ባለቤት ወይም በእርስዎ ቃል በእርሷ መሪነት ፍተሻው ተከናወነ አሉ እርሷ ምን ምን እየመራች ፍተሻው ተከናወነ እሷ ነች ስትመራው የነበረው ማለት ?
- ✓ በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ በሩን እየከፈተች ሳጥኑን እየከፈተች እምታሳየን እሷ ነች ማንም የነሱን እቃ አደለም ያደረገው እያንዳንዷን በር በሩንም የምትከፍተው እሷ ነች ፍራሹንም የምታስነሳ እሷ ነች ሳጥኑንም የምትከፍተው እሷ ነች እሷ ያሳየችን ያመጣችውን ነው ያየነው



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ቤት ውስጥ ስንት ክፍሎች ተፈተሹ በዚህ ሁኔታ ?
- ✓ ሦስት ፎቅ ነው ያለው ከምድር ጀመርን እስከ 3ኛ ፎቅ ድረስ ሄደን ፈተሽን
- ✓ እስከ 3ኛ ፎቅ ድረስ ፈተሹ ?
- ✓ አዎ
- ✓ ስንት ክፍሎች ፈተሻችሁ በዚህ መንገድ ?
- ✓ አላስታውሳቸውም ክፍሎቹን
- ✓ እሺ ቅድመምም ሲመሰክሩ ሞባይሎች ተገኙ ኮመዲኖው ስር ብለዋል የተከሳሽ ሚስት የእኛ ነው አለችን የእኛ ነው አለች እንጂ የሃሰን ነው አላለችም አደል የእኛ ነው ነው አደለ ያለችው?
- ✓ በመጀመሪያ ደረጃ ሞባይሉ ብቻ አደለም ፐስፖርቱም
- ✓ አይ ጥያቄዬ አሁን ቀጥታ ጥያቄዬ ስለሞባይሉ ነው ሞባይሉ የእኛ ነው አለች እንጂ የሃሰን ነው አላለችም አደል ይቺን ብቻ መልሱልኝ አዎ ወይም አይ ?
- ✓ የእኛ ነው ነው አደለም ያለችው ?
- ✓ ሞባይሉ ያለችው የሃሰን ነው የራሱ ነው የሚፈተሸው የሱን እቃ ነው እኮ የምንፈትሸው
- ✓ አሁን እሳቸው ያው መርተው እየጠየቁ ነው መርተው እየጠየቁ ስለሆነ ወይ ነው ወይ ብላለች ወይ አላለችም ወይ ያለችው ይሄ ነው ብሎ በቀጥታ እነዚህን ከሦስት አንዱ መመለስ ነው
- ✓ የእኛ ነው ነው አደለ ያለችው ሞባይሉ የእኛ ነው አለች ብለው ለአቃቤ ሕግ ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል ይሄንኑ ነው አደለም ያለችው ?
- ✓ መጀመሪያ ስትገባ ፖሊስ እየጠየቃት ያለው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አይ ዝርዝሩ ሳይሆን አሁን ሞባይሉ ቅድም እኮ አቃቤ ሕግ ጠይቆት ምላሽ ሰጥተዋል ለዚሁ ጥያቄ ይሄንኑ የማረጋገጥ ብቻ ነው ሌላ ነገር አዲስ ነገር አደለም የጠየቅኖት ሞባይሉ የእኛ ነው አለች እንጂ የሃሰን ነው አላለችም አደል?
- ✓ ሞባይሉ የሃሰን ነው ነው ያለችው እንጂ የእኛ ነው ብቻ አደለም ያለችው
- ✓ እሺ የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አይቼዋለሁ ብለዋል አንብበውታል በደንብ?
- ✓ ተጠይቄ መልሻለሁ እሱን
- ✓ ቆይ ምስክር ተረጋጉ እርስዎ ቀስ በሉና የሚጠየቁትን ጥያቄው አግባብ ነው ፍ/ቤት ያለውን ይቀጥላሉ አይቆጡ
- ✓ እሺ ትእዛዙ ላይ የሃሰን አቢ ቤት ይበርበር ይላል ብለው ለአቃቤ ሕግ ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል ምኑ ነው መግቢያው ላይ ነው ወይስ መጨሻ ላይ ነው ይበርበር የሃሰን አቢ ቤት ይበርበር የሚል ጽሁፍ አለ ?
- ✓ የሃሰን አቢ ቤት ይበርበር ትክክል ነው
- ✓ የሃሰን አቢ ቤት ይበርበር ይላል?
- ✓ በዚህ በዚህ ወንጀል የተጠረጠረ ስለሆነ ቤቱ ይፈተሽ ይበርበር ነው
- ✓ የፍ/ቤቱን ትእዛዝ መግቢያ ላይ መጀመሪያ ላይ ምንድን ነው የተፃፈዉ?
- ✓ አቤት
- ✓ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ መጀመሪያ ላይ የተፃፈው ነገር ምንድን ነው አንብቤዋለሁ ስላሉ ምንድን ነው መጀመሪያ ወረቀቱን ሲያዩ የሚያነቡት ምንድን ነው ?
- ✓ እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ በአሁኑ ሰዓት ማስታወስ አልችልም
- ✓ አንብቤዋለሁ ስላሉ መግቢያው ላይ የተፃፈውን ነገር
- ✓ እሺ ሌላ ካለ
- ✓ ማስታወስ አልችልም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ቆዩ ቆዩ
- ✓ ትእዛዙ ላይ የፍ/ቤት ማህተም አይተዋል ?
- ✓ ተጠይቋል ይሄ ሌላ ካለ
- ✓ የዳኛ ፊርማ አለ ትእዛዙ ላይ?
- ✓ እያንዳንዱን ቃላት መዘርዘር አልችልም በወቅቱ ግን አንብቤ አንብበነው
- ✓ የጠየቅኩት አይቻለሁ ወይም አላየሁም ነው ስለዚህ አሁን የዳኛ ፊርማ አይተዋል ለሚለው ጥያቄ ካዩ አይቻለሁ አዎ ካላዩ አላየሁም ይሄንን ነው
- ✓ በደንብ አይቻለሁ እኮ አልኩኝ አይቼ ነው ወረቀቶች ላይም የገባነው
- ✓ ስለዚህ የዳኛ ፊርማ አይተዋል ማለት ውነው?
- ✓ ትዝ አይለኝም እሱ
- ✓ ፖሊሶች ከዛ በኋላ ሃሰን ቤት ይቆዩ አይቆዩ የሚያውቁት ነገር አለ?
- ✓ እ
- ✓ ፖሊሶች ሃሰን ቤት ለሁለት እና ለሦስት ቀን ይቆዩ አይቆዩ የሚያውቁት ነገር አለ እርስዎ?
- ✓ ማንም አልቆየም በዛኑ ቀን ነው የወጡት
- ✓ ከእርስዎጋ መውጣታቸውን ነው ያዩት?
- ✓ አዎ አብረን ወጣን እሷ ቤቷን ዘጋች እኛ ወጣን እነሱም ወጡ እኛም ወጣን
- ✓ እሺ ቁጭ ብለን ተፈራረምን አሉ ምን ላይ ቁጭ አላችሁ ?
- ✓ ወምበር አወጣችልን እደጅ ላይ ቁጭ ብለን ተፈራረምን እሷም ፈረመች መጀመሪያ እሷ ነች የፈረመችው
- ✓ ቪዲዮ እየተቀረፀ ነበረ አልነበረም?
- ✓ ቪዲዮ እየተቀረፀ አልነበረም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ሌላ ሰወች ነበሩ ቤት ውስጥ 6 ፖሊስ ብቻ ነው የነበረው ሌላ አልነበረም ቤት ውስጥ ሌላ ሰወች አልነበሩም ?

✓ አላስታውሳቸውም

✓ አላስታውስም ማለት ቁጥራቸውን ነው ነበሩ አልነበሩም ወይስ ?

✓ ቁጥራቸውን አላስታውስም

✓ ነበሩ?

✓ ሊኖሩ ይችላሉ ብዙ ሰወች ግን ትዝ አይሉኝም ማን ማን ናቸው ብዬ መለየት አልችልም

✓ እሹ አቶ ክብሮም ቅድም ቤት ውስጥ የተለያዩ ሲዲዎች ተይዘዋል ብለዋል ሲዲዎቹ ውስጣቸው ያለውን ይዘት ምን እንደሆነ አላያችኋቸውም አደል ?

✓ ወደ ምርመራ አልሄድንም በአይናችን አየን እንጂ እያንዳንዱን እየከፈትን ያዳመጥንበት ነገር የለም

✓ ሲዲ መሆኑን ብቻ ነው ያያችሁት?

✓ ሲዲ መሆኑን አይተናል

✓ መጽሃፎችም ተይዘዋል ብለዋል መጽሃፎቹ መጽሃፍ መሆናቸውን ብቻ ነው እንጂ ይዘታቸውን አላያችኋቸውም ?

✓ የተለያየ ጽሁፍ አላቸው ጽሁፎቹ የተለያዩ ናቸው

✓ ዝርዝሩን አላያችሁም?

✓ ዝርዝሩ እያንዳንዷ ዝርዝር ውስጥ አላየንም

✓ እሺ ካሴትም ተይዟል ብለዋል ካሴቱንም በተመሳሳይ ይዘቱ ምን እንደሆነ አላያችሁትም ?

✓ ምንም ያየነው ነገር የለም በዛ ወቅት የነበሩት ተቆጠሩ ተቆጥረው ዝርዝራቸው ተፃፈ እንጂ እያንዳንዳቸውን ገልጠን አላየንም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አጀንዳዎችም ተይዘዋል ብለዋል አጀንዳዎቹም ውስጣቸው ምን እንደተፃፈባቸው እና ውስጣቸው ያለው ይዘት ምን እንደሆነ አላያችሁትም አደል?
- ✓ እያንዳንዱ ውስጡ ይታወቃል አጀንዳ ውስጥ አንድ ትልቅ አጀንዳ ውስጥ ያለ
- ✓ አይ ይኸውሎት አቶ ክብሮም አይታችሁ ከሆነ
- ✓ አጀንዳውን ነው ያየነው
- ✓ አጀንዳ መሆኑን ብቻ ነው ?
- ✓ የተለያየ ጽሁፍ አለበት ዉስጡ የስም ዝርዝር አለበት ግን እያንዳንዱን ሰው /ግልጽ ያልሆነ/ በማወቅ አይቻልም በአሁኑ ሰዓት
- ✓ እኮ አላያችሁትም ውስጡን ዝርዝሩን አላያችሁትም አደለም አቶ ክብሮም አላያችሁትም አሁን እኮ ማረጋገጥ ብቻ ነው ?
- ✓ ቆዩ እስቲ ይሄ ለእኛ ግልጽ ነው ይለፍና ሌላ ካለ
- ✓ እሺ እርስዎ በሚያውቁት ማለት ነው ከተያዘው ሲዲ ውስጥ በመንግስት እንዳይሰራጭ የተከለከለ ሲዲ አልተያዘም አደል ?
- ✓ አቤት
- ✓ እንዳይሰራጭ ወይም ለሕብረተሰቡ እንዳይከፋፈል የተደረገ ሲዲ የተያዘ ስለመሆኑ አላዩም አደል?
- ✓ ተቃውሞ አለን
- ✓ ቆዩ ቆዩ እስቲ ይሄ ምስክሩ ከመለሰው ውጪ ስለሆነ ከዚህም ከዛም አስተያየት አያስፈልግም ሲዲ ኮንቴንቱን አላየንም እያልን ስለሆነ ኮንቴንቱ ካልታየ የት ነው የተከለከለው የት እንዴት ይታወቃል?
- ✓ ምናልባት እላዩ ላይ ባለው ከቨር ወይንም
- ✓ በዚህ ምክንያት ይሄ አያስፈልግም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እሺ

✓ እያንዳንዱን መጽሃፍም ይዘቱን አላየንም የተባለ ሲዲ እንዴት ይታያል ?

✓ ምናልባት በሽፋኑ አይተው ከሆነ ብዬ ነው ፍ/ቤቱ በዚህ መልክ ከተረዳው ፍ/ቤቱን እቀበላለሁ እሺ

✓ ሚስት ስለመሆኗ ቅድም ቤቱን የከፈተችው ሴት ሚስት መሆኗን ነግራናለች ብለዋል እሷ ሚስት መሆኗን ከመናገሯ በፊት

✓ ቆዩ ቆዩ ድጋሚ ነው ይሄ ነገር

✓ ማስታወሻ ያዙ

✓ አቶ ክብሮም ቤት ሲገቡ ሚስት ነኝ ያለች ሴትዮ ከፍታ አስገባችን ሌላ ሰው ነበረ እንዴ ከሚስት ውጪ ?

✓ ተጠይቋል ስንት ሰው ነበረ ከላይ እስከ ታች ተብሎ ስንት ክፍል ነበር ስንት ሰው ነበር ተጠይቋል

✓ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

✓ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ

✓ ድጋሚ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት

✓ ጨርሰዋል እናመሰግናለን መመለስ ይችላሉ

✓ በእውነት ለመመስከር

✓ በእግዚአብሔር ስም

✓ ምያለሁ

✓ እሺ ለምስክርነት ነው የመጣኸው

✓ አዎ

✓ ስምህን የአባትህን ስም ሳትጨምር የራስህን ስም ብቻ ትነግረናለህ



http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ስንታየሁ

✓ 194ኛ ናቸው

✓ እሺ በተሰሙ ዝርዝር 67ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ 194 ላይ የተጠቀሱ የአቃቤ ሕግ ምስክር ቀርበዋል በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አቶ ስንታየሁ?

✓ ኑሩ ቱርኬ

✓ ሌላስ?

✓ በቃ

✓ ኑሪ ቱርኬን ያውቁታል በአካል ?

✓ አዎ በአካል አውቀዋለሁ

✓ መለየት ይችላሉ አሁን?

✓ አዎ

✓ ዝምድና ጥላቻ አሎት ?

✓ የለም

✓ እስቲ ያሳዩን እሳቸው ናቸው?

✓ አዎ

✓ እስትራክት ነው መነጽር ነው ያሉት አሁን?

✓ አረ መነጽር አላረገም እስትራይፕ ሹራብ የለበሱ ነው ያልኩት

✓ እሺ ምስክሩ 12ኛ ተከሳሽን ጠቁሞ አሳይቷል እንዴት ነው ምን ሲያደርግ ነው ያዩት ኑሪ?

✓ ኑሪ ቱርኬ ማለት ያው ፖሊስ መጀመሪያ ፖሊስ ነው ያገኘሁት በፀረ ሽብር ይጠረጠራል እና እዚጋ ትብብር ያርጉል አለ እና በፀረ ሽብር ወንጀል ተጠርጣሪ ነው

✓ እሺ



2547

993

http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ ትብብር ያርጉልን አሉ እኔ ወደ ሰፈሬ እየገባሁ ነበር ወደ መኖሪያ ቤት አካባቢ እሺ እተባበራለሁ አልኳቸው ደብዳቤውን አሳዩን የፍ/ቤት ትእዛዝ ደብዳቤ እንዳለ አየሁኝ አረጋገጥኩኝ ገባሁ

✓ ከዛ ምን አዩ?

✓ በታዛቢነት የአንቱ ቃል ወይም የእርስዎ ቃል

✓ ምን ታዘቡ?

✓ ቤቱ ሲከፈት እቃዎቹ ምናምን ሲወጡ

✓ እሺ ዋና ጥያቄ አቃቤ ሕግ

✓ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ስንታየሁ ይሄ መቼ ነበረ ጊዜው ቀኑ መቼ ነበር ወሩ ቦታው ልዩ ቦታው የት ነበረ እስቲ ?

✓ ሐምሌ 12 አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 3

✓ አመተምረቱ መቼ ነው ?

✓ 2004

✓ የት አካባቢ ነው ?

✓ ልዩ ቦታው  አዲስ አበባ ት/ቤት ወይም እስላም መቃብር የሚባል ቦታ

✓ እሺ የማን ቤት ነበረ የሚታየው ?

✓ ቤቱ  የት/ቤቱ ቁርአን ት/ቤት

✓ እሺ እስቲ ምንድን ነው በዚህ እለት መጀመሪያ ማንን አገኙ ምን ተባሉ እርስዎ ?

✓ መጀመሪያ ፖሊስ አገኘሁ ፖሊስ ጠየቀኝ

✓ ምን ብሎ ጠየቆት?

✓ ተባበረኝ በፀረ ሽብር ወንጀል ይጠረጠራል ተከሳሽ አለኝ ከዛ በኋላ ያንን ደብዳቤ አየሁን

✓ ምንድን ነው ደብዳቤው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ደብዳቤው የፍ/ቤት ትእዛዝ ነው
- ✓ እስቲ ምን ይላል የማን ቤት ወይም ምን ይፈተሽ ይላል ?
- ✓ ያው በፀረ ሽብር የተገኙት ማንኛውም ነገር ቤት ውስጥ የተገኙት ነገር ማንኛውን ነገር እንዲያዝ
- ✓ እሺ መጀመሪያ ፖሊስ እርስዎን ካገኘ በኋላ ወዴት አመራችሁ?
- ✓ እኛ ከፖሊሱ ከተገናኘን በኋላ እኔም ምስክሩ ታዛቢዎችም አሉ ያው የኔና የእርስዎ ቃል ፍ/ቤት ይቀርባል አሉ ከፖሊሶቹ ጋር ቁልፍ መጣ የቤቱ ቁልፍ ተቆለፈ ገባን ወደ ቤቱ
- ✓ ማን ከፈተ ?
- ✓ ቢሮ የአቶ ኑሪ ቢሮ ተከፍቶ ማለት ነው
- ✓ ማን ነው የተከፈተው?
- ✓ እራሳቸው
- ✓ አቶ ኑሪ ነበረ ?
- ✓ አዎ
- ✓ እሺ ከዛ ገባችሁ?
- ✓ ገባን ያለውን እቃ እነዚህ እቃዎቹን መዘርዘር ከተፈለገ እነዚህ ሲዲ ከ60 በላይ ካሴቶች የቴፕ ካሴቶች ከ20 በላይ እና እነዚህን ቁጥራቸው በእጅ የተፃፉ ጽሁፎች በእጅ የተፃፉ ቁርጥራጭ ወረቀቶች እና ደብዳቤ በእጅ በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ ደብዳቤዎች እና የተለያየ ፍላሽ የቪዲዮ ካሴት ምናምን ይሄ ሁለት ካሴቶች የቪዲዮ ካሴቶች እና እና አል እስላም የሚል ሰለፊ የሊል ካሴቶች እና አል እስላም የሚል እና ሰለፊ የሚል ጋዜጦች ምናምን ተመልክተናል ተመልክቻለሁ
- ✓ እሺ እነኚህ እስቲ ከሚያስታውሷቸው በእጅ የተፃፉ ወይም ደግሞ በጽሁፍ የተፃፉ ካዩዋቸው ውስጥ የሚያስታውሱት አለ ያነበቡት ወይም ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እሱም ስለፈረማቸው እኔም ስለፈረምኩኝ ምናልባት ፊርማውን አይቼ ካልሆነ በስተቀር አላስታውሳቸውም

✓ አይ የዛን እለት ከተገኙት ውስጥ ማለቴ ነው እንዲህ ከተገኙ ሰነዶች ወይም ደግሞ በብርበራ እርስዎም ታዛቢ ሆነው ከፈረሙስ ከሚያስታውሷቸው በጽሁፍ የተፃፉ የሚሏቸው እርእሶቹን ምናምን የሚያስታውሷቸው ነገሮች አሉ?

✓ አልእስማኤል የሚል ምንድን ነው አልእስላሚክ

✓ እሺ በምንድን ነው የተፃፈው እሱ?

✓ እሱ እርእስ ነው መጽሄት ነገር ነው

✓ እሺ ሌላስ ?

✓ እና ደግሞ ሰለፊ ጋዜጣ በቁጥር 2

✓ ማን ጋዜጣ ነው ያሉት?

✓ ሰለፊ ጋዜጣ

✓ እሺ ሌላስ የተፃፈ ?

✓ በእጅ የተፃፉ ብዙ ጽሁፎች አሉ ግን አላስታውሳቸውም እነሱን

✓ አያስታውሷቸውም ?

✓ አዎ

✓ ምን ያህል ይሆናሉ እነኚህ የተዘጋጁ ጽሁፎች ያሏቸው በገጽ በብዛት እንደዚህ የሚታወቁ ናቸው ?

✓ ምኖቹ ?

✓ እነኚህ የተፃፉ ጽሁፎች ያሏቸው በገጽ ብዛታቸው ይታወቃል?

✓ በገጽ ብዛታቸውን አላውቀውም አላስታውሰውም

✓ ትዝ አይሉትም?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ አዎ
- ✓ እሺ እነዚህ ሲዲስ ያሏቸው?
- ✓ ሲዲ ከስድሳ በላይ ይሆናል ሲዲው ካሴቱ ከሃያ በላይ
- ✓ ሲዲዎቹ ስለምን እንደሆኑ እሱ የተናገረው አለ ወይም የተነገራችሁ?
- ✓ አዎ ተጠርጣሪው ያሉት የዛ ሰዓት ላይ ምንድን ነው ቁርአን ነገር ነው ምናምን በነሱ እምነት እማዳምጣቸው ነገር ነው ምናምን ነው ያለው
- ✓ እሺ ሌሎቹስ የተገኙት ቅድም አሁን ሞባይል ብለዋል አደል ስለ ሞባይል ምንድን ነው ?
- ✓ እ?
- ✓ ስለሞባይሉስ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- ✓ ስለ ሞባይልምን የተገኘ አለ ቅድም ስለ ሞባይል ብለዋል ሞባይልስ ተገኝቷል ?
- ✓ ሞባይል አንደ ኖኪያ ሞባይል ተገኝቷል
- ✓ እሺ ምን አለ እነኚህ የተገኙት በሙሉ ስለነሱ ተጠየቀ የማን ነው ሲባል ምን አለ ተጠይቋል የማን እንደሆነ?
- ✓ የራሳቸው እንደሆነ ተናግረዋል
- ✓ የራሱ መሆኑን ገልጿል እሺ እነኚህ እያንዳንዳቸው ከተገኙ በኋላ ምን አደረጋችሁ ?
- ✓ ከተገኘ በኋላ
- ✓ ስለመገኘታቸው ስለመበርበሩ ?
- ✓ ያው ሲገኙ ካሴቶች ምናምን ተሰባስበው ቪዲዮ እንደተቀረፁ ያው እንደመረጃ ምናምን ነው ተብሎ ተቀረፀ
- ✓ እሺ እናንተስ ያረጋችሁት አለ ታዛቢዎች ?
- ✓ እኛ አቶ ኑሩ ሲፈርሙ እኔ ደግሞ ተቀብያቸው እሳቸው ከፈረሙ በኋላ እኔ እፈርማለሁ ሌላ ደግሞ አንድ ታዛቢ አለ እሱም ይፈርማል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ እሺ. ምን ብለው ፈረሙ እሳቸውስ?

✓ እሳቸው ያው ንብረቱ የኔ እንደሆነ ብለው

✓ የራሳቸው እንደሆነ አረጋግጠው ፈረሙ ?

✓ የራሳቸው እንደሆነ

✓ ሌላስ ከእርስዎ ጋር ታዛቢ ነበረ ሌላ ሰው ?

✓ አንድ ታዛቢ አለ

✓ እሱስ ፈርሟል ?

✓ እሱም ፈርሟል እኔ ከፈረምኩ በኂላ ለሱ እሰጠዋለሁ

✓ እና በዚሁ ተጠናቀቀ ማለት ነው ?

✓ አዎ

✓ የነበረው ታዛቢ ማለት የአባቱን ስም ሳትጠቅስ የሱን ታስታውሳለህ ከአንተ ጋር የነበረው ታዛቢ ማለት ነው አብሮ የነበረ የታዘበው የፈረመው ማን ነው እሱስሙን ብቻ?

✓ ስሙን አላስታውሰውም

✓ ትዝ አይልህም?

✓ አዎ ትዝ አይለኝም

✓ እሺ. ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

✓ እሺ. የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ

✓ እሺ. አቶ ስንታየሁ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ አይቼዋለሁ ብለዋል የፍ/ቤቱ ትእዛዝ የማን ቤት ይፈተሽ ነው የሚለው ?

✓ አቶ ኑሩ

✓ የአቶ ኑሩ ቱርኪ ቤት ይፈተሽ ነው የሚለው?

✓ አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ የተፈተሸው የቁርአን ት/ቤት ነው አደል ?
- ✓ የቁርአኑ ቤት እና መኖሪያ ቤት
- ✓ የቁርአን ት/ቤቱ ተፈትሿል?
- ✓ አዎ
- ✓ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ የቁርአኑ ት/ቤት ይፈተሽ አይልም አደል ?
- ✓ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ በአጠቃላይ ኑሪ ቱርኪ ላይ ይፈተሽ ነው የሚለው ይሄ የሱ ቤት ምናምን የሚለውን እንትን አላለም
- ✓ ቆይ አቶ ሽፈራው የምጠይቆት ጥያቄ አሁን የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አሁን በትክክል አይተውታል የፈተሸ የሚለው የኑሩ ቱርኪ ቤት ይፈተሽ ነው የሚለው አደል?
- ✓ አዎ የኑሩ ቱርኪ ቤት ኑሩ በፀረ ሽብር ስለተጠረጠረ ያው እንበረብራለን ቤቱን ያው እምንሰራበት ቦታ እኮ ነው ት/ቤቱ ቢሮ ነው
- ✓ ቆይ አሁን ይሽውሎት እሱን እኮ አደለም
- ✓ ግልጽ ነው ጥያቄው የተባለው የኑሩ ቱርኪን ቤት እንበረብራለን ነው ወይስ ሌላ ነገር ነው የሚለው ይቺን ነው የተጠየቀት ?
- ✓ እንበረብራለን እንጂ
- ✓ እኮ ቤቱን ነው?
- ✓ ቤቱን ነው
- ✓ እኮ ምን አይነት ቤት?
- ✓ እሺ ይፈተሽ ተብሎ የኑሩ ቱርኪ መኖሬያ ቤት ይፈተሽ ነው የሚለው የፍ/ቤቱ ትእዛዝ አደለም ?
- ✓ አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እናንተ ስትፈትሹ የነበረው ደግሞ የአሁኑ ቅድም ገልፀዋል የቁርአን ት/ቤት ፈትሸናል ብለዋል ትእዛዙ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ የቁርአን ት/ቤት ይፈተሽ አይልም አደል ?
- እሱን እኔ ልብ አላልኩም
- አቤት?
- አላነበብኩትም እኔ የቁርአን ቤት ይሁን የመኖሪያ ቤት ይሁን አላወቅኩም ግን ፈትሸናል እኔ ታዛቢ ተብዬ ስታዘብ ቤቱ ይሁን መኖሪያ ቤቱ ይሁን ስራ ቦታ ይሁን አላውቅም
- አቶ ስንተየሁ የሚያውቁትን አውቃለሁ የማያውቁትን አያውቁም አያምታቱኝ እኛን እኔ ግራ ስለገባኝ ነው ትእዛዙን አንብቤዋለሁ አይቼዋለሁ ብለው አረጋግጠው ስለመሰከሩ ትእዛዙ የኑሩ ቱርኪ ቤት ይፈተሽ ይላል ትእዛዙ የቁርአን ት/ቤት ይፈተሽ አይልም አደለም የሚያውቁት ?
- መልሷል እኮ እሱን ልብ አላልኩም ብሏል
- አይልም ነው ልብ አላልኩም ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- እሱን ልብ አላልኩም
- ትእዛዙን እንዴት ነው ያነበቡት ትእዛዙን እንዴት እንዳነበቡ ያስረዱን ልብ አላልኩም የሚለው ነገር ኋላ ለመመርመርም
- እስቲ ቤቱን በተመለከተ እኛ የመዘገብነው እሱን ልብ አላልኩም ነው ለማንኛውም ተመዝግቧል ከተጠራጠራችሁ እሪከርድ ላይ
- አዎ አይ ገብቶኛል ልብ አላልኩም የሚለውን ነገር እንዲያረጋግጡልኝ ነው እንጂ ልክ ነው ነየተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄን እለፉት እና ትእዛዙ አለ እኮ መጨረሻ ላይ ይታያል እሱ ይሄን እለፉት እና
- እሺ የፈተሻችሁት ት/ቤት ያላችሁት ቁርአን ት/ቤት መሆኑን በግልጽ ይታያለ አደለም የቁርአን ት/ቤት መሆኑ የሚያሳይ ነገር አለው አደለም ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

✓ አዎ

✓ መቃወሚያ አለኝ የተከበረው ፍ/ቤት

✓ ትእዛዙ ቤቱ መቼ ይፈተሽ ነው የሚለው አይተውታል ይሄንን ?

✓ ትእዛዙን አነበብኩት እንጂ ወረቀቱን ልብ ብዬ ዲቴል አላነበብኩትም

✓ እሺ ወደቤት ማነው ወደ ቁርአት ት/ቤቱ ገብታችሁ ፍተሻ ሲደረግ ቤቱን የከፈተላችሁ ማን ነበር ?

✓ አራሳቸው ተከሳሹ

✓ እሺ ለትሩ ቱርኪ ይሄ ትእዛዝ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ተሰጥቷችኋል ?

✓ ወረቀት አሳይተውታል

✓ ማሳየት አደለም ተሰጥቷቸዋል እሳቸው እንዲያነቡት ?

✓ አዎ አይተውታል ተሰጥቷቸዋል

✓ እሺ አሁን ቅድም ተያዙ ያሏቸው አሊስላሚክ የሚለው ጋዜጣ ሰለፊ የሚለው ገዜጣ በእጅ የተፃፉ ጽሁፎች ሲዲ ቴፕ እና ቁርአን ሁሉም የተያዙት ከቁርአን ት/ቤት ውስጥ ነው አደል?

✓ ከመኖሪያ ቤቶቹም ተይዟል እኔ አሁን የቁርአን ት/ቤት ይሁን የምን ት/ቤት ይሁን ት/ቤት ነው ግን ከመኖሪያ ቤትም ተይዟል

✓ እሺ ከት/ቤት ውስጥ የተያዘው የትኛው የትኛው ነው እስቲ ከት/ቤቱ ውስጥ የተያዘውን እና ከመኖሪያ ቤት የተያዘውን ?

✓ ከት/ቤት ውስጥ የተያዘው ሲዲዎች ሳይሆኑ ወረቀቶች እነዚህ አልእስላም ሰለፊ የተለያዩ የእጅ ጽሁፍ ደብዳቤዎች እነዚህ እነዚህ ናቸው የተያዙት ከት/ቤት ውስጥ

✓ ከመኖሪያ ቤትስ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ከመኖሪያ ቤቶች ደግሞ ሲዲዎች ካሴቶች እንደገና ድጋሚ ደግሞ ቁርጥራጭ አጫጭር ወረቀቶች እነዚህ ናቸው እና ሞባይል የባንክ ቤት ቼክ ከት/ቤት ነው እነዚህ እነዚህን ተመልክቻለሁ
- ✓ እሺ የተያዙትን ሲዲዎች ይዘት አላያችሁትም አደል ይዘቱ ምን እንደሆነ አላያችሁትም?
- ✓ ይዘቱ ምን እንደሆነ አላየነውም
- ✓ እሺ የቴፕ ካሴቱንም ይዘቱ ምን እንደሆነ አላያችሁትም?
- ✓ አላዳመጥነውም አዎ
- ✓ እሺ አል ኢስላሚክ የሚባለው ጋዜጣ ገበያ ላይ የሚሸጠው ጋዜጣ ነው አደለም በወቅቱ ይሸጥ የነበረው ጋዜጣ ነው አደለም?
- ✓ አል ኢስላሚክ የሚል መጽሄት ነገር ነው
- ✓ መጽሄቱ ገበያ ላይ ይሸጥ የነበረ መጽሄት ነው አደል?
- ✓ አላወቅኩም
- ✓ እሺ ሰለፊ የሚለው ጋዜጣ ገበያ ላይ ይሸጥ የነበረ ጋዜጣ ነው አደል?
- ✓ እሱን ገበያ ላይ ይሸጥ አይሸጥ እኔ አላውቅም ግን እዛ አይቻለሁ
- ✓ በጋዜጣ መልክ የተዓፈ ነው
- ✓ አቶ ስንታየሁ ብርበራ የተካሄደው ቁርአን ት/ቤት እና መኖሪያው ነው ብለዋል ሁለቱም አንድ ግቢ ውስጥ ነው እንዴ ያሉት ?
- ✓ ይለያያል አንድ ግቢ ውስጥ አደለም
- ✓ መኖሪያ ቤቱ የት ነው?
- ✓ ወደ መድሃኒአለም አካባቢ
- ✓ መኖሪያ ቤቱን ማን ነው የከፈተው ?
- ✓ መኖሪያ ቤቱ ቀድሞ የገባው ተጠርጣሪው አቶ ኑሩ ቱርኪ ናቼው ቀድመው የገቡት



2554 1002

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ስትገቡ ማን ነበረ?
- ✓ ሚስትየው ነበረች የከፈተችልኝ አባትየውም ነበረ
- ✓ ቃለ ጉባዔ ስትፈራረሙ የእቃውን አይነት እየቆጠራችሁ ሲዲ ይሄን ያህል ካሴት ይሄን ያህል ብዛቱን እየቆጠራችሁ ነው አደዋለም የተፈራረማችሁት?
- ✓ አዎ

---

- ✓ ስንት ሰዓት ጀምራችሁ ስንት ሰዓት ጨረሳችሁ?
- ✓ ከ11 ሰዓት ጀምረን ሦስት ሰዓት አካባቢ ጨረስን ከምሽቱ
- ✓ ት/ቤቱ ሲፈተሽ ተማሪዎች ነበሩ?
- ✓ ባዶ ነው ወደ መምሸቱ አካባቢ ነው
- ✓ መጀመሪያ የፈተሻችሁት የት ነበር?
- ✓ እ
- ✓ መጀመሪያ የተፈተሸው ት/ቤቱ ነው ቤቱ?
- ✓ ቢሯቸው የእሳቸው ቢሮ ነው
- ✓ ቢሮ ስትሄዱ ፖሊሶቹ ኑሩን ይዘውት ነው የደረስከው አንተ ወይስ አብርህ ከፖሊሶቹጋ ሄዳችሁ ነው ኑሩን ያገኛችሁት?
- ✓ ምኑን?
- ✓ ኑሩጋ ልትፈትሹ ስትሄዱ ማለት ነው አንተ ስትሄድ ወደዛ ቦታ ስትሄድ ከፖሊሶቹ ሄዳችሁ እዛው ኑሩን አገኛችሁት ወይስ ፖሊሶቹ ኑሩን ይዘውት ነው ያገኘሽው?
- ✓ እኔ ስገባ ኑሩ ጥግ ላይ ቆሟል ከፖሊሶች ጋር ከዛ ቁልፍ መጣ የቢሮውን ቁጥፍ ቆለፈ እኛ እያየን ማለት ነው
- ✓ እሺከፈተላችሁ ?
- ✓ ከፈተ እሱ ነው ቀድሞ የገባው ታዛቢዎች ነበሩ ገባን ሁላችንም አብረን አንድ ላይ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ብዛታቸው ስንት ይሆናሉ ፖሊሶቹ ?
- ፖሊሶቹ ሁለት መርመራ ሁለት ተዛቢ ሁለት ደግም ቪዲዮ ማን ካሜራ የሚይዙ ማለት ነው
- 6 ፖሊስ?
- 2 ፖሊስ መርማሪ ፖሊስ ሁለት አለ
- በቃ ሌላ ሌላ ፖሊስ አልነበረም?
- እኔ ታዛቢ አለሁ ሁለታችን ነን ታዛቢ ቪዲዮ የያዙ አሉ
- እኮ ፖሊሶቹ ከሁለቱ ውጪ ሌላ ፖሊስ አልነበረም ?
- አሃ የሚጠብቁማ ውጪ ላይ ይኖራሉ እንጂ አካባቢውን የሚጠብቁ የመጡ
- ማለት ከነሱጋ አብረው የመጡ ሌሎች ፖሊሶች ነበሩ እንዴ?
- አላየሁም ሌላ ፖሊስ አላየሁም
- እርስዎ ያዩት ግን እነዚህ ሁለቱን ብቻ ነው?
- እነዚህ ነው ያየሁት
- እሺ ቢሮውን ፈትሻችሁ ጨርሳችሁ ስትሄዱ ከነሱጋ እነዚህ ሁለቱ ብቻ አብረዋችሁ ነው የሄዱት ?
- አደለም በመኪና ነው የሄድነው ሁለት ሦስት ይሆናሉ መኪና ላይ የነበሩት ፖሊሶች ይኖራሉ
- እኮ ይኖራሉ ሳይሆን ነበሩ አደል ?
- ነበሩ አዎ
- ስንት ናቸው ?
- በቁጥር አላስታውሳቸውም
- ቤት ሄዳችሁ ሕፃናት አልነበሩም ነበሩ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ነበሩ
- ✓ ያለቅሱ ነበረ?
- ✓ አረ በተአምር አያለቅሱም
- ✓ አይተሃቸዋል እስከመጨረሻው ?
- ✓ እስከ መጨረሻው አይቻቸዋለሁ እንደውም አባትየው እያረጋጋቸው አይሄችሁ ሰላም ነው እያላቸዉ እየሳቁ እየጫወቱ ዘና እያሉ ነው
- ✓ ምን ሆነው ነው የሚያረጋጋቸው ?
- ✓ ያው ደንግጠው ነበረ አባትየው አረጋጋቸው እንደአባት ማለትም ኖርማል እንደሆነ ገብቶ አረጋጋቸው ሰላም ነው አላቸው በቃ
- ✓ እህ ስለደነገጡ ማለት ነው ?
- ✓ አዎ
- ✓ ሌላ ሰው ነበረ ተጨማሪ ሰው ቤት ውወሰጥ ?
- ✓ ቤት ውስጥ አለ አባት አለ እህት አለች ሰራተኞች አሉ ብዙ ናቸው
- ✓ ስንት ይሆናሉ በቁጥር?
- ✓ በቁጥር አላስታውሳቸውም
- ✓ ማለት አባት ማለት የማን አባት ናቸው?
- ✓ አባቴ ናቸው ብሏል እሱ
- ✓ የሲ አባት ?
- ✓ ያው የተጠርጣሪው አዎ
- ✓ አንድ የመጨረሻ ጥያቄ ስትፈርሙ ግን ታዛቢዎች ኑሩ ቱርኪ ስትፈርሙ ምን ብላችሁ ነው ይሄ ከቁርአን ት/ቤት የተገኘ ይሄ ከመኖሪያ ቤቱ የተገኘ ብላችሁ ለይታችሁ ነው የፈረማችሁት?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ✓ ከቁርአን ምናምን አላለም ይሄ ንብረት የኔ ስለሆነ ብሎ ይፈርማል እኛም ተቀብለን እንፈርማለን
- ✓ ማለት ከየት የተገኘ እናንተ ለብርበራ ታዛቢዎች ናችሁ ከኑሩ ቱርኪ ቤት የተገኘ ወይም ደግሞ ከኑሩ ቱርኪ ከከፈተው ቁርአን ቤት የተገኘ ብላችሁ ለይታችሁ ፈርማችኋል ?
- ✓ እንደዛ አልፈረምንም ንብረቱ ላይ ፈረመ እኛም ተከትለን ፈረምን
- ✓ የኑሩ ቱርኪ በሚል ነው የፈረማችሁት?
- ✓ አዎ እሱም ፈረመ የኔ ንብረት ነው እያለ እኛም ቀጥለን ፈረምን እሱ ሲፈርም እሱ ከፈረመ በኋላ ለእኛ ይሰጠናል
- ✓ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ✓ እሺ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ
- ✓ አለን ቅድም ሲገልፁ ብርበራው 11 ሰዓት እንደተጀመረና ሦስት ሰዓት እንዳበቃ ገልፀው ነበረ እና በዚህ መሃል ስለ ሰዓቱ ማለፍ በወቅቱ የተነገራችሁ የሚያስታውሱት ነበር?
- ✓ አዎ ስለሰዓቱ ያው የፍ/ቤት ትእዛዝ ከ12 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት ነበረ የሚለው ከዛ በኋላ ስራው ስላልተጠናቀቀ ደውለው ለዳኛ ቀጥሉ እንደተባለ ሰምቻለሁ
- ✓ ማን ነው የደወለው?
- ✓ የደወለው መርማሪዎች
- ✓ በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ በመኖሪያ ቤት እና በቁርአን ት/ቤቱ የተደረገውን ምርመራ ከፋፍለው ሲናገሩ ነበረ መኖሪያ ቤት ውስጥ ቁርጥራጭ ወረቀቶች ተገኝተዋል አጫጭር ወረቀቶች ብለዋል ?
- ✓ ወረቀቶች አዎ መኖሪያ ቤት ተገኝተዋል
- ✓ እነዛን ወረቀቶች እርእሳቸውን አንብበዋል?
- ✓ እርእሶቹን ልብ አልላቸውም



2058 1026

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ኦኬ አበቃን ድጋሚ
- እሺ በፍ/ቤቱ ጥያቄ በሞባይል ተደውሎ ተጨማሪ ሰዓት ይሰጠኝ ብሎ መርማሪው ሲጠይቅ ሰምቻለሁ በስልክ ነውያሉት እንዴት ሰሙ?
- አጠገባችን ነበሩዋ
- ይሰማል እንዴ ሞባይሉ?
- አስራ ሁለት ሰዓት ሆኗል ከአስራሁለት ሰዓት በኋላ ያው ሕግ አለ የማንም ቤት እንደማይበረበር ማለት ነው
- ቆይ ቆይ እስቲ ሕጉን ተወውና ለረዜው አሁን እንዴት ሰማህ ነው?
- በስልክ እያወራ ነበር ቀጥሉ አለ ማለትም ደውዬ ልጠይቅ አለ
- እኮ እንዴት ሰማህ አሁን እሱ የሚናገረውን ልትሰማ ትችላለህ ከዛ ወደዚህ ሲነገር እንዴት ሰማህ?
- ስለፈቀዳለሁ ቀጥሉ አለ መርማሪው
- መርማሪው ነው እንደዛ ያለህ
- አዎ
- እሺ እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ የዛሬውን ችሎት በዚሁ እናጠናቅቃለን ነገ በተመሳሳይ ሰዓት እንገናኛለን በደህና እደሩ::
- 



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

መጋቢት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ ፡- አቃቤ ሕግ ዘረሰናይ ምስግና እና ብርሃኑ ወንድም ለየሁ ቀርበዋል

ተከሳሾች፡- እነአቡበከር አህመድ 31 ተከሳሾች 6ኛ ተከሳሽ ለልቀረበም ለምንድን ነው ያልቀረበው ማረሚያ በምን ምክንያት ነው 6ኛ ተከሳሽ በሕመም ምክንያት ያልቀረቡ መሆኑን ማረሚያ ገልጿል

⇒ ምስክሮች ቀርበዋል አቃቤ ሕግ ከ6ኛ ተከሳሽ ጋር የሚገናኝ ምስክር አለ ?

⇒ አዎ እሱን በሚመለከት ችግር የለውም ያው መቀበል እንችላለን

⇒ እሺ ይግቡ ምስክሮች አስመዝግቡ

⇒ ከ1ኛ እስከ 27ኛ ድረስ ላሉት ባህሩ መኮንን እና ሃሰን ሁሴን

⇒ ስለ 28ኛ ተከሳሽ አህመድ ጀማል ቀርቢያለሁ

⇒ በእውነት ለመመስከር

⇒ በእግዚአብሔር ስም

⇒ ምያለሁ

⇒ በፍ/ቤት መዝገብ 68ኛ ምስክር ናቸው በአቃቤ ሕግ የማስረጃ ዝርዝር /ግልጽ ያልሆነ/



2580 1008

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ. ምስክር እዚህ ፍ/ቤት የመጡት ለምስክርነት ነው እሚገልፁት የመጀመሪያ ስሞን ነው ?

⇒ ደረጀ ጫነው

⇒ እዚህ ፍ/ቤት ለምንድን ነው የመጡት?

⇒ ለምስክርነት

⇒ በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?

⇒ ካሊድ ኢብራሂም

⇒ ካሊድ ኢብራሂምን ያውቁታል በአካል?

⇒ እረዥም ጊዜ ሆኖኛል ካየሁት

⇒ እሺ. አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል

⇒ እሺ. አቶ ደረጀ የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለዋል እምንመሰክረውም በአቶ ካሊድ ነው ብለዋል በምን ጉዳይ ላይ ነው የሚመሰክሩት?

⇒ በአጋጣሚ በተለምዶ ሸጉሌ አካባቢ የሚባለው በሽብር ወንጀል ተጠርጥሮ እን እንደ አጋጣሚ ቆሜ ነበረ ከሰወችጋር በሽብር ወንጀል ተጠርጥሮ ታዛቢ እንድትሆንልን እንፈልጋለን አሉኝ ፖሊሶች ባሉኝ መሰረት ከንድ ሰውዬጋ በውል ስማቸውን በማላውቀው አብረን ገባን ቤቱ በሚፈተሽበት ሰዓት ያየሁትን ነገር ለመመስከር ነው እዚህ የመጣሁት

⇒ ቦታውን እስቲ ንገረን ?

⇒ በተለምዶ ሸጉሌ ነው የሚባለው ወረዳ 10

⇒ ምን ክ/ከተማ?

⇒ ጉለሌ ክ/ከተማ

⇒ ምንድን ነው ያየሁት ነው ያልከን?

⇒ ከቤቱ የተገኘው ሲዲ ካሴት 86 የቴፕ ካሴት 6 አንድ ሃርድ ዌር የኢዮጵያ ሙስሊም የት ደረሰ የሚል መጽሃፍ ጋዜጣ እነዚህን ነው የማስታውሳቸው

⇒ ቤት ብለኸናል ቤት ቁጥሩን ታስታውሰዋለህ?

⇒ 044

⇒ እሺ. ስንት ሰዓት ላይ ነው ብርበራ የጀመራችሁት ወይም ደግሞ ስንት ሰዓት ላይ ነው የተካሄደው ?

⇒ ሦስት ከአርባ አምስት አካባቢ ነው አራት ተኩል እንደዚህ አካባቢ አልቋል ሰዓቱን በውል አላስታውሰውም



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ስንት ሰዓት ጀምራችሁ?

⇒ የተጀመረው ሦስት ተኩል

⇒ ስንት ሰዓት ላይ ጨረሳችሁ?

⇒ ለአራት አጭር ናት ብቻ

⇒ እሺ ሲዲ አግኝተናል ብለዋል ሲዲ የምታስታውሰው አለህ ሲዲ ምን አይነት ሲዲ ነው?

⇒ ምንም እንትኑ ላይ ከቨሩ ላይ የሙስሊም እንትኖች ጺም ያላቸው ሰወች ምስል ያለው ነው ያው ከእስልምና ጋር በተያያዘ እንዳሆነ ያስረዳል እዛ ላይ

⇒ ይዘቱን አይታችኋል እዛ?

⇒ ብዛቱን ነው እንጂ ይዘቱን ያየኋቸው የተወሰኑ የሙስሊም ሰወች ያሉበት ከላዩ ላይ ሲዲው ላይ በፎቶ የሚታዩ አሉ

⇒ ምን ያህል ነው በቁጥር?

⇒ 86 የቴፕ ካሴት 6

⇒ ሰነድስ?

⇒ ሰነድ በራሱ ጽሁፍ የተፃፉ በራሪ ወረቀቶች አሉ ወደ 5 ነው 6

⇒ በራሪ ወረቀት?

⇒ አዎ

⇒ ምን የሚል በራሪ ወረቀት?

⇒ እኔ አላነበብኳቸውም የዛኔ

⇒ በራሪ ወረቀት የምትለው ታዲያ በምንድን ነው?

⇒ እሱም ፈረመበት እኛም ፈረምን

⇒ አይ ሰነዶቹን አይነቶቹን ንገረን በራሪ ወረቀት የምትለው ምን አይነት ነው?

⇒ እንትን ናቸው ማለትም እራሱ ያዘጋጃቸው ጽሁፎች ናቸው እነዛ ጽሁፎች ላይ እሱ ከራቤ የተገኘ ብሎ ሲፈርም እኛ ደግሞ ታዛቢ ብለን ፈርመንበታል

⇒ በራሱ እጅ ጽሁፍ የተዘጋጀ?

⇒ አዎ

⇒ የምታስታውሰው እርእስ አለ?

⇒ አላስታውስም

⇒ ምን ያህል ገጽ ይሆናል?

⇒ 6 ፍሬ ናቸው ማለትም ብዛታቸው የወረቀቶቹ 6 ናቸው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ሌላስ?

⇒ ሌላ ምንም የማውቀው ነገር የለም እነዚህ ናቸው

⇒ በእጅ ጽሁፍ የተዘጋጀ ጋዜጣ እና ሌላ ምን አየህ?

⇒ በቃ የኢትዮጵያ ሙስሊም የት ደረሰ የሚል መጽሄፍ ጋዜጣ

⇒ እሺ አንተ እዛ በቦታው እንዴት ተገኘህ ?

⇒ እኔ በአጋጣሚ ጓደኛዬ እዛ መጋዘን የምናየው ነበረ እና በአጋጣሚ ለሚታደስ እሱጋ ስሄድ በአጋጣሚ ፌደራል ፖሊሶችጋር ተገናኘን መጥተው ጠየቁኝ ሲጠይቁኝ ፍቃደኛ ሆኜ ሄጀ ገብቼ አየሁላቸው

⇒ እሺ ሲጠይቁ የፍ/ቤት ማዘዣ ስለመኖሩ ጠይቀሃል አንተ?

⇒ ሕጉ ይፈቅዳል የሚል ነገር ነው የተነጋገርኩት ማለት ከእዛ ነው አብሮ የመጣው መሰለኝ ከእነሱጋር እና ሕጉ ይፈቅዳል የሚል ነገር ነው ተነጋግረን የገባነው

⇒ አሁን የጠቀስከው ካሊድ የት ነበረ?

⇒ ከነሱጋር ነው አብሮ የመጣው

⇒ ከየት?

⇒ ከፌደራል ፖሊስ

⇒ እስቲ አገባባችሁን ንገረን እንዴት ነው የገባችሁት?

⇒ እራሱ መኝታ ቤት ቀጥ ብለን ፎቅ ላይ ወጣን የራሱ መኝታ ቤት ብቻ ነው የተፈተሸው ሌላ እንኳን የተፈተሸ ነገር የለም የራሱን መኝታ ቤት በራሱ ፈቃድ ከፈተ ያቿ ያለችውን ነገር እና እንደውም አንድ የረሳኋት ሃርድ ዌር የምትል የኮምፒውተር ጋር የተያያዘች በራሱ ፍቃድ ሁሉ አውጥቶ የሰጠ በወረቀት ላይ የተለጠፈ ፕላስትር የተለጠፈበት እዛ ላይ እሱም ፈረመ እኛም ፈረምን እነዚህ እነዚህ ናቸው እኔ የማውቃቸው የማስታውሳቸው

⇒ ስንት ሰው ሆናችሁ ነው የገባችሁት ቤት ውስጥ?

⇒ ሁለት ነበርን ከኔጋር አንድ ሰውዬ ነበሩ

⇒ ታዛቢ ማለት ነው?

⇒ ታዛቢ ሁለት ነበሩ

⇒ ማን የሚባሉ?

⇒ ስማቸው አጥላዬ

⇒ እሺ ስለዚህ የፍ/ቤት ብርበራን በተመለከተ እናንተ የጠየቃችሁት ነገር አለ?

⇒ እ?



563 1011

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ማለት ጠይቃችሁ የተሰጣችሁ መልስ አለ የፍ/ቤት ማዘገየ የመበርበሪያ ትእዛዝ?

⇒ ምንም የጠየቅነው ነገር የለም እሱም የጠየቀው ነገር የለም ፍቃደኛ ሆኖ ነው ወደቤት የገባነው

⇒ ስለዚህ ምን አሏችሁ ፖሊሶቹ በምንድን ነው የምንበረብረው አሉ?

⇒ በቃ ቤቱን በወንጀል ስለተጠረጠረ ይሄ ወንጀለኛ ነው በሽብርተኛነት ወንጀል ስለተጠረጠረ ቤቱን ልንፈትሽ ስለሆነ ያያችሁትን እንድትታዘቡልን ነው አሉ ባየነው መሰረት ታዘብን

⇒ መጨረሻ ላይ ምን አደረጋችሁ?

⇒ ምንም በቃ ተለያየን

⇒ ማለት ብርበራ አደረጋችሁ የተወሰደ ንብረት አለ?

⇒ እነዚህ ሲዲዎች ናቸው የተወሰዱት ሲዲዎቹ የቴፕ ካሴት የኢትዮጵያ ሙስሊም የት ደረሰ የሚለው መጽሃፍ ጋዜጣው እነዚህ እነዚህ ነገሮች ተወስደዋል በፌደራል ፖሊስ ከቤቱ ማለት ነው

⇒ እኮ እነዚህ ንብረቶች ሲወሰዱ የተደረገ ነገር የለም ወይ?

⇒ የለም በቃ እሱን ፈረደበት ከቤቱ የተገኘ እያለ እኛ ደግሞ ታዛቢ ብለን ፈረምንበት

⇒ ከቤቱ የተገኘ ብሎ እሱ ፈረመበት?

⇒ አዎ

⇒ እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት

⇒ የከሳሽ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥል ተብሏል

⇒ አቶ ደረጀ እስቲ ፖሊሶች እንድትታዘብ ጠየቁህ ከዛ ተያይዛችሁ የበረበረው ቤት ደረሳችሁ እንዴት ተከፈተ ቤቱ?

⇒ እንዴት

⇒ ቤቱ እንዴት ተከፈተ እስቲ ንገረን እኛ ስላላየን ?

⇒ ቤቱ በወቅቱ ከነበሩት ፖሊሶች ጋር አብረን ገባን እራሱ ከፍቶ የራሱ መኝታ ቤት ብቻ ነው የተፈተሸችው እንደውም ቤት ተፈተሸ አይባልም

⇒ ከመኝታ ከበሩ ጀምሮ እስቲ ያለውን ንገረን ግቢ አለው ቤቱ ?

⇒ ግቢ አለው ፎቅ ነው እንደውም

⇒ ግቢውን ማን ከፈተላችሁ?

⇒ ግቢ ውስጥ ያሉት ሰወች ናቸው የሱ ቤተሰብ የሆኑ ወንድሙ ነበረ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ማለት ፖሊሶቹ አንኳኩ?

⇒ አንኳኩ

⇒ እሺ ምን አሉ?

⇒ ምንም ከፌደራል ፖሊስ ነው የመጣነው ብለው ወረቀት አሳዩዋቸው ባሳዩዋቸው መሰረት ገባን

⇒ ወረቀቱን እንዴት አርጎ አሳያቸው?

⇒ አላስታውሰውም አሁን

⇒ ሰወቹን ማለት ሰወቹ ወረቀቱን ወሰዱ ወይስ ወረቀቱን በእጃቸው ፖሊሶቹ አሳዩዋቸው ?

⇒ አልወሰዱም ለቤት ፍተሻ መሆኑ ተነገራቸው ገባን

⇒ ስለዚህ ለቤት ፍተሻ ነው ብለው ገቡ?

⇒ አዎ

⇒ እሺ ግቢ ውስጥ የካሊድ ቤት ብቻ ነው እንዴ ያለው?

⇒ ያው የመኖሪያ ቤታቸው የጋራ መሰለኝ እንደ ጠቅላላ እውቀት ሳስበው የራሱ መኝታ ቤት ብቻ ነው የተፈተሸችው

⇒ የራሱ መኝታ መሆኑን በምን አወቅከው እሱን?

⇒ እሱ እራሱ ነው የተናገረው ያሳየውም ወስዶም እዛች ፎቋ ላይም የራሱን መኝታ ቤት ብቻ እንድትፈተሽ ያሳየው በራሱ ፍቃድ ነው እራሱ

⇒ ባለቤት ልጆች አልነበሩም?

⇒ ነበሩ ሰወች

⇒ ቤት ውስጥ ?

⇒ አዎ ወንድሙ ነበረ የራሱ ወንድም

⇒ እሺ ግቢ ገባችሁ ከዛ የሚፈተሸው ክፍል ስትደርሱስ እንዴት ተከፈተላችሁ በሩየመኝታ ቤቱ?

⇒ እንደማንኛውም እንደሚከፈተው ነው በሩ የተከፈተው

⇒ ማለት አንኳኳችሁ አንኳኩ ፖሊሶቹ?

⇒ ቅድም መለስኩት አኮ ተንኳኩቶ ነው ሳይንኳኳ መቼም የሰው ቤት አይገባም

⇒ የለም ለተጠየቁት ብቻ ይመልሱ መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ስለሆኑ በሩ ፖሊሶቹ ደረሱና በሩን አንኳኩ?

⇒ አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከዛ ምን ሆነ?

⇒ ተከፈተልን ከፌደራል ፖሊስ እንደመጡ አስረዷቸው አብረን ተያይዘን ከወንጀለኛው ጋር ገባን

⇒ እስቲ ፍተሻው እንዴት እንደተካሄደ ይግለፁልን ?

⇒ የራሱን መኝታ ቤት ሊያሳየን በቀጥታ ተያይዘን ሁሉም ከፌደራል ፖሊስ የመጡትም መርመሪዎቹም ጭምር ተያይዘን መኝታ ቤቱ ብቻ ገባን ከመኝታ ቤቱ እነዚህ ቅድም የተናገርኳቸውን ነገሮች በሙሉ በፍተሻ ተገኙ ሲገኙ እሱም ፈረመበት እኛም ፈረምንበት

⇒ እርስዎ ምን ብለው ፈረሙ ?

⇒ ታዛቢ ነኝ እኔ ከቤት ውስጥ የተገኘ ነው ብሎ እሱ ፈርሞ ሲሰጠኝ እኔ ደግሞ ታዝቤያለሁ ብዬ ፈረምኩበት

⇒ የካሊድ መኝታ ቤት መሆኑን እርስዎ እዛ አካባቢ ነዋሪ ኖት እንዴ?

⇒ አደለሁም

⇒ ስለዚህ የካሊድ መኝታ ቤት ገባን ሲሉ በምን ያውቃሉ ነዋሪ ካልሆኑ ?

⇒ ተጠይቋል የዛን ጊዜ ተጠይቆ የት ነው ያንተ ምንድን ነው የት ነው የምንወጣው ሲባል እራሱ ነው ወደ ፎቅ ይዞን የወጣው

⇒ ጥሩ ከዛ በኋላ ቅድም የዘረዘሯቸው እቃዎች ከመኝታ ቤት ተገኙ ?

⇒ አዎ

⇒ ከዚያ ቃለ ጉባዔ ተፈራረማችሁ?

⇒ ምንም በቃ የተጠየቀው ያው ከቤት በፍተሻ እንደዚህ እንደዚህ እንደሆነ ተነገረው ግን በተነገረው መሰረት እያነሳ እሱ የማፈርምበት ላይ እኛ ፈረምን

⇒ እሱ ምኑ ላይ ነው የፈረመው ወረቀት ላይ ነው?

⇒ አሁን ለምሳሌ የኢትዮትያ ሙስሊም ከት ተገኘች የምትለው ሲዲዎቹ ቁጥራቸው ምን ያህል እንደሆኑ ያወ የሚፈረምበት ሰነድ አለ ፈርመናል

⇒ ሰነድ ላይ ነው የፈረማችሁት?

⇒ እነዛም ወረቀቶቹ ላይም ፈርመናል

⇒ ሲዲው ላይስ በላዩ ላይ በሲዲው ላይ ፈረማችሁ እንዴ?

⇒ አልተፈረመም ቁጥራቸው 86 መሆኑን ብቻ ነው ሲቆጠር አብረን አይተናል

⇒ እሺ ቆይ 86 ሲዲ ተገኘ ብላችሁ ወረቀት ላይ ፈረማችሁ አደል?

⇒ ምን አሉኝ



2566

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በምልክት ሳይሆን በድምጽ ይንገሩን 86 ሲዲ ከካሊድ ቤት ተገኝቷል ብላችሁ ወረቀት ላይ ፈረማችሁ ?

⇒ አዎ

⇒ ከዛ በኋላስ ቪዲዮ ምናምን አልቀረፁም እንዴ ፖሊሶች?

⇒ የለም እንደዚህ አይነት ነገር አልነበረም

⇒ ፖሊሶቹ ሲገቡ ምን ይዘው ነበረ ?

⇒ ምንም እስክሪፕቶ እና ወረቀት ደብተር

⇒ በእጃቸው ነበረ ያንጠለጠሉት ?

⇒ እ?

⇒ በእጃቸው ነበር የያዙት እስክሪፕቶ ወረቀት ደብተር?

⇒ አዎ

⇒ ቦርሳ አልያዙም ነበር?

⇒ አልያዙም ምንም ነገር አልያዙም

⇒ ቅድም ሰዓቱን ከሦስት ተኩል እስከ አራት ተኩል በምን አውቀው ነው እሱን ?

⇒ አዎ እረዥም ጊዜ ስለሆነ ሰዓቱን ለመለየት ይከብደኛል ቢያንስ እኮ የነበረው ወራት ወደ ሰባት ወር ስምንት ወር ሊሆነው ነው

⇒ ካሴቱም ላይ የካሴቱን ይዘት አላያችሁም ግን ይሄን ያህል ካሴት ተገኘ ብላችሁ ፈረማችሁ?

⇒ 6 ናቸው አረብኛ ጽሁፍ የተፃፈባቸው ናቸው ካሴቶቹ ላይ

⇒ ብላችሁ ፈረማችሁ እንጂ ካሴቱን ?

⇒ አይተናቸዋል

⇒ ማለት የካሴቱን ይዘት ሳታዩ ካሊድ ቤት 6 ካሴት ተገኘ አረብኛ ያለው ብላችሁ ፈረማችሁበት ?

⇒ አደለም ያየናቸውን ነዋ የፈረምንበት

⇒ ቅድም ታዲያ ወደ ፌደራል ብርበራውን ጨርሳችሁ ስትወጡ ተያይዛችሁ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዳችሁ እንዴ?

⇒ አረ አልሄድንም

⇒ ታዲያ ፌደራል ፖሊስ መሄዱን በምን አወቁ ካሴቱ?

⇒ እኛም ወደ ጉዳያችን እነሱም ወደመጡበት ነው የተለያየነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እናንተ በሩ ላይ ነው የተለያያችሁት?

⇒ በቃ ከጊቢ እንደወጣን ተለያይተናል

⇒ አቶ ደረጀ ቅድም በአቃቤ ሕግ ተጠይቀው ሲመልሱ ቤቶቹ ውስጥ ካገኛናቸው መጽሃፎች ጋዜጦች መካከል በራሱ እጅ የተገኘ ወይም የተፃፈ ጽሁፍ አግኝቻለሁ አይቻለሁ ብለው ነበረ እርግጠኛ ኖት በዚህ?

⇒ ማስታወሻ የሚያዙበት ወረቀቶች ማንኛውም ሰው ይኖረዋል ከዛ የራሱ መሆኑን ነው ሲጠይቁት የራሴ ነው አለ ከሚወጣው የአጀንዳ እንትን ላይ የራሱ መሆኑን በፍቃደኛነት ከተናገረ በኋላ እንዲቆጠሩ የተደረጉት

⇒ እኮ ጽሁፉ የኔ ነው አለ ይሄ ጽሁፉን ይዘቱን አላስታውሰውም

⇒ አደለም ይዘቱን አደለም የጠየቅኩት ጽሁፉ የኔ ነው አለ የተፃፈበት?

⇒ አዎ

⇒ በእስክሪፕቶ ነው የተፃፈው?

⇒ በእስክሪፕቶ ነው የተፃፈው አዎ

⇒ እነዚህ ቅድም አየናቸው የሚሏቸው ጋዜጣ እና መጽሄቶች ገበያ ላይ አይገኙም የተከለከሉ ናቸው በሕግ?

⇒ እሱን አላውቅም ሕጉ ይከልክል አይከልክል አላውቅም ግን ለኢትዮጵያ ሙስሊም የደረሰ የምትለዋል መጽሃፍ አስታውሳለሁ የሙስሊም ደግሞ ጋዜጣ ስሟን አሁን በውል አላስታውሳትም ጋዜጣ ከቤቱ የተገኙ አሉኝ አንድ

⇒ ጋዜጦቹ እና መጽሄቶቹ በካሊድ የተዘጋጁ ናቸው ይላል ?

⇒ በምን

⇒ በካሊድ ወይም ሄዳችሁ ባያችሁት ሰው ቤት ስም የተዘጋጀ ነው?

⇒ አደለም

⇒ እርስዎ ከዛ በፊት የካሊድን ቤት አያውቁትም ?

⇒ አላውቀውም

⇒ ከዛም በኋላ አልሄዱም ?

⇒ ከዛ በኋላ አላየሁም

⇒ ፖሊስ ነው አደል የካሊድ ቤት ነው ብሎ የወሰዶት ተባበረን ያሉት መንገድ ላይ?

⇒ አደለም

⇒ እ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በአጋጣሚ ነው እኔ ሽጉሌ ወደ መንደር 7 አካባቢ የምትባል እዛ ተገናኘን እነሱ ሲያልፉ

⇒ እኮ ከፖሊሶት ተገናኙና ፖሊስ ታዛቢ ትሆናለህ ብሎ ወሰዶት ?

⇒ አዎ

⇒ በሽብርተኛ ወንጀል የተጠረጠረ ሰው አለን ታዛቢ ትሆኑልናላችሁ ወይ የሚል ጥያቄ ተነሳልን ፍቃደኛ ሆነን ሄድን

⇒ እኮ ያን ቤት ያሳዮት ፖሊስ ነው አደለም ?

⇒ አዎ እኔ አላውቀውም ከዚህ በፊት የነካሊድን ቤት

⇒ እሺ በዚህ ጉዳይ ከዚህ በኋላ ማእከላዊ ሄደው ያውቃሉ በዚህ ጉዳይ?

⇒ አላውቅም ለምስክርነት መሆንን ብቻ ተደውሎ ተነገረኝ መጣሁ

⇒ ቀኑን በምን አስታወሱ?

⇒ ተደውሎ በተነገረኝ መሰረት ነው የምስክር ቀን በእንደዚህ ቀን አለ እንድትመጣ ተባልኩኝ በተባልኩበት መሰረት መጣሁ

⇒ የምስክር ቀን አለ ና ተባሉ ከዛ ውጪ የተነገሮት ነገር አለ?

⇒ አይ

⇒ እሺ ጨርሻለሁ

⇒ መስቀለኛ ጥያቄ የተከሳሾች ተከላካይ ጠበቆች አቅርበው ምስክሩ መልስ ሰጥቷል የከሳሽ አቃቤ ሕግ ዳግደኛ ጥያቄ ካለ ይቅረብ

⇒ የለንም የተከበረው ችሎት

⇒ አቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ የለም ብሏል ከፍ/ቤቱም የሚቀርብ የማጣሪያ ጥያቄ ስለሌለ ምስክሩ ተሰናብተዋል ጨርሰሃል ምስክር

⇒ በእውነት ለመመስከር

⇒ በእግዚአብሔር ስም

⇒ ምያለሁ

⇒ በፍ/ቤቱ መዝገብ 69ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር በማስረጃ ዝርዝሩ ስንተኛ ናቸው 128

⇒ እሺ ምስክር የመጀመሪያ ስሞትን ብቻ ይገልፃሉ ?

⇒ ወንደሰን

⇒ እሺ ዛሬ ለምንድን ነው የመጡት እዚህ ፍ/ቤት ?

⇒ ዛሬ የመጣሁበት የመጀመሪያው

⇒ ለን የመጡበትን በአጭሩ ምን ለማድረግ መጡ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ያየሁትን

⇒ በማን ላይ እንደሚመሰክሩ ያውቃሉ?

⇒ ያሲን ኑር የቤት ብርበራ

⇒ ተከሳሹን ያውቁታል እንዴ አሁን የጠቀሱትን?

⇒ አላውቀውም የለም ነበር

⇒ እሺ ከሳሽ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል

⇒ አቶ ወንደሰን

⇒ አቤት የመጣሁት ለምስክርነት ነው ያየሁትን ለመመስከር ነው ብለዋል በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?

⇒ የመጀሪያው በያሲን ኑር አህመዲን ጀበል አህመድ ሙስጠፋ

⇒ እስቲ በአቶ ያሲን ኑር እንጀምር መቼ ነው ጊዜውወ?

⇒ በ12/12/2004

⇒ ወሩ ምን ላይ ነው?

⇒ 12ኛ ወር ነሐሴ

⇒ ቀኑስ?

⇒ አላስታውስም

⇒ ሰዓቱን ያስታውሳሉ?

⇒ አዎ ሰዓቱ ከ3 ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ባለው

⇒ ቀን ነው ማታ ነው ?

⇒ ቀን

⇒ እንዴት ተገኙ እርስዎ እዛ?

⇒ ለራሴ ጉዳይ ሄጄ ያው እንሂድ እና እባክህ

⇒ ድምፃትን ከፍ ያርጉት?

⇒ ገጠመኝ ለራሴ ጉዳይ ነው የሄድኩት

⇒ እሺ ቦታው የት ነው ?

⇒ ጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 163

⇒ እሺ

⇒ በድሮው ወረዳ 10 ቀበሌ 10/11/12 ማለት ነው

⇒ እሺ በራሴ ጉዳይ እዛ ተገኝሁ አሉ ?



2569

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አዎ

⇒ እሺ በራሶት ጉዳይ እዛ ተገኝተው እንዴት ወደ አቶ ያሲን ኑሩ ቤት ገቡ?

⇒ እ

⇒ አሁን ወደጠቀሱት ግለሰብ ቤት ተከሳሹ ቤት እንዴት ገቡ?

⇒ ያው ፖሊሶች ነበሩ የፍ/ቤት ወረቀት ይዘዋል ያን ይዘን ገባን እሱ የለም ባለቤቱ ነበረች በፈቃደኛነት ያው ንብረቱ ተፈተሸ ቤቱ

⇒ የፍ/ቤት ትእዛዝ ይዘው ነበረ ፖሊሶቹ?

⇒ አዎ ይዘው ነበር

⇒ ተነቦላችኋል?

⇒ ተነቦልናል እኛም ተነቦልን እዛም ስንገባ ለሷ ተነቦላታል

⇒ ተነቦላቸዋል

⇒ ለማን ነው የተነበበው?

⇒ ለባለቤቱ

⇒ ባለቤቱ መሆኑን በምን አወቃችሁ?

⇒ ያው ባለቤቱ ነች ሲባል ስለሰማን

⇒ እሳቸውም ማለት አረጋገጡ?

⇒ አዎ

⇒ እሺ እሳቸው የት ሄዱ ተባለ አቶ ያሲን ኑሩ?

⇒ የለም በቤቱ የለም

⇒ በዚህ አሁን በሄዳችሁበት በብርበራ ቀን አልነበሩም?

⇒ አልነበሩም

⇒ እሺ ምንድን ነው በብርበራ ምን ምን ተያዘ?

⇒ ወደ 140 አካባቢ ሲዲዎች ላፕቶፕ መጽሄቶች በራሪ ወረቀቶች

⇒ ላፕቶፑን ማርኩን ያስታውሱታል ?

⇒ በጣም ቆይቷል

⇒ እሺ ላፕቶፕ እሺ ሌላ ?

⇒ እንትኖች የዴክ ካሴቶች ሁለት የባንክ ቡኮች  አዋሽ ባንክ ምናምን የሚል እና በራሪ ወረቀቶች በቃ ድምፃችን ይሰማ ምናምን የሚል በራሪ ወረቀቶች

⇒ ሌላስ የሚያስታውሱት?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ሌላ አላስታውስም

⇒ በራሪ ወረቀቶች ድምፃችን ይሰማ የሚል ሌላስ ሰነድ የያዛችሁት?

⇒ ሌላ አላስታውስም

⇒ እሺ ስንት ሰዓት ነው የጀመራችሁት?

⇒ ሦስት ሰዓት

⇒ ሦስት ሰዓት ጀምራችሁ ስንት ሰዓት አበቃችሁ?

⇒ አምስት ሰዓት

⇒ ስንት ሆናችሁ ነው የገባችሁት እዛ ቤት?

⇒ እንትኖች አሉ እዚህ ፖሊሶች ምናምን ካሜራ የሚያነሳ ነበር እያንዳንዷ የምትገኘውን እቃ ካሜራ የሚያነሳ ሰው ነበረ ሦስት ይሁን አራት ነው መሰለኝ

⇒ ከእርስዎ ውጪ ሌላ ታዛቢ አለ?

⇒ እኔ አላየሁም

⇒ ታዛቢ ሆኖ የገባ ከፖሊሶች ውጪ ከአንተ ጋር ታዛቢ አለ ወይ?

⇒ ይኖራል ግን እኔ አላየሁም ማለት እኔ የግሌን ነው የማየው

⇒ እኮ ቤት ውስጥ ብርበራ ስታረጉ ከፖሊስ ውጪ ሌላ ታዛቢ ነበረ ወይ?

⇒ አዎ አሉ

⇒ እሚያስታውሱት በስም አለ?

⇒ አላስታውስም

⇒ እሺ ይሄንን አሁን የጠቀስኳቸውን ንብረቶች መጨረሻ ላይ ምን አደረጋችሁ?

⇒ አንደኛው ቃል ጉባዔ ያዘና

⇒ ቃል ጉባዔ ማን ነው የያዘው?

⇒ ያው ከዛ ከሚፈትሹት አንዱ ነው ያዘ ስማችን ተፃፈ ዝርዝሩ ተያዘ እቃው ከዛ ፈረምን ሚስትየዋም ፈረመች ከኔ ጋ የተገኘ ነው ብሎ

⇒ ፈረመ?

⇒ ከኔ ጋ ቤት የተገኘ ነው ብላ አስፈረመችኝ ያው ፈረምኩኝ

⇒ እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት

⇒ የአቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የተከሳሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቡ ተብሏል

⇒ አቶ ወንደሰን



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አቤት

⇒ የፍ/ቤት ትእዛዝ አይቻለሁ ብለው ነበረ የየት ፍ/ቤት ትእዛዝ ነው ያዩት?

⇒ በደንብ አላነበብኩትም እሱን ዞሮ ዞሮ የፍ/ቤት ትእዛዝ ነበረ ጊዜው እኮ አልቋል ከ8 ወር በላይ ምናምን ማስታወስ

⇒ የትኛው ፍ/ቤት ትእዛዝ እንደሆነ አያውቁም?

⇒ አዎ

⇒ ምን ይፈተሽ እንደሚልም አያውቁም?

⇒ እ?

⇒ ምን ይፈተሽ እንደሚልም አያውቁም ብርበራው ምን ምን ይፈተሽ እንደሚል አያውቁም?

⇒ በአጠቃላይ ቤቱ እንዲፈተሽ ነው በቃ

⇒ ቤቱ ብቻ ነው የተባለው?

⇒ አዎ

⇒ ቤቱ ውስጥ ምን ይፈተሽ ተባለ?

⇒ በሙሉ ንብረቶቹ መሣሪያዎቹ ምኑ ሁሉ ነገር አዎ

⇒ በዝርዝር ነው የሚገልፀው ?

⇒ እ?

⇒ በዝርዝር መሣሪያ ይፈተሽ አልጋ ይፈተሽ ይላል?

⇒ እሱን እኔ እንግዲህ ያው ትዝ አይለኝም

⇒ ማህተም ፊርማ እንዳለው አረጋግጠዋል የፍ/ቤት ትእዛዝ ያሉት ነገር?

⇒ አዎ

⇒ ማን እንደፈረመበት ያስታውሳሉ?

⇒ ትዝ አይለኝም

⇒ ስንት ዳኛ እንደፈረመስ ያስታውሳሉ?

⇒ ስንት ምን

⇒ ዳኛ

⇒ አላስታውስም ጊዜው እኮ እርቋል

⇒ የፖሊስ ትእዛዝ ይሁን የፍ/ቤት ትእዛዝ በደንብ አይተዋል አረጋግጠው?

⇒ አዎ እሱማ አረጋግጬ ነው የገባሁት አለዚያ ተጠያቂ እኮ ነኝ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እነዚህ ቤት ውስጥ ተገኙ ያሏቸው ወደ 140 ሲዲ ላፕቶፕ የዘታቸውን አይተዋል ምን እንደሚሉ ?

⇒ ማለት

⇒ ምን እንደሚሉ አይተዋል?

⇒ ሲዲዎች እኮ ክብ ሲዲ ነው አልከፈትኩም

⇒ አልተከፈተም አላዩትም?

⇒ አላየሁም

⇒ በራሪ ወረቀቶች ያሏቸው አሉ እነሱንስ አንበባቸዋል ?

⇒ አዎ

⇒ ምን ይላሉ?

⇒ ድምፃችን ይሰማ ምናምን የሚል

⇒ ይልና ምን ይላል አርእስቱን ብቻ ነወ ያዩት?

⇒ ይቺን ነው ያየሁት

⇒ ስንት ድምፃችን ይሰማ የሚል ወረቀት አዩ?

⇒ በጣም ብዙ ነው

⇒ ስንት ይሆናል በግምት?

⇒ እኔ አላስታውስም

⇒ አርእስቱን ብቻ ነው ያዩት?

⇒ አዎ

⇒ የባንክ ቡክም አይተዋል?

⇒ አዎ ሁለት ነው ያየሁት

⇒ እነዚህ ድምፃችን ይሰማ የሚሏቸው ወረቀቶች በራሪ ወረቀቶች ሌሎች ያዩዋቸው በያሲን የተፃፉ ናቸው በያሲን የተደረጉ ናቸው?

⇒ ትዝ አይለኝም

⇒ እሱን አያውቁም?

⇒ አላስታውስም ያው እሱ ቤት የተገኘ

⇒ እሱ ቤት መገኘቱን ብቻ ነው ቅድም ወደቤት ስንሄድ ፖሊሶች ባለቤቱ ነች ብለው ነገሩኝ ብለዋል ከዚህ ሌላ እሷን ጠይቀው አላረጋገጡም አደል?

⇒ እሷም እኮ ባለቤት ነኝ አለች እኮ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እኮ ማን ሲል ሰምተው ነው ባለቤት ነች ያለችው ማን ጠይቋት ነው?

⇒ ያው ከፖሊሶቹ አንዱ ጠይቋትነው

⇒ ፖሊሱ ጠይቋት ነው?

⇒ አዎ ጠይቋታል ባለቤቱ ነኝ

⇒ ምን ብሎ ጠየቃት ?

⇒ እንደው የለም ወይ ተብላ እኮ የለም እኔ ባለቤት ነኝ ምናምን ብላለች እኮ

⇒ የለም ተብላ የጠየቃት ያሲንን ነው?

⇒ ታዲያ ሌላ ማን እሱ ቤት ነው

⇒ አይ ግምቱን አደለም እርስዎ የሰሙትን ያሲን የለም ነው ያላት የሰሙትን ማለት ነው?

⇒ /ግልጽ ያልሆነ/

⇒ ከዛ ውጪ ግን እርስዎ ባለቤት መሆኗን ያረጋገጡበት ሌላ መንገድ አለ ባለቤት ስለመሆኗ?

⇒ እየመራች እሷ ነበረች

⇒ አደለም ከዛ ውጪ ያረጋገጡበት መንገድ አለ?

⇒ መንገድ የለም እሷ እየመራች

⇒ አደለም እኔ የምጠይቆትን መልሱ ከዛ ውጪ ያረጋገጡበት መንገድ አለ የለም ካለ አለ?

⇒ ትዝ አይለኝም

⇒ አላረጋገጡም?

⇒ አዎ

⇒ ቤቱሳ የያሲን ቤት ነው ብሎ የወሰዶት ፖሊስ ነው አደል?

⇒ አዎ

⇒ የተያዘው ላፕቶፕ አይነቱ ምን እንደሆነ ብራንዱን ያስታውሳሉ?

⇒ አላስታውስም ከ7 ወር በላይ እኮ ነው

⇒ ከዛ መጨረሻ ቃል ጉባዔ ስትጽፉ ምን ብላችሁ ነው እርስዎ ሲፈርሙ እነዚህ ሲዲ 140 ላፕቶፕ እያላችሁ ዘርዝራችሁ ነው የፈረማችሁት አደል?

⇒ አዎ

⇒ እንደዛ ነው የፈረማችሁት?

⇒ ዝርዝሩ ተፃፈ ከተፃፈ በኋላ ባለቤቱ ከሷ ቤት የተገኘ መሆኑን [illegible] ትፈርም እኛም ደግሞ ከሱ የተገኘ ብለን ፈረምን

⇒ ካሴቱ ላይ ፈርማችኋል?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እንዴት ይፈረማል ምኑ ላይ?

⇒ አይ ፈርሜያለሁ ወይም አልፈረምኩም?

⇒ አልፈረምኩም

⇒ እንዴት የሚለውን ይተውት ሲዲውም ላይ ወረቀቱ ላይ ወረቀቱ ላይ ነው እንጂ ሲዲው ላይ አልፈረማችሁም ?

⇒ ምኑም ላይ አልፈረምኩም በቃ ወረቀቱ ላይ ቃለ ጉባዔ ላይ

⇒ የተከሳሾች ጠበቃ አዲስ መሃመድ ቀርቢያለሁ በር ተሰብሮ የተፈተሸ ክፍል ነበረ አልነበረም ?

⇒ አለ አዎ ነበር

⇒ አንድ ክፍል ነው?

⇒ አዎ አንድ ክፍል

⇒ ለምንድን ነበር በሩን መስበር ያስፈለገው?

⇒ ያው የሱ ክላስ ስለሆነ ነበራ

⇒ ስንት ነበራችሁ ብዛታችሁ ታዛቢዎቹ ?

⇒ ታዛቢዎቹ እኔ ትዝ አይሉኝም

⇒ ስንት እንደሆኑ ብዛታቸውን አታውቃቸውም

⇒ ፖሊሶቹ ጋራ የመጡት ታዛቢዎች ናቸው ሌላ አምጪ ታዛቢ ተብላ ያመጣችው ታዛቢ አለ ወይስ እናንተ ?

⇒ ማን ?

⇒ አሁን ባለቤት ነች ያልከው ያመጣችው ሰው አለ እሷ?

⇒ እህቶቿ ምናምን እኮ ሳይኖሩ እኮ አይቀሩም የሷ እህቶች

⇒ እኮ ቤት ውስጥ ነበሩ ነው?

⇒ አዎ

⇒ ምን ያክል ሰው ነበረ ቤት ውስጥ?

⇒ ትዝ አይለኝም አላስታውስም

⇒ ምን እያደረጉ ነበር እነሱ አንድ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብለው ነበር?

⇒ ኖ አብረው እያንዳንዱን እንቅስቃሴ እየመሩ እነሱ ናቸው የሚያሳዩን

⇒ እሺ እናንተ ታዛቢዎቹ ስንተ ነበራችሁ ፖሊስ ይዟችሁ የሄደው ከአንተ ጋር?

⇒ ትዝ አይለኝም እኔ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ብዛታቸውን አታውቅም?

⇒ አላስታውስም እኔ ቆይቷል

⇒ ጨርሰናል

⇒ መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የከሳሽ አቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ይትረብ ተብሏል

⇒ ድጋሚ ጥያቄ የለንም የተከበረው ችሎት

⇒ አቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ የለም በማለት

⇒ እንቀጥል ሌሎቹ ላይ ሁለት ሰወች አሉ አህመዲን ጀበል እና አህመድ ሙስጠፋ የነሱንሦት ሦስት ሰው ላይ ነው በአንደኛው እንጨርስ ብለን ነው

⇒ በያሲን ኑር ላይ ነው ?

⇒ አዎ

⇒ አሁን አህመዲን ጀበል እና አህመድ ሙስጠፋ

⇒ ለነገሩ ቅድም የረሳችሁት ነው የሚመለስለው እኛም ልንጠይቅ ይዘን ነበረ እረስታችሁት ነው ወይስ ምንድን ነው ?

⇒ ኦፍ ኮርስ አዎ ትክክል

⇒ ጉዳዩን ተመልክቷል በመሰረቱ ምስክሩ በሦስት ሰወች ላይ እንደሚመሰክር ለፍ/ቤቱ አስረድቷል እነዚህ በሦስት ሰወች ላይ የሚመሰክሩ ምስክሮች በምን አይነት መልኩ እንደሚመሰክሩ ማለትም አንደኛው ተከሳሽ ላይ ቀድሞ ጥያቄዎቹ ተጠናቀው መስቀለኛውም ድጋሚውም በሌሎቹ ተከሳሽ ላይ ጥያቄ እንዲቀጥል ወይም እሦስቱም ላይ አንድላይ ይቀጥል ምንም ጉዳይን በተመለከተ ግልጽ ነገር የለም በእኛም መካከል ሁለት አይነት ነገር ነበረ የያዝነው በመጀመሪያው በሦስቱም ላይ አንዴ መመስከር አለበት የሚል ነው የላይኛው ደግም በአንዱ ላይ ጥያቄዎቹ ካለቁ በኂላ በሌሎቹላይ መቀጠል የሚከለከል ነገር የለም የሚል ነው ኤኒዌይስ በፍ/ቤቱ የተያያዘ ጉዳይ ሆኖ ነው የነበረው እና ጥያቄው መቀጠሉ ችግር የለውም ብሏል ችሎቱ

⇒ እሺ አቶ አህመድ ማን?

⇒ አህመዲን ጀበል

⇒ እስቲ የእሳቸውን ንገረን?

⇒ የእሱ በ25/12/2004

⇒ እሺ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ኢሜሉ እራሱ ከፍቶ ፕሪንት እየተደረገ ወረቀቶቹ ወጡ

⇒ በ25/12/2004 እሺ. ሰዓቱ ስንት ሰዓት ላይ ነው?

⇒ ጠዋት ሦስት ሰዓት

⇒ ቦታው የት ነው ?

⇒ እዛው ነው

⇒ የት?

⇒ ማእከላዊ

⇒ እሺ. ምንድን ነው የተደረገው ?

⇒ እኔ ተጠራሁ ያው መጣሁ ከዛ እሱ መጣ አብረን ገባን ሌላም ፖሊስ ይሁን አብረን ገባን

⇒ ድምፆ አይሰማም ሁሉም ሰው እንዲሰማ

⇒ እሺ. ያው ገባን ሁላችንም

⇒ የት ነው የገባችሁት?

⇒ ቢሮ ቁጥር 26

⇒ ማን ነው ቀድሞ የገባው ቢሮ 26 ቁጥር?

⇒ ሁላችንም በሩ ተከፈተ እሱም ሌላም ታዛቢ ነበረ ከኢጋር

⇒ አቶ አህመድ ከየት መጡ ?

⇒ ከዛው ከማእከላዊ ከኋላ

⇒ እሺ. ምንድን ነው የተደረገው?

⇒ ሁላችንም ገባን ከዛ ኮምፒውተር ተከፈተ ኢሜሉን እራሱ እራሱ ከፋፍቶ ፕሪንት ተደረገ ወረቀት ወጣ

⇒ ኮምፒውተር ነው ምንድን ነው?

⇒ ማለት

⇒ ማለት ምንድን ነው ላፕቶፕ ነው ኮምፒውተር ?

⇒ ኢሜሉን ከፍቶ ወረቀት ፕሪንት ተደርጎ ወጣ

⇒ ኢሜሉ?

⇒ አዎ

⇒ እንዴት አድርጎ ነው የከፈተው ?

⇒ እራሱ እኛ አብረን እየነካካን ሲከፍት  አብረን ቁጭብለንእኮ ነው

⇒ ድምጽ አይሰማም



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ጉንፋን ስለያዘኝ እኮ ነው

⇒ ኢሜል እኮ ነው

⇒ እኮ ኢሜል ከምን ላይ ኢሜል እኮ የምልህ ?

⇒ ከኮምፒውተር ላይ ነዋ

⇒ እሺ እንዴት ነው የተከፈተው ?

⇒ እሱ ነው የከፋፈተው እኛ ማየት ነው እኮ

⇒ ምን ተብሎ ማለት እንደመጣ እንተ ምንድን ናችሁ ተባላችሁ ምን ተነገረው ?

⇒ የሱ መሆኑን እሱ እራሱ ሲያወጣ እያያችሁ እንትታዘቡልን ነው

⇒ እኮ እሱ አህመድ ከመጣ በኋላ እናንተ ምንድን ናችሁ ተብሎ ተነገረው ?

⇒ ታዛቢ

⇒ ታዛቢ ናችሁ  ተብሎ ተነገረው?

⇒ አዎ

⇒ እሺ እራሱ ነካክቶ ከፈተው ብለሃል ምንድን ነው የተገኘው ?

⇒ ወረቀቶች ፕሪንት እየተደረጉ ወጡ ወደ ሃምሳ ነው ምናምን ወረቀት

⇒ ይዘታቸውን ታስታውሳለህ እርእሳቸውን?

⇒ ማለት

⇒ ማለት የወጣው ፕሪንት ተደርጐ የወጣው ?

⇒ እንግሊዘኛ ነው ትገ አይለኝም አላነበብኩትም

⇒ ይዘቱን አታስታውሰውም ?

⇒ አዎ

⇒ እሺ ሌላስ የምታውቀው አለህ ከአህመዲን ጀበል ጋር?

⇒ ተያይዞ ድጋሚ በ5/1/2005 ~~ነው ቁጠረው በእሱ ጉዳይ የዛን ጊዜ~~ ደግሞ ላፕቶፕ ነው ይዞ የመጣው የራሱ ላፕቶፕ ወጣ ከዛ ያው ቁጭ አልን ከፈተ ከዛም ፕሪንት እየተደረገ ወደ መቶ ገጽ ወጣ አማርኛ እና እንግሊዘህ

⇒ የት ነው ይሄስ?

⇒ እዛው /ግልጽ ያልሆነ/ 26

⇒ ምርመራ ክፍል?

⇒ አዎ

⇒ እሺ ይሄስ እንዴት ነው የተከፈተው?



1027

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እራሱ ነው የከፈተው

⇒ እራሱ ነው የከፈተው ስትል አሁን ማለት ግልጽ እንዲሆን ምን እሚከፈት ነገር ነበረው ማለት ላፕቶፑን ማንም ሰውሊከፍተው አይችለም እንዴ?

⇒ የራሱ ስለሆነ እራሱ የራሱ ሲስተም ነው እኮ

⇒ እ?

⇒ እሱ ነው እንትኑን የሚያወቀው እራሱ ነው የከፈተው

⇒ ቆይ ምስክር /ግልጽ ያልሆነ/ እርስዎ ያዩትን

⇒ እሺ ከላፕቶፑ ውስጥ ምንድን ነው የተገኘው?

⇒ ወደ እንደዚሁ ፕሪንት እየተደገ ወጣ ወደ ስንት ገጽ መቶ ገጽ ይሁን ምናምን እንደዚህ ወጣ ወረቀት በእንግሊዘኛ እና በአማርኛ ነው

⇒ ድምጽህ አልተሰማኝም ?

⇒ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ የተፃፈ ወረቀት ፕሪንት እየተደረገ ወጣ

⇒ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ የተፃፈ ወረቀት?

⇒ አዎ

⇒ እርእሱን የምታስታውሰው አለ በእርእስ ?

⇒ አላስታውስም

⇒ ምን ያህል ይሆናል በገጽ ብዛት?

⇒ መቶ ይሆናል መቶ አራት መቶ ምናምን ይሆናል

⇒ የቅድሙ ስንት ነው ከኮምፒውተር ?

⇒ 50

⇒ እዚህ ላይ ምን ያደረጋችሁት ነገር አለ እንዴ?

⇒ ማለት?

⇒ እነዚህ ገፆቹ ፕሪንት ተደርገው ሲወጡ ?

⇒ እያንዳንዷ ላይ እሱ ከኔ ወጣ ብለው ይፈርማል ከኔ ላፕቶፕ የወጣ ነው ብለው እየፈረመ እኛ ደግሞ ከሱ ሲወጣ አይተናል እያልን ቀን እየፃፍን እንፈርማለን

⇒ በየገፁ ነው?

⇒ እያንዳንዷ ገጽ ኢንዲቪጁዋል አዎ

⇒ ሌላስ?

⇒ ሌላ በቃ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በአህመዲን ጀበል ላይ ከኮምፒውተር እና ከላፕቶፕ የምታስታውሰው ?

⇒ ጨረስኩ

⇒ እሺ 3ኛ ሰው ?

⇒ አህመድ ሙስጠፋ

⇒ እሺ ከአህመድ ሙስጠፋስ ምንድን ነው?

⇒ የሱም ከኢሜል ነው

⇒ መቼ ነው ቀኑ?

⇒ በዛው ቀን

⇒ መቼ?

⇒ በ25/12 የመጀመሪያው ቀን ማለት ነው

⇒ በ25/12/?

⇒ 2004

⇒ ሰዓቱ የት ነው ቦታውስ?

⇒ እዛው ቢሮ ቁጥር 26

⇒ ሰዓቱስ?

⇒ ሦስት ሰዓት ነዉ በቃ

⇒ ጠዋት ሦስት ሰዓት?

⇒ ያ

⇒ እሺ ያን ቀን አቶ አህመድ የት ነበረ?

⇒ ያው እኛ መጣን እሱም መጣ ተያይዘን ነው የገባነው አብረን

⇒ አብራችሁ ተያይዛችሁ ገባችሁ?

⇒ አብረን እዛው ክፍል ውስጥ

⇒ እቃውስ የት ነበር ?

⇒ እዛው ክፍል ውስጥ

⇒ የት ክፍል?

⇒ እዛ የተመረመርኩት ክፍል ውስጥ ነው

⇒ ምርመራ ክፍል ውስጥ?

⇒ ቢሮ ቁጥር 26 አዎ

⇒ እሺ እሱስ እንዴት ተከፈተ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እራሱ ነው የከፈተው እሱን

⇒ እራሱ ነው የከፈተው ?

⇒ አዎ

⇒ እሺ እራሱ ከፍቶ ምን ተገኘ ?

⇒ ፕሪንት እየተደረገ የሱ ደግሞ ወደ 46 ገጽ ነው የወጣው በአማርኛ በእንግሊዘኛ እና በአረብኛ

⇒ አማርኛ እንግሊዘኛ? አረብኛ

⇒ አጠቃላይ 46 ገጽ ነው?

⇒ 46

⇒ በይዘቱ የምታስታውሰው አለ በርእስ? ትዝ አይለኝም

⇒ እምታስታውሰው የለም?አዎ በጣም ቆይቷል 7 ወር ስምንት ወር

⇒ እሺ እዚህ ላይስ ምን አደረጋችሁ?እሱ ከኔ ኢሜል የተገኘ እያለ ይፈርማል

⇒ ከኢሜሌ?ስሙን እየፃፈ ይፈርማል አዎ አብረን ጉን ለጉን እኮ ነው ቁጭ ብለን የምናወራው እኛም ደግሞ ከሱ የተገኘ እያልን እኛ ደግሞ ፈረምን

⇒ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት

⇒ ከሳሽ አቃቤ ሕግ ምስክሩ በ3 ተከሳሾች ላይ ነው የመሰከሩት በ1ኛ ተከሳሽ ወይም በያሲን ኑር ላይ ቀደም ሲል መስቀለኛ ጥያቄ የተከሳሽ ጠበቆች አቅርበዋል በአሁን በአህመዲን ጀበል እና በአህመድ ሙስጠፋ በተባሉ ተከሳሾች ላይ በሰጠው የታዛቢነት ምስክርነት ላይ መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ አቅርቡ ተብሏል የተከሳሾች ጠበቆች

⇒ ምስክር አህመዲን ጀበል እና አህመድ ሙስጠፋ በአንድ ቀን ነው በ25/12/2004 ነው አደል እነሱን ኢሜል ሲያወጡ የታዘብከው ትክክል ነው አደል?

⇒ አዎ ሁለቱ በአንድ ቀን ግን አንድ ላይ አልገቡም በተራ ነው

⇒ ቆይ እመጣለሁ ቅድም አህመዲን ሦስት ሰዓት ተጀመረ ብለዋል ትክክል ነው አደል?እ?የአህመዲንን መታዘብ የጀመሩት በስንት ሰዓት ነበር አህመዲን ጀበል?ያው በተመሳሳይ ሰዓት እኮ ነው ያኛው ሁለት ተኩል ሦስት ሰዓት አካባቢ ነው አዎ ትዝ አይለኝም እኮ በጣም ቆይቷል

⇒ መታዘብ የጀመሩት የትኛውን እንውሰድ በግምት? እ?

⇒ የአህመዲን ጀበልን ጉዳይ ማእከላዊ ተገኝተው የታዘቡት በስንት ሰዓት ነበረ?

⇒ ሁለት ተኩል ወይ ሦስት ሰዓት



1030 2580

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እስቲ እንዴት ነው ለታዛቢነት የተመረጡት እስቲ ይንገሩን ?

⇒ መጀመሪያ ያው በያሲን ኑር እኮ ብርበራ ጊዜ ስልኬን ሰጥቼ ነበር በዛ ደውለው ጠሩኝ ታዘብልን ብለው

⇒ አሃ ከዛ ቀጥታ መጡና ታዛቢ ሆኑ እስቲ ቅድም ሲነግሩን ነበረ ለመታዘብ በስልክ ተጠርተው መጡ ቢሮ ቁጥር 26 በር ላይ ነው የቆሙት እንደመጡ ? ጊቢ ውስጥ ገባሁ

⇒ እና ግቢ አልፈው ቢሮጋ ደርሰዋል? አዎ

⇒ በር ላይ ቆሙ ወይስ በር አንኳኩተው ገቡ? ኖ በሩ ዝግ እኮ ነው

⇒ ዝግ ነበረ ቆሙ?

⇒ ቆምን እዛ በር ላይ ውጪ

⇒ ከዛ ተከሳሹ አህመዲን መጣ? አህመዲን ጀበል መጣ

⇒ ታጅቦ መጣ? አንድ ሰው ነው አጠገቡ ያለው

⇒ ሲመጣ እንዴት ነበር በሰንሰለት ታስሮ ?እጁን የታሰረ መሰለኝ አዎ

⇒ እሺ መጣ ማን ከፈተላችሁ ቢሮውን? የቢሮው ባለቤት መጣ ከፈተ ከዛ እሱም ተፈታ እጁ አብረን ተያይዘን ገባን

⇒ እሺ ገባችሁ? አዎ

⇒ ስትገቡ ምን አያችሁ? ማለት ? ስንት ጠረጴዛ ነበረ? አረ እኔ አላስታውስም አልቆጠርኩም

⇒ ማለት ቅድም ኮምፒውተር ቢያንስ ስንት ኮምፒውተሮችን አዩ አሁን እኮ እርስዎ ታዛቢ ስለሆኑ ያዩትን እያስታወሱ ይንገሩን ?ከጊዜ እንፃር እኮ ነው

⇒ ስንት ኮምፒውተር ነበር ቢሮ ላይ ?እኔ እንጃ ሁለት ኮምፒውተር ይመስለኛል

⇒ ምን አይነት ላፕቶፕ እና ትልቁ ነው ላፕቶፕ ያውቃሉ ትንሹ ኮምፒውተር ?አውቃለሁ

⇒ ሁለቱ እንደዛ እንበላቸው ?በዛ ቀን የለም ላፕቶፕ እኮ የመጣው በ5/1ኛ ወር ነው

⇒ አቤት?በ5/1ኛ ወር አህመዲን ጀበል ሲመጣ ነው ላፕቶፑን ሲከፍት ያየሁት ድጋሚ ሲመጣ አህመዲን ጀበል

⇒ በ25/1ኛ ወር?አደለም ድጋሚ በ5/1 ደግሞ አህመዲን ጀበል ድጋሚ ቀርቧል እኮ ከነላፕቶፑ

⇒ እሺ በመጀመሪያው በ25/12/2004 ስላለው ነው እየጠየቅኩት ያለው የዛን ቀን ስንት ኮምፒውተር ነበረ እዛ ማእከላዊ?አላስታውስም

⇒ እሺ አቀማመጣችሁ እንዴት ነበረ ?ተደርድረናል እኮ አብረን እያወራን እኮ ነው ከነሱ ጋር

⇒ እስቲ ማን ከማንጋር ተቀምጦ ነበረ? እኔ እና አንድ አስራት የ[illegible]ል ል[illegible]



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ የት.ጋ ተቀምጣችሁ ነበረ እስቲ አሁን እኛ በቦታው ስለሌለን ለእኛ ያስረዱን አቀማመጣችሁ በቢሮ ውስጥ መርማሪዎች አሉ?ልክ እንደ እናንተ ማለት ነው አሁን እንደዚህ 3 ሰው ተቀመጥን እሱ አጠገባችን ሁለታችን ምስክሮች እንደዚህ አብረን እያየን ማለት ነው

⇒ መርማሪዎቹስ የት.ጋ ነበሩ? መርማሪው ከፊት ለፊታችን መሰለኝ እነሱ አዎ

⇒ አቤት?ከፊት ለፊታችን እነሱ እኛ አብረን ነን ከሱ.ጋር

⇒ መርማሪው ሌላኛው ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ነበር?እ?ሌላኛው ጠረጴዛ እና ወምበር ላይ?አዎ ይሆናል እንግዲህ እኔ አላስታውስም

⇒ እሱ አጠገብ ኮምፒውተር ነበረ?እ? መርማሪው አጠገብ ኮምፒውተር አልነበረም?

⇒ እኔ እሱ እራሱ ይሄኛው የያዘውን ነው የማውቀው

⇒ ድምፆን ከፍ አድርገው ይናገሩ ?እሱ የተጠቀመበትን ነው ያየሁት

⇒ አንድ ኮምፒውተር ብቻነበር? እሱ የተጠቀመበትን አዎ እሱን ነበረ የማየው

⇒ ከዛ እሱ ከሚጠቀምበት ውጪ አሌላ ኮምፒውተር አልነበረም ቢሮ ውስጥ ? ትዝ አይልኝም

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር አሁን በ 25/12/2004 ስላለው እዚያ ላይ ኮምፒዩተር ከፈተ ብለዋል አሁን እስረኛው ገባ እንደገባ ዝም ብሎ ሄዶ ኮምፒዩተሩ ላይ ቁጭ ብሎ ነው የከፈተው ?
- ግባ እለፍ እና እዚያ ጋር ቁጭ በል ተባለ እንትን አለ
- እኮ ግባ ተባለ ቁጭ በል ተባለ ?
- አዎ
- ከእዚያስ ምን ተባለ አልታዘዘም ?
- በቃ እራሱ ነው ገባ መነካካት ጀመረ እኛ ቁጭ ብለን ማየት ነው
- መርማሪው ክፈት ሳይለው መርማሪው ክፈት ሳይለው ነው እራሱ የጀመረው ?
- የተጠራው እራሱ ለእዚያ ጉዳይ አይደለም እንዴ ሲመጣ ለእዚያ ጉዳይ
- በምን አወቁ በእዚያ ጉዳይ ስለመጠራቱ እርሶ ቢሮ ውስጥ ከመጣ በኋላ ስላለው ሁኔታ ነው የሚያውቁት ከእዚያ በፊት ያለውን ያውቃሉ ?
- አይደለም መጥቶ በቃ ቀጥታ እዚያ ውስጥ ገባ ኮምፒዩተሩ ጋር እኛም አብረነው ገባን
- የእርሶ ታዛቢነት አሁን ቢሮ ውስጥ ከገባ በኋላ ያለውን ነው እርሶ ቢሮ ከውጪ መጣ እንጂ ከመምጣቱ በፊት ውጪ ተነጋግራችዋል እንዴ ከአህመዲን ጋር ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አልተነጋገሩም አይደል ?
- የለም አዎ
- ስለዚህ መጣ እናንተ ልትታዘቡ ገባችሁ ገባ ቁጭ በል ተባለ ከእዚያ በኋላ ኮምፒዩተሩን ክፈት አልተባለም ?
- እኔ ትዝ አይለኝም በቃ ብቻ አዎ ከፈተ እንትን ማለት ጀመረ በቃ
- ድምፅዎ አይሰማም ?
- ሪከርድ ይገባል ትዝ አይለኝም ሲመጣ መነካካት ጀመረ ነው ያለው ሌላ ጥያቄ
- ኮምፒዩተሩ ከእዚያ በፊት ይከፈት ወይም እሱ ይከፈተው በምን ያውቃሉ ?
- እሱ ገብቶ ሲነካካ ስላየሁት ነዋ
- ማለት ኮምፒዩተር መነካካት የተከፈተን ኮምፒዩተር መነካካት አለ እራሱ ደግሞ መክፈት አለ እርሶ እርግጠኛ መሆን ይችላሉ እንዴ ?



1033 2883

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እራሱ ሲነካካ ነው ያየሁት
- ኮምፒዩተሩ ለማንኛውም ትልቅ ኮምፒዩተር ነው አይደል የጠረቤዛ ኮምፒዩተር ?
- አዎ በጣም ቆይቷል እኮ ትዝ አይለኝም ትልቅ ነው አዎ
- ኮምፒዩተሩም ትዝ አይሉትም የተከፈተው ?
- ትልቅ ነው አዎ
- ትልቁ ነው ?
- አዎ
- ይሄ ኮምፒዩተር የእኔ ነው አለ እንዴ ?
- አዎ
- የእኔ ኮምፒዩተር ነው አለ ?
- የራሱ ኢሜል እኮ ነው እንትን ብሎ /ግልፅ ያልሆነ/
- ለምጠይቆት አዎ ወይም አይደለም እያሉ ይመልሱ ድምፆዎን ከፍ አድርገው ይሄ ኮምፒዩተር የእኔ ኮምፒዩተር ነው ብሎ ከፈተው ?
- ትዝ አይለኝም
- የራሱ ኢሜል ይሉ ነበር የራሱ ኢሜል መሆኑን በምን አወቁ ?
- እንዴ ፕሪንት እየተደረገ ሲወጣ እኮ የራሱ ወረቀት መሆኑን ፈረመበት እኮ
- ስለዚህ ፕሪንት እየደተረገ ሲወጣ እኮ የራሱ ወረቀት መሆኑን ፈረመበት
- ስለዚህ ፕሪንት ተደርጎ ሲወጣ ስላዩ የራሱ ኢሜል ብለው ፈረሙ?
- የራሴ ኢሜል ብሎ እራሱ ከእኔ ኢሜል የወጣ እያለ የእሱን ፊርማ ሳላይ እኔ አልፈረምኩም
- የራሴ ኢሜል ብሎ ስለፈረመ ነው ከራሱ ኢሜል የወጣ ያሉት ?
- አዎ
- በ 5/1/05 ስላለው ነው አሁን የምጠይቆት አሁን በእዚያን ቀን እንደዚሁ መጣ እናንተ እንዳለፈው ውጪ ነበር የቆማችሁት ?
- አዎ ውጪ ነው
- ከእዚያ እስረኛው መጣ ተያይዛችሁ ገባችሁ ?
- አዎ



1834

2584

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእዚያን ቀን ስትገቡ ስንት ኮምፒዩተር ነበር ?
- አላስታውስም
- አያስታውሱም ?
- አዎ
- ከእዚያ ምን ሆነ እስቲ ገባ
- ኮምፒዩተር ሳይሆን የእዚያን ጊዜ ደግሞ ላፕቶፕ ነው
- ድምፆዎን ከፍ አድርጉ ?
- ላፕቶፕ ነው ያው ከፈተ ፕሪንት እየተደረገ ወጣ ወደ
- ላፕቶፑ የት ጋር ነበር የተቀመጠው ?
- እዚያው ጠረቤዛ ላይ ነው
- ጠረቤዛ ላይ ተቀምጦ ነው ያገኛችሁት ስትገቡ አይደል ?
- አዎ
- ላፕቶፑ ብራንዱን ያስታውሱታል ማለት ዓይነቱን አያስታውሱትም ?
- ከ 8 ወር ከ 7 ወር
- አያስታውሱም እሺ እላዩ ላይ ሌላ በእጅ ፁሑፍ የተፃፈበት ነገር ነበር ?
- ምን አሉኝ
- ላፕቶፑ ላይ የእጅ የተፃፈበት ነገር ነበር ?
- እኔ አላየሁም እሱን ትዝ አይለኝም
- ከአህመዲን እና ከአህመድ ማን ነበር ቀድሞ የመጣው ከአህመዲን እና ከአህመድ ማን ነው ቀድሞ የመጣው ?
- ከአህመዲን ጀባል /ግልፅ ያልሆነ/ አህመዲን ጀባል መጀመሪያ ገባ
- መጀመሪያ አህመዲን ጀባል ነው የገባው ?
- አዎ
- ሲገባ እጁ ላይ ምን ነበረ ?
- ሰንሰለት ውጪ ነበር ሰንሰለቱ ተፈታ ገባ
- ገባ እናንተ ቁጭ ብላችሁ ቀድማችሁ ነበር ?



1035

2580

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ውሬቢ
- ውሬቢ ላይ ቆማችሁ ነበር ?
- አዎ
- እሺ ከእዚያ ገባችሁ ?
- ኮሪደር ላይ ቆመን
- ከእዚያ በኋላ አልፈርምም ይሄ እኔ ከታሰርኩ በኋላ ወደ ኢሜል ወደ ኢንቦክስ የገባ ነው ብሎ ከፖሊሱ ጋር ሲነጋገሩ ነበረ ?
- እንደዚህ ዓይነት ጭቅጭቅ የለም እራሱ ሲወጣ እራሱ እየፈረመ ለእኔ ይሰጠኛል
- እኮ ለፖሊሶሱ እንደዚህ ብሎ ሲነግረው አልሰማህም ?
- ኧረ እንደውም
- እሺ መጀመሪያ ቁጭ እንዳለ ኮምፒዩተሩን ለመክፈት የሞከረው ማን ነበር አህመዲን ነበር ከጎኑ ያለ ሰው ነበር ?
- እራሱ ነው
- ፓስወርድ እምቢ ብሏቸው በወረቀት ከተፃፈ ፓስወርድ ላይ እምቢ ብሎናል ፓስወርድ እና ፓስወርድ ንገሩን ብለው በስልክ ሲጠየቁ ነበረ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አልሰማህም ?
- አዎ ትዝ አይለኝም
- ትዝ አይልህም ?
- አልሰማሁም አልሰማሁም
- ስልክ ሲደዋወሉ አልሰማህም ?
- አልሰማሁም ስልክ የሚባል የለም
- እሺ የፊርዶስ ደም ይጣራል የሚለውን መጀመሪያ ኢሜል ላይ ስለፈረምኩበት አልፈርምበትም ብሎ ነበረ ይሄኛውን መጀመሪያ ኢሜል ላይ መጀመሪያ ስለፈረምኩበት አሁን በድጋሚ አልፈርምምበትም ብሎ ሲከራከር ነበረ ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሲከራከር አልሰማሁም ሲፈርም ነው በቃ እኔ ሲፈርም እሱ የፈረመውን ነው እኔ የፈረምኩት እኮ
- እሺ በመካከሉ የመጣ ፖሊስ ነበር አልነበረም ?
- ኧረ ማንም የለም
- ፖሊሱ መጥቶ ይሄኛው ስለያም የሚያወራ ስለሆነ ስራ አታብዙ ይሄንን አትፈርሙበት ተብለው ፖሊሶቹ እርስ በእርሳቸው የተነጋገሩት አልነበረም ?
- ኧረ የለም ምንም ነገር የለም
- አላስታውሰው ብለህ ነው ወይስ ?
- አይ የለም የለም ስለሌለ ነው
- ሁሉም ላይ ታዛቢ ታዛቢ እያልክ እየፃፍክ ነው የፈረምከው ወይስ ገፁ ብዙ ስለነበረ የመጀመሪያው ላይ ታዛቢ ብለህ ከእዚያ በኋላ /ግልፅ ያልሆነ/
- ለምሳሌ እሱ እኔ ላይ የተገኘ ስሙን ፅፎ ነው የሚፈርመው ሲፈርም እኔም ከእሱ ኢሜል ሲወጣ አይቼአለሁ ብዬ ፈረምኩ
- ምን ሲል አይቼአለሁ ሁሉም ገፅ ላይ እንደሱ እያልክ ነው የፈረምከው ?
- የተወሰኑ መጨረሻ አካባቢ ምን ተባለ በቃ ፊርማቸውን አስቀምጡ ከላይ /ግልፅ ያልሆነ/ ተባለ በስምምነት ነው
- እኮ በስምምነት ዝም ብሎ ፊርማችሁን ብቻ አስቀመጣችሁ ?
- አዎ ስማችን ግን አለ
- እሺ ፕሪንት እምቢ ብሏችሁ ነበር አልነበረም ፕሪንት ለማድረግ ፕሪንተሩ ?
- አላለም
- ከኮምፒዩተሩ ላይ እየተጫነ ሶፍትዌር አልነበረም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አላየሁም ነው ወጥተህ ነበር እንዴ በመካከል ?
- ትዝ አይለኝም
- አልወጣህም አንተ በመካከል ?
- አልወጣሁም



1037

1587

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያው ነበርክ ?
- አዎ
- እሺ አህመድ ሙስጠፋን በተመለከተ ነው አህመድን በተመለከተ አህመድም እንደዚያው መጥቶ የራሱን ኮምፒዩተር እራሱ ነው የከፈተው ?
- እራሱ ነው
- አቀማመጣችሁ እንዴት ነበር ?
- መደዳ ተደርድረን እኮ ነው እንደእነሱ እንደዳኞቻችን
- እንደዚህ ተደርድራችሁ ነበር ?
- አዎ
- ከእዚያ አህመድ መጥቶ ኮምፒዩተሩን እራሱ ከፈተው ?
- አዎ
- የራሱን ኮምፒዩተር ማለት ነው
- አህመድ ሙስጠፋ ኮምፒዩተሩን ሲከፍት እንዲከፍት አልታዘዘም አይደል እንዲከፍት ታዟል በመርማሪው ?
- ትዝ አይለኝም
- ፕሪንት አድርግም አልተባለም ፕሪንት አድርገህ አውጣም አልተባለም ፕሪንት አድርገህ አውጣ አላለውም መርማሪው ?
- እሷ ያው እራሱ እንትን አለ እና ከእዚያ ፕሪንት ማድረግ ሲጀምር እኛ እየተቀበልነው እሱ ከፈረመ በኋላ እኛን አስፈረሞናል
- ምን እንደምትፈልጉ በምን አወቀ ምን ልትታዘቡ እንደመጣችሁ ካልተነገረው ለምን እንደመጣችሁ ታዛቢ እንዳለም አልተነገረውም እንዴ ?
- እንዴ ተነግሮታል ያው አንተ ስትፈርም ስታወጣ ከራስህ ስትፈርም የራስህ መሆኑን እነሱ ደግሞ አይተናል እያሉ ይፈርማሉ እኛም አይተናል እያልን ፈረምን
- እኮ እናንተ ታዛቢ ገብታችዋል መርማሪዎች አሉ እስረኛው መጣ እና ቁጭ ብሎ ከፍቶ ፕሪንት አድርጎ አወጣ ከእኔ ኢሜል ነው አለ ከእዚያ እናንተ ፈረማችሁበት በእዚህ መልክ ነው የሄደው ?



1038

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከውጪ ኡበረን ገባን ተከፈተ ፕሪንት እያደረገ ወጣ እሱ ሲፈርም እኛም ~~ፈረምን ኡበረን~~ ሁላችንም ገባን
- እንጂ እነዚህ ታዛቢዎች ናቸው ስለዚህ አውጣ እና አሳያቸው ኢሜልህን ክፈት
- አይ ዞሮ ዞሮ እሱ ሲፈርም እኛ ታዛቢ እያልን ስንፅፍ ያየነውን ስንፅፍ ያየል እሱ እያየ ኡበረን ነው የሄድነው ከእሱ ኢሜል ሲወጣ አይተናል እያልን ስንፈርም ያየናል እኮ እሱ
- አህመድ ሙስጠፋን በተመለከተ ፕሪንተሩ እምቢ ብሏችሁ ፕሪንት የተደረገ ስላለ እሱ ላይ ፈርምበት ተብላችሁ የፈረማችሁበት ወረቀት የለም ?
- የለም
- ፕሪንት ተደርጎ ነው የፈረማችሁት ?
- ሁሉም ፕሪንት እየተደርገ ወጣ እሱ ሲፈርም እኛ የእሱን እያየን ነው የፈረምነው የራሱ መሆኑን ሳይፈርም እኛ አንፈርምም እኮ
- አህመዲን ጀባልም ላይ ተመሳሳይ ነው አይደል መጣ ቁጭ ብሎ ኮምፒዩተሩን ከፍቶ ፕሪንት አደረገ ፈረማችሁ እንጂ ከእዚህ ውጪ ስለታዛቢዎች መኖርም ፕሪንት አድርጎ እንዲያወጣም አልታዘዘም አይደል ?
- ፕሪንት አድርጎ እንዲያወጣ ታዞ ነው እራሱ ፕሪንት እያደረገ የሚያወጣው
- ታዞ ነው ?
- የራሱ መሆኑን ካወቀ ፕሪንት ያውቀዋል እራሱ እንትን አለ ሲያወጣ እኛ ፈረምን ተመሳሳይ ጥያቄ
- እሺ እነዚህ ከአህመድም ሆነ ከአህመዲን
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አህመዲን ጀባልም ሆነ በአህመድ ሙስጠፋም ሆነ በአህመዲን ጀባል ኢሜል አድሬስ የተላከ ወረቀቶችን አይተዋል እርሶ አያውቁም አይደል ?
- ማለት አልገባኝም
- በኢሜል አድራሻቸው ለእነሱ የተለከ ?
- ከራሱ ኢሜል አይደል እንዴ የሚወጣው እንዴት ነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/ በእነዚህ ሰዎች የኢሜል አድራሻ ለእሱ ተብሎ የተላከ ወረቀት አይተዋል ያስታውሳሉ ?
- እየታተመ ፕሪንት እየሆነ የወጣው የራሱ እኮ ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ እነዚህ የወጡት ወረቀቶች እርሶ ፕሪንት ተደረጉ እያሉ ወጡ የሚሏቸው ወረቀቶች ፕሪንት ተደርጎ ወጡ የሚሏቸው ወረቀቶች ወይም ሰነዶች ለአህመዲን ጀባል ለአቶ አህመዲን ጀባል ወይም ከአቶ አህመዲን ጀባል ተብሎ የተላከ መሆኑን አያውቁም አይደል አላረጋገጡም ?
- አላስታውስም ቆይቷል /ግልፅ ያልሆነ/
- እንደዚህ ዓይነት ወረቀት መኖሩን ያውቃሉ ?
- ሊኖር ይችላል እኔ ትዝ አይለኝም
- አያውቁም እርግጠኛ አይደሉም ?
- ቆይቷል ጊዜው
- እኮ ጊዜው ስለቆየ አያውቁም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እነዚህን ሰነዶች ፕሪንት ያደርግ የነበረው ማን ነው ?
- እራሱ
- ማን ?
- ማን 2ቱም አህመዲን ጀባልም እራሱ ይሄኛውም ሙስጠፋም ለራሱ
- በ2ቱም ኬዝ በኮምፒዩተሩም በላፕቶፖቹም ጊዜ ፕሪንት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ፕሪንት ያደረገው ማን ነው ነው እራሳቸው ነው ፕሪንት የሚያደርጉት የሚያዙትም እነሱ ነበሩ ?
- ያው ወረቀት ውስጥ ተደርጎለታል ማሽኑ እንትን ያለ ነው
- ከማሽኑ ማን ነበር የሚያወጣው ፕሪንት ሲደረግ ከማሽኑ ማን ነበር የሚያወጣው ?
- አብሮ ያለው እዚያ ክፍል ውስጥ እያወጣ ለእሱ ይሰጠዋል እዚያው አጠገብ እኮ ነው ተደርድረን እኮ ነው



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ሌላ ሰው ነው የሚያወጣው ማለት ነው ?
- እራሱ ያወጣል ከእዚያ ይፈርማል መደዳውን ነን እየፈረመ /ግልፅ ያልሆነ/
- ፕሪንተሩ የማን ነው ?
- የመርማሪዎቹ ይመስለኛል የእዚያኔ ትዝ አይለኝም
- ላፕቶፖቹሳ የማን ናቸው ?
- አልጠየኩም ንብረት ይሄ የማን ነው የማን ነው ብዬ
- ላፕቶፖቹ የማን እንደሆነም አያውቁም ?
- እሱማ የራሱ መሆኑ ነው
- በምን አወቁ ?
- ቅድም የመለስኩ ይመስለኛል ከራሱ እንደሚወጣ እኮ እየፈረመ የእኔ ነው ማለት የራሱ ነው ማለት ነው
- ፖሊስ ነው የአህመዲን ነው የአህመድ ነው ብሎ የነገሮት ወይስ እርሶ አረጋግጠዋል ?
- ሲወጣ ከእኔ ኢሜል የወጣ ብሎ ካለ የራሱ አይደል እንዴ
- ልክ ኖት እርሶ የሚሉኝ ሰነዱን ነው እኔ ደግሞ ላፕቶፖችን ነው የምሎት
- ይሄ ተጠይቋል እየደጋገሙ ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/ አልተጠየቀም ምናልባት ፍ/ቤቱ በማጣሪያነት የሚጠይቀው 2ቱን ነገር ነው ወረቀቱን ሳይሆን እኔ የጠየኩት
- ላፕቶፑ የማን ነው ታውቃለህ ምናምን ተብሎ ይጠይቋል
- ማርኩ ነው የተጠየቀው የተከበረው ፍ/ቤት የማን ነው አልተጠየቀም
- ይሄንን ይለፍ እና ሌላ ተጠይቋል ሌላ መከታተል አለመከታተል ሌላ ነገር ነው
- አንድ ብቻ የመጨረሻ ጥያቄ ልጠይቆት /ግልፅ ያልሆነ/ ኢንተርናሽናል እኔ ከታሰርኩ ከ 1ወር በኋላ የላከው ነው እዚህ ላይ አልፈርምም ሲልስ አህመዲን ከእዚያ ወደ ኢንቦክስ የተላከ ነው ብለህ የእኔ ኢሜል ውስጥ የተገኘ ብዬ አልፈርምም ?
- ሲልም አልሰማሁም ትዝ አይለኝም አልሰማሁም አላየሁም [illegible] እየፈረመ ለእኛ ይሰጠናል እኛ እንፈርማለን
- ጨርሰናል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- *በቀረበ መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ዳግመኛ ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ ካላችሁ*
- አቶ ወንደሰን አቶ አህመዲን አቶ አህመድ አቶ አህመድ ጀባልም አቶ አህመድ ሙስጠፋም ኮምፒዩተሮቹ የእኔ ናቸው አይደለም የሚል ክርክር ነበረ ከፖሊሶች ጋር ?
- ኧረ የለም
- ይሄ ላፕቶፕ የእኔ አይደለም ይሄ ኮምፒዩተር የእኔ አይደለም ?
- የለም ምንም ክርክር የለም የለም ምንም ክርክር አልሰማሁም
- ፓስወርድህን ተናገር ተብሎ የተጠየቀ ሰው አለ ?
- ማንም የጠየቀ የለም እራሱ ማንም የጠየቃቸው የለም
- ስለዚህ ፓስወርዱ እንዴት ነው ከየት ነው የመጣው ፓስወርዱ ?
- እራሱ ነዋ
- ማን ነው እራሱ ለምሳሌ ?
- ለምሳሌ አህመዲን ከሆነ እራሱ አህመዲን ጀባል ነው ሙስጠፋም ከሆነ
- ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ስትጠየቅ ፓስወርድ እየተደወለ ሲጠየቅ ነበር ተብሎ ተጠይቀህል?
- ስልክ የለም እዚያ ቢሮ ውስጥ
- ስልት የተደወለ ስልክ የለም ?
- የተደወለ ስልክ የለም
- መጥተው እራሳቸው ናቸው የከፈቱት ?
- ያ
- ላፕቶፖቹ ኮምፒዩተሮቹ የተገኙት የት ነው ?
- እዚያው ቢሮ ውስጥ
- ቢሮ ውስጥ ?
- አዎ
- እነዚህ ላፕቶፖች ከአህመዲን ሙስጠፋ ወይም ከአህመዲን ጀባል ወይም ከአህመድ ሙስጠፋ በብርበራ ይገኙ አይገኙ የምታውቀው ነገር አለ ከእዚያ በፊት ይገኙ አይገኙ?
- አላውቅም



http://ethcriminalawnetwork.com/

- የምታውቀው ነገር የለም ?
- አዎ
- ክፈት ተብሎ የታዘዘ ሰው አለ ማለት እዚያ እናንተ የተገኛችሁበት ምክንያት አልተነገራቸውም ?
- ያው እቡ በፍት ፕሪንተ ቢደረግ
- ይኸውልህ ወንደሰን እናንተ እዚያ ስትገኙ ምንድን ናችሁ ተባላችሁ ቤተሰብ ናችሁ ጎብኚ ናችሁ ተባላችሁ ?
- ታዛቢ ነን እንጂ ልንታዘብ ነው
- እንድትታዘቡ ነው ስለዚህ እናንተ እዚያ ልትታዘቡ መሆናችሁን አልተረዱም እነ አህመድ ሙስጠፋ ?
- ተረድተዋል
- መረዳታቸውን በምንድን ነው የምታውቀው ?
- ማለት እነሱ /ግልፅ ያልሆነ/የሰጡንን ከእነሱ ኢሜል ሲወጣ አይተናል ብለን ስንፈርም ያዩናል እኮ
- ስለዚህ ተገንዝበዋል ?
- አዎ
- ተረድተዋል ?
- አዎ
- ታዛቢ እንደሆናችሁ ?
- አዎ
- የዐቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የፍ/ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ ስለሌለ ምስክሩ ተሰናብተዋል ምስክር ጨርሰዋል ቀጣይ ምስክር
- በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ
- በፍ/ቤት መዝገብ 70ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በዐቃቤ ሕግ የማስረጃ ዝርዝር በምን ማን ይባላል የዐቃቤ ሕግ ምስክር የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ?
- መኮንን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የመጠጥ ለምንድን ነው ?
- አቶ ሰይድ አሊ
- ሰይድ አሊ
- ሰይድ አሊ ምን ለማድረግ ሰይድ አሊ ምስክር ?
- ታዛቢነት ስላየሁ ማለት ነው
- እሱን ለመመስከር ነው ?
- አዎ
- ሰይድ አሊን ያውቁታል የትኛው ስንተኛ ተከሣሽ ኖት ምስክሩ 16ኛው ተከሣሽ ሰይድ አሊን ጠቁሞ አሳይቷል ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቅረብ
- አቶ መኮንን ?
- አቤት
- አሁን የጠቆሟቸውን ሰው በምንድን ነው የሚያውቋቸው የት ነው የሚያውቋቸው ?
- እኔ አላውቃቸውም በጽ/ቤታችን በቀበሌ መጥቶ እንድንታዘብ ስለጠሩን ነው
- ማን ነው የጠራዎት ?
- የፌዴራል ወንጀል መርማሪ
- መርማሪ ምን ብሎ ጠራዎት ምን ተብለው ነው የተጠሩት ?
- እንድንታዘብ
- እንድትታዘቡ ?
- አዎ
- ምንድን ነው ምን እንድትታዘቡ ?
- እኔ የምታዘበው ያለውን ነገር ከእሱ ውስጥ መጀመሪያ ፍ/ቤት ወረቀት ስላወጣ እዚያ ተነበበልን
- ምን የሚል ተነበበላችሁ ?
- የብርበራ ትዕዛዙ ማለት ነው
- የብርበራ ትዕዛዝ ?
- አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ይላል የፍ/ቤት ትዕዛዝ የብርበራ ትዕዛዙ ?
- የብርበራ ትዕዛዝ ቤቱ እንዲታይ
- ይላል ?
- አዎ
- ለማን ለማን ተነበበ የት ነው የተነበበው የት ነው የተነበበላችሁ ?
- የት ቤት
- የብርበራ ማዘዣው ተነቦልናል ብለኸናል ?
- ማዛዣው የወጣው የአንድ የአቶ /ግልፅ ያልሆነ /
- የት ነው ቤቱ የት ይገኛል ቦታው ?
- ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ
- የቤት ቁጥሩን ታስታውሰዋለህ ?
- አላውቅም
- አታስታውስም ?
- አዎ
- ምንድን ነው የተበረበረው ?
- የተመረመረው የተገኘውን ልንገራችሁ አይደል
- አዎ ንገረን እሺ ?
- የተገኘው አንድ ላፕቶፕ ነው የተገኘ አንድ ላፕቶፕ እና ከእነ ፍላሾቹ ማለት ነው
- ስንት ፍላሽ ?
- ፍላሾቹን አልቆጠርኳቸውም ግን ከእነ ፍላሾቹ ነው የተገኙት
- ሌላስ ?
- ሌላ ቪሲዲ 37 የቴፕ ካሴት 32 የተለያዩ በአረብኛ የተፃፉ መፅሐፎች 12 በቁርጥራጭ የተፃፉ በአማርኛ እና በአረብኛም በአማርኛም የተፃፉ በራሪ ወረቀቶች ነበሩ ለጊዜው
- ይዘታቸውን የምታስታውሳቸው አሉ ?
- የቁርጥራጮቹን ብዛታቸው ብዙ ናቸው በብዛት
- ይዘት ምን ምን ይላል ለምሳሌ ያነበብከው ካለ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነው የሚለው አንዱ ላይ ኢህዴግን አንመርጥም አናስመርጥም ይላል እንደዚያ ነው
- ምን ይላል ?
- ኢህዴግን አናስመርጥም አንመርጥም
- የሚል አለ ሌላስ ?
- በእጅ የተፃፈ ማለት ነው
- ሌላስ ?
- ሌላ ከመኖሪያ ቤቱ ወጥተን ቄራ ያገለገሉት መኪናዎት መሸጫ አለ እዚያ ስንሄድ አንድ ላፕቶፕ እና አንድ 2 ሲዲ 3 መፅሐፎች
- ይሄ ሌላ ቀን ነው የመጀመሪያ ?
- በእዚያው ቀን
- መቼ ቀን ነው ቀኑን ንገረን እስቲ ?
- ቀኑ ሐምሌ 12
- ዓ.ም ?
- 2004
- ሰዓቱስ ?
- ሰዓቱ 11 ሰዓት
- 11 ሰዓት ?
- አዎ
- እሺ 11 ሰዓት ቀን ነው ማታ ?
- ማታ ማለት ነው ወደ አመሻሽ አካባቢ ማለት ነው
- ወደ አመሻሽ አካባቢ ?
- አዎ
- ይሄ በተመሳሳይ ቀን ወደ ሌላ ቦታ ሄዳችዋል ?
- ወደ ሌላ ጉዳይ
- ሌላ ቦታ ቅድም ያልከን መኪና መለዋወጫ ?



1046 2596

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ ላይ እዚያው እያለን ወንጀል መርማሪው ደወለ /ግልፅ ያልሆነ/ መሰለኝ ከእዚያ ወጣን እና እዚያ ሄድን
- የት ሄዳችሁ ?
- እስከ 3 ሰዓት ቁራ ሄድን ማለቱ ነው
- የት ሄዳችሁ የት የሚባል ቦታ ?
- ቁራ
- ቁራ ?
- አዎ የመኪና
- ማን ማን ሆናችሁ ነው የሄዳችሁት ?
- ጌትነት ቶሎሳ እና ጌታቸው የሚባል ጋር ነው
- የሄዳችሁት ?
- አዎ
- ተከሣሹስ ?
- ተከሣሹ አሊ ሰይይ ሰይድ አሊ
- ሰይድ አሊ ?
- አዎ
- የት ነበር እሱ ?
- እኔ እንግዲህ እዚያው ነው ያየሁት
- እኮ ከየት ነው የመጣው እዚያው ቤቱ ነው እንዴ ያገኛችሁት ብርበራ ስትገቡ ?
- አይ ቤቱን አናገኝም መኪና ላይ መጥቶ ነው ያገኘነው መኪና ላይ ነው
- ከማን ጋር ?
- ያገኘነው
- ከማን ጋር ሆኖ ?
- ፖሊሶቹም አሉ
- ስትገቡ እንዴት ገባችሁ ?
- ስንገባ የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ተነበበልን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን ነበር ከእናንተ ውጪ ሌላ ማን ነበር ?
- ከእኛ ውጪ የፌዴራል ፖሊሶች አሉ ወንጀል መርማሪዎች አሉ
- ሌላስ
- ሌላ ቢቃ የለም
- እዚያ የምትበሩበሩበት ሰው አልነበረም እንዴ ?
- እዚያ የገባንበት አልነበረም ሰው
- ማንም ሰው አልነበረም ?
- አዎ
- ቤተሰብ ምናምን አልነበረም ?
- ቤተሰብ ከእዚያ በኋላ ነው ተደውሎለት የመጡት
- ማለት ከገባችሁ በኋላ ?
- አይደለም ሳንገባ ነው ቁልፍ ተቆልፎ ነበር
- እሱን ንገረን በደንብ አብራርተህ ንገረን ስትገቡ ማን ማንን አገኛችሁ ቤቱ ውስጥ እንዴት ገባችሁ የሚለውን ንገረን ?
- ቤቱ ውስጥ ማንም ሰው አላገኘንም
- እኮ እንዴት ከእዚያ ከየት እንዴት ገባችሁ ታዲያ በሩን በሩ ወደ በሩ እንዴት ገባችሁ በሩን ማን ከፈተላችሁ ?
- በሩማ ቁልፍ ነበረ ከእዚያ አምጥተውልን የከፈቱት
- ማን አመጣላችሁ ?
- ሚስቱ ናት አሉ እንዲህ አላወኩም
- ሚስቱ ናት እሺ ከእዚያስ ?
- ከእዚያ ያው የመበርበሪያ ትዕዛዝ ተነበበልን ያው ፍተሻ ተጀመረ
- ፍተሻ ተደረገ ቅድም የነገርከን ነገሮች ተያዙ ቅድም የገለፅካቸው እቃዎች ተይዘዋል ?
- ቅድም የነገርኩ
- የዘረዘርከልን እቃዎች ተያዙ ?
- አዎ የዘረዘርኩት እቃዎች ተገኙ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ ምን አደረጋችሁ እቃዎቹን ወዴት ወሰዳችሁ ?
- እቃውን ያው ይዘን ነው እንግዲህ እቃው ተይዟል ያው እቃው እቃውማ በወንጀል ስለተያዘ ወደ ምርመራ ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- እኮ እሱን ወደ ፖሊስ ምርመራ ይዛችሁ ከመሄዳችሁ በፊት ያደረጋችሁት ነገር አለ ?
- የለም
- ተከሣሹስ ማለት ስለንብረቶቹ ሲወሰዱ ያለው ነገር የለም ?
- አይ እሱም የእኔ ነው እቃ ብሎ እየፈረመ ነበር
- ምን ላይ ፈረመ ?
- ወረቀት ላይ
- ምን ዓይነት ወረቀት ላይ ?
- ወረቀት
- ማለት እዚያው የተያዘው ወረቀቱ ላይ ነው ወይስ ሌላ ወረቀት ላይ?
- አይ ቃሉን ነው የሰጠ በቃ
- ምን ብሎ ?
- የእኔ ነው ብሎ የተያዘብኝ ሁሉ የእኔ ነው ብሎ ማለት ነው
- የእኔ ነው ብሎ ፈረመ ?
- አዎ
- ሌላ ሰው ማን ፈረመበት ?
- ሌላ እኛ ያየነው ፈርመናል
- ፈርማችዋል ?
- አዎ
- ስንት ሰው ሆናችሁ ?
- 3
- 3 ሆናችሁ ታዛቢ ማለት ነው ?
- አዎ
- እሺ ወደ መኪና መለዋወጫ ነው ያልከን ?



1049 2598

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ በኋላ ከቤት ከወጣን አዎ
- እዚያ ወደ እዚያስ ማን ነው የመራችሁ ?
- እዚያም ያው ወንጀል መርማሪዎች ናቸው
- እኮ ማን ማን ሆናችሁ ሄዳችሁ ወደ እዚያ ?
- ባለጉዳዩ ያው እንትኖቹ
- ምኖቹ ?
- ወንጀል መርማሪዎች
- እናንተም አላችሁ ፖሊሶችም አሉ ተከሣሹም አለ ?
- አዎ
- እዚያ ሄዳችሁ ምን አገኛችሁ ?
- እዚያ ሄደን አንድ ላፕቶፕ እና 2 ሲዲ 3 መፅሐፍ በአረብኛ የተፃፈ
- ቤቱ የማን ነው ተባለ ቤቱ የማን ነው ?
- ቤቱ የማን እንደሆነ አላውቅም
- እኮ እንዴት ሄዳችሁ ወደ እዚያ ተከሣሹስ ?
- ተከሣሹ ነው ያሳየን
- እራሱ ?
- አዎ
- ምንድን ነው አለ ምኔ ነው አለ የሄዳችሁበት ?
- ቢሮ መስሪያ ቦታዬ ነው አለ
- የምሰራበት ቢሮዬ ነው አለ ?
- አዎ
- እዚያ ያገኛችሁት ይሄንን ብቻ ነው ?
- አዎ
- እሱንስ በተመለከተ ምን አደረጋችሁ ?
- እሱን ምን አደረጋችሁ ያው እሱ ወደ ቦታው ሄዶ እኛ ወደ ቢሮችን ሄድን

)



HDSD 2899

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወደ ቢታችሁ ሄዳችሁ ወደ ቢታችሁ ከመሄዳችሁ በፊት ንብረቱን እዚያው ትታችሁት ሄዳችሁ እንዴ ?
- እኛ ለሚመለከተው ያው እሱ ተረክቧል ለሚመለከተው ሰጠን ሄድን
- ተረከቦት የሚመለከተው ተረከቦት ሄደ እኮ ያደረጋችሁት ነገር የለም እንዴ ንብረቱን ስትወስዱ ?
- የእሱ ንብረት የእሱ ንብረትማ የአዲስ አበባ ፖሊስም አሉ ሌሎችም አሉ የምትፈልገውን ከእዚህ ምረጥ እና ወክል ተብሎ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ የእሱ ያን ጊዜ
- አይደለም አሁን ላፕቶፕ እና ሲዲዎች ወሰድን ብላችዋል ላፕቶፕ እና ሲዲ ወስደናል ብለኸናል ?
- ከእዚያ የተገኘ ነው እኮ የምነግርህ
- እኮ አዎ የተገኘውን ?
- አዎ
- እኮ እሱን ስለመውሰዳችሁ ማረጋገጫ ሰጣችሁት እንዴ ?
- ሰጥተናል አዎ
- ምን ብላችሁ ?
- ያው የእኔ ነው ብለህ ፈርም ተብሎ ፈርሟል
- እሱም ላይ ፈርሟል ?
- አዎ
- ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት
- ዋና ጥያቄ ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ አቅርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥቷል የተከሣሽ ተከላካይ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ቀጥሉ
- አቶ መኮንን የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ማን ነው ያነበበላችሁ?
- የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ
- ማን ነው ያነበበላችሁ ?
- ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ነው የወጣ ከእዚያ ሲያወጡ ተነበበ ከእዚያ በኋላ ፍተሻ ገባን
- ከፌደራል ፍ/ቤት መውጣቱን በምን አወቁ ከፌደራል ፍ/ቤት መውጣቱን በምን አወቁ ?
-



2800 1051

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በማህተሙ
- አይተውታል እርሶ አይተውታል እንዴ ወረቀቱን ፍ/ቤቱ ?
- አይቼ አዎ አይቼ ነው የገባሁት
- እርሶም አንብበውታል ?
- አዎ አንብቤ
- ምን ነበር የሚለው ምን ይል ነበር ?
- የአቶ ሰይድ  አሊ ቤት መበርበሪያ ትዕዛዝ እንዲበረበር የሚል ነው
- መቼ ነው የተፃፈው ቀኑን ያስታውሳሉ ?
- መቼ ነው ቀኑን አላስታውስም
- መዝገብ ቁጥሩን ያስታውሳሉ መዝገብ ቁጥሩን ያስታውሳሉ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ከየትኛው ፍ/ቤት እንደተፃፈ ያስታውሳሉ ?
- ያው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው የሚለው
- የት ነው የሚለው ንፋስ ስልክ ላፍቶ ነው የሚው
- ማን እኔ
- አይደለም ፍ/ቤቱ ክልሉ ምናልባት ንፋስ ስልክ ላፍቶ ስለሆነ ቅድም ሲናገሩ የእዚያ ነው የሚለው ወይስ ሌላ ነው የመጀመሪያ ደረጃ የሚሉት ፍ/ቤት የየትኛው ፍ/ቤት ነው የቄራ ነው የሚለው ልደታ ነው የሚለው የትኛው ፍ/ቤት ነው ካዩት ?
- የልደታ ነው
- የፌዴራል ?
- አዎ የፍ/ቤት መጀመሪያ ደረጃ ልደታ ነው
- የልደታ  ፍ/ቤት ነው ?
- አዎ
- እሺ ምን ምን ይፈተሽ ይላል ምን ምንድን ነው ይፈተሽ የሚለው አቶ ሰይድ ቤት ምን ምን ይፈተሽ ይላል ?
- ምን ይፈተሻል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ምን ይላል ያዩት ወረቀት ?
- ያው መበርበሪያ ትዕዛዝ መጣ ያው በእዚያ አካሄድ ገባን ያገኘውን ለመረጃ /ግልፅ ያልሆነ/ ፈትሸን አግኝተናል
- ገባኝ እዚያ ትዕዙን ካዩት መጣሪያ ነው ይፈለግ የሚለው ገንዘብ ነው ይፈለግ የሚለው ምንድን ነው የመበርበራያ ትዕዛዙ ?
- ገንዘብ አላገኘንም እኛ ገንዘብ
- አይደለም የመበርበሪያ ትዕዛዙ ላይ ምንድን ነው ይፈተሽ የሚለው ነው ጥያቄዬ ?
- ቤቱ እንዲፈተሽ ብቻ ነው
- ቤቱ ብቻ ነው ?
- አዎ
- ከቤቱ ምን ይገኝም አይልም ከቤቱ ይሄንን ነገር ካገኛችሁ ውሰዱም አይልም ?
- የዳኛ ፊርማ ምናምን አይተዋል የዳኞች ፊርማ አይተዋል ?
- አዎ አይቼአለሁ
- የስንት ዳኛ ፊርማ አዩ ?
- የ 3
- የ3 ዳኛ እርሶ የሰይድን ቤት ከእዚያ በፊት ያውቁታል ?
- አላውቅም
- ቤቱ ጋር የወሰዶት ፖሊስ ነው ?
- እኛ ቀበሌ ጽ/ቤት መጡ ከእዚያ ለታዛቢነት እንድታዩ ብለው ነው የሄድነው
- አይደለም እኔ እያልኮት ያለው አቶ መኮንን የፌዴራል ፖሊሶች ናቸው አይደል የሰይድ ቤት የወሰዶት ?
- ማን ሰይድ
- የሰይድ ቤት የወሰዶት የፌዴራል ፖሊሶች ናቸው አይደል ?
- አዎ እነሱ የጠሩን
- ይቺም ሴት የሰይድ ሚስት ነች ያሉቸች የፌዴራል ፖሊሶች ናቸው አይደል ?



1083 2602

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ያሉ
- ባለቤቱን የሰይድ ሚስት ነች ያሉት ፌዴራል ፖሊሶች ናቸው አይደል ?
- አይ ሚስቱ መሆኑን አላወኩም
- አያውቁም ሚስት መሆኗን አያውቁም ?
- አዎ
- እነዚህ የተገኙት ቪሲዲ ያሉት ቴፕ ያሉት ፅሑፎች ያሉት አንብበዋቸዋል እርሶ ?
- እኔ ርዕሱን አንብቤአለሁ
- ከርዕሱ ውጪ ያነበቡት ነገር የለም ከርዕሱ ውጪ ዘርዘር ብሎ ወደ ታች አልወረዱም ?
- ለእዚያ የዘረዘርኩት እኮ እኔ ስላየሁ እኮ ነው ይሄ ሁሉ ይገኛል ያልኩት የዘረዘርኩት ስላየሁ ነው
- እኮ አንብበዋል ሁሉንም ?
- አዎ
- ምን ይላል ?
- ምን ይላል
- ውስጡ ይዘቱ ምን ይላል ፅሑፎቹ ?
- ይዘቱ ቁርጥራጩ ላይ በአረብኛ የተፃፉ አሉ በአረብኛም የተፃፉ አለ ለእዚህ እዚያ ላይ በይዘቱ ላይ የሚለው ኢህዲግ አንመርጥም አናስመርጥም የሚል አለ
- ይሄ በኮምፒዩተር ነው የተፃፈው ወይስ በእጅ ፁሑፍ ነው የተፃፈው ?
- በእጅ ፁሑፍ
- በእጅ ፁሑፍ ነው የፃፈው ኢህዲግን አንመርጥም የሚሉት በአረብኛ የተፃፈ ነው ወይስ በእንግሊዘኛ ?
- ምን አልከ አልሰማሁም
- ኢህዲግን አንመርጥም ይላል ያሉት በእግሊዘኛ የተፃፈ ነው በአማርኛ የተፃፈ ነው ?
- በአማርኛ ነው
- በምን ዓይነት ነገር ነው የተፃፈው ?
- በእስክሪቢቶ ነው የተፃፈው



1054 2603

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስንት ገፅ ነው ?
- ገፁን አልቆጠርኩም
- ብዛት አለው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ብዛት አለው የለውም ?
- ብዛት አይኖርም አዎ
- አንድ ገፅ ነው ?
- ገፁን አላወኩትም
- ኢህዲንግ ለምን አንመርጥም ይላል ለምንድን ነው አንመርጥም የሚለው ካነበቡት ?
- እሱንማ ወረቀቱ ላይ ስላለ ስላገኘን ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ለምን እንደሆነ አላወኩም እኔ ለምን እንደሆነ አላወኩም
- እኮ አንብቤአለሁ ስላሉ እኮ ነው አላነበቡትም ሙሉ በሙሉ ?
- ባነብም ርዕስ ውስጥ ማለት አንመርጥም ጥላቻ ነዋ በቃ ሌላ ምን
- እኮ ጥላቻው ምን ምን ይላል ካነበቡት ግለፁ ለምን አንመርጥም በእዚህ በእዚህ ይላል ወይስ አይልም ምክንያት የለውም ?
- አንመርጥም አናስመርጥም ይላል ፅሑፉ
- እጅ ፁሑፉ የማን እንደሆነ ያውቃሉ ?
- የራሴ ነው ብሎ አምኗል ባለቤቱ
- የራሴ ነው እጅ ፁሑፉ ?
- አዎ
- ስለዚህ አንምረጥ ከሚለው ሌላ ሌላ ነገር የለውም ፁሑፉ ላይ ፁሑፉ ላይ አንመርጥም ከሚለው ውጪ ምክንያት የለውም ?
- ምክንያት የለውም እንግዲህ ይገኛል ምክንያቱማ አለ
- ታዲያ ንገሩና ምክንያቱ ካለ ምክንያት አለ ካሉ ለፍ/ቤቱ ግለፁ ?
- ነገርኩ እኮ ከእዚህ በላይ ምን ልንገርህ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምክንያቱ ይሄ ነው ከእዚህ በላይ ምን ልንገርህ ነው ምክንያቱን ካዩ እዚያ ላይ ግለሁ ለፍ/ቤቱ ካዩ ?
- እኔ እኮ ያለሁት አሁን ያየሁን ሁሉ ተናገርኩ አይደለም
- ያየሁት ስለዚህ ርዕሱን ብቻ ነው ነው የሚሉን ወይስ አያስታውሱትም ?
- በቃ ግልፅ ነው ይለፋት
- /ግልፅ ያልሆነ/ መፅሐፍም አለ
- ለእኛ ግልፅ ነው ይለፋት
- አቶ መኮንን የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የአቶ ሰይድ ቤት ይበርበር ብለዋል ብለዋል ነገር ግን ከእዚያ ወጥታችሁ የመኪና አሮጌ መኪና መሸጫ ጋር ሄዳችዋል ምንድን ነው ከፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ውጪ ነው እንዴ እርሶ የታዘቡት የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የመኖሪያ ቤት ነው የሚለው ?
- አጠቃላይ ነው የሚገልፀው እሱ የሚሰራበትን/ግልፅ ያልሆነ/ እሱ የሚሰራበትን ቢሮም እንዲፈተሽ ጋር ነው
- ቢሮ የሚልም አለው ትዕዛዙ ላይ ?
- አዎ
- ቤት ገባችሁ እስቲ ብርበራው እንዴት ነበር የተካሄደው ብርበራው እንዴት እንደተካሄደ የትኛው ክፍል ስንት ክፍል ነበረው እስቲ ዘርዘር አድርገው ይንገሩን ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ከመኖሪያ ቤቱ ጀምረው ሚስት መጣች ከፈተች እንዴት ተካሄደ እስቲ እናንተም ገባችሁ የት ጋር አገኛችሁት እቃውን አሁን በብርበራ የተገኘው እቃ የት ጋር ነው የተገኘው ?
- እቃውን ያየሁ ቤት ውስጥ ነው
- አንድ ክፍል ነው ቤቱ ቤቱ አንድ ክፍል ነው ?
- ኧረ ወደ 3 ነው
- እኮ አሁን እቃው ሳሎን ነው ያገኛችሁት መኝታ ቤት ነው እቃ ኪቺን አለ ሽንት ቤት አለ ብዙ ክፍል አለው አይደል ?
- ሳሎን እና መኝታ ቤት ነው የተገኘው
- እርሶ የት ጋር ነበር የተቀመጡት ሳሎን ነበር የተቀመጡት ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ
- ቤት ገቡ እና ሳሎን ሶፋ ላይ ነው የተቀመጡት ?
- ማን እኔ ሶፋ ላይ አልቀመጥም ታዘቢ አይደለሁም እታዘባለሁ ቆሜ
- እኮ የት ሆነው ነው የታዘቡት ?
- እዚያው ሳሎን ውስጥ ሆኜ
- ሳሎን ውስጥ ሆነው ?
- ሳሎን ውስጥ ሆኜ ከእዚያ ከሳሎኑ ሲጨርሱ እነሱ በሄዱበት እያየሁ
- እሺ ፖሊሶቹ ሲገቡ ምን ይዘው ነበር ገና ቤት ሳይገቡ ?
- ምንም አልያዙም ደብተር በስተቀር
- ደብተር ነበር የያዙት ?
- ዶክመንታቸውን በስተቀር የያዙት ነገር የለም
- በምን ይዘው ዶክመንቱን በቦርሳ ነበር የያዙት ?
- ምኑን ዶክመንቱን በቦርሳም ይዘዋል አዎ
- በቦርሳ ይዘው ነበር ገብተው ቀረፃ አካሄዱ እንዴ ?
- አዎ
- ተቀርፆዋል ?
- አዎ
- የተቀረፀው እቃው ነው ወይስ ሰውም ጭምር ?
- እቃ
- እቃው ብቻ ?
- አዎ
- ቃለጉባኤ ላይ ስትፈርሙ ቃለ ጉባኤ ፈርማችዋል አይደል ?
- ቃለ ጉባኤ ?
- ፈርማችዋል እንደታዛቢነት ?
- አዎ
- ምን ብላችሁ ነው የፈረማችሁት ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ ይሄ ተገኘ የዘረዘርኩትን ሁሉ ተገኘ ተብሎ
- እቃው ተዘረዘረ እና 37 ሲ.ሲ.ዲ ካሴት 32 እያላችሁ ወረቀቱ ላይ ፈረማችሁ ?
- አዎ
- ካሴቱ ላይ ሲዲው ላይስ ፈርማችዋል በእያንዳንዱ ሲ.ዲ ላይ ?
- እሱ ያው ያሳተመ ፈርሞበታል
- የለም አሁን ለተጠየቁት ነው አቶ መኮንን ?
- አይ ልክ ነዋ እኔ ምን ሲዲ ላይ እያንዳንዱ ይፈርማሉ
- ፈርመዋል አልፈረሙም ሲዲው ላይ ?
- ቆይ ቆይ አሁን እርሶ ጥያቄውን ብቻ መልሱ ሌላውን ተውእና ፈርመው ከሆነ መርመናል ካልፈረሙ ደግሞ አልፈረምንም አለቀ ሌላ ውስጥ አይግቡ
- አቶ መኮንን እነዚህ 37 ያሉት ሲዲው ላይ ሲዲው ላይ እራሱ ከወረቀቱ ውጪ ሲዲው ላይ ፈርመዋል ?
- አልፈረምኩም
- ሌሎች ታዛቢዎችስ ፈርመውበታል ?
- አልፈረሙምም
- ተከሣሹም አልፈረመበትም ተከሣሹስ አቶ ሰይድ ፈርሞበታል ?
- አልፈረመም
- ምርመራ ያካሄዳችሁት የተካሄደው እርሶ በታዛቢነት የተገኙት ምርመራው ማለት ብርበራው ከቀኑ 11 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት ነበር ያሉት ?
- አዎ
- የፍ/ቤት ማዘዣው ከስንት እስከ ስንት ነበር የሚለው ብርበራ የሚካሄድበት ጊዜ ጠቅሶ ነበር እንዴ ከእዚህን ሰዓት እስከ እዚህን ሰዓት የሚል ነገር ነበረው ብርበራው ትዕዛዝ ላይ?
- እሱን አላየሁም ግን ወደ ኃላፊው መርማሪው ደውሎ ጠይቆታል ያው መልስ እንደሰጠነው እንዲቀጠል ነው
- እዚያ መርማሪው ነው ደወለ ያሉን ?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን ጋር ደወለ ?
- ኃላፊው ጋር
- ከእዚያ ደውሎ በውስጥ የሚናገረውን ሰው ሰምተውታል ?
- አዎ ደወለ እንዲራዘም ነው መሰለኝ የጠየቀኝ እንግዲህ ያው እኛ ስራችን ቀጠልን
- የእርሶ ግምት ነው የምርመራ እዚያ ያለው ሰው ሲደውል አዩ ከእዚያ ስራችሁን ቀጠላችሁ?
- አዎ በቃ እንዲራዘምለት ነው የፈለገው መሰለኝ
- ግምትዎ ነው አይደል ይሄ የእርሶ ግምት ነው ?
- የእኔ ግምት አይደለም ሲደውል ስለሰማሁ ነው
- እኮ ሲደውል ሰሙ በውስጥ በስልኩ ውስጥ ግን ለሚደውለው ሰውዬ የሚናገረውን ነገር ሰምተዋል ?
- አልሰማሁም
- አቶ መኮንን ቢሮ ስንሄድ ምሽት ነበር ብለዋል ስንት ሰዓት ነበር በትክክል ?
- ወደ 1 ሰዓት አካባቢ
- ቢሮ ሰው ነበር እዚያ ?
- አዎ ነበሩ ሠራተኞች ነበሩ ፖሊሶቹም አሉ
- ሌላ የተያዘ ሰው ነበር ከሰይድ ጋር አብሮ ሌላ ሰው ነበር የተያዘ ከሰይድ ጋር አብሮ ?
- ሌላ ሰው
- ነበረ አልነበረም አብሮ የተያዘ ሰው ነበረ ?
- አይ እንግዲህ እሱን ሰይድ /ግልፅ ያልሆነ/
- ሰይድ ብቻ ነው የነበረው ነው የነበረው /ግልፅ ያልሆነ/ የሚያስታውሱትን የሰሙትን እና ያዩትን ነው አይደል የሚመሰክሩት ?
- አዎ
- በወቅቱ ሰይድ ከሰይድ ጋር ሌላ አብሮ የተያዘ ሰው ነበር አልነበረም ነው ያልኮት ከነበረ ነበረ ካልነበረ አልነበረም በሉ ?
- እሱ እንግዲህ አንድ ልጅ የስራው ባልደረባ ነው ብሎ ነበር



1059

2608

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ነበረ እሱም ?
- አዎ
- እሱም ታስሮ ነበር እጁ ላይ ካቴና ነበረው ?
- ያን ጊዜ አብሮ ነበር ከእሱ ጋር
- እኮ እጁ ላይ ካቴና ነበረው ?
- ኧረ አልነበረም ካቴና አልታሰረም
- ሰይድስ ?
- አልታሰረም
- የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ተነቦልናል ብለሀል ?
- አዎ
- ለታዛቢዎች ለሰይድ ግን አልተነበበለትም አይደል ?
- ሰይድ ባለበት ነው የተነበበው
- ኢህዲግን እንመርጥም አናስመርጥም ተብሎ ተፅፏል ያልከው ምን ላይ ነው የተፃፈው ?
- ማስታወሻ ደብተር
- ማስታወሻ ደብተር ላይ ነው እሱን በተመለከተ ማብራሪያ ተጠይቆ ነበረ አይደል ሰይድ ማብራሪያ ጠይቀውት ነበር ፖሊሶች ጠይቀውት ነበር አልነበረም ሲያብራራ ነበር ለፖሊሶቹ ሲያስረዳ እሺ ላስታውሶት ይሄ የተፃፈው የመጅሊስን በተመለከተ ምርጫ ወ/ሮ አበባ የተባለች የክፍለ ከተማው ስብሰባን ኢህዲግን ለመምረጥም ለማስመረጥም አይደለም ነገር ግን ይሄንን የሚመርጡት እራሳቸው ሙስሊሞች ናቸው ብላ ስትናገር ከእዚያ የወሰድኩት ነው ብሎ ሲያስረዳ ነበር አይደል ?
- አላስታውስም
- ምን ብሎ አስረዳ ፖሊሶቹ ማብራሪያ ሲጠይቁት ምን ብሎ ገለፀላቸው ?
- አላስታውስም እሱን
- አላስታውስም ነው ግን ሲያብራራ ነበር ሲያብራራ ነበረ አላስታውስም ነው እንጂ ያሉት ያብራራውን ነገር ነው ያላስታወሱት እንጂ ሲያብራራላቸው ነበር ?
- እንግዲህ አላስታወስኩም እነሱ ያው ስራቸውን ሲሰሩ እኔ ደግሞ ለ[illegible]ን /ግልፅ ያልሆነ/



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት አልሰማሁም በእዚያ ሲያብራራ አልሰማሁም ነው ?
- ያቢታል ሌላ ጥያቄ
- ስንት ነበሩ ፖሊሶቹ ብዛታቸው ፖሊሶቹ ብዛታቸው ስንት ነበሩ ?
- አልቆጠርኳቸውም
- በግምት ስንት ይሆናሉ 20/30
- መገመት አይቻልም
- ምን ከ 50 በላይ ናቸው መገመት የማይቻለው ?
- አይ ማለት ስላልቆጠርኩ ነው
- እኮ ገባኝ ግን በግምት ይሄንን ያህል ይሆናል በል ?
- አናሳ ናቸው
- ስንት ?
- አላውቅም
- አቶ መኮንን ቅድም ኃላፊ ነው የሚሉት ስልክ የተደወለላቸው የሚሉት የፖሊሲ አገኘሁ ማለትዎ ነው አይደል ስልክ ተደወሉ ተጠየቁ የሚሉት ኃላፊ ናቸው ብለዋል የፖሊሱ አገኘሁ ናቸው አይደል ?
- እኔ እኮ ያልኩት መርማሪው ስልክ  ደወለ
- የት ?
- ስራ ሲበዛብን ስልክ ደውሏል
- እኮ የት ደወለ ?
- ሲደውል እኔ እንደሚወስደው ከኃላፊው ጋር ተነጋግሮ እንዲቀጥል እንዲራዘምለት ነው የጠየቀኝ ነው ግምቴ
- የፖሊሱ ኃላፊ ማለትዎ ነው እያልኮት ነው የፖሊስ ኃላፊ ያሉት ሰውዬ የፖሊሱ አዛዥ ነው አይደል እርሶ ያሉት ?
- ወንጀል መርማሪው ነው የሚደውለው ተልኮ የመጣ ማለት ነው
- ኃላፊ የሚሉት ሰው እርሶ ኃላፊ አሉ አይደለም ይሄ ኃላፊ የሚሉት ሰውዬ የፖሊሱ አገኘሁ ነው ወይ ማለቴ ነው ልክ ነው ወይ ልክ አይደለም በሉ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የትኛው ነው ጥያቄው
- አሳቸው
- የተደወለለት ሰው ነው ?
- አዎ ኃላፊ ነው ስላሉ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ቅድም ቃለጉባኤ ተፈረመ ብለው ነበር በእያንዳንዱ ገፅ ነው የፈረማችሁት በእያንዳንዱ ቃለ ጉባኤ ላይ ነው የፈረማችሁት ?
- አዎ
- ስንት ገፅ ይሆናል እያንዳንዱ ቃለጉባኤ ?
- ብዙ ነው
- ስንት ገፅ ይሆናል ብዙ ሲሉ ?
- አልቆጠርኩም
- ስንት ሊሆን ይችላል እሺ በብዛት ከ 10 በላይ እንደዚህ መገመት ይችላሉ ?
- አልገምትም
- አላዩትም የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል
- መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የከሣሽ ዐቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ
- አሁን መጨረሻ ላይ ከተጠየቁት ቃለጉባኤ ከቃለጉባኤ ውጪ ምን ላይ ፈርማችዋል ?
- እዚያ ላይ /ግልፅ ያልሆነ/
- ማለት ሰነዶች የተያዙ ሰነዶች ላይ አልፈረማችሁም ?
- የተያዙ ሰነዶች ላይማ ፈርመናል
- ፈርማችዋል ከእዚያ በተጨማሪ ነው ቃለጉባኤ ላይ የፈረማችሁት ?
- ያው ሰነዶቹ ላይ ነው የፈረምነው
- እኮ ከእዚያ በኋላ ቃለጉባኤ አልተያዘም እንዴ ይሄንን ያህል ላፕቶፕ ተይዟል ይሄንን ያህል ሰነድ ተይዟል ተብሎ ዝርዝር አልተያዘም ?
- እንግዲህ ቃለጉባኤ እና ያው ሰነዱ ቃለጉባኤም ሰነዶቹም ላይ ፈርመናል
- ፈርማችዋል ሌላው አሁን ስልክ ተደወለ የሚባለው ስንት ሰዓት ስላለፈባችሁ ነው ?



1062 2611

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስከ ፣ ሰዓት ስለሆነብን
- ከእዚያ ስላለፈብችሁ ነው ?
- አዎ
- ለማን እንደተደወለ የሚያውቁት ነገር አለ ለፍ/ቤት ይሁን ለፖሊስ ኃላፊ ይሁን ?
- እኔ ግምት እንግዲህ ያው ከእዚያ በኋላ ነው ስልክ ከተደወለልን በኋላ ነው
- የቀጠላችሁት ?
- አዎ ይቀጥል የተባለ በግምት እንግዲህ ያው የሚመለከተው ነው ማለት
- እንጂ ለፍ/ቤት ይሁን ለፖሊስ ኃላፊ ይሁን እርግጠኛ አይደሉም ?
- አዎ
- ባለቤት የተከሣሹ የሰይድ ባለቤት ይሁኑ አይሁኑ የሚያውቁት ነገር አለ ወይ ሲባሉ የለም ብለዋል ባለቤት በዋና ጥያቄ ስጠይቆት ደግሞ ባለቤት ናቸው ተብለው ነው የመጡት ብለዋል እስቲ እሱን ያብራሩ እና ይንገሩን ቁልፉ ከየት ነው የመጣው ?
- እንግዲህ ያን ጊዜ በሩ ዝግ ሆኖብን ማለት ነው በሩ ዝግ ሆኖብን ከእዚያ በር ስለተዘጋ
- ስልክ ከየት ነው የተገኘው ?
- ስልክ ከወንጀል መርማሪው ከተዘጋብህ እንካ ደውል ተብሎ ተሰጠ
- ለማን ተሰጠ ?
- ለማን ነው የምትደውለው ሲባል ለሰይድ ለማን ነው የምትደውለው ሲባል ለባለቤቴ ነው አለ ባለቤቴ ትሁን ማን ትሁን አላወኩም
- ሰይድ ነው እንዴ የደወለው ስልኩን ?
- ስልኩን አዎ ለዕለቱ እንግዲህ እንድትከፍትለት እሱ ነው የደወለው
- ፖሊስ ስልክ ሰጥቶት ሰይድ ነው የደወለው ?
- አዎ
- ለባለቤቴ ልደውል ብሎ ባለቤቱ መጡ ?
- አዎ
- ድጋሚ ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት



1063 2612

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ድጋሚ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል ከፍ/ቤት የሚቀርብ የማጣሪያ ጥያቄ ባለመኖሩ ምስክሩ ተሰናብተዋል ጨርሰዋል የምስክር መስማት ሂደቱ በእዚሁ የዛሬው በእዚሁ ተጠናቋል የምስክር መስማት ሂደቱን ለመቀጠል ፍ/ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ ይይዛል ለመጋቢት ሚያዝያ 2 ነው እኛ የያዝነው ከሚያዝያ 2 እስከ 4 የሚቀጥለው ቀጠሮ
- ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል

## ***ት ዕ ዛ ዝ***

- የምስክር መስማት ሂደቱን ለመቀጠል ከሚያዝያ 2 እስከ 4 ቀን 2005 ቀጠሮ ተይዟል በእዚሁ ጨርሰናል።



http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ሚያዝያ 2 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ ፡- ዓቃቤ ሕግ ዘረሰናይ ምስግና ቀርበዋል

ተከሳሾች፡- ሼህ አቡበከር አህመድ 31 ሰወች የቀረበ አለ ሁሉም ቀርቧል

ጠበቆቻቸው ሁለት ሰው ቀርቧል ባህሩ መካንጋ እና መሃመድ

ዓብደላ ቀርቧል

⇒ በእውነት መመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ

⇒ እሺ 71ኛ አቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል ለምስክርነት ነው የመጣኸዉ?

⇒ አዎ

⇒ የመጀመሪያ ስምህን ብቻ ትነግረናለህ የአባት ዝርዝር ውስጥ አንገባም ?

⇒ ሰናይ



1065 2613

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

፦ ስንተኛ ገፃቸው አቃቤ ሕግ ? 140 ላይ .

፦ እሺ. በተሰመው ዝርዝር ልክ 71ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ 140 ላይ የተጠቀሱ ምስክር አቶ ሰናይ ቀርበዋል /የማይሰማ/? በሼህ መከተ በእሳቸው ብቻ

፦ /የማይሰማ/ 3ኛ? 3ኛ

፦ ቃል ያደረጉት?

፦ አዎ

፦ እስቲ ተነሱ እሳቸውን ነው አደል? አዎ

፦ ሼህ መከተ ዋትግ አዎ

፦ እሺ. ቁጭ በሉ ስንተኛ ዋት ሼህ መከተ እሺ ምስክሩ 6ኛ ተከሳሽ ላይ ነው የምመሰክረው ብለው በቃለመው አሳይተዋል ምን ሲያደርግ ነው ያዩት ምን ፈፀመ ተብሎ ተከሰሰ እስቲ አጠር አርገው ይንገሩኝ

፦ በአጋጣሚ ያው እዛ አካባቢ ነበርን ከባደቹጋ

፦ እሺ. ምስክሩ ያው 6ኛ ተከሳሽ ላይ ነው የምመሰክረው ብለው በቃለመው አሳይተው ነው ያቀምነው ዋና ጥያቄ ይቀጥል

፦ እሺ. አቶ ሰናይ የመጣሁት በሼህ መከተ ሙሂ ላይ ነው ብለሃል እና በምን ጉዳይ ነው ከእሳቸው ጋር የተዋወቅከው ?

፦ እስቲ ምስክር ፊቱን እንደዚሁ እኛን እንዳዩ ከዚህም ከዚህም ጥያቄ ሊሆን ይችላል ወደዛም ወደዚህም መዞር አይቻልም የሚያውቁትን ሳይዞሩ?

፦ እሺ. የመጣሁት ያው በእሳቸው ላይ ለመመስከር ነው የምመሰክረውም ያው በወንጀል ተጠርጥረው ቤታቸው ሲበረበር ያየሁትን ነገር ለመመስከር ነው የመጣሁት

፦ እስቲ ከጊዜው ጀምርና ንገረን?

፦ ጊዜው ሐምሌ 12 ነው



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ምን አመተምረት?ሐምሌ 12 ቀን 2004

⇒ እሺ ሰዓቱስ? ሰዓቱ ከሰዓት በኋላ ወደ አስር ሰዓት ዘጠኝ ተኩል አካባቢ ላይ ነው

⇒ እሺ በምን ጉዳይ ነበር የሄድከው እዛ?

⇒ እዛ አካባቢ የሄድኩት ያው ለመዝናናት ነበር ከጓደኛዬ ጋ እና እንዳጋጣሚ ፖሊሶች ነበሩ እዛ ሺህ መከተም ነበረ እና ጠርተውን ያው በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ስላለ ቤቱን ልንበረብር ነው በታዛቢነት እንድትተባበሩን ብለው ጠየቁን ከዛ ችግር የለውም ብለን እኛ ተስማማን

⇒ የት የሚገኝ ቤት ነው? ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13

⇒ የቤት ቁጥሩ?

⇒ የቤት ቁጥር መ 42/2

⇒ እሺ እዚህ ቤት ገብታችሁ ምንድን ነው ያየኸው?

⇒ እዛ ቤት ያየሁት ነገር የተለያዩ ወረቀቶች ነበሩ በአረብኛ እና በአማርኛ የተፃፉ አጀንዳዎች ወደ 8 አካባቢ የሚሆኑ

⇒ እስቲ በዝርዝር ንገረን መጀመሪያ ?

⇒ መጀመሪያ ያው የፍ/ቤት ወረቀት ነው ያየነው ተከሳሹም ተጠርጣሪውም እኛም ወረቀቱን አየን የፍ/ቤት ማዘዣ ወረቀቱን ከዛ በኋላ ታዛቢ እንደሆነ ለሱ ተገለፀለት ከዛ እሱ ቀድሞ ወደቤት ገባ ቤት ከገባን በኋላ ያው እሚበረብሩት ፖሊሶች ቤት መበርበር ጀመሩ ከዛ ሲበረብሩ ያው የተለያዩ ብሮሸሮች ነበሩ በአረብኛ የተፃፉ ብሮሸሮች 8 የሚሆኑ አጀንዳዎች ነበረ የሱ የእጅ ጽሁፍ የነበረባቸው ሁለት ቢኤች ኤስ ካሴት ነበር ሁለት ሲዲዎች በርካታ ሲዲዎች ነበሩ

⇒ በቁጥር? ወደ 15 አካባቢ የሚሆኑ ሲዲዎች ነበሩ አንድ ዩኒት ሲስተም ነበር እነዚህን ነው የማስታውሰው

⇒ እሺ የብርበራ ትእዛዝ ፖሊስ እንደያዘ ነግሮናል ብለሃል ? አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

> የብርበራ ትእዛዙ ተነቦላችኋል?

> አዎ አንብበነዋል እኛ እራሳችን አንብበነዋል ሰጥቶን

> ምን ይላል? ቃል በቃል ባላስታውሰውም የመጀመሪያ ፍ/ቤት ማህተም ያለበት ወረቀት ነው እና የእሳቸው ሙሉ ስም ነበረበት እንደዚሁም የጦር መሣሪያዎች የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች እንደዚሁም ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ያላቸው ቁሳቁሶች ሊገኙ ይችላሉ በሚል ጥርጥር ወረቀት እንደተሰጠ የሚገልጽ ወረቀት ነው ከዛ በኋላ እሱም አንብቦት እኛም አንብበን ነው ወደ ብርበራ የገባነው

⇒ እሺ አሁን ወደተያዙት ጉዳይ ስንመጣ አጀንዳዎች ተይዘዋል የሱ እጅ ጽሁፍ ናቸው ብለሃል? አዎ

⇒ ማለት በምን አወቅክ ይሄንን?እሱ እራሱ እያነበባቸው ነበር ማለት ይሄ ምንድን ነው እያለ እየጠየቁ ነበረና የሱ እጅ ጽሁፍ እንደነበረ ይገልጽ ነበረ በዛን ሰዓት

⇒ አሃ ይሄ ሰነድ የራሴ ነው ብሏል ?

⇒ አዎ ከራሱ ቤት ሁሉም ከራሱ ቤት እንደተገኘ የሱ እንደሆነ ነው አምኖ የነበረው

⇒ ከዚህ ውጪ የተያዘ ነገር አለ እንዴ አሁን ከነገርከን አጀንዳ ቪኤች ኤስ ሲዲ እና ዩኒት ሲስተሙ?

⇒ የተያዙ አሉ አሁን የማስታውሳቸው እነዚህን ነው ለምሳሌ የእርዳታ ድርጅት ስሙን አላስታውሰውም አሁን የእርዳታ ድርጅት መሆኑን የሚገልጽ ደረሰኞች እንደነበሩ አስታውሳለሁ እንደዚሁም በአረብኛ የተፃፉ ቁርአን የሚመስሉ የተለያዩ ብዛት ያላቸው ነበሩ ከእያንዳንዳቸው ሳምፕል ሳምፕል ተወስዶ ነበር

⇒ ከአጀንዳው ላይ በእጅ ጽሁፍ ከተፃፈ አጀንዳ ላይ የምታስታውሰው በይዘት የምታስታውሰው በርእስ የምታስታውሰው አለ? አላስታውስም

⇒ እሺ መጨረሻ ላይ እነዚህን ንብረቶች ወዴት ተወሰዱ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

> ልክ እነሱ ከተገኙ በኋላ ጨፈረስን ከጨፈረስን በኋላ ቃለ ጉባኤ ተያዘ እሱ ከኔ ቤት የተገኘ እያለ ፈርሞ እኛም ታዛቢዎች ሆነን እየፈረምን አንድላይ ነው ከሱጋር

> ስንት ታዛቢ ሆናችሁ ነው የገባችሁት? ሁለት ታዛቢ ሆነን

> በአጠቃላይ ስንት ሰው ፈረመበት ?

⇒ በአጠቃላይ 3 ሰው ማለት ነው ከሱጋ

⇒ ከማንጋር ? ከሼህ መከተጋር

⇒ እሺ ከዚህ ውጪ የተያዘ ነገር አለ?

⇒ ከዚህ ውጪ የተያዘ ነገር የለም

⇒ እሺ የተከበረው ችሎት ዋና ጥያቄ አብቅተናል

⇒ እሺ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካለ

⇒ አቶ ሰናይ ? አቤት

⇒ አሁን ቅድም ተገኙ ባሏቸው የጽሁፍ ሰነዶች ላይ ይዘታቸውን አላነበብንም ብለዋል አደል? በዛ ሰዓት አንብበናል

⇒ ምን ይላል?

⇒ ቃል በቃል እንደሚል ግን አላስታውሰውም አሁን

⇒ እሺ የገፃቸው ብዛት ስንት ነበር ያሉት? አጀንዳዎቹ ወደ 28 የሚሆን አንድ እንትን ነበር ማስታወሻ ወደ ገጽ 28 አካባቢ የሚሆን ማስታወሻ ነበር ከዛ ውጪ ያው አጀንዳዎች ነበሩ 8 አጀንዳዎች ተገኝተዋል

⇒ እኮ በየ አጀንዳዎቹ ላይ በተገኙት ገጽ በገጽ ፈርማችኋል አንዴ?

⇒ አዎ እያንዳንዱ የተፃፈባቸው አጀንዳዎቹ ላይ የተፃፉት ወረቀቶች ላይ ፈርመናል እሱ ነው የሚለው

⇒ ታዛቢዎች ፈርመዋል ? አዎ



1068

2617

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ቃለ ጉባኤው ምን በሚል ነው ቃለ ጉባዔ የያዛችሁት ?

⇒ ቃለ ጉባኤውን የያዝነው ያው የተገኙት ነገሮች ከሱ ቤት እንደተገኙ የሚገልፁ ናቸው እሱም ከኒ ቤት ተገኝቷል ብሎ ፈርሞበታል እኛም ከሼህ መከተ የተገኙ ብለን እያንዳንዱ የተገኙት ነገሮች ተዘርዝሮበት የፈረምነው ወረቀት

⇒ እርስዎ ሼህ መከተ ቤት አካባቢ አሁን ለመዝናናት ሄደው ነው ታዛቢ ሆኑ የተባሉት ? አዎ

⇒ በምን ያህል ከቤቱ ከሚበረበረው ቤት በምን ያህል እርቀት ነው ታዛቢ እንዲሆኑ የተጠየቁት?

⇒ ማለት መጀመሪያ የነበርንበት ቦታ ላይ?

⇒ የነበራችሁበት እርስዎን ታዛቢ እንዲሆኑ የጠየቁት የሚበረበረው ቤት አጠገብ ነው እራቅ ብሎ ነው ?

⇒ አይ እራቅ ብለን ነው የነበረው ሲጀምርም እኛ ወጣት ማእከል ነው የነበረው ከእሳቸው ፊት ለፊት ወጣት ማእከል አለ ከሱ ልክ ስንወጣ ከቤቱ ትንሽ እራቅ ብሎ ነው ሼህ መከተም ፖሊሶችም የነበሩት ከዛ እንዳጋጣሚ ጠርተው ነው ያነጋገሩን

⇒ ከዛ በመኪና ተያይዛችሁ ሄዳችሁ?

⇒ እዛ አካባቢ ነው

⇒ ስትደርሱ ማን ከፈተላችሁ ቤቱ ዝግ ነበር ክፍት ነበር ግቢ አለው እንዴ?

⇒ ግቢ አለው ቤተሰቡ የሱ ባለቤት ነበረች ሌላም አንድ ሴት ነበረች

⇒ ፖሊሶች አንኳኩተው ነው የከፈቱት?

⇒ ውስጥ ነበሩ አዎ ሰወች ውስጥ ነበሩ

⇒ ማን ውስጥ ማለት?

⇒ የሱ ባለቤት ትመስለኛለች



1069

268

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እኮ ግቢ ውስጥ ግቢው በምን ተከፈተላችሁ እናንተ መኖራችሁ በምን ታወቀ?

⇒ እነሱ ናቸው የከፈቱት ውስጥ የነበሩት

⇒ ማለት ፖሊሶች አንኳኩ? እሱን አላስታውስም

⇒ እኮ ስትገቡ አሁን ታዛቢ ስለሆኑ ግቢ ተከፈተላችሁ ይንኳኳ አይንኳኳ አያስታውሱም? ማለት ተንኳኩቶማ ነው የተከፈተው

⇒ ማለት ፖሊስ አንኳኳ? አዎ

⇒ ከዛ ምን አለ ፖሊስ አንኳኳና ?

⇒ እሱ ካንኳኳ በኋላ ያው ሼክ መከተ እዛ እንደነበረ ስላዩ ቤተሰቦቹ ወረቀት አሳየን ለፀሼህ መከተም አሳያቸው ያው ለነሱም ተነገራቸው ለቤተሰቦቹ

⇒ ምን ብሎ ተነገራቸው?

⇒ ማለት ያው በወንጀል እንደተጠረጠረና ቤቱ ሊበረበር እንደሆነ

⇒ ፖሊሶች ነገሯቸው?

⇒ አዎ

⇒ ወረቀት አልጠየቁም እንዴ ቤተሰብ የፍ/ቤት ወረቀት መኖሩን አልጠየቁም? አልጠየቁም

⇒ ፖሊሶቹ ይሄን ነገሯቸው እና ገባችሁ? አዎ

⇒ ከዛ የከፈተችው ባለቤት ነች ያለች ሴትዮ ነች ?

⇒ አላስታውስም ማን እንደከፈተ ግን ቤት ውስጥ የነበረ ሰው ነው

⇒ ሴት ነች የከፈተችው ወይስ ወንድ?

⇒ ሴት ነች

⇒ ከዛ ገባችሁ መጀመሪያ ከየት ጀመራችሁ እስቲ ንገረን ብርበራው እንዴት ተካሄደ? መጀመሪያ እሱ ነው የገባው ወደቤት ውስጥ ወደ መኖሪያ ቤት ውስጥ ማለት ነው እሱ ከገባ በኋላ ያው እኛም ተከታትለን ገባን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ?

⇒ ከዛ

⇒ ውስጥ ስትገቡ ሌሎች ሰወች አልነበሩም የቤተሰብ አባል?

⇒ ሚስቴ ነበረች

⇒ ከከፈተችው ሴትዮ ውጪ ማለት ነው?

⇒ ሚስትየው ነች የከፈተችው

⇒ እሺ ከዛ ውጪ ሌላ ሰው ነበር? ከዛ ውጪ ይመስለኛል አባቱ መሰሉኝ ትልቅ ሰውዬ ነበሩ

⇒ ሌላስ ሌላ ሰው ነበረ ?

⇒ ሌላ ዘመድ ነገር መሰለችኝ አንድ ወጣት ልጅ ነበረች

⇒ ሴት? አዎ

⇒ እሺ እነሱስ ምን ሆኑ እነዛ ታዛቢዎቹ ማለት ቤተሰብ የነበሩት ሽማግሌው ሰው እና ወጣት ልጅ ሚስት ቢያንስ 3 ሰው የቤተሰብ አባል ነበረ ማለት ነው? አዎ

⇒ ምን ሆኑ እነሱ? ምንም ነገር አላሉም

⇒ ማለት የት ቁጭ አሉ ወይስ ውጡ ተባሉ?

⇒ አልተባሉም

⇒ እዛው ቁጭ አሉ ?

⇒ እዛው ነው የነበሩት ማለት መኝታ ቤት ሲበረበት እነሱ ሳሎን ላይ ነው የነበሩት ከዛ ያው መኝታ ቤት ውስጥ ያውም ሲበረበር እሱና ታዛቢዎቹ እንደዚሁም መርማሪዎቹ ብቻ ነበሩ

⇒ ታዛቢዎቹም ገበ እንዴ መኝታ ቤት? ሲበረበት ያው አንድ ላይ የሚበረበረውን ነገር ለማየት ግዴታ ስለሆነ

⇒ ስለዚህ የተበረበረው መኝታ ቤት ነው?

⇒ ሁሉም ተበርብሯል



1071

2620

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ሁሉም ክፍል? አዎ

⇒ ስንት ክፍል ተበረበረ አሁን እዚህ ያለነው ስለማናውቅ ሁሉም ሲሉ ስንተ ክፍል?

⇒ እሱን አላስታውስም ሳሎን እንደነበረ አስታውሳለሁ መኝታ ቤት እንደነበረ አስታውሳለሁ

⇒ እቃው የት ጋ ተገኘ አሁን ተገኘ ያሉት እቃ ከክፍሎቹ ውስጥ ሳሎን መኝታ ቤት ብለዋል አሁን እነዚህ ሰነዶቹ ቅድም የገኟቸው ማስታወሻዎቹ የት ጋ ነው የተገኙት ?

⇒ አብዛኞቹ የተገኙት ሼልፍ ምናምን ያለበት እንደ መኝታ ቤት እንደ መስገጃ ይሄ የእንግዳ መቀበያ ነገር ነበር

⇒ ሼልፍ ላይ ተደርድረው? ሼልፍ ላይ የተደረደሩት እነዚህ በአረብኛ የተፃፉ በርካታ አጀንዳ የሚመስሉ ነገሮች ናቸው ብሮሸሮች ምናምን የተገኙት አብዛኛው እዛ ነው

⇒ እንጂ የሆነ ጣሪያ ላይ የተደበቀ ነገር አላገኛችሁም አደል ሼልፍ ላይ ተደርድሮ የተገኙትን እንጂ ተደብቆ እንዳይገኝ ተደርጎ ተቆፍሮ የወጣው ወይም ከጣሪያ የወረደ እንደዚህ ነገር አይታችኋል ?

⇒ ተቆፍሮ የወጣው ከጣሪያ የተገኘ ነገርም አልነበረም ግን ያው ሼልፍ ውስጥ ከፊት ለፊት የተወሰኑ አጀንዳዎች ኖርማል አጀንዳዎች ኖረው ከጀርባ ደግሞ የተደበቁ ነበሩ

⇒ እነዚህ ቅድም ያሏቸው ወደ 15 የሚጠጉ ሲዲዎች እዛው ከፍታችሁ አይታችኋል እንዴ? ይዘታቸውን አላየንም

⇒ ስትፈርሙም በቁጥራቸውን እየቆጠራችሁ ይሄን ያህል ሲዲ እያላችሁ ነው የፈረማችሁት አደል ቃለ ጉባዔው ላይ ?

⇒ አዎ

⇒ ሲዲዎቹ እያንዳንዱ ሲዲ ጀርባ ላይም አልፈረማችሁም?

⇒ ፈረመናል

⇒ ሲዲዎቹ ጀርባ ላይ ፈርማችኋል?

⇒ ሲዲዎቹ ላይም ፈርመናል እሱም ፈርሟል እኛም ፈርመናል

⇒ እሺ. አቶ ሰናይ ፍተሻ የተደረገው ከምሽቱ ሦስት ሰዓት እስከ ስደስት ሰዓት መሆኑን ያውቃሉ ?

⇒ አይደለም

⇒ ይሄንን አያውቁም እርስዎ?

⇒ በዛ ሰዓት አደለም

⇒ በሰዓቱ መደረጉን አያውቁም? አልነበረም በዛ ሰዓት አልነበረም የነበረው

⇒ እሺ. እርስዎ ወደ ፍተሻ የተደረገበት አካባቢ የሄድኩት ለመዝናናት ነው ብለዋል ከዚህ ቀደም ቤቱን ያውታል ፍተሻ የተደረረበትን ቤት ያውቁታል?

⇒ አላውቀውም

⇒ አሁን እንዴት ታዲያ የቤት ቁጥሩን ሳይቀር ዘርዝረው ማስረዳት ቻሉ?

⇒ ምክንያቱም ቃለ ጉባዔው ላይ ነበርን

⇒ ቃለ ጉባዔውን?

⇒ ቃለ ጉባዔው ላይም የፍ/ቤት ማዘገሇው ላይም ነበረ ያው

⇒ አሁን ከምጣቱ በፊት አይተውታል ቃለ ጉባዔውን?

⇒ አላየነውም

⇒ እኮ እንዴት ሊያስታውሱት ቻሉ በልዩ ሁኔታ?

⇒ ማለት ያው

⇒ የቤት ቁጥሩን እንዴት ለይተው ሊያስታውሱት ቻሉ ?

⇒ ፍ/ቤት ሊጠይቀኝ ይችላል በሚል

⇒ ፍ/ቤት ሊጠይቀኝ ይችላል ብለው መቼ ምን አደረጉ?

⇒ ማለት ያው ሊጠይቀኝ ይችላሉ ብዬ የገመትኳቸው ነገሮች በራሴ ተዘጋጅቼ ነው የመጣሁት



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ እርስዎ እና ሌላ ታዛቢ ነበረ ብለዋል ሁለት ነበራችሁ ታዛቢዎች?

⇒ አዎ

⇒ ከውጭ ፖሊሶች ሲያገኟችሁ አንድላይ ነበራችሁ?

⇒ አንድ ላይ ነበርን አዎ

⇒ ስንት ፖሊሶች ናቸው መጥተው ያናገሯችሁ ?

⇒ በዛን ሰዓት አላስታውሰውም ግን ከ5 ይበልጣሉ

⇒ ከ5 የሚበልጡ ፖሊሶች?

⇒ አዎ

⇒ ከዛ ቀጥታ ወደቤት ወሰዷችሁ?

⇒ አዎ ማለት በሩጋር ወስደውን ሲቢልም የለበሱ የተወሰኑ አንድ ሦስት አራት የሚሆኑ ወደ 3 የሚሆኑ

⇒ አሃ እናንተ ስትደርሱ አንኳኩታችሁ ስትገቡ ከውስጥ ፖሊሶች ነበሩ?

⇒ አልነበሩም

⇒ ሲቢል ያሏቸው ታዲያ ?

⇒ አብረዋቸው የነበሩ ናቸው የፍ/ቤት ወረቀቱን ያሳዩን እነዚህ ሲቪል ልብስ የለበሱት ናቸው የፍ/ቤቱን ወረቀት አሳይተው እንትን ያሉት

⇒ አንኳኩታችሁ ስትገቡ ሼህ መከተ ውስጥ ነበሩ?

⇒ አደለም ውጪ ነው የነበረው ከፖሊሶቹጋ

⇒ ውጪ የት ነው የነበሩት?

⇒ ከታጠቁት ፖሊሶችጋር

⇒ ታስረው ማለት ነው አደል?

⇒ አዎ



1074 263

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ ቤት ውስጥ የተገኙትን እያንዳንዱን እቃ ሼህ መከተን ይሄ ያንተ ነው ወይ እያሉ ያጠይቁ ነበረ እንደ ፖሊሶች ይሄ የአንተ ነው እያሉ ይጠይቁ ነበር?

⇒ አዎ

⇒ እያንዳንዱን?

⇒ አዎ

⇒ ለምሳሌ ምን ምን እያንዳንዱን ጠየቁ ይሄ ቤት ውስጥ ያሉትን እቃዎች እያንዳንዱን ይሄ የአንተ ነው እያሉ ያረጋግጡ ነበር?

⇒ ማለት ቤት ውስጥ አሁን ሲበረበር

⇒ መቃወሚያ አለን የተከበረው ችሎት አሁን በዚህ ሰዓት የተከበረው ችሎት መስቀለኛ ጥያቄ ነው በዋና ጥያቄ የተጠየቀ ነው አጠራጣሪ ነው ወይም ደግሞ ውሸት ነው ብሎ ለመጠየቅ ነው በዚህ ደረጃ ያለው ስለዚህ አሁን ዋና ጥያቄ ነው እየተጠየቀ ያለው ድጋሚ ሂደቱ ነው በድጋሚ እየተጠየቀ ያለው እና ይሄ የመስቀለኛ ጥያቄ አላማ ስላልሆነ መስቀለኛ ጥያቄ አቀራረብ መሰረት በዛ መሰረት እንዲጠይቁ እንዲደረግ ነው

⇒ እሺ ምላሽ ስጡበት

⇒ የተከበረው ፍ/ቤት ሲጀመር  እንዲህ አይነት ተቃውሞ መቅረቡ እኔ በየትኛው ሰዓት መሆኑ አልገባኝም እየቀረበ ያለው ዋናው ጥያቄ ነው ነው የአቃቤ ሕግ ተቃውሞ ይህ ከሆነ ደግሞ አቃቤ ሕግን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ነገር የለውም እኛ የጠየቅነው መሰረት ያደረገ አደለም ወይም ሌላ አደለም ጥያቄው ለነገሩ የተጠየቀን ጥያቄ ለማረጋገጥ ነው እየጠየቅን ያለነው የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ የአንተ ነው ወይ ተብሎ ተጠይቆ  አዎ ብለዋል ያለው ለምስክሩ ላለመንገር ተጠይቆ ያረጋገጠው አለ አቃቤ ሕግ ጠይቆት እንደውም መሪ ጥያቄ ጠይቀው እና እሱን በመስቀለኛ ለማውጣጣት ነው እንጂ ሌላ አደለም እና የተከበረው ፍ/ቤት ውድቅ የሚደረግበት ምክንያት የለም



1275

2624

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ የተነሳው መቃወሚያ ዋና ጥያቄ የተጠየቀ ነው የተነሳው ላይ የተመሰረተ አደለም የሚል ነው የተሰጠው ምላሽ የተነሳውን እየጠየቅን ነው የሚል ነው ጥያቄው አዲስ የተጠየቀ አዲስ ፋክት ጥያቄ መጀመሪያ ያልተነሳ መሆኑን ፍ/ቤቱ አልተረዳውም ስለዚህ የተነሳው ጥያቄ ላይም ተመስርቶ የቀረበ ጥያቄ ስለሆነ ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥሉ

⇒ አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ሰናይ ፖሊሶች ምን ምን እቃዎችን ይሄ ያንተ ነው እያሉ ሲያረጋግጡ ነበረ ?

⇒ በዛ ሰዓት ፖሊሶቹ ሲበረብሩ የሚፈልጓቸውን እነሱ እየለዩ ነበረ የሚለዩትን እያንዳንዷን የተገኘውን ነገር ለሼህ መከተ እያሳዩት ነበረ እሱም የሱ መሆኑን ወይም ደግሞ ከሱ ቤት እንደተገኘ እና የሱ መሆኑን እያመነ ነው ሲመልስላቸው ነበረ

⇒ ኦኬ እናንተ ምን ታረጉ ነበር በዛ ሁኔታ ይሄ የኔ ነው ሲሉ እናንተ ምን ታረጋላችሁ? ያው የተያዙት እየተያዙ የነበሩት ነገሮች እየለየን ነው የነበረው ተለይቶ የተቀመጠ ነው የነበረው ያው እሱ ሲያምን ያንን ነገር እኛ እየተከታተልን ነበረ

⇒ ከዛ ለይታችሁ ምን አደረጋችሁ?

⇒ ተለይቶ ተቀመጠ መጨረሻ ላይ ተጠራቅሞ እያንዳንዱ ላይ እየፈረምን ነው

⇒ እያንዳንዱ ላይ ፈረማችሁ? አዎ

⇒ ለምሳሌ አሁን ቅድም ማስታወሻ ብለዋል ማስታወሻ ላይ ሁለታችሁም ታዛቢዎች እያንዳንዲ ገጽ ላይ ፈረማችሁ ?

⇒ ፈርመናል

⇒ ድጋሚ ነው ይሄ

⇒ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ቃለ ጉባዔም ነበረ? አዎ

⇒ ቃለ ጉባዔ ላይም ፈረማችሁ?

⇒ አዎ



1076 2625

http://ethcriminalawnetwork.com/
ECLN

⇒ እሺ የዩኒት ሲስተም ያሉት ነገር ምንድን ነው?

⇒ የኮምፒውተር

⇒ የኮፒውተር ዩኒት ማለቱ ነው?

⇒ አዎ

⇒ ማዘዣው የጦር መሣሪያዎች እና የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ይገኛሉ በሚል የተሰጠ ወረቀት ነው ብለዋል ?

⇒ አዎ

⇒ ይሄ ማዘዣ ከየት ነው የተገኘው?

⇒ ከፌደራል መጀመሪያ ፍ/ቤት

⇒ ፌደራል መጀመሪያ ፍ/ቤት የትኛው ችሎት?

⇒ አራዳ

⇒ ምን ይላል ይሄንኑ እርስዎ ያሉትን ቃል አንብበዋል እዛ ላይ አለ?

⇒ አዎ

⇒ ሌላ ምን ዳኛ ማን ይላል?

⇒ አቤት?

⇒ ዳኛ ማን ይላል ፈራሚው ማለት ነው ?

⇒ አላስታውስም ግን ያው የዳኛ ፊርማ ነበረ

⇒ አይተውታል?

⇒ አዎ

⇒ እሺ ምን ምን እቃዎች ይያዝ ይላል ከዚህ በተጨማሪ ዝርዝር ነገር አለው?



http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዝርዝር ነገር የለውም ያው የጦር መሣሪያዎች ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች እና ከወንጀል ጋር ጉዳይ ያላቸው ተያያዥ ያላቸው ቁሳቁሶች ሊገኙ ይችላሉ በሚል ጥርጣሬ የሚገልጽ ነው

⇒ እሺ. ፐርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ ድጋሚ ካለ አቃቤ ሕግ እሺ. ድጋሚ ጥያቄ የለም የፍ/ቤት ጥያቄ

⇒ እስኪ. ምስክር ተከሳሽ ታስሮ ነው የመጣው ነው ያልከን በምንድን ነው የታሰረው?

⇒ በካቴና ነው

⇒ ታስሮ ማለት ተገዶ ነው እንዴ እነዛ የሚሰጠው እንደታሰረ?

⇒ ምንም የተገደደ ነገር አልነበረም ቤት ውስጥም እንትን ሲል ቤቱ ሲበረበር እና እንዲሁም መብቱ ተጠብቆለት ነው የነበረው ምግብ ብላ እያለ

⇒ እስቲ ምን ማለት ነው መብቱ ተጠብቆለት ማለት እስቲ እሱን ይግለፁልን?

⇒ ማለት ለምሳሌ ቤቱ ሲበረበር ምግብ እንዲበላ እራሱ ጠይቀውት ነበረ ፖሊሶቹ ምግብ አቅርቡለት ብለው ለባለቤቱ ነግረው ምግብ እንዲበላ መፀዳጃ ቤት ልሂድ ሲል እየፈቀዱለት እንደዚሁም ልስገድ ብሎ እንደውም አስፈቅዶ እየሰገደ ነበረ በዛን ሰዓት

⇒ ምግብ በላ? በልቷል አዎ

⇒ ሌላ የታየ ምልክት አለ እንዴ በሰውየው ላይ? ማለት?

⇒ የተያዘው ሰው ላይ ?

⇒ ምንም የታየ ነገር የለም

⇒ የአካል ጉዳይ ወይ ሌላ ነገር? ምንም ነገር አልነበረም

⇒ እሺ. በተራ ቁጥር 135 ላይ የተገለፁት አቶ እምሻው የሚባሉት አሁን ከቀረቡት በተራ ቁጥር 140 ላይ የተገለፁትጋ ላይ ነው የተገለፁት እኚህ ምስክር ከ140 አሁን ቀርበው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከመሰከሩት ተራ ቁጥር 140 ላይ ካሉት ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ችሎቱ እንዲያሰናብታቸው ነው በተመሳሳይ ተከሳሽ ነው ታዛቢ የነበሩት

⇒ እሺ አቶ እምሻው ኖት እሺ ያው ከዚህ በፊት ከተሰማው ምስክር ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ይሰናበቱልኝ ብሎ አቃቤ ሕግ በጠየቀው መሰረት የተሰማ ምስክር በቂ ነው ስላለ የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አቅርበው ፍትህ ለማገዝ ስለመጡ እናመሰግናለን እርስዎ መሄድ ይችላሉ

⇒ በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ

⇒ አሁን የቀረቡት በፊት በነበሩ ተከሳሽ ላይ ነው አሁን እኚህ የቀረቡት በዚህ ተከሳሽ ነው ስለዚህ በእሳቸው ላይ ያላችሁን ጨርሳችኋል

⇒ /የማይሰማ/ ሚሊዮን

⇒ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ እሺ በተሰሙት ዝርዝር 73ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል አሁን አንድ ስለተሰናበተ በክሱ ላይ 188 ላይ የተጠቀሱ ምስክር አቶ ሚሊዮን ቀርበዋል አቶ ሚሊዮን ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?

⇒ አቶ በድሩ ሁሴን

⇒ አቶ በድሩን ለይተው ያውቃሉ? አዎ

⇒ አሁን ማሳየት ይችላሉ? እችላለሁ

⇒ እሺ ያሳዩን የትኛው ነው 3ኛ? 3ኛ

⇒ እሺ ምስክሩ 5ኛ ተከሳሽን ለይቶ አሳይቷል ምን ሲደረግ ነው ያዩት እስቲ አጠር አርገው ዝርዝር ሳይገቡ ገማለት ለጉዳይ ማእከላዊ ሄጄ ነበረ መርማሪዎቹ ለታዛቢነት ፈልገንህ ነበረ ትተባበረናለህ ወይ አሉኝ እሺ ብዬ ፍቃደኛ ሆንኩኝ እና ሄድኩኝ

⇒ ምንድን ነው የታዘቡት? ላፕቶፕ

፦ እሺ ጥያቄ አቃቤ ሕግ



2628

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ. አቶ ሚሊዮን ማእከላዊ ለጉዳይ ለራሴ ጉዳይ ሄጄ በፖሊስ ላፕቶፕ የአቶ በድሩ ሁሴን ላፕቶፕ ሲበረበር እንዳይ ጠይቀውኝ እሱን አይቻለሁ ነው ያሉት? አዎ

⇒ እስቲ ከጊዜው ጀምሩና ይንገሩኝ መቼ ነው ቀኑ ወሩ አመተምረቱ ፊቶትን ወደ ችሎቱ ያዙሩ? መስከረም 8 ነው 1ኛ ወር 2005 ነው

⇒ ስንት ሰዓት ላይ ነው ?

⇒ አምስት ሰዓት

⇒ እሺ. ምንድን ነው ያዩት?

⇒ ማለት መጀመሪያ ላፕቶፑ ታሽጐ ነበረ ላፕቶፕ እሳቸው ፊት ተከፈተ

⇒ በምንድን ነው ታሽጐ ማለት ?

⇒ ማለት ፓክድ ሆኖ ነበረ እንደታሸገ ማለት ነው ታሽጓል እንደማለት

⇒ በምን? በፕላስተር ማለት ነው ያቺ ነገር ተላጠች እና አዎ እኔም ባለቤቱም የምንጠቀምበት ላፕቶፕ ነው ሲሉ ፓስወርዱን እራሳቸው ከፈቱ ውስጥ ላይ የነበረውን ዶክመንት ጠቅላላ ማለት ነው ከኔ የተገኘ ነው ሲሉ ፈረሙ እኛም ደግሞ ታዛቢ ነን ብለን ፈረምን

⇒ እሳቸው ከየት ነው የመጡት ?

⇒ በእለቱ መርማሪው ቢሮ ነው እኛ ተጠርተን ስንገባ ቁጭ ብለው ያገኘናቸው ?

⇒ እሳቸው የት ነበሩ?

⇒ መርማሪው ቢሮነው ያገኘናቸው

⇒ ቀድሞ ማን ገባ ከሁለታችሁ?

⇒ እሳቸው ነው የቀደሙት

⇒ እሺ. ከላፕቶፑ ላይ ከምን ፓስወርዳቸውን

⇒ ፓስወርዳቸውን ማን ጠየቃቸው?

⇒ መርማሪው እራሱ ፓስወርዱን ጠየቃቸው እራሳቸው ፓስወርዱን በራሳቸው ከፈቱት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እናንት ምን እንደሆናችሁ ተነግሯቸዋል?

⇒ ታዛቢ መሆናችን ተነግሯቸዋል

⇒ ምንድን ነው የተገኘው ሰነድ ምን ያህል ገጽ?

⇒ 53 ገጽ ነው በአማርኛ የተፃፈ የተለያዩ ነገሮች

⇒ እ? ማስታወስ ትንሽ ይከብደኛል በአማርኛ የተፃፉ የተለያዩ ሰነዶች ነው ያየነው

⇒ በርእስ የሚያስታውሱት አለ? እሱን እንኳን ትንሽ

⇒ እነዚህ 53 ገጽ ላይ ያደረጋችሁት መጨረሻ የተደረገ ነገር አለ?ማለት ከላፕቶፕ ላይ ወደ ሲዲ አዲስ ሲዲ መጣና ወደ ኮምፒውተር ተደረገ ከዛ ፕሪንት ሆኖ ወረቀት ላይ ወጥቶ ከኔ የተገኘ ዶክመንት ነው ሲሉ እሳቸው ፈረሙ እኛም ደግሞ ታዛቢ ብለን ፈረምን

⇒ ከምን ማለት ፕሪንት ሲደረግ እዛው ቆመው እያያችሁ ነበር?

⇒ እዛው ቆመን እያየን ነው ሁሉም ሲወጣ

⇒ ስለዚህ ፕሪንት የተደረገው እሳቸው በፓስወርድ ከከፈቱት ?

⇒ ከከፈቱት ላፕቶፕ ላይ ነው የተገኘው

⇒ እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል

⇒ እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ?

⇒ አቶ ሚሊዮን ከእርስዎ ጋ ስንት ምስክሮች ወይም ስንት ታዛቢዎች ነበሩ?

⇒ ሁለት ነን ታዛቢዎች አንድ መርማሪ እና አንድ ፖሊስ

⇒ አንድ መርማሪ አንድ ፖሊስ ?

⇒ አንድ መርማሪ አንድ ፖሊስ እና ሁለት ታዛቢዎች ነበርን

⇒ ከእርስዎ ጋ ማለት ነው? አዎ

⇒ ይሄን ታዛቢ ያውቁታል ?

⇒ እኔ አላውቀውም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አሁን በምስክርነት መጥቷል?

⇒ አልተገኘም ተብዬ እኔ ተደውሎልኝ ነው የመጣሁት

⇒ እሱ አልተገኘም ተባለ? አዎ

⇒ እርስዎ ተደውሎሎት ነው የመጡት?

⇒ አዎ

⇒ ከሰባት ስድስት ወር በላይ ይሆነዋል አሁን ይሄን ነገር ከታዘቡ ጊዜውን እርስዎ ከነገሩን ማለት ነው መቼ የተያዘ መሆኑን ያውቃሉ?

⇒ እሱን አላውቅም

⇒ ላፕቶፕ ያሉት መቼ የተለያዘ እና እንዴት አላውቅም እኔ ለጉዳዬ መጣሁኝ ሊ.ታዛቢ.ነት አንዴ ትተባበረናለች ሲሉ ብቻ ነው ለታዛቢነት ቆሜ ያየሁት ላፕቶፕ ላይ የተገኘው እቃ ሲወጣ ዶክመንቱ ሲወጣ ነው ያየሁት

⇒ አቶ በድሩ ብርበራው ወይም ላፕቶፑ ላይ ብርበራ ሲደረግ ለእርስዎ ያዩት ምንም አይነት እንትትን የለም አደል ይሄንን ለማድረግ የሚያስችል ነገር ያዩት ነገር የለም አደል?

⇒ ግልጽ አልሆነልኝም

⇒ እሺ ላፕቶፑ እንዲበረበር የፍ/ቤት ትእዛዝ አላዩም አደል እርስዎ?

⇒ እሱን አላየሁም

⇒ አቶ በድሩ ላፕቶፑ ተበርብሮ በማስረጃነት እንደሚቀርብ አልተነገረውም አደል ? በማስረጃነት እነደሚቀርብ ተነግሮናል

⇒ ለናንተ እንጂ ለሱ ሲነገረው አላያችሁም ?

⇒ አላየንም



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ. አቶ በድሩ ላፕቶፑን ተበራግሮ አገላብጦ ሲያየው አላዩም እርስዎ? ላፕቶፑ እንደመጣላገርው እኔም ባለቤቱም የምንጠቀምበት ላፕቶፕ ነው ብለው አምነው ፓስወርዱን እራሳቸው እንደከፈቱ አይቻለሁ

⇒ ፓስወርድ ይኑረው አይኑረው እንዴት አወቁ እርስዎ?

⇒ ኮምፒውተሩ እንደተከፈተ የራሱ መቼም ኮምፒውተር ሲከፈት ወይም ላፕቶፕ የራሱ ቁጥር ተሰጥቶት ስለሆነ

⇒ በዛ ግምት ነው እንጂ?

⇒ አይ በዛ እራሳቸው ናቸው እዛው ሲከፍቱ ያየሁት እኔ

⇒ እሺ. ላፕቶፑ ከተያዘ ከአንድ ወር ከአስራአምስት ቀን በኋላ ውስጡ ያለውን ነገር የኔ ነው ብለህ እመን ልትሉኝ አይገባም ወዲያው እንደተያዘ ከውስጡ የወጣ ነገር ካለ ነው እንጂ ልጠየቅ የሚገባው አሁን ከተያዘ ከአንድ ወር ከ15 ቀን በላይ ነው ብሎ ሲከራከር እርስዎ ይሄንን አያስታውሱም ?

⇒ ይሄን አላስታውስም

⇒ እሺ. እርስዎ እና ሌላ ታዛቢ ባሉበት ፋይሎቹ እየተከፈቱ ሲታዩ አቶ በድሩ የሚያያቸው ምስሎች ወይም ላፕቶፑ ላይ ያያቸው ፋይሎች በፍፁም የሱ አለመሆናቸወ እዛ ላፕቶፕ ውስጥ የተጨመሩ መሆናቸውን በጣም በከፍተኛ ስሜት ተበሳጭቶ ሲናገር አያስታውሱም ?

⇒ በከፍተኛ ስሜት ተበሳጪቶ ሲናገር አስታውሳለሁ

⇒ ይሄንን ተበሳጭቶ?

⇒ ሲናገር አስታውሳለሁ

⇒ ለምን ይሄን ታደርጋላችሁ እያለ ነበር እስቲ የሚያስታውሱትን ነገር ንገሩን ምን እያለ ነበር ሲናገር የነበረው?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እኔም ባለቤቴም ይሄን ላፕቶፕ የምንጠቀምበት ነው እኔ እንደዚህ አይነት ነገር አላኩም እኔ ዶክመንት ላይ ሊገኝ እንዴት እንደቻ አላውቅም ሲሉ ነበር

⇒ አዎ ይሄ ተጨምሮ ነው እኔ ላፕቶፕ ውስጥ እያለ ነበር አደል?

⇒ እንደዛ ብሎ ሲናገር ነበር

⇒ አዎ ይሄ እኔ ላፕቶፕ ውስጥ የተጨመረ እንጂ እኔ የምጠቀምበት ፋይል አይደለም እያለ ነበረ አደል? አዎ

⇒ እናንተ ምን አላችሁት ልታረጋግጡ ሞክራችኋል አደል?

⇒ እኛ በደንብ ልናይ ሞክርን ለራሳቸው ፓስዋርድ ተከፈተ የራሳቸው ላፕቶፕ መሆኑን በስነስርዓ ትአረጋገጡ

⇒ አይ እናንተ አሁን ቅድም ተበሳጭተው ነበር ብለው ነግረውናል ሲበሳጩ ምንም አደለም ፈርምና ያው እኛ ምስክር እንሆናለን እያላችሁ አልነበር ?

⇒ አይ እንደዛ አደለም

⇒ ምንድን ነው ያላችሁት እሺ ተበሳጭቶ ስታዩ?

⇒ ተበሳጭቶ እኔ ዶክመንት ውስጥ እንደዚህ አይነት ነገር እንዴት ሊገባ እንደቻለ አላውቅም በማለት ተበሳጭቷል እንጂ እኛ አብረን /ግልጽ ያልሆነ/ እንመስክራለን አላልንም

⇒ ስለዚህ የኔ አይደለም እዚህ ላይ ልፈርም አልችለም ብሎ ነበር አደል?

⇒ ፈርሟል

⇒ አይ እሱ አሁን ከመፈረሙ በፊት

⇒ አቶ ሚሊዮን ቅድም ያለውን ይሄ የኔ አይደለም አለ ከዛ በምን ተቋጨ ፖሊሶች ምን አሉት ?

⇒ መርማሪዎቹ የነበሩት ፖሊስ በስነስርዓት ላፕቶፑን አየ ዶክመንቱ ከኔ የተገኘ ነው ሲል ተስማምቶ ነው የፈረመበት



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አደልም የኔ ጥያቄ ቅድም ተበሳጭቶ ተናገረ ታዛቢዎች አላችሁ በምን ተፈታ ነው አንድ ሰው ተበሳጨ ለዛ በኋላ ይሄ የኔ አይደለም ከኔ የተገኘ አደለም አለ ዛ ፖሊሶች ምን አሉት? ምንም ነገር የተናገሩት ነገር የለም እነሱ

⇒ በቃ ይሄን ተናገረ ዛ ምንም ያሉት ነገር የለም?

⇒ በራሳቸው ነው የተበሳጩት ስለ ፖሊሶቹ ምንም አይነት ንግግር የተናገሩት ነገር የለም

⇒ ቅድም ታዛቢዎች እርስዎ እዛ ሲደርሱ ታዛቢ እንዲሆኑ ተጠየቁ የትጋ ነበር የተጠየቁት ታዛቢ እንዲሆኑ?

⇒ እኔ ለጉዳይ ሄጄ ነው ጉዳዬን መግለጽ አልፈልግም

⇒ አደለም ቦታው ግቢ ውስጥ ነው ከግቢ ውጭ ነው ?

⇒ እኔ ማእከላዊ ለራሴ ጉዳይ ሄጄ ነው ጉዳዬን መግለጽ ስለማልፈልግ ነው

⇒ ጉዳዩን እንዲገልፁ እኮ አልጠየቅኮትምታዛቢ እንዲሆኑ የተጠየቁት ማእከላዊ ግቢ ውስጥ ከገቡ ወይስ አስፋልት ላይ ሳይገቡ ነው?

⇒ አይ እኔ ጉዳዬን ጨርሼ ስወጣ ነው ልወጣ ስል በር ላይ እንደዚህ እንደዚህ አይነት ነገር ሲሉኝ እሺ ብዬ ተስማምቼ ገባሁ

⇒ ጥሩ እርስዎ ታዛቢ ይሁኑ ተባሉ ቢሮ ቁጥር ስንት ነው የት ነው ይሄ ኮምፒውተር ይከፈት የነበረው?

⇒ ቢሮ ቁጥሩ ትንሽ ዘግየት ስላለ አላስታውስም

⇒ ምንድን ነው የመርማሪ ቢሮ ነው የኮምፒውተር ቤት ነው ?

⇒ የመርማሪዎች ቢሮ ነው

⇒ ሁለት ኮምፒውተር ነበር አደል አንድ ላፕቶፕ አንድ ደግሞ የጠረጴዛው አደል ?መጀመሪያ የተደረገው ስራ ላፕቶፑ የመጀመሪያ ላፕቶፕ የራሴ ነው ያሉት ያመኑበትን ላፕቶፕ

⇒ ቆይ ወደዛ ይመጣሉ ስንት ኮምፒተር ነበረ ግቢ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

> ማለት በጊዜው የነበረው ነገር ላፕቶፕ የራሶቸውን ላፕቶፕ አመኑ ፓስወርዱን ከፈቱ 2ሀ ኮምፒውተር ላይ በአንትን ተገናኙ በኮምፒውተር ማገናኛ አለ አደል አስክሬኑን ትልቅ አርጉ እንዲያሳይ ማለት ነው ከዛ ያንን ዶክመንት በስነስርዓት ሁላችንም በደንብ አየነው ከዛ በሲዲ በወረቀት ላይ ተፈራረምን አንድ ኮምፒውተር ነው ያለው

⇒ አንድ ኮምፒውተር ሲሉ ላፕቶፕ አለ አሁን ተከሳሹ ፓስወርድ ተጠቅሞ ከፈተው ያሉት ላፕቶፕ አለ ከሱ ውጪ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠ ትልቅ የጠረጴዛ ኮምፒውተር ያውቃሉ? አዎ

⇒ እሱ ኮምፒውተር አልነበረም እንዴ?

⇒ እሱ ኮምፒውተር አልነበረም

⇒ ስለዚህ ላፕቶፕ ብቻ ነው ቢሮ ውስጥ የነበረው?

⇒ የሳቸው ላፕቶፕ አነስተኛ ስለሆነች እስክሪኗ ሌላ ላፕቶፕ ሌላ እዛው ያለ ላፕቶፕ እዛው ሲገናኝ ፊት ለፊት

⇒ ሌላ ላፕቶፕ ነው ሁለት ላፕቶፕ ነበረ ማለት ነው?

⇒ አዎ አንደኛው የእሳቸው ላፕቶፕ እስክሪኗ ትንሽ ስለሆነች በደንብ እንዲያዩት ስለተፈለገ ነው ያ ነገር የተደረገው ይመስለኛል

⇒ ቆይ ሁለቱ ላፕቶፓች ?

⇒ የእሳቸው ሶፍት ዌር ወጥቶ ሰፋ ያለ ላፕቶፕ ላይ ተደርጐ አየን ማለት ሶፍትዌር ስልሀ የእሳቸው ለፕቶፕ ጠባብ ስለሆነች ለእይታ አለ አደል ከዚህኛው እዚህ የምታሳይበት ሶፍትዌር ማለት ኮምፒውተር ላይ ያለችው አለች አደለ ውስጥ ያለችው ኮምፒውተሯ ላይ ሌንስ ምናምን አለች አደለ እነሱን በባለሙያ ነው እኔ አላውቅም አገናኝተው ነው ያየነው እኛ ከተሼባ ተለቅ ባለ ላፕቶፕ ማለት ነው

⇒ እሺ ሁለቱ ላፕቶፖች እርስ በእርስ ተገናኝተው ነበር ትክክል አደል? አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከዛ ከአቶ በድሩ ወይም ከተከሳሹ ላፕቶፕ ላይ የኢሱ ሰዓት ዊር ወጥቶ ትልቁ ላይ ተገናኘ ትልቁ ላይ ተሰካ? አዎ

⇒ ከዛ ቅድም ይዛ ላፕቶፕ ታሽጐ ነበረ እናንተ ስትገቡ ላፕቶፑ በድሩ አጠገብ አልነበረም እንዴ ስትገቡ በድሩ የከፈተው ትንሹ ላፕቶፕ እዛው ጠረጴዛ ላይ አልነበረም እንዴ? እንደገባ ላፕቶፑን መርማሪው ለጋሽ በድሩ ሰጣቸው አዩትና እኔም ባለቤቱም የምጠቀምበት የራሴ ላፕቶፕ ነው አሉ በራሳቸው ፓስወርድ ከፈቱት እዛው ጠረጴዛ ላይ እንዳለ ማለት ነው

⇒ ስለዚህ እናንተ ከገባችሁ በኋላ ላፕቶፑ መጣ ? እኛ ከገባን በኋላ አደለም ላፕቶፑ የመጣው ከዛ በፊት ነው እዛው ተቀምጧል ላፕቶፑ

⇒ እንደገና ይደግሙታል አልተሰማም?

⇒ የተቀመጠበት ቦታ ላፕቶፑ እራሱ እራሳቸውእኛ ሁላችንም በቆምንበት ላፕቶፑ ከራሳቸው ጋር ነው ቁጭ ብሎ ያወጣው

⇒ ቁጭ ብሎ ነበር በፕላስተር ታሽጐ ነበር ብለዋል ከፕላስተር ውጭ ሌላ ፊርማ የተፈረመበት ነገር ነበር ? ምንም አይነት ነገር የለውም

⇒ ፕላስተር ብቻ ነው የታሸገው በፕላስተር ብቻ ነው ?

⇒ የታሸገው በፕላስተር ነው እንደታሸገ እና ምንም አይነት ነገር እንዳልተከፈተ እራሳቸው አዩት ከፈቱት

⇒ እሺ አቶ ሚሊዮን ቅድም ሲመሰክሩ እኔ ጠይቄዎት ተበሳጭቶ ሲናገር ነበረ ብለዋል መጨረሻ ላይ ፊርማው ሲፈረም እነዚህ ፋይሎች የኔ አደሉም እኔ ኮምፒውተር ውስጥ የተጫመሩ ናቸው ነገር ግን ፊርም ካላችሁኝ ዛሬ የተገኙ ብዬ በ08/01/2005 የተገኙ ብዬ ነው የምፈርመው ብለው ነው አደለ የፈረሙት ?

⇒ ከኔ የተገኘ ነው ብለው ነው የፈረሙት



2635

1087

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እኮ ዛሬ የተገኘ ዛሬ 08/2005 በዛው ቀን የተገኘ? በዛው ቀን የተገኘ ብለው ፈርመዋል አዎ

⇒ እሺ አመሰግናለሁ ጨርሰናል

⇒ ላፕቶፑ የኔ ነው እኔና ባለቤቴ ነው የምንጠቀምበት ብለዋል ብለዋል አይደል? አዎ

⇒ ላፕቶፑ የኔ አይደለም ብለዋል እንዴ?

⇒ ላፕቶፑ እኔም ባለቤቴም እምንጠቀምበት ነው የሷ የሆስፒታል የምትማርበት አንዳንድ

⇒ አይ እኮ ይሄ ላፕቶፕ የኔ አይደለም አላሉም ?

⇒ በብዛት ሚስቴም እኔም የምንጠምበት ነው የኔ ነው ነው ያለው

⇒ እኮ ይሄ ላፕቶፕ የኔ አደለም አላሉም? ግልጽ ነው ሌላ ጥያቄ

⇒ አሁን ሲነግሩን ፓስወርድ እራሳቸው ከፍተው ፓስወርድ ክፈት ተብለው እኛም ታዛቢ እንደሆንን ተነግሯቸው ፓስወርድ እራሳቸው ነው የከፈቱት አሉ አደለም ?

⇒ አዎ

⇒ በሌላ ደግሞ አሁን መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ሲጠየቁ ተጨምሮ ነው የሚሆነው የኔ አደለም ብለዋል ማን ነው የጨመረብኝ ነው የሚሉት?

⇒ ማለት እኔ በጊዜው

⇒ ቆይ ምስክር

⇒ እኛ በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ያነሳነው ይሄ ፋይል የኔ አደለም ተጨምሯል የሚለውን እንጂ ማን ጨመረው የሚለውን እንትን አላልንም እና አሁን እየተጠየቀ ያለው ሌላ እርእስ ነው በዋና ጥያቄ አልተነሳም እኛም መስቀለኛ ላይ ያላነሳነው ስለሆነ ሊጠየቅ አይገባውም

⇒ የተከበረው ችሎት ግልጽ ነው አሁን ከአንድ ወር ከአስራአምስት በኋላ ነው ይሄ ላፕቶፕ የመጣልኝ ብለው ሁለ ጠይቀዋል ከተባለ ላፕቶፑ የተገኘው በዛ ወቅት የነበረው ፌደራል ፖሊስ ነው ስለዚህ ፌደራል ፖሊስ ነው የጨመረብኝ ሴት አፕ ተደርጎብኛል እንጂ ይሄ ሰነድ የኔ አደለም ብለዋል ብለው በመስቀለኛ ጥያቄ ያንን ለማስመስከር ነው ጥረት



2636 1088

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያደረጉት ስለዚህ ጨምሮብኛል የሚሉትን አካል ለይተዋል ወይ ቤት ውስጥ እያለ ነው ወይስ እዚህ መጥቶ ነው ማንን ነው ጨምሮብኛል እያሉ ያሉት የሚለው የክላሪፊኬሽን ጉዳይ ነው በዚህ ደረጃ ደግሞ ያ ነው አላማው

⇒ እሺ ብይን ሰጥተናል ጥያቄው ያልተነሳ ነው አዲስ ነው የሚል ተቃውሞ ነው የተነሳው የተሰጠው ምላሽ አዲስ አይደለም የሚል ነው ጥያቄው ተገቢ ነው አይደለም የሚለውን ፍ/ቤቱ አይቶታል መቃወሚያ የቀረበበት ጥያቄ በላፕቶፑ ላይ የተጨመረ ነገር አለ ብሎ አልፈርምም ብሎ ሲከራከር ነበር ብሏልና ማን ጨመረ አለ የሚል ጥያቄ ነው የቀረበው የተነሳው መቃወሚያ እኛ ይሄን አላነሳንም የሚል ነው በመሰረቱ ያው የመስቀለኛ ጥያቄ አላማው በዋና ጥያቄ የተነሳውን ነገር እውነት አለመሆኑን ወይ የተሳሳተ መሆኑን ማሳየት ነው በድጋሚ የሚቀርበው ደግሞ እሱን ወደ ቦታው መመለስ ነው አላማው ማለት ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ሰነዶች የኔ አይደሉም ተጨምሯል የሚል ክርክር ተነስቷል የሚል ምስክሩ መልሷል አሁን የተነሳው ጥያቄ ተጨምሯል ከተባለ ማን ጨመረ የሚለው ከሱጋ ተያይዞ የሚነሳ እንጂ አዲስ ጥያቄ ተብሎ የሚወሰድ አለመሆኑ ግልጽ የማድረጊያ ጥያቄ ስለሆነ ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥል ተብሏል

⇒ እሺ ሚሊዮን ማን ጨመረብኝ ነው የሚሉት ማለት ወደ ኢሜሌ ተልኮብኛል ነው እዚህ ፖሊስ ጨምሮብኛል እናንተ ናችሁ የጨመራችሁብኝ ነው?

⇒ እኔ ላፕቶፕ ላይ እንደዚህ አይነት ነገር አላኩም እኔ እንደዚህ አይነት ነገር ተጠቅሜ አላውቅም ላፕቶፑ የኔ ነው ነው የክርክራቸው የነበረው

⇒ እንደዚህ አይነት ነገር ተጠቅሜ አላውቅም?

⇒ አዎ እኔ ላፕቶፑ የኔ ነው ግን እንዚህ አይነት ነገር ተጠቅሜ አላውቅም የሚል ነው ከመርማሪዎቹ ጋር የተነጋገሩት ንግግር /ግልጽ ያልሆነ/



2837

1089

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እኮ ሰነዱ ምንድን ነው የትኛው ሰነድ ነው አሁን ያንን ያሉት ሁሉንም ነው ወይስ ከሰነድ ውስጥ እየለዩ ነው ?

⇒ ከሰነድ ውስጥ እየተለየ ነው ማለት 53 ሰነድ ነው ያለው ከ53 ሰነድ ውስጥ አንድ የማስታውሰው መለስ እንደታመመ ሆኖ አላንኳበር የሚል ጽሁፍ ያለበት ስለሆነ አስታውሳለሁኝ እና ይሄን እኔ አሁን እኔ እንደዚህ እንደዚህ ነው ሲሉ ነው የሰማሁት

⇒ እኮ ስለዚህ ሰነዶችን እየመረጡ ነው ይሄ?

⇒ አዎ ይሄን ሰነድ ጨርሼ እኔ እንደዚህ አይነት ነገር ምናምን እያሉ ሰነዱ ላይ እየተለየ ነበር ሲሉ የነበረው

⇒ ስለዚህ እሳቸው ይሄ የኔ አይደለም ተጨምሮብኝ ነው ተልኮብኛል እያሉ የነበሩት እየመረጡ ነው? ሙሉ በሙሉ አደለም አዎ

⇒ በትክክል ከምንድንነው የተገኘው እንትኑ እሳቸው በፓስዋርድ ከፍተው ከምንድን ነው የወጣው ስለ ኮምፒውተር እውቀት አሎት እርስዎ?

⇒ እኔ ስለኮምፒውተር እውቀቱ ስለሌለኝ ነው ይቅርታ እና

⇒ እኮ ከምንድን ነው የተገኘው ማለት ተልኮብኛል ነው ያሉት ተጨምሮብኛል ነው እዚሁ ተጨምሮብኛል ነው ?

⇒ ማለት እሳቸው ሉ የነበሩት እኔ አላውቀውም እኔ እንደዚህ አይነት ነገር ተላልኬ አላውቅም ነው ቃላቸውን ሲሰጡ የነበረው እንጂ

⇒ ተላልኬ አላውቅም?

⇒ አዎ እኔ እንደዚህ አይነት ነገር ተላልኬ አላውቅም እንጂ ፖሊስ እንዲህ ከተተብኝ እንደዚህ አይነት ነገር አልሰማሁም

⇒ እንደዛ አላሉም?

⇒ አልሰማሁም አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ ሶፍቴሩ ወጥቶ ወደ ሌላ ተገበጠ አሉ  እርግጠኛ ጥት ሶፍትዌር ነው የወጣው? ማለት እሳቸውም እውቀቱ ስላላቸው ኮምፒውሩ በስነስርዓት ተከፍቶ ማለት ነው ያ ነገር ሲገጣጠም እራሱ እየተነጋገሩ ነው አምነውበት ያንን ነገር ያደረጉት

⇒ እሳቸውም እየተባበሩ?

⇒ አዎ እሳቸውም እራሱ ይሄን እንደዚህ እንደዚህ ነው ተባብለው ስለኮምፒውተሩም እውቀቱ ስላላቸው

⇒ ለምን ነበረ ያ የተደረገው?

⇒ በደንብ እንዲታይ ነው

⇒ ለመታየት ብቻ ነው ? አዎ

⇒ እንጂ ከተገለበጠ በኋላ ወይም ከተያዘ በኋላ የተቀየረ ነገር የለም? ከተገለበጠ ምናምን በኋላ አደለም ማለት እሳቸውም በደንብ አውቀውት ይሄን አንደዚህ እንደዚህ አድርገው ይሄን እን ደዚህ ተባባሉ እስክሪኑ ላይ ሰፋ ብሎ እንዲታይ

⇒ ለእናንተም ለሳቸውም እንዲታይ ማለት ነው ?

⇒ ለሁሉም እንዲታይ ለማድረግ ነው ለምን ይቺን መጽሃፍ ነው የምታክለው የእሳቸው ላፕቶፕ ትንሽ ነች

⇒ ወደሌላ ላፕቶፕ በመደረግ ሌላ ሰነድ የተጨመረ ነገር የለም ?

⇒ ምንም ነገር የለም

⇒ እሺ ፈርምና ምስክር እንሆናለን አልፈርምም ብለዋል እንዴ ሰነድ ላይ?

⇒ ዛሬ የወጣ ነው ብዬ ነው የምፈርመው ብለው ሲፈርሙ ከኔ ዶክመንት የተገኘ ቀኑን ጽፈው ማለት ነው በ8/1/2005 ብለው ሲፈርሙ እኛም ታዛቢ ብለን ፈረምን እሳቸው እንትን ባሉበት ማለት ነው

⇒ ከኔ የተገኘ ብለው ቀን ጽፈዋል? አዎ



2639 1091

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከዛ ውጪ እናንተም ቀን ጽፋችኋል? እኛም ቀን ጽፈን ነው አዎ
- ስለዚህ የእናንተም የእሳቸውም የተገኘበትን ሰማችሁና የተገኘበት ቀን አለ? አለ አዎ
- ታዛቢ ነን ብላችሁ ማለት ነው? አዎ

⇒ ከዛ ውጪ ሌላ ነገር የለም? ሌላ ነገር ምንም የለም

⇒ ስለዚህ ምንድን ነው አልፈርምም ብሏል እንዴ?

⇒ አይ አልፈርምም አላሉም ግን ዛሬ የተገኘ ነው ብዬ ከኔ ዶክመንት የተገኘ ነው ብዬ በዛሬ ቀን ብዬ እፈርማለሁ ብለው ፈርመዋል እኛም ፈርመናል

⇒ ይሄ ላፕቶፕ ከዛ በፊት በብርበራ ከቤታቸው በሕጋዊ መንገድ ይገኝ አይገኝ የሚያውቁት ነገር አለ? እሱን ምንም የማውቀው ነገር የለም

⇒ እሺ ድጋሚ ጥያቄ አብቅተናል

⇒ እሺ የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

⇒ ስለ ኮምፒውተር አልችልም ነው ያልከው አደለ? አዎ

⇒ ስለዚህ ፓስወርድ እያልክ ነው ስታወራ የነበረው እንዴት አወቅከው ፓስወርድ መሆኑን ? አይ ያው እስከ ቴክኒክ እና ሙያም ብሆን ትንሽ ተምሬያለሁ

⇒ ታውቃለህ ስለ ፓስወርድ? ያው ኮምፒውተር ውስጥ ያለ ነገር አንዳንድ ነገሮች ፓስወርድ ምናምን ሲባል

⇒ እኮ ለምን ለምንድን ነው ፓስወርድ የሚያስፈልገው?

⇒ ጠለቅ ያለ እውቀቱ የለኝም ግን ፓስወርድ ምናምን ሲባል እሰማለሁ

⇒ እሺ ምናልባት ኢንተርኔት ነበረ እንዴ በወቅቱ ፓስወርድ የተጠቀምነው ኢንተርኔቱን ለመክፈት ነው ወይስ ኮምፒውተር ለመክፈት የሚጠቀሙት ፓስወርድ ነው ለይተዋል እሱን? ፓስወርድ ማለት የራሱ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እያ በዛን ቀን የተጠቀሙት ፓስወርድ ተከሳሹ የተጠቀመው ማለት ነው ኢንተርኔት ውስጥ ለመግባት የተጠቀመበት ነው ወይስ ኮምፒውተሩን ለመክፈት?

⇒ ኮምፒውተሩን ለመክፈት ነው

⇒ የራሱን ኮምፒውተር ?

⇒ የራሱን ኮምፒውተር ለመክፈት ነው የተጠቀመበት ፓስወርዱን

⇒ እኛ ታዛቢዎች እንደሆንን ለእኛ ተነግሯል ነገር ግን ለተከሳሽ መብቱ አልተነገረውም ብለሃል እና እሱን ነገር እስቲ ግልጽ አድርግ እኛ ታዛቢዎች መሆናችንን ለበድሩ እኛ ታዛቢ መሆናችንን ተገልፆላችኋል ብለህ ነበረ ቅድም?

⇒ አዎ

⇒ ከአሁን በብርበራው የሚገኘው ነገር በኋላ ማስረጃ እንደሚሆንበት ግን አልተገለፀላቸውም ብለህ ነበር ቅድም ማለት ነው ስትጠየቅ እና እናንተ ታዛቢዎች መሆናችሁ የተገለፀው በድሩ ባለበት ነው ወይስ እሱን ሳታገኙ በሌላ ቦታ ነው የተገለፀላችሁ ታዛቢ መሆናችሁ? እዛው በድሩ ባለበተ ነው

⇒ ከዛ በኋላ በእናንተ ታዛቢነት የሚገኘው ማስረጃ የሚገኘው ሰነድ ወይም ሌላ ነገር በማስረጃ እንደሚቀርብበት በወቅቱ አልገለፁም ማለት ነው ፖሊሶቹ ?

⇒ ማለት ይሄኛው 53 ገጽ ሲወጣ በዚህ ቀን

⇒ ገፁ ሲወጣ ወይም መጀመሪያ ይሄ ዛሬ የሚለው ነገር ተገልፆለት ነበር ወይስ አልነበረም ነው? ገፁ ሲወጣ ? ሲወጣም ይሁን ወይም መጀመሪያ?

⇒ ተነግሯል

⇒ ምን ተብሎ? ማለት በፍ/ቤት ደረጃ እንደምንቀርብ እና እኛም ታዛቢዎች ሆነን እንደምንመሰክር

⇒ እሺ ሰነዱስ ለፍ/ቤት እንደሚቀርብ ተገልፆለታል?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ስለፍ/ቤት የሚገልጽ ሰነድ?

⇒ ሰነዱ ለፍ/ቤት እንደሚቀርብ ለበድሩ ተነግሯል ወይ?

⇒ አዎ ተነግሯል

⇒ ሌላው ሶፍትዌር ከአንድ ኮምፒውተር ወደ ሌላ አሳልፏል ነው ያልከው እና እሱ ነገር ሶፍትዌር ነው ወይስ ዶክመንቱ ነው ተወስዶ ወደ ሌላ የተላለፈው የትኛው ነው?

⇒ ማለት ለማየት በእስክሪን ለማየት ?

⇒ አዎ ገባኝ ?

⇒ በቃ በባለሙያ አገናኘተው

⇒ ኤል ሲዲ ነው ኮምፒውተር ነው ያገናኙት ?

⇒ ከላፕቶፕጋ ሰፋ ካለ ላፕቶፕጋ ነው ያገናኙት

⇒ በሲዲ ወይ በሌላ ነገር ወስዳችሁ ነው ወይስ በኬብል?

⇒ በኬብል ነው ማለት ወረቀቱ ሲወጣ ነው በኬብል የሄደው መጀመሪያ በእሳቸው ኮምፒውተር ላይ የተላለፈው ነገር

⇒ እንዴት ወደ ትልቁ ኮምፒውተር ተላለፈ በምን? አገናኝተውት

⇒ በምንድን ነው ያገናኙት? ተፈታ ብሎትን ፈቱት መጀመሪያ የራሳቸው የጋሽ በድሩን ላፕቶፕ ተፈታ ብሎት እራሳቸው እዛ ቆመው ሲፈታ ከፈቱ በኋላ አገናኙት በራሳቸው ሲስተም ማለት ነው እና ያን ነገር አደረጉ

⇒ ጨርሰዋል እናመሰግናለን ቀጣይ ምስክር

⇒ በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ

⇒ እሺ ለምስክርነት ነው የመጡት ስሞን ያባቶን ስም ሳይጨምሩ የራሳን ስም ብቻ ይነግሩናል ?

⇒ መለሰ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በንተና ነተው አቃቤ ሐግ ?

⇒ እሺ ምስክሩ በ74ኛ ደርሰዋል በማስረጃ ዝርዝሩ 152 ላይ የተጠቀሱት አቶ መለሰ ለምስክርነት ቀርቧል አቶ መለቀ እነማን ላይ ነው የሚመስክሩት ዛሬ ?

⇒ አቶ ጀማል ያሲን እና ሙኒር ሁሴን አዎ አውቃቸዋለሁ አንደኛውን ለአንድ ቀን ነው ያየሁት ሌላኛውን ግን በደንብ አውቃቸዋለሁ አቶ ጀማል ያሲንን አውቃለሁ ሙኒርንም በአይኔ አውቃለሁኝ

⇒ እሺ ይቅርታ ምስክሩ 19ኛ እና 15ኛ ተከሳሾችን ለይተው አሳይቷል ምንድን ነው ያዩት ከነሱጋር በተያያዘ ምን ፈፀሙ ተብለው ተከሰሱ እስቲ አጠር አርገው ዝርዝር ሳይገቡ ይንገሩን?

⇒ አይ እኔ በእለቱ በእርግጥም በሽብርተኛ ወንጀለኛነት ስለሚጠረጠሩ ቤታቸው እንዲፈተሽ እናንተ ምስክር ትሆኑናላችሁ ተብዬ ነው የቀረብኩት

⇒ እሱን ነው ያዩት?

⇒ አዎ

⇒ የሁለቱንም ቤት ነው ያዩት? አዎ የሁለቱንም ቤት አይቻለሁ

⇒ እሺ ዝምድና ወይ ጥላቻ አሎት እንዴ?

⇒ ምንም የለም

⇒ ምንም ጥላቻም ዝምድናም የለም ?

⇒ የለም

⇒ እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ

⇒ እሺ አቶ መለሰ ጀማል ያሲን እና ሙኒር ሁሴን ቤታቸው ሲበረበር ተገኝተሀል ብለዋል

⇒ አቶ መለሰ እስቲ ፊቶን ወደኛ ያርጉና ጥያቄ ከዚህም ከዛም ሊሆን ይችላል ወደዛ ይዞሩ እሺ ቀጥሉ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ፣ ከአቶ ጀማል ያሲን ያጀምሩና መቼ ነው ቀኑ?

⇒ ቀኑ ሐምሌ 12

⇒ ዓመተምህረት?

⇒ 2004

⇒ ምንድን ነው ቦታው የት ነው ?

⇒ ቦታው ኮልፌ ቀራንዮ ወረዳ 13

⇒ የቤት ቁጥሩን ያስታውሳሉ?

⇒ አላስታውስም ኮንዶሚኒየም ስለነበረ አላስታውስም

⇒ እሺ እንዴት ነው እርስዎ እዛ የተገኙት? በአጋጣሚ እኔ እዛ ግቢ ውስጥ ነበርኩኝ

⇒ የት ግቢ ?

⇒ ኮንዶሚኒየም ግቢ ዉስጥ እዛጋ እያለን ፖሊሶች መጡና ጠየቁ

⇒ ኮንዶሚኒየሙ ምን ተብሎ ሪው የሚጠራው ?

⇒ ሚኪሊላንድ ኮንዶሚኒየም

⇒ እሺ ? ከዛ እንደዚህ ቤት ስለምንፈትሽ በታዛቢነት ትቆሙልናላችሁ ወይ ታዩልናላችሁ ወይ ሲሉን እሺ እኔ ምንም ችግር የለም ነው ያልኩት

⇒ እሺ ስንት ሰዓት ላይ ነው ሰዓቱ?

⇒ ኦል ሞስት 12 ሰዓት አካባቢ ነው 12 ሊሆን ይችላል ዝናባማ እና ጭጋጋማ ነበረ በእለቱ

⇒ ብግምት ነው የሚነግሩን ሰዓቱን? አዎ

⇒ እሺ ምንድን ነው በብርበራ የታዘቡት?

⇒ እኔ በወቅቱ ሲጠሩኝ 1ኛ የፍ/ቤት ትእዛዝ ይዛችኋል ወይ የፍ/ቤት ትእዛዝ ከያዛችሁ አሳዩን አልናቸው አሳዩን ከኮልፌ ማለትም ከአዲስ ከተማ ፍ/ቤት የመጣ ትእዛዝ ነው ቤታቸው እንዲፈተሽ የሚል ነው እሳቸውም ባሉበት ቦታ ይሄንን ጥያቄ ጠይቁ ከዛ በኋላ



http://ethcriminalawnetwork.com/

አሳዩን አነበብን ቆምን ከዛ በኋላ አጠገቤ ያሉት ሰወች ቤቱ እንዲከፈት ፈቃደኛ ናት ወይ ሲባል አዎ አሉ አንካኑ ተከፈተ ገባን

⇒ ቤት ውስጥ ሰው ነበረ ?

⇒ ቤተሰብ አዎ አሏቸው

⇒ እሺ እንካኑታችሁ ገባችሁ? አዎ

⇒ እሺ ምንድን ነው የታዘቡት?

⇒ ቤቱ በሚበረበርበት ሰዓት ላፕቶፕ ነበረ ፍቃድ ያለው ሽጉጥ ማለት በዘልማድ ኮሊሲያን መትረየስ ይሏታል ትንሿ ሦስተኛዋ እሷ ከ5 ጥይት ጋራ ፍቃድ አለው ወይ ስንል ፍቃዱን አውጥተው አሳይተውናል ከዛ ጽሁፎች ናቸው የተገኙት ማለትም በአረብኛም በአማርኛም የተፃፉ ናቸው ሲዲዎች ናቸው ከዛ ቢዲዮ ካሴት ነው አጀንዳዎች ተይዘዋል እነዚህን ነው ያየሁት

⇒ ጽሁፍ ማለት አጀንዳ ብለዋል አጀንዳው ምንድን ነው?

⇒ አይ አጀንዳው ይሄ የግል ነው ማለት የግል ማስታወሻ ማንኛውም ሰው የሚይዘው ነው ያንን በወቅቱ ውስጡን አገላብጠን አላነበብነውም ግን በማስረጃነት ፖሊሱ ይጠቅመኛል ስላለ ስለያዙ ያንን ማስታወሻ ከተያዘው ንብረት ጋራ አንድላይ አዳምረው ይዘውታል

⇒ ላፕቶፕ ሽጉጥ እና አጀንዳ ሌላ የተያዘ አለ?

⇒ ሲዲ ቪዲዮ ካሴት ጽሁፎች ደግሞ

⇒ ጽሁፎች ምን አይነት ?

⇒ ክርስትና እና እስልምና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚል እነዚህ ጽሁፎች አሉ ድምፃችን ይሰማ አንዲት ወረቀት ብቻ ነች የተገኘችው እነዚህ ናቸው

⇒ ሌላስ? ሌላ እኔ አላስታውስም ይሄው ነው

⇒ የት የት ነው የተገኙት እነዚህ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

> መደርደሪያ ሼልፍ ውስጥ ነው ሲሉችም ማለትም ኪታብ ነው የሚባለው ቁርአን አደለም ሌሎች መጽሃፍቶችም በአረብኛ የተፃፉ ነበሩ እነሱን ለመውሰድ ሲሉ ይሄ ከፖሊቲካጋራ የሚገናኝ አደለም ኃይማኖታዊ ትምህርት ስላለበት ቢወስዱም ለእናንተ አያጠቅምም መልሱት ብለን በወቅቱ እንዲመለስ አድርገናል ሌላ ነገር ብር የሆነች አንድ ሺ ብር አካባቢ እራስጌ ላይ ነበረች ይሄ ብር መመዝገብ አለበት ሲሉ አይ ይቺ አንድ ሺ አይ ይቺ አንድ ሺ ብር የቤተሰብም ብር ትሆናለች እና ይመለስልን በወቅቱ በፍቅር እና በስምምነት ነው አይተን የወጣነው

⇒ እናንተ ይሄ ከእንትንጋ ማለት ይገናኛል አይገናኝም እያላችሁ በታዛቢነት ከፖሊስጋ ማስረጃዎችን እየለያችሁ ነበር?

⇒ አዎ

⇒ እሺ እርስዎ እውቀት አሎት እንዴ አረብኛ እውቀት አሎት?

⇒ የለኝም

⇒ አሁን ታዲያ የነገሩን በምንድን ነው?

⇒ አይ መጽሃፍቶቹ የተጠረዙ ናቸው ማለትም የትኛውም ላይብረሪ ውስጥ አለ በዚህ ምክንያት እኔ መጽሃፎቹ እነዚህ መፃህፍቶች ማለት ከሃይማኖቱጋ ያላቸው ቁርኝት እንጂ በአሁን ከሚነሳው በመጅሊስ ጥያቄ ላይ ከሚነሳው ጋራ የሚያያይዝ መስሎ አልታየንም አለ ውስጡን ከፍተው በሚያዩበት ሰዓት ይሄንን እንደጋራ አቋም ነው የያዝነው እንጂ በግሌ አደለም

⇒ ኦኬ ሌላ ሰው አለ ከእስዎጋ ታዛቢ? ታዛቢ አሉ አዎ

⇒ ስንት ሰዓት ላይ ጨረሳችሁ? ኦል ሞስት እንግዲህ ወደ ሦስት ሰዓት አካባቢ ጨርሰናል በዚህ መሃከል እኔ ግን አንድ ጥያቄ አንስቼ ነበር ልክ 12 ሰዐት ከሌሊቱ በኋላ ይፈቀዳል ወይ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከ12 ሰዓት በኋላ ግን አጠገቤ ያሉት መርማሪ ስልክ ደውለው የት እንደደወሉ አላውቅም ተፈትቷል ሲሉ እሺ ብያለሁ

⇒ ይሄንን ሰዓት አላፉ ጠይቃችሁ?

⇒ አዎ ጠይቄያለሁ እኔ እራሴ

⇒ ስልክ ተደውሎ ተፈትዶልናል ተባላችሁ?

⇒ አዎ እሳቸው አቶ ጀማል እራሳቸው በወቅቱ ሊመሰክሩ ችለዋል እኔ እደውም በአጋጣሚ እሳቸው ጠሩኝ እንጂ አቃቤ ሕግ አቃቤ ሕግ የጠራኝ አልመሰለኝም ምክንያቱም በሰላም በፍቅር ነው ያን ለታ እሳቸው የፈለጋችሁትን ቦታ በርብረ ብለው ቤቱን ክፍት አድርገው ጓዳ መኝታ ቤት

⇒ ፍቃደኛ ሆነው ማለት ነው ?

⇒ አዎ ፈቃደኛ ሆነው

⇒ ሦስት ሰዓት ላይ ጨረሳችሁ?

⇒ አዎ ወደ ሦስት ሰዓት አካባቢ እንደዚህ ጨረስን

⇒ ከዛ ምን አደረጋችሁ መጨረሻ ላይ?

⇒ መጨረሻ ላይ ተፈራረምን

⇒ ምን ተፈራረማችሁ?

⇒ ማለት የተገኙትን ንብረቶች እላዩ ላይ ወረቀቶቹ ላይ ፊርማችንን አኖርን

⇒ ምን እያላችሁ ፈረማችሁ?በቃ የተገኘው ላይ ሦስታችንም እሳቸው ማለትም ታዛቢው እሳቸውም ፊት ለፊት እያየን ሁሉንም እያንዳንዷን ለማንበት አንችልም ነበር ጊዜ የለንም ለመረጃ ይጠቅሙኛል ያሏቸውን ወረቀቶች እሳቸውም እኛም

⇒ እሳቸው ምን እያሉ ፈረሙ?

⇒ ምን ይላሉ ፈረሙ ስማቸውን ፃፉ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እናንተስ ምን ብላችሁ ፈረማችሁ?

⇒ ፈረምን ሰማችንን ፃፍን

⇒ እኮ ምን እያላችሁ ማለት ሰነዱ ምን ተባለ?

⇒ እርእስ አልሰጠነውም እርእስ ከቤታቸው የተገኘ ነው በቃለ ጉባኤው ላይ በቃ የተገኙትን ንብረቶች ቆጠርን ቃለ ጉባኤ ላይ ፈረምን

⇒ ከቤት የተገኘ ብላችሁ?

⇒ አዎ በወቅቱም ያልኩት ነገር አለ አቶ ጀማልንም ሆነ አቶ ሙኒርን ያላመናችሁት

⇒ ቆይ የአቶ ሙኒርን እንቆይ?

⇒ እሺ የአቶ ጀማልን ያላመኑበት ነገር ካለ ወደ ቃለ ጉባዔ ከፈረሞ መጀመሪያ አንብቡና ያላመኑበትን ነገር ለእኛም ንገሩ እኛም ያላመንበት ነገር ካለ ፊርማችንን አናኖርም አልን ከዛ እሳቸው አነበቡ ፈረሙ ፈረምን

⇒ በዚህ ተጠናቀቀ?

⇒ አዎ በዚህ ተጠናቀቀ

⇒ እሺ ወደ አቶ ሙኒር እንምጣ አቶ ሙኒርጋስ?

⇒ አቶ ሚኒር ወንደላጤ ናቸው በእርግጥ በግሕ ጥላ ስር

⇒ መቼ ነው ቀኑ?

⇒ 15 ይመስለኛል ቀኑኑ በትክልል ለማስታወስ

⇒ ምን ወር?

⇒ ሐምሌ

⇒ ዓመተምሪቱስ? 2004 ቦታው የት ነው?

⇒ እዛው ሚኪሊላንድ

⇒ እዛው አሁን የጠቀሱት ኮንዶሚኒየም?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አዎ

⇒ እሺ ይንገሩን የአሳቸውንም ይንገሩን በዝርዝር ?

⇒ በቃ ያው እሱንም እኔ በስልክ ተጠርቼ ነው እዛ አካባቢ ማለት የመጀመሪያው ቀን ስልክ ሰጥቻለሁ እንደዚህ ተባበረን ሲሉ እኔ ይሄ ምንም ችግር የለውም ብዬ መጣሁ ስመጣ የመጀመሪያ ጥያቄ ልክ ቅድም እንደተናገርኩት የፍ/ቤት ጥያቄ ነው የጠየቅኩት ስጠይቅ አሳዩን በሩን ለመክፈት ፈቃደኛነህ ወይ ሲሉት አዎ አለ ከፈተ እኔ እንደውም እየሳቀ ነው በቃ ምንም ይሄን ያህል ተጽኖ የለም ከፈተ ቤቱን ማየት ጀመርን እቤቱ ውስጥ የሚገኙትን ጽሁፎች ጋዜጣዎች አገኘን ብር አልሞስት

⇒ እስቲ ንገሩን በዝርዝር ይንገሩን ምን ምን ?

⇒ ያገኘነው ሲዲዎች ወደ ሁለት መቶ አርባ አካባቢ አግኝተናል

⇒ ሲዲዎች? አዎ

⇒ እሺ?

⇒ ቪዲዮ ካሜራ አግኝተናል ፍላሽ ፎር ጂቢ የምትል አግኝተናል ከዛ አንድ ቲሸርቶች አግኝተናል

⇒ ምን አይነት ቲሸርት ?

⇒ የቦንድ ግገር ይመስለኛል ከዛ እሱን አግኝተናል ከዛ ፍትህ የምትል እና አንድ ደግሞ አላልፊያ ኦር ምን የምትል ጋዜጣዎችን አግኝተናል ከዛ ጽሁፎችን ነው ያገኘነው የቪዲዮ ካሜራ ካሴቶችን አግኝተናል

⇒ እስቲ ጽሁፍ ከሚኗቸው በይዘት የሚያስታውሷቸው በርእስ የሚያስታውሷቸው አሉ ?

⇒ አዎ ሰፊው ሙስሊም ያልመረጠው የመጅሊስ አመራር አመ[illegible] የምትል በዚች ጽሁፍ ያላት ነገር አንብቤያለሁ

⇒ በምን የተፃፈ ነው?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በእጅ ጽሁፍ ነው

⇒ እሺ እነዚህን አሁን የዘረዘሯቸውን ንብረቶች ወዴት ምን አደረጋችኋቸው ?

⇒ እኛ ብር ነበር ብር እቤት ውስጥ በፔርሙዝ ካርቶን ነበረ አጋጣሚ ፖሊስ ሲያገኘው ዘጠና ሺ ብር ነው ባለመቶ ስምንት

⇒ በቃ ቁጥሩን ከነገሩን በቂ ነው ጥቅል ቁጥሩ ስንት ነው በመጠን? ዘጠና ሺ ብር

⇒ እሺ ይሄን ጭምር ተይዟል?

⇒ አዎ ይሄንንም ብር ከየት ነው ያመጣሽው ብለው ሲጠይቁት ?

⇒ ከባንክ ነው ቤት የጀመርኩት ቤት ስላለ ባለቤቱ ውጪ ነው ያለችው እሷ ስለላከችልኝ ቤቱን የማጽፈጽምበት ነው ብለው በእለቱ ተናግረዋል

⇒ እሺ ይሄንንስ ንብረቶች በተመለከተ ምን አደረጋችሁ? ተፈራረምን ምክንያቱም እላዩ ላይ የራሳችንን የታዛቢዎችም የሱንም ፊርማ አንድ ላይ አኖርን ካኖርን በኋላ ቃለ ጉባዔ ተያዘ በቃለ ጉባዔዉ ላይ አሁንም እሱን ነው ያልኩት እዚህ ቃለ ጉባዔው ላይ ሌላ ተጨማሪ አሁን ካሉት ነገሮች ተጨማሪ ካለ እንዳትፈርም ቅሬታ ካለህ ካለህ ንገረን አልኩት እኔም ሌሎቻችንም ምንም ቅሬታ የለኝም አለ ከዛ አብረን ተፈራረምን ወጣን

⇒ ስንት ሰዓት ላይ ጨረሳችሁ? ኦል ሞስት ወደ ሁለት ሰዓት ሦስት ሰዓት ይሆናል የጨረስነው

⇒ ስንት ሰዓት ጀምራችሁ? ወደ አስር ሰዓት ይሆናል

⇒ ሰዓቱን በተመለከተ አቶ ጀማል ያሲን ላይ ማለት ጥያቄ ጠይቄያለሁ ብለው ነበር እዚህ

⇒ ሰዓቱን ያስተካክሉት ከቀኑ አስራአንድ ሰዓት ለማለት ነው? አዎ

⇒ ከቀኑ አስር ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ? ሁለት ሰዓት ተኩልአካባቢ ነው

⇒ እዚህ ላይስ ጥያቄ አቅርበዋል እንዴ? አዎ ጠይቄያለሁኝ ደውሉ አስፈትደናል ማለት መርማሪ የነበሩት ፊታሽ የነበሩት ይሄንን ነግረውኛል



2001 2680

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት

⇒ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካለ

⇒ አቶ መለሰ እርስዎ ከእንትና እንጀምር ከጀማል ያሲን ምርመራው ሲካሄድ ከምሽቱ አስራሁለት እስከ ሦስት ሰዓት ብርበራው እንደተካሄደ ገልፀዋል ? አዎ

⇒ ስንት ሰዓት ላይ ነው እርስዎ የጠየቁት ተፈቅዷል ወይ የሚለውን ፖሊሱን ? አስራሁለት ሰት ከመሆኑ መጀመሪያ ነው የጠየቅኩት

⇒ ማለት ብርበራው ሳይጀመር? ተጀምሮ ማለት ከገባን በኋላ ሰዓት እላፊ እንዴት መግባት ማለት መስራት እንችላለን የሚለውን ጥያቄ ጠይቂያለሁ ቅድም እንደገለጽኩት

⇒ ልክ ብርበራውን ሳትጀምሩ ነው ይሄን ያሉት ከአስራሁለት እስከ ሦስት ሰዓት ስላሉን ? አዎ እንደጀመርን ነው እኔ የጠየቅኩት

⇒ ልክ ቤት ውስጥ እንደገባችሁ እንውሰደው ?አዎ

⇒ ቤት ውጥ እንደገባችሁ? ኖ በር ላይ ያለን ጊዜ የመግቢያውን ነው ከገባን በኋላ ደግሞ ሰዓቱን እንደዚህ ብዬ ጠይቂያለሁ ቅድም ልክ እንዳስቀመጥኩት ማለት ነው

⇒ ፖሊስ ስንት ፖሊስ ነበረ አሁን ከተከሳሹ ከጀማል ያሲን ጋር ? እኔ በእርግጥ ፖሊሶች መሬት ነው ያሉት እዛ እኛጋ የነበሩት መርማሪዎች ብቻ ነበሩ

⇒ ስንተ መርማሪ ነበር? ሁለት መርማሪዎች አሉ ማለት ያው ሌላው ግን ውጪ ነው የቆሙት ውስጥ አልገቡም

⇒ ውስጥ ስትገቡ ጀማል ያሲንጋ አሁን ቤቱን ስትገቡ አንኳኩ እንዴ መርማሪዎቹ ነው ያንኳኩት ? ቀደለም አላንኳኩም እነሱ

⇒ እንዴት ተከፈተ ቤቱ ? እሳቸው እዛ በረንዳ ላይ ነበሩ ቀድመው ከእኛ ፈቃኛ ኖት ወይ ቤቱ ሊፈተሽ ሲባል አዎ አሉ እሳቸው

⇒ አቶ ጀማል ማለቶ ነው ? አዎ



2002 2651

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ? ከዛ በኋላ እሳቸው አንኳኩ በር ተከፈተ

⇒ በር ተከፍቶ ማን ወጣ? ቤተሰብ ነበረ ቤቱ ውስጥ

⇒ ማለት ወንድ ሴት? አረ ሴቶችም አሉ ወንድ ሁለት ልጆች ያሉ ይመስለኛል

⇒ በሩን የከፈቱት ሴት ናቸው? አዎ ሴት ናቸው

⇒ እሺ. ከዛ ምን ተባለ አሁን እናንተ ታዛቢዎች መርማሪዎች አቶ ጀማል አሉ አቶ ጀማል በሩን አንኳኩ ከዛስ ? ከዛ መጀመሪያ በር ላይ ተነግሮናል በር ላይ ስለተነገረን ገባን ለቤተሰብ መርማሪው ገለፁላቸው

⇒ ምን ብለው ገለፁ? አይ ቤቱ በሕግ የሚፈተሽ እና በእነደዚህ አይነት ስለተጠረጠረ ከፍ/ቤት ትእዛዝ መጥተን እንዲፈተሽ ነወ አሉ ይሄንን ገለፁላቸው

⇒ እሺ. ገለፁ ከዛ ገባችሁ? አዎ ገባን

⇒ ስንት ሰው አገኛችሁ አሁን መጀመሪያ በር የከፈቱት ሴት አሉ እራሳቸውን አስተዋወቁ እንዴ ሴትየዋ? አላስተዋወቁም

⇒ እሺ. አንድ ሴት ከፈተች ከዛስ ስንት ሰው ነበረ ውስጥ ? እኔ በእርግጥ ልጆች አሉ ሕፃናት ልጆች ሁለት ሴቶች ይሁኑ እንደዛ አሉ እኔ በውል አሁን

⇒ ሌላ ትልቅ ሰው አልነበረም? ወጣቶች ሁለት ወጣቶች

⇒ ከፖሊሶቹጋር ሲገቡ ፖሊሶች ምን ይዘው ነበር ?ምንም አልያዙም ማስታወሻ ደብተር ብቻ ነው የያዙት

⇒ ቦርሳ አልያዙም? ምንም ነገር አልያዙም

⇒ ብርበራው ሲጠናቀቅ ቪዲዮ አልቀረፁም እንዴ? ካሜራ አንስተዋል ቪዲዮ ቀርፀዋል

⇒ ስለዚህ የሆነ ቦርሳ ነገር አልያዙም ሲገቡ? እኔ አላየሁም በእርግጥ እኔ ማለት እዚህ መጥቼ ነፍሴን ሽጬ የምዋሽበት ምንም ነገር የለም



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ይኸውሎት አቶ መለሰ አሁን ሌላ ነገር እኮ አላልንም ያዩትን እዚህ እንዲገልፁልን እንጂ ነፍሶን ሽጠዋል አልሽጡም የሚለው ውስጥ አልገባንም? አውቂያለሁ ቦርሳ እኔ በእርግጥም አላየሁም ማለት

⇒ እኮ ካሜራ ይዘው ሲገቡ አላዩም እንዴ ? አዎ ካሜራ የያዘበት ቦርሳ አለ ቪዲዮ የያዘበት ቦርሳ ይዘዋል ማለት ካሜራ ማነ

⇒ እሺ ማለት ቦርሳ ይዘው ነበረ ከዛ ፖሊሶቹ ይሄንን ቦርሳ ከእናንተጋር ገባችሁ ውስጥ ? አዎ

⇒ እሺ ይሄንን ቦርሳ የትጋ ነው የከፈቱት? ከፊጠገባችን ነው የከፈቱት

⇒ ማለት የትጋ ተከፈተ ሳሎን መኝታ ቤት? ሳሎን ፊት ለፊት ነው እንደገባን በርጋ ሳሎን ላይ ነው የከፈቱት

⇒ ገና ብርበራው ከመጀመሩ በፊት ነው ካለቀ በኂላ? ኖ እንደተጀመረ

⇒ ስለዚህ ካሜራውን ከፍተው ምን አረጉ? በቃ ካሜራውን ከፈተ መድረክ ማለትም አዘገጃጀ ውስጡን ከፍቶ  አሳየ ምንም ነገር እንደሌለ

⇒ ቅድም እርስዎ ሰዓት እላፊ ብለው ሲጠይቁት እንደደወለ ነግረውናል የደወለው በስልኩ ውስጥ ሆኖ የሚነጋረው ሰው ምን እንዳለ የሚያውቁት ነገር የለም አደል ?ማለት ስልኬ እራሱ የግል ነው እኔ ደግሞ ታዛቢ ነኝ እንጂ ስልክህን አምጣ ላድምጥ መብትም የለኝ የዛኔ

⇒ እኮ ተደወለና መርማሪው ተፈቅዷል ብሎ ? አዎ አስፈቅደናል ብሏል

⇒ የሚለውን ሰሙ እንጂ ይፈቀድ አይፈቀድ የሚያውቁት ነገር የለም? አስፈቅጃለሁ ማለቱን ሰምቻለሁ

⇒ የብርበራ ወረቀቱ ላይ ፍ/ቤት ዝርዝር ይሄ ይሄ ይሄ ንብረት ይያዝ የሚል ዝርዝር አለው ? አይ እኔ ዝርዝሩን በእርግጥ ከላይ ጀምሮ አነበበልን በዚህ ቤታችን የምንፈትሽ እና



http://ethcriminalawnetwork.com/

መሣሪያዎች ካሉ እና ለጊዜው አረብሻ የሚፈጥሩ ነገሮች ካሉ በቁጥጥር ስር እናውላለን ብለው ማብራሪያ ሰጥተን

⇒ እንጂ ወረቀቱን እርስዎ አላዩትም? አነበበልን ቢጋራ

⇒ ሲያነቡ ዝርዝር ነገር ይሄ ይሄ ነገር ? መሣሪያዎች ለቅስቀሳ የሚያመቹ ነገሮች ካሉ እነዚህ እነዚህን ነገሮች እንይዛለን በቁጥጥር ከወንጀሉ ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች እንይዛለን ሲል እኛ ታዛቢዎች ነን

⇒ ኢኸውሎት አቶ መለሰ አሁን መርማሪው የነገሮትን አደለም የጠየቅኮት

⇒ የተከበረው ችሎት አሁን መቃወሚያው ማለት ምንድን ነው ምስክሩን በዋና ጥያቄ ተጠይቀው መልሰዋል አሁንም በተደጋጋሚ እየተናገሩ ነው ስለዚህ አሁን ሃራስመንት አይነትም ባይባልም ማሰልቸት ነው የሚሆነው ምስክሩን ወደ እንትን ውስጥ ነው እየተገባ ያለው ስለዚህ ምስክሩን በማሰልቸት ሌላ ነገር እንዲናገሩ ከሆነ አልገባኝም ግን እየተሰላቹ ነው ምስክሩን ከጠበቅ አንፃር ማለት ነው

⇒ እሺ አካሄድ ስለሆነ ምንም መልስ የምናሰጠው ነገር የለም ድግግሞሹ ይታያል እሱን አስተካክሉና ቀጥሉ

⇒ አቶ መለሰ ቅድም የፍ/ቤት ትእዛዝ መኖሩን እንዳነበቡ ገልፀውልናል የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ስላነበቡ እዛ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ላይ የሚያዙ የሚበረበሩ ንብረቶች

⇒ ይሄንን በሚያውቀው ገልጿል ወደሌላ ቢያልፉ ይሻላል

⇒ ቅድም ቃለ ጉባዔ ላይ ስትፈራረሙ አቶ ጀማልጋ የተገኙ እቃዎች ውስጥ ሲዲዎች እነዚህ ቪዲዮ ካሴቶች አጀንዳዎች ያሏቸው ነገሮች ይሄን ያህል አጀንዳ ይሄን ያህል ሲዲ ይሄን ያህል ቪዲዮ ካሴት እያላችሁ በቃለ ጉባዔዉ ላይ ነው አደል የተፈራረማችሁት? አዎ

⇒ ሲዲው ላይ ፈርማችሁበታል ?ሲዲው ላይ እኔ በወቅቱ አልፈረምንም 26 ሲዲዎች ምልክት አድርገን ማለትም 26 /ግልጽ ያልሆነ/



2654

2005

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ቆጥራችሁ? አዎ ቆጠርን ኢሂ ሲዲው ላይ ማለት ጀርባው የተላጠ ስለሆነ ለፊርማ የሚያመች አደለም ቆጠርን አስቀመጥን ይሄንን ነው የተፈራረምነው

⇒ አጀንዳዎቹ ላይስ? አጀንዳዎቹ ላይ ፊት ለፊታቸው ላይ ተፈርሟል

⇒ አንድ ገጽ ላይ? አዎ

⇒ ቪዲዎ ካሴትስ ? ቪዲዮ ካሴቱ እሱ አራት ነው እሱ ላይም እሱ አንደኛ የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ምን የሚል ነው ግልጽ እላዩ ምልክት ያለበት ስለሆነ ይሄ የራሶት መሆኑን ያረጋግጡልናል በሚል እኛ እላዩ ላይ አልፈረምንም ምክንያቱም ግራና ቀኙ ልሙጥ ነው ለፊርማ የሚመችበት ቦታ የለም እላዩ ላይም ያለው ወረቀት አደለም ስለዚህ ፈልፈረምንም እላዩ ላይ እኔ አልፈረምኩኝም ሌሎቹም አልፈረሙም

⇒ እሺ አቶ መለሰ ቅድም እርስዎ እራሶት ጠይቄ ፖሊስ አንብቦልኛል ብለዋል ወይም አሳይቶኛል የፍ/ቤት የብርበራ ትእዛዝ ብለዋል ይሄ ግን ለአቶ ጀማል ሲነበብ አላዩም አደል እርስዎ አይተውታል ጠይቀው አንብበውታል ነገር ግን ለአቶ ጀማል ሲነበብ አላዩም አደል ወይም አቶ ጀማል ሲያነበው አላዩም አደል እርስዎ ?ማለት እኔ ለክቡር ፍ/ቤቱ የምገልፀው ቅድምም የተናገርኩት ነው በር ላይ እንደተደረሰ በጋራ ተነቦልናል እሳቸው መሃላችን አሉ አቶ ጀማል

⇒ ቅድም ግን እኔ ጠይቄ ነው በደንብ እንደውም ሲያብራሩ የነበረው ጠይቄ እያሉ ነው በሁለቱም ጉዳይ ጠይቄ የፍ/ቤት ትእዛዝ የብርበራ ትእዛዝ አላችሁ ወይ ብዬዬ ሰጥተውኝ አንብቤ ነው እያሉ ያሉት ? አንብቤ አላልኩም

⇒ እሺ የትኛውን እንያዝ ? አንብቤ አሉጣኝም

⇒ እነሱ ነው ያነበቡላችሁ? አዎ በጋራ ነው የተነበበልን

⇒ ለአቶ ጀማል ተነቦለታል ? አቶ ጀማልም መሃላችን እኮ አሉ



2685

2086

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. ምን ምን ይበርበር ወይም ይያዝ ይላሉ ትእዛዙ? ቅድም እኮ ለጠየቁኝ የሕግ ጠበቃ የመለሱላቸው ይመስለኛል
- በቃ መልሰው ከሆነ እዘለዋለሁ ስላልሰማሁት ነው
- የአቶ ጀማል ቤት ተበርብሮ ሲወጡ ፖሊሶች ምንድን ነው ይዘው የወጡት? ያንን የተፈራረምንበትን እና በወቅቱ የተያዙትን ንብረቶች ብቻ ይዘን ነው የወጣነው
- ከዛ ከግቢ ሲወጡም ጭምር እርስዎ አይተዋል? እዛው አጠገባችን ተሳፈሩ ሄዱ

⇒ የአቶ ጀማል ሁለት ወንድሞች ዶ/ር ሰአድ ማእሩፍ እና መሃመድ ማእሩፍ የአቶ ጀማል የባለቤታቸው ወንድሞች ሁለት ወንድሞች ዶ/ር ጀማል ማእሩፍ እና

⇒ እስቲ እንደዚህ እናርገው አሁን የዝምድናው የምናምን ብዙም እንትን ማብዛት ነው እና የሚሆነው ቀጥታ የሚጠይቁትን ብቻ አሁን ስንት ዘመዶች ምናምን የሚለው

⇒ የተከበረው ፍ/ቤት የአቶ ዘመዶች የሆኑ የባለቤታቸው ሁለት ሰወች ዶ/ር ሰዓድ ማእሩፍ እና መሃመድ ማእሩፍ የተባሉ ፖሊሶች ይዘዋቸው 19 ቀን ማእከላዊ የታሰሩ መሆኑን ያውቃሉ በዛው በብርበራው ቀን እዛ ቤት ስለተገኙ? አዎ በእለቱ ሁለት ሰወች ነበሩ በእርግጥ አላውቀውም

⇒ እኮ ይዘው ሲሄዱስ አላዩም? በእውነቱ ምንድን ነው እነዚህ ሰወች ምንድን ናቸው ወይ የሚፈለጉ ይሆናሉ

⇒ ብለው ይዘዋቸው ሄዱ? ቆያ ልጨርስሎት የኔ ወንድም

⇒ እሺ ? በእለቱ እንዚህ ሰወች ምንድን ናቸው ሲባል እኔ እራሴም እንግዶች ሊሆኑ ይችላሉ ምናልባትም እንግዶች ሊሆኑ ይችላሉ እሱ በመታሰሩ ሊጠይቁ የመጡ ይሆናሉ የሚል የራሴን ነው እኔም እንደተናገርኩት ከዛ በኋላ መኪና ላይ ውጡ አሏቸው ወጡ

⇒ ይዘዋቸው ሄዱ? አንድ ቀን ይታሰሩ አስር ቀን ይታሰሩ

⇒ እርስዎ አያውቁም 19 ቀን መታሰራቸውን ግን ይዘዋቸው ሲሄዱ አይተዋል? አዎ በወቅቱ



2656

2007

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እነዚህን ሰወች ለመያዣ የሚሆን ትእዛዝ ግን አልያዙም ወይም የተነበበው ትእዛዝ ሰው ይያዝ? እኔ እንዚህ አይነት ነገር

⇒ የተከበረው ፍ/ቤት ያው ብቻ ከቤቱ እምነት ፖሊስ የብርበራ ትእዛዙንም ሆነ ሌላውንም ስራ ሲሰራ በሕጉ አግባብ ከፍ/ቤት ትእዛዝ አውጥቶ እየሰራ አይደለም የሚለውን ለማሳየት ነው ማንኛውንም ሰው ከቤት ጉትቶ ይዞ የሚሄድ ከሆነ

⇒ ቆዩ እና ስለ ሁለቱ ሰወች ጥብቅና አልቆሙም አደል ስለዚህ እሱን መጠየቅ አይችሉም ወደ ፍሬው ነገር ተመለሱና ጠይቁ

⇒ ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት አልጠይቅ እዚህ ዙሪያ ላይ ይሄ እንትን ላይ በሕጉ አግባብ አደለም ሰወች የተያዙት ወይም ብርበራው ሲከናወን የነበረው በሕጉ ግባብ አደለም የሚለውን ነው እየጠየቅኩ ያለሁት እሱን ልተው

⇒ አሁን ምንድን ነው በእሳቸው ላይ በሕገ ወጥ መንገድ ነው ብለው የሚያሲዙት ነገር ካለ በእሳቸው ዙሪያ አልተከለከሉም እዚህ የሌለ ሰው ግን በእነሱ ጊዜ የሚደርስ ጊዜ የእነሱ ጉዳይ ሲመጣ በዛ ጉዳይ ተጠይቆ ምላሽ ይሰጣል አሁን ጊዜ ማባከን ነው የሚሆነው ምንድን ነው የሚጠቅመው አጠቃለይ ፖሊስ እንደተቋም ሕገወጥ ስራ ነው የሚሰራው የሚለውን ነው እያወመለከቱን ያሉት ይሄ ደግሞ እስፔስፊክ ኬዝ ነው አጠቃላይ እንደፖሊስ አጠቃላይ ፖሊስ እንዲህ ነው የሚለው ነገር ለአንድ ሰው ይሆናል ወይ የሚለው ነገር እሱን ባለሙያ ናችሁ መመዘን ትችላላችሁ

⇒ የተከበረው ፍ/ቤት በአግባቡ ካልተረዳኝ እኔ እንደዛ አደለም እያልኩ ያለሁት ትእዛዝ ሰነዱ በሕጋዊ አግባብ አልተያዘም ሰው የሚያክል መብቱ እንዲከበር በሕገ መንግስት የተጠበቀ አካል ዝም ብሎ የሚያዝ ከሆነ ሰነድ በቀላሉ ነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ቆየ እስቲ አሁን ብዬን ተሰጥቶታል ለሁለቱ ሰወች ጠበቃ አደሉም መጠየቅ አይችሉም ያለው ኢቲክሰም እሱን አይፈቅድም ከተከሳሹጋ ተያይዞ የሚያነሱት ነገር ካለ ወደዛ ተመለሱና ጠይቁ ከዚህ በኋላ ያለውን /ግልጽ ያልሆነ/ እናስተናግድም

⇒ አቶ መለሰ የአቶ ጀማል ቤት ሲበረበር የነበረው ከአንድ ሰዓት ከምሽቱ አንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት መሆኑን ያውቃሉ? እኔ ይሄንን የመጨረሻውን ሰዓት ይበሉ እንጂ የመጀመሪያው ሰዓት አለመሆኑን ልገልጽሎት እፈልጋለሁ

⇒ ግልጽ ያድርጉት እስቲ? በምን አይነት አማርኛ ልግለፀው

⇒ አይ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ያሉት? የመጀመሪያ ማለት ቅድም ለፍ/ቤቱ ቃሌን ሰጥቻለሁ ሰዓቱንም አስመዝግቤያለሁ አሁን እንገና ያንን መልሰህ ተናገር የምትሉኝ ካልሆነ በስተቀረ የተጀመረበትን ሰዓት የወጣንበትን ሰዓት በትክክል አስቀምጫለሁ ስለዚህ አሁንም በተደጋጋሚ ያንኑ ጥያቄ የሚጠየቅ ከሆነ ልመልስ ነው

⇒ ይኸውሎት እንደተባለው ተደጋጋሚ ሲሆን እኛ እናስቆማለን ከዛ ውጪግን ፍ/ቤቱ እስካላቆሞት ድረስ 9 ጊዜ ቢጠየቁም ዘጠኙንም ጥያቄ ግልጽ ማድረግ የግድ ይላል

⇒ እሺ እቀበላለሁ

⇒ ስለዚህ እርስዎ መመለስ ብቻ ነው የሚያውቁትን

⇒ እሺ ሙሉ ቀንም ቢሆን ማለት ነው

⇒ አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄን አላውቅም ወይ ይሄ ነው ትክክል እንዲሉን ነው የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ባልደረባዬ ሲጠይቆት አንድ መርማሪ ፖሊስ ነው አብሮ የነበረው ብኋል ሦስት የታጠቁ ፖሊሶች አብረው ነበሩ  አደል? እኔ መጀመሪያም ለፍ/ቤቱም ገልጫለሁ የታጠቁ ሰወች መሬት ናቸው አጅበው ይዘው የመጡት ሌላ የታጠቀ ሰው ወደ ቤት ውስጥ ገብቶ እንደውም አዛዥም ውጪ ነው የቆሙት እኔ በበኩሌ ያየሁት ይሄንን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ነው ሦስት የታጠቁ ሰወች እቤት ውስጥ ገብተዋል የሚለው እኔ ከእውነት ውጪ ምንም ማድረግ አልችልም

⇒ እሺ አካባቢውን በደንብ ያውቁታል እርስዎ? አዎ አውቀዋለሁ

⇒ የአቶ ጀማል ቤት በተበረበረበት ወቅት ግቢው በፌደራል ፖሊሶች ቁጥጥር ስር ወይም ጥበቃ ስር ነበር አደል? በፍፁም አደለም

⇒ የዛን ሰሞን ብዙ የፌደራል ፖሊሶች ግቢ ውስጥ አልነበሩም ? በፍፁም የሉም ስለእውነት

⇒ ቅድም ሲያስረዱ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ የመጣው ከአዲስ ከተማ ፍ/ቤት ነው ብለዋል ከአዲስ ከተማ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ነው የመጣው የአዲስ አበባ ፍ/ቤት ማለቶ ነው ? አዎ የአዲስ አበባ

⇒ እርግጠኛ ኖት የአዲስ አበባ ፍ/ቤት ነው ? እኔ እኮ መጀመሪያ የአዲስ ከተማ

⇒ እርግጠኛ ከሆኑ እርግጠኛ ነኝ ይበሉ ? እርግጠኛ ነኝ

⇒ ቅድም አቃቤ ሕግ ሲጠይቆት አንዳንድ መፃሕፍ ፖሊሶች እንዳይዙ እኛ ይሄ እኮ ከፖለቲካ የሚገናኝ አይደለም ብለን አስጥለናል ብለዋል ሌላ ከፖለቲካ የሚገናኘው ነገር ምንድን ነው? እኔ ማለትም ማንኛውም ላይብረሪ ሼልፍ ውስጥ እንደዚህ አይነት መፃሕፎቶች የሉም

⇒ ልትጠይቁ የፈለጋችሁትን ነገር ጠይቁ እስቲ ምስክሩ ቅድም ሲመልሱ መርማሪው ይሆነኛል በለው የመረጡትን እኛም ፈርመንበታል የተወሰነ የተጠረዙ መፃሕፍት ግን ቤትም ይገኛሉ ብለን መልሰናል ነው ያሉት ግን በዚህ እስፔስፊክ ውስጥ

⇒ የተከበረው ፍ/ቤት እኔ እራሴ ያመጣሁት አለኝ እሳቸው ከተናገሩት ላይ መሰረት አርጌ ነው በእርግጥ በእንዳትጠይቅ የተባልኩትን እጠይቃለሁ መርቼ ቅድም ሲያስረዱ አሁን ከሚነሳው የመጅሊስ ጥያቄ ጋር የሚያያዝ አደለም አልናቸው ብለዋል አቶ ጀማል



http://ethcriminalawnetwork.com/

ከመጅሊስ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ምን ሲሰሩ እንደነበረ ያውቃሉ? እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለም

⇒ ከመጅሊስ ጥያቄ ጋር በተያያዘ ምንድን ነው የሚያውቁት ነገር ይሄንን ለፖሊሶቹ ሲሉ? እኔ ምንም በወቅቱ መጅሊስ ይመረጥ አይመረጥ በአገር ደረጃ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ አረብኛ ነበረ በዚህ የተነሳ መያዛቸውን ተረድተናል ስለዚህ መፃሕፍቱ ደግሞ በወቅቱ የነበሩት ኸሊዩም አላቸው ማለት ዋግ ቱ ስሪ ፎር የሚለው በአረብኛ የተፃፈ አለ ይሄን ማንኛውም ላይብረሪ ውስጥ በምንገባበት ሰዓት የምናያቸው ነው አውቃለሁ ስለዚህ ፖሊስ በወቅቱ እነዚህ ነገሮች ለመረጃ አይጠቅሙኝም በሚልበት ሰዓት አዎ ይሄ መፃሕፍት ነው ምን ጊዜም ሊነበብ የሚችል ነው ብለናል

⇒ እሺ ጥሩ መልሰውልኛል ቅድም ሲጀምር አቶ ጀማልን በደንብ አውቀዋለሁ እነደውም እሱ የጠራኝ መስሎኝ ነበር ወደ መጨረሻ አካባቢ ብለዋል እና በደንብ የሚያውቁት ከሆነ አቶ ጀማል በኑሮ አካባቢው ላይ ሰላማዊ ሰው ነው አደል?

⇒ መቃወሚያ አለን ማለት ስለ ባህሪያቸው በዋና ጥያቄ እኛ አላስመሰከርንም ስለ አቶ ጀማል ባህሪ ሰላማዊ አኗኗር በተመለከተ ማለት ነው የጠራናቸው ታዛቢ ነበሩ ታዛቢ ሆነው የተመለከቱትን እንዲመሰክሩ ነው ስለዚህ ይሄ መስቀለኛ ጥያቄ ሊሆን አይገባም ነው ዋሕና ጥያቄም አልተጠየቀም

⇒ እሺ ምላሽ

⇒ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ በዚህ ጉዳይ የሚያቁትን ቢጠይቁ አቃቤ ሕግን የሚጐዳው ጥያቄ አደለም እራሳቸው ከተናገሩት ላይ ነው እኛ ፈጥረን ሳይሆን አቶ ጀማልን በደንብ አውቀዋለሁ ብለዋል ስለዚህ የሚያውቁትን ነገር ነው የሚያስረዱት ለፍ/ቤቱ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ የሚያውቁትን ለፍ/ቤቱ እንዲናገሩ ቢፈቀድ የሚጐዳ ነጥብ ስለሌለው እንድንጠይቅ ይፈቀድልን



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

> ብያን ስጥተናል የቀረበው ጥያቄ ተከሳሹ ሰላማዊ ሰው መሆኑን ታውቃለህ ወይ የሚል ተነስቷል በዋና ጥያቄ አልተነሳም የሚል ተቃውሞ ቀርቦቧታል ጥያቄው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን አይተናል ተከሳሽ ሊመሰክሩ የመጡት ቀድም በዝርዝ ያስቀመጡት ስለ ብርበራ በተገኘ ጊዜ እና የብርበራ ማካሄድ ስነስርዓቱን ነው ተከሳሹንም አውቀዋለሁ ብለዋል ተከሳሽን ስለ ተከሳሽ ባህሪ ስለ ተከሳሽ ሰላማዊ ሰው ወይ ወንጀል የሚፈጽም ሰው የክርክሩ አካል አይደለም በዋና ጥያቄ አልተነሳም ስለዚህ ተከሳሹ ምን አይነት ሰው ነው በህሪው ሰላማዊ ነው የሚለው ነገር በዋና ጥያቄ ያልተነሳ ስለሆነ ጥያቄው ተገቢነት የለውም ተብሏል ሌላ ጥያቄ

⇒ እሺ አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ መለሰ

⇒ አቤት

⇒ አቶ ጀማል ቤቱ እንዲበረበር ምክንያት የሆነ የፈፀመውን ወንጀል አይተዋል ይኑር አይኑር የሚያውቁት ነገር የለም አደል? እኔ በበኩሌ ምንም የማውቀው ነገር የለም

⇒ እሺ አቶ ሙኒርን በተመለከተ የፊልም ባለሙያ መሆናቸውን ያውቃሉ ? ከዛ በኋላ እኔ ቲቪ አፍሪካ ላይ በማይበት ሰዓት ድራማዎችን ሲሰሩ አይቻለሁ ከዛ በፊት ግን እኔ በአካልም አይቻቸዋለሁ ሥራቸውም የት እንደሆነም አላውቅም በእውነት ለመናገር ከሆነ

⇒ ከዚህ በመነሳት ነው የሚያውቁት? አዎ በኋላ ላይ ነው

⇒ ቅድም ከአቶ ሙኒር ቤት በተገኙት ጽሁፎች ወይም እነዚህ በብርበራ ወቅት በተገኙት ቃለ ጉባዔ እንደያዛችሁ ገልፀዋል በጽሁፎቹ ላይስ በእያንዳንዱ ፈርማችኋል? ፈረመናል እሱም ፈርሟል እኛም ፈርመናል

⇒ እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ የለንም የተከበረው ችሎት

⇒ እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን



2012 264

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ የተከበረው ችሎት ከእሳቸው ጋር ተመሳሳይ ምስክር አለ

⇒ እሺ ይምጣ

⇒ ችሎቱ እንዲያሰናብታቸው ነው

⇒ አቃቤ ሕግ አስቀድመው ከተሰሙት ምስክሮች ጋር ተመሳሳይ ናቸው የተሰሙት ይበቁኛል ስላሉ ያው እናንተን በክብር አሰናብተናችኋል መሄድ ትችላላችሁ ችሎቱን የጠዋቱን በዚሁ አጠናቀናል 8 ሰዓት ላይ እንቀጥላለን ከሰዓት

⇒ እንደምን ዋላችሁ ያው የጠዋቱን ችሎት ከሰዓት እንቀጥላለን አቃቤ ሕግ እና ዳኞች ያው ጠዋት የነበሩት አልተቀየሩም ተተከሳሾች የቀረ የተጨመረ አለ ጠዋት የነበሩ በሙሉ አሉ እሺ የተጨመሩ ጠበቆች እስቲ ስማችሁን አስመዝግቡ

⇒ አዲስ መሃመድ እና ሃሰን ሁሴን

⇒ በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ

⇒ ለምስክርነት ነው የመጡት አደል ? አዎ

⇒ የአባቶን ስም ሳይጨምሩ የራሶን ስም ብቻ ይነግሩናል ? ሰቦቃ

⇒ እሼ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ እሺ 75ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝር 149 ላይ የተጠቀሱ አቶ ሰቦቃ ቀርበዋል እነማን ላይ ነው የሚመስክሩት አቶ ሰቦቃ? አቶ አሊ መኪ /የማይሰማ/

⇒ እንግዲህ ያን ለታ ነው ያየኋቸው ምናልባት ግር እንዳይለኝ ልያቸው

⇒ /የማይሰማ/ ቤታቸው ሲፈተሽ ነው ያየሁት

⇒ እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ

⇒ እሺ አቶ ሰቦቃ ቤታቸው ሲፈተሽ ነው ያየሁት ብለዋል መቼ ነው ? ሐምሌ 15 ቀን 2004

⇒ ስንት ሰዓት ላይ ነው ?ዘጠኝ ሰዓት ከ15 ደቂቃ ይሆናል

⇒ የት ነው ቦታው ? ኮልፌ ቀራንዮ ወረዳ 4



http://ethcriminalawnetwork.com/

> የቤት ቁጥሩን ያስታውሱታል ?

> የቤት ቁጥር ያን ጊዜ ጠይቀን ነበረ እኛም አዲስ ነው ነው ያልነው

⇒ እሺ ቤት ሲፈተሽ በታዛቢነት ነበርኩ ብለዋል ምን ምን ታዘቡ?

⇒ እሳቸው ታስረው መጡ ከዛ በኋላ ውስጥ ገባን ፍተሻ ተጀመረ እቤት ውስጥ ሲፈተሽ መጽሄቶች እና መፃሕፍቶች ነበሩ እነሱ ተሰበሰቡ የኮምፒውተር ሲስተም ነበር ካሴቶች ነበሩ

⇒ እስቲ በቁጥር በይዘት የሚያስታውሱት ካለ እንደዛ እያረጉ ይንገሩን ለምሳሌ በቁጥር የሚገለፁትን በቁጥር ?

⇒ የማስታውሰውን ያህል ነው መጽሃፍቶች 6 መጽሃፍቶች ነበሩ

⇒ በርእስ የሚያስታውሱት አለ?

⇒ ሁሉን ለማስታወስ አልችልም ግን ምርጥ የእስልምና ታሪክ የሚል አለ አህባሽ እና የአላህ ባህሪያት የሚል አለ የኢትዮጵያ ሙስሊም የት ነው የሚል አለ እና እነዚህ እነዚህን አስታውሳለሁ

⇒ በመጽሃፍ እነዚህን ያስታውሳሉ ? አዎ

⇒ ሌላስ ? ሌላ መጽሄቶች ነበሩ

⇒ በቁጥር ያስታውሳሉ በርእስ ?

⇒ አዎ መጽሄቶች አሉ በቁጥር ይሄን ያህል ባልልም እርእሳቸው አልፎ አልፎ የእስልምና ጉዳይ ምናምን የሚል አለ ንቁ የአላህ አምላክ ከእኛጋር ቅርብ ነው የሚል ነገር አለበት ድምፃችን ይሰማ የሚል አለ

⇒ ምንድን ነው ድምፃችን ይሰማ እና አሁን ንቁ አላህ ከእኛጋር ነው የሚለው ምንድን ነው መጽሄት ነው ምንድን ነው? አዎ በራሪ ወረቀቶችን እና መጽሄቶች ናቸው

⇒ ሌላስ? ሌላ ጋዜጦች አሉ ጋዜጦች ብዙ ናቸው አንድ ወደ 18 አካባቢ ይሆናሉ እነዚህ ነው ያየሁት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

> ሌላስ ከመጽሄት ከጋዜጣ እና ከመጽሃፍቶች ውጪ ?

> ከዛ ውጪ ያው አንድ ገጾራ ነበረ በቃ ይሄንን ነው ያየሁት

> እርስዎ እንዴት ተገኙ እዛ በቦታው? እኔ በአጋጣሚ እዛ አካባቢ እየሄድኩ ነበረ እና እነሱ ሲመጡ መኪና እያቋረጥኩ ስለነበረ እዚህ አካባቢ መሆኔን ፖሊሱ ጠየቀኝ ስነግራቸው እዚህ ሰወች ስለምንፈትሽ ታዛቢ ትሆናለን ከዛ ቤት ውስጥ የሚገኘውን ነገር ብቻ ትመለከትልናለና ና ብለው አሉኝ ከዛ አብረን ገባን

⇒ እናንተ የጠየቃችሁት ነገር የለም ፖሊስን ታዛቢ ሁኑ ሲላችሁ ?

⇒ ነበረ እኛ የጠየቅነው ምንድን ነው ለመፈተሽ ፍተሻ የፍ/ቤት ትእዛዝ ጠይቀን ነበር የፍ/ቤት ትእዛዝ ስንጠይቅ የፍ/ቤት ትእዛዝ የለም ነገር ግን አንድ የሆነ አንቀጽ እሱ የጠቀሰልን ነገር ነበር በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት 32 መሰረት ፖሊስም የመፈሽ ስልጣን ስላለው ይሄንን መሰረት አድርገን ነወ የምንፈትሸው ነው ያለኝ

⇒ እንደዛ ነው ያሉት? አዎ

⇒ ስንት ሰዓት ጨረሳችሁ ብርበራ ? 9:15 ነበረ የጀመርነው 10:55 ላይ ነው ያለቀው

⇒ የጨረሳችሁት ? አዎ

⇒ መጨሻ ላይ እነዚህን ቅድም የነገሩንን ንብረቶች ምን አደረጋችሁ?

⇒ አዎ ንብረቶቹ ከተሰበሰቡ በኂላ ቃለ ጉባዔ ተጽፏል እዛ ላይ እዛ ቃለ ጉባዔ ከተፃፈ በኂላ ዝርዝራቸው ንብረታቸው ዝርዝር ተጽፏል በንብረቱ ላይ አቶ አሊ ይሄ ከእርስዎ ቤት ስለመገኘቱ ቅሬታ አሉት ወይ እዚህ ላይ ፈርሙ ሲል እፈርማለሁ አሉ ፈረሙ እሳቸው ከፈረሙ በኂላ እኛም ፈረምን

⇒ ቃለ ጉባዔዉ ላይ ብቻ ነው የፈረማችሁት ሌላ ነገር ላይ ፈርማችኂል ? አቤት? ከቃለ ጉባዔ ውጪ ሌላ ቦታ የፈረማችሁት አለ? አዎ

⇒ ምን ላይ? የተገኙት መጽሄቶች እና ጋዜጦች ላይ መጽሃፍቶች ላይ ፈርመናል



2015

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ሌላ ነገር ላይስ? ሌላ የለም

⇒ መጽሄቶች እና ሰነዶች ላይ ነው የፈረማችሁት ? አዎ ሰነዶች ላይ ነው የፈረምነው

⇒ እሺ ስትገቡ እንዴት ነበረ የገባችሁት አገባባችሁ? አገባባችን ከውጪ ወደ ግቢ ስንገባ ቤተሰቦቻቸው ነበሩ

⇒ ቤተሰቦቻቸው ቤት ውስጥ ነበሩ? ነበሩ አዎ ግቢ ውስጥ ነበሩ ትንሽ የመደናገጥ ነገር ነበረባቸው ይታይባቸው ነበር ከዛ በኋላ ፖሊሱ አረጋጋቸው ምንምነገር ችግር የለበትም ምናምን ነገር አላቸው ከዛ እነሱም ተረጋጉ አንድ እህታቸው ነኝ የምትል ነበረች ታለትስ ነበረ ባለቤታቸው አሉ ባለቤታቸውም ምንም ነገር ድምጽ አላሰሙም አላለቀቁም ምንም አላሉም ከዛ ወደበር ስንገባ ፖሊሱ እና አቶ አሊ አብረው ገቡ እኛም ተከትለን ገባን ይሄ ነው

⇒ አሁን የገለጿቸው ንብረቶች የት ነው የተገኙት?ግማሾቹ ከዚህ ከቤት ውስጥ ነው

⇒ በክፍል ይንገሩን ? ተፈልገው ነው የተገኙት

⇒ በክፍል የት የት ክፍል ነው የተገኙት ወይ በቦታ ?ቦታቸው ግማሾቹ ከመጽሃፍትን ከእንትን ውስጥ ነው ከቁምሳጥን ውስጥ ነው የተገኙት ግማሾቹም ደግሞ ከሆነ ፍራሾች አካባቢ ነው የተገኙት

⇒ ከምን?

⇒ ፍራሾች ነበሩ በትርፍነት የተቀመጡ ከነሱ አካባቢ ተደርድረው የነበሩ

⇒ በስያሜ ምን የሚባል ክፍል ውስጥ ሪው በክፍል በስም ማለት የትኛው ክፍል በስም አለ አደል? በስም አዎ

⇒ የትኛው ክፍል የሚባል ላይ ነው የተገኙት?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አዎ ክፍሎቹ ሳሎን ክፍል ነው መኝታ ክፍል ነው መኝታ ክፍልም የተገኙ አሉ በብዛት መኝታ ክፍል የተገኙ ናቸው ሌሎቹ ደግሞ ጋዜጦች እና በራሪ ወረቀቶች የተገኙት ከሳሎን ነው

⇒ እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት

⇒ እሺ የተከሳሾች ጠበቃ መስቀለኛ ካለ

⇒ አቶ ሰቦቃ

⇒ አቤት

⇒ እርስዎ ከሚበረበረው ቤት ታዛቢ ሆነው ተጠይቀው ከእስረኛውጋር ስንት ፖሊሶች ነበሩ? አቤት?

⇒ ስንት ፖሊሶች ጋር ነው የገቡት ወደ ብርበራ የሚደረግበት ቤት? ፖሊሶቹ ሁለት ናቸው

⇒ ምን ይዘው ነበረ ?ምንም የያዙትነገር የለም

⇒ ቦርሳ ነገር ያንጠለጠሉት? የለም

⇒ በእጃቸው ምንም ነገር አልያዙም ነበር? በእጃቸው ላይ ያሉት የእሳቸው አጀንዳ የሆነች አጀንዳ ነገር ይዘዋል በተረፈ ሌላ ነገር የለም

⇒ አጀንዳ ብቻ ነው? አዎ

⇒ ሁለቱም ከዚህ ውጪ ሌላ ነገር አልያዙም? ምንም ነገር አልያዙም

⇒ ውስጥ ገብታችሁ አልተቀረፀም እንዴ ቪዲዮ? አልተቀረፀም

⇒ የተከሳሹ ቤት ሲደርሱ ቤቱ ግቢ አለው ነው ያሉት? ግቢ አለው አዎ

⇒ ማን አንኳኳ ፖሊስ ነው ያንኳኳው መርማሪዎች ?

⇒ የሆኑ ሰወች ነበሩ እና በር ላይ እሳቸው መኪና ውስጥ ነበሩ መኪና ቆሞ ሲወርዱ በር ላይ የነበሩ ሰወች ከፍተው ገቡ የራሳቸው ሰወች ናቸው

⇒ እኮ እናንተ ስትገቡ በሩ ተከፈተ ገባችሁ ከመርማሪዎች ጋር ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከዛ ወደቤት ስትገቡም ክፍት ሆኖ አገኛችሁት ወይስ መኖሪያ ቤት ስትገቡ?

⇒ ቤቱ ነበሩዋ ሰወች ስለነበሩ ክፍት ነው ቤቱ

⇒ እከ ምንድን ነው ዝም ብላችሁ መርማሪውም ተከሳሹም ተያያዛችሁ ገባችሁ? አዎ እኛ ከኋችን ገባን ከኋላቸው ነበርን እና ገባን እነሱ ገቡ እኛም ተከትለን ገባን

⇒ ፖሊሱ ቅድም ለእርስዎ የነገረውን የፍ/ቤት ትእዛዝ የለንም መበርበር እንችላለን ብሎ ነገረ እንዴ? እኛ ስለጠየቅነው ነዋ

⇒ እናንተ ታዛቢ እንድትሆኑ ?

⇒ እዚህ በታዛቢነት ለመገኘት እኛ ቤቱ ሲፈተሽ ለታዛቢነት ለመገኘት የመበርበሪያ ትእዛዝ ሊኖር ይገባል እና ያንን አንብልን የሚል ነገር ነበረ ጥያቄ ያነሳሁት እኔ ነኝ ያነሳሁት እንደውም በዛ ምክንያት ነው የነገረኝ

⇒ እንጂ ቤተሰብ አልጠየቀም ?

⇒ የነሱ ቤተሰብ አልጠየቀም ግቢ ውስጥ እንደገባን እዩ የሚል ጥያቄ ቅድሚያ አነሳሁ እነሱ ከመምጣታቸው በፊት

⇒ ማለት ይሄን ጥያቄ ሲያነሱ እርስዎ ታዛቢ እንዲሆኑ ሲጠየቁ ነው ይሄን ጥያቄ ያነሱት ከዛ ይሄ ከግቢ ውጪ ነው አደል እርዎ ታዛቢ እንደሆኑ የተጠየቁት ከግቢ ውጪ ነው ? ከግቢ ውስጥ ጠየቅኩኝ

⇒ ታዛቢ እንዲሆኑ መጀመሪያ ፖሊሲ ታዛቢ እንዲሆኑ የጠየቆት ከግቢ ውጪ ነው አደል?አዎ

⇒ ያኔ አልጠየቁትም እንዴ?አልጠየቅኩትም

⇒ ውስጥ ከገቡ በኋላ ነው ? ግቢ ውስጥ ሆኜ ነው የጠየቅኩት

⇒ ማን ነበረ እዛ ሲጠይቆት በአጠገቦ?አቤት? ይሄንን ታዛቢ እንዲሆኑ ሲጠይቁ ማን ነበረ ? ሌላ ሰው ? እ ከፖሊሶች ውጪ ? አንድ ልጅ ነበረ ከእኛጋር

⇒ ሌላ ታዛቢ ነው እሱ? አዎ ታዛቢ ነበረ



2018 266

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በዚህን ሰዓት ቤተሰቦቹ የትጋ ነበሩ?

⇒ የማን ቤተሰብ የተከሳሽ ?

⇒ የተከሳሽ? የተከሳሽ ቤት ግቡ ውስጥ ነበሩ አንድ ሌላ ወንድሜ ነው ብለው እሳቸው ለፖሊስ ያስተዋወቁት ልጅ ነበረ እቃዎቹም ከየቦታ አንስቶ ያቀበል የነበረ ሲፈተሽ እሱ በር ላይ ቆሞ ነበረ

⇒ ኦኬ ይሄ ታዛቢዎቹ ከፖሊሶችጋር ተነጋገራችሁ እና መፈተሽ እንደሚችሉ ከተነጋገራችሁ በኋላ ነው ወደ ብርበራ የሄዳችሁት? አዎ

⇒ በዚህን ሰዓት እናንተ ስትነጋገሩ የተከሳሽ የሚስት ያሉት እህት ያሉት ነበሩ እህት ያሉት ነበሩ ይሰሟችሁ ነበረ እንዴ እናንተን ? ይሰሙ ነበር

⇒ ቅድም ቤት ውስጥ ነበሩ እኮ በለውናል ? ግቢ ውስጥ ነበሩ ነው ያልኩት

⇒ ሴቶቹም ግቢ ውስጥ ነበሩ?

⇒ አዎ በረንዳ ነበረው ቤቱ እንዲህ ወረድ ብሎ በረንዳው ስር አብሮ ቆመው ነበር እነሱ

⇒ ቅድም አንድ ገጀራ አግኝተናል ብለዋል ? አዎ

⇒ የትጋ ነው ያገኛችሁት ይሄን ?

⇒ አንድ ምንጣፍ ስር ነው አንድ ምንጣፍ ብድግ ተደርጎ ምንጣፍ ስር ሲፈተሽ ከምንጣፍ ስር ነው የተገኘው

⇒ ሌላ ተቆፍሮ የወጣ ነገር አለ እንዴ? የለም

⇒ ካጣሪያ የወጣ ነገር የለም? የለም

⇒ ቅድም አቃቤ ሕግ ሲጠይቆት እነዚህ ተገኙ ያላቸው ወረቀቶች እያንዳንዱ ላይ ነው የፈረማችሁት እያንዳንዱ ወረቀት ላይ ገጽ በገጽ ?

⇒ አይደለም በመጀመሪያው ገጽ ላይ ነው የፈረምነው

⇒ የመጀመሪያ ገጽ ላይ ፈረማችሁ? አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከዛ በኋላ ብዛት እየቆጠራችሁ ቃለ ጉባኤ ላይነው ? አዎ

⇒ ይሄን ያህል ተገኘ እያለ? አዎ

⇒ ስንት ሰዓት ተጠናቀቀ ብርበራው 9:15 አካባቢ ጀመራችሁ?

⇒ 10 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ተጀመረ ማነው 9 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ተጀመረ አስር ሰዓት ከሃምሳ አምስት አለቀ

⇒ ቅድም የኮምፒውተር ሲስተም ሲሉ ነበረ ምን ማለት ነው?

⇒ የኮምፒውተር ሲስተም ያው እርስዎም እንደሚያውቁት ነው ኮምፒውተር ሲስተም

⇒ ኮምፒውተር ማለቶ ነው? ሲስተሙ ነው

⇒ እኮ እሱን ግልጽ ያርጉት ሲስተም ማለት የኮምፒውተር ሲስተም ውስጡ ብዙ ነው ? የኮምፒውተር ሲስተም

⇒ ሃርድ ዌሩ ነው ወይስ ውስጡነው? አቤት? ኮምፒውተር አለ እሚታየው አለ በአይን የሚታየው? እሱ አደለም ኮምፒውተሩ አደለም የኮምፒውተር ሲስተሙ መቀበያው ነው

⇒ ተገነጣጥሎ ማለት ነው?

⇒ አልተገነጣጠለም ክፍት ነበረ ዝግ ነው

⇒ ሲፒዩ ለማለት ነው? እንደዛ ነው እኔ

⇒ እሺ እሱን ቀጥሉ እሺ

⇒ አቶ ሰቦቃ ቅድም በአቃቤ ሕግ ሲጠየቁ የፍ/ቤት ትእዛዝ አላየንም ብለዋል ከዛ በኋላ ፖሊስ የፍ/ቤት ትእዛዝ አያስፈልግም ብሎ በወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ ቁጥር 32 መሰረት የምንፈትሸው ነው ያለኝ ብለዋል ልክ ነኝ? አዎ

⇒ ከዚህ ውጪ ሌላ ያዩት ሰነድ አለ ፖሊስ ያሳዮት? የለም

⇒ በአዛዥ የተፈረመ ነገር ያዩት የለም ? አላየሁም



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በዚህ ፖሊሱ በነገሮት መሰረት ከአቶ አለ. መኪ. ቤት ምን ምንድን ነው የምንፈልገው ያሉት ወይም ፖሊስ ይፈልጋል ያሉት ነገር አለ ?

⇒ እነሱ ከአቶ  አለ. መኪ. ቤት ይሄን ይሄን እንፈልጋለን ብለው በአይነት የተናገሩት ነገር የለም

⇒ የነገሮት ነገር የለም ምን እንደሚለን አሉት ታዲያ ?

⇒ ለእኛ የነገሩት አሁን እሳቸው ከቤታቸው የምንፈልገው ነገር ካለ እምናነሳውን ነገሮች ብቻ በትክክል ያያችሁትን ብቻ /ግልጽ ያልሆነ/ ትመለከታላችሁ

⇒ እሺ. ቅድም የዘረዘሯቸው ጋዜጦች መጽሄቶች አሉ እነዚህ ነገሮች በሕግ የተከለከሉ መሆን አለመሆናቸው ያውቃሉ እርስዎ ?

⇒ እኔ አላውቅም ይዘታቸውን ውስጣቸውን አላነበብኩም

⇒ ቅድም ሲጠየቁ አሁንም በአቃቤ ሕግ አለ. መኪ. ፈርሞባቸዋል በቃለ ጉባዔዉ ላይ ብለው ነበረ ምን ብሎ ነው የፈረመው አለ. መኪ.?

⇒  የተገኘው ንብረት ላይ ንብረቱ ከእሳቸው ቤት የተገኘ ስለመሆኑ ነው የፈረሙት

⇒ ቤቱ ስለመገኘቱ ብሎ ነው የፈረመው እንጂ እንደዚህ ነው የፈረመው አደል?

⇒ የተገኘው ንብረት ተቆጠረ ፊት ለፊታቸው ታየ እይቆሙ ነው እሳቸው ባሉበት ነው እቃው ወጣ ከእቤታቸው

⇒ እኔ ቤት የተገኘ ነው ፖሊስ ፈርም ሲለው እኔ ቤት የተገኘ ስለሆነ ብሎ ነው የፈረመው አደለም? አዎ

⇒ እንጂ. የኔ ነው አላለም ? አላለም

⇒ እሺ. መጀመሪያ አቶ ስቦቃ መጀመሪያ ወደነ አለ. ቤት ስትሄዱ ፖሊሶቹ ከየት አንስተው ነው የወሰዷችሁ እናንተን ? ማንን? የት ነው የተገናኛችሁት ከእናንተ ጋ? እኔ እዛ አካባቢ



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

እየሄድኩ ነበረ እነሱ በመኪና መጡ ድንገት ተገናኘን መኪናቸውን አቁመው እዚህ አካባቢ መሆኑን ጠየቁኝ ከዛ ይሄንን ጠየቁኝ

⇒ እሺ ከዛ ሄዱ ማለት ነው? አዎ

⇒ አሊ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እጁ ላይ ካቴና ነበረ ?

⇒ እሳቸው ግቢ ቤት ውስጥከገቡ በኋላ ፍተሻ ይካሄድ ነበረ ፍተሻ ከተካሄደ በኋላ ልስገድ ፍቱልኝ አሉ ፈቷቸው ሰገዱ የዛን ጊዜ ተፈቶላቸዋል

⇒ አሃ ሊሰግዱ ሲሉ ነው የፈቱላቸው ? አዎ

⇒ ስልክ እንዳታነሱ እያሉ ፖሊሶቹ ሲከለክሉ ነበር አደል? እኔ አላየሁም

⇒ ጐረቤትስ ወደ ግቢ ሲገቡ ሲሉ ሲከለክሉ አልነበረም?/ግልጽ ያልሆነ/ አረብኛ የለም ግርግር የለም ያነሱት ምንም ነገር የለም

⇒ ቤት ውስጥ ስትገቡ ስንት ሆናችሁ ነው የገባችሁት? አቶ አሊ አለ እኔ አለሁ ሌላ ታዛቢ አለ ሁለት ፖሊሶች አሉ የአቶ አሊ ባለቤት አሉ ሴትየዋ አሉ ወንድማቸው አሉ

⇒ ሌላ ሰው አልገባም ሌላ መሣሪያ የያዙ ፖሊሶች አልገቡም ውስጥ?

⇒ አልገቡም ውጪ ነበሩ

⇒ በር ላይ ነው የነበሩት እነሱ? አዎ

⇒ እሺ አቶ ሰቦቃ ወደነ አቶ አሊ ጊቢ ስትገቡ የታጨደ ሳር ነበር አደል ? አቤት? የታጨደ ሳር መኖሩን አስተውለዋል ያስታውሳሉ? አላስታውስም

⇒ አቶ አሊ ፖሊስ ወይ መርማሪውን ጠይቆት ገጀራው ሰራተኛዋ ሳሩን ለማጨድ ቁጥቋጦዎችን ለማስወገድ እምትጠቀምበት እንደሆነ የተናገረውንስ የሰሙትን ያስታውሳሉ ጠይቆት ሲያስረዳው ማለት ነው አቶ አሊ? አቶ አሊ አላስረዱም ገጀራው ከተነሳ በኋላ ባለቤታቸው አንድ የተናገሩት ነገር ነበር እራሳችንን መጠበቂያ ነው እዚህ የምንቀመጥነው ብለው ከፍራሹ ውስጥ ሲወጣ ይሄን ቃል ተናግረዋል



2022 2668

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አቶ አሊ ይሄንን አልተናገረም አደል? አልተናገረም

⇒ እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እሺ አቃቢ ሕግ ድጋሚ ካለ?

⇒ እሺ አንድ ጥያቄ አለኝ አቶ ስቦቃ ንብረቶቹ ላይ የኔ ማለት የተያዙት ሰነዶች ላይ ከኔ የተገኙ ብለው ፈርመዋል አደል? አዎ

⇒ እነዚህ ሌላ ሰው አስቀምጧቸዋል የኔ አደሉም ብለው የተናገረረት ነገር አለ ለእናንተም ወይ ለፖሊሶቹ ለመርማሪዎቹ የኔ አደሉም ሌላ ሰው ያስቀመጣቸው ናቸው የሌላ ሰው ነው በለው ተናግረዋል የተያዙትን ጋዜጦች ሰነዶች ሲዲዎች ቅድም ሲስተም ያሏቸውን ?

⇒ አዎ በተነሱት ነገሮች ላይ አቶ አሊ ማንኛውንም ነገር ላይ ያነሱት ጥያቄም ወይም ተቃውሞ የለም

⇒ የኔ አደለም አላሉም ? አላሉም

⇒ እሺ ጨርሰናል ድጋሚ ጥያቄ የተከበረው ችሎት

⇒ እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን

⇒ እሺ ምንድን ነው የሚሉት ?

⇒ በተራ ቁጥር 148 ላይ የተገለፁት አቶ ወንድምአገኝ የተባሉት ምስክር በእሳቸው /ግልጽ ያልሆነ/ በተራ ቁጥር 149 ላይ ያሉት ከመሰከሩት የተለየ ስላልሆነ ምክርነታቸውን ስለማንፈልገው ችሎቱ እንዲያሰናብት ነው የምንጠይቀው

⇒ እሺ አቶ ወንድም አገኝ ያው የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አክብረው ፍትህ ለማገዝ ስለመጡ እናመሰግናለን አስቀድመው ከመሰከሩት ጋር ተመሳሳይ ነው ስለተባለ እርስዎን እንደዚሁ ሸኝተናል መሄድ ይችላሉ

> በእውነት ለመመስከር በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ

→ የአባቶን ስም ሳይጨምሩ የመጀመሪያ ስሞን ብቻ ይነግሩናል



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ስንተኛ ናቸው አቃ ሕግ?

⇒ የአቃቤ ሕግ ምስክር በማስረጃ ዝርዝሬ 190 ላይ የተጠቀሱ አቶ ኤፍሬም ቀርበዋል አቶ ኤፍሬም ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?

⇒ ሼህ ሱልጣን ፣ ሃጂ አማን

⇒ እሺ አንድ ሰው ላይ ብቻ ነው ? አዎ

⇒ ሼህ ሱልጣንን ለይተው ማሳየት ይችላሉ አሁን ያውቁታል? አዎ

⇒ እሺ ያሳዩንተነስተውም ማሳየት ይችላሉ /የማይሰማ/

⇒ የለኝም እኔ በአጋጣሚ ያው ከዚሁ /ግልጽ ያልሆነ/ ወይም ደርሞ ከሞላ ማሩ ወደ ልደታ በሚያስወርደው መንገድ ላይ እየተጓዝኩ የድሮ ፈረሰኛ የአሁን ደግሞ ፌደራል ካምፕ ማለትም ያው የመኪና ብርበራ ላይ እንድታዘብ ነው

⇒ እሺ አቶ ኤፍሬም አሁን በችሎት የለዩዋቸውን ምስክር የማውቀው መኪናቸው ሲበረበር ነው ብለዋል መቼ ነው ቀኑ?

⇒ ቀኑ ክረምትላይ ነው ቀኑ ወደ ሐምሌ 16 ላይ ነው

⇒ አመተምረቱስ? 2004 11ኛ ወር

⇒ ሰዓቱስ ? ሰዓቱ ግምቱ ከዘጠኝ ሰዓት ተኩል እስከ አስር ሰዓት አካባቢ ነው

⇒ ቦታው የት ነው ?

⇒ ቦታው ወደ አብነት አካባቢ ነው

⇒ መኪናቸው ብለዋል መኪናቸው ምንድን ነው ሲደረግ እርስዎ የተገኙት እዛ?

⇒ መኪናቸው የቤት ነው ኤክስኪዩቲቭ ነች መኪናው እዛ መኪና ውስጥ የነበሩ እቃዎች ነበሩ ያው እሱን እንድታዘብ ነው የተገኙ እቃዎች ነበሩ

⇒ እሺ ማለት በምን ጉዳይ ተጠርጥረው ነው አሁን መኪናቸው እንዲበረበር ከሆነ ታዛቢ የተነገሮት ምን አድርገዋል ተብሎ ነው እርስዎ የተነገሮት ?



2024 2074

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ማለትም እኔ ያው በዛ ወቅት የፍ/ቤት ማዘዣ እንደያዙ ጠይቂያቸው ነበር ግን ያው ፖሊስ ያለ ፍ/ቤት ማዘዣ በአንቀጽ 32/2 መሰረት ያው መበርበር እንደሚችል ገልፀውልኝ ያው ያንን እንድመለከት በጋበዙኝ መሰረት እኔም ለማየት ችያለሁ

⇒ እሺ በዚህ መሰረት እንበረብራለን አሉት ? አዎ

⇒ ግን የአንድ ሰው ግለሰብ ማለት መኪና ዝም ብሎ አይበረበርም ምን አድርገዋል ተብሎ ነው መኪናቸው የተበረበረው ?

⇒ ያው በወቅቱ ያው የተነሱ ነገሮች ነበሩ እኔ እዛው መርካቶ ኤርያ ላይ ነኝ በወቅቱ ያው ግርግሮች ተፈጥረው ነበረ በዛ አካባቢ ላይ ያው ወቅታዊ ጉዳይ ስለነበረ ያንን እንድመለከትም በታዛቢነትም ስለተጋበዝኩ ያንን እንትን ለማለት ነው ወደዛ ቦታ ላይም የሄድኩት

⇒ እሺ ማለት አጠር ተደርጎ በፖሊስ የተነገሮት የለም በዚህ ምክንያት ነው ?

⇒ ማለትም በዚህ በአክራሪነት ዙሪያ ላይነው የተጠሩት ይሄንን እንዲመለከቱልን ብሎ ስላለኝ ነው እኔም ፍቃደኛ ሆኜ ወደዛ ግቢ የገባሁት ?

⇒ ፈቃኛ ሆኜ ወደዛ ወደ ፌደራል ካምፕ ግቢ ውስጥ የገባሁትም ለዛ ነው እንድታዘብ በዚህ በተጠቀስኩት አንቀጽ መሰረት መበርበር እንችላለን ሲሉኝ የፍ/ቤት ማዘዣ ይዛችኋል ወይ ብዬ ስላቸው ያንን

⇒ ኦኬ እሱን ነግረውናል አሁን ቦታው የት ነው መኪናዋ የት ነው የተበረበረችው?

⇒ እዛው ፌደራል ካምፕ ውስጥ ነው

⇒ ፌደራል ካምፕ ግቢ ውስጥ? አዎ

⇒ ማን ነው ማለት እዛ እንዴት ተገኘች ፌደራል ካምፕ ግቢ ውስጥ እንዴት ተገኘች ተባለ? ያው በክትትል ነው የያዝነው ነው ያሉት

⇒ ምን ምን ተገኘ? ላፕቶፕ ቶሺባ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከዛ በፊት ይቅርታ ታርጋ ቁጥሩን ያስታውሱታል?

⇒ ታርጋ ቁጥሩን አላስታውሰም የቤት አሆኗን አውቃለሁ /ግልጽ ያልሆነ/ ለይቻታለሁ ያው ሲልቨር ከለር ነች

⇒ ምን ምንድን ነው የተያዘው ?

⇒ የተያዘው ላፕቶፕ ቶሽባ ሲዲ ካሴት አንድ በርካታ የሞባይል ቀፎዎች ናቸው ቁጥራቸውን አላስታውሰውም ግን ብዛት አላቸው በርካታ ናቸው ሌላ ድምፃችን ይሰማ የሚል 24ኛ እና 25ኛ እትም በብሮሽር ወረቀት ነው ድምፃችን ይሰማ የሚል አለው በሃይት መልክ አስፍረውታል ከዛ በኋላ ደግሞ ያው የተገኙት የተለያየ መንግስት መስሪያቤትን የሙስሊሙን ጥያቄ መልእክት የሚል የተለያየ መስሪያቤት የጠየቁበት ደብዳቤ ነው ወደ 12 ገጽ ከዛ በኋላ ደግሞ ያው የተመለከትኩት

⇒ እሺ አሁን ካሏቸው ?

⇒ እ ወልቂጤ ከተማ ላይ የሚል የተለያየ ስም ዝርዝር የያዘ ወረቀት ተመልክቻለሁ በዛ ላይም ሼህ ሱልጣን የምትሉትን ነገር ምንም ነገር ሳይጨመርብኝ ይሄንን የምታዩትን ብቻ መስክሩልኝ ሲሉ እላቸውም እኛም የምናየውን ነው ከዚህ ውጪ ያላየሁትን እኔም እንደማልመሰክር ገልጨላቸው ከዛው ወጥቻለሁ ወደ አስራአንድ ሰዓት ተኩል ይሆናል ከዛ ግቢ ወጥቻለሁ

⇒ እነዚህን ንብረቶች መኪናዋን ስትበረብሩ ማን ማን ነበራችሁ? የሚያጣሩ መርማሪዎች ነበሩ

⇒ ከነሱ ውሥ ማን ማን ነበር? ሌላ ከኔጋር የቀረቡት እንትን ነበሩ ምስክር ተብሎ

⇒ ስንት ታዛቢ ነበራችሁ በቁጥር? ሁለት ነን

⇒ እሺ መጨረሻ ላይ ንብረቶቹን ወዴት ወሰዳችሁ ወይም ወዴት ተወሰዱ አሁን የገለጿቸው ንብረቶችን አሁን የገለጿቸውን ንብረቶች ምን አደረጋችሁ እዛው ጥላችሁ ሄዳችሁ ምን አደረጋችሁ መጨረሻ ላይ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እኛም ወረቀቶቹ ላይ ፈርመናል

⇒ ምን ብላችሁ ፈረማችሁ?

⇒ ያው ያየነውን ያየን መሆኑን እዛ ላይ ፈርሜበታለሁ ወረቀቶቹ ላይ

⇒ ማን ማንን ነው የፈረማችሁት? እኔ አቶ ጉታ እና ሼህ ሱልጣን

⇒ ምን ብለው ፈረሙ እሳቸው? በቃ የተገኙብኝ ብለው እንትን አሉ

⇒ ከየት የተገኘ ? ከዛ ከመኪና ውስጥ የተገኘ

⇒ ከዛ ውጪ እነዚህ ንብረቶች የኔ አደሉም ወይም ደግሞ ሌላ ነገር የተባለ ነገር አለ? የለም

⇒ እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት

⇒ ጥያቄ ካለ

⇒ አቶ ኤፍሬም

⇒ አቤት

⇒ እርስዎ ለተዛቢነት ተጠርተው ቅድም ወዳሉት ወደ ፌደራል ፖሊስ ወደ ካምፕ ሲገቡ እንማለት ሼህ ሱልጣን እዛው ከነመኪናቸው ግቢ ውስጥ ነበሩ አደል? አዎ

⇒ እነሱ ግቢ ዉስጥ ገብተው ከዛ በኋላ ነው የተጠራችሁት? እኔ በዛ ሳልፍ ነው የገባሁት እንጂ ተጠርቼ አደለም በታዛቢነት እንድታዘብ ጋበዙኝ ወደዛ ግቢ ገባሁ

⇒ ልክ ወደዛ ግቢ ሲገቡ ተከሳሹን ሼህ ሱልጣንን አገኟቸው መኪና ውስጥ ነበሩ?

⇒ እሳቸው አልነበሩም

⇒ እሺ እርስዎ ሲገቡ መኪናው ማንም በውስጡ ሰው አልነበረም?

⇒ መኪናው በውስጡ ሰው አልነበረም ያው እሳቸው ግቢ ውስጥ ነበሩ ከዛ በኋላ ያው ወደ መኪናው አምርተን መኪና ውስጥ የተገኙትን እቃዎች ቅድም በዝርዝር የገለጽኳቸውን የራሳቸው መሆኑን መኪናውም የራሳቸው መሆኑን ገልፀዋል



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ኤፍሬም ቅድመ ሲመሰክሩ የፍ/ቤት ትእዛዝም እርስዎ ሲጠይቁ ፖሊስ የለም ብለውታል እንደገናም ደግሞ የፖሊስ ሲጠየቁ ያው ምን ነበረ አለኝ ያሉት ?

⇒ እሱ ግልጽ እኮ ነው አሁን ከሱ ተነስቶችሁ የፍ/ቤት ትእዛዝ የለም

⇒ ትእዛዝ አለ ፊርማ ያለበት ቤት ይበርበር የሚል አይተዋል እርስዎ አላዩም አይደል?

⇒ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ 32 የሚያሳየውን ማህተም ያለው ወረቀትም አሳይተውኛል በዚህ መሰረት እንደሚበረብሩ ማለት ነው

⇒ ኦኬ ምን ምን የሚል ነበረ ብርበራው ምን ይፈተሽ የሚል ነበረ ?

⇒ ማለትም ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ከዚህ ከወቅቱ ጋር የሚያገናኛቸውን ሰነዶች ያው መበርበር እንደሚገልጽ የሚያሳይ ጽሁፍ ነው

⇒ የምን ብርበራ ነው የሚለው የመኪና ነው የሰው ነው የቤት ነው እርስዎ ያዩት?

⇒ እኔ ያየሁት የመኪና ብርበራ ነው

⇒ ቅድም በወቅቱ ግርግር ነበረ ከአክራሪነት ጋር የተያያዘ ብለዋል ምንድን ነው አክራሪነት?

⇒ እኔ ያው ማለትም የራስን የሆነ ሃሳብን ሌላ ላይ መጫን ነው አክራሪነትን የማውቀው የራስን የሆነ እንትን ወደ ሌላ ሰው መጫን ወይም ደግሞ የኔን ተቀበሉልኝ ብሎ ሰውን ማስገደድ ነው እኔ እንደማውቀው አክራሪነት ማለት ነው

⇒ ያስገደደ ሰው አይተዋል እርስዎ?

⇒ እኔ አላየሁም

⇒ ቅድም መኪናዋ ስትያዝ አይተዋል እርስዎ?

⇒ መኪናዋ ስትያዝ አላየሁም

⇒ እነዚህ መኪና ውስጥ ተያዙ የሚሉት እቃዎች ላፕቶፕ ሲዲ እና ሌሎች ሰነዶች ያሉዋቸው በሕግ የተከለከሉ እቃዎች ናቸው ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እኔ በወቅቱ መኪና ሲበረበር ያየሁት እቃ ነው ብሎ ነው የመሰከርኩት አሁንም የምመሰክረው ያንን ነው

⇒ አዎ በሕግ ስለመከልከል አለመከልከላቸው የሚያውቁት ነገር የለም?

⇒ የለም

⇒ አቶ ኤፍሬም አንድ ጥያቄ ብቻ ነው የምጠይቆት በወቅቱ ግርግር ተፈጥሮ ነበረ ብለዋል እርስዎ ሲታዘቡ ሲገቡ ፌደራል ፖሊስ ግቢ ውስጥ ሌላ የሚፈተሽ መኪና ነበር ከእሳቸው ውጪ?

⇒ የለም

⇒ እሺ አቶ ኤፍሬም ሞባይሎቹ ሲያዙ እነዚህ ሞባይሎች ከኔጋር አብረው የነበሩ ሰወች ሞባይሎች ናቸው እንጂ የኔ አይደለም እያሉ ሲናገሩ ነበር ሼህ ሱልጣን?

⇒ አዎ

⇒ አልሰማህም እንደዚህ ሲሉ?

⇒ እኔ አልሰማሁም

⇒ አምስቱም የኔ ናቸው ብለው ነው የፈረሙት?

⇒ የኔ ናቸውም ያሉት ሞባይል ነበረ ሲፈርሙ ግን ቁጥሩን የኔ ነው የኔ አይደለም

⇒ እኮ አንድ ነው የኔ ነው ያሉት ወይስ ሌሎቹ ከኔጋ አብረው የተያዙ ሰወች ሞባይል ነው የኔ አደለም እያሉ ሲያስረዱ ነበረ አደለ?

⇒ እንደዛ ይሉ ነበር ግን ይሄ ሞባይል የኔ ነው ብለው የለዩዋቸው ሞባይሎች ነበሩ

⇒ እኮስንት ሞባይል ነው የኔ ነው ብሎ የለየው?

⇒ እኔ እንኳ ቁጥሩን አላውቀውም

⇒ ላፕቶፑም የኔ አደለም እያሉ ነበር አደል?

⇒ ያው የራሳቸው መሆኑን እየገለፁ ነው እንትን ያሉት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ይቅርታ አንድ ጥያቄ አለኝ አቶ ኤፍሬም ቅድም ሲያዙ ወይም ሃጂ ሱልጣን መኪና ውስጥ ከያዛችሁት ነገር ውስጥ አንዱ ላፕቶፕ ሲዲ በርካታ ወረቀቶች እና ድምፃችን ይሰማ ብሎ እንደገና የሙስሊሞች ጥያቄ ወደ 12 መስሪያቤት የተጠየቀበት አይቻለሁ ብለው ነበር እስቲ የቱን የቱን መስሪያቤት ያስታውሳሉ ከተጠየቀበት ውስጥ?

⇒ ወቅቱም እኮ አረጅም ጊዜ ነው

⇒ አይ ከአስራሁለት በሚያስታውሱት ግድ የለም አስራሁለቱንም ባይሆን የተወሰነውን ለየትኛው ለየትኛው መስሪያቤት እንደተጠየቀ የሚያስታውሱትን ?

⇒ እኔ የማስታውሰው ነገር የለም

⇒ በአስራሁለት /ግልጽ ያልሆነ/ አይተዋል ግን?

⇒ አዎ

⇒ የመንግስት መስሪያቤት ነው?

⇒ የመንግስት መስሪያቤት ነው

⇒ ላስታውሶት እኔ ምናልባት አያስታውሱትም?

⇒ እኔ አላስታውሰውም

⇒ እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እሺ ድጋሚ ካለ አቃቤ ሕግ

⇒ አሁን መጨረሻ ላይ ከተጠየቁት ጥያቄ ለ12 የመንግስት መስሪያቤት ነው ወይስ የገጽ ብዛት ነው አስራሁለት ያሉት?

⇒ 12 ገጽ ብዛት ነው

⇒ እንጂ የመንግስት መስሪያቤት አደለም?

⇒ የመንግስት መስሪያቤት አደለም 12 ገጽ ብዛት ነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ ሌላው የፖሊስ ትእዛዝ ይኑር ማለት የፖሊስ አዛዡ የሰጠው ትእዛዝ ይኑር አይኑር የሚያውቁት ነገር አለ አሁን ፖሊሱ የመበርበሪያ ትእዛዝ የለንም በዚህ መሰረት ነው የምንበረብረው ብሎ ነግሮናል ብላችኋል ፖሊሱ የተሰጠው ትእዛዝ በቢሮ የተሰጠው ትእዛዝ ይኑር አይኑር የሚያውቁት ነገር አለ?

⇒ የለም

⇒ እሺ ሲገልፁ በዋና ጥያቄ ስጠይቆት እነዚህ ንብረቶች ከመኪናዬ የተገኙ ናቸው ከዚህ ውጪ ያያችሁትን ብቻ መስክሩልኝ ብሏል ብለው ነግረውናል በዋና ጥያቄ ?

⇒ አዎ

⇒ ሞባይሎቹን በተመለከተ የኔ ሞባይል አደሉም ያሉት ነገር አለ ይሄ ላፕቶፕ የኔ አደለም ይሄ ንብረት የኔ አደለም ብለው ቅድም ጠይቄዎታለሁ ይሄ ንብረት አለ ይሄ ንብረት የኔ ነው አደለም የሚል ጥያቄ ነበረ ወይ?

⇒ መኪናውም ያው የራሳቸው እንደሆነ እና እቃዎቹም የራሳቸው እንደሆኑ የገለፁበት ሁኔታ አለ ከዚህ ውስጥ ግን ሞባይሉን ብቻ ቅድም ከዛ አቅጣጫ በተጠየቅኩት መሰረት

⇒ ስንት ሞባይል ነው የያዛችሁት የሚያስታውሱት?

⇒ በርካታ ነው ወደ አስራ ምናንም ነው

⇒ ከዛ ውስጥ ምን ያህሉን ነው የኔ አደለም ያሉት?

⇒ እኔ እንጃ ቁጥሩን አላስታውሰውም

⇒ ለይተው ?

⇒ የኔ ነው የኔ አደለም የሚለውን ጊዜውም በጣም እረጅም ስለሆነ ይረሳል በወረቀትም የያዝኩት ነገር የለም በአምሮዬ ነው የያዝኩት

⇒ የኔ ነው የተባሉት ናቸው የተመዘገቡት በርባን ላይ?

⇒ እ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በርባን ላይ የኔ ናቸው የተባሉትን ብቻ ነው ለይታችሁ የያዛችሁት ወይስ ሁሉንም ነው የያዛችሁት?

> ሁሉም ነው የተያዘው የፊረምንበትም ሁሉም የተመዘገበበት ላይ ነው

⇒ ከመኪናዩ ተገኘ ብለው?

⇒ ከመኪና የተገኘው ላይ ሁሉም ላይ ፈርመናል

⇒ እሺ ድጋሚ ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት

⇒ በእውነት ለመመስከር

⇒ በእግዚአብሔር ስም

⇒ ምያለሁ

⇒ እሺ ለምስክርነት ነው የመጡት

⇒ አዎ

⇒ የአባቶን ስም እና ሌላ ዝርዝር ሳይጠቅሱ የራሶን ስም ይነግሩናል

⇒ ስሜ መልካሙ ፈረደ ይባላል

⇒ ስንተኛ ናቸው አቃቤ ሕግ 71 እሺ 77ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ሆነው የቀረቡት አቶ መልካሙ በማስረጃ ዝርዝር 171 ላይ የተጠቀሱት ቀርበዋል አቶ መልካሙ እስቲ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት?

⇒ አቶ በድሩ ሁሴን

⇒ ሌላ አለ?

⇒ ሌላ የለም የአያት ስም ኑሩ

⇒ አቶ በድሩ ሁሴንን በአካል ለይተው ያውቁታል?

⇒ አዎ

> ማሳየት ይችላሉ አሁን?



2692

2032

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

> እችላለሁ

> እሺ ተነስተው ያሳዩ ስንተኛ ናቸው እሺ ምስክሩ 5ኛ ተከሳሽን ለይተው አሳይተዋል ከተከሳሹ ጋር ጥላቻ ዝምድና ነገር አለ?

⇒ በፍፁም የለንም

⇒ ምንድን ነው ያዩት ለምን ተከሰሱ እስቲ ዝርዝር ውስጥ ሳይገቡ አጠር አርገው ወደ ዝርዝሩ በኋላ እገባለሁ

⇒ እሺ በአጭሩ በወቅተ መንግስት ባለው ወቅታዊ ችግር ስለተጠረጠሩ በዛ ምክንያት ነው እኔ የቀረብኩት

⇒ እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ

⇒ እሺ አቶ መልካሙ አሁን በችሎት የለዩዋቸውን አቶ በድሩ ሁሴንን በምንድን ነው የሚያውቋቸው?

⇒ እሳቸውን የማውቃቸው ከዚህ ቀደም ምንም እውቅና የለንም እኔ በአጋጣሚ ቤተሰብ ታሞ እዛ አካባቢ ሄጀ

⇒ ጠጋ አርጉት ወምበሩን እንዲመቾት

⇒ እሺ በወቅቱ መንግስት አካባቢው ላይ ፖሊሶችን አገኘኋቸው ፖሊሶቹ እንዲህ እንዲህ አቶ በድሩ ሁሴን የተባሉ ግለሰብ በእንዲህ አይነት ወንጀል ስለምንጠረጥራቸው ታዛቢነት ወይም ምስክርነት እንድሆን ተጠየቅኩኝ እኔም በዛ መሰረት የዜግነት ግዴታዬ ስለሆነ ለመተባበር ገብቻለሁኝ

⇒ መቼ ነው ቀኑ?

⇒ ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

⇒ ሰዓቱ ስንት ሰዓት ላይ ነው ?

⇒ ሰዓቱ አራት ሰዓት ጀምሮ እስከ አምስት ሰዓት



2680

2033

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አራት ሰዓት ማለት ማታ ነው ቀን ?

⇒ ቀን ከጠዋቱ አራት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ባለው ማለት ነው

⇒ ቦታው የት ነው?

⇒ ቦታው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ሆኖ ወረዳ 3 በብስራተ ገብርኤል ቤተክርስትያን ወረድ ብሎ ትንሽ

⇒ የቤት ቁጥሩን ያስታውሱታል?

⇒ የቤት ቁጥሩን ያስታውሱታል ?

⇒ የቤት ቁጥሩ ተከራይ ስለነበሩ ቁጥሩን አልያገዙትም

⇒ ተከራይ መሆናቸውን በምንድን ነው ያወቁት?

⇒ ጠይቀናቸው እሳቸውም ተከራይ ነኝ ብለው ስለሰጡ

⇒ ስላሉ?

⇒ ስላሉ ነው

⇒ እሺ አሁን በገለፁት ቦታ እና ግዜ ምንድን ነው የታዘቡት?

⇒ በወቅቱ የተገኙ ቁሶች 1ኛ 146 የሲዲ ካሴቶች 2ኛ ኤች ፒ የሚል 148 ኤ 100 የሆነ አነስተኛ ላፕቶፕ 205 የቴፕ ካሴቶች ድምፃችን የሚሰማ በራሪ ወረቀት የሙስሊሞች ጉዳይ የሚል 8 መጽሄቶች አዲስ ጉዳይ የሚል አሁንም መጽሄቶች በሚል ርእስ የተዘጋጀ ጋዜጦች ቋንቋችን በሙስሊም ምንድን ነው በአረብኛ ቋንቋ የተፃፉ አሁንም መጽሄቶች 7 እነዚህን አይተናል ከ12 ቱ እነዚህን ዘረዘርኩ

⇒ እነዚህን አይታችኋል?

⇒ አዎ

⇒ እነዚህን የት ነው ያገኛችኋቸው?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በወቅቱ ቤቱ ሲፈተሽ በተለያዩ ቦታዎች ተቀምጠው ማለስቡም እኒህ የኔ ናቸው አንድ በአንድ ቤቱ ውስጥ የተገኙ ናቸው እያሉ አሳዩን አየናቸው በደንብ አረጋገን

⇒ እነዚህ አሁን የገለጿቸውን ንብረቶች ከያዛችሁ በኋላ ምን ተደረገ?

⇒ እነዚህ ንብረቶች ከተያዙ በኋላ ምንድን ነው የተደረገው ዋናው ሰውየው አቶ በድሩ ሁሴን ማለቱ ነው የኔ ንብረት ናቸው እኔ ቤት ውስጥ ነው የተገኙት አሳዩን በዛ መሰረት አንድ በአንድ ወደ ፎርማ ውስጥ ገቡ አንደኛ እሳቸው ፈረሙ ከዛ በኋላ ተከትለንም እኔም አብሬ ፈርሜያለሁ

⇒ ምን እያላችሁ ፈረማችሁ?

⇒ በቤታቸው ውስጥ የተገኙ ለመሆናቸው አይተናል ታዝበናል በሚል ማለት ነው

⇒ ከቤቱ ውስጥ ሲገኙ አይተናል ብላችሁ ፈረማችሁ?

⇒ አዎ በትክክል

⇒ ምን ላይ ነው የፈረማችሁት ሁሉም የፈረማችሁበት ላይ እስቲ ይንገሩን?

⇒ በሁሉም ከአንድ ከጥራዙ ውስጥ በሙሉ እንዳለ ማለት ነው

⇒ ሌላስ የተያዘ ነገር አለ?

⇒ ከነዚህ ከ12 ውጪ የተያዘ ነገር የለም

⇒ ስትገቡ ስንት ሆናችሁ ነው የገባችሁት?

⇒ ስንገባ እኛ ታዛቢዎች አለን 3 ሁለት መርማሪ ፖሊሶች አሉ የፀጥታ ጉዳይ የሚያስከብር ደግሞ ሦስት አለ

⇒ እሳቸው የት ነበሩ?

⇒ እሳቸው በር ላይ ነው ያገኘናቸው ከበር አልፈን ነው ወደቤታችን የገባነው

⇒ ቤቱ ውስጥ ማን ነበረ?

⇒ አንድ የቤት ሰራተኛ ነበረች



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ሌላ ሰውስ?

⇒ ሌላ ሰው አንድ ጥበቃ ግቢው ትልቅ ስለነበረ አንድ ጥበቃ የቤት ባለቤት ነበሩ እሳቸውንም አልጠየቅናቸውም

⇒ እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል

⇒ እሺ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካለ

⇒ አቶ መልካሙ

⇒ አቤት

⇒ ታዛቢ እንዲሆኑ ተጠይቀው ፈቃደኛ እንድትሆኑ በመግለጽ መታዘቦን ገልፀውልናል ፖሊሶቹ ታዛቢ እንዲሆኑ ሲጠይቆትምንን መሰረት አርገው ነው ማለት እርስዎ ምን ጠየቁ ዝም ብለው ታዛቢ ይሁኑ ሲባሉ እሺ ብለው ነው የሄዱት?

⇒ እግዜር ይስጥልኝ በወቅቱ ቅድም እንዳልኩት እዛ አካባቢ ቤተስብ ልጠይቅ ሄጄ ነበረ እናም ፖሊሶቹ እንድታዘብላቸው ጠየቁኝ ሲጠይቁኝ የዜግነቴ ግዴታ መብት ግዴታ ስለሆነ ምንም ሃጢያትነት የለውም በማለት ለምስክርነ ተቀርቤያለሁ

⇒ ከዚህ ውጪ ፖሊሶች ያሳዮት ነገር አለ?

⇒ አይ እኔ ማለት ፖሊሶች ያሳዩኝ አንድ ከፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ደረጃ አራዳ ምድብ ችሎት የብርበራ ትእዛዝ ያወጡ ለመሆኑ አይቻለሁኝ እሱንም ምን ምን ማለት አንድ በአንድ የጦር መሣሪያም ከተገኘ የተለያዩ ቁሶችን ወንጀሉን በተጠረጠሩበት ክስ ማስረጃ ይሆናል የሚል ነገር እንዲበረበር የታዘዘውን ትእዛዝ አይቻለሁ

⇒ ስንት ዳኛ ነበር የፈረመበት ?

⇒ የዳኛ ስም አንድ ነው

⇒ ቤቱ ግቢ ነበረው እንዴ?

⇒ አዎ ገቢ ነበረው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ማን ነው የከፈተው ማን ነው ያንኳኳው ግቢውን ?

⇒ ግቢውን እራሳቸው ተከሳሹ ናቸው ያንኳኩት

⇒ ከዛ ሰራተኛዋ ነች የከፈተችው?

⇒ ሰራተኛዋ ሳትሆን የግቢው ጥበቃ

⇒ የግቢው ጥበቃ ከፈተ?

⇒ አዎ

⇒ ከዛ ከፍቶ አስገባቸው ምንም አልጠየቃችሁም አደል?

⇒ ከየት ነው የመጣችሁት የሚል ጥያቄ ቀረበ ከዚህ ከፖሊስ ነው የመጣነው አሉ ከፍተው ገባን

⇒ ገባችሁ ከዛ ወደ አቶ በድሩ ቤት ደረሳችሁ እሱንም አንኳኳችሁ አደል?

⇒ ክፍት ነበረ ቤቱ

⇒ ክፍት ነበረ ገባችሁ?

⇒ ሰራተኛ ስለነበረች እሳቸው ግለሰቡ እየመሩን ነው ይዘውን የገቡት ቤቴ ይህ ነው ብለው አሳዩን ገባን

⇒ ቅድም አቃቤ ሕግ ሲጠይቆት በተገኙት እቃዎች ላይ እነዚህ ሰነዶቹ ላይ መጽሄቶች ጋዜጦች በራሪ ወረቀት ያሏቸው ላይ እያንዳንዱ ላይ ነው እንዴ የፈረማችሁት እያንዳንዱ ገጽ በገጽ?

⇒ አዎ እያንዳንዱ ላይ ነው

⇒ መጽሄቱም ጋዜጣውም ላይ?

⇒ አዎ

⇒ መጽሃፍቶቹም ላይ?

⇒ አዎ



2037 2684

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ በርባሪዎቹ ሲገቡ ምን ይዘው ነበር ማለት መርማሪዎቹ ?

⇒ አጀንዳ እና ወረቀቶች ናቸው የያዙት

⇒ በእጃቸው ነው ወይስ በቦርሳ?

⇒ በእጃቸው

⇒ በቦርሳ የያዙት ነገር አልነበረም?

⇒ አንድም የለም

⇒ ውስጥ ከገባችሁ በኋላ ብርበራው ካለቀ በኋላ አልተቀረፀም እንጴ ቪዲዮ ካሜራ ?

⇒ ተቀርጿል

⇒ ተከሳሹ እና የተገኘው ነገር አብሮ ነው የተቀረፀው ?

⇒ አዎ

⇒ አሃ ቅድም ምንም ነገር አልያዙም ብለዋል ቪዲዮ ካሜራው ከየት ተገኘ ታዲያ?

⇒ ማለትም ቦርሳውን ነው አልያዙም ያልኩህ እንጂ ቪዲዮ እና ካሜራው ማለት ግልጽ በሆነ ነገር እየታየ ስለነበረ

⇒ በእጃቸው ይዘው ነበር ?

⇒ አዎ

⇒ እናንተ ከመግባታችሁ በፊት የገቡ ሌሎች ፖሊሶች ነበሩ?

⇒ አይ አንድም የለም እኛ ነን እንደውም 1ኛ ተከሳሹ ከዛ እኛ ቀጥሎ ፖሊሶች ነበሩ

⇒ ስንት ክፍል ነው ብርበራ የተደረገው ሳሎን ነው እንጴ የተገኘው ይሄ እቃ?

⇒ ሳሎን እና መኝታ ክፍል

⇒ እርስዎ ብርበራው ሲካሄድ የትጋ ነበሩ?

⇒ በመጀመሪያ ሳሎኑ ተበረበረ ሳሎኑ ላይም አብሬ ነበርኩኝ የሳሎኑን ስንጨርስ ቀጥታ ወደ መኝታ ቤት ነው የገባነው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እርስዎም እዛ ገብተዋል?

⇒ አዎ

⇒ ሰራተኛዋስ?

⇒ ሰራተኛዋም አብራን ገብታለች

⇒ ከእናንተ ጋር ትታዘብ ነበረ እየዞረች?

⇒ አዎ ማለት ውስጥ ውስጥ የተከጠፉ ምንጣፎች ስለነበሩ ምንጣፎች መረገጥ ስለሌለባቸው ምንጣፎቹን እያነሳች ወደ ጐን እያደረገች ነው አብራን ስታይ የነበረው

⇒ ቅድም የተናገሯቸው እነዚህ መጽሃፍት ሲዲዎች እና ሌሎችም ጋዜጣ መደርደሪያ ላይ ነበር ነው ያሉት የተገኙት?

⇒ አዎ መደርደሪያዎች ላይ ነው

⇒ ተቆፍሮ የወጣ ነገር አለ እንዴ?

⇒ ተቆፍሮ የወጣ አንድም ነገር የለም

⇒ ጣሪያ ተቀዶ የወጣ ነገር የለም?

⇒ የለም አዎ

⇒ ጨርሰል የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እሺ ድጋሚ ካለ ጠይቁ?

⇒ አቶ መልካሙ የፍ/ቤት ትእዛዙን በተመለከተ በትክክል ያስታውሳሉ ማለት ፖሊስ የሚበረብርበት ምክንያት የገለፀው ነው ወይስ የፍ/ቤት ትእዛዝ በትክክል ነበረ?

⇒ በትክክል የፍ/ቤት ትእዛዝ ነበር

⇒ ያስታውሱታል ማለት ፖሊስ የነገሮት ሊበረብርበት የሚችልበት የሕግ መሰረት ወይም ወይስ የፍ/ቤት ሰነድ አለኝ ብሎ ነው የትኛውን ነው ያሉት?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ግለሰቡ የተከሰሱበትን ወንጀል ቤታቸው ውስጥ ማንኛውም ከንጀሉ ጋራ ተያያዥነት ያለው ጉዳይ እንዲበረበር ማዘዙ ነው ከብዙ በጥቂቱ እነዚህ ነው

⇒ እሺ ቀጥሉ

⇒ የፍ/ቤት ትእዛዝ ከግለሰቡ ወይም ከተጠርጣሪው ከወንጀሉ ጋራ በተጠረጠረበት ወንጀል ላይ ከዚህጋር ተያይዘው ያሉ የጦር መሣሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ እንዳዚሁም ቁሶችም በራሪ ወረቀቶችም ሊሆኑ ይችላሉ በዚህ ዙሪያ ላይ ያሉትን ነገሮች ተበርብረው እንዲቀርቡ የሚል ትእዛዝ ነው በከፊሉ ይሄንን ነው ያነበብነው

⇒ የሚያስታውሱት ይሄንን ነው?

⇒ አዎ

⇒ እሺ ድጋሚ ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ ማጣሪያ ጥያቄም የለም ጨርሰዋል እሰመግናለን ቀጣይ ምስክር

⇒ በእውነት ለመመስከር

⇒ በእግዚአብሔር ስም ምያለሁ

⇒ ለምስክርነት ነው የመጡት?

⇒ አዎ

⇒ የራሶን ስም የአባቶን ስም እና ሌላ ዝርዝር ሳይጨምሩ ይነግሩናል የራስህን ስም ብቻ ማለት ነው ?

⇒ ዳዊት

⇒ 78ኛ ምስክር ላይ ደርሰናል በማስረጃ ዝርዝሩ 166 ላይ የተጠቀሱ አቶ ዳዊት ቀርበዋል አቶ ዳዊት በነማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ዛሬ?

⇒ በየሲፍ ጌታቸው

⇒ ያውቁታል አቶ የሱፍን ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አውቀዋለሁ

⇒ /የማይሰማ/

⇒ የለኝም ቤቱ ሲበረበር ነው ያየሁት በታዛቢነት

⇒ እሺ አቶ ዳዊት አሁን በችሎት የጠቆሟቸቸውን አቶ የሱፍን ቤት ሲበረበር ነው የማውቃቸው ብለዋል መቼ ነው?

⇒ በ12 ሐምሌ ወር ላይ ነው

⇒ ዓመተ ምረቱስ?

⇒ 2004

⇒ ሰዓቱ?

⇒ ሰዓቱ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ

⇒ ቀን ነው ማታ?

⇒ ቀን ላይ ነው

⇒ ቦታው የት ነው?

⇒ ቦታው ወደ ሾላ አካባቢ

⇒ ምን ክፍለ ከተማ ይባላል?

⇒ የካ ክ/ከተማ

⇒ ወረዳው?

⇒ ወረዳ 8

⇒ የቤት ቁጥሩን ያስታውሳሉ?

⇒ 230

⇒ በዚህ አሁን በነገሩን ቦታና ጊዜ ምንድን ነው የታዘቡት?



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከፍተኛ ፍርድ ቤት
ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ያው ፖሊሶች እንዴ ታዛቢ ትሆንልናለህ በሚል ቤታቸው ገብቼ የተለያዩ ነገሮችን አይቻለሁ

⇒ እርስዎ እዛ እንዴት ተገኙ?

⇒ እንደ አጋጣሚ ከስራ ወጥቼ ከካፌ ሻይ ቡና ብዬ ሳልፍ ነው በዛ በኩል

⇒ ፖሊስ እንዲታዘቡ ጠየቆት?

⇒ አዎ ከዛ የፍ/ቤት እንትኑን አሳዩን በዛ መሰረት ልታዘብ ችያለሁ

⇒ ስንት ሆናችሁ ነው እሳቸው የት ነበሩ?

⇒ እቤት ውስጥ ነበሩ

⇒ እ?

⇒ ተከሳሽ ናቸው?

⇒ አዎ

⇒ እቤት ውስጥ ነበሩ

⇒ ማለት ከየት ነው የመጡት እርስዎ የት ነው ያገኟቸው ተከሳሹን ?

⇒ መኖሪያ ቤታቸው

⇒ ከማንጋር ?

⇒ ከቤተሰቦቻቸው ነው ሕፃናቶችም አሉ

⇒ እሺ ምን ምንድን ነው የተበረበረው ማለት የተያዘው ምንድን ነው በብርበራ?

⇒ የተለያዩ በተለያዩ ቋንቋ የተፃፉ ትናንሽ እና ትላልቅ መፃህፍቶች ፍላሽ ሞባይሎች እና ተንሸራታች ላፕቶፕ አንድ ቶሺባ ላፕቶፕ ሁለት የመቅረጫ ድምጽ እነዚህ እነዚህን ሲዲዎችን እና ካሴቶችን አይቻለሁ

⇒ ሌላስ?

⇒ ስድስት ሺ ብር አይቻለሁኝ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አሁን ከገለፁት ቶሺባ ሲዲዎች እና ገንዘብ ሌላ የተያዘስ ነገር አለ የሚያስታውሱት ?

⇒ ፍላሽ ዲስክ አንድ ነው ሚሞሪ ደግሞ ሁለት ነው

⇒ ሌላስ?

⇒ ሌሎቹን ጥራዥ የሆኑ ብጥስጣሽ ወረቀቶችን አይቻለሁ

⇒ ማለት በምን የተፃፉ?

⇒ አንድ ሌሎቹ አሉ በአረብኛ ምናምን የተፃፉ አሉ አንዱ ግን በአማርኛ ብጣሽ ወረቀት ላይ ያየሁት የቢላል ድምጽ ምናምን የሚል ድምጽ አይቻለሁ

⇒ የምን?

⇒ የቢላል ድምጽ የሚል ብቻ በጽሁፍ ተቀርፆ እንትን ብሎ አይቻለሁ

⇒ በሰነድ ገጽ የሚያስታውሱት አለ?

⇒ የለም

⇒ በገጽ ብዛት በግምት የሚያስታውሱት?

⇒ መፃህፍቶቹን ቁጥራቸውን ነው እንጂ ሌሎቹን እንትን አላልኩም

⇒ መጽሃፍ ተይዟል?

⇒ አዎ ትናንሽ እና ትላልቅ መፃህፎቶች ወደ 92 አካባቢ ተይዟል

⇒ ምን ያህል?

⇒ ወደ 92 አካባቢ

⇒ መጽሃፍቶች ተይዘዋል?

⇒ አዎ

⇒ በርእስ የሚስታውሱት አለ ?

⇒ በርእስ ብዙም የማስታውሰው ነገር የለም

⇒ እነዚህ አሁን የዘረዘሯቸው ንብረቶች የት ነው የተገኙት?



2043

2680

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ከመኖሪያ ቤታቸው

⇒ የት የት ማለት በቦታ  እስቲ ይንገሩን?

⇒ መጽሃፎቹ ሼልፍ ላይ ነበሩ ላፕቶፕ ደግሞ የሆነች ሳጥን ነገር ነበረች እዛ ላይ ነው የነበሩት ሞባይሎቹም ሳጥን ላይ ነበሩ

⇒ ስትገቡ እንዴት ብላችሁ ነው የገባችሁት?

⇒ እ?

⇒ እስቲ ስትገቡ እንዴት ብላችሁ እንደገባችሁ ንገሩኝ ?

⇒ ስንገባ ቀጥታ ፖሊሶች ነበረ አንዴ ተባበረን ለፍተሻ ነው ታዛቢ ትሆናለህ በሚል ነው ገባን በዛ ሁኔታ ነው ስታዘብ የነበርኩት

⇒ ምን አሉኝ ስትገቡም ያናገራችሁት ማንን ነው ያገኛችሁት?

⇒ ስንገባ ፖሊሶች ነበሩ ውስጥ አንድ ሁለት ፖሊሶች ነበሩ በቃ አሳዩን የፍ/ቤት ደግሞ ፈታሽ የነበሩ ሰወች እንድትታዘብ ነው በሚል ነው ቤት ውስጥ የነበርነው

⇒ እህ እሺ እነዚህን ንብረቶች መጨረሻ ላይ ምን አደረጋችሁ ?

⇒ እየተቆጠሩ እና እየተመዘበ በተከሳሹ ፈቃድ እንዲወጡ ተደርጓል እሱም እያየ ማለት ነው

⇒ ማለት በተከሳሽ ፈቃድ ሲሉ ማለት እስቲ ይንገሩን አብራርተው ?

⇒ የሱፍ ጌታቸው ባለበት እየተቆጠሩ እነዚህ ተቆጥረው ይተመዘገቡት ንብረቶቹ ላይ ሦስት ታዛቢዎች እንድንፈርም ተደረገናል

⇒ ምን ብላችሁ ፈረማችሁ?

⇒ የተዘረዘሩ እቃዎች አሉ እነዚህ የተገኙት መሆናቸውን በዛ ቤት ውስጥ አይተን ፈርመናል

⇒ አቶ የሱፍ ጌታቸውስ ምን ብለው ፈረሙ?

⇒ አቶ የሱፍ ጌታቸው እኔ እዚህ ይሄ  ሁሉ ንብረት የኔ የሚለው ላይ ፈርመዋል በኔ ቤት ተገኝቷል የሚል ማለት ነው



2684 2691

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ስንት ሰዓት ላይ ጨረሳችሁ?

⇒ ለአምስት ምናምን ጉዳይ ላይ ጨርሰናል

⇒ ለስንት?

⇒ ከምሽ፡

⇒ ለስንት?

⇒ ለአምስት ምናምን ጉዳይ

⇒ ጨርሳችኋል?

⇒ አዎ ጨርሰናል

⇒ ዋና ጥያቄ አብቅተናል

⇒ ጠበቆች መስቀለኛ ካላችሁ

⇒ አቶ ዳዊት

⇒ አቤት

⇒ እርስዎ ለዛቢነት ተጠርተው ሲሄዱ ከእርስጋር ሌሎች አብረው ነበሩ እንዴ ታዛቢዎች?

⇒ አዎ አብረን ጓደኞቻችን ነበሩ ሻይ ቡና እየጠጣን እያለ ነው ስንሄድ አንዴ እንደዚህ ተባበሩን በሚል ታዝበናል

⇒ ከዛ ለመታዘብ ስትገቡ ተከሳሹን ከሌሎች ፖሊሶች ጋር እቤት ውስጥ ነው ያዩዋቸው አደል?

⇒ አይ ቤት ውስጥ አልነበሩም አንዴ ኑና እንትን በሉና በሩ ተከፈተ የሱፍ ጌታቸውም ቁጭ ብሎ ነበረ እንደዛ ነው ልታዘብ የቻልኩት

⇒ እኮ የሱፍ ጌታቸው ቤት ውስጥ ነበረ አደል የተቀመጠው?

⇒ አዎ

⇒ ስለዚህ እናንተ ስትገቡ እንዴ ፖሊሶችስ ከየሱፍጋር አልነበሩም እንዴ ቤት ውስጥ ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሱ አልበሩም በሩ ላይ ነበሩ በሩን ከፍተው ነው ያስገቡን እኛን ሌሎች ፖሊሶች ግን ውጭ ላይ ነበሩ

> ልክ አሁን ታዛቢ ሁኑ ተባላችሁ የሱፍ ጌታቸው ቤት ደረሳችሁ እንደዴት ገባችሁ ማን አንኳኳ?

⇒ ፖሊሶቹ ናቸው

⇒ ማን ከፈተላቸው?

⇒ ባለቤቱ

⇒ በቃ ከፈተች ገቡ አደል?

⇒ እኛ ግቡ ተባልን ገባን አዎ

⇒ ከዚህ ውጪ ከባለቤቶ ጋር እገባለሁ አልገባም የሚል ነገር ተፈጥሮ ነበር?

⇒ አይ ምንም ነገር አልተፈጠረም

⇒ አንኳኳች ገቡ?

⇒ አዎ

⇒ ውስጥ ስትገቡ የሱፍ ምንድን ነው እጁ ታስሮ ነበር?

⇒ አልታሰረም

⇒ ከከብርበራው በኋላ አልተወሰደም እንዴ የሱፍ?

⇒ ተወስዷል ከነ እቃዎቹ  ተጭኖ ማለት ነው

⇒ ቅድም የፍ/ቤት የብርበበራ ትእዛዝ እንዳሳዮት ገልፀዋል ይሄንን የብርበራ ትእዛዝ ቤት ውስጥ ገብተው ለባለቤትየው አሳይተዋል እንዴ ለየሱፍ ለባለቤትየው ሲያሳይ አይተዋል?

⇒ አዎ ለሁላችንም ነው የገለፁት

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ለናንተማ መንገድ ላይ ነው የገለፁላችሁ እንድትታዘቡ ስትጠየቁ መንገድ ላይ አሳዩዋችሁ የናንተ አለቀ እዛጋ ከዛ በኋላ ወደ ውስጥ ገባችሁ ውስጥ ገብታችሁ ወደ ብርበራው ነው አደለም የተገባው ?

⇒ አሳይተውናል የፍ/ቤቱም ደዩ ተብሎ በድጋሚ አብረን ሆነን አይተናል

⇒ እነዚህ በተገኙት ወረቀቶች ላይ ታዛቢዎች ገጽ በገጽ ፈረሙበት ወይስ ቃለ ጉባዔው ላይ ነው የፈረሙት?

⇒ ቃለ ጉባኤው ላይ ነው እንጂ ገጽ በገጽ ላይ አልተፈረመም

⇒ ስለዚህ ወረቀቶቹ ላይ አልፈረማችሁም?

⇒ አልፈረምንም

⇒ ይሄን ያህል መጽሃፍ ይሄን ያህል በራሪ ወረቀት እያላችሁ በቃለ ጉባዔው ፈረማችሁ?

⇒ እሱ ላይ ፈርመናል እንጂ እያንዳንዱን ገጽ መጽሃፉን እየገለጥን መጽሃፉ ላይ አልፈረምንም

⇒ በራሪ ወረቀቶቹ ላይስ?

⇒ በራሪ ወረቀቶቹ ላይም አልፈረምንም

⇒ ንብረቶቹ ቅድም ገልፀውታል እሺ ብርበራውን የጀመራችሁት ከቀኑ አስራአንድ ሰዓት ነበረ የተጠናቀቀው ለአምስት ምናምን ጉዳይ አስር ጉዳይ እንደዚህ አካባቢ ነው ብለዋል ከአስራ አነድ ሰዓት እስከ ለአምስት ምናምን ጉዳይ ሲደረግ የብርበራ ሰዓቱን አይታችሁ ነበረ እንዴ ምርመራ ትእዛዙ ላይ የፍ/ቤት ትእዛዙ ላይ ከዚህ ሰዓት እስከዚህ ሰዓት የሚል አይተዋል?ከ

⇒ እሱን አላየሁም

⇒ ስለዚህ መጀመሪያ አሳዩዋችሁ ለቤተሰብም አሳዩ ከዛ ብርበራው ተጠናቆ በዚሁ ነው የወጣችሁት አደል?

⇒ አልገባኝም ጥያቄው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ማለት ፖሊሶቹ በመሃል ያደረጉት ነገር ነበር ብርበራ ለናንተም አሳዩ ለቤተሰብም አሳዩከዛ ብርበራው ተካሄደ እቃ ተሰበሰበ ይሄ ሆኖ እስኪያልቅ ድረስ ፖሊሶቹ ከዚህ ውጪ ያደረጉት ነገር አለ ?

⇒ ምንም ነገር ያደረጉት ነገር የለም

⇒ በወቅቱ ከየሱፍ እና ከቤተሰብ ከሚስቱ ውጭ ሌላ ሰው ነበረ እንደ የቤተሰብ አባል ?

⇒ ሌሎች ሴቶች ነበሩ አዎ ሕፃናትም ነበሩ

⇒ ስንት ሴት?

⇒ ሁለት ሴቶች አካባቢ ነበሩ ሕፃናትም ነበሩ እነሱ ብርበራው ሲካሄድ የት ነበሩ?

⇒ እዛው ቁጭ ብለው ነበር

⇒ እሺ በዚህን ጊዜ ውስጥ ከፖሊሶች ወይም ከቤተሰብ ወይም ከየሱፍ ወይም ታዛቢዎች ሞባይል የደወለ ሰው አለ ?

⇒ የሱ ስልክ ላይ ሲደወል ነበረ

⇒ የማን ስልክ ላይ የየሱፍ?

⇒ አዎ

⇒ ማን ነበረ የሚደውለው?

⇒ አልታወቀም

⇒ መደወሉን እንጂ ፖሊሶች ተቀብለው አልደወሉም በየሱፍ ስልክ ላይ?

⇒ አይ አልደወሉም

⇒ ፖሊሶች እስከ መጨረሻውም አልደወሉም?

⇒ አልደወሉም

⇒ ቅድም የብርበራ የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አይተውታል በአይኖ ?



2018 265

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ያው አነበበልን እንደዚህ እንደዚህ ብሎ ለመታዘብ ፍቃደኛ ከሆናችሁ ምናምን በሚለው ፍቃደኛ መሆናችንን ገልፀን ታዘብን

⇒ አነበበሎት እንዴ እርስዎ አላዩም ?

⇒ አይቻለሁ ማህተም ምናምን ብዙ ጽሁፍ ስለሆነ ላነበው አልቻልኩም

⇒ ስለዚህ አሳይቶት ነው ያላነበቡት ወይስ እሱ ነው ያነበበው?

⇒ አዎ ልብ ብዬ አላነበብኩትም የትእዛዝ እንትን አለ ብሎ ወረቀት አሳዩን

⇒ ትእዛዙ ምን እንደሚልም አላዩትም ?

⇒ አላየሁትም

⇒ የፍ/ቤት መሆኑን ግን አይተዋል ?

⇒ የፍ/ቤት ወረቀቶች ያው ሕጋዊ ፖሊሶች ስለሆኑ እንትን ስለለበሱ

⇒ አይተዋል አላዩም?

⇒ ምኑን ?

⇒ የፍ/ቤት ትእዛዝ መሆኑን ፖሉስ ነገሮት እንዴ እርስዎ አይተውታል ካዩ አይቻለሁ ካላዩ ?

⇒ ወረቀቷን እንደዚህ ይኸዊ ማዘዣ ነው ብሎ አሳይቶኛል

⇒ የፍ/ቤት ይሁን የፖሊስ ለይተዋል?

⇒ እሱን አላየሁም

⇒ እሺ በዚህ ትእዛዝ ላይ ይፈተሽ የሚለውን ነገር ለይተው አይተዋል እርስዎ ከየሱፍ ቤት መሣሪያ ሌላ ነገር ይፈተሽ የሚለውን ዝርዝር አይተዋል?

⇒ እሱን አላየሁም

⇒ ፖሊስም አልነገሮትም?

⇒ አዎ

⇒ መጨረሻ ላይ ገንዘቡን ወሰዳችሁ?



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ አዎ

⇒ የብርበራው ትእዛዝ ላይ ገንዘብ ይወሰድ የሚል አይተዋል?

⇒ አልገባኝም ጥያቄው

⇒ ቆይ አላየሁም ነው ያሉት ከመጀመሪያ ጀምሮ

⇒ እሺ የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እነዚህ ከሱ ቤት የተያዙ ካሏቸው ውስጥ መጽሄቶች በራሪ ወረቀቶች ውስጥ በሕግ የተከለከለ ስለመኖሩ የሚያውቁት ነገር አለ?

⇒ አላውቅም

⇒ የሱፍ የደረሰው እናንተ ከደረሳችሁ በኋላ ወይስ ከመድረሳችሁ በፊት ነው?

⇒ አይ እቤት ውስጥ ነበረ እሱ

⇒ እሺ ያን ጊዜ አስራ ሁለት ሰዓት ሆኗል እና አትገቡም ሲል እናንተ ምን አደረጋችሁ ታዛቢዎቹ ፖሊሱን አትገባም ብለው የሱፍጋ ሲከራከሩ ነር እናንተ ያደረጋችሁት ነገር ነበረ ታዛቢዎቹ?

⇒ አልተከራከሩም ጭራሽ ክርክር የለውም ነበር

⇒ አትገቡም እያለ ሲል አልነበረ የሱፍ?

⇒ የለም

⇒ ቤት ውስጥ የሚያለቅስ ሕፃን ነበር?

⇒ ሕፃን ልጅ

⇒ ያለቅስ ነበር ?

⇒ አይ አላለቀሰም

⇒ ነበረ ቤት?

⇒ ነበረ



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ እሺ መሣሪያውን ወደታች አድርገው ወይም ይዘህ ውጣ ከቤት እያለ ሲል ነበረ የሱፍ፡ እንደዛ እያለ ከፖሊሱ ጋ ምን አደረገ ?

⇒ እንደዛ አይነት ምንም ነገር ከፖሊሶችጋም ከምን ጋም አተካሩ ምንም ነገር የተደራረጉት ነገር የለም የሱፍም ቁጭ ብሎ ቤቱ በትዝብት ሲያስፈትሽ ነበር ቁጭ ብሎ ማለት ነው

⇒ እኮ ይሄን ሲለው ይዞ ወጣ መሣሪያውን ወይስ ምን አደረገ ወደታች አደረገው ምን አደረገ?

⇒ እንዴት ነው ጥያቄው መሣሪያውን ይዞ ወጣ የሚለው ነገር ወይ በጥያቄ ይጠይቁ ወይ ምስክሩ አኮ አልተናገረም ያልጠየቀውን እንደዘሁ ሲል ምን አደረገ እያሉማ አያስተካክሉ

⇒ እሺ ይዞ ነበረ መሣሪያ ይዘው ነበር ፖሊሶቹ?

⇒ ምንም ነገር እኔ አላየሁም ጨርሶ

⇒ እሺ መጽሃፎቹ ላይ እያንዳንዱ ላይ እንፈርም ሲል የሱፍ አይ በቁጥር ነው እንጂ ሰዓት ስለሚወስድ አናስፈርምም እያሉ ሲነጋገሩ ነበረ አደለ?

⇒ አዎ ሰዓቱም ከመሄዱ አንፃር መጽሃፍቶቹም ብዙ ከመሆኑ አንፃር ተብሎ በዛ ተስማምተ ነው እንዲወጣ የተደረገው በቁጥር

⇒ እኮ በቁጥር ነው እንጂ እያንዳንዱ ላይ አይፈረምም ?

⇒ እያንዳንዱ ላይ አይፈረምም ያው ከሰዓት አንፃር ስለተባለ ብዛት ያለው መጽሃፍ ስለሆነ ማለት ነው

⇒ መጽሄቶቹን በተመለከተ እኔ የመጽሄቱ ዋና አዘጋጅ ነኝ ሲላቸው ሰላም ሲበዛ እራስ ያማል የሚለውን መጽሄት አምጣ እያሉ ሲሉት ነበር አደል?

⇒ አላሉም

⇒ መጽሄቱን እንዳለ ነው ሁሉንም አውጥተው የወሰዱት ?

⇒ አይ ተመሳሳይ ስለሆነ የሙስሊሞች ጉዳይ የሚል መጽሄትነበር ተመሳሳይ ስለነበር አምስቱን ብቻ ነው ቀንሰው ይዘው የወጡት



http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ፎቶ የሚያነሳ ሰው ነበረ እንዴ?

⇒ አይ የለም

⇒ ሴት ነበረ አልነበረም?

⇒ ሴት ማለት ?

⇒ ፈታሾች ውስጥ አብረው የገቡ?

⇒ ወንዶች ናቸው ፈታሾቹ

⇒ ፎቶ ግራፍ የምታነሳ ሴት አልነበረችም?

⇒ አላየሁም

⇒ አንተ በነበርክበት ወቅት አልነበረችም ?

⇒ ሁላችንም እኔ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ነበርኩ አላየሁም

⇒ እሺ ታዛቢዎችን አላውቃቸውም ወይም ጐረቤት ያሉ የሚያውቁኝ ሰዎች ይታዘቡ ባለቤቴ ታውቂያቸዋለሽ ተብላ አላውቃቸውም ብላለች አደለ ሌላ ሰው ይምጣልን ሲሉ ምንድን ነበር ፖሊሶቹ የሰጡት መልስ እሺ እናንተ ታዛቢዎቹን አላውቃቸውም ሲል ነበረ አልነበረም የሱፍ ?

⇒ ብሏል እኛም አናውቀውም ከዚህ በፊትም

⇒ እሺ ባለቤቱስ ታዛቢዎቹን አላውቃቸውም አለች አላለችም?

⇒ እሷ ምንም አላለችም

⇒ እሺ እነሱን ስለማናውቃቸው እኛ የምናውቃቸው ታዛቢዎች ይምጡ ሲሉ ነበ አልነበረም ?

⇒ ማንም ያለን የለም

⇒ አላውቃቸውም ብቻ ነው ያለው እሺ

⇒ አቶ ዳዊት

⇒ አቤት



2697

http://ethcriminalawnetwork.com/

⇒ ፖሊሶቹ ሲገቡ ምን ይዘው ነበረ በእጃቸው መርማሪዎቹ ?

⇒ አጀንዳ

⇒ ሌላ ቦርሳ እንደዚህ ነገር አልያዙም?

⇒ አልያዙም

⇒ ውስጥ ገብተውስ ተከሳሹ አንአቶ የሱፍን ከተገኘው ኢቃጋር ቪዲዮ አላነሱትም ?

⇒ አይ እሱን

⇒ ቪዲዮ አላነሱትም እንዴ ውስጥ?

⇒ አላነሱትም

⇒ እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

⇒ እሺ አቃቤ ሕግ ድጋሚ ካለ

⇒ እሺ አቶ ዳዊት የፍ/ቤት ትእዛዙን እኔ አላነበብኩትም አላየሁትም ወይስ አልተነበበልኝም የትኛውን እንውሰድ የፍ/ቤት ትእዛዝ አልተነበበላችሁም?

⇒ ተነቦልናል

⇒ እያንዳንዱ መጽሃፍ ላይ በጊዜ ምክንያት እያንዳንዱ ገጽ ላይ መፈረም አልቻልንም ብለዋል ፊት ገጽ ላይ ፈርማችኋል እንዴ?

⇒ አልፈረምንም

⇒ ምንድን ነው ያደረጋችሁት?

⇒ በቃ እየተቆጠረ መጽሃፉ ያሉት እንዳለ የተገኙት ንብረቶች ተቆጥረው በቃለ ጉባዔ እሱ ላይ ነው የፈረምነው

⇒ እሺ እናንተ ገለልተኛ አደላችሁም ብሎ አቶ የሱፍ ጥያቄ ጥቋል ቤቴን መበርበር አትችሉም እናንት ገለልተኛ ሰወች አደላችሁም?

⇒ አላለም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

፦ እሺ. ድጋሚ ጥያቄ አብቅተናል የተከበረው ችሎት

፦ የተሰሙት /ያልተቀረበ/

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ሚያዝያ 3 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች ፡- ብስራት ተህልቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ ፡- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድም አገኝ ቀርቧል

ተከሳሾች፡- እነአቡበከር አህመድ ሁሉም ቀርበዋል የተከሳሾቹ ጠበቃ አዲስ መሃመድ እና ባህሩ መካንጋን መዝግበናል እሳቸው ስም አዲስ ሳይሆን ሃሊማ ሰኢድ ሃሊማ ይቅርታ እሺ ሃሊማ ሰኢድ ፣ባህሩ መካንጋ እና ሞላልኝ መለሰ ቀርበዋል

- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- እሺ ለምስክርነት ነው የመጡት ስምህን እስቲ የአባትህን ስም ሳትጨምር የራስህን ብቻ ትንግረናለህ?
- አለማየሁ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዝርዝሩ የተከበረው ፍ/ቤት ይቅርታ 170 ላይ ነው የተጠቀሰው የማስረጃ መግለጫ 170 ላይ
- 79ኛ ምስክር ናቸው እሺ አቶ አለማየሁ
- አቤት
- ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለዋል ቅድም እና ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- አቶ ሳቢር ላይ
- እሺ ሌላ እሱ ላይ ብቻ ነው?
- አዎ
- አቶ ሳቢርን ለይተው ያውቃሉ በአካል?
- አዎ
- ማሳየት ይችላሉ አሁን ተነስተው ቆመው ማሳየት ይችላሉ ?
- ወደዛ ወጥተህ ማየት ትችላለህ
- በአካል ሲንቀሳቀስ ባየው አውቀዋለሁ
- ይኸውልህ ምስክር ችግር የለውም እኮ ምስክር ና ና ቆይ አዳምጠን መጀመሪያ ቆይ ቆይ 1ኛ በደንብ ማሰብ አለብህ እምትመሰክራትን እያንዳንዷን ምክንያቱም እናንተን መሰረት አድርገን ነው ብይን ውሳኔ የምንሰጠው ስለዚህ ዝም ብለህ ዞር ብለህ እንዲህ ብትል እሱ ሳይሆን በደንብ ለይተህ የትኛው እንደሆነ አስበህ እሱን ትናገራለህ ካለየህ ደግሞ ግዴታ የለብህም
- ተመሳሳይነት ስላላቸው



2056

http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ እሺ. ምስክሩ ተከሳሹን ለይቶ ለማሳየት ሲነሱ አንደኛው ከአቶ ካሚል ጋር ይመሳሰላሉ ብለው አቶ ካሚልን አሳይተዋል በመጨረሻ ግን ስለተመሳሰሉብኝ ነው ብለው 7ኛ ተከሳሹን ለይተው አሳይተዋል እሺ. አሁን ካሳዩን ተከሳሽ ጥላቻ ወይ. ዝምድና አለህ?

➢ የለኝም

➢ ምንድን ነው ያየኸው እስቲ አጠር አርገህ ምን ፈጽሞ ነው የተከሰሰው አንተ ያየኸው ?

➢ ማለት በዛን ሰዓት ላይ የሽብር ወንጀል ፈጽሟል በሚል ነው

➢ የሽብር ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ እሱ ምን ሲደረግ ነው አንተ ያየኸው?

➢ እኔ ያየሁት ቤት ብርበራ እንደሚደረግ በፍ/ቤት ትእዛዝ

➢ ቤት ሲበረበር ነው ያየኸው?

➢ አዎ ቤት ሲበረበር

➢ እሺ. አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ

➢ እሺ. የተከበረው ፍ/ቤት አቶ አለማየሁ ያው በአቶ ሳቢር ላይ ነው የመጣሁት ብለሃል በብርበራ ታዛቢ. መሆንህን ገልፀሃል እና እስቲ ይሄ ጊዜ መቼ ነበር ቀኑ ጊዜው ቦታ የት ነው ያየኸው?

➢ ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.

➢ እሺ. የት አካባቢ. ነበር?

➢ ኮልፌ ቀራንዮ ወረዳ 1 ቀበሌ 02/03

➢ ምንድን ነው በዚህ ላይ ከታዘብከው እስቲ ከመጀመሪያው መጀመሪያ ማንን አገኘህ ከዛ ምን ተባልክ ?

➢ ድምፁ በደንብ አይሰማም



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ. መጀመሪያ ማንን አገኘህ አሁን ያልክበት ኮልፌ ቀራንዮ አሁን የጠቀስክበት ቦታ ስንት ሰዓት ላይ ማንን አገኘህ ከዛ ምን አሉህ ወዴት ሄድክ?
- ማለት በዛን ሰዓት ላይ ያው
- ኮልፌ ቀራንዮ የት ነው ያልከው ?
- ኮልፌ ቀራንዮ
- ልዩ ቦታው ?
- ከቻይና ካምፕ ከፍ ብሎ ያለ ሰፈር ነው
- ወረዳ ስንት ነው ?
- ወረዳ 1
- እሺ. ወደዛ ሄድክ ከማን ጋር ሄድክ?
- ማለት እዛ ከሄድኩኝ በኋላ ያው ለምስክርነት ነው የሰፈር ልጆች ናቸው ጓደኞቼ ነበሩ እዛ አካባቢ ነዋሪ ነኝ እና ለምስክርነት እንፈልግሃለን ብለው ጠሩኝ ሄድን ያው እሱን ነው ከዛ በኋላ
- እሺ. ከዛ እነማንን ነው ያገኘሽው?
- ያገኘሁት አቶ ሳቢርን
- አይ ከሱ በፊት ማንን አገኘህ ምን አሉህ?
- ያው የፍ/ቤት ትእዛዝ እንዳላቸው ቤት ለመፈተሽ በሽብር ወንጀል የተጠረጠረ ቤት ለመፈተሽ እንደሆነ እና እሱን የፍ/ቤት ትእዛዝ የታዘዘ እንደሆነ ማህተም ያለው የማይነበብ ፎርማ እንዳለው
- ይሄን ያሉት እነማን ናቸው?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ ይሄን ያሳዩን ከፌደራል ፖሊስ አባላት ናቸው

➢ እሺ ከዛ እሱ ነበረ ሳቢር?

➢ አዎ አብሮ ነበር

➢ ከዛ ምን አሉ ገባችሁ?

➢ ያው በሱ መሪነት እቤት አንኳኳን ከዛ በኋላ በአቶ ሳቢር መሪነት ተንኳኳ ከዛ የተከፈተው ሰራኛ እንደዛ ነገር ነው ከዛ በኋላ ሁኔታው ተነገራት እና ወደ ውስጥ ገባን

➢ ምን ተባለ?

➢ ግቢ ውስጥ ከገባን በኋላ ወደዋናው ቤት ለመግባት ሲንኳኳ ምናልባት ይመስለኛል ወንድም ይመስለኛል እሱ ከፈተ ሁኔታው ተነገረው ከየት እንደመጡ ሁኔታው ተነገረው ተነበበለት ከዛ በኋላ ወደ ውስጥ ገባን ውስጥ ገብተን መጀመሪያ ላይ የተጠየቀው ጥያቄዎች አሉ ያንን ነገር ሙሉውን ቤት ከማስሳቸው በፊት ያሉት ነገሮች እሱን የተጠየቀበት ሁኔታ

➢ ምን አገኛችሁ ምን አየህ ምን ታዘብክ ምን ተገኘ?

➢ ማለት እውስጥ የተጠየቁት ጥያቄዎች መጀመሪያ ብርበራው ከመጀመራችን በፊት የጦር መሣሪያ ካለ አውጣና አስረክበን ሌላ ነገር ከምናረግ በሚል ነው የተጠየቀው ማለት ነው ከዛ ጦር መሣሪያ የለኝም የሚል ነገር ነው የመለሰው

➢ እሺ ከዛስ?

➢ ከዛ በኋላ ያው ብርበራው ተጀመረ እሱ የተጀመረበት ሰዓት ላይ ያው የተገኙት ነገሮች ዘ ስቶሪ ኦፍ እሬት ኤክስፐርሚሽን የሚል በእንግሊዘኛ የተፃፈ ... ነው ዘ እስቶሪ ኦፍ ግሬት ኤክስፓንሽን በእንግሊዘኛ የተፃፈ ... ሰዓት ላይ



http://ethcriminalawnetwork.com/

ዲስክሪቢውትድ ባይ ቢላደን ግሩፕ ነው የሚለው እሱ ተገኝቷል ሰለፊያ ጋዜጣ ብዛት 8 በሜክሲኮ  እና ጀርመን አበሾች እረብሻ አካሄዱ የሚል በመስኪድ ውስጥ አረቦች እረብሻ አካሄዱ የሚል አለ አንድ ሜክሲኮ እና ጀርመን አበሾች በስኪድውስጥ እረብሻ አካሄዱ የሚል አለ እንዲሁም የተለያዩ ዶክመንቶች ናቸው የተገኙት በራሪ ወረቀት በአማርኛ የተፃፈ በራሪ ወረቀት ነው ያው እሱ ነገሮች ነው የተገኙት ማለት እነዛን ነገሮች ከተያያዘ በኋላ ሙሉውን ዶክመንቶቹ ላይ የተፈረመበትን ሁኔታ ነው ያለው

- እሺ ከዚጋር በተያያዘ አሁን ካልካቸው በተጨማሪ የምታስታውሰው አለ እዛ የተገኙ?
- ያው የተገኘው የአወልያ ስንቅ የሚል አለ እዛው ላይ ከበራሪ ወረቀት ከነዚህ የሚያስፈልጓቸው ከዛ ሁኔታ ላይ የሚያስፈልጉ ዶክመንቶች ውጪ የተገኙ ነገሮች የሉም ማለት እነጦር መሣሪያ የኤሌክትሮኒክስ ነገሮች የተገኙ ነገሮች የሉም እነዛ ነገሮች ብቻ ናቸው የተገኙት እንደውም የገለፃቸው ነገሮች አሉ እነዚህን ብቻ ነው እንጂ የምበትነው ሌላ ነገር እኔ እዛ ውስጥ አልገባም የሚል ነገር የገለፀበት ሁኔታም አለ እዛችው ላይ እነዚህ በራሪ ወረቀቶችን መበተን ነው እንጂ የኔ ስራ ሌላ ነገሮችጋ አደለም በሚል የገለፁት ማለት በራሪ ወረቀቶች አሉ እዛው ላይ የተገኙት ማለት ነው
- እስቲ እነማን ናቸው አሁን ያልካቸው?
- የአወልያ ስንቅ የሚል በራሪ ወረቀትነው
- ሌላስ ከዚህ በራሪ ወረቀት ካልከውጋር ማለት ነው የምታስታውሳቸው አሉ?
- ማለት ላስታውሰው
- ከአወልያው ሌላ ማለት ነው ?



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ ማለት ስምንት አይነት ናቸዋ እረዘም ያለ ጊዜ ስለቆየ ትንሽ የረሳኋቸው ነገሮች ስላሉነው እንጂ 8 ዓይነት ነገሮች ናቸው በዝርዝር የተያዙት

➢ ስምንት ዓይነት ማለት እርእሳቸው የተለያየ ማለት ነው ?

➢ የተለያየ እርእስ ኖሯቸው 8 ዓይነት ዶክመንቶች ናቸው የተያያዙት እነዛማለት መጽሃፉ ማለት ቅድም የገለጽኩት አለ ምንድን ነው ዘስቶሪ ኦፍ ግሬት ኤክስፓንሽን እንደሚለው ሁሉ በጀርመንኛ ስለፊያ ጋዜጣ እነሱ እነሱ እንደነሱ አይነቶች ማለት የተያዙ ነገሮች ናቸው

➢ የተያዙ በሙሉ ናቸው ?

➢ ላስታውሳቸው ስላልቻልኩ ነው ሙሉውን ማለቴ ነው

➢ 8 ያልከው የተያዙ በሙሉ ነው ?

➢ በዝርዝር የተፃው ማለት ነው

➢ እሺ እነኚህ ቅድም ምንድን ነው ያልከው የኔ ስራ ምንድን ነው ምን አለ ነው ያልከው ምን ሲባል ነው እሱን ያሉት?

➢ ይደገምልኝ

➢ ቅድም ያልከው የኔ ስራ ከበራሪ ወረቀት ጋር በተያያዘ ያልከው ነገር አለ ምንድን ነው ያለው በራሪ ወረቀትን በሚመለከት ማለት ነው ቅድም ከበራሪ ወረቀት ጋር በተያያዘ የገጽከው አለ እና ከስምንቶቹ የምታስታውሰው አለ ወይ በራሪ ወረቀትን በሚመለከት በራሪ ወረቀት ካልካቸው ውስጥ ማለት ነው ?

➢ /ግልጽ ያልሆነ/

➢ ከስምንቶቹ ውስጥ ከተፃፉት የምታስታውሳቸው አሉ ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ስምንቶቹን እኮ ማለት ስለፌያ ጋዜጣ ላይ ስምንቱ አለ 8 ዝርዝር ያልኩት ምንድን ነው ከ1-8 ዘ ስቶሪ ኦፍ ግሬት ኤክስፓንሽን እንደሚለው ሁሉ አንድ ተብሎ እንደተያዘው ማለት ነው አንድ ዘስቶሪ ኦፍ ግሬት ኤክስፓንሽን ሁለት አወልያ ጋዜጣ ግልጽ እናርግና 8 ያልከው በራሪ ወረቀቶችን ብቻ ናቸው ወይስ የተያዘውን በሙሉ ?
- ከሱጋ የተያያዙ ዶክመንቶች ጭምር ነው
- ማለት አንድ ላይ ከቤቱ የተያዙትን በራሪ ወረቀቶች ጭምር በሚል የዘረዘርኳቸው ማለት ነው
- 8 ያልከው?
- ስምንቱ ማለት ነው እንደገና በአረብኛ የተፃፈ ሁለት እንትን አለ የተያዘ ማለት ነው
- ምንድን ነው መጽሃፍ ነው በራሪ ወረቀት ነው ምንድን ነው?
- በራሪ ወረቀት በአረብኛ የተፃፈ
- ምን እንደሆነ ይታወቃል ትርጉም አለው?
- እኛ ትርጉሙን ስለማናውቀውም እኔ ይሄ በኔ በኩል አላውቀውም ሌሎቹም የነበርነው አብረን የምናውቀው
- እሺ ሌላስ የምታስታውሰው አለህ ከበራሪ ወቀት ጋር በተያያዘ ማለት ነው እሺ እነኚህ አህን አጠቃላይ ተገኙ ከተገኙ በኋላ ምን አረጋችሁ?
- ከተገኘ በኋላ ውሉ ላይ ያው የፊርማ የሁላችንም ከአቶ ሳቢር ጀምሮ ሦስታችንም ምስክሮች የፈረምንበት ሁኔታ
- በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ፈረማችሁ?
- በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ተፈርሟል



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ ፈረመ?
- አዎ በወቅቱ ይሄ ነገር ሲበረበር ከነበሩት /ግልጽ ያልሆነ/ እንዴት ነው ምን ይታይበት ነበር የነፃነት ሁኔታ ?
- ይደገም እስቲ
- አይ ነፃ ሆነው ነው ወይ ነፃነት ይታይበት ነበር ወይ ማለቴ ነው ፈቃደኛነት ማለቴ ነው ይታይበት ነበር አንተ ስታየው?
- አዎ ፍቃደኛነት አለበት
- እሺ ጨርሰናል
- እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ
- እሺ አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ አለማየሁ
- አቤት
- ተከሳሽ መጀመሪያ በቦታው ላይ የተገኘሁት ጓደኞቼን ሄጀ ነው ብለዋል ቅድም ስንት ሰዓት ነበር ሰዓቱ?
- እዛ ማለት የደረስነው
- አንተ ጓደኞችህጋር የደረስክበር ሰዓት ስንት ሰዓት ነው ?
- የደረስነው እዛ ቦታ ላይ የተደረሰው ሦስት ሰዓት ተኩል ነው ነገር ግን የተጀመረው ከ4-6 ሰዓት ነው ሙሉ በሙሉ ያለቀው
- እሺ አንተ እዛጋር ጓደኞችህጋር ለግል ጉዳይህ ነው ሄደህ የነበረው አደል ?
- ማለት አቤት ነበርኩኝ ለግል ጉዳዬ ሳይሆን ጠርተውኝ ነው ለእንደዚህ አይነት ጉዳይ ስለምንፈልግህ እንድትገኝ በሚል ነው



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ እዛ ቦታ ስትሄድ ተከሳሽን መጀመሪያ ያየሽው የቱጋ ነው ?
- አልተሰማኝም
- መጀመሪያ ያገኘሽው አንተ አሁን መኖሪያ ቤትህ ነው ጓደኞችህ ጋር ነው የነበርከው አንተ?
- ማለት መኖሪያ ቤት ነው በቀጥታ የሄድነው ተያይዘን
- አደለም አሁን አንተ መጀመሪያ ውጪ ነው የነበርከው አደል ከዛ ነው ከዛ ነው ለምስክር ትፈለጋለህ ተብሎ የተጠራሽዉ?
- አዎ
- ለምስክር ትፈለጋለህ ተብለህ ተጠርተህ ስትሄድ ተከሳሽን መጀመሪያ ያየሽው ወይም ያገኘሽው የት ነው ?
- ያገኘሁት እዛው አካባቢ ማለት ነው ቤቱጋ
- ቤት ውስጥ ነው ወይስ ከቤት ውጪ ?
- አይ መንገድ ላይ ይዘን አብረን ነው የሄድነው
- ማለት እሱን ነዋ የጠየቅከው መንገድ ላይ ያልከውን ነው እንድታስረዳን የፈለግኩት መንገድ ላይ ስትል የቱጋ ነው ያገኘሽው?
- መጠምዘገሮው የሱ ቤት መጠምዘገሮጋ ማለት ነው
- እሺ ስታገኘው የት ከማን ጋር ነው የነበረው እሱ?
- እሱ ከፖሊሶችጋ ነው
- መሣሪያ ታጥቀው የነበሩ ፖሊሶች ናቸው ይዘውት የነበረው አደል?
- አዎ



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ እጁን በካቴና ታስሮ ነበረ አደል እሱ?
- አዎ
- ከዛ ከሱጋ ሆናችሁ ወደ እሱ መኖሪያ ቤት ስትሄዱ አንተ አብረህ ተከትለህ ነው የሄድከው?
- አዎ
- ፖሊሶቹ ለፍተሻ በምስክርነት እንደምትፈለግ ነግረውህ ብቻ ነው የሄድከው?
- ሁሉን ነገር አንብበውልኛል
- እሺ አሁን ስለ ፍ/ቤት ትእዛዝ ቅድም አይቻለሁ መጀመሪያ ጥያቄዬን ስማኝ ወደ ስትሄድ የፍ/ቤት ትአዛዝ የተመለከትክ መሆኑን የፍ/ቤት ትእዛዝ ለአንተ ተሰጥቶህ እራስህ አንብበኸዋል ?
- ማለት የዛን ሰዓት ላይ ተሰጠኝ አየሁትኝ የፍ/ቤት ትእዛዝ መሆኑን ማህተም መኖሩን አየሁትኝ ነገር ግን ሁሉንም ነገሮች አላነበብኩም ተነበበልን እንጂ ትእዛዙ
- እሺ አንተ አላነበብክም ?
- እኔ አላነበብኩትም
- እሺ የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ያነበበው ማን ነው ?
- ማለት የፖሊስ አካል ነው የነበበው
- የት ነው የተነበበው?
- እዛው
- እዛው ስትል የት ?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ ማለት መጀመሪያ ያገኙኝ ቦታ ላይ ነው ያነበበኩት አንብበውልን ከዛ በኋላ ውስጥ ነው ድጋሚ የተነበበት ሁኔታ ነው ነበረ

➢ ውስጥ ስትገቡ?

➢ በር ላይ ከተንኳኳ በኋላ የከፈተችዋ ሴትጋ የተነበበት ከዛ ውስጥ ደግሞ እንደገና የተነገረበት ሁኔታ ነው

➢ እሺ ሁለት ጊዜ ከተነበበ በትክክል ታስታውሳለህ ትእዛዙን ብዬ እገምታለሁ እሃ ትእዛዙ የማን ቤት ይፈተሽ ነው የሚለው?

➢ አቶ ሳቢር

➢ የሱ ቤት ይፈተሽ አሉ መቼ ይፈተሽ ይላል ?

➢ ይፈተሽ የሚለው ማለት የተፈተሸበት በሐምሌ 12 ትእዛዙ የመጣበት

➢ አደለም ይኸውልህ የተፈተሸበት ቀን ምናምን ሳይሆን የሰማኸውን ነው የምትነግረኝ ሲነበብ የሰማኸውን ትእዛዙን ?

➢ ሐምሌ 12 ቀን 2004

➢ የተፈተሸው ግን መቼ ነው?

➢ የተፈተሸው በ17 ነው

➢ ትእዛዙ ግን ሐምሌ 12 ነው የሚለው ልክ ነኝ ?

➢ 17 ነው

➢ እሺ ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ይፈተሽ ይላል?

➢ ሰዓቱን እንኳን ብዙም አላስታውሰውም ከሰባት እስከ ስድስት ነው እኛ የነበርነው



http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ይኸውልህ አለማየሁ ሁለት ነገር እኔ እየጠየቅኩህ ያለሁት ሲነበብ የሰማኸውን የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ይዞት ነው የምጠይቅህ የተደረገው ስለተደረገው ምርመራ ያሉኝን ጥያቄዎች እጠይቃለሁ አሁን ሲነበብ ሰምቻለሁ ስላልክ ስለሰማኸው ነገር ብቻ ትእዛዙ ሲነበብ ቤቱ ከመቼ ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ይፈተሽ ይላል ?
- ቤቱ ይፈተሽ እስከ አስራሁለት ሰዓት ነው እኔ ያው
- በፍተሻው ጊዜ ምን ምን እቃዎች ይያዙ ነበር?
- የጦር መሣሪያ ኤሌክትሮኒክስ እቃ እንዲሁም ደግሞ ከዚህ ወንጀልጋር ሊገናኝ የሚችል ወረቀቶች ዶክመንቶችን ማለት ነው መረጃው በሙሉ ይገልፃል?
- አዎ
- እሺ ወደቤት ከገባችሁ በኋላ ፍተሻው ሲደረግ ከአንተ ሌላ ታዛቢ ነበረ አደለ?
- አዎ
- ማን ነው ያታዛቢ ?
- አበባው
- እሺ እሱም እንዳንተ ከሰር የመጣ ነው ወይንስ ከነሱጋር አብሮ የመጣ ሰው ነው ?
- ማለት እኔን የጠራኝ እንደውም እሱ ነው ከሱጋ በደንብ እንግባባለን ከሱጋ ነው ጓደኝነታችን
- ሁለታችሁ ባላችሁበት ፍተሻ ሲደረግ የተከሳሽ አብሯችሁ ነበር አደል እስከ መጨረሻው ድረስ ሳቢር ፍተሻው ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ አብሯችሁ ነበር?
- አዎ
- በዚህ ሁሉ ጊዜ እጁ እንደታሰረ ነበር አደለም?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እሺ በፍተሻው ላይ ተገኝ ያልከው አሁን መጽሃፍ አንደኛው እስቶሪ ኦፍ ግሬት ኤክስፓንሽን የሚለው መጽሃፍ ነው አደል?
- በእንግሊዘኛ የተፃፈ መጽሃፍ ነው
- ምን ያህል ይሆናል ገፁ በግምት?
- ገፁን እንኳን ብዙ አላውቀውም ማለት ተለቅ ያለ ነው የመጀመሪያውን ከቨር ነው ገለጥ አርገን ያየነው ስናየው
- መገመት ትችላለህ ካልቻልክ አልቻልክም ነው?
- ከ600 በላይ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ
- ጋዜጦቹም ሰለፊያ የሚል ጋዜጣ ብለሃል መደበኛ ጋዜጦች ገበያ ላይ የሚታየው አይነት ጋዜጣነው አደለም አይነቱን ማለቱ ነው?
- አይነቱ ገበያ ላይ ያለ አይነት ነው
- በፍተሻ ጊዜ ሲዲ አልተገኝም አደል ቤቱ ውስጥ?
- ሲዲ አልተገኘም
- ካሴትም አልተገኘም ?
- የነሱ አልተገኘም የነዛ ነው
- እሺ የፍተሻው ሂደት በቪዲዮ ይቀረጽ ነበር አደል?
- አልተሰማኘም
- የፍተሻው ሂደት ጠቅላላ ተጀመሮ እስኪያልቅ ድረስ በቪዲዮ ይቀረጽ ነበር አደል?
- አዎ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተከሳሽ እንዲንበረከክ የተደረገው ለምንድን ነበር?
- እንዲንበረከክ አልተደረገም
- እንዲንበረከክ አልተደረገም በፍተሻው ሂደት ውስጥ?
- አላየሁትም እኔ እንዲንበረከክ ሲደረግ
- እሺ
- አንተ ፍተሻው ሲደረግ በሁሉም ክፍሎች ላይ አብረህ ተከትለህ ሄደሃል?
- አዎ
- ማን ማን ነበረ ከእናንተ ከሁለታችሁ ታዛቢዎች ሌላ በፍተሻው ቦታ ላይ በሁሉም ተ ላይ የተገኘው?
- ማለት ሶስት ነን ታረቢዎቹ አንደኛው ምን ያህል የሚባል ነው
- ሦስት ታዛቢዎች ከዛ ሌላ ማን ነው አብሯችሁ ይዞር የነበረው?
- ከፌደራል ፖሊስ የመጡ
- የትኞቹ ከፌደራል ፖሊስ የመጡት መሣሪያ ይዘው የሚያጅቡት ናቸው ወይንስ ሌሎች ሰወች ናቸው ?
- ማለት መሣሪያ ይዘው ነው የሚያጅቡት እንደገና ደግሞ በአመራር ደረጃም ያለ ሰው ያለው አብሯቸው የነበረው
- እቃዎቹን ይፈተሽየነበረው ማን ነው መሣሪያ የያዙት ናቸው ወይንስ የትኞቹ ፖሊሶች ነበሩ እቃውን ይፈትሹ የነበሩት?
- መሣሪያ የያዙት አደሉም መሣሪያ ያልያዘ ፖሊስም ሲፈትሽ ነበረ

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ እነዚህ ፖሊሶች ያልነቸው ሰወች ፖሊሶች መሆናቸውን አንተ በምን አዋቅክ ፍተሻውን ያረጉ የነበሩት ሰወች ፖሊሶች መሆናቸውን በምን አወቅክ?
- የደንብ ልብስ ለብሰዋል
- ሁሉም ፈታሾቹ የደንብ ልብስ የለበሱ ነበሩ?
- አዎ
- እሺ ቃለ ጉባዔ ተጽፎ ፈርመናል ብለሃል መጨረሻ ላይ ?
- አዎ
- ቃለ ጉባዔውን ሲፈረምም የተከሳሽ እጅ እንደታሰረ ነበረ አደለ የፈረመው?
- አዎ
- ቅድም ግቢ የከፈቱ በሩን የከፈተ ሰው እንደነበረ የቤተሰብ አባል ማለት ነው ስንት ሰው ነበረ እናንተ ስትገቡ ቅድም ግቢ የከፈተች አንድ ሰራተኛ ትሆን የሚል አንድ ገልፀሀልናል ትክክል ነው አደል ?
- አዎ የከፈተች አለች
- ከዛ ሌላ ወንድ ደግሞ ቤት ከፈተ ?
- አዎ ውስጥ ነበረ ንድሙ ይመስለኛል
- እሺ ሌላ ሰው ነበረ ?
- በኋላ ላይ ዘግይታ የመጣው አንድ ሴት ነበች ዘመድ ናት እንደዛ ነገር ነው ያላት /ግልጽ ይልሆነ/
- እነዚህ ሰወች የት ሄዱ አሁን ሦስተ ነሆነወ ማትነው መጀመሪያ ሁለት ነበሩ?
- እዛው ግቢ ውስጥ ነው የጠበቁት



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሃ እንዲገቡ አልተፈቀደም ?
- እውስት አልገቡም ውጪ ነው እንዲጠብቁ የተደረገው
- ፖሊሶቹ ወይም ወደቤት የገቡት ከፌደራል ፖሊስ የመጡ ያልካቸው ምን ምን ይዘው ነበር ሲገቡ ?
- ማለት የመጀመሪያ የፍ/ቤት ትእዛዙ ነው ከዛ ውጪ ያው እሱ እና የጦር መሣሪያ የተያዘበት ሁኔታ ነው ሌላ ነገር የለም
- ሌላስ ቦርሳ ነገር አልያዙም ነበር?
- ቦርሳ ነገር አልተያዘም
- ማለት ቅድም ሲቀረጽ ነበር ስላልክ ?
- አዎ የቪዲዮ ካሜራ አለ
- በምን በቦርሳ ነበረ የያዙት?
- የራሱ ቦርሳ አለው የቪዲዮ ካሜራው መያዣ ቦርሳው
- እሺ ቪዲዮ ካሜራ የያዘ ቦርሳ ይዘው ገቡ?
- የራሱ የሆነ ቦርሳ ይሗል የቪዲዮ ካሜራው መክተቻዉ ውስጠ መክፈቻ ያለው
- እኮ በቦርሳ ውስጥ ሆኖ ቪዲዮ ካሜራ ያለበት ቦርሳ ይዘው ገቡ ከዛ ፍተሻ ሲጀመር ይሄንን ቦርሳ ይዘውት አብረው ነበር የሚዞሩት?
- አዎ አብረው ነው
- ቦርሳውን እንደያዙ ነው ሳሎን አስቀመጡት?
- ቦርሳውን እንደያዙት ነው ያለው በእጁ ይዞታል አንደኛው ፖሊስ በእጁ ይዞታል ለእሱ ሰጥቶ ነው ቦርሳውን ቪዲዮ ካሜራ የያዘው ሰው ነው እንትን ያለው



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ ቦርሳውን የተቀበለው ሰው ቪዲዮ ካሜራ የያዘው ሰው በየክፍሉ ነበረ እንዴ የሚቀርፀው?
- አይተከተለ ነው አብሮት ነወ ያለው
- እሺ ቦርሳ የያዘውስ?
- ቦርሳ የያዘው ያው ምንም የያዘው ነገር የለም
- የት እሱ የት ሳሎን ተቀመጠ አሁን ቪዲዮ የያዘው ተከትሎ ይቀርፃል የሚበረብር ሰው አለ ታዛቢዎች አብረው ይዞራሉ ቦርሳ የያዘው ሰውስ የት ሄደ ?
- አብሮ ነው ያለው ከኋላ ማለት ነው ከቪዲዮ ካሜራው አጠገብ ሆኖ ነው ያለው
- ቪዲዮ ቀረፃውገና ተከሳሹ አቶ ሳቢር ሲገባ በርም ላይ ተቀርጿል አደል?
- በር ላይ ሲቀረጽ አላየሁም ውስጥ ነው ቀረፃ የተጀመረው እንዳየሁት ከሆነ ማለት ነው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ጥያቄ ካላችሁ
- የለንም
- እሺ በፍ/ቤቱ ጥያቄ
- እሺ ሐምሌ 12 ነው ይፈተሽ የሚለው ትእዛዙ ብለህ ነበረ ቅድም?
- ሐምሌ 17
- ይፈተሽ የሚለው ?
- ማለት እኛ የፈተሽነው ሐምሌ 17 ነው
- ትእዛዙ ይፍተሽ የሚለው መቼ ነው?
- በእርግጠኛነት ሐምሌ 12 ትእዛዙ የወጣው የሚለው ሐምሌ 12



http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ የወጣበት ቀን አደለም የኔ ጥያቄ 12 ሊወጣ ይችላል ከዛም በፊት በኋላ ሊወጣ ይችላል ትእዛዙ ላይ ያለው ይፈተሽ የሚለው ቀን መቼ ነው ?
- ሐምሌ 12
- ሐምሌ 12 ይፈተሽ ይላል?
- አዎ
- እናንተ ደግሞ የፈተሻችሁት ሐምሌ 17 ?
- 17 ነው የተፈተሸው
- በትክክል ታስታውሳለህ ይሄንን?
- ግን ትንሽ ማለት ጥርጣሬዎች ስላሉ እረጅም ጊዜ ስለቆየሁ ጥርጣሬ ማለት የተፈተሸበትን ቀን ነው በደንብ የማስታውሰው ማለት ነው ያኛውን ትንሽ ጥርጣሬ
- እሺ ቅድም ስተጠየቅ የሆኑ ጥያቄዎች ነበሩ እና የሆኑ መሣሪያ አምጡ ሌላ ነገር ከማድረጋችን በፊት የሚል ቃል ነግረሽናል ቅድም?
- አዎ
- ምን ማለት ነው ይሄ ሌላ ነገር ከማድረጋችን በፊት ማለት ምን ማለት ነው?
- ማለት ወደ ብርበራ ከመፈተሻችን በፊት ቅድሚያ ልታስረክቡን የሚገባ ማለት ነው ልታስረክቡን የሚገባ ጦር መሣሪያ ካለ ያንን ነገር ከመፈተሻችን ማለት ቤቱን ከመበርበራችን በፊት የምታስረክቡን ነገር ካለ ጦር መሣሪያ ብታስረክቡን የሚል ጥያቄ ነው የቀረበው
- ጨርሰሃል እናመሰግናለን
- ቀጣይ ምስክር



http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእውነት ለመመስከር
- በእግዚአብሔር ስም
- ምያለሁ
- ተራ ቁጥር 193
- ለምስክርነት ነው የመጡት?
- አዎ
- ስሞን ያባቱን ስም ሳይጨምሩ የመጀመሪያ ስሞን ብቻ ይነግሩናል
- ስሜ ሕብርተ
- እሺ 80ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል ምስክሩ 80ኛ ምስክር ነው በማስረጃ ዝርዝሩ በ193 ላይ የተጠቀሱ ወ/ሮ ሕብርተ /የማይሰማ/ የሚመሰክሩት ዛሬ?
- እኔ በአቶ ካሚል ሸምሱ
- እሺ ሌላስ?
- ሌላ የለም
- እሱ ብቻ ነው ?
- አዎ
- አቶ ካሚል ሸምሱን በአካል ለይተው ያውቃሉ?
- አይ አላውቀውም
- በአካል መለየት አይችሉም?
- አልችልም አላውቀውም
- እሺ ምንድን ነው ያዩት?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእለቱ ቤታቸው ሲፈተሽ ታዛቢ እንድሆን
- እኬ እሺ እቃቢ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ ወ/ሮ ሕብርት የአቶ ካሚል ሽምሱ ቤት ሲበረበር ይሄ መቼ ነበረ ጊዜው ?
- በ13/11ኛ ወር ነበር
- የት አካባቢ ነበር ቦታው የት ነበር?
- ቤተል አካባቢ በብሩክ ብረታ ብረት ገባ ብሎ
- የት ክ/ከተማ ማለት ነው ? ቀ
- ኮልፌ ወረዳ 6
- እርስዎ በዚህ ቀን ማን ጠራዎት እንዴት እዛ ቦታ ተገኙ ምን አዩስ?
- የተገኘሁት እዛው አካባቢ ነዋሪ ነኝ እና እንድተባበራቸው ጠየቁኝ
- ማን ነው የጠየቆት ?
- እዛ አካባቢ ወታደሮቹ
- ይተባበሩኝ ብለው ሲሎት ምን አሳዮት?
- መጀመሪያ ግቢው ዝግ ነበረ አንኳኩተን ከወታደሮቹጋር ከተከፈተ በኋላ የሱን ቤት ለመበርበር የሚያስፈልግ ዶክመንት አሳዩን
- እሺ?
- ቤቱን ለመፈተሽ ማዘዣ ይዘዋል
- ከየት የመጣ ነው አሎት?
- ከአራዳ ክ/ከተማ
- ምንድን ነው ማዘዣው የምንድን ነው የፖሊስ ነው የፍ/ቤት ነው?



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ ማዘገርው የሚለው በተፈታሹ ቤት የጦር መሣሪያ እና ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ እና የተለያዩ ቁሳቁሶች ይላል ጊዜው ቆይቷል እኔ እንግዲህ መጀመሪያው ላይ ግን የጦር መሣሪያ እና ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ለመፈተሽ ይላል ያንን እንዲታይ ማለት ነው

➢ እሺ ይሄንን አሳዮት እሱስ ነበረ ?

➢ አቤት ?

➢ አቶ ካሚል ነበረ እዛ አካባቢ?

➢ አይ እሳቸውን አላየኋቸውምም አላውቃቸውም ግቢውን ከተከፈተ በኋላ ባለቤቱ ከውስጥ ተጠርታ ባለቤቱ ነኝ አለችኝ አንድ ጉረቤት እዛው አለች ከዛ በኋላ አብረን ገባን ከዛን በኋላ ወደ ፍተሻው

➢ እሺ ወዴት ገባችሁ?

➢ መጀመሪያ ሰርቪሶች አሉ ሰርቪሶች ውስጥ ገባን አየን ከዛ ወደ ዋናው ቤት ገባን

➢ ግን ከመርባታችሁ በፊት ባለቤቱ ነኝ ብለው የነገሯችሁ ሰው ማለት ነው አልጠየቋችሁም ለምን እንደመጣችሁ ምን ይዛችኋል ብለው ጠየቋችሁ ?

➢ አይ እንግዲህ ቀድማ ያው ፖሊሶቹ የነገሯት ይሁን ያው ስንገባ ግን ተነገራት ለፍተሻ እንደተመጣ

➢ እሲ ከዛ ገባችሁ?

➢ ገባን ሰርቪሶች ውስጥ አየን ከዛ በኋላ ደግሞ ወደ ዋናው ቤት ገባን እንደቤተ መፃህፍት ነገር አለ ከዛ ውስጥ የሆኑ መጽሄቶች ከዛ ላይ በናሙናነት መድሎክ የሚል ማንነት ከአንዱ አንደበት የሚል የተወሰኑ ናሙናዎች እንደ ላይብረሪ ትልቅ ሼልፍ ነው ያለው ከዛ ተነሳ ወደ መኝታው ቤት ሄድን ከዛ በኋላ እዛ ደግሞ አንዳንድ ነገሮች ላፕቶፕ ቶሺባ



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ላፕቶፕ ተገኘ ከዛ ወጣን ተመዘገበ በቁጥር 18 የሚሆኑ ተመዘገቡ ቃለ ጉባዔ መዘገብን እዛ ውስጥ የቴፕ ካሴቶችም ነበሩ 18 ነጥቦች ናቸው የተመዘገቡት በዋናነት እነዚህ ናቸው ጊዜው ቀይቷል ሌሎቹን የተንክ ደብተሮችም ነበሩ

- እነኚህ 18 ያሏቸው በዝርዝር የተለያዩ ናቸው ማለት የተፃፉ መጽሃፍ ?
- ያው እዛው ቁጭ ብለን ተመዘገቡ የሚወጡት ነገሮች እየተመዘገቡ 18 አተምስ የያዙ ነገሮች መዘገብን ከዛ ውስጥ የቴፕ ክር ያልኩህ አሁን መድሎት የሚለው መጽሃፍ ማንነት በአንዱ አንደበት የሚል በናሙናነት ከዛ ከሼልፍ
- /የማይሰማ/
- አቤት የተለያዩ ናቸው እርእሳቸው መጽሃፎቹ
- /የማይሰማ/
- አይ ሁለት ሁለት ይሁን ሦስት ሦስት እንጃ እኔ ጊዜው ቀይቷል ግን እነዛን እርእሶቹን ያየሁትን ነው የተለያዩ ናቸው ውስጣዊ ይዘታቸውን ግን አላነበብንም እርእሳቸውን ብቻ ነው ያየነው ተመዘገቡ
- መድሎት በምን የተፃፈ ነው?
- አቤት?
- በምን የተፃፈ ነው መድሎት የሚለው?
- የተፃፈው በአማርኛ
- እና ሌሎችስ የሚያስታውሷቸው ምን ምን ናቸው ከ18ቱ ውስጥ?
- ሌላ የማስታውሰውም የባንክ ደብተሮች ካሴቶች
- ምን አይነት ካሴት?

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት *



ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

➢ የቴፐ ካሴት

➢ ሌላስ?

➢ ሌሎቹን አላስታውስም ቆይቷል ጊዜው

➢ እሺ እነኚህ 18 ያሏቸው ከተገኙ በኋላ ምንድን ነው ያደረጋችሁት መጨረሻ?

➢ አቤት ?

➢ መጨረሻ ምን አደረጋችሁ?

➢ በቃ 18 ነገሮች ናቸው ወጡ ተመዘገቡ ተፈራረምን ሁላችንም አብረን ወጣን ግቢው ሰፊ ነው እዛ ውጪ ቁጭ ብለን ፃፍን የወጡትን ተመርጠው የወጡትን ገነገሮች ፃፍን ተፈራረምን ሁላችንም አንድ ላይ ወጣን ግቢውን ለቀን

➢ አቶ ካሚልስ ፈርሟል?

➢ አይ ተከሳሽ የሉም ተከሳሽ በእለቱ የሉም

➢ ባለቤቱስ ?

➢ ባለቤቱ ነበረች

➢ ባለቤቱ ፈረሙ?

➢ ፈርማለች አዎ

➢ እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት

➢ እሺ የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ

➢ እሺ ወ/ሮ ሕብርተ ቀኑ ሐምሌ 18 ነው ብለዋል ሐምሌ 13 ምን ቀን ነበረ የሚውለው ሰኞ ነው ማክሰኞ ነው ምን ቀን ነበረ የሚውለው?

➢ እኔ ቀኑ አሁን ሰኞ ማክሰኞ ይሁን አላውቅም ግን 18 ሐምሌ 13

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት



27.7.2018

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ የስራ ቀን ነው ወይስ የሰንበት ቀን ነው?
- እኔ መምህር ነበርኩ እሁድ ነው አላውቀውም ቀኑ ትዝ አይለኝም እኔ ምስክርነት ይኖረዋል ብዬ አላሰብኩም
- እሺ ለእርስዎ ታዛቢ እንዲሆኑ የተነገሮት የት ነው መጀመሪያ?
- ከግቢ ከወጣሁ ግቢ አካባቢ ነበርኩኝ ወደዚህ ዞረን ወደ እሱ ቤት ስንዞር ለዛ ጉዳይ እንደፈለጉን ጉዳዩ ክብደት እንደሌለው ቆመን እንድናይ ነው የተነገረኝ እኔም
- በአጋጣሚ ተገኝተው ነው ወይንስ ተጠርተው ነው?
- በአጋጣሚ ውጪ ነበርኩኝ
- እሺ እዛጋር ቅድም አሁን ሲገልፁ ካሚልን በአካል አላውቀውም ብለውናል ያ የሚፈተሸው ቤት የካሚል ቤት ስለመሆኑ ምንም ያጣራችሁት ነገር የለም አደል?
- የአቶ ካሚል ቤት መሆኑን በኋላ
- አደለም በኋላ ሳይሆን ልክ የዛን እለት ስትገቡ ይሄ ቤት የካሚል ቤት ስለመሆኑ ያጣራችሁበት ምንም ነገር የለም አደለም?
- የፍ/ቤት ማዘዣ የአቶ ካሚል ቤት እንደሚፈተሽ እዛ በሩ ላይ አየን ከዛ ውጪ ደግሞ ትእግስት የምትባል ጉረቤት አለችው የሱ ባለቤት እንደሆነች ከጉረቤቱ ነው የተነገረኝ እኔ ሚስቱንም እሱንም አላውቀውም
- እርስዎ ግን ያጣሩት ነገር የለም ?
- አዎ ግን ከገባን እና ያው በቃ ሚስቱ አራስም እንደሆነች ችግር እንደገጠማት ሁሉ ከጉረቤቱ አንዷ ታዛቢ ጉረቤት ነበረች አጥራቸው የጋራ የሆነ አስድታኛለች
- ሚስት የተባለችዋ ሴት የአቶ ካሚል ሚስት ስለመሆኗም አላጣራችሁም አደል?

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/